## መግቢያ

የአዲስ አበበ ከተማ አስተዳደር በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አዋጅ ቁጥር 1/1987 አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 2 ራሱን በራሱ እንደሚያስተዳድርና ዝርዝሩም በሕግ እንደሚወሰን ይደነግጋል፡፡

ይህን ሕገ-መንግሥታዊ ድንጋጌ ተከትሎ የከተማ አስተዳደሩ በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አሰተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1996 እንዲቋቋም ተደርጓል በዚህ ቻርተር አዋጅና ማሻሻያዎቹ ነዋሪውን እያስተዳደረ ይገኛል፡፡

አስተዳደሩ በቻርተር አዋጅ ከተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት ውስጥ የሕግ አውጭነት፣ የሕግ አስፈፃሚነትና የዳኝነት ሥልጣኖች ይገኙበታል፡፡ በሕግ አውጭነት ሥልጣኑ ያወጣቸው አዋጆች፣ ደንቦችና እና መመሪያዎች ለነዋሪውና ለአገልግሎት ተጠቃሚው ተደራሽ ባለመሆናቸው ነዋሪው ወይም አገልግሎት ተጠቃሚው መብቱን ለማስከበርና ሕግና ሥርዓትን ለማስፈን የበኩሉን አስተዋጽዖ እንዳያበረክት፣ የሚጠበቅበትን ግዴታ እንዳያውቅና እንዳይወጣ አድርጎታል፡፡

በሕግ አስፈፃሚነቱ በከተማ አስተዳደሩና በፌዴራል መንግሥት የወጡ ሕጎችን ከማስፈፀም አንፃር ምሉዕ አላደረገውም፡፡ ከዳኝነት ጋር ተያይዞ ፍትሕን ለማረጋገጥ ሕጎቹ በቀላሉ የማይገኙ በመሆናቸው ፍርድ ቤቶች አገልግሎት ተጠቃሚው ሕጎቹን እንዲያቀርብ ሲጠይቅ ይስተዋላል፡፡

ይህንን ችግር ለመቅረፍ የከተማ አስተዳደሩ በሥልጣን ወሰኑ አስተዳደራዊ፤ ፍትሕ፤ ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ነክ መብቶቹን ለማልማት ያወጣውን አዋጅ፣ ደንብ እና በፌዴራል መንግሥት ወጥተው ዕለት ተዕለት የሚያስፈፅማቸውን በመፅሐፍ መልክ በማዘጋጀት አቅርቧል፡፡ በተጨማሪም የበለጠ ተደራሽ ለማድረግ በድህረ-ገጽ በመጫን እንድትጠቀሙና በየጊዜው ወቅታዊ ስለምናደርጋቸው ድህረ-ገፁን እንድትጉበኙ እንጋብዛለን፡፡

በዚህም ቅጽ አንድ አስተዳደራዊ እና የፍትህ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ጉዳዮችን ያካትታል፡፡ በህጎች ስብስብ ላይ ቢካተቱ የሚሏቸው እንዲሁም ማንኛውንም ሃሳብ  የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ ለመቀበል እና ለማስተናገድ ዝግጁ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

# ማውጫ


መግቢያ ........ 1

ቅፅ አንድ ........ 4

አስተዳደራዊ እና ፍትህ ነክ ህጎች ........ 4

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አዋጅ ቁጥር ፩/፲፱፻፹፯ ........ 4

የክልል አስራ አራት መስተዳድር አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ፩/፲፱፻፹፰ ........ 45

አዋጅ ቁጥር 361/1995 የተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር ........ 47

የተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ፴፯/፲፱፻፺፯ ........ 76

የተሻሻለውን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ፩ሺ፺፬/፪ሺ፲ ........ 77

የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የከተማ ነክ ጉዳዮች ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ ደንብ ፩/፲፱፻፺፭ ........ 81

በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ምክር ቤት በወረዳ ምክር ቤትና በቀበሌ ምከር ቤት አባላት ላይ ህዝብ አመኔታ በሚያጣባቸው ጊዜ ስለሚወስደው እርምጃ የወጣ ደንብ ፬/፲፱፻፺፭ ........ 89

የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፺፰ ዓ.ም ........ 95

የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች ........ 98

የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፺፰ ዓ.ም ........ 98

የአዲስ አበባ ከተማ አሰተዳደር ዐቃብያነ ሕግ የሙያሥነ- ምግባር ደንብ ፱/፲፱፻፺፭ ........ 104

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የክፍለ ከተማ የፀጥታ ምክር ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ፱/፲፱፻፺፰ ........ 109

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት እንደገና ማቁቋሚያ አዋጅ ፳፱/፪ሺ፬ ........ 113

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ለማቋቋም የወጣውን አዋጅ ቁጥር ፳፱/፪ሺ፬ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ........ 123

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤቶች አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ፴፩/፲፱፻፺፱ ........ 124

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአማካሪ ምክር ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ፮/፲፱፻፺፰ ........ 140

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ፷፬/፪ሺ፲፩ ........ 149

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚ አካላትን እንደገና ለማደራጀት፣ ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣ ማሻሻያ አዋጅ ፷፯/፪ሺ፲፪ ........ 239

አዋጅ ቁጥር ፸/፪ሺ፲፪ ........ 250

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚ አካላትን እንደገና ለማደራጀት፣ ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ቁጥር ፷፬/፪ሺ፲፩ እንደገና ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ........ 250

የአዲስ አበባ ከተማ የትራንስፖርት ባለስልጣን አደረጃጀትና አሠራርን ለመወሰን የወጣ ደንብ ፸፩/፪ሺ፫ ........ 254

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ አደረጃጀትና አሰራርን ለመወሰን የወጣ ደንብ ፸፪/፪ሺ፫ ........ 260

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን አደረጃጀትና አሠራርን ለመወሰን የወጣ ደንብ ፸፫/፪ሺ፫ ........ 266

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤቶች ዳኞች መከተል ስለሚገባቸው ሥነ-ምግባር ለመወሰን የወጣ ደንብ ፳/፪ሺ፩ ........ 273

የአዲስ አበባ ከተማ የመንገድ አጠባበቅ ደንብ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንገድ አጠባበቅ ደንብ ቁጥር ፪/፲፱፻፺፫ዓ.ም ........................................ 283

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ሕዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ምክር ቤት ለማቋቋም የወጣ ደንብ ፵፩/፪ሺ፫ ........................................ 289

በአዲሰ አበባ ከተማ አስተዳደር የኪነ ጥበብ የፈጠራ ሥራዎች፣ ባለሙያዎች ማበረታቻና የአገልግሎት ክፍያ አፈፃፀምን ለመደንገግ የወጣ ደንብ ፶፫/፪ሺ፭ ........................................ 296

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የደንብ ጥሰትን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና የደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽህፈት ቤት አደረጃጀትና አሠራር ለመወሰን የወጣ ደንብ ፶፬/ ፪ሺ፭ ........................................ 303

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ፶፮/፪ሺ፲ ዓ.ም ........................................ 319

ከኃላፊነት የሚነሱ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የበላይ ኃላፊዎች፣ ከፍተኛ ኃላፊዎች፣ ሌሎች ኃላፊዎች፣ በቋሚነት የሚሠሩ እና ልሎች የምክር ቤት አባላትና ዳኞች የሚያገኛቸውን መብቶችና ጥቅሞች ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ለመተካት የወጣ አዋጅ ፹፩ /፪ሺ፲ ........................................ 357

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መደበኛ ያልሆነ የንግድ ሥራ ለመምራትና ሥርዓት ለማስያዝ የወጣ ደንብ ፹/፪ሺ፱ ........................................ 375

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኮንስትራክሽን ባለሙያዎች የስነምግባር ደንብ ፻፪/፪ሺ፲ ........................................ 387

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን እንደገና ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፻፭/፪ሺ፲፩ ........................................ 397

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንገዶች ባለስልጣን፣ የውኃና ፍሳሽ ባለስልጣን እና የቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን የስራ አመራር ቦርድ ማቋቋሚያ ደንብ ፻፯/፪ሺ፲፩ ........................................ 403

# ቅፅ አንድ

# አስተዳደራዊ እና ፍትህ ነክ ህጎች

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አዋጅ ቁጥር ፩/፲፱፻፹፯**

የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መርጠው በላኳቸው ተወካዮቻቸው አማካይነት ኅዳር ፳፱ ቀን ፲፱፻፹፯ ዓ.ም. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥትን ያጸደቁ በመሆኑ የሚከተለው ታውጇል፡፡

<u>፩. አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አዋጅ ቁጥር ፩/፲፱፻፹፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

<u>፪. ሕገ መንግሥቱ በሥራ ላይ ስለመዋሉ</u>

ኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት ከነሐሴ ፲፫ ቀን ፲፱፻፹፯ ዓ.ም. ጀምሮ ሙሉ በሙሉ በሥራ ላይ ውሐል፡፡

<u>፫. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከነሐሴ ፲፫ ቀን ፲፱፻፹፯ ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ነሐሴ ፲፫ ቀን ፲፱፻፹፯ ዓ.ም.

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

**<u>መ ግ ቢ ያ</u>**

እኛ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች፡ በሀገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ ዘላቂ ሰላም፣ ዋስትና ያለው ዴሞክራሲ እንዲሰፍን፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ እድገታችን እንዲፋጠን፣ የራሳችንን ዕድል በራሳችን የመወሰን መብታችንን ተጠቅመን፣ በነጻ ፍላጐታችን፣ በሕግ የበላይነት እና በራሳችን ፈቃድ ላይ የተመሰረተ አንድ የፖለቲካ ማኅበረሰብ በጋራ ለመገንባት ቆርጠን በመነሳት፤ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስ፣ የግለሰብና የብሔር/ብሔረሰብ መሰረታዊ መብቶች መከበራቸው፣ የጾታ እኩልነት መረጋገጡ፣ ባሕሎችና ሃይማኖቶች ካለአንዳች ልዩነት እንዲራመዱ የማድረጉ አስፈላጊነት ጽኑ እምነታችን በመሆኑ፤ኢትዮጵያ ሀገራችን የየራሳችን አኩሪ ባሕል ያለን፣ የየራሳችን መልክዓ ምድር አሰፋፈር የነበረንና ያለን፣ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በተለያዩ መስኮችና የግንኙነት ደረጃዎች ተሳስረን አብረን የኖርንባትና የምንኖርባት ሀገር በመሆንዋ፤ ያፈራነው የጋራ ጥቅምና አመለካከት አለን ብለን ስለምናምን፤መጪው የጋራ ዕድላችን መመስረት ያለበት ከታሪካችን የወረስነውን የተዛባ ግንኙነት በማረምና የጋራ ጥቅማችንን በማሳደግ ላይ መሆኑን በመቀበል፤ ጥቅማችንን፣ መብታችንና ነጻነታችንን በጋራ እና በተደጋጋፊነት ለማሳደግ አንድ የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ የመገንባቱን አስፈላጊነት በማመን፤ በትግላችንና በከፈልነው መስዋዕትነት የተገኘውን ዴሞክራሲና ሰላም ዘላቂነቱን ለማረጋገጥ፤ይህ ሕገ መንግሥት ከዚህ በላይ ለገለጽናቸው ዓላማዎችና እምነቶች ማሰሪያ እንዲሆነን እንዲወክሉን መርጠን በላክናቸው ተወካዮቻችን አማካይነት በሕገ መንግሥት ጉባኤ ዛሬ ኅዳር ፳፱ ቀን ፩፱፹፯ አጽድቀነዋል፡፡

**<u>ምዕራፍ አንድ</u>**

**<u>ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>**

**አንቀጽ 1: የኢትዮጵያ መንግሥት ስያሜ**

ይህ ሕገ መንግሥት ፌዴራላዊና ዴሞክራሲያዊ የመንግሥት አወቃቀር ይደነግጋል። በዚህ መሰረት የኢትዮጵያ መንግሥት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በሚል ስም ይጠራል።

**አንቀጽ 2: የኢትዮጵያ የግዛት ወሰን**

የኢትዮጵያ የግዛት ወሰን የፌዴራሉን አባሎች ወሰን የሚያጠቃልል ሆኖ በዓለም አቀፍ ስምምነቶች መሰረት የተወሰነው ነው።

**አንቀጽ 3:የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ**

1. የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ከላይ አረንጓዴ፣ ከመሐል ቢጫ፣ ከታች ቀይ ሆኖ በመሐሉ ብሔራዊ ዓርማ ይኖረዋል። ሦስቱም ቀለማት እኩል ሆነው በአግድም ይቀመጣሉ።
2. ከሰንደቅ ዓላማው ላይ የሚቀመጠው ብሔራዊ ዓርማ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች እና ሃይማኖቶች በእኩልነትና በአንድነት ለመኖር ያላቸውን ተስፋ የሚያንጸባርቅ ይሆናል።
3. የፌዴራሉ አባሎች የየራሳቸው ሰንደቅ ዓላማና ዓርማ ሊኖራቸው ይችላል። ዝርዝሩን በየራሳቸው ምክር ቤት ይወስናሉ።

**አንቀጽ 4:የኢትዮጵያ ብሔራዊ መዝሙር**

የኢትዮጵያ ብሔራዊ መዝሙር የሕገ መንግሥቱን ዓላማዎችና የኢትዮጵያ ሕዝቦች በዴሞክራሲ ሥርዓት አብረው ለመኖር ያላቸውን እምነት፣ እንዲሁም የወደፊት የጋራ ዕድላቸውን የሚያንጸባርቅ ሆኖ በሕግ ይወሰናል።

**አንቀጽ 5: ስለ ቋንቋ**

1. ማናቸውም የኢትዮጵያ ቋንቋዎች በእኩልነት የመንግሥት እውቅና ይኖራቸዋል።
2. አማርኛ የፌዴራሉ መንግሥት የሥራ ቋንቋ ይሆናል።
3. የፌዴሬሽኑ አባሎች የየራሳቸውን የሥራ ቋንቋ በሕግ ይወስናሉ።

**አንቀጽ 6: ስለ ዜግነት**

1. ወላጆቹ/ወላጆችዋ ወይም ከወላጆቹ/ከወላጆችዋ አንደኛቸው ኢትዮጵያዊ/ኢትዮጵያዊት የሆነ/የሆነች የኢትዮጵያ ዜጋ ነው/ናት።
2. የውጭ ሀገር ዜጎች የኢትዮጵያ ዜግነት ሊያገኙ ይችላሉ።
3. ዜግነትን በሚመለከት ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

**አንቀጽ 7: የፆታ አገላለጽ**

በዚህ ሕገ መንግሥት ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል።

## ምዕራፍ ሁለት: የሕገ መንግሥቱ መሰረታዊ መርሆዎች

**አንቀጽ 8: የሕዝብ ሉዓላዊነት**

1. የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች የኢትዮጵያ ሉዓላዊ ሥልጣን ባለቤቶች ናቸው፡፡
2. ይህ ሕገ መንግሥት የሉዓላዊነታቸው መግለጫ ነው፡፡
3. ሉዓላዊነታቸውም የሚገለጸው በዚህ ሕገ መንግሥት መሰረት በሚመርጧቸው ተወካዮች በቀጥታ በሚያደርጉት ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎ አማካይነት ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 9: የሕገ መንግሥት የበላይነት**

1. ሕገ መንግሥቱ የሀገሪቱ የበላይ ሕግ ነው፡፡ ማንኛውም ሕግ፣ ልማዳዊ አሰራር፣እንዲሁም የመንግሥት አካል ወይም ባለሥልጣን ውሳኔ ከዚህ ሕገ መንግሥት ጋር የሚቃረን ከሆነ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡
2. ማንኛውም ዜጋ፣ የመንግሥት አካላት፣ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ ሌሎች ማኅበራት እንዲሁም ባለሥልጣኖቻቸው፣ ሕገ መንግሥቱን የማስከበርና ለሕገ መንግሥቱ ተገዢ የመሆን ኃላፊነት አለባቸው፡፡
3. በዚህ ሕገ መንግሥት ከተደነገገው ውጭ በማናቸውም አኳኋን የመንግሥት ሥልጣን መያዝ የተከለከለ ነው፡፡
4. ኢትዮጵያ ያጸደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች የሀገሪቱ ሕግ አካል ናቸው፡፡

**አንቀጽ 10: የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች**

1. ሰብዓዊ መብቶችና ነጻነቶች ከሰው ልጅ ተፈጥሮ የሚመነጩ፣ የማይጣሱና የማይገፈፉ ናቸው፡፡
2. የዜጐች እና የሕዝቦች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ይከበራሉ፡፡

**አንቀጽ 11: የመንግሥትና የሃይማኖት መለያየት**

1. መንግሥትና ሃይማኖት የተለያዩ ናቸው፡፡
2. መንግሥታዊ ሃይማኖት አይኖርም፡፡
3. መንግሥት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም፡፡ ሃይማኖትም በመንግሥት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም፡፡

**አንቀጽ 12: የመንግሥት አሠራርና ተጠያቂነት**

1. የመንግሥት አሠራር ለሕዝብ ግልጽ በሆነ መንገድ መከናወን አለበት፡፡
2. ማንኛውም ኃላፊና የሕዝብ ተመራጭ ኃላፊነቱን ሲያጓድል ተጠያቂ ይሆናል፡፡ሕዝብ በመረጠው ተወካይ ላይ እምነት ባጣ ጊዜ ከቦታው ለማንሳት ይችላል፡፡ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡

## ምዕራፍ ሦስት: መሰረታዊ መብቶችና ነጻነቶች

**አንቀጽ 13: ተፈጻሚነትና አተረጓጐም**

1.በማንኛውም ደረጃ የሚገኙ የፌዴራል መንግሥትና የክልል ሕግ አውጪ፣ ሕግ አስፈጻሚ እና የዳኝነት አካሎች በዚህ ምዕራፍ የተካተቱን ድንጋጌዎች የማክበርና የማስከበር ኃላፊነትና ግዴታ አለባቸው፡፡

2. በዚህ ምዕራፍ የተዘረዘሩት መሠረታዊ የመብቶችና የነጻነቶች ድንጋጌዎች ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ሕግጋት፣ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ ስምምነቶችና ዓለም አቀፍ ሰነዶች መርሆዎች ጋር በተጣጣመ መንገድ ይተረጐማል፡፡

## <u>ክፍል አንድ</u>

## <u>ሰብዓዊ መብቶች</u>

### <u>አንቀጽ 14</u>

የሕይወት፣ የአካል ደህንነትና የነጻነት መብት ማንኛውም ሰው ሰብዓዊ በመሆኑ የማይደፈርና የማይገሰስ በሕይወት የመኖር፣ የአካል ደህንነትና የነጻነት መብት አለው፡፡

### <u>አንቀጽ 15 የሕይወት መብት</u>

ማንኛውም ሰው በሕይወት የመኖር መብት አለው፡፡ ማንኛውም ሰው በሕግ በተደነገገ ከባድ የወንጀል ቅጣት ካልሆነ በስተቀር ሕይወቱን አያጣም፡፡

### <u>አንቀጽ 16 የአካል ደህንነት መብት</u>

ማንኛውም ሰው በአካሉ ላይ ጉዳት እንዳይደርስበት የመጠበቅ መብት አለው፡፡

### <u>አንቀጽ 17 የነጻነት መብት</u>

1. በሕግ ከተደነገገው ሥርዓት ውጭ ማንኛውም ሰው ወንድም ሆነ ሴት ነጻነቱን/ቷን አያጣም/አታጣም፡፡
2. ማንኛውም ሰው በሕግ ከተደነገገው ሥርዓት ውጭ ሊያዝ፣ ክስ ሳይቀርብበት ወይም ሳይፈረድበት ሊታሰር አይችልም፡፡

### <u>አንቀጽ 18 ኢሰብዓዊ አያያዝ ስለመከልከሉ</u>

1. ማንኛውም ሰው ጭካኔ ከተሞላበት፣ ኢሰብዓዊ ከሆነ ወይም ክብሩን ከሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት የመጠበቅ መብት አለው፡፡
2. ማንኛውም ሰው በባርነት ወይም በግዴታ አገልጋይነት ሊያዝ አይችልም፡፡ለማንኛውም ዓላማ በሰው የመነገድ ተግባር የተከለከለ ነው፡፡
3. ማንኛውም ሰው በኃይል ተገዶ ወይም ግዴታ ለማሟላት ማንኛውንም ሥራ እንዲሠራ ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 «በኃይል ተገዶ ወይም ግዴታን ለማሟላት»የሚለው ሐረግ የሚከተሉትን ሁኔታዎች አያካትትም፤

ሀ/ ማንኛውም እስረኛ በእስራት ላይ ባለበት ጊዜ በሕግ መሠረት እንዲሠራ የተወሰነውን ወይም በገደብ ከእስር በተለቀቀበት ጊዜ፣ የሚሠራውን ማንኛውም ሥራ፣

ለ/ ማንኛውም ወታደራዊ አገልግሎት ለመስጠት ሕሊናው የማይፈቅድለት ሰው በምትክ የሚሰጠውን አገልግሎት፣

ሐ/ የማኅበረሰቡን ሕይወት ወይም ደህንነት የሚያሰጋ የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ወይም አደጋ በሚያጋጥምበት ጊዜ የሚሰጥ ማንኛውም አገልግሎት፣

መ/ በሚመለከተው ሕዝብ ፈቃድ በአካባቢው የሚፈጸመውን ማንኛውንም ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ የልማት ሥራ።

## አንቀጽ 19 የተያዙ ሰዎች መብት

1. ወንጀል ፈጽመዋል በመባል የተያዙ ሰዎች የቀረበባቸው ክስና ምክንያቶቹ በዝርዝር ወዲያውኑ በሚገባቸው ቋንቋ እንዲነገራቸው መብት አላቸው።
2. የተያዙ ሰዎች ላለመናገር መብት አላቸው፤ የሚሰጡት ማንኛውም ቃል ፍርድ ቤት በማስረጃነት ሊቀርብባቸው እንደሚችል መረዳት በሚችሉት ቋንቋ እንደተያዙ ወዲያውኑ ማስገንዘቢያ እንዲሰጣቸው መብት አላቸው።
3. የተያዙ ሰዎች በአርባ ስምንት ሰዓታት ውስጥ ፍርድ ቤት የመቅረብ መብት አላቸው። ይህም ጊዜ ሰዎቹ ከተያዙበት ቦታ ወደ ፍርድ ቤት ለመምጣት አግባብ ባለው ግምት የሚጠይቀውን ጊዜ አይጨምርም። ወዲያውኑ ፍርድ ቤት እንደቀረቡ በተጠረጠሩበት ወንጀል ለመታሰር የሚያበቃ ምክንያት ያለ መሆኑ ተለይቶ እንዲገለጽላቸው መብት አላቸው።
4. የያዛቸው የፖሊስ መኮንን ወይም የሕግ አስከባሪ በጊዜው ገደብ ፍርድ ቤት በማቅረብ የተያዙበትን ምክንያት ካላስረዳ፣ ፍርድ ቤቱ የአካል ነጻነታቸውን እንዲያስከብርላቸው የመጠየቅ ሊጣስ የማይችል መብት አላቸው። ሆኖም ፍትሕ እንዳይጓደል ሁኔታው የሚጠይቅ ከሆነ ፍርድ ቤቱ የተያዘው ሰው በጥበቃ ሥር እንዲቆይ ለማዘዝ ወይም ምርመራ ለማካሄድ ተጨማሪ የምርመራ ጊዜ ሲጠየቅ አስፈላጊ በሆነ መጠን ብቻ ሊፈቅድ ይችላል። የሚያስፈልገውን ተጨማሪ ጊዜፍርድ ቤቱ ሲወስን ኃላፊ የሆኑት የሕግ አስከባሪ ባለሥልጣኖች ምርመራውን አጣርተው የተያዘው ሰው በተቻለ ፍጥነት ፍርድ ቤት እንዲቀርብ ያለውን መብት የሚያስከብር መሆን አለበት።
5. የተያዙ ሰዎች በራሳቸው ላይ በማስረጃነት ሊቀርብ የሚችል የእምነት ቃል እንዲሰጡ ወይም ማናቸውንም ማስረጃ እንዲያምኑ አይገደዱም።በማስገደድ የተገኘ ማስረጃ ተቀባይነት አይኖረውም።
6. የተያዙ ሰዎች በዋስ የመፈታት መብት አላቸው። ሆኖም በሕግ በተደነገጉ ልዩ ሁኔታዎች ፍርድ ቤት ዋስትና ላለመቀበል ወይም በገደብ መፍታትን ጨምሮ በቂ የሆነ የዋስትና ማረጋገጫ እንዲቀርብ ለማዘዝ ይችላል።

**አንቀጽ 20 የተከሰሱ ሰዎች መብት**

1. የተከሰሱ ሰዎች ክስ ከቀረበባቸው በኃላ ተገቢ በሆነ አጭር ጊዜ ውስጥ በመደበኛ ፍርድ ቤት ለሕዝብ ግልጽ በሆነ ችሎት የመሰማት መብት አላቸው፡፡ ሆኖም የተከራካሪዎቹን የግል ሕይወት፣ የሕዝብን የሞራል ሁኔታና የሀገሪቱን ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል ብቻ ክርክሩ በዝግ ችሎት ሊሰማ ይችላል፡፡
2. ክሱ በቂ በሆነ ዝርዝር እንዲነገራቸው እና ክሱን በጽሁፍ የማግኘት መብት አላቸው፡፡
3. በፍርድ ሂደት ባሉበት ጊዜ በተከሰሱበት ወንጀል እንደ ጥፋተኛ ያለመቆጠር፣በምስክርነት እንዲቀርቡም ያለመገደድ መብት አላቸው፡፡
4. የቀረበባቸውን ማናቸውንም ማስረጃ የመመልከት፣ የቀረቡባቸውን ምስክሮች የመጠየቅ፣ ለመከላከል የሚያስችላቸውን ማስረጃ የማቅረብ ወይም የማስቀረብ እንዲሁም ምስክሮቻቸው ቀርበው እንዲሰሙላቸው የመጠየቅ መብት አላቸው፡፡
5. በመረጡት የሕግ ጠበቃ የመወከል ወይም ጠበቃ ለማቆም አቅም በማጣታቸው ፍትሕ ሊጓደል የሚችልበት ሁኔታ ሲያጋጥም ከመንግሥት ጠበቃ የማግኘት መብት አላቸው፡፡
6. ክሩ በሚታይበት ፍርድ ቤት በተሰጠባቸው ትእዛዝ ወይም ፍርድ ላይ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብት አላቸው፡፡
7. የፍርዱ ሂደት በማይገባቸው ቋንቋ በሚካሄድበት ሁኔታ በመንግሥት ወጪ ክርክሩ እንዲተረጐምላቸው የመጠየቅ መብት አላቸው፡

**አንቀጽ 21 በጥበቃ ሥር ያሉና በፍርድ የታሰሩ ሰዎች መብት**

1. በጥበቃ ሥር ያሉና በፍርድ የታሰሩ ሰዎች ሰብዓዊ ክብራቸውን በሚጠብቁ ሁኔታዎች የመያዝ መብት አላቸው፡፡
2. ከትዳር ጓደኞቻቸው፣ ከቅርብ ዘመዶቻቸው፣ ከጓደኞቻቸው፣ ከሃይማኖት አማካሪዎቻቸው፣ ከሐኪሞቻቸው እና ከሕግ አማካሪዎቻቸው ጋር
3. ለመገናኘትና እንዲጐበኟቸውም ዕድል የማግኘት መብት አላቸው፡፡

**አንቀጽ 22 የወንጀል ሕግ ወደኋላ ተመልሶ የማይሰራ ስለመሆኑ**

1. ማንኛውም ሰው የወንጀል ክስ ሲቀርብበት የተከሰሰበት ድርጊት በተፈጸመበት ጊዜ ድርጊቱን መፈጸሙ ወይም አለመፈጸሙ ወንጀል መሆኑ በሕግ የተደነገገ ካልሆነ በስተቀር ሊቀጣ አይችልም፡፡ እንዲሁም ወንጀሉን በፈጸመበት ጊዜ ለወንጀሉ ተፈጻሚ ከነበረው የቅጣት ጣሪያ በላይ የከበደ ቅጣት በማንኛውም ሰው ላይ አይወሰንም፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ቢኖርም፣ ድርጊቱ ከተፈጸመ በኋላ የወጣ ሕግ ለተከሳሹ ወይም ለተቀጣው ሰው ጠቃሚ ሆኖ ከተገኘ ከድርጊቱ በኋላ የወጣው ሕግ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

<u>አንቀጽ 23 በአንድ ወንጀል ድጋሚ ቅጣት ስለመከልከሉ</u>

ማንኛውም ሰው በወንጀል ሕግና ሥነ ሥርዓት መሠረት ተከሶ የመጨረሻ በሆነ ውሳኔ ጥፋተኛነቱ በተረጋገጠበት ወይም በነጻ በተለቀቀበት ወንጀል እንደገና አይከሰስም ወይም አይቀጣም፡፡

<u>አንቀጽ 24 የክብርና የመልካም ስም መብት</u>

1. ማንኛውም ሰው ሰብዓዊ ክብሩና መልካም ስሙ የመከበር መብት አለው፡፡
2. ማንኛውም ሰው የራሱን ስብዕና ከሌሎች ዜጐች መብቶች ጋር በተጣጣመ ሁኔታ በነጻ የማሳደግ መብት አለው፡፡
3. ማንኛውም ሰው በማንኛውም ስፍራ በሰብዓዊነቱ እውቅና የማግኘት መብት አለው፡፡

<u>አንቀጽ 25 የእኩልነት መብት</u>

ሁሉም ሰዎች በሕግ ፊት እኩል ናቸው፤ በመካከላቸውም ማንኛውም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግ በሕግ እኩል ጥበቃ ይደረግላቸዋል፡፡ በዚህ ረገድ በዘር፣በብሔር፣ ብሔረሰብ፣በቀለም፣ በጾታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ፣ በማኅበራዊ አመጣጥ፣ በሀብት፣በትውልድ ወይም በሌላ አቋም ምክንያት ልዩነት ሳይደረግ ሰዎች ሁሉ እኩልና ተጨባጭ የሕግ ዋስትና የማግኘት መብት አላቸው፡፡

<u>አንቀጽ 26 የግል ሕይወት የመከበርና የመጠበቅ መብት</u>

1. ማንኛውም ሰው የግል ሕይወቱ፣ ግላዊነቱ፣ የመከበር መብት አለው፡፡ ይህ መብት መኖሪያ ቤቱ፣ ሰውነቱና ንብረቱ ከመመርመር እንዲሁም በግል ይዞታው ያለ ንብረት ከመያዝ የመጠበቅ መብትን ያካትታል፡፡
2. ማንኛውም ሰው በግል የሚጽፋቸውንና የሚጻጻፋቸው፣ በፖስታ የሚልካቸው ደብዳቤዎች፣ እንዲሁም በቴሌፎን፣ በቴሌኮሙኒኬሽንና በኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች የሚያደርጋቸው ግንኙነቶች አይደፈሩም፡፡
3. የመንግሥት ባለሥልጣኖች እነዚህን መብቶች የማክበርና የማስከበር ግዴታ አለባቸው፡፡ አስገዳጅ ሁኔታዎች ሲፈጠሩና ብሔራዊ ደህንነትን፣ የሕዝብን ሰላም፣ወንጀልን በመከላከል፣ ጤናንና የሕዝብን የሞራል ሁኔታ በመጠበቅ ወይም የሌሎችን መብትና ነጻነት በማስከበር ዓላማዎች ላይ በተመሰረቱ ዝርዝር ሕጐች መሰረት ካልሆነ በስተቀር የእነዚህ መብቶች አጠቃቀም ሊገደብ አይችልም፡፡

<u>አንቀጽ 27 የሃይማኖት፣ የእምነትና የአመለካከት ነጻነት</u>

1. ማንኛውም ሰው የማሰብ፣ የሕሊና እና የሃይማኖት ነጻነት አለው፡፡ ይህ መብት ማንኛውም ሰው የመረጠውን ሃይማኖት ወይም እምነት የመያዝ ወይም የመቀበል፣ ሃይማኖቱንና እምነቱን ለብቻ ወይም ከሌሎች ጋር በመሆን በይፋ ወይም በግል የማምለክ፣ የመከተል፣ የመተግበር፣ የማስተማር ወይም የመግለጽ መብትን ያካትታል፡፡
2. በአንቀጽ 90 ንዑስ አንቀጽ 2 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የሃይማኖት ተከታዮች ሃይማኖታቸውን ለማስፋፋትና ለማደራጀት የሚያስችሏቸው የሃይማኖት ትምህርትና የአስተዳደር ተቋማት ማቋቋም ይችላሉ፡፡
3. ማንኛውንም ሰው የሚፈልገውን እምነት ለመያዝ ያለውን ነጻነት በኃይል ወይም በሌላ ሁኔታ በማስገደድ መገደብ ወይም መከልከል አይቻልም፡፡
4. ወላጆችና ሕጋዊ ሞግዚቶች በእምነታቸው መሰረት የሃይማኖታቸውንና የመልካም ሥነ ምግባር ትምህርት በመስጠት ልጆቻቸውን የማሳደግ መብት አላቸው፡፡
5. ሃይማኖትና እምነትን የመግለጽ መብት ሊገደብ የሚችለው የሕዝብን ደህንነት፣ሰላምን፣ ጤናን፣ ትምህርትን፣ የሕዝብን የሞራል ሁኔታ፣ የሌሎች ዜችን መሰረታዊ መብቶች፣ ነጻነቶች እና መንግስት ከሃይማኖት ነጻ መሆኑን ለማረጋረገጥ በሚወጡ ሕጐች ይሆናል፡፡

**<u>አንቀጽ 28 በስብእና ስለሚፈደሙ ወንጀሎች</u>**

1. ኢትዮጵያ ባጸደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች እና በሌሎች የኢትዮጵያ ሕጐች በሰው ልጅ ላይ የተፈጸሙ ወንጀሎች ተብለው የተወሰኑትን ወንጀሎች፤የሰው ዘር የማጥፋት፣ ያለፍርድ የሞት ቅጣት እርምጃ የመውሰድ፣ በአስገዳጅ ሰውን የመሰወር፣ ወይም ኢሰብዓዊ የድብደባ ድርጊቶችን
2. በፈጸሙ ሰዎች ላይ ክስ ማቅረብ በይርጋ አይታገድም፡፡ በሕግ አውጪው ክፍልም ሆነ በማንኛውም የመንግሥት አካል ውሳኔዎች በምሕረት ወይም በይቅርታ አይታለፉም፡፡
3. ከዚህ በላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተቀሱትን ወንጀሎች ፈጽመው የሞት ቅጣት ለተፈረደባቸው ሰዎች ርዕሰ ብሔሩ ቅጣቱን ወደ ዕድሜ ልክ ጽኑ እስራት ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

**<u>ዴሞክራሲያዊ መብቶች</u>**

**<u>አንቀጽ 29 የአመለካከት እና ሐሳብን በነጻ የመያዝና የመግለጽ መብት</u>**

1. ማንኛውም ሰው ያለማንም ጣልቃ ገብነት የመሰለውን አመለካከት ለመያዝ ይችላል፡፡
2. ማንኛውም ሰው ያለማንም ጣልቃ ገብነት ሐሳቡን የመግለጽ ነጻነት አለው፡፡ ይህ ነጻነት በሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጭ ወሰን ሳይደረግበት

3. በቃልም ሆነ በጽሑፍ ወይም በሕትመት፣ በሥነ ጥበብ መልክ ወይም በመረጠው በማንኛውም የማሰራጫ ዘዴ፣ ማንኛውንም ዓይነት መረጃና ሐሳብ
4. የመሰብሰብ፣ የመቀበልና የማሰራጨት ነጻነቶችን የካትታል፡፡
5. የኘሬስና የሌሎች መገናኛ ብዙኃን፣ እንዲሁም የሥነ ጥበብ ፈጠራ ነጻነት ተረጋግጧል፡፡ የኘሬስ ነጻነት በተለይ የሚከተሉትን መብቶች ያጠቃልላል፣

ሀ/ የቅድሚያ ምርመራ በማንኛውም መልኩ የተከለከለ መሆኑን፣

ለ/ የሕዝብን ጥቅም የሚመለከት መረጃ የማግኘት ዕድልን፡፡

6. ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች፣ ሐሳቦችና አመለካከቶች በነጻ መንሸራሸራቸውን ለማረጋገጥ ሲባል ኘሬስ በተቋምነቱ የአሠራር ነጻነትና የተለያዩ አስተያየቶች የማስተናገድ ችሎታ እንዲኖረው የሕግ ጥበቃ ይደረግለታል፡፡
5. በመንግሥት ገንዘብ የሚካሄድ ወይም በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ያለ መገናኛ ብዙኃን የተለያዩ አስተያየቶችን ለማስተናገድ በሚያስችለው ሁኔታ እንዲመራ ይደረጋል፡፡
6. እነዚህ መብቶች ገደብ ሊጣልባቸው የሚችለው የሀሳብና መረጃ የማግኘት ነጻነት በአስተሳሰባዊ ይዘቱና ሊያስከትል በሚችለው አስተሳሰባዊ ውጤት ሊገታ አይገባውም በሚል መርህ ላይ ተመስርተው በሚወጡ ሕጐች ብቻ ይሆናል፡፡
7. የወጣቶችን ደህንነት፣ የሰውን ክብርና መልካም ስም ለመጠበቅ ሲባል ሕጋዊ ገደቦች በነዚህ መብቶች ላይ ሊደነገጉ ይችላሉ፡፡ የጦር ቅስቃሴዎች እንዲሁም ሰብዓዊ ክብርን የሚነኩ የአደባባይ መግለጫዎች በህግ የሚከለከሉ ይሆናል፡፡
8. ማንኛውም ዜጋ ከላይ በተጠቀሱት መብቶች አጠቃቀም ረገድ የሚጣሉ ሕጋዊ ገደቦችን ጥሶ ከተገኘ በሕግ ተጠያቂ ሊሆን የችላል፡፡

<u>**አንቀጽ 30 የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነጻነትና አቤቱታ የማቅረብ መብት**</u>

1. ማንኛውም ሰው ከሌሎች ጋር በመሆን መሣሪያ ሳይዝ በሰላም የመሰብሰብ፣ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነጻነትና፣ አቤቱታ የማቅረብ መብት አለው፡፡ ከቤት ውጭ የሚደረጉ ስብሰባዎችና ሰላማዊ ሰልፎች በሚንቀሳቀሱባቸው ቦታዎች በሕዝብ እንቅስቃሴ ላይ ችግር እንዳይፈጥሩ ለማድረግ ወይም በመካሔድ ላይ ያለ ስብሰባ ወይም ሰላማዊ ሰልፍ ሰላምን፣ ዴሞክራሲያዊ መብቶችንና የሕዝብን የሞራል ሁኔታ እንዳይጥሱ ለማስጠበቅ አግባብ ያላቸው ሥርዓቶች ሊደነገጉ ይችላሉ፡፡
2. ይህ መብት የወጣቶችን ደህንነት፣ የሰውን ክብርና መልካም ስምን ለመጠበቅ፣የጦርነት ቅስቀሳዎች እንዲሁም ሰብዓዊ ክብርን የሚነኩ የአደባባይ መግለጫዎችን ለመከላከል ሲባል በሚወጡ ሕጐች መሰረት ተጠያቂ ከመሆን አያድንም፡፡

**አንቀጽ 31 የመደራጀት መብት**

ማንኛውም ሰው ለማንኛውም ዓላማ በማኅበር የመደራጀት መብት አለው፡፡ ሆኖም አግባብያለውን ሕግ በመጣስ ወይም ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን በሕገ ወጥ መንገድ ለማፍረስ የተመሰረቱ ወይም የተጠቀሱትን ተግባራት የሚያራምዱ ድርጅቶች የተከለከሉ ይሆናሉ፡፡

**አንቀጽ 32 የመዘዋወር ነጻነት**

1. ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወይም በሕጋዊ መንገድ ሀገሪቱ ውስጥ የሚገኝ የውጭ ዜጋ በመረጠው የሀገሪቱ አካባቢ የመዘዋወርና የመኖሪያ ቦታ የመመስረት፣እንዲሁም በፈለገው ጊዜ ከሀገር የመውጣት ነጻነት አለው፡፡
2. ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወደ ሀገሩ የመመለስ መብት አለው፡፡

**አንቀጽ 33 የዜግነት መብቶች**

1. ማንኛውም ኢትዮጵያዊ/ኢትዮጵያዊት ከፈቃዱ/ከፈቃዷ ውጭ ኢትዮጵያዊ ዜግነቱን/ዜግነትዋን ሊገፈፍ ወይም ልትገፈፍ አይችልም/አትችልም፡፡ኢትዮጵያዊ / ኢትዮጵያዊት ዜጋ ከሌላ ሀገር ዜጋ ጋር የሚፈጽመው/የምጽትፈጽመው ጋብቻ ኢትዮጵያዊ ዜግነቱን / ዜግነትዋን አያስቀርም፡፡
2. ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ የኢትዮጵያ ዜግነት በሕግ የሚያስገኘውን መብት ጥበቃና ጥቅም የማግኘት መብት አለው፡፡
3. ማንኛውም ዜጋ ኢትዮጵያዊ ዜግነቱን የመለወጥ መብት አለው፡፡
4. ኢትዮጵያ ከአጸደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ጋር በማይቃረን መንገድ በሚወጣ ሕግ እና በሚደነገግ ሥርዓት መሰረት የኢትዮጵያ ዜግነት ለውጭ ሀገር ሰዎች ሊሰጥ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 34 የጋብቻ፣ የግልና የቤተሰብ መብቶች**

1. በሕግ ከተወሰነው የጋብቻ ዕድሜ የደረሱ ወንዶችና ሴቶች በዘር፣ በበሔር፣በብሔረሰብ ወይም በሃይማኖት ልዩነት ሳይደረግባቸው የማግባትና ቤተሰብ የመመስረት መብት አላቸው፡፡ በጋብቻ አፈጻጸም፣ በጋብቻው ዘመንና በፍቺ ጊዜ እኩል መብት አላቸው፡፡ በፍቺም ጊዜ የልጆችን መብትና ጥቅም እንዲከበር የሚያደርጉ ድንጋጌዎች ይደነገጋሉ፡፡
2. ጋብቻ በተጋቢዎች ነጻና ሙሉ ፈቃድ ላይ ብቻ ይመሰረታል፡፡
3. ቤተሰብ የኅብረተሰብ የተፈጥሮ መሰረታዊ መነሻ ነው፡፡ ከኅብረተሰብና ከመንግሥት ጥበቃ የማግኘት መብት አለው፡፡
4. በሕግ በተለይ በሚዘረዘረው መሰረት በሃይማኖት፣ በባሕል የሕግ ሥርዓቶች ላይ ተመስርተው ለሚፈጸሙ ጋብቻዎች እውቅና የሚሰጥ ሕግ ሊወጣ ይችላል፡፡

5. ይህ ሕገ መንግሥት የግል እና የቤተሰብ ሕግን በተመለከተ በተከራካሪዎች ፈቃድ በሃይማኖቶች ወይም በባሕሎች ሕጐች መሰረት መዳኘትን አይከለክልም፡፡ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡

<u>አንቀጽ 35 የሴቶች መብት</u>

1. ሴቶች ይህ ሕገ መንግሥት በአረጋገጣቸው መብቶችና ጥበቃዎች በመጠቀም ረገድ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው፡፡
2. ሴቶች በዚህ ሕገ መንግሥት በተደነገገው መሰረት በጋብቻ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው፡፡
3. ሴቶች በበታችነትና በልዩነት በመታየታቸው የደረሰባቸውን የታሪክ ቅርስ ከግምት ውስጥ በማስገባት ይህ ቅርስ እንዲታረምላቸው በተጨማሪ የድጋፍ እርምጃዎች ተጠቃሚ የመሆን መብት አላቸው፡፡ በዚህ በኩል የሚወሰዱት እርምጃዎች ዓላማ በፖለቲካዊ፣ በማኅበራዊና በኢኮኖሚያዊ መስኮች እንዲሁም በመንግሥት እና በግል ተቋሞች ውስጥ ሴቶች ከወንዶች ጋር በእኩልነት ተወዳዳሪና ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማድረግ እንዲቻል ልዩ ትኩረት ለመስጠት ነው፡፡
4. ሴቶች ከጐጂ ባሕል ተጽዕኖ የመላቀቅ መብታቸውን መንግሥት ማስከበር አለበት፡፡ ሴቶችን የሚጨቁኑ ወይም በአካላቸው ወይም በአዕምሮአቸው ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ ሕጐች፣ ወጐችና ልማዶች የተከለከሉ ናቸው፡፡
5. ሴቶች የወሊድ ፈቃድ ከሙሉ የደመወዝ ክፍያ ጋር የማግኘት መብት አላቸው፡፡

   ሀ/ የወሊድ ፈቃድ ርዝመት ሴቷ የምትሠራውን ሥራ ሁኔታ፣የሴቷን ጤንነት፣ የሕጻኑንና የቤተሰቡን ደህንነት ከግምት ውስጥ በማስገባት በሕግ ይወሰናል፡፡

   ለ/ የወሊድ ፈቃድ በሕግ በሚወሰነው መሰረት ከሙሉ የደመወዝ ክፍያ ጋር የሚሰጥ የእርግዝና ፈቃድን ሊጨምር ይችላል፡፡
6. ሴቶች በብሔራዊ የልማት ፖሊሲዎች ዕቅድና በፕሮጀክቶች ዝግጅትና አፈጻጸም፣በተለይ የሴቶችን ጥቅም በሚነኩ ፕሮጀክቶች ሐሳባቸውን በተሟላ ሁኔታ እንዲሰጠ የመጠየቅ መብት አላቸው፡፡
7. ሴቶች ንብረት የማፍራት፣ የማስተዳደር፣ የመቆጣጠር፣ የመጠቀምና የማስተላለፍ መብት አላቸው፡፡ በተለይም መሬትን በመጠቀም፣ በማስተላለፍ፣ በማስተዳደርና በመቆጣጠር ረገድ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው፡፡ እንዲሁም ውርስን በሚመለከት በእኩልነት የመታየት መብት አላቸው፡፡
8. ሴቶች የቅጥር፣ የሥራ እድገት፣ የእኩል ክፍያና ጡረታን የማስተላለፍ እኩል መብት አላቸው፡፡

9. ሴቶች በእርግዝናና በወሊድ ምክንያት የሚደርስባቸውን ጉዳት ለመከላከልና ጤንነታቸውን ለማስጠበቅ የሚያስችል የቤተሰብ ምጣኔ ትምህርት፣ መረጃ እና አቅም የማግኘት መብት አላቸው፡፡

## አንቀጽ 36 የሕጻናት መብት

1.ማንኛውም ሕጻን የሚከተሉት መብቶች አሉት፤

ሀ/ በሕይወት የመኖር፣

ለ/ ስምና ዜግነት የማግኘት፣

ሐ/ ወላጆቹን ወይም በሕግ የማሳደግ መብት ያላቸውን ሰዎች የማወቅና የእነሱንም እንክብካቤ የማግኘት፣

መ/ ጉልበቱን ከሚበዘብዙ ልማዶች የመጠበቅ፣ በትምህርት½ በጤናውና በደህንነቱ ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ሥራዎች እንዲሠራ ያለመገደድ ወይም ከመሥራት የመጠበቅ፣

ሠ/ በትምህርት ቤቶች ወይም በሕጻናት ማሳደጊያ ተቋሞች ውስጥ በአካሉ ከሚፈጸም ወይም ከጭካኔና ኢሰብዓዊ ከሆነ ቅጣት ነጻ የመሆን፡፡

2. ሕጻናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች በሚወሰዱበት ጊዜ በመንግሥታዊ ወይም በግል የበጐ አድራጐት ተቋሞች፣ በፍርድ ቤቶች፣ በአስተዳደር ባለሥልጣኖች ወይም በሕግ አውጪ አካላት የሕጻናት ደህንነት በቀደምትነት መታሰብ አለበት፡፡

3. ወጣት አጥፊዎች፣ በማረሚያ ወይም በመቋቋሚያ ተቋሞች የሚገኙ፣ በመንግሥት እርዳታ የሚያድጉ ወጣቶች፣ በመንግሥት ወይም በግል እጓለ ማውታን ተቋሞች ውስጥ የሚገኙ መጣቶች ከአወቂዎች ተለይተው መያዝ አለባቸው፡፡

4. ከጋብቻ ውጭ የተወለዱ ሕጻናት በጋብቻ ከተወለዱ ሕጻናት ጋር እኩል መብት አላቸው፡፡

መንግሥት ለእጓለ ማውታን ልዩ ጥበቃ ያደርግላቸዋል፡፡ በጉዲፈቻ የሚያድጉበትን ሥርዓት የሚያመቻቹና የሚያስፋፉ እንዲሁም ደህንነታቸውን ትምህርታቸውን የሚያራምዱ ተቋሞች እንዲመሰረቱ ያበረታታል፡፡

## አንቀጽ 37 ፍትሕ የማግኘት መብት

1. ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለው፡፡

2. . በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተውን ውሳኔ ወይም ፍርድ፤

ሀ/ ማንኛውም ማኅበር የአባላቱን የጋራ ወይም የግል ጥቅም በመወከል፣

ለ/ ማንኛውም ቡድን ወይም ተመሳሳይ ጥቅም ያላቸውን ሰዎች የሚወክል ግለሰብ ወይም የቡድን አባል የመጠየቅና የማግኘት መብት አለው፡፡

## አንቀጽ 38 የመምረጥና የመመረጥ መብት

1. ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ በቀለም፣ በዘር፣ በብሔር፣ በብሔረሰብ፣ በጾታ፣በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ ወይም በሌላ አመለከካከት ወይም በሌላ አቋም ላይ የተመሰረተ ልዩነት ሳይደረግበት የሚከተሉት መብቶች አሉት፤

   ሀ/ በቀጥታ እና በነጻነት በመረጣቸው ተወካዮች አማካኝነት በሕዝብ ጉዳይ አስተዳደር የመሳተፍ፣

   ለ/ ዕድሜው 18 ዓመት ሲሞላ በሕግ መሰረት የመምረጥ ፣

   ሐ/ በማናቸውም የመንግሥት ደረጃ በየጊዜው በሚካሄድ ምርጫ የመምረጥና የመመረጥ። ምርጫው ሁሉ አቀፍ፣ በሁሉም እኩልነት ላይ የተመሰረተና በሚስጥር ድምጽ አሰጣጥ መራጩ ፈቃዱን በነጻነት የሚገልጽበት ዋስትና የሚሰጥ መሆን አለበት።

2. በፖለቲካ ድርጅቶች፣ በሠራተኞች፣ በንግድ፣ በአሠሪዎችና በሙያ ማኅበራት ለተሳትፎ ድርጅቱ የሚጠይቀውን ጠቅላላና ልዩ የአባልነት መስፈርት የሚያሟላ ማንኛውም ሰው በፍላጐቱ አባል የመሆን መብቱ የተከበረ መሆን አለበት።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 በተመለከቱት ድርጅቶች ውስጥ ለኃላፊነት ቦታዎች የሚካሄዱ ምርጫዎች ነጻና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ይፈጸማሉ።
4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 ድንጋጌዎች የሕዝብን ጥቅም ሰፋ ባለ ሁኔታ የሚነኩ እስከሆነ ድረስ በሕዝባዊ ድርጅቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ።

## አንቀጽ 39 የብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች መብት

1. ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ የራሱን ዕድል በራሱ የመወሰን እስከመገንጠል ያለው መብቱ በማናቸውም መልኩ ያለ ገደብ የተጠበቀ ነው።
2. ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ በቋንቋው የመናገር፣ የመጻፍ፣ቋንቋውን የማሳደግ እና ባሕሉን የመግለጽ፣ የማዳበርና የማስፋፋት እንዲሁም ታሪኩን የመንከባከብ መብት አለው።
3. ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ ራሱን የማስተዳደር ሙሉ መብት አለው። ይህ መብት ብሔሩ፣ ብሔረሰቡ፣ ሕዝቡ በሰፈረበት መልክዓ ምድር ራሱን የሚያስተዳድርበት መንግሥታዊ ተቋማት የማቋቋም እንዲሁም በክልልና በፌዴራል አስተዳደሮች ውስጥ ሚዛናዊ ውክልና የማግኘት መብትን ያጠቃልላል።
4. የብሔር፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን እስከ መገንጠል መብት ከሥራ ላይ የሚውለው፤

ሀ/ የመገንጠል ጥያቄ በብሔር፣ በብሔረሰቡ ወይም በሕዝቡ የሕግ አውጪ ምክር ቤት በሁለት ሦስተኛ የድምጽ ድጋፍ ተቀባይነት ማግኘቱ ሲረጋገጥ፤

ለ/ የፌዴራሉ መንግሥት የብሔር፣ የብሔረሰቡ ወይም የሕዝቡ ምክር ቤት ውሳኔ በደረሰው በሦስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ለጠያቂው ብሔር፣ብሔረሰብ ወይም ሕዝብ ሕዝበ ውሳኔ ሲያደራጅ፤

ሐ/ የመገንጠሉ ጥያቄ በሕዝበ ውሳኔው በአብላጫ ድምጽ ሲደገፍ፤

መ/ የፌዴራሉ መንግሥት መገንጠሉን ለመረጠው ብሔር፣ ብሔረሰብ ወይም ሕዝብ ምክር ቤት ሥልጣኑን ሲያስረክብ፤

ሠ/ በሕግ በሚወሰነው መሠረት የንብረት ክፍፍል ሲደረግ ነው፡፡

5. በዚህ ሕገ መንግሥት ውስጥ «ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ» ማለት ከዚህ ቀጥሎ የተገለጸውን ባህርይ የሚያሳይ ማኅበረሰብ ነው፡፡ ሰፋ ያለ የጋራ ጠባይ የሚያንጸባርቅ ባሕል ወይም ተመሳሳይ ልምዶች ያላቸው፣ ሊግባቡት የሚችሉበት የጋራ ቋንቋ ያላቸው፣ የጋራ ወይም የተዛመደ ሕልውና አለን ብለው የሚያምኑ፣የሥነ ልቦና አንድነት ያላቸውና በአብዛኛው በተያያዘ መልክዓ ምድር የሚኖሩ ናቸው፡፡

<u>**አንቀጽ 40 የንብረት መብት**</u>

1. ማንኛውም የኢትዮጵያ ዜጋ የግል ንብረት ባለቤት መሆኑ/መሆኗ ይከበርለታል/ ይከበርላታል፡፡ ይህ መብት የሕዝብን ጥቅም ለመጠበቅ በሌላ ሁኔታ በሕግ እስካልተወሰነ ድረስ ንብረት የመያዝና በንብረት የመጠቀም ወይም የሌሎችን ዜጐች መብቶች እስካልተቃረነ ድረስ ንብረትን የመሸጥ የማውረስ ወይም በሌላ መንገድ የማስተላለፍ መብቶችን ያካትታል፡፡
2. ለዚህ አንቀጽ ዓላማ «የግል ንብረት» ማለት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ወይም ሕጋዊ ሰውነት በሕግ የተሰጣቸው ኢትዮጵያዊ ማኅበራት ወይም አግባብ በአላቸው ሁኔታዎች በሕግ በተለየ በጋራ የንብረት ባለቤት እንዲሆኑ የተፈቀደላቸው ማኅበረሰቦች በጉልበታቸው፣ በመፍጠር ችሎታቸው ወይም በካፒታላቸው ያፈሩት ተጨባጭ የሆነና የተጨባጭነት ጠባይ ሳይኖረው ዋጋ ያለው ውጤትነው፡፡
3. የገጠርም ሆነ የከተማ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት መብት የመንግሥትና የሕዝብ ብቻ ነው፡፡ መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የጋራ ንብረት ነው፡፡
4. የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች መሬት በነጻ የማግኘትና ከመሬታቸው ያለመነቀል መብታቸው የተከበረ ነው፡፡ አፈጻጸሙን በተመለከተ ዝርዝር ሕግ ይወጣል፡፡
5. የኢትዮጵያ ዘላኖች ለግጦሽም ሆነ ለእርሻ የሚጠቀሙበት መሬት በነጻ የማግኘት፣የመጠቀምና ከመሬታቸው ያለመፈናቀል መብት አላቸው፡፡ ዝርዝር አፈጻጸሙ በሕግ ይወሰናል፡፡

6. የመሬት ባለቤትነት የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ መንግሥት ለግል ባለሀብቶች በሕግ በሚወሰን ክፍያ በመሬት የመጠቀም መብታቸውን ያስከብርላቸዋል፡፡ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡
7. ማንም ኢትዮጵያዊ በጉልበቱ፣ ወይም በገንዘቡ በመሬት ላይ ለሚገነባው ቋሚ ንብረት ወይም ለሚያደርገው ቋሚ መሻሻል ሙሉ መብት አለው፡፡ ይህ መብት የመሸጥ፣ የመለወጥ፣ የማውረስ፣ የመሬት ተጠቃሚነቱ ሲቋረጥ ንብረቱን የማንሳት፣ ባለቤትነቱን የማዛወር ወይም የካሳ ክፍያ የመጠየቅ መብትን ያካትታል፡፡ ዝርዝር አፈጻጸሙ በሕግ ይወሰናል፡፡
8. የግል ንብረት ባለቤትነት መብት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ መንግሥት ለሕዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ተመጣጣኝ ካሳ በቅድሚያ በመክፈል የግል ንብረትን ለመውሰድ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 41 የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የባሕል መብቶች

1. ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በሀገሪቱ ውስጥ በማንኛውም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የመሰማራትና ለመተዳደሪያው የመረጠውን ሥራ የመሥራት መብት አለው፡፡
2. ሁሉም ኢትዮጵያዊ መተዳደሪያውን፣ ሥራውንና ሙያውን የመምረጥ መብት አለው፡፡
3. የኢትዮጵያ ዜጎች ሁሉ በመንግሥት ገንዘብ በሚካሄዱ ማኅበራዊ አገልግሎቶች በእኩልነት የመጠቀም መብት አላቸው፡፡
4. መንግሥት የጤና፣ የትምህርትና ሌሎች የማኅበራዊ አገልግሎቶችን ለሕዝብ ለማቅረብ በየጊዜው እየጨመረ የሚሄድ ሀብት ይመድባል፡፡
5. መንግሥት የአካል እና የአዕምሮ ጉዳተኞችን፣ አረጋዊያንንና ያለወላጅ ወይም ያለአሳዳጊ የቀሩ ሕጻናትን ለማቋቋምና ለመርዳት የሀገሪቱ የኢኮኖሚ አቅም በፈቀደው ደረጃ እንክብካቤ ያደርጋል፡፡
6. መንግሥት ለሥራ አጦችና ለችግረኞች ሥራ ለመፍጠር የሚያስችል ፖሊሲ ይከተላል፤ እንዲሁም በሚያካሂደው የሥራ ዘርፍ ውስጥ የሥራ ዕድል ለመፍጠር የሥራ ኘሮግራሞችን ያወጣል፣ ኘሮጀክቶችን ያካሂዳል፡፡
7. መንግሥት ዜጎች ጠቃሚ ሥራ የማግኘት ዕድላቸው እየሰፋ እንዲሄድ ለማድረግ አስፈላጊ እርምጃዎችን ይወስዳል፡፡
8. ገበሬዎችና ዘላን ኢትዮጵውያን በየጊዜው እየተሻሻለ የሚሄድ ኑሮ ለመኖር የሚያስችላቸውና ለምርት ካደረጉት አስተዋጽኦ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ተገቢ ዋጋ ለምርት ውጤቶቻቸው የማግኘት መብት አላቸው፡፡ መንግሥት የኢኮኖሚ፣የማኅበራዊና የልማት ፖሊሲዎችን በሚተልምበት ጊዜ በዚህ ዓላማ መመራት አለበት፡፡

9. መንግሥት የባሕልና የታሪክ ቅርሶችን የመንከባከብና ለሥነ ጥበብና ለስፖርትመስፋፋት አስተዋጽኦ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡

## አንቀጽ 42 የሠራተኞች መብት

1፡፡የፋብሪካና የአገልግሎት ሠራተኞች፣ ገበሬዎች፣ የእርሻ ሠራተኞች፣ ሌሎች የገጠር ሰራተኞች፣ከተወሰነ ኃላፊነት ደረጃ በታች ያሉና የሥራ ጠባያቸው የሚፈቅድላቸ የመንግሥት ሠራተኞች የሥራና የኢኮኖሚ ሁኔታዎችን ለማሻሻል በማኅበር የመደራጀት መብት አላቸው።

ሀ/ይህ መብት የሠራተኛ ማኅበራትና ሌሎች ማኅበራትን የማደራጀት፣ ከአሠሪዎችና ጥቅማቸውን ከሚነኩ ሌሎች ድርጅቶች ጋር የመደራደር መብትን ያካትታል፡፡

ለ/ በንዑስ አንቀጽ /ሀ/ የተመለከቱት የሠራተኛ ክፍሎች ሥራ ማቆምን ጨምሮ ቅሬታቸውን የማሰማት መብት አላቸው፡፡

ሐ/ በንዑስ አንቀጽ /ሀ/ እና /ለ/ መሠረት እውቅና ባገኙት መብቶች ለመቀም የሚችሉት የመንግሥት ሠራተኞች በሕግ ይወሰናሉ፡፡

መ/ ሴቶች ሠራተኞች ለተመሳሳይ ሥራ ተመሳሳይ ክፍያ የማግኘት መብታቸው የተጠበቀ ነው፡፡

2. ሠራተኞች በአግባቡ የተወሰነ የሥራ ሰዓት ዕረፍት፣ የመዝናኛ ጊዜ፣ በየጊዜው ከክፍያ ጋር የሚሰጡ የዕረፍት ቀኖች፣ ደመወዝ የሚከፈልባቸው የሕዝብ በዓላት እንዲሁም ጤናማና አደጋ የማያደረስ የሥራ አካባቢ የማግኘት መብት አላቸው፡፡

3. እነዚህን መብቶች ተግባራዊ ለማድረግ የሚወጡ ሕጎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት እውቅና ያገኙትን መብቶች ሳይቀንሱ የተጠቀሱት ዓይነት የሠራተኛ ማኅበራት ስለሚቋቋሙበትና የጋራ ድርድር ስለሚካሄድበት ሥርዓት ይደነግጋሉ፡፡

## አንቀጽ 43 የልማት መብት

1. የኢትዮጵያ ሕዝቦች በአጠቃላይም ሆነ በኢትዮጵያ ያሉ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች በተናጠል የኑሮ ሁኔታቸውን የማሻሻልና የማያቋርጥ እድገት የማግኘት መብታቸው የተጠበቀ ነው፡፡
2. ዜጎች በብሔራዊ ልማት የመሳተፍ በተለይም አባል የሆኑበትን ማኅበረሰብ የሚመለከቱ ፖሊሲዎችና ኘሮጀክቶች ላይ ሐሳባቸውን እንዲሰጡ የመጠየቅ መብት አላቸው፡፡
3. መንግሥት በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚገባቸው ስምምነቶችም ሆኑ የሚያደርጋቸው ግንኙነቶች የኢትዮጵያን የማያቋርጥ እድገት መብት የሚያስከብሩ መሆን አለባቸው፡፡
4. የልማት እንቅስቀሴ ዋና ዓላማ የዜጐችን እድገትና መሰረታዊ ፍላጐቶች ማሟላት ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 44 የአካባቢ ደህንነት መብት

1. ሁሉም ሰዎች ንዐህና ጤናማ በሆነ አካባቢ የመኖር መብት አላቸው፡፡

2. መንግሥት በሚያካሂዳቸው ኘሮግራሞች ምክንያት የተፈናቀሉ ወይም ኑሮአቸው የተነካባቸው ሰዎች ሁሉ በመንግሥት በቂ እርዳታ ወደ ሌላ አካባቢ መዘዋወርን ጨምሮ ተመጣጣኝ የሆነ የገንዘብ ወይም ሌላ አማራጭ ማካካሻ የማግኘት መብት አላቸው፡፡

## ምዕራፍ አራት : የመንግሥት አወቃቀር

### አንቀጽ 45 ሥርዓተ መንግሥት

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሥርዓተ መንግሥት ፓርላሜንታዊ ነው፡፡

### አንቀጽ 46 የፌዴራል ክልሎች

የፌዴራሉ መንግሥት በክልሎች የተዋቀረ ነው፡፡

1. ክልሎች የሚዋቀሩት በሕዝብ አሰፋፈር፣ ቋንቋ፣ የማንነት እና ፈቃድ ላይ በመመስረት ነው፡፡

### አንቀጽ 47 የፌዴራል መንግሥት አባላት

1. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አባላት የሚከተሉት ናቸው፡፡

   1. የትግራይ ክልል
   2. የአፋር ክልል
   3. የአማራ ክልል
   4. የኦሮሚያ ክልል
   5. የሱማሌ ክልል
   6. የቤንሻንጉል/ጉሙዝ ክልል
   7. የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል
   8. የጋምቤላ ሕዝቦች ክልል
   9. የሐረሪ ሕዝብ ክልል

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከቱት ክልሎች ውስጥ የተካተቱ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች በማንኛውም ጊዜ የየራሳቸውን ክልል የማቋቋም መብት አላቸው፡፡
3. የማንኛውም ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ የራሱን ክልል የመመስረት መብት ሥራ ላይ የሚውለው፧

   ሀ/ የክልል መመስረት ጥያቄው በብሔሩ፣ በብሔረሰቡ ወይም በሕዝቡ ምክር ቤት በሁለት ሦስተኛ ድምጽ ተቀባይነት ማግኘቱ ሲረጋገጥና ጥያቄው በጽሑፍ ለክልሉ ምክር ቤት ሲቀርብ፧

   ለ/ ጥያቄው የቀረበለት የክልል ምክር ቤት ጥያቄው በደረሰው በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ለጠየቀው ብሔር፣ ብሔረሰብ ወይም ሕዝብ ሕዝበ ውሳኔ ሲያደራጅ፧

   ሐ/ ክልል የመመስረት ጥያቄው በብሔሩ፣ በብሔረሰቡ ወይም ሕዝቡ ሕዝበ ውሳኔ በአብላጫ ድምጽ ሲደገፍ፧

   መ/ የክልሉ ምክር ቤት ሥልጣኑን ለጠየቀው ብሔር፣ ብሔረሰብ ወይም ሕዝብ ሲያስረክብ፧

ሠ/ በሕዝበ ውሳኔ የሚፈጠረው አዲስ ክልል ጥያቄ ማቅረብ ሳያስፈልገው በቀጥታ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አባል ሲሆን ነው።

4. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አባላት እኩል መብትና ሥልጣን አላቸው።

**<u>አንቀጽ 48 የአከላለል ለውጦች</u>**

1. የክልሎች ወሰን በሚመለከት ጥያቄ የተነሳ እንደሆነ ጉዳዩ በሚመለከታቸው ክልሎች ስምምነት ይፈጸማል። የሚመለከታቸው ክልሎች መስማማት ካልቻሉ የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት የሕዝብን አሰፋፈርና ፍላጐት መሠረት በማድረግ ይወስናል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አስቀጽ 1 መሰረት የቀረበ ጉዳይ ከሁለት ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በፌዴሬሽኑ ምክር ቤት የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጥበታል።

**<u>አንቀጽ 49 ርዕሰ ከተማ</u>**

1. የፌዴራሉ መንግሥት ርዕሰ ከተማ አዲስ አበባ ነው።
2. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር ራሱን በራሱ የማስተዳደር ሙሉ ሥልጣን ይኖረዋል። ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።
3. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ተጠሪነቱ ለፌዴራሉ መንግሥት ይሆናል።
4. የአዲስ አበባ ነዋሪዎች በዚህ ሕገ መንግሥት በተደነገገው መሰረት በፌዴራሉ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይወከላሉ።
5. የኦሮሚያ ክልል፤ የአገልግሎት አቅርቦት ወይም የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀምንና የመሳሰሉትን ጉዳዮች በተመለከተ፣ እንዲሁም አዲስ አበባ በኦሮሚያ ክልል መሐል የሚገኝ በመሆኑ የሚነሱ ሁለቱን የሚያስተሳስሩ አስተዳደራዊ ጉዳዮች በተመለከተ ያለው ልዩ ጥቅም ይጠበቅለታል። ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል።

## <u>ምዕራፍ አምስት</u>

## <u>የሥልጣን አወቃቀር እና ክፍፍል</u>

**<u>አንቀጽ 50 ስለ ሥልጣን አካላት አወቃቀር</u>**

1. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በፌዴራል መንግሥትና በክልሎች የተዋቀረ ነው።
2. የፌዴራሉ መንግሥትና ክልሎች የሕግ አውጪነት፣ የሕግ አስፈጻሚነትና የዳኝነት ሥልጣን አላቸው።

3. የፌዴራሉ መንግሥት ከፍተኛ የሥልጣን አካል የፌዴራሉ መንግሥት የሕዝብተወካዮች ምክር ቤት ነው፡፡ ተጠሪነቱም ለሀገሪቱ ሕዝብ ነው፡፡ የክልል ከፍተኛ የሥልጣን አካል የክልሉ ምክር ቤት ነው፤ ተጠሪነቱም ለወከለው ክልል ሕዝብ ነው፡፡
4. ክልሎች፤ በክልልነትና ክልሎች አስፈላጊ ሆነው በሚያገኙአቸው የአስተዳደር እርከኖች ይዋቀራሉ፡፡ ሕዝቡ በዝቅተኛ የአስተዳደር እርከኖች በቀጥታ ይሳተፍ ዘንድ ለዝቅተኛ እርከኖች በቂ ሥልጣን ይሰጣል፡፡
5. የክልል ምክር ቤት በክልሉ ሥልጣን ስር በሆኑ ጉዳዮች የክልሉ የሕግ አውጪ አካል ነው፡፡ ይህንን ሕገ መንግሥት መሰረት በማድረግ የክልሉን ሕገ መንግሥት ያዘጋጃል፣ ያጸድቃል፣ ያሻሽላል፡፡
6. የክልል መስተዳድር የክልሉ ከፍተኛ የሕግ አስፈጻሚ አካል ነው፡፡
7. የክልል የዳኝነት ሥልጣን የፍርድ ቤቶች ብቻ ነው፡፡
8. የፌዴራሉ መንግሥትና የክልሎች ሥልጣን በዚህ ሕገ መንግሥት ተወስኗል፡፡ ለፌዴራሉ መንግሥት የተሰጠው ሥልጣን በክልሎች መከበር አለበት፡፡ ለክልሎች የተሰጠው ሥልጣን በፌዴራሉ መንግሥት መከበር አለበት፡፡
9. የፌዴራል መንግሥት በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 51 ከተሰጡት ሥልጣን እና ተግባሮች እንደአስፈላጊነቱ ለክልሎች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

<u>አንቀጽ 51 የፌዴራል መንግሥት ሥልጣንና ተግባር</u>

1. ሕገ መንግሥቱን ይጠብቃል፤ ይከላከላል፡፡
2. የሀገሪቱን አጠቃላይ የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የልማት ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና ዕቅድ ያወጣል፤ ያስፈጽማል፡፡
3. የጤና፣ የትምህርት፣ የባሕልና ታሪካዊ ቅርስ፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሀገር አቀፍ መመዘኛዎችና መሰረታዊ የፖሊሲ መለኪያዎችን ያወጣል ያስፈጽማል፡፡
4. የሀገሪቱን የፋይናንስ፣ የገንዘብ፣ የውጭ ኢንቨስትመንት ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን ያወጣል፤ ያስፈጽማል፡፡
5. የመሬት፣ የተፈጥሮ ሀብትና የታሪክ ቅርሶች አጠቃቀምና ጥበቃን በተመለከተ ሕግ ያወጣል፡፡
6. የሀገርና የሕዝብ የመከላከያና የደህንነት እንዲሁም የፌዴራል መንግሥት የፖሊስ ኃይል ያደራጃል፤ ይመራል፡፡
7. ብሔራዊ ባንክን የስተዳድራል፤ ገንዘብ ያትማል፤ ይበደራል፤ የውጭ ምንዛሪና ገንዘብ ልውውጥን ይቆጣጠራል፡፡ ክልሎች ከውስጥ ምንጮች ስለሚበደሩበት ሁኔታ ሕግና መመሪያ ያወጣል፡፡

8. የውጭ ግንኙነት ፖሊሲን ይወስናል፤ ፖሊሲውንም ያስፈጽማል፤ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ይዋዋላል፤ ያጸድቃል።
9. የአየር፣ የባቡር፣ የባሕር መጓጓዣ፤ የፖስታና የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች እንደዚሁም ሁለት ወይም ከሁለት በላይ ክልሎችን የሚያገናኙ አውራ መንገዶችን ያስፋፋል፤ ያስተዳድራል፤ ይቆጣጠራል።
10. ለፌዴራሉ መንግሥት በተሰጡት የገቢ ምንጮች ክልል ግብርና ቀረጥ ይጥላል፤ያስተዳድራል፤ የፌዴራል መንግሥት በጀት ያረቃል፤ ያጸድቃል፤ ያስተዳድራል።
11. ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ክልሎችን የሚያስተሳስሩ ወይም ድንበር ተሻጋሪ የሆኑ ወንዞችና ሀይቆችን አጠቃቀም ይወስናል፤ ያስተዳድራል።
12. በክልሎች መካከል የሚደረግን የንግድ ግንኙነትና የውጭ ንግድን ይመራል፤ይቆጣጠራል።
13. በፌዴራል መንግሥት ገንዘብ የተቋቋሙ አንድ ወይም ከአንድ ክልል በላይ የሚሸፍኑ የአገልግሎት ተቋሞችን ያስተዳድራል፤ ያስፋፋል።
14. ከክልል አቅም በላይ የሆነ የጸጥታ መደፍረስ ሲያጋጥም በክልሉ መስተዳድር ጥያቄ መሰረት የሀገሪቱን የመከላከያ ኃይል ያሰማራል።
15. በዚህ ሕገ መንግሥት የተረጋገጡትን የፖለቲካ መብቶች ለማስፈጸም አስፈላጊ የሆኑ የፖለቲካ ድርጅቶችን እንዲሁም ምርጫን በሚመለከት ሕጐች ያወጣል።
16. በሀገሪቱ በአጠኝላይም ሆነ በተወሰኑ የሀገሪቱ ክፍሎች የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ያውጃል፤ አዋጁን ያነሳል።
17. የዜግነት ጥያቄ ይወስናል።
18. የኢምግሬሽንና የስፖርት፤ ወደ ሀገር የመግቢያና፤ የመውጫ ጉዳዮችን፤ ስለስደተኞችና ስለ ፖለቲካ ጥገኝነት ይወስናል፤ ይመራል።
19. የፈጠራና የድርሰት መብቶችን ይፈቅዳል፤ ይጠብቃል።
20. አንድ ወጥ የመለኪያ ደረጃዎችና የጊዜ ቀመር ያወጣል።
21. የጦር መሳሪያ ስለመያዝ የጦር መሣሪያ ሕግ ያወጣል።

## <u>አንቀጽ 52 የክልል ሥልጣንና ተግባር</u>

1. በሕገ መንግሥቱ ለፌዴራሉ መንግሥት በተለይ ወይም ለፌዴራሉ መንግሥትና ለክልሎች በጋራ በግልጽ ያልተሰጠ ሥልጣን የክልል ሥልጣን ይሆናል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የክልሎች ሥልጣንና ተግባር የሚከተሉትን ያጠቃልላል፤

ሀ/ ራስን በራስ ማስተዳደርን ዓላማ ያደረገ ክልላዊ መስተዳደር ያዋቅራል፤ የሕግ የበላይነት የሰፈነበት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ይገነባል፤ ይህን ሕገ መንግሥት ይጠብቃል፤ ይከላከላል፤

ለ/ የክልል ሕገ መንግሥትና ሌሎች ሕጐችን ያወጣል፤ ያስፈጽማል፤

ሐ/ የክልሉን የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የልማት ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና እቅድ ያወጣል፤ ያስፈጽማል፤

መ/ የፌዴራሉ መንግሥት በሚያወጣው ሕግ መሰረት መሬትና የተፈጥሮ ሀብትን ያስተዳድራል፤

ሠ/ ለክልሉ በተወሰነው የገቢ ምንጭ ክልል ግብርና ታክስ ይጥላል፤ ይሰበስባል፤ የክልሉን በጀት ያወጣል፤ ያስፈጽማል፤

ረ/ የክልሉን መስተዳድር ሠራተኞች አስተዳደር የሥራ ሁኔታዎች በተመለከተ ሕግ ያወጣል፤ ያስፈጽማል፤ ሆኖም ለአንድ የሥራ መደብ የሚያስፈልጉ የትምህርት የሥልጠናና የልምድ መመዘኛዎች ከአጠቃላይ የሀገሪቱ መመዘኛዎች ጋር የተቀራረቡ መሆናቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

ሰ/ የክልሉን የፖሊስ ኃይል ያደራጃል፤ ይመራል፤ የክልሉን ሰላምና ጸጥታ ያስብቃል፡፡

## ምዕራፍ ስድስት : ስለፌዴራሉ መንግሥት ምክር ቤቶች

### አንቀጽ 53 የፌዴራል መንግሥት ምክር ቤቶች

የፌዴራሉ መንግሥት ሁለት ምክር ቤቶች ይኖሩታል፤ እነዚህም የሕዝብተወካዮች ምክር ቤት እና የፌዴሬሽን ምክር ቤት ናቸው፡፡

## ክፍል አንድ

## የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት

### አንቀጽ 54 የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት

1. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት፤ ሁሉ አቀፍ፣ ነጻ ፣ ቀጥተኛ፣ ትክክለኛ በሆነና ድምጽ በሚስጥር በሚሰጥበት ሥርዓት በየአምስት ዓመቱ በሕዝብ ይመረጣሉ፡፡
2. የምክር ቤቱ አባላት በአንድ የምርጫ ክልል ውስጥ ከሌሎች ተወዳዳሪዎች መካከል አብላጫ ድምጽ ያገኘ ተወዳዳሪ አሸናፊ በሚሆንበት የምርጫ ሥርዓት ይመረጣሉ፡፡ የተለየ ውክልና ያስፈልጋቸዋል ተብሎ የታመነባቸው አናሳ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች በምርጫ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል ይሆናሉ፡፡ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡
3. የምክር ቤቱ አባላት ቁጥር የሕዝብ ብዛትንና በልዩ ትኩረት ውክልና የሚሰጣቸው አናሳ ብሔረሰቦችና ሕዝቦችን ቁጥር መሰረት በማድረግ 550 የማይበልጥ ሆኖ ከዚህ ውስጥ አናሳ ብሔረሰቦች 20 የማያንስ መቀመጫ ይኖራቸዋል፡፡ ዝርዝሩ በሕግ ይደነግጋል፡፡
4. የምክር ቤቱ አባላት የመላው ሕዝብ ተወካዮች ናቸው፡፡ተገዢነታቸውም፣

ሀ/ ለሕገ መንግሥቱ፤

ለ/ ለሕዝቡ፤ እና

ሐ/ ለሕሊናቸው ብቻ ይሆናሉ፡፡

5. ማንኛውም የምክር ቤቱ አባል በምክር ቤቱ ውስጥ በሚሰጠው ድምጽ ወይም አስተያየት ምክንያት አይከሰስም፡፡ አስተዳደራዊ እርምጃ አይወሰድበትም፡፡
6. ማንኛውም የምክር ቤቱ አባል ከባድ ወንጀል ሲፈጽም እጅ ከፍንጅ ካልተያዘ በስተቀር ያለ ምክር ቤቱ ፈቃድ አይያዝም፤ በወንጀልም አይከሰስም፡፡
7. ማንኛውም የምክር ቤቱ አባል የመረጠው ሕዝብ አመኔታ ባጣበት ጊዜ በሕግ መሰረት ከምክር ቤት አባልነቱ ይወገዳል፡፡

__አንቀጽ 55 የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር__

1. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በዚህ ሕገ መንግሥት መሰረት ለፌዴራሉ መንግሥት በተሰጠው ሥልጣን ክልል ሕጎችን ያወጣል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ዝርዝር ሕግ ያወጣል፤

   ሀ/ የመሬትና የተፈጥሮ ሀብት፤ እንዲሁም ድንበር ተሻጋሪ ወይም ከአንድ ክልል በላይ የሚያስተሳስሩ ወንዞችና ሐይቆች አጠቃቀምን በተመለከተ፤

   ለ/ በክልሎች መካከል የሚኖረውን የንግድ ልውውጥ፤ እንዲሁም የውጭ ንግድ ግንኙነትን በተመለከተ፤

   ሐ/ የአየር፣ የባቡርና የባሕር መጓጓዣ፤ የፖስታና የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶችን እንዲሁም ሁለት ወይም ከሁለት በላይ ክልሎችን የሚያገናኙ

   አውራ መንገዶችን በተመለከተ፤

   መ/ በዚህ ሕገ መንግሥት የተደነገጉትን የፖለቲካ መብቶች አፈጻጸምን እንዲሁም ምርጫን በተመለከተ፤

   ሠ/ የዜግነት መብትን፤ የኢምግሬሽን፤ የስፖርትን፤ ወደ ሀገር የመግቢያና የመውጫ ጉዳዮችን እንዲሁም የስደተኞችና የፖለቲካ ጥገኝነት ጉዳዮችን በተመለከተ፤

   ረ/ አንድ ወጥ የመጠን መለኪያ ደረጃና የጊዜ ቀመርን በተመለከተ፤

   ሰ/ የፈጠራና የሥነ ጥበብ መብቶችን በተመለከተ፤

   ሸ/ የጦር መሣሪያ መያዝን በተመለከተ፡፡
3. የሠራተኛ ጉዳይ ሕግ ያወጣል፡፡
4. የንግድ ሕግ /ኮድ/ ያወጣል፡፡

5. የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ያወጣል። ይህ እንደተጠበቀ ሁኖ ክልሎች የፌዴራሉ መንግሥት የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በግልጽ ባልተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ሕግ የማውጣት ሥልጣን ይኖራቸዋል።

6. አንድ የኢኮኖሚ ማኀበረሰብን ለመፍጠር ሲባል በፌዴራል መንግሥት ሕግ እንዲወጣላቸው የሚያስገድዱ ለመሆናቸው በፌዴሬሽኑ ምክር ቤት የታመነባቸው የፍትሐብሔር ሕጎችን ያወጣል።

7. የፌዴራል መንግሥት፣ የሀገርና የሕዝብ መከላከያ፣ የደህንነትና የፖሊስ ኃይል አደረጃጀት ይወስናል። በሥራ አፈጻጸም ረገድ የሚታዩ መሠረታዊ የዜጐችን ሰብዓዊ መብቶችና የሀገርን ደህንነት የሚነኩ ጉዳዮች ሲከሰቱ ያጣራል፣ አስፈላጊ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ያደርጋል።

8. በአንቀጽ 93 በተመለከተው መሰረት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ያውጃል፣ የሕግ አስፈጻሚው የሚያወጣውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ተመልክቶ ይወስናል።

9. የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያቀርብለት የሕግ ረቂቅ መሰረት የጦርነት አዋጅ ያውጃል።

10. የሀገሪቱን አጠቃላይ የኢኮኖሚ፣ የማኀበራዊ፣ የልማት ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን፣ የፋይናንስና የገንዘብ ፖሊሲን ያጸድቃል፣ ገንዘብን፣ የብሔራዊ ባንክ አስተዳደር፣ የውጭ ምንዛሪንና ልውውጥን በተመለከተ ዝርዝር ሕግ ያወጣል።

11. ለፌዴራል መንግሥት በተከለለው የገቢ ምንጭ ክልል ግብርና ታክስ ይጥላል።የፌዴራል መንግሥት በጀት ያጸድቃል።

12. የሕግ አስፈጻሚው አካል የሚዋዋላቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ያጸድቃል።

13. የፌዴራል መንግሥት ፍርድ ቤት ዳኞችን፣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት አባላትን፣የኮሚሽነሮችን፣ የዋናው ኦዲተርን እንዲሁም የሌሎች ሹመታቸው በምክር ቤቱ መጽደቅ ያለበትን ባለሥለጣኖች ሹመት ያጸድቃል።

14. የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን ያቋቁማል፣ ሥልጣንና ተግባሩን በሕግ ይወስናል።

15. የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋምን ያቋቁማል፣ ተቋሙን የሚመሩ አባላትን ይመርጣል፣ይሰይማል። ሥልጣንና ተግባሩን በሕግ ይወስናል።

16. በማንኛውም ክልል ሰብዓዊ መብቶች ሲጣሱና ክልሉ ድርጊቱን ማቆም ሳይችል ሲቀር፣ በራሱ አነሳሽነትና ያለክልሉ ፈቃድ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ለፌዴሬሽኑ ምክር ቤትና ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የጋራ ስብሰባ ጥያቄ ያቀርባል፣ በተደረሰበት ውሳኔ መሰረት ለክልሉ ምክር ቤት መመሪያ ይሰጣል።

17. ምክር ቤቱ ጠቅላይ ሚኒስትሩን እና ሌሎች የፌዴራሉ መንግሥት ባለሥለጣናትን ለጥያቄ የመጥራትና የሕግ አስፈጻሚውን አካል አሠራር የመመርመር ሥልጣን አለው።

18. ለሕግ አስፈጻሚው አካል በተሰጠ ማንኛውም ሥልጣን ላይ የምክር ቤቱ አባላት በአንድ ሦስተኛ ድምፅ ሲጠይቁ ምክር ቤቱ ይወያያል። ምክር ቤቱ በጉዳዩ ላይ የመመካከርና አስፈላጊ መስሎ የታየውን እርምጃ የመውሰድ ሥልጣን አለው።

19. ምክር ቤቱን የሚመሩ አፈ ጉባኤና ምክትል አፈ ጉባኤ ይመርጣል፤ ለምክር ቤቱ ሥራ የሚያስፈልጉትን ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎች ያዋቅራል፡፡

**<u>አንቀጽ 56 የፖለቲካ ሥልጣን</u>**

በምክር ቤቱ አብላጫ መቀመጫ ያገኘ የፖለቲካ ድርጅት ወይም ጣምራ ድርጅቶች የፌዴራሉን መንግሥት የሕግ አስፈጻሚ አካል ያደራጃል/ያደራጃሉ፤ ይመራል/ይመራሉ፡፡

**<u>አንቀጽ 57 ስለሕግ አጸዳደቅ</u>**

ምክር ቤቱ መክሮ የተስማማበት ሕግ ለሀገሪቱ ፕሬዚዳንት ለፊርማ ይቀርባል፤ ፕሬዚዳንቱ በአሥራ አምስት ቀናት ውስጥ ይፈርማል፡፡ ፕሬዚዳንቱ በአሥራ አምስት ቀናት ውስጥ ካልፈረመ ሕጉ በሥራ ላይ ይውላል፡፡

**<u>አንቀጽ 58 የምክር ቤቱ ስብሰባና የሥራ ዘመን</u>**

1. ከምክር ቤቱ አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይኖራል፡፡
2. የምክር ቤቱ የሥራ ጊዜ ከመስከረም ወር የመጨረሻ ሳምንት ሰኞ እስከ ሰኔ ሰላሳ ነው፤ በመካከሉም ምክር ቤቱ በሚወስነው ጊዜ የአንድ ወር ዕረፍት ይኖረዋል፡፡
3. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚመረጠው ለአምስት ዓመታት ነው፤ የሥራ ዘመኑ ከማብቃቱ ከአንድ ወር በፊት አዲስ ምርጫ ተካሂዶ ይጠናቀቃል፡፡
4. ምክር ቤቱ ዕረፍት ላይ በሚሆንበት ጊዜ የምክር ቤቱ አፈጉባኤ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡ ከምክር ቤቱ አባላት ከግማሽ በላይ ስብሰባ እንዲጠራ ከጠየቁ አፈ-ጉባኤው ስብሰባ የመጥራት ግዴታ አለበት፡፡
5. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ስብሰባዎች በግልጽ ይካሄዳሉ፤ ሆኖም በምክር ቤቱ አባላት ወይም በፌዴራል የሕግ አስፈጻሚ አካል በዝግ ስብሰባ እንዲደረግ ከተየቀና ከምክር ቤቱ አባላት ከግማሽ በላይ ከደገፉት ዝግ ስብሰባ ሊደረግ ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ 59 የምክር ቤቱ ውሳኔዎችና የሥነ ሥርዓት ደንቦች</u>**

1. በዚህ ሕገ መንግሥት በግልጽ በተለይ ካልተደነገገ በስተቀር ማናቸውም ውሳኔዎች የሚተላለፉት በምክር ቤቱ አባላት የአብላጫ ድምጽ ነው፡፡
2. ምክር ቤቱ ስለ አሠራሩና ስለ ሕግ አወጣጡ ሂደት ደንቦችን ያወጣል፡፡

**<u>አንቀጽ 60 ስለምክር ቤቱ መበተን</u>**

1. ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሥልጣን ዘመኑ ከማለቁ በፊት አዲስ ምርጫ ለማካሄድ በምክር ቤቱ ፈቃድ ምክር ቤቱ እንዲበተን ለማድረግ ይችላል፡፡
2. በጣምራ የመንግሥት ሥልጣን የያዙ የፖለቲካ ድርጅቶች ጣምራነታቸው ፈርሶ በምክር ቤቱ የነበራቸውን አብላጫነት ያጡ እንደሆን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ተበትኖ በሕዝብ ተወካዮች ምክር

ቤት ባሉ የፖለቲካ ድርጅቶች ሌላ ጣምራ መንግሥት በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ ለመመስረት እንዲቻል ኘሬዚዳንቱ የፖለቲካ ድርጅቶችን ይጋብዛል፡፡ የፖለቲካ ድርጅቶቹ አዲስ መንግሥት ለመፍር ወይም የነበረውን ጣምራነት ለመቀጠል ካልቻሉ ምክር ቤቱ ተበትኖ አዲስ ምርጫ ይደረጋል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ወይም 2 መሰረት ምክር ቤቱ የተበተነ እንደሆነ ከስድስት ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ አዲስ ምርጫ መደረግ አለበት፡፡
4. ምርጫው በተጠናቀቀ በሰላሳ ቀናት ውስጥ አዲሱ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሥራውን ይጀምራል፡፡
5. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከተበተነ በኍላ ሀገሪቱን የሚወራው ሥልጣን ይዞ የነበረው የፖለቲካ ድርጅት ወይም የፖለቲካ ድርጅቶች ጣምራ የዕለት ተዕለት የመንግሥት ሥራ ከማከናወንና ምርጫ ከማካሔድ በስተቀር አዲስ አዋጆችን፣ ደንቦችንና ድንጋጌዎችን ማውጣት ወይም ነባር ሕጐችን ማሻርና ማሻሻል አይችልም፡፡

<u>**ምዕራፍ ስድስት ክፍል ሁለት : የፌዴሬሽን ምክር ቤት**</u>

<u>**አንቀጽ 61 የፌዴሬሽን ምክር ቤት አባላት**</u>

1. የፌዴሬሽን ምክር ቤት በፌዴራሉ መንግሥት አባል ክልሎች የሚገኙ ብሔሮች፣ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች የሚልኩዋቸው አባላት የሚወከሉበት ምክር ቤት ነው፡፡
2. እያንዳንዱ ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ ቢያንስ አንድ ተወካይ ይኖረዋል፤በተጨማሪም የብሔር ወይም ብሔረሰቡ አንድ ሚሊዮን ሕዝብ አንድ ተጨማሪ ወኪል ይኖረዋል፡፡
3. የፌዴሬሽን ምክር ቤት አባላት በክልል ምክር ቤቶች ይመረጣሉ፤ የክልል ምክር ቤቶች በራሳቸው ወይም በቀጥታ በሕዝብ እንዲመረጡ በማድረግ የፌዴሬሽን ምክር ቤት አባል እንዲወከሉ ያደርጋሉ፡፡

<u>**አንቀጽ 62 የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር**</u>

1. ምክር ቤቱ ሕገ መንግሥቱን የመተርጐም ሥልጣን ይኖረዋል፡፡
2. የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤን ያደራጃል፡፡
3. የብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን እስከ መገንጠን መብትን በተመለከተ በሚነሱ ጥያቄዎች ላይ በሕገ መንግሥቱ መሰረት ይወስናል፡፡
4. በሕገ መንግሥቱ የተደነገገው የሕዝቦች እኩልነትና በሕዝቦች መፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ አንድነት ሥር እንዲሰድና እንዲዳብር ያደርጋል፡፡
5. ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጋር በጣምራ የተሰጡትን ሥልጣኖች ያከናውናል፡፡
6. በክልሎች መካከል ለሚነሱ አለመግባባቶች መፍትሄ ይፈልጋል፡፡
7. የክልሎችና የፌዴራሉ መንግሥት የጋራ ተብለው የተመደቡ ገቢዎች በሁለቱ መካከል የሚከፋፈሉበትን፤ እንዲሁም የፌዴራሉ መንግሥት ለክ ድጐማ የሚሰጥበትን ቀመር ይወስናል፡፡

8. በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሕግ ሊወጣላቸው የሚገቡ የፍትሐብሔር ጉዳዮችን ይለያል፡፡

9. ማንኛውም ክልል ይህን ሕገ መንግሥት በመጣስ ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን አደጋ ላይ የጣለ እንደሆነ የፌዴራሉ መንግሥት ጣልቃ እንዲገባ ያዛል፡፡

10. የምክር ቤቱን የተለያዩ ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎች ያቋቁማል፡፡

11. ምክር ቤቱ የራሱን አፈጉባኤና ምክትል አፈጉባኤ ይመርጣል፤ የራሱን የሥራ አፈጻጸምና የውስጥ አስተዳደር ደንብ ያወጣል፡፡

**<u>አንቀጽ 63 የፌዴሬሽን ምክር ቤት አባላት መብት</u>**

1. ማንኛውም የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት አባል በማናቸውም የምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ በሚሰጠው አስተያየት ወይም ድምጽ ምክንያት አይከሰስም፤ አስተዳደራዊ እርምጃም አይወሰድበትም፡፡

2. ማንኛውም የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት አባል ከባድ ወንጀል ሲፈጽም እጅ ከፍንጅ ካልተያዘ በስተቀር ያለ ምክር ቤቱ ፈቃድ አይያዝም፤ በወንጀልም አይከሰስም፡፡

**<u>አንቀጽ 64 ውሳኔዎችና የሥነ ሥርዓት ደንቦች</u>**

1. የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት ምልዓተ ጉባኤ የሚኖረው ከአባላቱ ሁለት ሦስተኛው የተገኙ እንደሆነ ነው፡፡ ማናቸውም ውሳኔ የሚያልፈው ስብሰባ ላይ ከተገኙት የምክር ቤቱ አባላት ከግማሽ በላይ ድምጽ ሲደገፍ ብቻ ነው፡፡

2. አባላት ድምጽ መስጠት የሚችሉት በአካል ሲገኙ ብቻ ነው፡፡

**<u>አንቀጽ 65 ስለ በጀት</u>**

የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት በጀቱን ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በማቅረብ ያስወስናል፡፡

**<u>አንቀጽ 66 የምክር ቤቱ አፈጉባኤ ሥልጣን</u>**

1. የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት አፈ ጉባኤ የምክር ቤቱን ስብሰባዎች ይመራል፡፡

2. ምክር ቤቱን በመወከል ጠቅላላ የአስተዳደር ሥራዎችን ይመራል፡፡

3. ምክር ቤቱ በአባሎቹ ላይ የወሰነውን የዲስኘሊን እርምጃ ያስፈጽማል፡፡

**<u>አንቀጽ 67 ስብሰባና የሥራ ዘመን</u>**

1. የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ ይሰበሰባል፡፡

2. የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል፡፡

**<u>አንቀጽ 68 በሁለቱም ምክር ቤቶች አባል መሆን የማይቻል ስለመሆኑ</u>**

ማንኛውም ሰው በአንድ ጊዜ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት አባል ሊሆን አይችልም፡፡

## <u>ምዕራፍ ሰባት ፡ ስለ ሪፐብሊኩ ኘሬዚዳንት</u>

**<u>አንቀጽ 69 ስለ ኘሬዚዳንቱ</u>**

ኘሬዚዳንቱ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ርዕሰ ብሔር ነው፡፡

**አንቀጽ 70 የኘሬዚዳንቱ አሰያየም**

1. ለኘሬዚዳንትነት እጩ የማቅረብ ሥልጣን የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ነው፡፡
2. የቀረበው እጩ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና በፌዴሬሽኑ ምክር ቤት የጋራ ስብሰባ በሁለት ሦስተኛ ድምጽ ከተደገፈ ኘሬዚዳንት ይሆናል፡፡
3. የምክር ቤት አባል ኘሬዚዳንት ሆኖ ከተመረጠ የተወከለበትን ምክር ቤት ወንበር ይለቃል፡፡
4. የኘሬዚዳንቱ የሥራ ዘመን ስድስት ዓመት ይሆናል፡፡ አንድ ሰው ከሁለት ጊዜ በላይ ለኘሬዚዳንትነት ሊመረጥ አይችል፡፡
5. የሪፐብሊኩ ኘሬዚዳንት ምርጫ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ከጸደቀ በኍላ ሥራውን ከመጀመሩ በፊት የጋራ ስብሰባው በሚወስነው ጊዜ ስብሰባው ፊት ለሕገ መንግሥቱና ለኢትዮጵያ ሕዝቦች ያለውን ታማኝነት በሚቀጥሉት ቃላት ይገልጻል፡፡

«እኔ ....... በዛሬው ዕለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኘሬዚዳንት በመሆን ሥራዬን ስጀምር የተጣለብኝን ከፍተኛ ኃላፊነት በታማኝነት ለመፈጸም ቃል እገባለሁ፡፡»

**አንቀጽ 71 የኘሬዚዳንቱ ሥልጣንና ተግባር**

1. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና የፌዴሬሽኑን ምክር ቤት ዓመታዊ የጋራ ስብሰበባ ይከፍታል፡፡
2. በዚህ ሕገ መንግሥት መሰረት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያጸደቃቸው ሕጐችና ዓለም አቀፍ ስምምነቶች በነጋሪት ጋዜጣ ያውጃል፡፡
3. ሀገሪቷን በውጭ ሀገሮች የሚወክሉትን አምባሳደሮችና ሌሎች መልክተኞች በጠ ቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት ይሾማል፡፡
4. የውጭ ሀገር አምሳደሮችንና የልዩ መልዕክተኞችን የሹመት ደብዳቤ ይቀበላል፡፡
5. በሕግ መሰረት ኒሻኖችና ሽልማቶችን ይሰጣል፡፡
6. በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት በሕግ በተወሰነው መሰረት ከፍተኛ የውትድርና ማዕረጐችን ይሰጣል፡፡
7. በሕግ መሰረት ይቅርታ ያደርጋል፡፡

## ምዕራፍ ስምንት ፡ የሕግ አስፈጻሚ አካል

**አንቀጽ 72 ስለ አስፈጻሚነት ሥልጣን**

1. የኢትዮጵያ ፌዴራል መንግሥት ከፍተኛ የአስፈጻሚነት ሥልጣን የተሰጠው ለጠቅላይ ሚኒስትሩና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ነው፡፡
2. ጠቅላይ ሚኒስትሩና የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተጠሪዎች ናቸው፡፡ የሚኒስትሮች ምክር ቤት አባላት በመንግሥት ተግባራቸው በጋራ ለሚሰጡት ውሳኔ የጋራ ኃላፊነት አለባቸው፡፡
3. በዚህ ሕገ መንግሥት መሰረት በሌላ አኳኍን ካልተወሰነ በስተቀር የጠቅላይሚኒስትሩ የሥራ ዘመን የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሥራ ዘመን ነው፡፡

**<u>አንቀጽ 73 የጠቅላይ ሚኒስትሩ አሰያየም</u>**

1. ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት መካከል ይመረጣል፡፡
2. በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አብላጫ መቀመጫ ያገኘው የፖለቲካ ድርጅት ወይም ያገኙት የፖለቲካ ድርጅቶች የመንግሥት ሥልጣን ይረከባል/ይረከባሉ፡፡

**<u>አንቀጽ 74 የጠቅላይ ሚኒስትሩ ሥልጣንና ተግባር</u>**

1. ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሀገሪቱ ርዕሰ መስተዳድር፣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሰብሳቢና የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ ነው፡፡
2. ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚኒስትሮች ምክር ቤት አባሎችን ከሁለቱ ምክር ቤቶች አባላት ወይም ለሥራው ብቃት ካላቸው ሌሎች ግለሰቦች መካከል ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በእጩነት አቅርቦ ሹመታቸውን ያጸድቃል፡፡
3. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያወጣቸው ሕጐች፣ ፖሊሲዎች፣ መመሪያዎችና ውሳኔዎች ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፡፡
4. የሚኒስትሮች ምክር ቤትን ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይወክላል፡፡
5. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ያወጣቸውን ፖሊሲዎች፣ ደንቦች መመሪያዎችና ውሳኔዎች ተፈጻሚነት ይከተተላል፡፡
6. የሀገሪቱን የውጭ ፖሊሲ በበላይነት ያስፈጽማል፡፡
7. ኮሚሽነሮችን፣ የማዕከላዊ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ኘሬዚዳንትና ምክትል ኘሬዚዳንትን እና ዋና ኦዲተርን መርጦ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሹመታቸውን ያጸድቃል፡፡
8. የመስተዳድሩን ሥራ አፈጻጸምና ብኘት ይቆጣጠራል፣ አስፈላጊ የሆኑ የእርምት እርምጃዎችን ይወስዳል፡፡
9. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 እና 7 ከተዘረዘሩት ውጭ የሆኑ ከፍተኛ የመንግሥት የሲቪል ሹመቶችን ይሰጣል፡፡
10. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚያወጣው ሕግ ወይም በሚሰጠው ውሳኔ መሠረት ኒሻኖችንና ሽልማቶችን ለኘሬዚዳንቱ አቅርቦ ያሰጣል፡፡
11. ስለ ሀገሪቱ ሁኔታ፣ በመንግሥት ስለተከናወኑ ተግባራትና ስለወደፊት እቅዶች ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በየወቅቱ ሪፖረት ያቀርባል፡፡
12. በዚህ ሕገ መንግሥትና በሌሎች ሕጐች የተሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል፡፡
13. ሕገ መንግሥቱን ያከብራል፤ የስከበራል፡፡

**<u>አንቀጽ 75 ስለ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር</u>**

1. ምክትል ጠቅላይሚኒስትሩ፣

    ሀ/ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ተለይተው የሚሰጡትን ተግባሮች ያከናውናል፤

    ለ/ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በማይኖርበት ጊዜ ተክቶት ይሰራል፡፡

2. ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሆናል፡፡

**<u>አንቀጽ 76 የሚኒስትሮች ምክር ቤት</u>**

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት፤ ጠቅላይ ሚኒስትር፣ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስተር፣ ሚኒስትሮችና በሕግ በሚወሰን መሰረት ሌሎች አባሎች የሚገኙበት ምክር ቤት ነው፡፡
2. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒሰትሩ ነው፡፡
3. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለሚወስነው ውሳኔ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተጠሪ ነው፡፡

**<u>አንቀጽ 77 የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር</u>**

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የወጡ ሕጐችና የተሰጡ ውሳኔዎች በሥራ መተርጐማቸውን ያረጋግጣል፣ መመሪያዎችን ይሰጣል፡፡
2. የሚኒስትሮችንና በቀጥታ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ተጠሪ የሆኑ ሌሎች የመንግሥት አካላትን አደረጃጀት ይወስናል፣ ሥራቸውን ያስተባብራል፣ ይመራል፡፡
3. የፌዴራሉን መንግሥት ዓመታዊ በጀት ያዘጋጃል፣ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲጸድቅም ተግባራዊነቱን ያረጋግጣል፡፡
4. የገንዘብና የፋይናንስ ፖሊሲን ተግባራዊነት ያረጋግጣል፣ ብሔራዊ ባንክን ያስተዳድራል፣ ገንዘብ ያትማል፣ ከሀገር ውስጥና ከውጭ ይበደራል፣ የውጭ ምንዛሪና የገንዘብ ልውውጥን ይቆጣጠራል፡፡
5. የፈጠራና የኪነ ጥበብ መብቶችን ያስጠብቃል፡፡
6. የኢኮኖሚያዊ፣ የማኅበራዊና የልማት ፖሊሲዎች እና ስትራቴጂዎችን ይነድፋል፣ ያስፈጽማል፡፡
7. አንድ ወጥ የመለኪያ ደረጃዎችና የጊዜ ቀመር ያወጣል፡፡
8. የሀገሪቱን የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ያወጣል፣ የስፈጽማል፡፡
9. ሕግና ሥርዓት መከበሩን ያረጋግጣል፡፡
10. የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ያውጃል፣ በዚህ ሕገ መንግሥት በተደነገገው የጊዜ ወሰን ውስጥ፣ የታወጀውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርቦ ያስጸድቻል፡፡
11. የጦርነት ጉዳዮችን ጨምሮ በማናቸውም ጉዳዮች ላይ የሕግ ረቂቅ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያቀርባል፡፡
12. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል፡፡
13. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚሰጠው ሥልጣን መሠረት ደንቦችን ያወጣል፡፡

## <u>ምዕራፍ ዘጠኝ : ስለ ፍርድ ቤቶች አወቃቀርና ሥልጣን</u>

**<u>አንቀጽ 78 ስለ ነጻ የዳኝነት አካል</u>**

1. ነጻ የዳኝነት አካል በዚህ ሕገ መንግሥት ተቋቁሟል፡፡
2. የፌዴራሉ መንግሥት ከፍተኛ የዳኝነት አካል የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይሆናል፡፡ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ሆነ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሀገሪቱ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲደራጅ በሁለት ሦስተኛ ድምጽ ሊወስን

ይችላል። ጉዳዩ በዚህ አኳኋን ካልተወሰነ የፌዴራል ከፍተኛና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች ሥልጣን ለክልል ፍርድ ቤቶች ተሰጥቷል።

3. ክልሎች፣ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች፣ የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤቶችና የክልል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች ይኖራቸዋል። ዝርዝሩ በሕግ ይዋሰናል።
4. የዳኝነት ሥልጣንን ከመደበኛ ፍርድ ቤቶች ወይም በሕግ የመዳኘት ሥልጣን ከተሰጠው ተቋም ውጭ የሚያደርግ፣ በሕግ የተደነገገን የዳኝነት ሥርዓት የማይከተል ልዩ ፍርድ ቤት ወይም ጊዜያዊ ፍርድ ቤት አይቋቋምም።መሰረት የሃይማኖትና የባሕል ፍርድ ቤቶችን ሊያቋቁሙ ወይም እውቅና ሊሰጡ ይችላሉ። ይህ ሕግ መንግሥት ከመጽደቁ በፊት በመንግሥት እውቅና አግኝተው ሲሰራባቸው የነበሩ ሃይማኖቶችና የባሕል ፍርድ ቤቶች በዚህ ሕገ መንግሥት መሰረት እውቅና አግኝተው ይደራጃሉ።

__አንቀጽ 79 የዳኝነት ሥልጣን__

1. በፌዴራልም ሆነ በክልል የዳኝነት ሥልጣን የፍርድ ቤቶች ብቻ ነው።
2. በየትኛውም ደረጃ የሚገኝ የዳኝነት አካል ከማንኛውም የመንግሥት አካል፣ከማንኛውም ባለሥልጣን ሆነ ከማንኛውም ሌላ ተጽዕኖ ነጻ ነው።
3. ዳኞች የዳኝነት ተግባራቸውን በሙሉ ነጻነት ያከናውናሉ። ከሕግ በስተቀር በሌላ ሁኔታ አይመሩም።
4. ማንኛውም ዳኛ ከዚህ በታች በተመለከቱት ሁኔታዎች ካልሆነ በስተቀር በሕግ ከተወሰነው የጡረታ ዕድሜ ከመድረሱ በፊት ከፈቃዱ ውጭ ከዳኝነት ሥራው አይነሳም፤
   ሀ/ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ በዳኞች የዲሲኘሊን ሕግ መሠረት ጥፋት ፈጽሟል ወይም ጉልህ የሆነ የሥራ ችሎታና ቅልጥፍና አንሶታል ብሎ ብሎ ሲወስን፣ ወይም
   ለ/ በህመም ምክንያት ተግባሩን በተገቢው ሁኔታ ማከናወን አይችልም ብሎ ሲወስን፣ እና
   ሐ/ የጉባኤው ውሳኔ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ወይም በክልል ምክር ቤቶች ከግማሽ በላይ ድምጽ ሲጸድቅ።
5. የማንኛውም ዳኛ የጡረታ መውጫ ጊዜ አይራዘምም።
6. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፌዴራሉን መንግሥት የዳኝነት አካል የሚያስተዳድርበትን በጀት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርቦ ያስወስናል፣ ሲፈቀድም በጀቱን ያስተዳድራል።
7. የክልል የዳኝነት አካሎች በጀት በየክልሉ ምክር ቤቶች ይመደባል። የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የፌዴራሉን የከፍተኛና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን ደርበው ለሚሠሩት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶችና የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች የበጀት ማካካሻ ይሰጣል።

__አንቀጽ 80 የፍርድ ቤቶች ጣምራነትና ሥልጣን__

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፌዴራል ጉዳዮች ላይ የበላይና የመጨረሻ የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል።

2. የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በክልሉ ጉዳይ ላይ የበላይና የመጨረሻ የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪ የፌዴራል የከፍተኛ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተጠቀሰው ቢኖርም፣
   ሀ/ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ያለበትን ማናቸውንም የመጨረሻ ውሳኔ ለማረም በሰበር ችሎት የማየት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡
   ለ/ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበትንበክልል ጉዳዮች የተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ ለማረም በሰበር ችሎት የማየትሥልጣን ይኖረዋል፡፡ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡
4. የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በክልሉ ከሚኖረው የዳኝነት ሥልጣን በተጨማሪየፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡
5. የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣኑ መሰረት በሚሰጠው ውሳኔ ላይ የሚቀርበው ይግባኝ በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይታያል፡፡
6. የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፌዴራል የዳኝነት ሥልጣኑ በሚሰጠው ውሳኔ ላይየሚቀርበው ይግባኝ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይታያል፡፡

<u>አንቀጽ 81 ስለዳኞች አሿሿም</u>

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ኘሬዚዳንትና ምክትል ኘሬዚዳንት በፌዴራልመንግሥት ጠቅላይ ሚኒስትር አቅራቢነት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይሾማሉ፡፡
2. ሌሎች የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞችን በተመለከተ በፌዴራል የዳኞችአስተዳደር ጉባኤ የቀረቡለትን እጩዎች ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርቦ ያሾማል፡፡
3. የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ኘሬዚዳንትና ምክትል ኘሬዚዳንት በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት ይሾማሉ፡፡
4. የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤትና የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኞች በክልሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት ይሾማሉ፡፡ የክልሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የዳኞችን ሹመት ለምክር ቤቱ ከማቅረቡ በፊት የፌዴራሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ በእጩዎቹ ላይ ያለውን አስተያየት መጠየቅና አስተያየቱን ከራሱ አስተያየት ጋር በማያያዝ ለክልሉ ምክር ቤት የማቅረብኃላፊነት አለበት፡፡ የፌዴራሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ አስተያየቱን በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ካላቀረበ የክልሉ ምክር ቤት ሹመቱን ያጸድቃል፡፡
5. የክልል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዳኞች በክልሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት ይሾማሉ፡፡
6. በየትኛውም ደረጃ የሚገኙ ዳኞች የዲሲፕሊንና የዝውውር ጉዳይ በሚመለከተው የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ይወሰናል፡፡

**አንቀጽ 82 የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ አወቃቀር**

1. የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በዚህ ሕገ መንግሥት ተቋቁሟል፡፡
2. የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ አሥራ አንድ አባላት ይኖሩታል፡፡አባላቱም የሚከተሉት ናቸው፣
   ሀ/ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ኘሬዚዳንት፣ ሰብሳቢ፤
   ለ/ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ኘሬዚዳንት፣ ምክትል ሰብሳቢ፤
   ሐ/ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅራቢነት በሪፐብሊኩ ኘሬዚዳንት የሚሾሙ በሙያ ብቃታቸውና በሥነ ምግባራቸው የተመሰከረላቸው ስድስት የሕግ ባለሙያዎች፤
   መ/ የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት ከአባላቱ መካከል የሚወክላቸው ሦስት ሰዎች፡፡
3. የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ የሥራ ቅልጥፍናን ለማረጋገጥ የሚያስችለው መዋቅር ሊዘረጋ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 83 ሕገ መንግሥቱን ስለመተርጎም**

1. የሕገ መንግሥታዊ ክርክር ጉዳይ ሲነሳ በፌዴሬሽኑ ምክር ቤት ውሳኔ ያገኛል፡፡
2. የፌዴሬሽን ምክር ቤት፣ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በሚያቀርብለት ሕገ መንግሥታዊ ጉዳይ ላይ በሠላሣ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

**አንቀጽ 84 የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ሥልጣንና ተግባር**

1. የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ሕገ መንግሥታዊ ጉዳዮችን የማጣራት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡ በሚያደርገው ማጣራት መሰረት ሕገ መንግሥቱ መተርጎም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ለፌዴሬሽን ምክር ቤት በጉዳዩ ላይ የውሳኔ ሐሳብ ያቀርባል፡፡
2. በፌዴራሉ መንግሥትም ሆነ በክልል ሕግ አውጪ አካላት የሚወጡ ሕጐች ከዚህ ሕገ መንግሥት ጋር ይቃረናሉ የሚል ጥያቄ ሲነሳና ጉዳዩምበሚመለከተው ፍርድ ቤት ወይም በባለ ጉዳዩ ሲቀርብለት መርምሮ ለመጨረሻ ውሳኔ ለፌዴሬሽኑ ምክር ቤት ያቀርባል፡፡
3. በፍርድ ቤቶች የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ሲነሳ፣
   ሀ/ ሕገ መንግሥቱን መተርጐም አስፈላጊ ሆኖ ሳያገኘው ሲቀር ጉዳዩን ለሚመለከተው ፍርድ ቤት ይመልሳል፤ በአጣሪ ጉባኤው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ባለጉዳይ ቅሬታውን ለፌዴሬሽኑ ምክር ቤት በይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡
   ለ/ የትርጉም ጥያቄ መኖሩን ያመነበት እንደሆነ በጉዳዩ ላይ የሚሰጠውን ሕገ መንግሥታዊ ትርጉም ለፌዴሬሽኑ ምክር ቤት ለመጨረሻ ውሳኔ ያቀርባል፡፡ የሚመራበትን ሥነ ሥርዓት አርቅቆ ለፌዴሬሽኑ ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

## ምዕራፍ አሥር : የብሔራዊ ፖሊሲ መርሆዎችና ዓላማዎች

**አንቀጽ 85 ዓላማዎች**

1. ማንኛውም የመንግሥት አካል ሕገ መንግሥቱን፣ ሌሎች ሕጐችንና ፖሊሲዎችን ሥራ ላይ ሲያውል በዚህ ምዕራፍ በተመለከቱት መርሆዎችና ዓላማዎች ላይ መመስረት አለበት፡፡
2. በዚህ ምዕራፍ ውስጥ «መንግሥት» ማለት እንደየሁኔታው የፌዴራል መንግሥት ወይም የክልል መስተዳድሮች ማለት ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 86 የውጭ ግንኙነት መርሆዎች**

1. የኢትዮጵያ ሕዝቦች ጥቅም የሚያስጠብቅና የሀገሪቱን ሉዓላዊነት የሚያስከብር የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ማራመድ፡፡
2. የመንግሥታትን ሉዓላዊነትና እኩልነት ማክበር፣ በሌሎች ሀገሮች ጉዳዮች ውስጥ ጣልቃ አለመግባት፡፡
3. የሀገሪቱ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ በጋራ ጥቅምና በእኩልነት ላይ የተመሰረተ መሆኑን እንዲሁም በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚደረጉ ስምምነቶችየኢትዮጵያን ጥቅም የሚያስከብሩ መሆናቸውን ማረጋገጥ፡፡
4. የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት የሚያስከብሩና የሕዝቦቿን ጥቅም የማይጻረሩ ዓለም አቀፍ ሕጐችና ስምምነቶችን ማክበር፡፡
5. ከጐረቤት ሀገሮችና ከሌሎችም የአፍሪካ ሀገሮች ጋር በየጊዜው እያደገ የሚሄድ ኢኮኖሚያዊ ኅብረትና የሕዝቦች ወንድማማችነትን ማጐልበት፡፡
6. በሀገሮች መካከል የሚነሱ ግጭቶች ሰላማዊ በሆነ መንገድ እንዲፈቱ ጥረት ማድረግ፡፡

**አንቀጽ 87 የመከላከያ መርሆዎች**

1. የሀገሪቱ የመከላከያ ሠራዊት የብሔሮች፣ የብሔረሰቦች እና የሕዝቦችን ሚዛናዊ ተዋጽኦ ያካተተ ይሆናል፡፡
2. የመከላከያ ሚኒስትር ሆኖ የሚሾመው ሲቪል ይሆናል፡፡
3. የመከላከያ ሠራዊት የሀገሪቱን ሉዓላዊነት ከመጠበቅ በተጨማሪ በዚህ ሕገ መንግሥት መሰረት በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የሚሰጡትን ተግባሮች ያከናውናል፡፡
4. የመከላከያ ሠራዊቱ በማናቸውም ጊዜ ለሕገ መንግሥቱ ተገዥ ይሆናል፡፡
5. የመከላከያ ሠራዊቱ ተግባሩን ከፖለቲካ ድርጅቶች ወገናዊነት ነጻ በሆነ አኳኋን ያከናውናል፡፡

**አንቀጽ 88 ፖለቲካ ነክ ዓላማዎች**

1. መንግሥት በዴሞክራሲያዊ መርሆዎች ላይ በመመሥረት ሕዝቡ በሁሉም ደረጃዎች ራሱን በራሱ የሚያስተዳድርበትን ሁኔታ ማመቻቸት አለበት፡
2. መንግሥት የብሔሮችን፣ የብሔረሰቦችን፣ የሕዝቦችን ማንነት የማክበርና በዚሁ ላይ በመመርኮዝ በመካከላቸው እኩልነት፣ አንድነትና ወንድማማችነትን የማጠናከር ግዴታ አለበት፡፡

**አንቀጽ 89 ኢኮኖሚ ነክ ዓላማዎች**

1. መንግሥት ሁሉም ኢትዮጵያውያን የሀገሪቱ የተጠራቀመ እውቀትና ሀብት ተጠ ቃሚዎች የሚሆኑበትን መንገድ የመቀየስ ኃላፊነት አለበት፡፡
2. መንግሥት የኢትዮጵያውያንን የኢኮኖሚ ሁኔታዎች ለማሻሻል እኩል ዕድል እንዲኖራቸው ለማድረግና ሀብት ፍትሐዊ በሆነ መንገድ የሚከፋፈሉበትን ሁኔታ የማመቻቸት ግዴታ አለበት፡፡
3. የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋ እንዳይደርስ መከላከልና አደጋው ሲደርስም ለተጐጂው እርዳታ በወቅቱ እንዲደርስ ማድረግ፡፡
4. በእድገት ወደኍላ ለቀሩ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች መንግሥት ልዩ ድጋፍ ያደርጋል፡፡
5. መንግሥት መሬትንና የተፈጥሮ ሀብትን በሕዝብ ሥም በይዞታው ሥር በማድረግ ለሕዝቡ የጋራ ጥቅምና እድገት እንዲውሉ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡
6. የሀገር ልማት ፖሊሲዎችና ኘሮግራሞች በሚዘጋጁበት ወቅት መንግሥት ሕዝቡን በየደረጃው ማሳተፍ አለበት፡፡ የሕዝብንም የልማት እንቅስቃሴዎች መደገፍ አለበት፡፡
7. መንግሥት በሀገር ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ልማት እንቅስቃሴ ውስጥ ሴቶች ከወንዶች ጋር በእኩልነት የሚሳተፉበትን ሁኔታ የማመቻቸት ኃላፊነት አለበት፡፡
8. መንግሥት የሠራተኛውን ሕዝብ ጤንነት፣ ደህንነትና የኑሮ ደረጃ ለመጠበቅ መጣር አለበት፡፡

**አንቀጽ 90 ማኀበራዊ ነክ ዓላማዎች**

1. የሀገሪቱ አቅም በፈቀደ መጠን ሁሉም ኢትዮጵያዊ የትምህርት፣ የጤና አገልግሎት፣ የንፁህ ውሃ፣ የመኖሪያ፣ የምግብና የማኅበራዊ ዋስትና እንዲኖረው ይደረጋል፡፡
2. ትምህርት በማናቸውም ረገድ ከሃይማኖት፣ ከፖለቲካ አመለካከቶች እና ከባህላዊ ተፅእኖዎች ነጻ በሆነ መንገድ መካሔድ አለበት፡፡

**አንቀጽ 91 ባሕል ነክ ዓላማዎች**

1. መንግሥት መሰረታዊ መብቶችንና ሰብዓዊ ክብርን፣ ዴሞክራሲንና ሕገ መንግሥቱን የማይቃረኑ ባሕሎችና ልማዶች በእኩልነት እንዲጐለብቱናእንዲያድጉ የመርዳት ኃላፊነት አለበት፡፡
2. የሀገር የተፈጥሮ ሀብቶችንና የታሪክ ቅርሶችን መጠበቅ የመንግሥትና የሁሉም ኢትዮጵያዊ ግዴታ ነው፡፡
3. መንግሥት አቅም በፈቀደ መጠን ኪነጥበብን፣ ሳይንስንና ቴኖሎጂን የማስፋፋት ግዴታ አለበት፡፡

**አንቀጽ 92 የአካባቢ ደህንነት ጥበቃ ዓላማዎች**

1. መንግሥት ሁሉም ኢትዮጵያዊ ንዑሕና ጤናማ አካባቢ እንዲኖረው የመጣር ኃላፊነት አለበት፡፡
2. ማንኛውም የኢኮኖሚ ልማት እርምጃ የአካባቢውን ደህንነት የሚያናጋ መሆን አለበት፡፡
3. የሕዝብን የአካባቢ ደህንነት የሚመለከት ፖሊሲና ኘሮግራም በሚነደፍበትና ሥራ ላይ በሚውልበት ጊዜ የሚመለከተው ሕዝብ ሁሉ ሐሳቡን እንዲገልጽ መደረግ አለበት፡፡
4. መንግሥትና ዜጐች አካባቢያቸውን የመንከባከብ ግዴታ አለባቸው፡፡

## ምዕራፍ አሥራ አንድ ፡ ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## አንቀጽ 93 ስለ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ

1.ሀ/ የውጭ ወረራ ሲያጋጥም ወይም ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን አደጋ ላይ የሚጥል ሁኔታ ሲከሰትና በተለመደው የሕግ ማስከበር ሥርዓት ለመቋቋም የማይቻል ሲሆን፣ ማናቸውም የተፈጥሮ አደጋ ሲያጋጥም ወይም የሕዝብን ጤንነት አደጋ ላይ የሚጥል በሽታ ሲከሰት፣ የፌዴራሉ መንግሥት የሚኒስትሮች ምክር ቤት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የመደንገግ ሥልጣን አለው።

ለ/ የተፈጥሮ አደጋ ሲያጋጥም ወይም የሕዝብን ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል በሽታ ሲከሰት የክልል መስተዳድሮች በክልላቸው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ሊያውጁ ይችላሉ።ዝርዝሩ ክልሎች ይህን ሕገ መንግሥት መሰረት በማድረግ በሚያወጧቸው ሕገመንግሥቶች ይወሰናል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 /ሀ/ መሰረት የሚታወጅ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ፣

ሀ/ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሥራ ላይ ባለ ጊዜ የታወጀ ከሆነ በታወጀ በአርባ ስምንት ሰዓታት ውስጥ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መቅረብ አለበት አዋጁ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሁለት ሦስተኛው ድምጽ ተቀባይነት ካላገኘ ወዲያውኑ ይሻራል።

ለ/ ከላይ በንዑስ አንቀጽ /ሀ/ ሥር የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሥራ ላይ ባልሆነበት ወቅት የሚታወጅ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መቅረብ ያለበት አዋጁ በታወጀ በአሥራ አምሥት ቀናት ውስጥ ነው።

3. በሚኒስትሮች ምክር ቤት የተደነገገው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በምክር ቤቱ ተቀባይነት ካገኘ በኋላ ሊቆይ የሚችለው እስከ ስድስት ወራት ነው። የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሁለት ሦስተኛ ድምጽ አንድን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በየአራት ወሩ በተደጋጋሚ እንዲታደስ ሊያደርግ ይችላል።

4. ሀ/ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በሚታወጅበት ጊዜ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣቸው ደንቦች መሰረት የሀገርን ሰላምና ሕልውና፣ የሕዝብን ደህንነት፣ሕግና ሥርዓትን የማስከበር ሥልጣን ይኖረዋል።

ለ/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሥልጣን በሕገ መንግሥቱ የተቀመጡትን መሰረታዊ የፖለቲካና የዴሞክራሲ መብቶችን፣ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን

ለማወጅ ምክንያት የሆነውን ጉዳይ ለማስወገድ ተፈላጊ ሆኖ በተገኘውደረጃ፣ እስከ ማገድ ሊደርስ የሚችል ነው።

ሐ/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ሥራ የሚያወጣቸው ድንጋጌዎችና የሚወስዳቸው እርምጃዎች በማናቸውም ረገድ በዚህ ሕገመንግሥት አንቀጽ 1፣፣ 88፣ 25፣ እና 39 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተቀመጡትን መብቶች የሚገድቡ ሊሆኑ አይችሉም።

5. በሀገሪቱ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በሚታወጅበት ወቅት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከአባላቱና ከሕግ ባለሙያዎች መርጦ የሚመድባቸው ሰባት አባላት ያሉት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አፈጻጸም መርማሪ ቦርድ ያቋቁማል። ቦርዱ አዋጁ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚጸድቅበት ጊዜ ይቋቋማል፣

6. የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አፈጻጸም መርማሪ ቦርድ የሚከተሉት ሥልጣንና ኃላፊነቶች አሉት፡፡

ሀ/ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ምክንያት የታሰሩትን ግለሰቦች ስም በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ይፋ ማድረግና የታሰሩበትን ምክንያት መግለጽ፣

ለ/ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ወቅት የሚወሰዱት እርምጃዎች በማናቸውም ረገድ ኢሰብዓዊ አለመሆናቸውን መቆጣጠርና መከታተል፣

ሐ/ ማናቸውም የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እርምጃ ኢሰብዓዊ መሆኑን ሲያምንበት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ወይም የሚኒስሮች ምክር ቤት እርምጃውን እንዲያስተካክል ሐሳብ መስጠት፣

መ/ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እርምጃዎች ኢሰብዓዊ ድርጊት የሚፈጽሙትን ሁሉ ለፍርድ እንዲቀርቡ ማድረግ፣

ሠ/ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እንዲቀጥል ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥያቄ ሲቀርብ ያለውን አስተያየት ለምክር ቤቱ ማቅረብ፡፡

## አንቀጽ 94 የፋይናንስ ወጪን በሚመለከት

1. የፌዴራሉ መንግሥትና ክልሎች በሕግ የተሰጧቸውን ኃላፊነቶችና ተግባሮች ለማከናወን የሚያስፈልጋቸውን ወጪ በየበኩላቸው ይሸፍናሉ፤ ሆኖም ማንኛውም ክልል በውክልና ለሚፈጽመው ተግባር የሚያስፈልገው ወጪ ሌላ ስምምነት ከሌለ በቀር ውክልናውን በሰጠው ወገን ይሸፈናል፡፡
2. የፌዴራሉ መንግሥት ለክልሎች የተመጣጠነ እድገት እንቅፋት ካልሆነ በስተቀር ለአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ፣ ለመልሶ መቋቋምና ለልማት ማስፋፊያ ለክልሎች ብድርም ሆነ እርዳታ ሊሰጥ ይችላል፡፡ የፌዴራሉ መንግሥት ክልሎች ለሚያስፈልጋቸው ወጪ የሚያደርገውን ድጐማ በሚመለከት ኦዲትና ቁጥጥር የማድረግ ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

## አንቀጽ 95 የፋይናንስ ገቢን በሚመለከት

የፌዴራሉ መንግሥትና ክልሎች የሚዋቀረውን የፌዴራል አደረጃጀት የተከተለ የገቢ ክፍፍል ያደርጋሉ፡፡

## አንቀጽ 96 የፌዴራል መንግሥት የታክስና የግብር ሥልጣን

1. የፌዴራል መንግሥት በወጪና ገቢ ዕቃዎች ላይ የጉምሩክ ቀረጥ፣ የታክስና ሌሎች ክፍያዎች ይጥላል፣ ይሰበስባል፡፡
2. በፌዴራል መንግሥትና በዓለም አቀፍ ድርጅቶች ተቀጣሪዎች ላይ የሥራ ግብር ይጥላል፣ ይሰበስባል፡፡
3. በፌዴራል መንግሥት ባለቤትነት ሥር በሆኑ የልማት ድርጅቶች ላይ የንግድ ትርፍ ግብር፣ የሥራ ግብር፣ የሽያጭና የኤክሳይስ ታክስ ይጥላል፣ ይሰበስባል፡፡
4. በብሔራዊ የሎተሪ እና ሌሎች የዕድል ሙከራ ገቢዎች ላይ ታክስ ይጥላል፣ይሰበስባል፡፡

5. በአየር፣ በባቡርና በባሕር ትራንስፖርት ገቢዎች ላይ ታክስ ይጥላል፣ ይሰበስባል።

6. በፌዴራል መንግሥት ባለቤትነት ሥር በሚገኙ ቤቶችና ሌሎች ንብረቶች ገቢ ላይ ግብር ይጥላል፣ ይሰበስባል፤ ኪራይ ይወስናል።

7. የፌዴራል መንግሥት አካላት ከሚሰጧቸው ፈቃዶችና አገልግሎቶች የሚመነጩ ክፍያዎችን ይወስናል፣ ይሰበስባል።

8. የሞኖፖል ታክስ ይጥላል፣ ይሰብሰባል።

9. የፌዴራል የቴምብር ሽያጭ ቀረጥ ይጥላል፣ ይሰበስባል።

**<u>አንቀጽ 97 የክልል መስተደድሮች የታክስና የግብር ሥልጣን</u>**

1. ክልሎች፣ በክልል መስተዳድርና በድርጅት ተቀጣሪዎች ላይ የሥራ ግብር ይጥላሉ፣ ይሰበስባሉ።
2. የመሬት መጠቀሚያ ክፍያ ይወስናሉ፣ ይሰበስባሉ።
3. በግል የሚያደርሱና በኅብረት ሥራ ማኅበራት በተደራጁ ገበሬዎች ላይ የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር ይጥላሉ፣ ይሰበስባሉ።
4. በክልሉ በሚገኙ ግለሰብ ነጋዴዎች ላይ የንግድ ትርፍ ግብርና የሽያጭ ታክስ ይጥላሉ፣ ይሰበስባሉ።
5. በክልሉ ውስጥ በውኃ ላይ ከሚደረግ ትራንስፖርት በሚገኝ ገቢ ላይ ግብር ይጥላሉ፣ ይሰበስባሉ።
6. በክልል መስተዳድር በግል ባለቤትነት ሥር ካሉ ቤቶችና ሌሎች ንብረቶች በሚገኝ ገቢ ላይ ግብር ይጥላሉ፣ ይሰበስባሉ፣ በባለቤትነታቸው ሥር ባሉ ቤቶችና ሌሎች ንብረቶች ላይ ኪራይ ያስከፍላሉ።
7. በክልል መስተዳድር ባለቤትነት ሥር በሚገኙ የልማት ድርጅቶች ላይ የንግድ ትርፍ፣ የሥራ ግብር፣ የሽያጭና ኤክሳይስ ታክስ ይጥላሉ፣ ይሰበስባሉ።
8. ብአንቀጽ 98 ንዑስ አንቀጽ 3 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በማዕድን ሥራዎች ላይ የማዕድን ገቢ ግብር፣ የሮያሊቲና የመሬት ኪራይ ክፍያዎች ይጥላሉ፣ይሰበስባሉ።
9. በክልል መስተዳድር አካላት ከሚሰጡ ፈቃዶችና አገልግሎቶች የሚመነጩ ክፍያዎች ይወስናሉ፣ ይሰበስባሉ።
10. ከደን የሚገኝ የሮያሊቲ ክፍያ ይወስናሉ፣ ይሰበስባሉ።

**<u>አንቀጽ 98 የጋራ የታክስና የግብር ሥልጣን</u>**

1. የፌዴራል መንግሥትና ክልሎች በጋር በሚያቋቁሟቸው የልማት ድርጅቶች ላይ የንግድ ትርፍ ግብር፣ የሥራ ግብር፣ የሽያጭና የኤክሳይስ ታክስ በጋራ ይጥላሉ፣ይሰበስባሉ።
2. በድርጅቶች የንግድ ትርፍ ላይ እና በባለ አክሲዮኖች የትርፍ ድርሻ ላይ ግብርና የሽያጭ ታክስ በጋራ ይጥላሉ፣ ይሰበስባሉ።
3. በከፍተኛ የማዕድን ሥራዎችና በማናቸውም የፔትሮሊየምና የጋዝ ሥራዎች ላይ የገቢ ግብርና የሮያሊቲ ክፍያዎች በጋራ ይጥላሉ፣ ይሰበስባሉ።

**አንቀጽ 99 ተለይተው ስላልተሰጡ የታክስ እና የግብር ሥልጣኖች**

በዚህ ሕገ መንግሥት ተለይተው ያልተሰጡ ታክስና ግብር የመጣል ሥልጣኖችን በሚመለከት የፌዴሬሽኑ ምክር ቤትና የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በጋራ ስብሰባ በሁለት ሦስተኛ ድምጽ ይወስናሉ፡፡

**አንቀጽ 100 የታክስና የግብር አጣጣል መርሆዎች**

1. ክልሎችና የፌዴራሉ መንግሥት ታክስና ግብር በሚጥሉበት ጊዜ የሚጠየቀው ታክስና ግብር ከምንጩ ጋር የተያያዘና በአግባቡ ተጠንቶ የተወሰነ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡
2. በመካከላቸው የሚኖረውን መልካም ግንኙነት የማይጐዳና ከሚቀርበው አገልግሎት ጋር ተመጣጣኝ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡
3. ለትርፍ የቆመ ድርጅት ካልሆነ በስተቀር ክልሎች በፌዴራሉ መንግሥት ንብረት ላይ፣ የፌዴራሉ መንግሥትም በክልሎች ንብረት ላይ ግብር ወይም ቀረጥ የማስከፈል ሥልጣን አይኖራቸውም፡፡

**አንቀጽ 101 ዋናው ኦዲተር**

1. ዋናው ኦዲተር በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅርቢነት በሕዝብ ተወካዮቸ ምክር ቤት ይሾማል፡፡
2. ዋናው ኦዲተር የፌዴራሉን የሚኒስቴርና ሌሎች መሥሪያ ቤቶች ሂሳቦች በመቆጣጠር በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተመደበው ዓመታዊ በጀት፣ በበጀት ዓመቱ ለተሰሩት ሥራዎች በሚገባ መዋሉን መርምሮ ለምክር ቤቱ ሪፖርት ያቀርባል፡፡
3. ዋናው ኦዲተር የመሥሪያ ቤቱን በጀት በቀጥታ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርቦ ያስጸድቃል፡፡
4. የዋናው ኦዲተር ዝርዝር ተግባር በሕግ ይወሰናል፡፡

**አንቀጽ 102 የምርጫ ቦርድ**

1. በፌዴራልና በክልል የምርጫ ክልሎች ነጻና ትክክለኛ ምርጫ በገለለተኝነት እንዲያካሂድ ከማንኛውም ተጽእኖ ነጻ የሆነ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ይቋቋማል፡፡
2. የቦርዱ አባላት በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይሾማሉ፡፡ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡

**አንቀጽ 103 የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን**

1. የሀገሪቱን የሕዝብ ቁጥር በየጊዜው የሚያጠናና ቆጠራ የሚያካሂድ የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን ይኖራል፡፡
2. የኮሚሽኑ አባላት በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይሾማሉ፡፡
3. ኮሚሽኑ ዋና ጸሐፊ፣ አስፈላጊ ባለሙያዎችና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡
4. የኮሚሽኑ ዓመታዊ በጀት በቀጥታ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርቦ ይጸድቃል፡፡
5. የሕዝብ ቆጠራ በየአሥር ዓመቱ ይካሔዳል፡፡ በውጤቱም መሰረት የምርጫ ክልሎችን አከላለል የምርጫ ቦርድ በሚያቀርበው ረቂቅ መሠረት የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት ይወስናል፡፡

6. የኮሚሽኑ ተጠሪነት ለሕዝብ ተወካዮቸ ምክር ቤት ነው። ስለ ሥራው አፈጻጸፍ በየጊዜው ለምክር ቤቱ ሪፖርት ያቀርባል።

**አንቀጽ 104 የሕገ መንግሥት ማሻሻያ ሐሳብን ስለማመንጨት**

አንድ የሕገ መንግሥት ማሻሻያ ሐሳብ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሁለት ሦስተኛ ድምጽ የደገፈው፣ የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት በሁለት ሦስተኛ ድምጽ የደገፈው ወይም ከፌዴሬሽኑ አባል ክልሎች ውስጥ አንድ ሦስተኛው የክልል ምክር ቤቶች በድምጽ ይወክላልጫየደገፉት ከሆነ ለውይይትና ለውሳኔ ለመላው ሕዝብና የሕገ መንግሥቱ መሻሻል ለሚመለከታቸው ክፍሎች ይቀርባል።

**አንቀጽ 105 ሕገ መንግሥቱን ስለማሻሻል**

1 በዚህ ሕገ መንግሥት ምዕራፍ ሦስት የተዘረዘሩት መብቶችና ነጻነቶች በሙሉ፣ይህ አንቀጽ፣ እንዲሁም አንቀጽ 104 ሊሻሻሉ የሚችሉት በሚከተለው አኳኃን ብቻ ይሆናል።

ሀ/ ሁሉም የክልል ምክር ቤቶች የቀረበውን ማሻሻያ በድምጽ ይወክላልጫ ሲያጸድቁት፣

ለ/ የፌዴራሉ መንግሥት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሁለት ሦስተኛ ድምጽ የቀረበውን ማሻሻያ ሲያጸድቀው፣ እና

ሐ/ የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት በሁለት ሦስተኛ ድምጽ ማሻሻያውን ሲያጸድቀው ነው።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ከተዘረዘሩት ውጭ ያሉት የሕገ መንግሥቱ ድንጋጌዎች ሊሻሻሉ የሚችሉት በሚከተለው አኳኍን ብቻ ይሆናል፤

ሀ/ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት በጋራ ስብሰባ በሁለት ሦስተኛ ድምጽ የቀረበውን ማሻሻያ ሲያጸድቁት፣ እና

ለ/ ከፌዴሬሽኑ አባል ክሌሎች ምክር ቤቶች ውስጥ የሁለት ሦስተኛ ክልሎች ምክር ቤቶች በድምጽ ይወክላልጫ የቀረበውን ማሻሻያ ሲያጸድቁት ነው።

**አንቀጽ 106 የመጨረሻ ሕጋዊ እውቅና ስላለው ቅጂ**

የዚህ ሕገመንግሥት የአማርኛ ቅጂ የመጨረሻው ሕጋዊ እውቅና ያለው ሰነድ ነው።

የክልል አስራ አራት መስተዳድር አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ፩/፲፱፻፹፭ አጭር መግለጫ

ማውጫ

፩. አጭር ርእስ

፪. መቋቋም

፫. በአዲስ ነጋሪ ጋዜጣ የሚወጡ ጉዳዮች

፬. የሕጎች ተፈጻሚነት

፭. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

<u>አጭር መግለጫ</u>

በክልሉ ምክር ቤት የተለያዩ ሕጎች ኃይል ኑሯቸው ተፈጻሚ የሚሆኑት የሕጉ ተጠቃሚ የሆነው ሕዝብና የክልሉ መስተዳድር የሕግ አወጭ፣ የሕግ ተርጓሚና የሕግ አስፈጻሚ አካላት በሕዝብ ጋዜጣ በቅድሚያ እንዲያውቁት ሲደረግ ስለሆነ ሕጎቹ የሚወጡበት ኦፊሴል ጋዜጣ ማቋቋመ በማስፈለጉ የተዘጋጀ ህግ ነው፡፡

## <u>የክልል አስራ አራት መስተዳድር አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ፩/፲፱፻፹፭</u>

የክልል አስራ አራት ክልላዊ መስተዳድር በሕግ የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር ለመወጣት የሚያስችሉ የራሱ ሕጎች በክልሉ ምክር ቤት ተመክረው የወጡና የሚወጡ በመሆኑ፤
በክልሉ ምክር ቤት የተለያዩ ሕጎች ኃይል ኑሯቸው ተፈጻሚ የሚሆኑት የሕጉ ተጠቃሚ የሆነው ሕዝብና የክልሉ መስተዳድር የሕግ አወጭ፣ የሕግ ተርጓሚና የሕግ አስፈጻሚ አካላት በሕዝብ ጋዜጣ በቅድሚያ እንዲያውቁት ሲደረግ ስለሆነ ሕጎቹ የሚወጡበት ኦፊሴል ጋዜጣ ማቋቋመ በማስፍለጉ፤
በክልል አስራ አራት የሽግግር መስተዳድር ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፳፪ መሠረት የሚከተለው ታውጅዋል።

**<u>አንቀጽ ፩</u>**

**፩. አጭር ርእስ**

ይህ አዋጅ "የክልል አስራ አራት አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ማቋቋሚያ አዋጅ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**አንቀጽ ፪**

**፪. መቋቋም**

በዚህ አዋጅ "አዲስ ነጋሪት ጋዜጣ" ተብሎ የሚጠራ የክልሉ መስተዳድር ጋዜጣ ተቋቁሟል።

**አንቀጽ ፫**

**በአዲስ ነጋሪ ጋዜጣ የሚወጡ ጉዳዮች**

፩. በአዲስ ነጋሪ ጋዜጣ የሚወጡ ጉዳዮች ለክልሉ መስተዳድር የተለያዩ አካላት በክልሉ ሕገ መንግስት በተሰጣቸው ሥልጣን መሰረት፣

ሀ) የክልሉን ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊ እና አስተዳደራዊ ጉዳዮች፣

ለ) ከፍተኛ የክልሉ ባለስልጣኖቸ ሹመት፣ ሽረት፣ የማዕረግ ስም ሽልማትና ኒሻን፣

ሐ) ለህዝብ ጥቅም ያላቸው የክልሉ ህዝብ ማወቅ የሚገባቸው ማስታወቂያዎች ናቸው።

፪. ስለሆነም በአዲስ ነጋሪ ጋዜጣ የሚወጡ ሕጎች በክልሉ ሕገ መንግስት ደንብ ለማውጣት ሥልጣን ባላቸው አካሎች ከዚህ በላይ የተገለጹት ጉዳዮዮችን ለሕዝብ ለማስታወቅ የሚወጡ አዋጆች ድንጋጌዎች ደንቦች እና የህግ ክፍል ማስታወቂያዎች ይሆናሉ።

**አንቀጽ ፬**

፩. አዲስ ነጋሪ ጋዜጣው ተከታታይ ቁጥሮች በመያዝ የክልሉን መስተዳደር አርማ ያለው ሆኖ የማዕከ ላዊ መንግስት ነጋሪት ጋዜጣ ቅርጽ (ፎርም) ይኖረዋል።

፪. በአዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ግርጌ የክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት ማህተም ያረፈበት መሆን አለበት።

፫. የአዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ቅርጽ (ፎርም) ሕጋዊ ሆኖ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚሠራ አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ የሚከተለውን ቅርጽ (ፎርም) የሚያሟላ ነው፤

**፬. የሕጎች ተፈጻሚነት**

በዚህ አዋጅ በተቋቋመ አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ የሚወጡ አዋጆች፣ ድንጋጌዎች ደንቦችና ልሎች የሕግ ክፍል ማስታወቂያዎች በማንኛውም የክልሉ መስተዳደር አካላት ተፈጻሚ ይሆናሉ።

**፭. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ ዓዋጅ በዚህ ዓዋጅ መሠረት በተቋቋመ በአዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ታኅሣሥ ፲፪ ቀን ፲፱፻፹፭ ዓ.ም

አዋጅ ቁጥር 361/1995 የተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አጭር መግለጫ

ማውጫ

1. ክፍል አንድ ጠቅላላ
2. ክፍል ሁለት የከተማው አስተዳደር ዓላማ፣ አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባር
3. ክፍል ሦስት ስለከተማው ምክር ቤት
4. ክፍል አራትየከተማው አስፈጻሚ አካላት
5. ክፍል አምስት ሌሎች አስፈጻሚ አካላት

6. ክፍል ስድስት ክፍለ ከተማና ቀበሌ
7. ክፍል ሰባት የከተማው ፍርድ ቤቶችና የመዳኘት ሥልጣን የተሠጣቸው ሌሎች አካላት
8. ክፍል ስምንት ስለ በጀት እና ፋይናንስ
9. ክፍል ዘጠኝ መስተዳድራዊ ግንኙነት
10. ክፍል አሥር ልዩ ልዩ ጉዳዮች

**አጭር መግለጫ**

ከአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ቻርተር አዋጅ ቁጥር87/1889 አፈጻጸም የተገኙትን ተሞክሮዎች በማጤንና የአዲስ አበባ ከተማን አደረጃጀትና አመራር እና አሰራር ከጊዜው ጋር የሚሄድ ቻርተር ለማዘጋጀት የወጣ ህግ ነው፡፡

## አዋጅ ቁጥር 361/1995 የተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር

አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ርዕሰ ከተማ እና የአፍሪካ ህብረትና የተለያዩ ዓለም አቀፋዊ ተቋማት መቀመጫ በመሆኑ እንዲሁም የሀገሪቱን ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ጥንቅር የሚያንፀባርቅ ሰፊና አዳጊ ነዋሪ ያለበት በመሆኑ በዘመናዊነቱ ደረጃውን የጠበቀ መልካም የሥራና የመኖሪያ ከተማ መሆን እንዳለበት በማመን፤
የአዲስ አበባ ነዋሪ ራሱን በራሱ የማስተዳደር ሙሉ ሥልጣን እንዳለውና ዝርዝሩ በሕግ እንደሚወሰን በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት የተደነገገውን መሠረት በማድረግ፤
የከተማው ነዋሪ ለከተማው ዕድገት ያለውን በጎ ምኞትና ታታሪነት በማጤንና ከተማው ያለውን የልማት አቅም በመመርኮዝ የዕድገት ዓላማውን በይበልጥ ለማሣካት የሚያስችለውን ሁኔታ ማመቻቸት በማስፈለጉ፤

ከተማው ኢንቨስትመንትን በመሳብ ለነዋሪው የኑሮ መሻሻልና ለሀገሪቱ የኢኮኖሚ እድገት በር ከፋች በመሆን ተጨባጭ አስተዋጽኦ ሊኖረው እንደሚችል በመገንዘብ፤ የከተማው ተወዳዳሪነትና የልማት ቀጣይነት እውን እንዲሆን የከተማው አሠራርና አካሄድ ሥሉጥ፣ ውጤታማና ፍትሐዊ እንዲሆንና ለውጥ አምጭና አስተናጋጅ በመሆን ከተማው ራሱን በራሱ እያደሰ ከጊዜው ጋር እንዲሄድ ማስቻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤ ከአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 87/1889 አፈጻጸም የተገኙትን ተሞክሮዎች በማጤንና የአዲስ አበባ ከተማን አደረጃጀትና አመራር ከዲሞክራሲ መርሆዎችና ከመልካም የአስተዳደር ሥርዓት እንዲሁም ከወቅታዊ የዕድገትና የልማት አቅጣጫ ጋር በሚጣጣም መልኩ በማየት የተሻሻለ ቻርተር ማውጣት በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 49/2/ እና አንቀጽ 55/1/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1995" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ቻርተር ውስጥ፡-

1. "ከተማ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤
2. "የከተማ አስተዳደር" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤
3. "ከንቲባ" ማለት የከተማውን አስተዳደር የሚመራ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ነው፤
4. "የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት" ማለት የውሃና ፍሳሽ አገልግሎት፣ የመንገድ ሥራ አገልግሎት፣ የእሳትና ድንገተኛ አደጋ አገልግሎት፣ የክብር መዝገብ ሥራዎችን ጨምሮ የነዋሪዎች የእለት ተዕለት አገልግሎት፣ የመሬት ልማት እና አስተዳደር አገልግሎት፣ የከተማ ጽዳትና ውበት አገልግሎት እና የከተማው አስተዳደር የሚወስናቸውን ሌሎች አገልግሎቶች ይጨምራል፤
5. "ክፍለ ከተማ" ማለት የከተማው ሁለተኛው ደረጃ የአስተዳደር እርከን ነው፤
6. "ቀበሌ" ማለት የከተማው ሦስተኛ ደረጃ የአስተዳደር እርከን የሆነ የክፍለ ከተማ አካል ነው፤
7. "የሥራ ሁኔታ" ማለት የከተማው አስተዳደር ከሥራ ኃላፊዎቹና ከሠራተኞቹ ጋር ያለውን ጠቅላላ ግንኙነት የሚመለከት ሲሆን ይህም የሥራ ሰዓትን፣ ደመወዝን፣ ፈቃዶችን፣ ከሥራ በሚሰናበትበት ጊዜ የሚገባውን ክፊያ "ካሳ"፣ የጤንነት እና ደህንነት፣ በሥራ ምክንያት ጉዳት ለደረሰባቸው ስለሚከፈል ካሣ፣ የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓቶችንና የመሣሰሉትን ያጠቃልላል፡፡

3. **ሕጋዊ ሰውነት**

የከተማው አስተዳደር ሕጋዊ ሰውነት አለው፡፡

4. **ስም**

የከተማው ስም አዲስ አበባ ነው፡፡

5. <u>ወሰን</u>

አሁን ያለው የከተማው ክልል እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የከተማው ወሰን የከተማው አስተዳደር ከኦሮሚያ ክልል ጋር በሚያደርገው ስምምነት ወይም በፌዴራል መንግሥት ይወሰናል፣ የወሰን ምልክትም ይደረግበታል፡፡

6. <u>የሥራ ቋንቋ</u>

የከተማው አስተዳደር የሥራ ቋንቋ አማርኛ ነው፡፡

7. <u>የነዋሪዎች መብት</u>

1. በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት እና በሌሎች የሀገሪቱ ሕጐች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ነዋሪዎች ስለ ከተማው የሚወስኑ ጉዳዮችን በሚመለከት መረጃ የማግኘት፣ ሃሳብና ጥያቄ የማቅረብ እና መልስ የማግኘት መብት አላቸው፡፡
2. ነዋሪዎች የከተማው አስተዳደር የሚሰጠውን አገልግሎት በእኩልነት፣ በግልጽነትና በፍትሐዊነት መርህ መሠረት የማግኘት መብት አላቸው፡፡
3. የከተማው አስተዳደር ፖሊሲ፣ በጀት፣ የሥራ ዕቅድና መመሪያ ለነዋሪዎች ይፋ መሆን አለበት፡፡

8. <u>ስለምርጫ</u>

በዚህ ቻርተር መሠረት የሚከናወኑ የከተማው ምርጫዎች በሀገሪቱ የምርጫ ሕግ መሠረት ይከናወናሉ፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የከተማው አስተዳደር ዓላማ፣ አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባር</u>

9. <u>ዓላማ</u>

የከተማው አስተዳደር የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፣

1. ብቁ፣ ግልፅና ለነዋሪው ተጠያቂነት ያለበት መልካም የአስተዳደር ሥርዓት፣ ቀልጣፋና ፍትሐዊ የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት እንዲሁም አስተማማኝ ፀጥታና ማህበራዊ ትስስር የተረጋገጠበት ከተማ የማድረግ፤
2. የፌዴራል መንግሥት ርዕሰ ከተማ፣ ለአፍሪካ ህብረትና ለተለያዩ ዓለማቀፍ አህጉራዊ ድርጅቶች መቀመጫ የመሆን ሚናውን የማሳደግ፤
3. አመቺ የመኖሪያ የሥራ ሁኔታ የመፍጠር እንዲሁም ነዋሪዎች የከተማውን ሁለገብ እንቅስቃሴ የሚወስኑበትንና የልማት ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ሁኔታ የማመቻቸት፤
4. የሀገሪቱ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በእኩልነት የሚኖሩበት፣ የባሕላቸው መግለጫ የሆነ ማዕከል እንዲሆን ማድረግ፤

5. የነዋሪዎች ደህንነትና ምቾት የተጠበቀበት በተለይም ሕፃናት፣ ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞችና አረጋውያን ሌሎች የተጐዱ የሕብረተሰብ ክፍሎች የተለየ ድጋፍ የሚያገኙበት ከተማ የማድረግ፤
6. ኢንቨስትመንትና ምርምርን በማበረታታትና በማጎልበት ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት የማምጣት፤
7. ከተማውን የሀገሪቱ የንግድና የኢንዱስትሪ ማዕከል እንዲሆን የማድረግ፤ እና
8. የአካባቢ ብክለትን በመከላከል የተፈጥሮ ሚዛኑን የጠበቀ ፅዱ፣ አረንጓዴና ምቹ ከተማ የማድረግ።

10.<u>የከተማው አስተዳደር የሥልጣን አካላት አደረጃጀት</u>

1. የከተማው አስተዳደር የሥልጣን አካላት የሚከተሉት ናቸው፣
   ሀ/ የከተማው ምክር ቤት፣
   ለ/ ከንቲባ፣
   ሐ/ የከተማው ካቢኔ፣
   መ/ የከተማው የዳኝነት አካላት፣ እና
   ሠ/ የከተማው ዋናው ኦዲተር መሥሪያ ቤት።
2. የክፍለ ከተማ የሥልጣን አካላት የሚከተሉት ናቸው፣
   ሀ/ የክፍለ ከተማው ምክር ቤት፣
   ለ/ የክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈፃሚ፣ እና
   ሐ/ የክፍለ ከተማው ቋሚ ኮሚቴ፤
3. የቀበሌ የሥልጣን አካላት የሚከተሉት ናችው።
   ሀ/ የቀበሌ ምክር ቤት፣
   ለ/ የቀበሌ ዋና ሥራ አስፈጻሚ፣
   ሐ/ የቀበሌ ቋሚ ኮሚቴ፤ እና
   መ/ የቀበሌ ማኅበራዊ ፍ/ቤት።

11.<u>የከተማው አስተዳደር ሥልጣንና ተግባር</u>

1. የከተማው አስተዳደር በዚህ ቻርተር ተለይተው በተሰጡት ጉዳዮች ላይ የሕግ አውጪነትና የዳኝነት ሥልጣን እንዲሁም በፌዴራል መንግሥት አስፈጻሚ አካላት ሥልጣንና ተግባራት ዝርዝር ተለይተው ባልተካተቱ ጉዳዮች ላይ የሕግ አስፈፃሚነት ሥልጣን ይኖረዋል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የከተማው አስተዳደር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

ሀ/ የከተማውን ልማት የሚመለከቱ ፖሊሲዎችን የማውጣትና በሥራ ላይ የማዋል፤

ለ/ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ልማት ዕቅዶችን ማፅደቅ፣ በሥራ ላይ የማዋል፤

ሐ/ የከተማውን አስተዳደር ሠራተኞች እና ኃላፊዎች እንዲሁም በዚህ ቻርተር የተገለፁትን የሥልጣን አካላት ባልደረቦች የሥራ ሁኔታ የመወሰን፤

መ/ የከተማውን አስተዳደር አስፈጻሚ አካላትን የማቋቋም እንዲሁም የከተማውን የልማት ድርጅቶች ሕጋዊ አካል አድርጎ በእራሱ ወይም ከግሉ ዘርፍ ወይም ከሌሎች ሦስተኛ ወገኖች ጋር አግባብ ባለው ሕግ መሠረት በሽርክና የማቋቋም፤

ሠ/ ክፍለ ከተማዎችንና ቀበሌዎችን የማቋቋም፣ ወሰናቸውን የመወሰን እንዲሁም ለክፍለ ከተማዎች የበጀት ድጎማን የመመደብ፤

ረ/ በከተማ፣ በክፍለ ከተማና በቀበሌ ደረጃ የሚሰጡ የማዘጋጃ ቤት አገልግሎቶች ለይቶ መወስንና የማደራጀት፣ የተለያዩ የማዘጋጃ ቤት የአገልግሎት መስጫ አማራጮችን በመጠቀምና ነዋሪውን በማሳተፍ ስሉጥ፣ ውጤታማና ፍትሐዊ አገልግሎት ማቅረብ፤ ደረጃውን የጠበቀና ተቀባይነት ያለው የአገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት መኖሩን የማረጋገጥ፤

ሰ/ በከተማው ክልል ውስጥ የሚገኘውን መሬትና የተፈጥሮ ሀብት በሕግ መሠረት የማስተዳደር፤

ሸ/ የከተማ ቦታና ትርፍ ቤትን የመንግሥት ንብረት ለማድረግ በወጣው አዋጅ ቁጥር 47/1967 መሠረት የተወረሱና የሚያስተዳድራቸውን ቤቶች፣ የሠራቸውን ወይም በሕጋዊ መንገድ ያገኛቸውን ሌሎች ቤቶች የማስተዳደር፣ የማልማት ወይም የመሸጥ፤

ቀ/ ለሕዝብ ጥቅም አስፈላጊ የሆነ የግል ንብረትንና የቦታ ይዞታን በሕግ መሠረት ተመጣጣኝ ካሣ በመክፈል የማስለቀቅና የመውሰድ

በ/ የከተማውን በጀት የማዘጋጀት፣ የማጽደቅና የማስተዳደር፣ በዚህ ቻርተር ተለይተው በተሰጡት የገቢ ምንጮች ክልል ግብር፣ ቀረጥ እና የአገልግሎት ክፍያ በሕግ መሠረት የመወስን፤ የመሰብሰብ፤ ፍሬ ግብርንና የተጣሉ ቅጣቶችን በሕግ አግባብ የማንሳት፣ በገቢ ማስገኛ ተግባራት የመሳተፍ እና ዕርዳታና ስጦታ የመቀበል፤

ተ/ በፌዴራል መንግሥት በማስፈቀድ ከሀገር ውስጥ ምንጮች መበደርና ከሀገር ውጭ ያሉ የብድር ምንጮችን በማፈላለግ የፌዴራል መንግሥት እንዲበደርለት መጠየቅ፤ እና

ቸ/ ከፌዴራል መንግሥት እና ከክልል አካላትና ተቋማት፣ ከግሉ ዘርፍ፣ መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች እንዲሁም በፌዴራል መንግሥት ፈቃድ ከልዩ ልዩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር ግንኙነቶችን መመሥረትና የትብብር ስምምነቶችን የማድረግ።

## ክፍል ሦስት

## ስለከተማው ምክር ቤት

### 12.ስለ ምክር ቤት አባላት

1. የምክር ቤቱ አባላት በየአምስት ዓመቱ በከተማው ነዋሪይመረጣሉ።

2. የምክር ቤቱ አባላት ቁጥር በምርጫ ሕግ መሠረት ይወሰናል፡፡
3. ማንኛውም የምክር ቤት አባል በምክር ቤቱ ውስጥ በሚሰጠው ድምጽ ወይም አስተያየት አይከሰስም፣ አስተዳደራዊ እርምጃም አይወሰድበትም፡፡
4. ማንኛውም የምክር ቤት አባል ከባድ ወንጀል ሲፈጽም እጅ ከፍንጅ ካልተያዘ በስተቀር ያለምክር ቤቱ ፈቃድ አይያዝም፣ በወንጀልም አይከሰስም፡፡
5. የምክር ቤቱ አባላት ነፃ ናቸው፡፡ ተጠያቂነታቸውም፣
   ሀ/ ለኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት፤
   ለ/ ለዚህ ቻርተር፤
   ሐ/ ለህሊናቸው፤ እና
   መ/ ለከተማው ነዋሪ ብቻ ይሆናል፡፡
6. ማንኛውም የምክር ቤቱ አባል የመረጠው ነዋሪ አመኔታ ባጣበት ጊዜ በሕግ መሠረት ከምክር ቤት አባልነቱ ይወገዳል፡፡
7. ማንኛውም የምክር ቤት አባል በተመረጠበት ምክር ቤት የሥራ ዘመን በፈቃዱ ካልለቀቀ ወይም ካልተሰናበተ በስተቀር በምርጫ ቦርድ በሚከናወኑ ሌሎች ምርጫዎች ሊወዳደር አይችልም፡፡
8. ማንኛውም የምክር ቤት አባል የግል ጥቅሙና የከተማው ጥቅም የሚጋጩበት ሁኔታ ሲኖር ውሳኔ ከመስጠት መገለል እና ለምክር ቤቱ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

**13.<u>የከተማውን የሕግ አስፈፃሚ አካል ስለማደራጀት</u>**

በምክር ቤቱ አብላጫ መቀመጫ ያለው የፖለቲካ ድርጅት ወይም አብላጫ መቀመጫ ያለው የፖለቲካ ድርጅት ከሌለ የፖለቲካ ድርጅቶች ጣምራ የከተማውን የሕግ አስፈፃሚ አካል ያደራጃል (ይመራል)፡፡

**14.<u>የከተማው ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር</u>**

1. ለከተማው አስተዳደር የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ለማዋል የከተማው ምክር ቤት በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ አዋጅ የማውጣት ሥልጣን አለው፡፡
   ሀ/ የከተማውን አስፈፃሚ አካላት ለማቋቋም፣
   ለ/ የከተማውን አስተዳደር በጀት ለማጽደቅ፣
   ሐ/ የከተማውን መሪ ፕላን ለማውጣት፣
   መ/ በዚህ ቻርተር በተደነገገው መሠረት የከተማውን የዳኝነት አካላት ለማቋቋምና እንደየአግባቡ ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሠን፣
   ሠ/ በዚህ ቻርተር መሠረት በከተማው አስተዳደር ሥልጣን ሥር በሚወድቁ የፋይናንስ ጉዳዮች ላይ ግብር እና ቀረጥ ለመጣል፣ የአገልግሎት ክፍያ ለመወሰን፤ እና

ረ/ የከተማውን ከንቲባ ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ይመርጣል፡፡[4]

2. የከተማው ምክር ቤት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

ሀ/ በሥልጣኑ ክልል ሥር በሚወድቁ ጉዳዮች ላይ ከተማ አቀፍ ፖሊሲ ያወጣል

ለ/ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚወጡ አዋጆች ላይ ሥልጣን ሲሰጠው ደንብ ያወጣል፤

ሐ/ የከተማውን የአጭርና የረጅም ጊዜ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማት ዕቅድ እና በ24/55(2010) አ.1094 አንቀፅ 2(1) ተሻሻለ፡፡

መ/ በዚህ ቻርተር ተለይተው በተመለከቱት የገቢ ምንጮች ላይ ግብር እና ቀረጥ ይጥላል፣ የአገልግሎት ክፍያ ይወስናል፤

ሠ/ የምክር ቤቱን አፈጉባዔ፣ ምክትል አፈ ጉባዔና ፀሐፊ ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ይመርጣል እንዲሁም የምክር ቤቱን ጽህፈት ቤት ያቋቁማል፤

ረ/ የከተማውን ከንቲባና ምክትል ከንቲባ ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ይመርጣል፤

ሰ/ በከንቲባው አቅራቢነት የከተማውን ካቢኔ አባላት ሹመት ያፀድቃል፤ ሸ/ የከተማውን ፍርድ ቤቶች ፕሬዚዳንት፣ ምክትል ፕሬዚዳንት እና ዳኞች እንዲሁም የዋናው ኦዲተር ሹመት ያፀድቃል፡፡ የጃኞች አስተዳደር ጉባዔን ያቋቁማል፣ አባላቱንም ይሠይማል፤

ቀ/ ተጠሪነታቸው ለእርሱ የሆኑ የአስተዳደራዊ የመዳኘት ሥልጣን የተሠጣቸው ሌሎች አካላት ፕሬዚዳንቶችን እንዲሁም በሕግ መሠረት ሹመታቸው በምክር ቤቱ መጽደቅ ያለበትን ሌሎች ባለሥልጣናት ሹመት ያፀድቃል፤

በ/ የከተማውን አስፈጻሚ አካላትና የልማት ድርጅችን ያቋቁማል፤

ተ/ የምክር ቤቱን ኮሚቴዎች ያቋቁማል፤ አባላቱንም ከምክር ቤቱ አባላት ውስጥ ይሰይማል፤

ቸ/ በማንኛውም ወቅት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከንቲባው ከሚያቀርባቸው ሦስት ዕጩዎች መካከል ምክር ቤቱ የውጭ ኦዲተር ይሠይማል፣ የውጭ ኦዲተሩ የሚያቀርበውን ሪፖርት መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፤

ኀ/ የማዘጋጃ ቤት አገልግሎቶችን የጥራት ደረጃ እና የአገልግሎት ክፍያ ያፀድቃል፤

ነ/ የክፍለ ከተማና የቀበሌ ምክር ቤት አባላት ብዛት ይወስናል፤

ኘ/ በሚያወጣው ቀመር መሠረት የክፍለ ከተማዎችን የበጀት ድጎማ ይመድባል፤

አ/ ከከንቲባው ወይም ተጠሪነታቸው ለእርሱ ከሆኑ አካላት የሚቀርቡለትን ወቅታዊ ሪፖርቶች መርምሮ ውሣኔ ይሠጣል፤

ከ/ በፌዴራል መንግሥት በተፈቀደው መሠረት ከሀገር ውስጥ ምንጮች ጋር የሚደረጉ የብድር ስምምነቶችን መርምሮ ያፀድቃል፤

ኸ/ ለምክር ቤቱ አባላት የሥነ ምግባር ደንብ ያወጣል፤

ወ/ የከተማው ከንቲባ፣ ምክትል ከንቲባ፣ የምክር ቤቱ አፈጉባዔ፣ ምክትል አፈጉባዔ፣ የከተማው ካቢኔ አባላት፣ ዋና ኦዲተር እንዲሁም ሌሎች የምክር ቤት አባላት የሥነ ምግባር ጉድለት ፈፅመዋል በሚባልበት ጊዜ በሚያወጣው ደንብ መሠረት ምርመራ ያደርጋል፣ ምሥክሮች ይሠማል፣ ሌላ ማስረጃ እንዲቀርብ ያደርጋል፣ ውሣኔም ይሰጣል፡፡

15.<u>የከተማ ምክር ቤት የስራ ዘመን እና የስብሰባ ስነስርዓት</u>

1. የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል፡፡ ሆኖም ግን ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ገጥሞ በአምስት ዓመት መጠናቀቂያ ወቅት ምርጫ ማካሄድ ያልተቻለ እንደሆነ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርቦ የምርጫ ግዜው ሊራዘም ይችላል፡፡ ምክር ቤቱ መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባ ይኖረዋል፤ መደበኛ ስብሰባው በየሁለት ወሩ ይሆናል፡፡
2. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የምርጫ ግዜ እንዲራዘም የወሰነ እንደሆነ ቀጣይ ምርጫ ተደርጎ በምርጫው መሰረት አዲስ አስተዳደር እስኪደራጅ ድረስ በስራ ላይ ያለው ምክር ቤት እና አጠቃላይ የከተማ አስተዳደሩ በነበረበት ይቀጥላል፡፡
3. በማናቸውም የምክር ቤቱ ስብሰባ ውሣኔ ሊተላለፍ የሚችለው በስብሰባው ላይ የተገኙት አባላት ከግማሽ በላይ ሲደግፉት ነው፡፡
4. ለከተማው ፀጥታ ወይም ደህንነት ወይም የግለሰቦችን ወይም የሕጋዊ አካላትን ጥቅም ለማስከበር አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር የምክር ቤቱ ስብሰባ ለሕዝብ ክፍት ይሆናል፡፡
5. የምክር ቤቱ አፈጉባዔ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፤ የምክር ቤቱ አባላት ከግማሽ በላይ ስብሰባ እንዲጠራ ከጠየቁ አፈጉባዔው ስብስባ የመጥራት ግዴታ አለበት፡፡
6. ምክር ቤቱ ስለአሠራሩ የሚወስን መተዳደሪያ ደንብ ያወጣል፡፡
7. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሰረት የምክር ቤቱ የስራ ዘመን የተራዘመ እንደሆነ በስራ ላይ የሚገኙ በህግ የተቋቋሙ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በ24/55(2010) አ.1094 አንቀፅ 2(2) መሰረት የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) እና (2) የተሻሻሉ ሲሆን ንዑስ አንቀፅ (7) አዲስ የተጨመረ ነው፡፡ የመንግስት አካላት ምርጫ እስከሚካሄድ ድረስ ተግባር እና ሀላፊነታቸውን መወጣት ይቀጥላሉ፡፡

16.<u>የከተማው ምክር ቤት መዝገብ አያያዝ</u>

ምክር ቤቱ አሠራሩን እና ውሣኔውን የሚመዘግብበት መዝገብ ይኖረዋል፤ ለከተማው ፀጥታ ወይም ደህንነት ወይም የግለሰቦችን ወይም የሌሎችን መብት ይጋፋል ተብሎ በምክር ቤቱ ካልተወሰነ በስተቀር መዝገቡ ለሕዝብ ግልጽ ይሆናል፡፡

17.<u>ስለ ምክር ቤቱ ተጠሪነትና መበተን</u>

1. የከተማው ምክር ቤት ተጠሪነት ለፌዴራል መንግሥትና ለከተማው ነዋሪዎች ይሆናል፡፡

2. የከተማው ምክር ቤት ሊበተን የሚችለው በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ወይም በእራሱ ውሣኔ ይሆናል። በዚህ ቻርተር አንቀጽ 61 ንኡስ አንቀጽ (3) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣

ሀ/ የከተማው ምክር ቤት የሥልጣን ዘመኑ ከማለቁ በፊት አዲስ ምርጫ ለማካሄድ በራሱ ውሳኔ ሊበተን ይችላል።

ለ/ በጣምራ አስፈፃሚነት ሥልጣን የያዙ የፖለቲካ ድርጅቶች ጣምራነት ፈርሶ በምክር ቤቱ የነበራቸውን አብላጫነት ያጡ እንደሆነ የከተማው ካቢኔ ተበትኖ በምክር ቤቱ ባሉ የፖለቲካ ድርጅቶች ሌላ ጣምራ ካቢኔ በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ ለመመሥረት እንዲቻል በፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር[6] ይጋበዛል። የፖለቲካ ድርጅቶች አዲስ ካቢኔ ለመፍጠር ወይም የነበረውን ጣምራነት ለመቀጠል ካልቻሉ ምክር ቤቱ ይበትናል።

ሐ/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 "ሀ" ወይም "ለ" መሠረት ምክር ቤቱ የተበተነ እንደሆነ ከስድስት ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ አዲስ ምርጫ መደረግ አለበት።

መ/ ምርጫው በተጠናቀቀ በሠላሣ ቀናት ውስጥ አዲሱ የከተማው ምክር ቤት ሥራውን ይጀምራል።

ሠ/ የከተማው ምክር ቤት ከተበተነ በኋላ ከተማውን የሚመራው ሥልጣን ይዞ የነበረው የሕግ አስፈፃሚ አካል የዕለት ተዕለት የአስፈፃሚነት ሥራ በ22/1292008) አ.916 አንቀፅ 9(2) መሰረት መሰረት የፌዴራል እና አርብቶ አደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስተር በሚል ይነበብ፡፡ከማከናወንና ምርጫ ከማካሔድ በስተቀር አዲስ ሕጎችን ማውጣት ወይም ነባር ሕጎችን መሻርና ማሻሻል አይችልም።

18.<u>የከተማው ምክር ቤት አፈጉባኤ</u>

ተጠሪነቱ ለምክር ቤቱ ሆኖ አፈጉባኤው፣

1. የሥራ ዘመኑ የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን ይሆናል፣ ሥራውን በፈቃዱ ሲለቅ ወይም በምክር ቤቱ ከኃላፊነት ሲታገድ ወይም የምክር ቤት አባልነቱ ሲቋረጥ የሥራ ዘመኑ ሳያልቅ ከኃላፊነቱ ሊሰናበት ይችላል፣ ዝርዝሩ በምክር ቤቱ መተዳደሪያ ደንብ ይወሰናል፤
2. የምክር ቤቱን ጽሕፈት ቤት ይመራል፤
3. ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረግ ግንኙነት ምክር ቤቱን ይወክላል፣
4. የምክር ቤቱን ስብሰባ ይጠራል፣ ይመራል፣ የምክር ቤቱን ኮሚቴዎች ያስተባብራል፤
5. የምክር ቤቱን ጽሕፈት ቤት በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤
6. የምክር ቤቱን ጽሕፈት ቤት ሠራተኞች በመንግሥት ሠራተኞች አስተዳደር ሕግ መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤
7. ምክር ቤቱ ያፀደቃቸው ሕጎች በአዲስ ነጋሪ ጋዜጣ እንዲወጡ ያደርጋል፤
8. ምክር ቤቱ በአባላት ላይ የሚወስዳቸውን የሥነ ሥርዓት እርምጃዎች ያስፈጽማል፤

9. በምክር ቤት ስለሚወሰኑት ውሳኔዎች ወቅታዊ መግለጫ ለነዋሪዎች ይሰጣል፣ ለሚመለከታቸው አካላት ያሳውቃል፣ የምክር ቤቱ ሰነዶች ለነዋሪዎች ክፍት እንዲሆኑ ያደርጋል፤

10. የምክር ቤቱን አባላት የአቅም ግንባታ ሥራ እቅድ ያዘጋጃል፣ ከሚመለከታቸው አስፈፃሚ አካላት ጋር በመቀናጀት ያስፈጽማል፤

11. ከሀገር ውስጥና ከውጭ አገር አቻ ምክር ቤቶች ጋር በመተባበር የልምድ ልውውጥ ያደርጋል፤

12. ከምክር ቤቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

**19. <u>የከተማው ምክር ቤት ምክትል አፈጉባኤ</u>**

ተጠሪነቱ ለምክር ቤቱ አፈጉባኤ ሆኖ ምክትል አፈጉባኤ፣

1. በአንቀጽ 18 ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው ለምክትል አፈጉባኤውም የሚሠራ ይሆናል፣
2. አፈጉባኤው በሌለበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶት ይሠራል፣
3. በአፈጉባኤው የሚሠጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናወናል።

**20. <u>የከተማው ምክር ቤት ፀሐፊ</u>**

ተጠሪነቱ ለምክር ቤቱ አፈ ጉባዔ ሆኖ የምክር ቤቱ ፀሐፊ፣

1. ከአፈ ጉባዔው ጋር በመመካከር የምክር ቤቱን አጀንዳ ያዘጋጃል፣ የምክር ቤቱን ቃለ ጉባዔ ይይዛል፣ ያትማል፤
2. የምክር ቤቱ ኮሚቴዎች ቃለ ጉባዔዎችና ሰነዶች እንዲያዙና እንዲጠበቁ ያደርጋል፣ በምክር ቤቱ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ቃለ ጉባዔዎችን ያሠራጫል፤
3. ሥራውን በራሱ ፈቃድ ሲለቅ፣ በምክር ቤቱ ከኃላፊነቱ ሲታገድ ወይም የምክር ቤት አባልነቱን ሲያቋርጥ የሥራ ዘመኑ ሳያልቅ ከኃላፊነቱ ሊሰናበት ይችላል፣ ዝርዝሩ በምክር ቤቱ መተዳደሪያ ደንብ ይወሰናል፤
4. በአፈ ጉባዔው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>የከተማው አስፈጻሚ አካላት</u>

**21. <u>ከንቲባ</u>**

1. ተጠሪነቱ ለከተማው ምክር ቤትና ለፌዴራል መንግሥት ሆኖ ከንቲባው የከተማው አስተዳደር ዋና ሥራ አስፈፃሚ ነው።

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከንቲባው፡-

ሀ/ በከተማው ምክር ቤት የሚወስኑትን ውሣኔዎች፣ የሚወጡቱን ሕጐች የሚፀድቁትን ዓመታዊ እቅድና በጀት ያስፈጽማል፤

ለ/ የከተማው ልዩ ልዩ ፖሊሲ፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ልማት እቅድ፣ ዓመታዊ በጀት በካቢኔው ከተመከረበት በኋላ ለምክር ቤቱ ያቀርባል፣ ሲጸድቅም ተግባራዊነቱን ያረጋግጣል፤

ሐ/ የከተማው አምባሳደር በመሆን ከተማውን ይወክላል፤

መ/ የከተማውን ህግና ሥርዓት ያስከብራል፤

ሠ/ የካቢኔ አባላትን መርጦ ሹመታቸውን በምክር ቤቱ ያፀድቃል፣ ካቢኔውን ይመራል፤

ረ/ የከተማው ምክር ቤት እንደአስፈላጊነቱ የውጭ ኦዲተር ለመሠየም ሲወስን ሦስት ዕጩ ኦዲተሮች ያቀርባል፤

ሰ/ ካቢኔውን በማማከር ሙያዊ ብቃትን መሠረት በማድረግ የከተማውን ሥራ አስኪያጅ በተወሰነ ጊዜ የሥራ ውል ይቀጥራል፣ ያሠናብታል፤

ሸ/ የነዋሪዎችን ቅሬታ ያስተናግዳል፤

ቀ/ በብሔራዊና የሕዝብ በዓላት ሥነ ሥርዓቶች ከተማውን ይወከላል፤

በ/ የከተማው ዕቅድ፣ በጀት፣ እንዲሁም የሥራ አፈጻጸም ለሕዝብ የሚቀርብበት እና አስተያየት የሚሰጥበት መድረክ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤

ተ/ ዓመታዊ እና እንደአስፈላጊነቱ ምክር ቤቱ በሚወስነው መሠረት ወቅታዊ ሪፖርት ለምክር ቤቱ ያቀርባል፤ እንዲሁም በዚህ ቻርተር አንቀፅ 61 ንዑስ አንቀፅ 6 በተገለፀው መሠረት ለፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር[7] ሪፖርት ያቀርባል፤ ቸ/ ደረጃውን የጠበቀ ፍትሐዊ የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አሰጣጥ ተግባራዊ መሆኑን ያረጋግጣል፤

ኀ/ ለከተማው የሚያስፈልገውን የድጋፍ መጠን በማዘጋጀት በከተማው ካቢኔ ከተመከረበት በኋላ ለፌዴራል መንግሥት ያቀርባል፤

ነ/ የአዋጅ እና የደንብ ረቂቆችን በማዘጋጀት በካቢኔው ከተመከረበት በኋላ ለምክር ቤቱ ያቀርባል፤

ኘ/ ሹመታቸው በምከር ቤቱ መጽደቅ ያለበትን ሣይጨምር የከተማውን አስፈጻሚ አካላት የበላይ ኃላፊዎች ይሾማል። ለከተማው የልማት ድርጅቶችና ሌሎች አካላት የቦርድ ሰብሳቢዎችና አባላትን ይሰይማል፤

አ/ የራሱን ጽሕፈት ቤት ያደራጃል፤

ከ/ በህግ መሠረት ሽልማቶችን ይሠጣል፤

ኸ/ በከተማው ምክር ቤት እና በፌዴራል መንግሥት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

3. የከንቲባው የሥራ ዘመን የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን ይሆናል፣ ሆኖም በራሱ ፈቃድ ሲለቅ፣ በምክር ቤቱ ከኃላፊነቱ ሲታገድ ወይም የምክር ቤት አባልነቱን ሲያቋርጥ የሥራ ዘመኑ ሳያልቅ ከኃላፊነት ሊሠናበት ይችላል፣ ዝርዝሩ በምክር ቤቱ መተዳደሪያ ደንብ ይወሰናል።

22.<u>ምክትል ከንቲባ</u>

ተጠሪነቱ ለከንቲባው ሆኖ ምክትል ከንቲባው፡-

1. ከንቲባው በሌለበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶት ይሠራል፤
2. በከንቲባው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።
3. ምክትል ከንቲባው ከምክር ቤት አባላት ውስጥ ወይም ከምክር ቤት አባላት ውጪ የሚሾም ሆኖ የስራ ዘመኑ የምክር ቤቱ የስራ ዘመን ይሆናል። ሆኖም በራሱ ፈቃድ ሲለቅ፣ በምክር ቤቱ ከሀላፊነት ሲታገድ የስራ ዘመኑ ሳያልቅ ከሀላፊነት ሊሰናበት ይችላል፤ ዝርዝሩ በምክር ቤቱ መተዳደሪያ ደንብ ሊወሰን ይችላል።[8]

23.<u>የከተማው ካቢኔ</u>

1. ተጠሪነቱ ለከንቲባው እና በጋራ ለሚወስነው ውሣኔም ለከተማው ምክር ቤት ሆኖ የከተማው ካቢኔ፣
   ሀ/ በፌዴራል መንግሥትና በከተማው ምክር ቤት የወጡ አዋጆች፣ ደንቦች፣ ውሣኔዎችና ደረጃዎች መፈጸማቸውን ያረጋግጣል፤
   ለ/ ምክር ቤቱ ያወጣቸው ፖሊሲዎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤
   ሐ/ ከተማ አቀፍ ፖሊሲና የአዋጅና የደንብ ረቂቅ ያመነጫል፤
   መ/ በከተማው ዓመታዊ እቅድና በጀት ላይ ይመክራል፤
   ሠ/ የከተማውን አስተዳደር አስፈጻሚ አካላት አደረጃጀት ይወስናል።
   ረ/ በምክር ቤቱ በሚወጡ አዋጆች ላይ በሚሰጠው ሥልጣን መሠረት ደንቦችን ያወጣል፤
   ሰ/ በከንቲባውና በምክር ቤቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።
2. የካቢኔው የሥራ ዘመን የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን ይሆናል።

24.<u>የከተማ ሥራ አስኪያጅ</u>

1. ተጠሪነቱ ለከንቲባው ሆኖ የከተማው ሥራ አስኪያጅ የማዘጋጃ ቤት አገልግሎቶች አስፈጻሚ ነው።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የከተማው ሥራ አስኪያጅ፤

ሀ/ ለእርሱ ተጠሪ የሆኑ የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት እንዲቋቋሙ ወይም ሌሎች የአገልግሎት መስጫ አማራጮች በሥራ ላይ እንዲውሉ ለከንቲባው ሃሳብ ያቀረባል፤

ለ/ የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት ኃላፊዎች እንዲሾሙ ለከንቲባው ያቀርባል፤ ሹመታቸው ሲፀድቅም ሥራቸውን በሕግ መሠረት ይመራል፣ ያሰናብታል፤

ሐ/ ብቃት ያላቸውን ባለሙያዎች በክፍለ ከተማ ሥራ አስኪያጅነት በተወሰነ ጊዜ የሥራ ውል ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፣ ከክፍለ ከተማ ሥራ አስኪያጆች ዓመታዊና አስፈላጊ ሲሆን ወቅታዊ ሪፖርቶችን ይቀበላል፤ መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፤

መ/ ከተማ አቀፍ እና ክፍለ ከተማ ዘለል የማዘጋጃ ቤት አገልገሎትን በተመለከተ እቅድ እና በጀት ለከንቲባው ያቀርባል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

ሠ/ የአገልግሎት አቅርቦት መለኪያዎች እና መመሪያዎች በማጠናከር ለከንቲባው ያቀርባል፣ ሲወሰንም ተግባራዊ ያደረጋል፤

ረ/ ሥሉጥ፣ ግልፅና ፍትሐዊ የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት መሠጠቱን ያረጋግጣል፤

ሰ/ የማዘጋጃ ቤት አገልግሎትን የሚመለከቱ ውሣኔዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፤

ሸ/ የማዘጋጃ ቤት አገልግሎትን የሚመለከት የፖሊሲ ሃሳብ እና የህግ ረቂቀ በማመንጨት ለከንቲባው ያቀርባል፣

ቀ/ የከተማው ምክትል ሥራ አስኪያጅ እንዲቀጠር ለከንቲባው ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ይቀጥራል፤

በ/ የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት ለከንቲባው ያቀርባል፤

ተ/ የማዘጋጃ ቤት አገልግሎትን በተመለከተ የነዋሪዎችን አቤቱታ ያስተናግዳል፣ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች በተቻለ ፍጥነት መልስ ይሠጣል፤

ቸ/ በሥሩ ከሚሠሩ አካላት ኃላፊዎች የተውጣጣ የሥራ አመራር ኮሚቴ ያቋቁማል፣ ይመራል፤

ኀ/ በከንቲባው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

3. የከተማው ሥራ አስኪያጅ በከተማው ምክር ቤት ስብሰባዎች ያለድምፅ መሳተፍ ይችላል፡፡

25.<u>ምክትል የከተማ ሥራ አስኪያጅ</u>

ተጠሪነቱ ለከተማው ሥራ አስኪያጅ ሆኖ ምክትል የከተማ ሥራ አስኪያጁ፣

1. የከተማው ሥራ አስኪያጅ በሌለበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶት ይሠራል፤
2. በከተማው ሥራ አስኪያጅ የሚሠጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

## ክፍል አምስት

## ሌሎች አስፈጻሚ አካላት

**26.የከተማው ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት**

1. የከተማውን አስተዳደር የሥልጠት፣ የክንዋኔ ብቃት፣ የሐብት አጠቃቀምና አስተዳደር በመቆጣጠር ለከተማው ምክር ቤት ሪፖርት የሚያቀርብ የዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ይኖራል።
2. የዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ሥራውን የሚያከናውነው በነፃነት ነው።
3. ዋናው ኦዲተር ቀጥሎ ካሉት ምክንያቶች ውጭ ያለፈቃዱ የጡረታ ዕድሜ ከመድረሱ በፊት ከሥራው አይነሣም፤

   ሀ/ የዲስፕሊን ጥፋት በመፈጸም ወይም በከባድ ችሎታ ማጣት ወይም ቅልጥፍና ማጣት፣

   ለ/ በሕመም ምክንያት ኃላፊነቱን ለመወጣት የማይችል መሆኑ ሲረጋገጥ፣ ወይም

   ሐ/ የከተማው አስተዳደር ምክር ቤት በአብላጫ ድምጽ ሲወስን።
4. የከተማው ዋና ኦዲተር የመሥሪያ ቤቱን በጀት በማዘጋጀት ለከተማው ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲጸድቅም በጀቱን ያስተዳዳራል።

**27.የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን**

1. በዋነኛነት ለፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን እና በውክልና ለከተማው አስተዳደር ተጠሪ የሆነ የከተማው ፖሊስ፣

   ሀ/ በፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ መሠረት በሚወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ መሠረት ይቋቋማል፣

   ለ/ ዕቅድና በጀቱን በማዘጋጀት ለከንቲባው ያቀርባል፣ በከተማ ምክር ቤት ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፣ ዓመታዊና ወቅታዊ የሥራ አፈፃፀም ሪፖርቶችን ለከንቲባው ያቀርባል፣ ሪፖርቶቹም በከተማው ካቢኔና ምክር ቤት ተመርምረው ውሣኔ ይሰጥባቸዋል።
2. የከተማው ፖሊስ ከሚሽነርና ምክትል ኮሚሽነር በፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ይሾማሉ።
3. የከተማውን ፖሊስ የዕለት ተዕለት ሥራ የመከታተል ኃላፊነት የከንቲባው ይሆናል።

**28.የአዲስ አበባ ከተማ ዐቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤት**

1. የከተማው ዐቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤት አግባብ ባለው ሕግ መሠረት በከተማው ፍርድ ቤቶች ሥልጣን ሥር የሚወድቁ የወንጀል ጉዳዮችን በተመለከተ ክስ ይመሰርታል፣ ይከራከራል አግባብነት ያላቸውን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።
2. የመሥሪያ ቤቱ አደረጃጀት በከተማው ምክር ቤት በሚወጣ ሕግ ይወስናል።

29.<u>የሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን</u>

የከተማው አስተዳደር በከተማው ምክር ቤት በሚወጣ ሕግ መሠረት የሚቋቋምና የሚሠራ የሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ይኖረዋል፡፡

## <u>ክፍል ስድስት</u>

## <u>ክፍለ ከተማና ቀበሌ</u>

30.<u>ስለ ክፍለ ከተማ</u>

1. ክፍለ ከተማዎች ባልተማከለ የሥልጣን ክፍፍል መርህ በተሰጠው የቦታ ክልል ማዘጋጃ ቤት በመሆንና ከከተማው ማዕከል ጋር በመቀናጀት ይሠራሉ፡፡ 2. ክፍለ ከተማ በሥሩ የሚገኙትን ቀበሌዎች ያስተዳድራል፡፡
3. ክፍለ ከተማዎች በአካባቢያቸው ሕግና ሥርዓት የማስከበር ኃላፊነት አለባቸው፡፡
4. የክፍለ ከተማ ምክር ቤት የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል፡፡

31.<u>ስለክፍለ ከተማና ቀበሌ ወሰን</u>

1. የክፍለ ከተማዎችና የቀበሌዎች ወሰን በዚህ ቻርተር አንቀጽ 5 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በከተማው ምክር ቤት ይወሰናል፡፡
2. የከተማው ምክር ቤት የነዋሪዎችን አስተያየት፣ አመቺ የአገልግሎት አቅርቦት፣ የከተማ ልማት ዕቅድና የሕዝብ ብዛት መሠረት በማድረግ አዲስ ክፍለ ከተማ ወይም ቀበሌ ሊያቋቁም ወይም ያለውን ክፍለ ከተማ ወይም ቀበሌ እንደገና ሊያዋቅር ይችላል፡፡

32.<u>የክፍለ ከተማ ምክር ቤት</u>

1. ተጠሪነቱ ለክፍለ ከተማው ነዋሪና ለከተማው ምክር ቤት ሆኖ የክፍለ ከተማው ምክር ቤት፣

   ሀ/ የክፍለ ከተማውን የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊ ልማት እና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት ዕቅድ ያፀድቃል፣

   ለ/ የምክር ቤቱን አፈ ጉባዔ፣ ምክትል አፈጉባዔ እና ፀሐፊ ከአባላቱ መካከል ይመርጣል፤

   ሐ/ የክፍለ ከተማውን ዋና ሥራ አስፈፃሚ እና ምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚ አብላጫ የምክር ቤት መቀመጫ ባለው የፖለቲካ ድርጅት አቅራቢነት ከአባላቱ መካከል ይመርጣል፤

   መ/ በክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቅራቢነት የክፍለ ከተማውን ቋሚ ኮሚቴ አባላትን ሹመት ያፀደቃል፣

   ሠ/ ከከተማው ምክር ቤት የሚመድብለትን በጀት ይደለድላል፤

   ረ/ የክፍለ ከተማውን ምክር ቤት ኮሚቴዎች ያቋቁማል፤

ሰ/ ከክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈፃሚ ዓመታዊና ወቅታዊ ሪፖርት ይቀበላል፤ መርምሮ ውሣኔይሰጣል፤

ሸ/ የክፍለ ከተማው ምክር ቤት ስለ አሰራሩ የሚወስን ውስጥ ደንብ ያወጣል፡፡

2. የከተማው ምክር ቤት የክፍለ ከተማው ምክር ቤት ውሣኔ ሕገ-ወጥ ወይም የክፍለ ከተማውን ነዋሪ ጥቅም የሚጐዳ አደገኛ መሆኑን ሲያምን የክፍለ ከተማውን ምክር ቤት ይበትናል፣ የመልሶ ማቋቋም የጊዜ ገደብና የዕለት ተዕለት የአስፈፃሚነት ሥራ እየተከከናወነ ስለሚቆይበት ሁኔታ ይወሰናል፣ ይህ በተመሳሳይ መልክ በቀበሌ ምክር ቤትም ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፤

33.<u>የክፍለ ከተማ ምክር ቤት አፈጉባዔ፣ ምክትል አፈጉባዔ እና ጸሐፊ</u>

የክፍለ ከተማ ምክር ቤት አፈጉባዔ፣ ምክትል አፈጉባዔ እና ፀሐፊ ሥልጣንና ተግባር በተመለከተ በዚህ ቻርተር አንቀጽ 18፣ 19 እና 20 የተደነገገው እንደየአግባቡ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

34.<u>ስለ ክፍለ ከተማ ዋና ሥራ አስፈፃሚ</u>

1. ተጠሪነቱ ለክፍለ ከተማው ምክር ቤት እና ለከንቲባው ሆኖ የክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈፃሚ ክፍለ ከተማውን ይመራል፤
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ዋና ሥራ አስፈፃሚው፣

ሀ/ የቋሚ ኮሚቴ አባላትን ከምክር ቤት አባላት ወይም የምክር ቤት አአባላት ካልሆኑት መካከል ለክፍለ ከተማው ምክር ቤት አቅርቦ ሹመታቸውን ያፀድቃል፣

ለ/ የክፍለ ከተማው ዓመታዊ እቅድና የበጀት ድልድል ሀሳብ በክፍለ ከተማው ቋሚ ኮሚቴ ከተመከረበት በኋላ ለክፍለ ከተማው ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፣

ሐ/ የክፍለ ከተማውን ቋሚ ኮሚቴ ይሰበስባል፤ ይመራል፣

መ/ በክፍለ ከተማው ህግና ሥርዓት ያስከብራል፣ ከክፍለ ከተማው አቅም በላይ የሆነ የፀጥታ ችግር ሲያጋጥም ለከንቲባው ያሳውቃል፣

ሠ/ ከክፍለ ከተማው ሥራ አስኪያጅ የሚቀርብለትን ሪፖርት ይቀበላል፣ መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፣

ረ/ የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አቅርቦት በክፍለ ከተማው ቋሚ ኮሚቴ እንዲገመገም ያደርጋል፤ ውጤቱን ለክፍለ ከተማው ምክር ቤት እና ለከንቲባው ሪፖርት ያደርጋል፣

ሰ/ በብሔራዊና የሕዝብ በዓላት ስነስርዓቶች ላይ ክፍለ ከተማውን ይወክላል፣

ሸ/ ዓመታዊና ወቅታዊ ሪፖርት ለከንቲባውና ለክፍለ ከተማው ምክር ቤት ያቀርባል፣

ቀ/ በክፍለ ከተማው ምክር ቤት እና በከንቲባው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

3. የዋና ሥራ አስፈጻሚው የሥራ ዘመን የክፍለ ከተማው የሥራ ዘመን ይሆናል፡፡ ሆኖም በራሱ ፈቃድ ወይም ጥፋት በመፈፀም ከምክር ቤቱ የሥራ ዘመኑ ከማለቁ በፊት በማንኛቸው ጊዜያት ከኃላፊነት ሊሰናበት ይችላል፡፡ ይህም ሁኔታ ለምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚው ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

35.<u>የክፍለ ከተማ ምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚ</u>

ተጠሪነቱ ለክፍለ ከተማው ዋና አስፈፃሚ ሆኖ የክፍለ ከተማው ምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚ፤

1. የክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈፃሚ በሌለበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶት ይሰራል፣
2. በዋና ሥራ አስፈፃሚው የሚሠጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

36.<u>የክፍለ ከተማ ቋሚ ኮሚቴ</u>

1. ተጠሪነቱ ለክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈፃሚ እና በጋራ ለሚወሰነው ውሣኔም ለክፍለ ከተማው ምክር ቤት ሆኖ የክፍለ ከተማው ቋሚ ኮሚቴ፣

ሀ/ በክፍለ ከተማው ዕቅድና የበጀት ድልድል ሀሳብ ላይ ይመከራል፣

ለ/ በክፍለ ከተማው ውስጥ ፖሊሲዎች፣ አዋጆች፣ ደንቦችና የከተማው የበላይ አካላት ውሣኔዎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

ሐ/ በክፍለ ከተማው ምክር ቤትና በክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈፃሚ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

2. የቋሚ ኮሚቴው የሥራ ዘመን የክፍለ ከተማው ምክር ቤት የሥራ ዘመን ይሆናል፡፡

37.<u>የክፍለ ከተማ ሥራ አስኪያጅ</u>

1. ተጠሪነቱ ለከተማው ሥራ አስኪያጅ እና ለክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈፃሚ ሆኖ የክፍለ ከተማው ሥራ አስኪያጅ የክፍለ ከተማው የማዘጋጃ ቤት አገልግሎቶች አስፈፃሚ በመሆን ይሠራል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ የክፍለ ከተማው ሥራ አስኪያጅ፣

ሀ/ ከከተማው ሥራ አስኪያጅ ጋር በመመካከር በክፍለ ከተማው ደረጃ ያሉ የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት እና የአገልግሎት መስጫ አማራጮች በሥራ ላይ እንዲውሉ ለክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈፃሚ ሀሳብ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

ለ/ የክፍለ ከተማውን የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት ሠራተኞች አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ያስተዳድራል፡፡

ሐ/ በሥሩ ከሚሰሩ አካላት ኃላፊዎች የተውጣጣና በከተማው ሥራ አስኪያጅ በሚወሠነው መሠረት የሚሠራ የሥራ አመራር ኮሚቴ ያቋቁማል፣ ይመራል፤ መ/ ስለሥራው አፈፃፀም ዓመታዊና ወቅታዊ ሪፖርት ለከተማው ሥራ አስኪያጅ እና ለክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈፃሚ ያቀርባል፤

ሠ/ ከከተማው ሥራ አስኪያጅ ጋር በመመካከር የክፍለ ከተማውን የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት ዕቅድ በማዘጋጀት ለክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈፃሚ ያቀርባል፤ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

ረ/ የማዘጋጃ ቤት አገልግሎትን የሚመለከቱ ውሳኔዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፤

ሰ/ የቀበሌ ሥራ አስኪያጆችን በተወሠነ ጊዜ የሥራ ውል የሙያ ብቃትን መሠረት በማድረግ ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፤ ያሰናብታል፤

ሸ/ ከከተማው ሥራ አስኪያጅና ከክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈፃሚ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

3. የክፍለ ከተማ ሥራ አስኪያጅ በክፍለ ከተማው ምክር ቤት ስብሰባዎች ያለድምፅ መሳተፍ ይችላል፡፡

**38.<u>የቀበሌ ሥልጣንና ተግባር</u>**

1. ቀበሌ የልማትና የህዝብ ቀጥተኛ ተሣትፎ ማዕከል በመሆንና በቀበሌ ደረጃ ሊሰጡ ለሚችሉ አገልግሎቶች ጣቢያ ሆኖ፣

ሀ/ የቀበሌ ምክር ቤት ተጠሪነቱ ለቀበሌው ነዋሪና ለክፍለ ከተማው ምክር ቤት ሆኖ በከተማው ምክር ቤት ተለይቶ የሚወሰን ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፤

ለ/ ነዋሪው በተቻለ መጠን አገልግሎት ባቅራቢያው የሚያገኝበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡

2. ቀበሌ ምክር ቤት፣ አፈጉባዔ፣ ፀሐፊ፣ ዋና ሥራ አስፈፃሚ፣ ቋሚ ኮሚቴ፣ ሥራ አስኪያጅ፣ ማሕበራዊ ፍ/ቤት እና የተለያዩ አስፈጻሚ አካላት ይኖሩታል፡፡ ሥልጣንና ተግባራቸው በከተማው ምክር ቤት በሚወጣ ህግ ይወሰናል፡፡

## ክፍል ሰባት

## የከተማው ፍርድ ቤቶችና የመዳኘት ሥልጣን የተሠጣቸው ሌሎች አካላት

**39.<u>ፍርድ ቤቶች</u>**

የከተማው አስተዳደር የሚከተሉት ፍርድ ቤቶች ይኖሩታል፣

1. የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች፣ እና

2. የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤቶች።

40.<u>የመዳኘት ሥልጣን ስለተሠጣቸው ሌሎች አካላት</u>

የከተማው አስተዳደር የመዳኘት ሥልጣን የተሠጣቸው የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል፣

1. የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ፤
2. የመንግሥት ሠራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤት፤
3. የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ፤ እና
4. የከተማ ቦታ ማስለቀቅ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ።

41.<u>የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን</u>

የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ የዳኝነት ሥልጣን ይኖራቸዋል፤

1. የፍትሐ ብሔር ዳኝነት ሥልጣን

ሀ/ የከተማውን መሪ ፕላን አፈጻጸም የሚመለከት የይዞታ ባለመብትነት፣ የፈቃድ አሰጣጥ ወይም የቦታ አጠቃቀምን በተመለከተ የሚነሱ ጉዳዮች፤

ለ/ ከከተማው አስተዳደር አስፈጻሚ አካላት የመቆጣጠር ሥልጣንና ተግባር ጋር በተያያዘ የሚነሱ ጉዳዮች፤

ሐ/ በዚህ ቻርተር አንቀጽ 52 በተመለከቱ የፋይናንስ ጉዳዮች ላይ የሚነሱ ክሶች፣

መ/ የከተማው አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት ወይም በከተማው አስተዳደር ባለቤትነት ሥር ያሉ ተቋማት የሚገቧቸውን አስተዳደራዊ ውሎች በተመለከተ የሚነሱ ጉዳዮች፤

ሠ/ በከተማው አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት ወይም በሥሩ ባሉ ተቋማት መካከል የሚነሱ ክርክሮች፤

ረ/ የከተማው አስተዳደር ከሚያስተዳድራቸው የመንግሥት ቤቶች ጋር በተያያዘ የሚነሱ ጉዳዮች፤

ሰ/ የስም ለውጥ አቤቱታ፤

ሸ/ የወራሽነት፣ የባልና ሚስትነት፣ የሞግዚትነት እና የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚቀርብ አቤቱታ፡[9]

ቀ/ የመጥፋትና የሞት ውሳኔ አቤቱታ።

2. የወንጀል/የደንብ መተላለፍ ዳኝነት ሥልጣን

ሀ/ በዚህ ቻርተር አንቀጽ 52 በተመለከቱ የፋይናንስ ጉዳዮች ላይ የሚነሱ የወንጀል ጉዳዮች፤

ለ/ የደንብ መተላለፍ ጉዳዮች፤

ሐ/ በፌዴራል ወንጀሎች ላይ የፌዴራል ፍ/ቤቶች ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በ1954 ዓ/ም የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 33፣ 35፣ 53 እና 59 መሠረት የሚቀርቡ ጉዳዮቹን መርምሮ ትዕዛዝ መስጠት፤[10]

መ/ ሌሎች የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በከተማው አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት የሚጣሉ የደንብ መተላለፍ ቅጣቶችን የማስፈፀም ጉዳዮች።

42.<u>የዳኝነት ሥልጣን ግጭትና ሰበር</u>

1. በአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣንና በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን መካከል የሥልጣን ግጭት ሲያጋጥም በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ ያገኛል።
2. የአዲስ አበባ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይግባኝ አይቶ የመጨረሻ ውሳኔ በሰጣቸው ጉዳዮች መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት የሚል ወገን ወደዚሁ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ጉዳዮችን ሊያቀርብ ይችላል።
3. በአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች የመጨረሻ ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለው የሚል ወገን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር አቤቱታ ማቅረብ ይችላል።

43.<u>የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች አደረጃጀትና አሠራር</u>

1. የከተማው ፍርድ ቤቶች የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች እና ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ይኖራቸዋል።
2. የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በከተማው ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን ሥር በሚወድቁ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል።
3. የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እና የመዳኘት ሥልጣን በተሰጣቸው ሌሎች አካላት የተወሰኑ ጉዳዮችን በይግባኝ ያያል።
4. የከተማ ፍርድ ቤቶች ሥራቸውን የሚያካሂዱት አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት ይሆናል።
5. በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል።
6. የከተማ ፍርድ ቤቶች አደረጃጀት የከተማው ምክር ቤት በሚያወጣው ሕግ ይወሰናል።

44.<u>የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ</u>

1. የከተማ ፍርድ ቤቶችን የዳኝነት ሥራ አካሄድ የሚመራ የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ በከተማው ምክር ቤት ይቋቋማል፣ ዝርዝሩ በከተማው ምክር ቤት በሚወጣ ሕግ ይወሰናል።
2. በጉባዔው ውስጥ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ተወካይ ይኖራል።

45.<u>የዳኞች ሹመትና የሥራ ዘመን</u>

1. የከተማው የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ በአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች የሚሾሙ ዕጩ ዳኞች ዝርዝር ለከተማው ምክር ቤት ከማቅረቡ በፊት የፌዴራል የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ በዕጩዎች ላይ ያለውን አስተያየት መጠየቅና ይህንኑ አስተያየት ከራሱ አስተያየት ጋር በማያያዝ በከንቲባው አማካይነት ለከተማው ምክር ቤት የማቅረብ ኃላፊነት አለበት። የፌዴራሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ አስተያየቱን በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ካላቀረበ የዕጩዎቹ ዝርዝር ለሹመት ለከተማው ምክር ቤት ይቀርባል።
2. ዳኞች ከዚህ በታች በተመለከቱት ሁኔታዎች ካልሆነ በስተቀር ከፈቃዳቸው ውጭ ከዳኝነት ሥራ አይነሱም፤
   ሀ/ የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ዳኛው የዲስፒሊን ደንቦችን በመጣሱ ወይም የሙያ ብቃትና ጥራት በማጓደሉ ምክንያት ከሥራ እንዲሰናበት ሲወሰን፣ ወይም
   ለ/ በሕመም ምክንያት ዳኛው ሥራውን መቀጠል እንደማይችል ሲወሰን፣ እና
   ሐ/ የከተማው ምክር ቤት ከግማሽ በላይ በሆነ ድምፅ የዳኞች አስተዳደር ጉባዔውን ውሣኔ ሲያፀድቀው።

**46.<u>የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ</u>**

የከተማው አስተዳደር የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ የዳኝነት ሥልጣን፣ አደረጃጀትና አሠራር በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 42/1985[11] (እንደተሻሻለ) በተደነገገው መሠረት ይሆናል።

**47.<u>የመንግሥት ሠራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤት</u>**

1. የከተማው አስተዳደር የመንግሥት ሠራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤት በመንግሥት ሠራተኞች ሕግ መሠረት የሚቀርቡለትን የአስተዳደሩን ሠራተኞች ጉዳይ በይግባኝ የማየት ሥልጣን አለው።
2. የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ አደረጃጀትና አሠራር በከተማው ምክር ቤት በሚወጣ ሕግ ይወሰናል።

**48.<u>የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ</u>**

1. የከተማው የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ በከተማው አስተዳደር የሚሰበሰቡ ግብሮችና ቀረጦችን በተመለከተ የሚቀርበለትን ይግባኝ የማየት ሥልጣን ይኖረዋል።
2. የጉባዔው አደራጃጀትና አሰራር በግብር ህጎች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በከተማው ምክር ቤት በሚወጣ ሕግ ይወሰናል።

**49.<u>የከተማ ቦታ ማስለቀቅ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ</u>**

1. የአዲስ አበባ ከተማ የቦታ ማስለቀቀ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ የከተማ ቦታ ስለመያዝ እንደገና ለመደንገግ በወጣው አዋጅ ቁጥር 272/1994 መሠረት ይሠራል።
2. የጉባዔው አደረጃጀትና አሠራር በከተማው ምክር ቤት በሚወጣ ሕግ ይወሰናል።

**50.<u>የቀበሌ ማኅበራዊ ፍርድ ቤቶች</u>**

1. የቀበሌ ማኅበራዊ ፍርድ ቤቶች ግምታቸው ከብር 5000(አምስት ሺህ) ያልበለጡ የንብረትና የገንዘብ ክርክሮችን የማየት ሥልጣን ይኖራቸዋል።
2. የቀበሌ ማኅበራዊ ፍርድ ቤቶች የከተማውን የሃይጂንና የጤና አጠባበቅ ደንብ እና ሌሎችም ተመሳሳይ የደንብ መተላለፍ ጉዳዮች ለማየት የሚኖራቸው ሥልጣን በከተማው ምክር ቤት በሚወጣ ሕግ ይወሰናል።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የቀበሌ ማኅበራዊ ፍርድ ቤቶች በሚሰጡአቸው ውሳኔዎች ቅሬታ ያለው ወገን ለከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሊያቀርብ ይችላል። በዚህ ፍርድ ቤት የሚሰጠው ውስኔ የመጨረሻ ይሆናል።
4. የቀበሌ ማኅበራዊ ፍርድ ቤቶች የሚሰጡአቸው ውሳኔዎች መሠረታዊ የሕግ ስህተት ካለባቸው ለከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አቤቱታ ሊቀርብባቸው ይችላል። የከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል።[13]
5. የቀበሌ ማኅበራዊ ፍርድ ቤቶች አደረጃጀትና አሠራር በከተማው ምክር ቤት በሚወጣ ሕግ ይወሰናል።

## ክፍል ስምንት

## ስለ በጀት እና ፋይናንስ

**51.የበጀት ዓመት**

የከተማው አስተዳደር የበጀት ዓመት የፌዴራሉ መንግሥት የበጀት ዓመት ይሆናል።

**52.የፋይናንስ ሥልጣን**

የከተማው አስተዳደር የሚከተለው የፋይናንስ ሥልጣን ይኖረዋል፣

1. የኦሮሚያ ክልልን፣ የፌዴራል መንግሥትንና የፌዴራል መንግሥት የልማት ድርጅቶች ተቀጣሪዎችን ሳይጨምር በከተማው ክልል ውስጥ በመቀጠር በሚገኝ ገቢ ላይ የሥራ ግብር በሕግ መሠረት ይወሰናል፣ ይሰበሰባል፤
2. በከተማው ውስጥ የመሬት መጠቀሚያ ክፍያ ይወስናል፤ ይሰበሰባል፤
3. በከተማው ውስጥ የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር ይጥላል፤ይሰበስባል፤
4. በከተማው በሚገኙ ግለሰብ ነጋዴዎች ላይ የንግድ ትርፍ ግብር የኤክሳይዝና የተርንኦቨር ታክስ በሕግ መሠረት ይወሰናል፣ ይሰበሰባል፤
5. በከተማው ከሚኖሩ ግለሰብ ነጋዴዎች እና በከተማው ባለቤትነት ሥር ከሚገኙ የልማት ድርጅቶች የተጨማሪ እሴት ታክስ በፌዴራል መንግሥት ተሰብስቦ ለከተማው አስተዳደር ይሰጣል፤
6. በከተማው ውስጥ የከተማ ቦታ ኪራይና የቤት ግብር ይወሰናል፤ ይሰበስባል፤
7. በከተማው ውስጥ ከተከራዩ ቤቶችና ሌሎች ንብረቶች ኪራይ በሚገኝ ገቢ ላይ የገቢ ግብር በሕግ መሠረት ይወሰናል፤ ይሰበሰባል፤

8. በከተማ ከሚፈፀሙ ውሎችና ስምምነቶች እንዲሁም ከንብረት ባለቤትነት ስም ምዝገባ ላይ የቴምብር ቀረጥ በሕግ መሠረት ይወሰናል፤ ይሰበሰባል፤
9. በከተማ አስተዳደር ባለቤትነት ሥር በሚገኙ የልማት ድርጅቶች ላይ የንግድ ትርፍ ግብር፣ የኤክሳይዝ እና የተርን ኦቨር ታክስ በህግ መሰረት ይወስናል፤
10. የከተማውን መንገዶች ከሚጠቀሙ ተሽከርካሪዎች የመንገድ መጠቀሚያ ክፍያ ይወሰናል፣ ይሰበሰባል፤
11. በከተማው አስተዳደር ባለቤትነት ሥር በሚገኙ የመንግሥት ቤቶችና ሌሎች ንብረቶች ላይ ኪራይ ይወሰናል፣ ይሰበሰባል፤
12. በከተማው ውስጥ በሚካሄዱ አነስተኛ የማዕድን ሥራዎች ላይ የማዕድን ገቢ ግብር፣ የሮያሊቲና የመሬት ኪራይ ክፍያዎችን በሕግ መሠረት ይወሰናል፣ ይሰበሰባል፤
13. በከተማ ውስጥ የደን መጠቀሚያ ሮያሊቲ ክፍያ በሕግ መሠረት ይወስናል፣ ይሰበሰባል፤
14. በከተማ አስተዳደር ከሚሰጡ ፈቃዶችና አገልግሎቶች የሚመነጩ ክፍያዎችን ይወሰናል፣ ይሰበሰባል፤
15. የከተማ ነክ ታክሶች፣ ቀረጦችንና የአገልግሎት ክፍያዎችን ይጥላል፣ ይሰበሰባል፤ 16. በከተማ ውስጥ የፈጠራ መብትን በማከራየት በሚገኝ ጥቅም ላይ የገቢ ግብር በሕግ መሠረት ይወሰናል፣ ይሰበሰባል፤
17. በከተማው ውስጥ በሚገኝ ንብረት የካፒታል ዋጋ ዕድገት ጥቅም ግብር በሕግ መሠረት ይወሰናል፣ ይሰበሰባል።

53. ገቢ ማስገኛ

የከተማው አስተዳደር፣

1. በሕግ እስካልተከለከለ ድረስ ከተማው ከሚያንቀሳቅሰው ወይም ከልዩ ፈቃድ የገቢ ማግኛ ተግባራት በማከናወን፣ ከጋራ ኢንቨስትመንት፣ ከፈንድ ኢንቨስትመንት፣ ከኪራይና ከለጋሾች ገንዘብ በማሰባሰብ ለከተማው ገቢ ያስገኛል፤
2. ክፍያ በሚያስገኙ ልዩ ልዩ ተግባራት ውል በመዋዋል መሳተፍ ይችላል።

54. ብድር

1. የከተማው አስተዳደር የፌዴራል መንግሥት በሚፈቅደው መሠረት ከሀገር ውስጥ ምንጮች በአጭርና በረጅም ጊዜ ክፍያ ቀጥታ ብድር ወይም የዋስትና ሰነዶችን በመሸጥ ሊበደር ይችላል።
2. ብድሩ የሀገሪቱ አጠቃላይ ኢኮኖሚ መረጋጋትንና የከተማው አስተዳደር በየወቅቱና በቋሚነት ተግባርና ግዴታዎቹን ለማሟላት የሚያስፈልገውን የገንዘብ አቅም የማይጎዳ መሆኑን ግምት ውስጥ ያስገባ መሆን ይኖርበታል።

3. የከተማው አስተዳደር ከዓለም አቀፍ የገንዘብ ምንጭ ብድር የሚያገኝበትን ሁኔታ በማጥናት የፌዴራሉ መንግሥት እንዲበደርለት ይጠይቃል፡፡

4. ክፍለ ከተሞችና ቀበሌዎች መበደር አይችሉም፡፡

5. በመንግሥትና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች፣ በከተማው አስተዳደር፣ በክፍለ ከተማዎችና ቀበሌዎች ተሳታፊነት የከተማው አስተዳደር የቁጠባና ልማት ባንክ በሕግ መሠረት ሊያቋቁም ይችላል፡፡ የባንኩ አሠራር እንደሌሎች መደበኛ ባንኮች ይሆናል፡፡

55.**<u>የከተማው አስተዳደር ከፌዴራል መንግሥት ስለሚያገኘው የፋይናንስ ድጋፍ</u>**

1. የከተማው አስተዳደር ኃላፊነቱን በአግባቡ ለመወጣት ይችል ዘንድ እንደአስፈላጊነቱ የአሰቸኳይ ጊዜ የማቋቋሚያና የልማት እርዳታ በፌዴራል መንግሥቱ ሊሰጠው ይችላል፡፡ እንዲሁም ልማታዊ ጠቀሜታቸው ሀገር አቀፍ እንደምታ ላላቸው ፕሮግራሞች የሚያስፈልገውን ወጪ የፌዴራል መንግሥቱ ሊያግዘው ይችላል፡፡

2. በፌዴራል መንግሥት የሚሰጠውን የገንዘብ ድጋፍና ብድር በተመለከተ የፌዴራል መንግሥት በቀጥታ ኦዲት ለማድረግና ገንዘቡ በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን ለመቆጣጠር ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

56.**<u>በጎ አድራጎት</u>**

የከተማው አስተዳደር ባለአደራና የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን ማቋቋም እና ሌሎች በሕግ መሠረት እንዲያቋቁሙ መፍቀድ ይችላል፡፡

57.**<u>ያልተማከለ የፋይናንስ ሥርዓት</u>**

1. የክፍለ ከተማዎች የገቢ ክፍፍል ሥርዓት ተወዳዳሪነትንና ውጤታማነትን የሚያበረታታ እንዲሁም ፍትሃዊነትን መሠረት ባደረገ ቀመር እንዲከናወን ይደረጋል፡፡

2. ክፍለ ከተማዎች ከከተማው ለተወሰነ ልዩ ሥራ የተመደበና የበጀት ድጎማ ይሰጣቸዋል፡፡ ከድጎማ በጀቱ የተወሰነው በሥራቸው ለተዋቀሩት አስፈፃሚ አካላትና ለቀበሌዎች ይከፋፈላል፡፡ ክፍፍሉም የአገልግሎት አቅርቦትና በልማት ወደኋላ የቀሩ ቀበሌዎችን ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል፡፡

3. የከተማው ምክር ቤት በልዩ ሁኔታ እንዲበረታቱ ለሚፈልጋቸው ፕሮጀክቶች ወጪ መሸፈኛ ለክፍለ ከተማዎችና ቀበሌዎች ከቀመር ውጪ ድጎማ ሊሰጥ ይችላል፡፡

4. የከተማው የልማት ድርጅቶች መነሻ ካፒታል ይመድብላቸዋል፡፡

5. ከከተማው ገቢዎች መካከል በክፍለ ከተማ ተሰብስበው በጥቅም ላይ የሚውሉት በከተማው ምክር ቤት ይወስናሉ፡፡

58.**<u>የፋይናንስ አስተዳደር</u>**

1. የከተማው የፋይናንስ አስተዳደር ተቀባይነት ባላቸው የሂሣብ አያያዝ ስርዓቶች፣ የሀገሪቱ የፋይናንስ ህግና የከተማው ምክር ቤት ይህንኑ አስመልክቶ በሚያወጣው ሕግ መሠረት ይከናወናል።
2. የከተማው አስተዳደር የከተማ ሀብት መጠበቁንና በህግ መሠረት በሥራ ላይ መዋሉን የሚያረጋግጥ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ይኖረዋል።
3. ከንቲባው ወቅታዊና አመታዊ የፋይናንስ ሪፖርት ለከተማው ምክር ቤት ያቀርባል። የክፍለ ከተማ ዋና ሥራ አስፈፃሚዎች በተመሳሳይ መልኩ ለክፍለ ከተማ ምክር ቤቶች ሪፖርት ያቀርባሉ።
4. የከተማው አስተዳደር እና ክፍለ ከተማዎች የተሟላ ኦርጅናል ገንዘብ ነክ ሰነዶች እንዲሁም ትክክለኛና የተሟላ የሂሣብ መዝገብ ይይዛሉ።
5. ማንኛውም የተሰበሰበ ገንዘብ በፋይናንስ ህግ በተፈቀደው መሠረት በባንክ ሂሣብ ውስጥ ይቀመጣል።
6. የከተማው አስተዳደርና ክፍለ ከተማዎች በስማቸው የሚከፈት የባንክ ሂሣብ ይኖራቸዋል።
7. የከተማው አስተዳደር በህግ መሠረት የግብር፣ የወለድና የመቀጫ ምሕረት የማድረግ እንዲሁም ዕዳን የመሠረዝ ሥልጣን ይኖረዋል።

59.<u>የበጀት ዝግጅትና አስተዳደር</u>

1. የከተማው የበጀት አስተዳደር የፌዴራል መንግሥቱን የበጀት መርህ የተከተለ ይሆናል።
2. የከተማው በጀት በግልጽና ነዋሪውን በሚያሳትፍ መልኩ ይዘጋጃል። የበጀት ጥያቄው ከመጽደቁ በፊት ባለበጀት መሥሪያ ቤቶችንና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት አስተያየታቸውን ይሰጡበታል፣ የመገናኛ ብዙሃንን በመጠቀም ነዋሪው እንዲሳተፍ ይደረጋል። በበጀት ላይ የሚደረጉ የምክር ቤቱ ስብሰባዎች ለነዋሪው ክፍት ይሆናሉ። በአዳዲስ የስራ ፕሮግራሞች፣ የካፒታል ወጪዎችና ገቢዎች ላይ የሚደረጉ ውይይቶች ነዋሪው እንዲያውቃቸው ይደረጋሉ።
3. የከተማው ምክር ቤት መጠባበቂያ በጀት ይመድባል። ከንቲባው የከተማውን ካቢኔ በማሳወቅ መጠባበቂያውን ለተፈላጊው ሥራ መድቦ በአግባቡ በሥራ ላይ ያውላል፣ ለከተማ ምክር ቤትም ያሳውቃል።

60.<u>የከተማው የልማት ድርጅቶች</u>

1. የከተማው የልማት ድርጅቶች በቦርድ ይመራሉ።
2. የከተማው የልማት ድርጅቶች አግባብ ባለው ህግ መሠረት የሚተዳደሩ ተቋማት ናቸው።
3. ከንቲባው የቦርድ ሰብሳቢዎችንና አባላትን የከተማው ሥራ አስኪያጅ ከሚያቀርባቸው ዕጩዎች መካከል ይሰይማል። የቦርዱ ተጠሪነትም ለከተማው ሥራ አስኪያጅ ይሆናል።

4. የልማት ድርጅቶች ለከተማው ሥራ አስኪያጅ ሪፖርት ያቀርባሉ፡፡

## ክፍል ዘጠኝ

## መስተዳድራዊ ግንኙነት

### 61.የከተማው አስተዳደርና የፌዴራል መንግሥት ግንኙነት

1. የከተማው አስተዳደር ከፌዴራል መንግሥቱ ጋር የሚኖረው ግንኙነት የፌዴራሉን መንግሥት ኃላፊነት ያገናዘበ መሆን አለበት፡፡
2. የከተማው አስተዳደር የፌዴራል መንግሥት አካል ነው፡፡ ፀጥታን፣ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነትን፣ የፌዴራል መንግሥት ፖሊሲዎችን፣ ሕጐችንና የሥራ ደረጃዎችን በተመለከተ ለፌዴራሉ መንግሥት ተጠሪ ነው፡፡
3. የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚወስነው መሠረት ሕገ መንግሥቱን አደጋ ላይ የሚጥል ተግባር በከተማው ምክር ቤት ሲፈፀም ወይም የከተማው አስተዳደር ፀጥታንና ድንገተኛ ሁኔታን መቆጣጠር ሲያቅተው የፌዴራል መንግሥት የከተማውን አስተዳደር የማፍረስና የሽግግር አስተዳደር የማቋቋም ሥልጣን አለው፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ሲወሠን የፌዴራል መንግሥት በሥልጣን ላይ ያለውን አስተዳደር ያሰናብታል፣ ለከተማው የሽግግር አስተዳደር ያደራጃል፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩም በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በተቀመጠው የጊዜ ገደብና ውሣኔ መሠረት ተግባራዊ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡
5. የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር የፌዴራል መንግሥትን በመወከል የከተማውን አስተዳደር ሥራ ይከታተላል፣ የከተማውን አቅም ግንባታ ሥራ ይደግፋል፡፡ 6. የከተማው አስተዳደር ዕቅዱን፣ በጀቱንና የከተማውንአጠቃላይ ሁኔታ በተመለከተ ለፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር አመታዊና ወቅታዊ የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት ያቀርባል፡፡
7. በከተማው ውስጥ የሚገኙት የፌዴራል መንግሥት አካላት የከተማውን አዋጆችና ደንቦች የማክበር ግዴታ አለባቸው፡፡
8. ከተማውን የሚመለከቱ በፌዴራል ተቋማት የሚካሄዱ አገልግሎቶች ከከተማው አስተዳደር ጋር በቅንጅትና በስምምነት ይፈፀማሉ፡፡

### 62.የከተማው አስተዳደርና የኦሮሚያ ክልል ግንኙነት

1. የከተማው አስተዳደር ከኦሮሚያ ክልል ጋር ፍሬያማ ትብብርን መሠረት ያደረገ ግንኙነት ይኖረዋል፡፡
2. በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥት አንቀፅ 49(5) መሠረት የኦሮሚያ ክልል ልዩ ጥቅም የተጠበቀ ነው፡፡ ዝርዝሩ በከተማው አስተዳደርና በኦሮሚያ ክልል መካከል በሚደረግ ስምምነት ወይም በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚወጣ ሕግ ይወስናል፡፡

### 63.ከሌሎች ከተሞችና ክልሎች ጋር ስለሚኖር ግንኙነት

1. የከተማው አስተዳደር ከሀገሪቱ ክልሎችና ከተሞች እንዲሁም ከውጭ ሀገር ከተሞች ጋር ግንኙነት መፍጠር ይችላል፤
2. በአገር ውስጥ የከተማው አስተዳደር ከሌሎች ከተሞችና ክልሎች ጋር የነዋሪዎችን ጥቅም ለማስጠበቅ በፖሊሲዎች፣ በመሠረተ ልማትና በአገልግሎት አቅርቦት የልምድ ልውውጥ እና ትብብር ለማድረግ ይችላል፤
3. ከሀገር ውጭ ከሚገኙ እህት ከተሞች ጋር ግንኙነት ለመመስረት ይችላል፣ በተለይም የኢኮኖሚና የቴክኒክ ትብብር፣ የባህል ልውውጥ፣ የበጐ ፈቃድ አገልግሎት፣ የዕቃዎች ልውውጥ፣ ሥልጠና፣ የቱሪዝምና የኢንቨስትመንት ዕድሎችን ማስተዋወቅ የሚያካትት ሊሆን ይችላል፡፡

## ክፍል አሥር

## ልዩ ልዩ ጉዳዮች

### 64.የሙከራ ሥራ

የከተማው አስተዳደር ከሥልጣንና ተግባሩ ጋር በተያያዘ የሙከራ ሥራዎችን እንዲያካሂድ በከተማው ምክር ቤት ሊፈቀድለት ይችላል፡፡ የሙከራ ስራው ክንዋኔና ግምገማ ምክር ቤቱ በሚወስነው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ይካሄዳል፡፡

### 65.ቻርተሩን ስለማሻሻል

የቻርተሩ ማሻሻያ ሃሣብ በከተማው በምክር ቤት ወይም አግባብ ባለው የፌዴራል መንግስት አካል ሊቀርብ ይችላል፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የቻርተሩን የማሻሻያ ሃሣብ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት አቅርቦ ተቀባይነት ሲያገኝ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውሣኔ እንዲያገኝ ያደርጋል፡፡

### 66.የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

1. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የከተማው ጊዜያዊ አስተዳደር እንደተቋቋመ ይህ ቻርተር ከመፅናቱ በፊት በየደረጃው ተቋቁመው የነበሩት ምክር ቤቶችና የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴዎች ይበተናሉ፡፡
2. እስከ ተከታዩ የምክር ቤት ምርጫ የሚቆይ ጊዜያዊ የከተማ አስተዳደር በጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሰየማል፣ ሥራውንም ይረከባል፡፡ ጊዜያዊ አስተዳደሩ በዚህ ቻርተር ለከተማው ምክር ቤት እና ለከተማው ካቢኔ የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡ የጊዜያዊ አስተዳደሩ ከንቲባም በዚህ ቻርተር ለከንቲባው የተሰጠ ሙሉ ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፡፡
3. ጊዜያዊ አስተዳደሩ፣

ሀ/ የክፍለ ከተማና የቀበሌ ጊዜያዊ አስተዳደሮችን ይሰይማል፤

ለ/ የክፍለ ከተማና የቀበሌ አከላለልን በዚህ ቻርተር መሠረት ተግባራዊ ያደርጋል፤

ሐ/ የከተማውን አስተዳደር መሥሪያ ቤቶች እንደገና ያደራጃል፣ ሠራተኞችን በሚያጸድቀው መዋቅር መሠረት እንደገና ይመድባል፣ ይቀጥራል፣ ያሰናብታል፣

መ/ ለሽግግሩ ወቅት በልማት፣ በዲሞክራሲ ግንባታና በአገልግሎት አቅርቦት የነዋሪው የተደራጀ ተሣትፎ ለማጐልበትና የህዝቡን ጥቅም የሚያስጠብቁ ውሣኔዎች ለመወሠን እንዲቻል ከነዋሪዎችና ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የተወከሉ ሠዎች የሚሣተፉበት አማካሪ ምክር ቤቶች በከተማው፣ በክፍለ ከተማ እና በቀበሌ ደረጃ ሊያቋቁም ይችላል፣ ዝርዝሩም በጊዜያዊ አስተዳደር ይወሰናል፡፡

4. ጊዜያዊ አስተዳደሩ በሥራ ላይ ያሉትን የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ይመድባል፣ ያሰለጥናል፣ እንዳስፈላጊነቱ ለማሰናበት ይችላል፡፡ ጊዜያዊ አስተዳደሩ የአመራረ አባላቱን በሹመትና በዝውውር ይመድባል፣ ሲያስፈልግም ያሰናብታል፡፡
5. የጊዜያዊ አስተዳደሩ በሚያጸድቀው መዋቅር መሠረት የከተማው አስተዳደር አካላት ወይም ተቋማት በሕግ መሠረት በሌላ አካላት ሲተኩ ወይም ሲዋሃዱ መብትና ግዴታቸው ለሚቋቋሙት አካላት ወይም ተቋማት ይተላለፋሉ ወይም እንደአግባቡ በጊዜያዊ አስተዳደሩ ይወሰናል፡፡
6. የከተማው ጊዚያዊ አስተዳደር ለሽግግሩ ወቅት የሚያገለግል፤

   ሀ/ የመንግስት ሰራተኞች አስተዳደር ሕግ ያወጣል፣ በመሆኑም የፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች ሕጎች ለሽግግር ወቅት በከተማው አስተዳደር ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፤

   ለ/ የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 42/1985 (እንደተሻሻለ) ተፈፃሚ የሚሆንበትን ዝርዝር ሁኔታ የሚወስን የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ደንብ ያወጣል፡፡
7. የከተማው አስተዳደር እስካልተካቸው ድረስ በዚህ ቻርተር ውስጥ የተገለጹትን የማይቃረኑ በሥራ ላይ የነበሩ አዋጆች፣ ደንቦች፣ ውሳኔዎች፣ ትዕዛዞችና መመሪያዎች ተፈፃሚነት ይቀጥላል፡፡
8. በፌዴራል ፍርድ ቤቶች በመታየት ላይ ያሉና በዚህ ቻርተር መሰረት በከተማው ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን ስር የሚወድቁ ጉዳዮች በፌዴራል ፍርድ ቤቶች መታየታቸው ይቀጥላል፡፡
9. አሁን በስራ ላይ ያሉት የከተማ ነክ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እና ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት እንዲሁም የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤቶች በዚህ ቻርተር አንቀፅ 41 እና 50 ለመለከቱት ፍርድ ቤቶች የተሰጡት የዳኝነት ስልጣን ይኖራቸዋል፡፡
10. በአዲስ አበባ ከተማ ነክ ጉዳዮች ፍ/ቤት በመታየት ላይ የነበሩና በአዋጅ ቁጥር 361/1995 በከተማው ፍ/ቤት የዳኝነት ሥልጣን ሥር የማይወድቁ ጉዳዮች በአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤት መታየታቸው ይቀጥላል፡፡

67. <u>የተሻሩ ህጐች</u>

1. የሕግ አወጣጡን ሥነ ሥርዓት ባልተከተለ አኳኋን የይዘት ለውጥ ተደርጎበት የታተመ በመሆኑ፣ የተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ 311/1995 ተሰርዞ በዚህ ቻርተር ተተክቷል፡፡
2. ከዚህ ቻርተር ጋር የሚቃረን ሕግ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ ቻርተር በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

68. <u>ቻርተሩ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ቻርተር ከጥር 15 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሐምሌ 17 ቀን 1995 ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

## የተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ፬፻፷/፲፱፻፺፯
## አጭር መግለጫ

**ማውጫ**

1. አጭር ርዕስ

2.ማሻሻያ

3.አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

**አጭር መግለጫ**

የተሸሻለውን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር ለማሻሻል እና ከወቅቱ ነባራዊ ሁኔታ ጋር አብሮ እንዲሄድ ለማስቻል የወጣ ህግ ነው፡፡

## <u>የተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ፩፻፷/፲፱፻፺፯</u>

የተሸሻለውን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር ማሻሻል በማስፈለጉ ፣

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግስት አንቀፅ ፶፭/፩ መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

<u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ የተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር ፩፻፷/፲፱፻፺፯_ተብሎ ሊፀቀስ ይችላል፡፡

<u>ማሻሻያ</u>

የተሸሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ እንደሚከተለው እንደገና ተሸሽሏል፡፡

፩. የአዋጁ አንቀፅ ፵፩ንዑስ አንቀፅ ፩ (ሸ) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ ፩ (ሸ) ተተክቷል፡፡

ሸ. የወራሽነት ፣ የባልና ሚስት ፣ የሞግዚትነት እና የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚቀርብ አቤቱታ፡፡

፪ የአዋጁ አንቀፅ ፵፩ ንዑስ አንቀፅ፩(ሐ) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ ፪(ሐ) ተተክቷል፡፡

ሐ. በፌደራል ወንጀሎች ላይ የፌደራል ፍ/ቤቶች ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ ፣በ፲፱፻፺፩ዓ.ም የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርአት ቁጥር ፴፫፣ ፴፭፣ ፺፫መሰረት የሚቀርቡ ጉዳዮችን መርምሮ ትዕዛዝ መስጠት፡፡

፫. በአዋጁ አንቀፅ ፶፯ ስር የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ (፶) ተጨምሯል፡፡

፲. በአዲስ አበባ ከተማ ነክ ጉዳዮች ፍ/ቤት በመታየት ላይ የነበሩና በአዋጅ ቁጥር ፺፻፲፩/ ፲፱፻፺፫ በከተማው ፍ/ቤት የዳኝነት ሥልጣን ስር የማይወድቁ ጉዳዮች በአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤት መታየታቸው ይቀጥላል፡፡

**<u>፫. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ ከሰኔ ፲ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሰኔ ፲ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፕሬዚዳንት

## <u>የተሻሻለውን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ፩ሺ፺፬/፪ሺ፲</u>

የተሻሻለው የኢትዮጵያ ምርጫ ህግ አዋጅ ቁጥር ፭፻፴/፲፱፻፺፱ (እንደተሻሻለ) አንቀጽ ፳፰ (፩) ላይ ጠቅላላ ምርጫ በየአምስት ዓመቱ የሚፈጸም መሆኑን የሚደነግግ በመሆኑ፤

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፰ ላይም ምርጫን አስመልክቶ በከተማ አስተዳደሩ የሚከናወኑ ምርጫዎች በሀገሪቱ የምርጫ ሕግ መሠረት እንደሚከናወኑ የሚደነግግ በመሆኑ፤

የአዲስ አበባ ምክር ቤት የሥራ ዘመኑ ሰኔ ፴ ቀን ፪ሺ፲ ዓ/ም የሚጠናቀቅ ሲሆን በደጋሚ ካልተመረጠ ወይም የሕግ ማሻሻያ ካልተደረገ በስተቀር የቀጣይ ሥራ ለመሥራት ሥልጣን ስለማይኖረው ምርጫ እስከሚከናወን ድረስ ሥራውን እንዲቀጥል የሕግ ማሻሻያ ማድረግ በማስፈለጉ፤

ምርጫ ተከናውኖ ምክር ቤት እስከሚደራጅ ድረስ አሁን ያለው ምክር ቤትና ስራ አስፈፃሚ ሥራውን ይዞ እንዲቀጥል ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በምክትል ከንቲባነት መስተዳድሩን ለመምራት ብቃት ያለውን ሰው ከምክር ቤቱ አባላት ወይም ከምክር ቤቱ ውጪ ለመሼም ዕድል የሚሰጥ ድንጋጌ ማካተት በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፵፱/፪/ እና አንቀጽ ፶፭ (፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ የተሻሻለው "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፺፩/፪ሺ፲" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## ፪. <u>ማሻሻያ</u>

የተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ (እንደተሻሻለ) እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

፩/ የአዋጁ አንቀጽ ፲፬ ንዑስ አንቀጽ (፪) ፊደል ተራ (ረ) ተተክቷል፤

"(ረ) የከተማውን ከንቲባ ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ይመርጣል፤"

፪/ የአዋጁ አንቀጽ ፲፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እንደሚከተለው ተሻሽሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) ተጨምሯል፡-

"፩/ የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል፤ ሆኖም ግን ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ገጥሞ በአምስት ዓመት መጠናቀቂያ ወቅት

ምርጫ ማካሄድ ያልተቻለ እንደሆነ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርቦ የምርጫ ጊዜው ሊራዘም ይችላል፡፡ ምክር ቤቱ መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባ ይኖረዋል፤ መደበኛ ስብሰባው በየሁለት ወሩ ይሆናል፡፡”

“፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የምርጫ ጊዜ እንዲራዘም የወሰነ እንደሆነ ቀጣይ ምርጫ ተደርጐ በምርጫው መሠረት አዲስ አስተዳደር እስኪደራጅ ድረስ በሥራ ላይ ያለው ምክር ቤትና አጠቃላይ የከተማ አስተዳደሩ በነበረበት ይቀጥላል፡፡”

“፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን የተራዘመ እንደሆነ፤ በሥራ ላይ በሚገኙ በሕግ የተቋቋሙ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግሥት አካላት ምርጫ እስከሚካሔድ ድረስ ተግባርና ኃላፊነታቸውን መወጣት ይቀጥላሉ፡፡”

፫/ የአዋጁ አንቀጽ ፳፪ ንዑስ አንቀጽ (፫) እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-

“፫/ ምክትል ከንቲባ ከምክር ቤት አባላት ውስጥ ወይም ከምክር ቤቱ አባላት ውጪ የሚሾም ሆኖ የሥራ ዘመኑ የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን ይሆናል፡፡ ሆኖም በራሱ ፈቃድ ሲለቅ፣ በምክር ቤቱ ከኃላፊነት ሲታገድ የሥራ ዘመኑ ሳያልቅ ከኃላፊነት ሊሰናበት ይችላል፤ ዝርዝሩ በምክር ቤቱ መተዳደሪያ ደንብ ይወሰናል፡፡

## ፫. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከፀደቀበት ከሰኔ ፴ ቀን ፪ሺ፲ ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ነሐሴ ፲ ቀን ፪ሺ፲**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

## የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኘሬዚዳንት

## ማረሚያ ቁጥር ፲፫/፪ሺ፲

የኢትዮጵያ ጂኦ-ስፖሺያል ኢንፎርሜሽን ኤጀንሲ እንደገና ማቋቋም አዋጅ ፲ሺ፹፱/፪ሺ፲ አንቀጽ ፲፪ (፩) “የኤጀንሲውን የተሟላና ትክክለኛ የሂሳብ …”የተባላው የኤጀንሲውን የተሟላና ትክክለኛ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል” ተብሎ ይነበብ፡፡

## የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የከተማ ነክ ጉዳዮች ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ ደንብ ፩/፲፱፻፺
## አጭር መግለጫ

ማውጫ

፩.አጭር ርዕስ

፪. ስለመቋቋም

ክፍል ሁለት

የፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣንና የሚመሩባቸው ሥነ ሰረዓርቶች

፫ የዳኝነት ሥልጣን

፬. የሰበር ሰሚነት ሥልጣን

፲፯. በቂ ምክንያት ሳይኖር የሚቀርብ ማመልከቻ ስለሚያስከትለው ቅጣት

፲፰.ስለውሳኔ አሰጣጥ

ክፍል አራት

ስለፍርድ ቤቶቹ ፕሬዚዳንቶች

፲፱. የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ሥልጣንና ተግባር

፳. የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዳንት ሥልጣንና ተግባር

፭. ፍርድ ቤቶቹ የሚመሩባቸው ሥነ ሥርዓቶች

ክፍል ሦስት

የፍርድ ቤቶች አደረጃጀትና የዳኝነት ሥራ አካሄድ

፮.ፍርድ ቤቶቹ የሚኖሩዋቸው ዳኞችና ሠራተኞች

፯. ችሎት

፰. በግልጽ ችሎት ማስቻል

፱. ዳኝነት ነፃነት

፲. አስተያየት ስለመቀበል

፲፩.የሰበር አቤቱታ አቀራረብ ሥነ-ሥርዓት

፲፪. የፍርድ ቤቶች የሥራ ቋንቋ

፲፫. የማስቻያ ሥፍራ

የዳኞች ከችሎት መነሳት

፲፭. ዳኛ ከችሎት እንዲነሳ ስለማመልከት

ማመልከቻ ስለሚያስከትለው ኪሳራ

፳፩. ,የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ሥልጣንና ተግባር

ክፍል አምስት

ስለመስተዳድሩ ፍርድ ቤቶች ጉባኤ

፳፪. የመስተዳድሩ ፍርድ ቤቶች ጉባኤ

፳፫. የጉባኤ አባላት

፳፬. የጉባኤው ሥልጣንና ተግባር

፳፭.የጉባኤው አሠራር

፳፮.ጉባኤውን ስለመጥራት

፳፯.ስለጉባኤው ውሣኔዎና መመሪያዎች

፳፰. ተፈጻሚነት ስለሌላቸው ሕጎች

፳፱. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

<u>አጭር መግለጫ</u>

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማ ነክ ጉዳዮችን የሚዳኙ ፍርድ ቤቶችን ለማቋቋምና አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባርና አሰራራቸውን በሕግ ለመደንገፊግ የወጣ ደንብ ነው፡፡

## <u>የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የከተማ ነክ ጉዳዮች ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ ደንብ ፩/፲፱፻፺</u>

የአዲስ አበባ ከተማ ራሱን በራሱ ለማስተዳደር እንዲችል በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት ሙሉ ስልጣን የተሰጠው በመሆኑ፡

በዚህ መሰረትም የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የዳኝነት ሥልጣን እንደሚኖረው በደኢስ አበባ ከተማ መስተዳድር ማቋቋሚያ ቻርተር አዋጅ በግልጽ የተደነገገ በመሆኑ እና መስተዳድሩ ከሚኖሩት ፍርድ ቤቶች መካከል የከተማ ነክ ጉዳዮችን የሚዳኙ ፍርድ ቤቶችን ለማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፡

የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳርን ለማቋቋም በወጣው ቻርተር አዋጃ ቁጥር ፹፯/፲፱፹፱ አንቀጽ ፸፩ መሰረት የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ምክር ቤት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

**፩፥<u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ ደንብ የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የከተማ ነክ ጉዳዮች ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ተብሎ ሊጠቀሱ ይችላል፡፡

## ፪. ስለመቋቋም

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ከዚህ በኋላ ‹‹ፍርድ ቤቶች›› ተብለው እንደአስፈላጊነቱ በጥቅል የሚጠቀሱ የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የከተማ ነክ ጉዳዮች ፍርድ ቤቶች በዚህ ደንብ ተቋቁመዋል፡፡

፩. የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የከተማ ነክ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ከዚህ በኋላ ‹‹ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት›› ተብሎ የሚጠቀስ እና

፪. የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የከተማ ነክ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከዚህ በኋላ ‹‹የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት›› ተብሎ የሚጠቀስ፡፡

## ክፍል ሁለት

## የፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣንና የሚመሩባቸው ሥነ ሥረዓርቶች

## ፫ የዳኝነት ሥልጣን

፩. የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዮችን በመጀመሪያ ደረጃ አይቶ ዳኝነት ይሰጣል፡፡

፪. ይግባኝ ሰሚ ፍርደ ቤት በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዳኝነት ላይ ይግባኝ ሲቀርበለት የይግባኝ ዳኝነት ይሰጣል፡፡

## ፬. የሰበር ሰሚነት ሥልጣን

በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት መደበኛ ችሎት የተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያበት ሆ ሲገኝ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በሰበር የማየት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

## ፭. ፍርድ ቤቶቹ የሚመሩባቸው ሥነ ሥርዓቶች

ፍርድ ቤቶች፡

፩. በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግና በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሥነ ሥርዓት ይመራሉ፡፡

፪. ሆኖም አስፈላፊ በሚሆንበት ጊዜ የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ምክር ቤት በሚወጣው ደንብ በሚደነገጉ የሥነ ሥርዓት ህጎች ይመራል፡፧

## ክፍል ሦስት

## የፍርድ ቤቶች አደረጃጀትና የዳኝነት ሥራ አካሄድ

## ፮.ፍርድ ቤቶቹ የሚኖሩዋቸው ዳኞችና ሠራተኞች

፩. ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አንድ ፕሬዚዳንት አንድ ምክትል ፕሬዚዳንትና ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ዳኞች ይኖሩታል፡፡

፪. የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አንድ ፕሬዚዳንትና ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ዳኞ ይኖሩታል፡፡

፫. ማናቸውም ፍርድ ቤት ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞ ይኖሩታል፡፡

፯ **ችሎት**

፩. ማናቸውም ፍርድ ቤት እንደ አስፈላጊነቱ አንድ ወይም ከአንድ በላይ ችሎቶች ይኖሩታል፡፡

፪. በእያንዳንዱ ችሎት አንድ ሰ ብሳቢና ሁለት ዳኞች ሆነው ያስችላሉ፡፡ ሆኖም በተለይ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ አንድ ዳኛ ብቻ እንዲያስችል በችሎ ሊሰይም ይችላል፡፡

፫. የፍርድ ቤቱ ፕሬዚዳንት ወይም ምክትል ፕሬዚዳንት የፍርድ ቤቶቻቸው ችሎቶች ሰብሳቢ ሆነው ሊሰየሙ ይችላሉ፡፡

**፰. በግልጽ ችሎት ማስቻል**

ፍርድ ቤቶች በግልጽ ችሎት ያስችላሉ፡፡ ሆኖም ከህዝብ ደህንነትና ከሞራል አንጻር አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በዝግ ችሎት ይችላሉ፡፡

**፱. ዳኝነት ነፃነት**

ዳኞች የዳኝነት ተግባራቸውን በሙሉ ነፃነት ያከናውናሉ፡፡ ከሕግ በስተቀር ለማንኛውም ሌላ ሥልጣን ተገዢ አይሆኑም፡፡

**፲.አስተያየት ስለመቀበል**

፩. በክርክር ላይ ያለ ጉዳይ የሚመለታቸው የመንግስት መስሪያ ቤቶች ጉዳዩ ከህዝብ ጠቃሚታ አንጻር ያውን ተጽእኖ በሚመለከት አስተያየትና ዝርዝር ትንታኔ ለፍርድ ቤቶች ማቅረብ ይችላሉ፡፡

፪. ፍርድ ቤቶች የሚቀርብላቸውን አስተያየትና ትንታኔ ለጉዳዩ አወሳሰን አንደ አንድ ማስረጃ አድርገው መቀበል ይኖርባቸዋል፡፡ አለበቂ ማፍረሻና ማብራሪያ የቀረበላቸውን አስተያየትና ትንታኔ ውድቅ ማድረግ አይችሉም፡፡

፫. በዚህ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ፍርድ ቤቶች በተሰጠው አስተያየትና ትንታኔ ብቻ ተመሥርተው ውሳኔ እንዲሰጡ አይገደዱም።

**፲፩የሰበር አቤቱታ አቀራረብ ሥነ-ሥርዓት**

፩. ጉዳዩ በሰበር እንዲታይለት የሚፈልግ አቤቱታ አቅራቢ ውሳኔው መሰረታዊ የህግ ስህተት አለው የሚልበትን ምክንያት በማመልከቻ ላይ በዝርዝር ጽፎ ለይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ማቅብ አለበት።

፪. አቤት ባዩ ከማመልከቻ በተጨማሪ አቤቱታ የተቀረበበትን የመጨረሻ ውሳኔ ቅጅ ማቅረብ አለበት።

፫. በሰበር የሚሰማው አስቀድሞ ሶስት የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ዳኞች የተሰየሙበት ችሎት ውሳኔ ለሰበር የሚበቃ መሰረታዊ የህግ ስህተት የሚጠቁም ሁኔታ አለበት ብሎ ሲወስን ነው፡፡ ስለሆነም የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት በንዑስ አንቀጽ እንደተመለከተው የሰብር አቤቱታ ሲቀርብለት ጉዳዩን ላልወሰኑ ሦስት ዳኞች መምራት አለበት፡፡

፬. የሰበር ጥያቄ ማመልከቻ ለይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት መቅረብ የሚገባው የሰበር ጥያቄ በሚቀርብበት ጉዳይ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ በተሰጠው በዘጠና (90) ቀን ውስጥ ይሆናል፡፡

፭. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሰረት የቀረበው አቤቱታ በሰበር እንዲታይ ሲወሰን አቤቱታ የቀረበበትን ውሳኔ የሰጡት ዳኞች የማይኖሩበት የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ዳኞች በሙሉ በሚሰየሙበት የሰብር ችሎት ይታያል፡፡

፮. ችሎቱ ለውሳኔ አሰጣጥ በሚያመች ሁኔታ በኢ ተጋማሽ ቁጥር ሊሰይም ይችላል፡፡

## ፲፪. የፍርድ ቤቶች የሥራ ቋንቋ

፩. የፍርድ ቤቶች የሥራ ቋንቋ አማርኛ ነው፡፡

፪.የአማርኛ ቋንቋ ለማይችል ባለጉዳይ አስተርጓሚ ይመደብለታል፡፡

## ፲፫. የማስቻያ ሥፍራ

የፍርድ ቤቶች የማስቻያ ሥፍራ የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር አመቺ ነው ብሎ በሚመድበው ቦታ ይሆናል፡፡

## ፲፬. የዳኞች ከችሎት መነሳት

፩. ማንኛውም ዳኛ ከዚህ ቀጥሎ
በአንዱ ከችሎት ይነሳል፡-

ሀ) ዳኛው ከተከራካሪዎቹ ከአንደኛው ወገን ወይም ከጠበቃው ጋር የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ያለው እንደሆነ፡

ለ) ዳኛ ከተከራካሪዎቹ የአንደኛው ወገን ሞግዚት ወይም ነገረፈጅ በሆነበት ጉዳይ ላይ የተነሳ ክርክር የሆነ እንደሆነ፡

ሐ) ዳኛው ክርክር የተነሳበትን ጉዳይ አስቀድሞ በዳኝነት ወይም በእርቅ መንገድ ያየው ወይም የሚያውቀው ሆኖ የተገኘ እንደሆነ፡

መ) ዳኛው ከተከራካሪዎቹ ከአንደኛው ወይም ከጠበቃው ጋር በፍርድ ቤት የተያዘ ክርክር ወይም ሙግት ያለው እንደሆነ እና

ሠ) ከዚህ በላይ ከ(ሀ) እስከ (መ) ከተመለከቱት ምክንያቶች ውጭ ትክክለኛ ፍትሕ አይሰጠም የሚያሰኝ ሌላ በቂ ምክንያት ሲኖር፡፡

፪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት ዳኛው በችሎ ሊቀመጥ የማይገባው መሆኑን ሲያውቅ ወዲያውኑ ከችሎት ተነስቶ ሌላ ዳኛ እንዲተካ ማድረግ አለበት፡፡

፲፭. <u>ዳኛ ከችሎት እንዲነሳ ስለማመልከት</u>

፩. ከተከራካዎቹ አንደኛው በአንቀጽ ፲፬ በተረዘሩት ምክንያቶች መሰረት አንድ ዳኛ ከችሎት መነሳት የሚገባው መስሎ የታየው እንደሆነ እንዲነሳለት ለፍርድ ቤቱ ማመልከቻ ማቅረብ ይችላል፡፡

፪. ማመልከቻ የሚቀርበው ክርክሩ ከመጀመሩ በፊት ወይም ማመልከቻ ለማቅረብ ምክንያት መኖሩን አመልካቹ እንዳወቀ ወዲውኑ መሆን አለበት፡፡

፫. አንድ ዳኛ ብቻውን የሚያስችል ከሆነ ከችሎ ስለመነሳት የሚቀርብለትን ማመልከቻ ተመልክቶ ጥያቄውን የተቀበለው እንደሆነ ከችሎ ይነሳል፡፡ ጥያቄውን ያልተቀበለው እንደሆን ግን በዚህ ፍርድ ቤት በሚገኝ ሌላ ችሎት፤ ሌላ ችሎት ከሌለ የዚህኑ ፍርድ ቤት ውሳኔ ይግባኝ በሚያየው ፍርድ ቤት እንዲወሰን ማመልከቻውን ማስተላለፍ አለበት፡፡

፬. ከችሎት እንዲነሳ ማመልከቻ የቀረበበት ዳኛ ከሌሎች ዳኞች ጋር በሚያስችልበት ጊዜ ከሆነ ማመልከቻ የቀረበበት ዳኛ በሌለበት በቀሩት ዳኞች ማመልከቻው ውሳኔ ያገኛል፡፡

፭. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ እና ፬ መሰረት የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻና ይግባኝ የማይባልበት ይሆናል፡፡

፮. የሚሰጠውን ማናቸውንም ውሳኔ ዳኛው ወዲያውኑ መፈጸም አለበት፡፡

፲፮. <u>ማመልከቻ ስለሚያስከትለው ኪሳራ</u>

ፍርድ ቤቱ ማመልከቻውን ተገቢ አይደለም በማለት ሳይቀበለው ከቀረ የዋናው ነገር ውጤት ሳይጠብቅ ኪሳራውን የሚከፍለው ማመልከቻውን ያቀረበው ሰው ይሆናል፡፡

፲፯. <u>በቂ ምክንያት ሳይኖር የሚቀርብ ማመልከቻስለሚያስከትለው ቅጣት</u>

ከተከራካሪዎቹ አንደኛው ወገን ዳኛው ከችሎት እንዲነሳለት ያቀረበው ማመልከቻ በቂ ምክንያት ሳይኖረው የቀረ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ማመልከቻውን ውድቅ አድርጎ በአመልካቹ ላይ ከብር ፫፻-፩ሺ (ከሶስት መቶ ብር እስከ አንድ ሺህ ብር) መቀጫ ሊጥልበት ይችላል፡፡

፲፰.<u>ስለውሳኔ አሰጣጥ</u>

፩. ዳኞች በውሳኔ አሰጣጥ ልዩነት ሲኖራቸው አብዛኛው ድምጽ የተሰጠው ውሳኔ የፍርድ ቤቱ ውሳኔ ይሆናል፡፡

፪. አነስተኛ ድምጽ አስተያየት በመዝገቡ መስፈር አለበት፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ስለፍርድ ቤቶቹ ፕሬዚዳንቶች</u>

፲፱. <u>የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ሥልጣንና ተግባር</u>

የይግባኝ በሰሚው ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት በህግ መሰረት ፍርድ ቤቶቹን በኃላፊነት ያስተዳድራል ይመራል በተለይም

፩. ፍርድ ቤቱን ይወክላል፡፡

፪. ለፍርድ ቤቶቹ አስፈላጊ የሆኑትን ሠራተኞ ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፡፡

፫. የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ዳኞችን ከምክትል ፕሬዚዳንቱ ጋር በመመካከር ይደለድላል፡ ሥራ ይሰጣል፡፡

፬. የፍርድ ቤቶችን የሥራ ዕቅድና በጀት አዘጋጅቶ ለመስተዳድሩ ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲጸድቅም ሥራ ላይ ያውላል፡፡

፭. ስለፍርድ ቤቶቹ ሥራ በእስታስቲክስ የተደገ መግለጫ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፡፡

፮.የዳኞችና የሌሎች ሠራተኞች ትምህርትና ሥልጠና የሚካሄድበት ሁኔታ ያመቻቻል፡፡

፯. ስለ ፍርድ ቤቶቹ የዳኝነት ስራ አካሄድ ለምክር ቤት ዘገባ ያቀርባል፡፡

፰. ትምህርታዊ የሆኑ የዓመቱ ፍረዶችና ውሳኔዎች ተመርጠው እንዲታተሙ ያደርጋል፡፡

፱. የፍርድ ቤቶቹ የህግ መጽሔት እንዲዘጋጅ ያደርጋል፡፡

፲. በዚህ ደንብና ሌሎች ህጎች የተሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

<u>የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዳንት ሥልጣንና ተግባር</u>

የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት፡

፩. በፕሬዚዳንቱ የሚመራለትን ሥራ ያከናውናል፡፡

፪. ፕሬዚዳንቱ በማይኖርበት ጊዜ ፕሬዚዳንቱን ተክቶ ይሠራል፡፡

፫. በዳኞች ድልድል ላይ ይሳተፋል፡፡

**<u>፩.የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ሥልጣንና ተግባር</u>**

የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት፡-

፩. የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት፡-
፪. ከይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንት ጋር በመመካከር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዳኞችን ይደለድላል፡፡
፫. ከይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በሚሰጠው መመሪያ መሰረት የፍርድ ቤቱን ሠራተኞች ያስተዳድራል፡፡
፬. ስለፍርድ ቤቱ በስታቲስቲክስ የተደገፈ መግለጫ እንዲዘጋጁ ያደርጋል፡፡
፭. የፍርድ ቤቱን ዕቅድና በጀት አዘጋጅቶ ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ያቀርባል፡ ሲፈቀድም ሥራ ላይ ያውላል፡፡
፮. ትምህርታዊ የሆኑ የየዓመቱ ፍርዶችና ውሳኔዎች ተመርጠው ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት እንዲላኩ ያደርጋል፡፡
፯. በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ፕሬዚዳትና ምክትል ፕሬዚዳንት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

፰. ስለሥራው እንቅስቃሴ በየጊዜው ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ሪፖርት ያቀርባል፡፡

## ክፍል አምስት
## ስለመስተዳድሩ ፍርድ ቤቶች ጉባኤ

**፪.የመስተዳድሩ ፍርድ ቤቶች ጉባኤ**

የመስተዳደሩ ፍርድ ቤቶች ጉባኤ ከዚህ በኃላ ‹‹ጉባኤ›› የተባለው የሚጠራ ይኖረዋል፡፡

**፫. የጉባኤ አባላት**

፩. የጉባኤው አባላት የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ምክትል ፕሬዚዳንት የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ዳኞች የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንትና ዳኞች በሙሉ ይሆናል፡፡

፪. በጉባኤው የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ዐቃቤ ህግ መስሪያ ቤት ኃላፊ እና ምክትል ኃላፊ አባል ይሆናሉ፡፡ ሆኖም ድምጽ የመስጠት መብት አይኖራቸውም፡፡

፫. አግባብ ያላቸው የመንግስት መስሪያ ቤቶችን ማህበራትን ድርጅቶንና ተቋማትን የሚወክሉ ሰዎች ወይም ሌሎች ግለሰቦች በጉባኤው እንዲሳተፉ ሊጋብዙ ይችላሉ፡፡ ሆኖም አስተያየት ከመስጠት በስተቀር ድምጽ የመስጠት መብት አይኖራቸውም፡፡

**፬.የጉባኤው ሥልጣንና ተግባር**

ጉባኤው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡፡

፩. በዳኝነት ሥራ አስተዳደር ረገድ ባጋጠሙ ችግሮች ላይ ተወያይቶ መፍትሔ ይሰጣል፡፡

፪. የፍርድ ቤቶችን የዳኝነት አሠራር ለማሻሻል የሚረዱ መመሪያዎችንና ውሳኔዎን ያሳልፋል፡፡

፫. አዳዲስ ሕጎች እንዲወጡ ወይም ነባር ህጎች እንዲሻሻሉ ኃሳብ ያቀርባል፡፡

፬. የዳኝነት ሥራ አካሄድን ለማቀላጠፍና ለማጠናከር የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

፭. ለጉባኤው ሥራ አፈጻጸም አስፈላጊውን መመሪያ ያወጣል፡፡

**፭.የጉባኤው አሠራር**

፩. የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት የጉባኤው ሰብሳቢ ይሆናል፡፡

፪. ጉባኤው የራሱን ፀሐፊ ይመድባል፡፡

፫. የጉባኤው አባላት በሙሉ በጉባኤው የመገኘት ግዴታ አለባቸው፡፡

፬. ከጉባኤው አባላት ሁለት ሦስተኛው ከተገኙ ምልዐተ ጉባኤው ይሆናል፡፡ ውሳኔው በድምጽ ይወክላልጫ ይሰጣል፡፡ ድምጽ እኩል ለእኩል በተከፈለ ጊዜ የጉባኤው ሰብሳቢ ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡

**፮.ጉባኤውን ስለመጥራት**

፩.ጉባኤው በዓመት ሁለት ጊዜ ይሰበሰባል፡፡

፪.ሆኖም የጉባኤው ሰብሳቢ ሲጠራ ወይም ከጉባኤው አባላት ከግማሽ በላይ ሲጠይቁ ጉባኤው በማንኛውም ጊዜ ይሰበሰባል፡፡

፮.ስለጉባኤው ውሣኔዎና መመሪያዎች

በጉባኤው የሚወጡት መመሪያዎችና የሚተላለፉት ውሳኔዎች በቀጣይ ጉባኤ እስካልተሻሩ ድረስ በፍርድ ቤቶች ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፯. ተፈጻሚነት ስለሌላቸው ሕጎች

፩. ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ደንብ ወይም መመሪያ ወይም አሠራር ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

፪. ይህን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ሕግ ተፈጻሚነት አይኖረውም

፱. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ ከሕዳር ፩ ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሕዳር ፩ ቀን

የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር

ምክር ቤት

## በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ምክር ቤት በወረዳ ምክር ቤትና በቀበሌ ምከር ቤት አባላት ላይ ህዝብ አመኔታ በሚያጣባቸው ጊዜ ስለሚወስደው እርምጃ የወጣ ደንብ ፬/፲፱፻፺ አጭር መግለጫ

ማውጫ

፩ አጭር ርዕስ፣

፪ ትርጓሜ፣

፫ መሰረታዊ መብቶች

፬ የህዝብ አመኔታ የሚለካበት ዘዴ፣

፭ የስነ-ምግባር መለኪያዎች

፮ ከምክር ቤት መወገድ የሚኖረው ውጤት፣

፯. መመሪያ ስለማውጣት

፱. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

አጭር መግለጫ

የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ በመረጠው የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ምክር ቤት አባል፣ የወረዳ ምክር ቤት አባል እና የቀበሌ ምክር ቤት አባል ላይ አመኔታ ባጣ ጊዜ በሕግ መሰረት ከምክርት ቤት አባልነት ለማስወገድ ስለሚወስደው እርምጃ በዝርዝር የሚደነግግ ሕግ ነው፡፡

## <u>በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ምክር ቤት በወረዳ ምክር ቤትና በቀበሌ ምከር ቤት አባላት ላይ ህዝብ አመኔታ በሚያጣባቸው ጊዜ ስለሚወስደው እርምጃ የወጣ ደንብ ፩/፲፱፻፺</u>

የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፹፯/፲፱፻፹፱ በአንቀጽ ፯/፯ በማናቸውም የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ምክር ቤት አባል፣ የወረዳ ምክር ቤት አባል እና የቀበሌ ምከር ቤት አባል ላይ መራጩ ህዝባ አመኔታ በሚያጣበት ጊዜ በሕግ መሰረት ከምክርት ቤት አባልነት ለማስወገድ እንደሚችል የሚደነግግ በመሆኑ፣

መራጩ ህዝብ በመረጠው የምከር ቤት አባል ላይ አመኔታ ባጣ ጊዜ ስለሚወስደው እርምጃ በሕግ በዝርዝር መደንገግ በማስፈለጉ፣

በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፹፯/፲፱፻፹፱ አንቀጽ ፯/፮/ በተሰጠው ስልጣን መሰረት የመስተዳድሩ ምክር ቤት ይህን ደንብ እንዲሚከተለው አውጥቷል፡፡

### <u>ክፍል አንድ</u>

### <u>ጠቅላላ</u>

፯ <u>አጭር ርዕስ፣</u>

ይህ ደንብ "በአዲስ አበባ መስተዳድር ምክር ቤት በወረዳ ምክር ቤትና በቀበሌ ምክር ቤት አባላት ላይ መራጩ ህዝብ አመኔታ በሚያጣባቸው ጊዜ ስለሚወስደው እርምጃ የወጣ የአዲስ አበባ መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩/፲፱፻፺፯ " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፰ <u>ትርጓሜ፣</u>

፩. በዚህ ደንብ ውስጥ "ተመራጭ" ወይም "ተወካይ" ማለት በኢትዮጵያ የምርጫ ቦርድ አስፈፃሚነት በተካሄደ ምርጫ የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ምክር ቤት ወይም የወረዳ ምከር ቤት ወይም የቀበሌ ምክር ቤት በመወከል የተመረጠና በምርጫ ቦርድ የምስክር ወረቀት የተሰጠው የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ምከርት ቤት ወይም የወረዳ ምክር ቤት ወይም የቀበሌ ምክር ቤት አባል ነው፡፡

፪. "የምርጫ ክልል" ማለት በምርጫ ሕግ መሰረት ለመስተዳድሩ ምክር ቤት ወይም ለወረዳ ምክር ቤት ወይም ለቀበሌ ምክር ቤት አባላት ምርጫ የተከለለ አካባቢ ነው፡፡

፫. "መራጭ" ማለት በምርጫ ሕግ መሰረት አስራ ስምንት ዓመት የሞላውና በምርጫ ክልሉ ከሁለት ዓመት በላይ የኖረ ሰው ነው፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>መብቶችና ግዴታዎች</u>

፱ <u>መሰረታዊ መብቶች</u>

፩. በማንኛውም የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ ሕግ በሚፈቅደው መሰረት ለአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ምክር ቤት፣ ለወረዳ ምክር ቤትና ለቀበሌ ምክር ቤት ተወካዩን የመምረጥ መብት አለው፡፡

፪. ማንኛውም የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ ከሌሎች መራጮች ጋር በመሆን መርጦ የወከለውን ተወካይ በየጊዜው መመርመር መገምገምና መመዘን ይችላል፡፡

፫. ማንኛውንም የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ መርጦ ለወከለው ተወካይ ሲሰጥ የነበረውን ድጋፍ የመሰረዝ፣የማቋረጥ ወይም የመቀጠል መብት አለው፡፡፡

፬. ማንኛውንም የህዝብ ተመራጭ በመራጮች የሚቀርብለትን ምስጋና፣ ተግሳፅ፣ ግምገማ ወይም ሂስ በግልፅና በአደባባይ የማስተጋባት ፣የመቃወምና ሂስ የማድረግ መብት አለው፡፡

**፩፲ የህዝብ አመኔታ የሚለካበት ዘዴ፣**

አንድ የህዝብ ተወካይ የህዝብ አመኔታ የለውም ሊባል የሚችለው፣

፩. የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ምክር ቤት አባል ከተወከለበት የምርጫ ክልል ከሚገኙ ከ፲፭ ሺ(ከአስራ አምስት ሺህ) በላይ መራጮች የምርጫ ቦርድ በሚያወጣው ደንብ መሰረት የይውረድልን ጥያቄ ለምርጫ ቦርድ ሲያቀርቡ፤

፪. የወረዳ ምክር ቤት አባል ከተወከለበት የምርጫ ክልል ከሚገኙ ከአንድ አራተኛ በላይ መራጮች የምርጫ ቦርድ በሚያወጧው ደንብ መሰረት ተወካዩ ተመልሶ እንዲጠራ ለምርጫ ቦርድ ጥያቄ ሲያቀርቡ፤

፫. የቀበሌ ምክር ቤት አባል ከተወከለበት የምርጫ ክልል ከሚገኙ ከአንድ አራተኛ በላይ መራጮች የምርጫ ቦርድ በሚያወጣው ደንብ መሰረት ተወካዩ ተመልሶ እንዲጠራ ለምርጫ ቦርድ ጥያቄ ሲያቀርቡ፤

፬. የመስተዳድሩ ምክር ቤት ተወካይ ከተወከለበት የምርጫ ክልል ከሚገኙ ከ፲ሺ(ከአስር ሺህ) በላይ መራጮች አሳሳቢነት የምርጫ ቦርድ በሚያወጣው ደንብ መሰረት የወረዳ ምክር ቤቶች በአብላጫ ድምጽ ተወካዩ ተመልሶ እንዲጠራ ውሳኔ ያሳለፉ እንደሆነ፤

፭. የመስተዳድሩ ምክር ቤት ወይም የወረዳ ምክር ቤት ወይም የቀበሌ ምክር ቤት ተወካይ በሚያሳየው ስነ ምግባር የወከለውን ህዝብ በብቃት ሊወክል አልቻለም ብሎ በሁለት ሶስተኛ ድምጽ ሲወስን ይሆናል፡፡

**፩፩ የስነ-ምግባር መለኪያዎች**

ማንኛውንም የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳዱር ምክር ቤት ወይም የወረዳ ምክር ቤት ወይም የቀበሌ ምክር ቤት አባል፤

፩. ተገኘነቱ ለህሊናው ጭምር በመሆኑ በማናቸውም ረገድ የፀዳና የጠራ መሆን አለበት፡፡

፪. የህዝብን ጉዳይ በሚወያይበት ጊዜ ሀቀኛና ግልጽ የመሆን ኃላፊነት አለበት፡፡

፫. የሀሰት ማስረጃዎች መፍጠር፣ መቅጠፍ፣ ያልተጣሩ ጉዳዮች ወደ ምክር ቤቱ መድረክ ማቅረብና መዋሸት የስነ ምግባር ብልሹነት ዋነኞቹ መግለጫዎች ናቸው፡፡

**፩፪ በስነ-ምግባር ይወክላል ሹነት ላይ የሚወሰዱ እርምጃዎች**

የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ምክር ቤት ወይም የወረዳ ምክር ቤት ወይም የቀበሌ ምክር ቤት፣

፩.በየእርከኑ ባሉ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴዎች አማካይነት በስነ ምግባር ብልሹነት የተከሰሰ ተወካይ ጉዳይ ተጣርቶ እንዲቀርብ ብለት ወይም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በሚያቋቁመው አጣሪ ኮሚቴ አማካይነት ጉዳዩ እንዲጣራ ያደርጋል።

፪. በየእርከኑ ያለ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ወይም የሚቋቋም አጣሪ ኮሚቴ በሚሰጠው የውሳኔ ሃሳብ መሰረት ተወያይቶ ይወስናል፡፡

፫. አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የሚከተሉትን እርምጃዎች መውሰድ ይችላል፡፡

ሀ/ የስነ ምግባር ብልሹነት ለተገኘበት አባል ለህዝብ ይፋ በሆነ መልኩ የማስጠንቀቂያ ተግሳፅ ቤቱ ሊሰጠው ይችላል፡፡

ለ/ የስነ-ምግባር ብልሹነት የተገኘበት አባል ለተወሰነ ጊዜ ከምክር ቤቱ እንዲታገድ ማድረግ ይችላል፡፡

ሐ/ የስነ-ምግባር ብልሹነት የተገኘበት አባል በዚህ ንዑስ አንቀጽ (ሀ) እና (ለ) የተደነገጉትን ቅጣቶች ከተቀበለ በኋላ የስነ-ምግባር ይወክላልሹነቱ የቀጠለ እንደሆነ ምክር ቤቱ በሁለት ሶስተኛ ድምጽ ከምክር ቤቱ አባልነቱ ሊሰርዘው ይችላል፡፡

፬. በንዑስ አንቀጽ ሶስት ከ ሀ-ሐ የተመለከቱት ተከታታይ የዲሲፕሊን እርምጃዎች እንደተወካዩ የጥፋት ክብደት ቅደም ተከተላቸው ሳይጠበቅ ተፈፃሚ ሊደረጉ ይችላሉ፡፡

፺. ከምክር ቤት መወገድ የሚኖረው ውጤት፣

፩. አንድ የምክር ቤት አባል በዚህ ደንብ አንቀጽ ፬ እና ፺ በተደነገገው መሰረት መቀመጫውን ሲያጣ በምርጫ ቦርድ የተሰጠው የተወካይነት መታወቂያ ሕጋዊነት ያከትማል፡፡

፪. ከላይ በንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የምክር ቤት መቀመጫውን ያጣ ተወካይ በሚመለከተው ምክር ቤት መቀመጫውን ለመሙላት በሚደረገው ምርጫ ተወዳዳሪ ለመሆን ይችላል፡፡

፫. ከላይ በንዑስ አንቀጽ ፪ የተጠቀሰው ምርጫ የሚከናወነው የመስተዳድሩ ምክር ቤት ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ከምርጫ ቦርድ ጋር በመመካከር መቀመጫው ከታጣበት ጊዜ ጀምሮ ለሦስት ወራት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሦስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፺፩. መመሪያ ስለማውጣት

የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድረ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይህን ደንብ ለማስፈጸም የሚረዳ መመሪያ ማውጣት ይችላል፡፡

፺፪. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ ከህዳር ፪ ቀን ፲፱፻፺ ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ህዳር ፪ ቀን ፲፱፻፺ ዓ.ም

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማ ፍርድ ቤቶች የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ አዋጅ ፩/፲፱፻፺፰ አጭር መግለጫ

ማውጫ


፩. አጭር ርዕስ

፪. ትርጓሜ

፪. የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ መቋቋም

፫. የጉባኤው አባላት

፬. የጉባኤው ሥልጣንና ተግባር

፭. ስለጉባኤው ስብሰባ

፮. በዳኝነት ለመመረጥ የሚያበቁ ሁኔታዎች

፯. የጉባኤው ሰብሳቢ ሥልጣንና ተግባር

፰. ስለ ዳኞች ከሥራ መሰናበት

፱.አቤቱታ ስለማቅረብ

፲. ስለቃለመሐላ

፲፩. ደንብና መመሪያዎች ስለማውጣት

፲፪. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ


<u>አጭር መግለጫ</u>

ይህ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማ ፍርድ ቤቶች የዳኞች አስተዳደር ማቋቋሚያ አዋጅ በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፲፩/፲፱፻፺፭ ዓ.ም አንቀጽ ፵፩ (፩) እና ፷፯ (፪) መሰረት የወጣ አዋጅ ነው፡፡አዋጁ ብቁ ዳኞች የሚሆኑ ሰዎችን በመምረጥ እንዲሾሙ ለማድረግና የከተማውን ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥራ አካሄድ በበላይነት ለመምራት

ሲባል የታወጀ ሲሆን ሥራውን እንዲለቅ የሚደረግ ዳኛ በከተማው ምክር ቤት ሁለት ሶስተኛ ድምጽ ውሳኔ ብቻ እንዲሆን በማድረግ የዳኞችን ነጻነት የሚያረጋግጥ ነው

## <u>የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፺፮ ዓ.ም</u>

የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች የከተማው የዳኝነት አካል ሆነው በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፲፩/፲፱፻፺፭ የተቋቋሙ በመሆኑ ፣

የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥራ አካሄድን በበላይነት የሚመራ የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ በማቋቋም የዳኝነት ነፃነትን በማረጋገጥ የዳኝነት አስተዳደርን ከማናቸውም አካል ወይም ባለስልጣን ተጽእኖ ነፃ በሆነ ሁኔታ እንዲመራ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፣

በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፲፩/፲፱፻፺፭ ዓ.ም አንቀጽ ፵፬(፩) እና ፷፮ (፪) በተደነገገው መሠረት የከተማው ጊዜያዊ አስተዳደር ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡

### <u>፩. አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማ ፍርድ ቤቶች የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፺፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### <u>፪ ትርጓሜ</u>

በዚህ አዋጅ ውስጥ፤

፩. "የዲሲኘሊን ጥፋት" ማለት በፍርድ ቤቱ የዲሲኘሊንና የሥነ ምግባር ደንብ የተመለከተው ጥፋት ነው፤

፪. "ጉልህ የሆነ የሥራ ችሎታና ቅልጥፍና ማነስ" ማለት በዲሲኘሊንና በሥነ ምግባር ደንብ የተመለከተውን መተላለፍ፣ ተፈላጊ የጥራትና የብዛት መለኪያ ያላሟላ ሆኖ የዳኝነት ሥራው ላይ ሙያው ከሚጠይቀው የትምህርትና የልምድ ችሎታ በታች በሆነ የሕግና የፍሬ ነገር ስህተት የሚፈጽምን ወይም ከሚገባው ጊዜ በላይ ጉዳዮች የሚያጓትትን ይጨምራል፤

፫. "ዳኛ" ማለት በአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች ውስጥ ተሹሞ የሚሠራ የፍርድ ባለስልጣን ነው፡፡

### <u>፪. የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ መቋቋም</u>

የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ከዚህ በኃላ "ጉባዔ" እየተባለ የሚጠራ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

### <u>፫. የጉባዔው አባላት</u>

፩. ጉባዔው የሚከተሉት አባለት ይኖሩታል፤

ሀ) የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ኘሬዚዳንት ……………………ሰብሳቢ፣

ለ) የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ምክትል ኘሬዚዳንት ………አባል፣

ሐ) በከተማው ምክር ቤት የሚወክሉ ሁለት አባላት ………………………አባላት፣

መ) የከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ኘሬዚዳንት ………………አባል፣

ሠ) በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የሚወከል አንድ ሰው ……………………..አባል፣ እና

ረ) በከተማው ፍርድ ቤት ዳኞች የሚመረጥ አንድ ዳኛ ……………………..አባል፡፡

፪. ጉባዔው የራሱ ፀሐፊ ይኖረዋል፡፡

፫. ሰብሳቢው በማይኖርበት ጊዜ የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ምክትል ኘሬዚዳንት ሰብሰባውን ተክቶ ይሠራል፡፡

**፬. የጉባዔው ሥልጣንና ተግባር**

ጉባዔው ከዚህ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

፩. ለዳኝነት ብቁ የሆኑ ዳኞችን በመምረጥ በከተማው ምክር ቤት እንዲሾሙ በፌዴራል የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ከሚሰጠው አስተያየት ጋር የራሱን አስተያየት በማከል ለከንቲባው ያቀርባል፣

፪. የከተማውን ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥራ አካሄድ በበላይነት ይመራል፣ ይከታተላል፤

፫. የፍርድ ቤቱን ዳኞች የሥነ ምግባርና የዲሲኘሊን ደንብ ያፀድቃል፤

፬. ስለዳኞች ዝውውር፣ ደመወዝ፣ አበል፣ ዕድገትና ምደባ በመንግሥት ፓሊሲ መሠረት ይወስናል፤ ስለዳኞች የሕክምናና ልሎች ማበረታቻዎች አፈፃፀም በማጥናት ለከንቲባው ያቀርባል፤

፭. ስለዳኞች ስንብትና የዲሲኘሊን ጥፋት የሚቀርቡለትን ጉዳዮች መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ውሣኔ እስኪሰጥ ድረስ ጉዳዩ የሚመለከተው ዳኛ ከሥራ ታግዶ እንዲቆይ ለማድረግ ይችላል ፡፡ ዝርዝሩ በጉባዔው በሚወጣ የዲሲኘሊን አፈፃፀም የሥነ ሥርዓት መመሪያ ይወስናል፡፡

**፭. ስለጉባዔው ስብሰባ**

፩. ጉባዔው በወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ይኖረዋል፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፡፡

፪. ከጉባዔው አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል ፡፡

፫. የጉባዔው ውሣኔዎች በድምጽ ይወክላልጫ ያልፋሉ ፡፡ ሆኖም ድምጽ እኩል ከተከፈለ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡

፬. የዲሲኘሊን ክስ የቀረበበት ማንኛውም የጉባዔ አባል የሆነ ዳኛ ጉዳዩ በሚታይበት ጊዜ ዳኛው በጉባዔው ስብሰባ በአባልነት መቀመጥ አይችልም፡፡

፭. በዚህ አንቀጽ የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው ጉባዔው የራሱን የስብሰባ መተዳደሪያ ደንብ ያወጣል፡፡

**፮. የጉባዔው ሰብሳቢ ሥልጣንና ተግባር**

የጉባዔው ሰብሳቢ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

፩. የጉባዔው ጽሕፈት ቤት በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤

፪. የጉባዔው ስብሰባ ይጠራል፤

፫. የጉባዔውን ስብሰባ በሊቀመንበርነት ይመራል፤

፬. የዕጩ ዳኞችን አጭር የትምህርት ዝግጅት እና የሥራ ልምድ መግለጫ በማዘጋጀት ለጉባዔው ያቀርባል፣ በጉባዔው የተመረጡትን ዕጩ ዳኞች ለሚመለከታቸው አካላት ያስተላልፋል፡፡

**፯. <u>በዳኝነት ለመመረጥ የሚያበቁ ሁኔታዎች</u>**

፩.በከተማው ፍርድ ቤቶች በዳኝነት ለመሾም የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው፤

ሀ) ለፌዴራል ሕገ መንግሥቱና ለከተማው ቻርተር ታማኝ የሆነ፣

ለ) በሕግ ትምህርት የሰለጠነ እና በቂ ተግባራዊ ልምምድ ያለው፣

ሐ) በታታሪነቱ፣ በፍትሐዊነቱና በሥነ ምግባሩ መልካም ስም ያተረፈ፣

መ) በዳኝነት ሥራ ለመሰማራት ፈቃደኛ የሆነ፣ እና

ሠ) ዕድሜ ከ ፳፭ ዓመት ያላነሰ ፡፡

፪. ማንኛውም ሰው በመንግሥት ሕግ አውጪ ወይም ሕግ አስፈፃሚ ውስጥ ወይም በማንኛውም የፓለቲካ ድርጅት በአባልነት በሚያገለግልበት ጊዜ አጣምሮ የዳኝነት ሥራ ሊሰራ አይችልም፡፡

<u>፰. ስለዳኞች ከሥራ መሰናበት</u>

፩. የከተማው ፍርድ ቤቶች ዳኛ ከሥራ የሚሰናበተው

ሀ) ሥራውን ለመልቀቅ ሲፈልግ የሁለት ወር የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት፤

ለ) በሕመም ምክንያት ተግባሩን በተገቢው ሁኔታ ማከናወን አይችልም ተብሎ ሲወሰን፤

ሐ) ጉልህ የሆነ የሥራ ችሎታና ቅልጥፍና አንሶታል ተብሎ ሲወሰን፤

መ) የዳኞች የዲሲኘሊንና የሥነ ምግባር ደንብ ተላልፎ የደዲኘሉን ጥፋት በመፈፀም ከሥራ እንዲሰናበት ሲወሰን፤ ወይም

ሠ) የጡረታ ዕድሜ ሲደርስ፤ ይሆናል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) (ለ) (ሐ) እና (መ) በተገለጹት ምክንያቶች የሚሰጥ የዳኛ ከሥራ መሰናበት ውሣኔ በከተማው ምክር ቤት ከግማሽ በላይ በሆነ ድምጽ መጽደቅ አለበት፡፡

**<u>፱. አቤቱታ ስለማቅረብ</u>**

ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት በጉባዔው የሚታይ አቤቱታ በዳኛ ላይ ለማቅረብ ይችላል ፡፡ ዝርዝር ሥነ ሥርዓቱ በጉባዔው በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፡፡

**<u>፲. ስለ ቃለመሐላ</u>**

ዳኞች ሥራቸውን ከመጀመራቸው በፊት የሚከተለውን መሐላ ይፈጽማሉ፡፡

"እኔ …………………… በዛሬው ዕለት የከተማው ፍርድ ቤት ዳኛ በመሆን ተሹሜ ሥራዬን ስጀምር በከተማው አስተዳደር ምክር ቤት የተጣለብኝን ከፍተኛ ኃላፊነት በታማኝነትና በቅንነት ለመፈፀም ቃል እገባለሁ፡፡"

***፲፩ ደንብና መመሪያዎች ስለማውጣት***

፩. የከተማው አስተዳደር ካቢኔ ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም አስፈላጊ የሆኑ ደንቦችን ማውጣት ይችላል፡፡

፪. ጉባዔው ለዚህ አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎች ማውጣት ይችላል፡፡

**፲፪. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ የካቲት ፳ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ

የካቲት ፳ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም.

የአዲስ አበባ ከተማ

ጊዜያዊ አስተዳደር

## የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች
## የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፺፫ ዓ.ም

የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች የከተማው የዳኝነት አካል ሆነው በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፲፩/፲፱፻፺፫ የተቋቋሙ በመሆኑ ፣

የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥራ አካሄድን በበላይነት የሚመራ የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ በማቋቋም የዳኝነት ነፃነትን በማረጋገጥ የዳኝነት አስተዳደርን ከማናቸውም አካል ወይም ባለስልጣን ተጽእኖ ነፃ በሆነ ሁኔታ እንዲመራ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፣

በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፲፩/፲፱፻፺፭ ዓ.ም አንቀጽ ፵፬(፩) እና ፳፮ (፪) በተደነገገው መሠረት የከተማው ጊዜያዊ አስተዳደር ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡

## <u>፩. አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማ ፍርድ ቤቶች የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፩/፲፱፻፺፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## ፪ <u>ትርጓሜ</u>

በዚህ አዋጅ ውስጥ፤

፩. "የዲሲፕሊን ጥፋት" ማለት በፍርድ ቤቱ የዲሲፕሊንና የሥነ ምግባር ደንብ የተመለከተው ጥፋት ነው፤

፪. "ጉልህ የሆነ የሥራ ችሎታና ቅልጥፍና ማነስ" ማለት በዲሲፕሊንና በሥነ ምግባር ደንብ የተመለከተውን መተላለፍ፣ ተፈላጊ የጥራትና የብዛት መለኪያ ያላሟላ ሆኖ የዳኝነት ሥራው ላይ ሙያው ከሚጠይቀው የትምህርትና የልምድ ችሎታ በታች በሆነ የሕግና የፍሬ ነገር ስህተት የሚፈጽምን ወይም ከሚገባው ጊዜ በላይ ጉዳዮች የሚያጓትትን ይጨምራል፤

፫. "ዳኛ" ማለት በአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች ውስጥ ተሹሞ የሚሠራ የፍርድ ባለስልጣን ነው፡፡

## ፪. <u>የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ መቋቋም</u>

የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ከዚህ በኃላ "ጉባዔ" እየተባለ የሚጠራ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

## ፫. <u>የጉባዔው አባላት</u>

፩. ጉባዔው የሚከተሉት አባለት ይኖሩታል፤

ሀ) የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ……………………ሰብሳቢ፣

ለ) የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዲዳንት ………አባል፣

ሐ) በከተማው ምክር ቤት የሚወክሉ ሁለት አባላት ………………………አባላት፣

መ) የከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ………………አባል፣

ሠ) በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የሚወከል አንድ ሰው ……………………አባል፣ እና

ረ) በከተማው ፍርድ ቤት ዳኞች የሚመረጥ አንድ ዳኛ ……………………አባል፡፡

፪. ጉባዔው የራሱ ፀሐፊ ይኖረዋል፡፡

፫. ሰብሳቢው በማይኖርበት ጊዜ የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት ሰብሰባውን ተክቶ ይሠራል፡፡

**፬. የጉባዔው ሥልጣንና ተግባር**

ጉባዔው ከዚህ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

፩. ለዳኝነት ብቁ የሆኑ ዳኞችን በመምረጥ በከተማው ምክር ቤት እንዲሾሙ በፌዴራል የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ከሚሰጠው አስተያየት ጋር የራሱን አስተያየት በማከል ለከንቲባው ያቀርባል፣

፪. የከተማውን ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥራ አካሄድ በበላይነት ይመራል፣ ይከታተላል፤

፫. የፍርድ ቤቱን ዳኞች የሥነ ምግባርና የዲሲፕሊን ደንብ ያፀድቃል፤

፬. ስለዳኞች ዝውውር፣ ደመወዝ፣ አበል፣ ዕድገትና ምደባ በመንግሥት ፓሊሲ መሠረት ይወስናል፤ ስለዳኞች የሕክምናና ልሎች ማበረታቻዎች አፈፃፀም በማጥናት ለከንቲባው ያቀርባል፤

፭. ስለዳኞች ስንብትና የዲሲፕሊን ጥፋት የሚቀርቡለትን ጉዳዮች መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ውሣኔ እስኪሰጥ ድረስ ጉዳዩ የሚመለከተው ዳኛ ከሥራ ታግዶ እንዲቆይ ለማድረግ ይችላል ፡፡ ዝርዝሩ በጉባዔው በሚወጣ የዲሲፕሊን አፈፃፀም የሥነ ሥርዓት መመሪያ ይወስናል፡፡

**፭. ስለጉባዔው ስብሰባ**

፩. ጉባዔው በወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ይኖረዋል፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፡፡

፪. ከጉባዔው አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል ፡፡

፫. የጉባዔው ውሣኔዎች በድምጽ ይወክላልጫ ያልፋሉ ፡፡ ሆኖም ድምጽ እኩል ከተከፈለ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡

፬. የዲሲፕሊን ክስ የቀረበበት ማንኛውም የጉባዔ አባል የሆነ ዳኛ ጉዳዩ በሚታይበት ጊዜ ዳኛው በጉባዔው ስብሰባ በአባልነት መቀመጥ አይችልም፡፡

፭. በዚህ አንቀጽ የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው ጉባዔው የራሱን የስብሰባ መተዳደሪያ ደንብ ያወጣል፡፡

**፮. የጉባዔው ሰብሳቢ ሥልጣንና ተግባር**

የጉባዔው ሰብሳቢ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

፩. የጉባዔው ጽሕፈት ቤት በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤

፪. የጉባዔው ስብሰባ ይጠራል፤

፫. የጉባዔውን ስብሰባ በሊቀመንበርነት ይመራል፤

፬. የዕጩ ዳኞችን አጭር የትምህርት ዝግጅት እና የሥራ ልምድ መግለጫ በማዘጋጀት ለጉባዔው ያቀርባል፣ በጉባዔው የተመረጡትን ዕጩ ዳኞች ለሚመለከታቸው አካላት ያስተላልፋል፡፡

**፮. <u>በዳኝነት ለመመረጥ የሚያበቁ ሁኔታዎች</u>**

፩.በከተማው ፍርድ ቤቶች በዳኝነት ለመሾም የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላት  አለባቸው፤

ሀ) ለፌዴራል ሕገ መንግሥቱና ለከተማው ቻርተር ታማኝ የሆነ፣

ለ) በሕግ ትምህርት የሰለጠነ እና በቂ ተግባራዊ ልምምድ ያለው፣

ሐ) በታታሪነቱ፣ በፍትሐዊነቱና በሥነ ምግባሩ መልካም ስም ያተረፈ፣

መ) በዳኝነት ሥራ ለመሰማራት ፈቃደኛ የሆነ፣ እና

ሠ) ዕድሜ ከ ፳፫ ዓመት ያላነሰ ፡፡

፪. ማንኛውም ሰው በመንግሥት ሕግ አውጪ ወይም ሕግ አስፈፃሚ ውስጥ ወይም በማንኛውም የፓለቲካ ድርጅት በአባልነት በሚያገለግልበት ጊዜ አጣምሮ የዳኝነት ሥራ ሊሰራ አይችልም፡፡

**፳. <u>ስለዳኞች ከሥራ መሰናበት</u>**

፩. የከተማው ፍርድ ቤቶች ዳኛ ከሥራ የሚሰናበተው

ሀ) ሥራውን ለመልቀቅ ሲፈልግ የሁለት ወር የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት፤

ለ) በሕመም ምክንያት ተግባሩን በተገቢው ሁኔታ ማከናወን አይችልም ተብሎ ሲወሰን፤

ሐ) ጉልህ የሆነ የሥራ ችሎታና ቅልጥፍና አንሶታል ተብሎ ሲወሰን፤

መ) የዳኞች የዲሲፕሊንና የሥነ ምግባር ደንብ ተላልፎ የደዲፕሉን ጥፋት በመፈፀም ከሥራ እንዲሰናበት ሲወሰን፤ ወይም

ሠ) የጡረታ ዕድሜ ሲደርስ፤ ይሆናል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) (ለ) (ሐ) እና (መ) በተገለጹት ምክንያቶች የሚሰጥ የዳኛ ከሥራ መሰናበት ውሣኔ በከተማው ምክር ቤት ከግማሽ በላይ በሆነ ድምጽ መጽደቅ አለበት፡፡

**፱. <u>አቤቱታ ስለማቅረብ</u>**

ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት በጉባዔው የሚታይ አቤቱታ በዳኛ ላይ ለማቅረብ ይችላል ፡፡ ዝርዝር ሥነ ሥርዓቱ በጉባዔው በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፡፡

**፲. <u>ስለ ቃለመሐላ</u>**

ዳኞች ሥራቸውን ከመጀመራቸው በፊት የሚከተለውን መሐላ ይፈጽማሉ፡፡

"እኔ ...................... በዛሬው ዕለት የከተማው ፍርድ ቤት ዳኛ በመሆን ተሹሜ ሥራዬን ስጀምር በከተማው አስተዳደር ምክር ቤት የተጣለብኝን ከፍተኛ ኃላፊነት በታማኝነትና በቅንነት ለመፈፀም ቃል እገባለሁ፡፡"

፲፩ ደንብና መመሪያዎች ስለማውጣት

፩. የከተማው አስተዳደር ካቢኔ ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም አስፈላጊ የሆኑ ደንቦችን ማውጣት ይችላል፡፡

፪. ጉባዔው ለዚህ አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎች ማውጣት ይችላል፡፡

፲፪. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ የካቲት ፳ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ

የካቲት ፳ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም.

የአዲስ አበባ ከተማ

ጊዜያዊ አስተዳደር

## የአዲስ አበባ ከተማ አሰተዳደር ዐቃብያነ ሕግ የሙያሥነ- ምግባር ደንብ ፱/፲፱፻፺ አጭር መግለጫ

<u>ማውጫ</u>

፩. አጭር ርዕስ

፪. ትርጉም

፫. መሠረታዊ መርሆዎች

፬. በሥራ ላይ

፭. ከሥራ ውጪ

፮. በዲስፒሊን ተጠያቂ ስለመሆን

፯. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

<u>አጭር መግለጫ</u>

ሕዝብ በፍትሕ አሰተዳደሩ ትክክለኛነት ላይ እምነት እንዲኖረው ስለሚያስፈግ እና የሙያሥነ-ምግባር ግልጽና ተጠያቂነት ያለበት አሰራር ስለሚፈጥር ለመልካም አሰተዳደር መስፈን ቀዳሚ ጉዳይ በመሆኑ በሚል የወጣ ህግ ነው፡፡

## የአዲስ አበባ ከተማ አሰተዳደር ዐቃብያነ ሕግ የሙያሥነ- ምግባር ደንብ ፱/፲፱፻፺

በወንጀሉ ፍትህ አሰተዳደር ውስጥ የዐቃብያነ ሕግ ተግባር ገለልተኛ ትክክለኛ መሰረታዊ የሕግ መርሆዎችን የተከተለ መሆን ስለሚገባው፤

ሕዝብ በፍትሕ አሰተዳደሩ ትክክለኛነት ላይ እምነት እንዲኖረው ስለሚያስፈግ፤

የሙያሥነ-ምግባር ግልጽና ተጠያቂነት ያለበት አሰራር ስለሚፈጥር ለመልካም አሰተዳደር መስፈን ቀዳሚ ጉዳይ በመሆኑ፤

የአዲስ አበባ ከተማ ጊዜያዊ አሰተዳደር በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፷፰(፪) እና ፷፯(፪) መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል።

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "አዲስ አበባ ከተማ አሰተዳደር ዐቃብያነ ሕግ የሙያ ሥነ-ምግባር ደንብ ቁጥር ፱/፲፱፻፺፯ ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪. ትርጉም**

በዚህ ደንብ ውስጥ፤

፩."ሥነምግባር" ማለት ዐቃብያነ ሕጉ በሥራቸው ላይ እና ከሥራቸው ውጭ በግል ህይወታቸው የተጣለበቸውን የሙያ ኃላፊነት ከዳር ለማድረስ ሊከተሉት የሚገባ ባህሪና ተግባር ነው፤

፪." ዐቃቤ ሕግ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አሰተዳደር ዐቃቤ ሕግ ነው፤

፫."ደንብ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አሰተዳደር ዐቃብያነ ሕግ መተዳደሪያ ደንብ ቁጥር ፯/፲፱፻፺፭ ነው

### ክፍል ሁለት

### ስለ ዐቃብያነ ሕግ ግዴታዎች

**፫. መሠረታዊ መርሆዎች**

፩. ዐቃቢያነ ሕግ ለሰብአዊ መብት መከበር ግንባር ቀደምተሚጋቾች በመሆናቸው በዚሁ መሠረት ኃላፊነታቸውን የመውጣት ግዴታ አለባቸው።

፪. የህግ የበላይነት የመልካም አሰተዳደር መሠረት በመሆኑዐቃብያነ ሕግ ጽንስ ሀሳቡን ሥራላይ የማዋል ኃላፊነት አለባቸው።

፫. ዐቃብያነ ሕግ ከሕግ በሰተቀር በሌላ ሁኔታ አይመሩም።

፬. ንጹሁን ሰው የመጠበቅ እና አጥፊውን ለሕግ ማቅረብ፡ የዐቃብያነ ሕግ ግዴታ ነው።

፭. ዐቃብያነ ሕግ በማንኛውም የፖሊቲካ ድርጅት ገለልተኛ መሆን አለባቸው።

፯. በፍትህ  አሰተዳዳሩ ውስጥ ግልፅነትና ተጠያቂነት ያለው አሰራርእንዲሰፍን ዐቃብያነ ሕግ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

፯. የዘገየ ፍትህ እንደተነፈገ ይቆጠራል የሚለው ብሂል የዐቃብያነሕግ መሪ አስተሳሰብ መሆን ስለሚገባው የፍትህ አሰተዳደሩ አገልግሎት የተሳለጠና የተፋጠነ እንዲሆን የመስራት ኃላፊነት አለባቸው፡

፰. በወንጀል የፍትህ አሰተዳደር የምርመራ ሂደት የሰዎች ሰብአዊናዲሞክራሲያዊ መብቶች እንዲጠበቁ ዐቃብያነ ሕግ የምርመራ ክፍሎች ሥራቸውን በሕግ መሠረት መሥራታቸውን የረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

፱. ዐቃብያነ ሕግ ሥራቸውን ያለፍራቻ፣ ያለጥቅምና ያለጥላቻ  ማከናወን አለባቸው፡፡

፲. በሕገወጥ መንገድ የተገኘ ማስረጃ የመርዛማ ዛፍ ፍሬ በመሆኑበየትኛውም የፍትህ አሰተዳደር ደረጃ እንዳይቀመስ የመከላከል የዐቃብያነ ሕግ ግዴታ ነው፡፡

፲፩.ባለጉዳይ በትህትና ማስተናገድ ላቀረበው አቤቱታ ህጋዊ የሆነአፋጣኝ ምላሽ መስጠት የዐቃብያነ ሕግ ግዴታ ነው።

**፬. በሥራ ላይ**

የዐቃብያነ ሕግ አሠራር ግልጽና ተጠያቂነት ያለበት በመሆኑ  ሥራቸውን በሚያከናወኑበት ጊዜ ተገቢው ሥነምግባር  እንዲኖራቸው ስለሚያስፈልግ የሚከተሉትን ድንጋጌዎች የማክበር ግዴታ አለባቸው፡፡

፩. ዐቃብያነ ሕግ የመንግስት የሥራ መግቢያንና መውጫ ሰዓትንየማክበር ግዴታ አለባቸው፡፡

፪. አለባበሳቸው መሥሪያ ቤቱንና ሞያቸውን የሚያስከብር መሆን  አለበት።

፫. ባለጉዳዮችን በእኩል አይን ማየት የዐቃብያነ ሕግ ግዴታ  ነው፡፡

፬. ዐቃብያነ ሕግ ለሕዝቡና ለሕገ መንግስቱ ታማኝ በመሆንጉልበታቸውንና ችሎታቸውን ለዚሁ ተግባር ማዋል  አለባቸው፡፡

፭. የሀገርና የህዝብን ደህንነት የሚነዱ በመሆናቸው በምስጢርእንዲጠበቁ የተባሉ መረጃዎችን በምስጢርነት የመጠበቅ  ግዴታ  አለባቸው፡፡

፮. ዐቃብያነ ሕግ በመንግስታት የሥራ ጊዜ ከሥራቸው ጋር የሚጋጭም ሆነ የማይጋጭ የግል ሥራ ያለመሥራት ግዴታ  አለባቸው፡፡

፯. ዐቃብያነ ሕግ በሥራ ኃላፊነታቸው ለሰጡት ወይንም    ለሚሰጡት አገልግሎት ማንኛውንም አይነት ስጦታ ከማናቸውም ሰው መጠየቅ ወይንም መቀበል የለባቸውም፡፡

፰. ዐቃብያነ ሕግ ለሥራቸው ማከናወኛ የተሰጧቸውን የመንግስት ንብረቶች በአግባቡ በመጠቀም የመጠበቅ ግዴታ አለባቸው።

፱. ዐቃብያነ ሕግ የቀረበላቸውን ጉዳይ ሁሉ በተቻለ ፍጥነትውሳኔ መስጠት ስለሚጠብቅባቸው በቂ ባልሆነ ምክንያት ቀጠሮ ያለመስጠት ግዴታ አለባቸው፡

፲. ዐቃብያነ ሕግ በአሰራራቸው የመሥሪያ ቤታቸውን ክብር  መጠበቅ አለባቸው፡፡

፲፩.ዐቃብያነ ሕግ እርስ በእርሳቸው ተግባብተውና ተባብረው መስራት አለባቸው፡፡

፲፪. ዐቃብያነ ሕግ የሚሰጡት ውሳኔ ሁሉ ህግን ብቻ መሰረት ያደረገ መሆን ይገባዋል፡፡

፲፫.ዐቃብያነ ህግ ሥራቸውን ሲያከናውኑ ስለ ህግያላቸውንእውቀት ለማዳበር ዘውትር ጥረት ማድረግ አለባቸው፡፡

፭. ከሥራ ውጪ

ዐቃብያነ ህግ የሕዝብን አክብሮትና እምነት እንዲያገኙ እንዲሁም የተጣለባቸውን የሥራኃላፊነት ከዳር ለማድረስ እንዲችሉ በመሥሪያ ቤት ብቻ ሳይሆን በውጭም መልካም ሥነምግባር እንዲኖራቸው ያስፈልጋል፡፡ በዚህም ምክንያት የሚከተሉትን ድንጋጌዎች የማክበር ግዴታ ተጥሎባቸዋል፡

፩. ዐቃብያነ ህግ በሥራቸው ጋር የጥቅም ግጭትን የሚፈጥር ማንኛውንም ዓይነት ሥራ ያለመሥራት ግዴታ አለባቸው፡፡

፪.ዐቃብያነ ሕግ በማናቸውም ጊዜ አግባብ ባለው የመንግስትባለስልጣን ሲጠየቁ ሀብትና ንብረታቸውን የማሳወቅ ግዴታ አለባቸው፡፡

፫.ህዝቡ በአለው የፍትህ አስተዳደር ትክክለኛነት ላይ እምነትእንዲኖረው በሚኖሩበት ኅብረተሰብ ውስጥ መልከም ሥነምግበር ይዘው መታየት አለባቸው፡፡

፬.ዐቃብያነ ሕግ የሚያስክር መጠጥ እንዳይጠጡ ይመከራሉ፡፡ነገር ግን በማናቸውም ጊዜና ቦታ ሰክረው መታየት የለባቸውም፡

፭.ዐቃብያነ ሕግ በሚያከናውኑት ሥራ ባለጉዳይ ከሆነ ሰውጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት ያለማድረግ ግዴታ አለባቸው፡፡

፮.ዐቃብያነ ሕግ በየትኛውም ቦታና ጊዜ የሕግ አምበሳደርበመሆናቸው ከሥራ ውጭ የሚያጋጥማቸውን የሕግ የመጣስ ተግባር መከታተል የሥራቸው አንዱ አካል መሆኑን ተረድተው በዚህ አንጻር የመንቀሳቀስ ግዴታ አለባቸው፡፡

፮. ዐቃብያነ ሕግ ጫትና የሚያደነዝዝ ዕፅ መጠቀም የለባቸውም፡፡

፰.ዐቃብያነ ሕግ ከማንኛውም ባለጉዳይ ገንዘብ መበደር የለባቸውም.፡፡

## ክፍልሶስት

## ልዩልዩድንጋጌዎች

፮. በዲስፒሊን ተጠያቂ ስለመሆን

፩. በደንቡአንቀጽ፫፣፬ እና ፭ የተዘረዘሩትን ድንጋጌዎች የጣሰ ማንኛውም ዐቃቤ ህግ በዐቃብያነ ሕግ መተዳደሪያ ደንብ የተጠቀሰው የዲስፒሊን ቅጣት ይፈጸምበታል፡

፪. በዚህ ደንብ በአንቀጽ ፫ ንዑስ አንቀጽ ፩, ፪, ፫, ፮, ፱,አንቀጽ፬ ንዑስ አንቀጽ ፫, ፬, ፭, ፮, ፮, ፱, ፩፪ እና በአንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ ፩, ፪, ፭ እና ፰ የተዘረዘሩትንበመጣስ የሚፈጸም ተግባር ከባድ የዲስፕሊን ጥፋት ተደርጎ ይቆጠራል፡፡

፫ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ ከተዘረዘሩት ውጭ ያሉትን ድንጋጌዎች በመጣስ የሚፈጸም ተግባር ቀላል የዲስፒሊን ጥፋት ተደርጎ ይቆጠራል፡፡

፮. <u>ደንቡየሚጸናበትጊዜ</u>

ይህ ደንብ ከጥቅምት ፯ ቀን፲፱፻፺፮ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስአበባ

ጥቅምት ፯ ቀን፲፱፻፺፮ዓ.ም

የአዲስ አበባ ከተማ ጊዜያዊ አስተዳደር

## በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርና የክፍለ ከተማ የፀጥታ ምክር ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ፱/፲፱፻፺፭

አዲስ አበባ ሚያዝያ ፱ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ/ም

ማውጫ

፩. አጭር ርዕስ

፪. ትርጓሜ

ክፍል ሁለት

መቋቋም፣ሥልጣንና ተግባር

፫. መቋቋም

፬. ዓላማ

፭. የከተማው ፀጥታ ምክር ቤት አመሰራረትና ጽሕፈት ቤት

፮. የክፍለ ከተማ ፀጥታ ምክር ቤት አመሰራረትና ጽሕፈት ቤት

፯. የከተማው ፀጥታ ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

፰. የክፍለ ከተማው ፀጥታ ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

፱. የመተባበር ግድታ

፲. ደንብ የማውጣት ሥልጣን

፲፩. አዋጁ የሚፀናበት ቀን

አጭር መግለጫ

ይህ አዋጅ በአዲስ አበባ ከተማ ጊዜያዊ አስተዳደር በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፲፩/፲፱፻፺፭ ዓ.ም አንቀጽ ፲፫ (፩) (ሀ) እና አንቀጽ ፷፮ (፪) መሰረት የከተማውን ሠላምና ፀጥታ በህብረተሰቡ ተሳትፎ ለማረጋገጥና ከፌደራል መንግስት የፀጥታ ኃይሎች ጋር ቅንጅት በመፍጠር የፀጥታ ማስከበር ስራውን ለማሳካት አደረጃጀት በመፍጠር ሚናውን እንዲወጣ ለማድረግ የወጣ አዋጅ ነው፡፡

# የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የክፍለ ከተማ የፀጥታ ምክር ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ
## ፱/፲፱፻፺፭

በከተማው አስተዳደር እርከኖች ላይ በመመርኮዝ አግባብ ያላቸው አካላት የሚሳተፉበት የፀጥታ አጠበቅ ማቀናጀት በማስፈለጉ፣ በዚህ ረገድ የፌደራል መንግሥት የሚከተለውን ሀገር አቀፍ የተቀናጀ የፀጥታ አጠባበቅ ስልት በሥራ ላይ መዋልና ከፌድራል የደህንነት ምክር ቤት ጋር ተቀናጅቶ መሥራት በማስፈለጉ፣ የአዲስ አበባ ከተማ ጊዜያዊ አስተዳደር በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፲፩/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፲፫ (፩) (ሀ) እና አንቀጽ ፳፮ (፪) መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የአዲስ አበባ ከተማና የክፍለ ከተማ የፀጥታ ምክር ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፱/፲፱፻፺፭ ዓ/ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. ትርጓሜ በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

፩. " ከተማ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፣

፪. "የከተማ አስተዳደር" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፣

፫. "ክፍለ ከተማ" ማለት በአዲስ አበባ ክፍለ ከተማዎችና ቀበልዎች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፩/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፬ /፩/ የተመለከተ ክፍለ ከተማ ነው፣

፬. "ቀበል" ማለት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፫/ በተጠቀሰው አዋጅ አንቀጽ ፲፪ የተመለከተው ነው፡፡

## ክፍል ሁለት
## መቋቋም፣ ሥልጣንና ተግባር

**፫. መቋቋም**

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፀጥታ ምክር ቤትና የየክፍለ ከተማው የፀጥታ ምክር ቤት ሕጋዊ ሰውነት አግኝተው በዚህ አዋጅ ተቋቁመዋል፡፡

**፬. ዓላማ**

የፀጥታ ምክር ቤቶች በየክፍለ ከተማውና በቀበሌው የሚያጋጥሙ የፀጥታ ችግሮችን የከተማው አስተዳደር ከፌደራል መንግሥት የፀጥታ ኃይሎች ጋር በመቀናጀት በጋራ ለማቃለል የሚያስችለው አደረጃጀትና አሠራር መፍጠሪያ አካላት ሆነው የመሥራት ዓላማ አላቸው፡፡

፭. የከተማው የፀጥታ ምክር ቤት አመሠራረትና ጽሕፈት ቤት

፩. የከተማው ፀጥታ ምክር ቤት የሚከተሉት ቋሚ አባላት ይኖሩታል፣

ሀ) የከተማ ከንቲባ ............... ሰብሳቢ፣

ለ) የከተማው ም/ከንቲባ ...... ም/ሰብሳቢ፣

ሐ) የከተማው አስተዳደር የፍትህና የህግ ጉዳዮች ቢሮ ኃላፊ ........ አባል፣

መ) የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፖሊስ ኮሚሽነር ..... አባል፣

ሠ) የክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈፃሚ .... አባል፣

ረ) የፌደራል ፖሊስ ተወካይ ...... አባል፣

ሰ) የደህንነት፣ የኢሚግሬሽንና የስደተኞች ጉዳይ ባለሥልጣን ተወካይ ....... አባል፣

ሸ) በፌድራል ፖሊስ የወንጀል መከላከል መምሪያ ኃላፊ ...... አባል፤

፪. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም ከንቲባው፤

ሀ) ተጨማሪ የምክር ቤት አባላትን ለመሰየም፣ እና

ለ) ማንኛውም ሰው ሙያዊ ምክር ለመስጠት በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ በአስረጅነት እንዲገኝ ለመፍቀድ ይችላል፡፡

፫. የከተማው ፀጥታ ምክር ቤት ፀሐፊ በምክር ቤቱ ይሰየማል፡፡

፯. የክፍለ ከተማ የፀጥታ ምክር ቤት አመሠራረትና ጽሕፈት ቤት

፩. የክፍለ ከተማው የፀጥታ ምክር ቤት የሚከተሉት ቋሚ አባላት ይኖሩታል፤

ሀ) የክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈፃሚ ........ ሰብሳቢ፤

ለ) የክፍለ ከተማው ም/ዋና ሥራ አስፈጻሚ ..... ም/ሰብሳቢ፤

ሐ) የክፍለ ከተማው ፖሊስ አዛዥ ........ አባል፤

መ) የቀበሌው ዋና ሥራ አስፈፃሚ ....... አባል፤

ሠ) የኢሚግሬሽንና የዜጐች ጉዳይ ዋና መምሪያ የክፍለ ከተማ ተወካይ ..... አባል፤

፪. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም፤ የክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ማንኛውም ሰው ሙያዊ ምክር ለመስጠት በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ በአስረጅነት እንዲገኝ ለመፍቀድ ይችላል፡፡

፫. የክፍለ ከተማ ፀጥታ ምክር ቤት ፀሐፊ በምክር ቤቱ ይሰየማል፡፡

፫. የከተማው ፀጥታ ምክር ቤት የከተማውን ነዋሪ የፀጥታ ሥነ-አእምሮ ለማዳበርና የሆቴሎችም ሆኑ የልሎች ተቋማት ጥበቃ ሠራተኞች ለማሠልጠን በሚቀይሳቸው አጠቃላይ ሥልቶች መሠረት የክፍለ ከተማውን ነዋሪ የፀጥታ ሥነ-አእምሮ ከፍ ለማድረግ የሚያስችል ዕቅድ በማዘጋጀት ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤

፬. በየክፍለ ከተማው ያሉ ሆቴሎች በየእለቱ ያሳደሩትን ሰው በመመዝገብ እንዲይዙና ለፖሊስ ሪፖርት እንዲያደርጉ ሁኔታዎች መመቻቸታቸውን ያረጋግጣል፤

፭. በክፍለ ከተማው ያሉ ቀበልዎችና የተቋማት የጥበቃ ሠራተኞች ከፖሊስ ጋር በመተባበር መሥራት የሚችሉበት ሁኔታ መመቻቸቱን ያረጋግጣል፤

፮. የክፍለ ከተማው ፖሊስና የደንብ ማስከበር አገልግሎት ተቀናጅተው በክፍለ ከተማው ውስጥ ያሉ የኤልክትሪክ ምሰሶዎችና መስመሮች፤ የስልክ ምሰሶዎችና ሳጥኖች እንዲሁም የሕዝብ ስልኮች፤ የውኃ ጋኖችና መስመሮች፤ ድልድዮች፤ የሚጠበቁበት ሁኔታ መመቻቸቱን ያረጋግጣል፤

፯. በክፍለ ከተማው ውስጥ ሕገወጥ የትጥቅ፤ የዕጽ ዝውውር፤ ሕገወጥ ንግድ እና ህገወጥ ግንባታ እንዳይካሄድ የሚያደርገውን የክፍለ ከተማውን ፖሊስና የደንብ ማስከበር አገልግሎት እንቅስቃሴ ይከታተላል፤

፰. በክፍለ ከተማው ውስጥ ከቀበል ወደ ቀበልና ከሰፈር ወደ ሰፈር በመንቀሳቀስ የሚካሄዱ የቡድንም ሆነ የተናጠል ግጭቶችና ልሎች ወንጀሎችን ለመከላከል በክፍለ ከተማው ፖሊስ የሚደረገውን እንቅስቃሴ ይከታተላል፤ የማስተካከያ እርምጃዎች መወሰዳቸውንና በወንጀሎች ላይ ምርመራ ተጣርቶ ለሚመለከተው የፍትህ አካል መቅረቡን ያረጋግጣል፤

፱. ፀጥታን በሚመለከት ለከተማው የፀጥታ ምክር ቤት ሪፖርት ያደርጋል፤

፲. በየሁለት ሳምንቱ ቢያንስ አንድ ጊዜ መሰብሰቡ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የስብሰባና የአሠራር ሥርዓቱን የሚወስን ውስጠ ደንብ ያወጣል፡፡

## ክፍል ሦስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፱. የመተባበር ግድታ

ማንኛውም ሰው ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

፲. ደንብ የማውጣት ሥልጣን

ይህን አዋጅ ለማስፈፀም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የከተማው ካቢኔ ደንብ ማውጣት ይችላል፡፡

፲፩. አዋጁ የሚፀናበት ቀን

ይህ አዋጅ በአዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ

ሚያዝያ ፱ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ/ም

## የአዲስ አበባ ከተማ ጊዜያዊ አስተዳደር የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፳፱/፪ሺ፬ አጭር መግለጫ

ማውጫ

፩ አጭር ርእስ

፪ ትርጓሜ

፫ የጾታ አገላለጽ

፬ እንደገና መቋቋም

፭ የመስሪያ ቤቱ ስልጣንና ተግባር

፮ ለሹመት የሚያበቁ መመዘኛዎች

፯ የአስተዳደሩ ዋና ኦዲተር አሿሿም እና ተጠሪነት

፰ ምክትል ዋና ኦዲተር አሻሻም እና ተጠሪነት

፱ ደመወዝና ጥቅማጥቅም ክፍያ

<u>አጭር መግለጫ</u>

ይህ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኦዲት ቁጥጥር መስሪያ ቤት እንደገና ማቋቋሚያ ቁጥር ፰/፩፱፰፮ የሻረ ሲሆን አዋጁ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ፫፮፩/፩፱፱፭ (እንደተሻሻለ) አንቀጽ ፩፬ (፩) ሀ እና አንቀጽ ፪፮ (፩) መሰረት ራሱን የቻለ የህግ ሰውነት ያለው አካል አድርጎ አቋቁሞታል፡፡ አዋጁ የመስሪያ ቤቱን ስልጣንና ተግባራትን በዝርዝር ያስቀመጠ ሲሆን በተጨማሪ ለሹመት የሚያበቁ ዝርዝር መስፈርቶችንና የአስተዳደሩ ዋና ኦዲተር በከንቲባው አቅራቢነት በምክር ቤቱ የሚሾምና ተጠሪነቱም በዋናነት ለምክር ቤቱ መሆኑን አስቀምጧል፡፡ በተጨማሪ የዋና ኦዲተሮች ስልጣንና ተግባራትንና ከበጀትና ሂሳብ ምርመራ፣ የኦዲት ስርአትና የጊዜ ገደብን ጨምሮ የኦዲት ተደራጊና የኦዲተሮች ግዴታን አካቷል፡

# የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ፳፱/፪ሺ፬

የከተማው አስተዳደር በልዩ ልዩ የልማትና አስተዳደር መስኮች የተሰማሩ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች የገንዘብ አስተዳደር ተገቢውን የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት የተከተ፣ የገቢ አሰባሰባቸው፣ የወጪ አፈቃቀዳቸውና የንብረት አስተዳደራቸው የመንግሥት ሕግ፣ ደንብና መመሪያን ተከትል የተፈፀመ መሆኑንና ዕቅዱና ፕሮግራማቸውንም በቅልጥፍና እና ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገድ በማከናወን የሚጠበቅባቸውን ግብ ማሻካታቸውን ማረጋገጥ አስፈላጊ በመሆኑ፤

የአስተዳደሩን የኢኮኖሚ ፓሉሲ በሚገባ ተግባራዊ ማድረግ ይቻል ዘንዴ በከተማው አስተዳደር ይዞታ ሥር የሚገኙ የአስተዳደር፣ የልማትና የአገልግሎት መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶችን በብቃት ለመቆጣጠር በተጠናከረና ዘመናዊ በሆነ የኦዲት ተግባር መታገዝ ያለበት በመሆኑ፣

በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፲፬ (፩) (ሀ) መሠረት የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ “የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፳፱፪ሺ፬” ተይወከላል ሉጠቀስ ይችላል ፡፡

### ፪. ትርጓሜ

የቃል አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩. “ምክር ቤት” ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት ነው፡፡

፪. “ አስተዳደር” ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፡፡

፫ .“ መሥሪያ ቤት” ማለት የአዲስ አበባ ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ነው፡፡

፬. “ ዋና ኦዲተር” ማለት በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዲዲር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፭፻፲፩/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፲፬ (፪ ) (ሸ) እና በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፮ መሠረት የተሾመ የአዲስ አበባ ዋናው ኦዲተር ነው፡፡

፭.“ድርጅት” ማለትማናቸውም በሙለ ወይም በከፊል የአስተዳደሩ የሆነ የማምረቻ፣ የማከፋፈያ፣ የአገልግሎት ሰጭ ወይም ሌላ የንግዴ ድርጅት ነው፡፡

፯. "የለጋሽ ሂሣብ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወይም የአስተዳደሩ መሥሪያ ቤት ወይም ድርጅት በዓይነት ወይም በጥሬ ገንዘብ ከእርዳታ ሰጭው የተቀበለው ስጦታ ወይም እርዳታ ነው፡፡

፫. በዚህ አዋጅ ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

**፬. እንደገና መቋቋም**

የአዲስ አበባ ከተማ ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ከዚህ በኋላ "መሥሪያ ቤቱ" እየተባለ የሚጠራ በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ (፲) (፩) ሀ እና አንቀጽ &፯ (፩) መሠረት የተቋቋመ የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የአስተዳደሩ አካል ሆኖ እንደገና በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ሥልጣንና ተግባር

**፭. የመሥሪያ ቤቱ ሥልጣንና ተግባር**

፩. የአስተዳደሩን የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እና ድርጅቶች ሂሣብ ኦዲት ያደርጋል፣ ያስደርጋል፡፡

፪. አስተዳደሩ መንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ያስገኙት ውጤት ሕጉን የተከተለ ኢኮኖሚያዊ በሆነ አሠራር እና በብቃት የተፈፀመ መሆኑንና ተፈሊጊውን ግብ መምታቱን ለማረጋገጥ እንደአስፈላጊነቱ የክዋኔ ኦዲት ያደርጋል፣ ያስደርጋል፣

፫. የአስተዳደሩ መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ያስገኙት ውጤት ሕጉን የተከተለ ኢኮኖሚያዊ በሆነ አሠራር እና በብቃት የተፈፀመ መሆኑንና ተፈሊጊውን ግብ መምታቱን ለማረጋገጥ እንደአስፈላጊነቱ የክዋኔ ኦዲት ያደርጋል፣ ያስደርጋል፣

፬. ውጤታማ የሀብት አጠናቀቀምን ለማሣደግና ወቅታዊና ለውሳኔ አጋዥ የሆነ የኦዲት ሪፓርት ለማቅረብ እንዲረዳው ሂሣብ ከመዘጋቱ በፊት የኦዲት ሥራውን ሊጀምሮ ይችላል ፡፡

፭. አስተዳደሩ ከብር ፩ሚሊዮን /አንድ ሚሉዮን ብር/በላይ የሚጠይቅ ሥራየግል ሥራ ተቋራጮች እንዲሰሩ በውል የሰጠ እንደሆነ ይህንኑ መንግሥት ነክ የሆነ የግልሥራ ሂሣብ ኦዲት ያደርጋል፡፡ይሁን እንጂ አፈፃፀሙ ሕግን ያልተከተለ መሆኑ በማስረጃ የተደገፈ ጥቆማ ከደረሰው ከብር ፩ ሚሊዮን _አንድ ሚሉዮን ብር/ በታችም ኦዲት ያደርጋል፡፡

፯. የመንግሥትንና የሕዝብን ጥቅም ለማስጠበቅ ሲባል የግል ወይም የሕዝባዊ ድርጅቶችን ኦዲት ያደርጋል፣ ያስደርጋል፣

፯. ከፌዳራልና ከክልል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤቶች ከግል ኦዲት ድርጅቶች እና ከሚመለከታቸው መሥሪያ ቤቶች ጋር በመመካከር የሂሣብና የንብረት ኦዲት ሥርዓትን ደረጃን የሚመለከቱ መመሪያዎችን ያወጣል፡፡

፰. የሂሣብ አያያዝና የኦዲት ሙያ ትክክለኛውን ፈር ይዞ እንዲዳብር ጥረት ያደርጋል፣ ያስተዳድራልም ቁጥጥር ያደርጋል፡፡

፱. ያስተዳድራል ሆኖ ሲያገኘው የማናቸውም የአስተዳደር መሥሪያ ቤት የውስጥ ኦዲተሮች የመሥሪያ ቤታቸውን ሂሣብና ንብረት በመመርመር ውጤቱ እንዲገለጽለት ሊያደርግ ይችላል ፡፡

፲. የአስተዳደሩ የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ስለገንዘብ አጠባበቅ፣ የሂሣብ አያያዝና የንብረት አስተዳደርን በተመለከተ በሚያዘጋጀው መመሪያ ላይ አስፈላጊውን ምክር ይሰጣል፡፡

፲፩. እንደአስፈላጊነቱ ከሚመለከታቸው መሥሪያ ቤቶች እና ድርጅቶች ጋር በመተባበር ለውስጥ ኦዲተሮች ሥልጠና ይሰጣል፣ እንዲሁም የውስጥ ኦዲት አሠራርን በማጥናት አስተዳደሩ አካላት ተገቢውን ምክር ይሰጣል፣

፲፪. አንዴ ሂሣብ የወንጀል ጥርጣሬ ባለበት ሁኔታና ታማኝነት በጎደለው አኳኋን መያዙን ለማመን በቂ ምክንያት ያለው እንደሆነ ይህንን ሂሣብ የሚመለከቱ ጽሑፎች፣ መዘክሮች፣ መዝገቦች፣ ሠነዶችና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸው መረጃዎችን ያሸጋል፡፡

፲፫. በአስተዳደሩ በግል ኦደት እና ሂሣብ ስራ ለሚሰሩ ኦዲተሮችና ለሂሣብ አዋቂዎች በስራው መስክ ለመሰማራት የሚያስችሊቸውን የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ ያዴሣል፣ ያግዲል፣ ይሠርዛል፣ በዚህም

፲፬. ከፌዳራል እና ከሌሎች ክልላዊ መንግስታት ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤቶች ጋር የኦዲት ተግባር የሚዲብርበትን ሁኔታ በተመለከተ የቅርብ የሥራ ግንኙነትና ትብብር ያደርጋል፡፡

<u>**፯. ለሹመት የሚያበቁ መመዘኛዎች**</u>

በመሥሪያ ቤቱ ለሹመት የሚያበቁ መመዘኛዎች የሚከተለት ይሆናል፣

፩. ዜግነት ኢትዮጵያዊ የሆነ፣

፪. ለኢትዮጵያ ፌዳራሊዊ ዳሞክራሲያዊ ሪፐብሉክ ሕገመንግስት ተገዥ የሆነ፣

፫. ኦዲት ሥራ ወይም አግባብነት ባለው ሌላ ሙያ የሰለጠነ እና በመንግሥት የኦዲት ሥራ ሰፊ እውቀትና ልምዱ ያለው፣

፬. በታታሪነት፣ በታማኝነቱ እና በሥነምግባሩ መልካም ስምን ያተረፈ፣

፭. በወንጀል ጥፋት ተከሶ ያልተፈረደበት፣

፮. ሥራውን ለመሥራት የሚያስችል የተሟላ ጤንነት ያለው፣

፯. ከማንኛውም የፓለቲካ ፓርቲ ገለልተኛ የሆነ መሆን አለበት፡፡

፯. የአስተዳደሩ ዋና ኦዲተር አሿሿምና ተጠሪነት፣

፩. የአስተዳደሩ ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤትን የሚመራው ዋና ኦዲተር በከተማ አስተዳደሩ ከንቲባ አቅራቢነት በምክር ቤቱ ይሾማል፣

፪. የአስተዳደሩ ዋና ኦዲተር ተጠሪነቱ ለምክር ቤቱ ይሆናል፣

፫. የአስተዳደሩ ምክር ቤት በሥራ ላይ በማይሆንበት ጊዜ ተጠሪነቱ አስተዳደሩ ከንቲባ ይሆናል፡፡

**፰. የምክትል ዋና ኦዲተሮች አሿሿምና ተጠሪነት፣**

፩. የአስተዳደሩ ዋና ኦዲተርን በመሥሪያ ቤቱ ዋና ኦዲተር ለከንቲባው ቀርበው በከተማው ምክር የሚሾሙ ሁለት የአስተዳደሩ ምክትል ዋና ኦዲተሮች ይኖራል፣

፪. አንደኛው የኦዲት ዘርፍ ምክትል ዋና ኦዲተር ሲሆን ሁለተኛው የኦዲትና ሂሣብ ሙያ ምስክር ወረቀት ሙያዊ ምክር፣ ድጋፍ እና የሌሎች የድጋፍ አገልግልቶች /የሥራ ሂደቶች ዘርፍ/ ምክትል ዋና ኦዲተር ናቸው፣

፫. እነርሱም ተጠሪነታቸው ለዋና ኦዲተሩ ይሆናል፡፡

**፱. ደመወዝና ጥቅማጥቅም ክፍያ**

፩. የዋና ኦዲተርና የምክትል ዋና ኦዲተሮች ደመወዝ፣ አበልና ሌሎች ጥቅማጥቅሞች በከተማ አስተዳደሩ የበላይ ኃላፊዎች ደረጃ መሠረት ይሆናል፣

፪. ተሿሚዎች የጡረታ ዘመናቸው ከደረሰ የአስተዳደሩ ተሿሚዎች በሚስተናገድበት የጡረታ ሕግ የሚስተናገደ ይሆናል፡፡

**፲. የሥራ ዘመን**

የዚህ አዋጅ አንቀጽ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የዋና ኦዲተር እና የምክትል ዋና ኦዲተሮች የሥራ ዘመን እስከ ጡረታ ዕድሜ ይሆናል፣

**፲፩. የዋና ኦዲተር እና ምክትልና ዋና ኦዲተሮች ከሓላፊነት የሚነሱበት ሁኔታ**

የአስተዳደሩ ዋና ኦዲተር እና ምክትል ዋና ኦዲተሮች በሚከተለት ሁኔታዎች ከሓላፊነት እንዱነሱ ሉደረግ ይችላል ፡-

፩. በሕመም ምክንያት ሥራቸውን በአግባቡ ለማከናወን የማይችለ መሆኑ ሲረጋገጥ፣

፪. ግልፅ የሆነ የሥራ ችልታ ማነስ መኖሩ ሲረጋገጥ፣

፫. በሥራው ላይ የሚያሳየው ቸልተኝነት ጥፋተኛ ሲሆን ወይም ምግባረ ብልሹ ሆኖ ሲገኝ፣

፬. ሙስና መሥራቱ ወይም ሕግን የሚፃረር ሌላ ድርጊት መፈፀሙ ሲረጋገጥ፣

፭. የጡረታ ዕድሜ ላይ ሲደርስ፣

፮. ቀጣይነት ባለው የጤና ጉድለት ወይም በሌላ በቂ በሆነ ምክንያት በገዛ ፈቃደ ሥራውን ለመልቀቅ በጽሐፍ ሲጠይቅ፣

፯. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ እስከ ፮ ያለት በዋና አደተሩ ላይ ተፈፃሚ የሚሆኑት ጉዳዩ በሚመለከተው የምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴ ተጣርቶ በምክር ቤቱ የውሣኔ አሰጣጥ ሥነሥርዓት መሠረት ሲረጋገጥ እና ለምክር ቤቱ ቀርቦ ውሣኔ ሲያገኝ ነው፣

፰. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ እስከ ፯ ያለት በምክትል ዋና ኦዲተሮች ላይ ተፈፃሚ የሚሆኑት በዋና ኦዲተሩ ተጣርቶ ለከንቲባው ቀርቦ ውሣኔ ሲያገኝ ነው፣

፱. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፯ እና ፰ የተደነገገው ቢኖርም ተሚው ለተሾመበት ሥራ አስጊ ሆኖ ሲገኝ የከተማው ምክር ቤት ውሣኔ እስከሚሰጥበት ድረስ ከንቲባው ከሦስት ወር ለማይበልጥ ጊዜ አግድ ማቆየት ይችላል ፡፡

__፲፪. ክፍት ቦታ__

፩. በዚህ አዋጅ አንቀጽ ውስጥ በተገለፁት እና በሞት ምክንያት የአስተዳደሩ ዋና ኦዲተር በሌላ ጊዜ የኦዲት ሥራዎች ዘርፍ ምክትል ዋና ኦዲተሩ ከሶስት ወር ላልበለጠ ጊዜ ተክቶ ይሠራል፣

፪. የኦዲት ሥራዎች ዘርፍ ምክትል ዋና ኦዲተር በላለ ጊዜ የኦዲትና ሂሣብ ሙያ ምሥክር ወረቀት ምክርና ድጋፍ አሰጣጥ እና የሌሎች የድጋፍ አገልግሎቶች ዘርፎች ምክትል ዋና ኦዲተር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ለተጠቀሰው ጊዜ ዋና ኦዲተሩን ተክቶ ይሠራል፣

፫. የአስተዳደሩ ዋና ኦዲተርና የምክትል ዋና ኦዲተር ቦታ በተመሳሳይ ጊዜ ክፍት የሆነ እንደሆነ የከተማው ከንቲባ ከኦዲት ዲይሬክተሮች መካከል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ለተጠቀሰው ጊዜ መዴቦ ሊያሠራ ይችላል፡፡

__፲፫. የዋና ኦዲተሩ ሥልጣንና ተግባር__

የአስተዳደሩ ዋና ኦዲተር የመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ ሆኖ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፰ ለመስሪያ ቤቱ የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር በሥራ ላይ ከማዋል በተጨማሪ ከዚህ የሚከተለት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡

፩. በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ (፩) እስከ (፯) በተሰጠው ሥልጣንና ተግባር መሠረት ስለ መሥሪያ ቤቱ ሥራዎች ዓመታዊ ዘገባ ወቅቱን ሣይጠብቅ እንደ አስፈላጊነቱ ለምክር ቤቱ ያቀርባል፣ ምክር ቤቱ በሥራ ላይ በማይሆንበት ጊዜ አስተዳደሩ ካቢኔ ያቀርባል፣

፪. የአስተዳደሩ የፋይናንስ እና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ የአስተዳደሩን ያለፈውን በጀት ዓመት ገቢና ወጭ፣ ሀብትና እዳ እንዱሁም የመንግሥት ገንዘብ ነክ የሆኑ መረጃዎችን ሂሣብ ዘግቶ ሲልክ ዋና ኦዲተሩ የሂሣብ ሪፓርቱ በደረሰው በ፬ ወር ጊዜ ውስጥ ኦዲት በማድረግ በሪፓርቱ አስተያየቱን አክል ለቢሮው ይልካል በግልባጭ ለከንቲባው ጽሕፈት ቤት ያሣውቃል፣ ለምክር ቤት በሚያቀርበው ዓመታዊ ዘገባ ውስጥ ሪፖርቱ እንዲካተት ያደርጋል፣

፫. ተግባሩን በሚገባ ለማከናወን በሚያስችል አኳኋን መሥሪያ ቤቱን ያደራጃል፣

፬. የመሥሪያ ቤቱን በጀትና ዕቅድ አዘጋጅቶ ለምክር ቤቱ ያቀርባል፡፡ ሲፈቀዱለትም በሥራ ላይ ያውሊል፣

፫. ያስተዳድራል ሆኖ ባገኘው ጊዜ በአስተዳደሩ መሠረታዊ የፋይናንስ አስተዳደር መርህ መሠረት የመሥሪያ ቤቱን ውስጣዊ በጀት ከአንድ ርዕስ ወደ ሌላ ርዕስ ሊያዘዋውረው ይችላል ፣

፬. የመሥሪያ ቤቱ መዋቅር፣ የደመወዝ ስኬል እና የጥቅማ ጥቅም ከፍያ የከተማ አስተዳደሩን አቅም ባገናዘበ መልኩ አዘጋጅቶ በምክር ቤቱ በማፀደቅ ያስተዳድራል የሆኑ ሠራተኞችና ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ደመወዛቸውንና የጥቅማ ጥቅም ክፍያቸውን ይፈፅማል፣

፭. ለሥራው አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በቂ መመሪያ በመስጠትና በመቆጣጠር የኦዲት ሥራ እንደአግባቡ በግል ኦዲተሮች ወይም በሌሎች ባለሙያዎች እንዲከናወን ይወክላል፣

፮. እስከ ዓመታዊ አጠቃላይ ዘገባ የማቅረቢያ ጊዜ ድረስ ሊቆዩ የማይችል አስፈላጊ አፋጣኝ ናቸው ይወክላል ባመነባቸው ጉዳዮች ላይ ልዩ ዘገባ ለምክር ቤቱ ያቀርባል፡፡

**<u>፲፬. የምክትል ዋና ኦዲተሮች ስልጣንና ተግባር</u>**

፩. የኦዲት ሥራዎች ዘርፍ ምክትል ዋና ኦዲተር ሥልጣንና ተግባር

ሀ. የመሥሪያ ቤቱን የኦዲት ሥራዎችን በማቀድ፣ በማደራጀት በመምራት፣ በማስተባበር እና በመቆጣጠር የአስተዳደሩን ዋና ኦዲተር ይደግፋል፡፡

ለ. የአስተዳደሩ ዋና ኦዲተር በሌላ ጊዜ ተክቶ ተግባራቱን ያከናውናል፡፡

ሐ. በአስተዳደሩ ዋና ኦዲተር የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

፪። የኦዲትና ሂሣብ ሙያ ምስክር ወረቀት ምክርና ድጋፍ አሰጣጥና ሌሎች የድጋፍ አገልግልቶች ዘርፍ ምክትል ዋና ኦዲተር፡

ሀ. የመ/ቤቱን የኦዲትና ሂሳብ ሙያ ምስክር ወረቀት፣ ድጋፍ እና ሌሎች የድጋፍ አገልግሎት ዘርፍ በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በመምራት፣ በማስተባበር እና በመቆጣጠር የአስተዳደሩን ዋና ኦዲተር ይደግፋል፡፡

ለ. የአስተዳደሩን ዋና ኦዲተር እና የኦዲት ሥራዎች ዘርፍ ምክትል ዋና ኦዲተር በላለ ጊዜ በመተካት ተግባሮቹን ያከናውናል፡፡

ሐ. በአስተዳደሩ ዋና ኦዲተር የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

**<u>፲፭. በጀትና የሂሣብ ምርመራ</u>**

፩. አዲስ አበባ ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ከተፈቀደው በጀት ውስጥ የሥራ ማስኬጃ በአዲስ አበባ ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ስም በተከፈተው ባንክ ሂሣብ ውስጥ በወቅቱ እንዲቀመጥ ያደርጋል፣

፫. የመሥሪያ ቤቱ ሂሣብ ኦዲት በምክር ቤቱ በሚሰየም ብቁ እና ነፃ በሆነ ኦዲተር ኦዲት ተደርጎ ውጤቱ ለምክር ቤቱ ይቀርባል፡፡ ምክር ቤት በማይኖርበት ጊዜ በአስተዳደሩ ካቢኔ በሚሰየም ብቁና ነፃ ኦዲተር ኦዲት ይደረጋል ውጤቱም ለካቢኔ እንዲቀርብ ይደረጋል፡፡

**፲፮. የኦዲት ስርዓት ወሰን እና የጊዜ ገደብ**

፩. የአስተዳደሩ ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት አንዴን ሂሣብ አዱት ሲያደርግ አንዴ በአንዴ፣ በዝርዝር ወይም አልፎ አልፎ የኦዲት ዘዴ በመጠቀም ሊመረምር ይችላል ፡፡ ሆኖም የእያንዳንዱን ተቋም ሂሣብ አዱት አድርጎ በሚያቀርበው ሪፓርት ውስጥ የኦዲት ወሰኑን፣ ዘዴውን፣ ሁኔታውንና ጥልቀቱን መግለፅ አለበት፣

፪. የአስተዳደሩ ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት የሚያደርጋቸው ምርመራዎች ከሚመረምረው በጀት ዓመት ወደ ኋላ ከሁለት የበጀት ዓመታት ማለፍ የለበትም፡፡ ነገር ግን ወንጀል ተፈጽሟል ብሎ ካመነ ወደ ኋላ አልፎ ሊመረምር ይችላል ፡፡

፫. የአስተዳደሩ ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት የሂሣብ ምርመራ ሲያደርግ በዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃ መሠረት ይሆናል፡፡

**፲፯. የኦዲት ተደራጊዎች ግዴታ**

፩. የአስተዳደሩ ዋና አዱተር መሥሪያ ቤት ኦዲተሮች ወይም ወኪልች ለኦዲት ጠቃሚና ያስተዳድራል የሚመስሎቸውን መፃሕፍት፣ መዘክሮች፣ መዝገቦች፣ ሰነዶችና ሌሎች የጽሁፍና የቃል መረጃዎችን ሲጠየቁ የተጠየቀው ግለሰብ፣ ሠራተኛ ወይም ሓላፊ በትክክልና በተሟሊ አኳኋን ወደያውኑ የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

፪. የአስተዳደሩ ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት እንዱቆጣጠር በዚህ አዋጅ ሥልጣን የተሰጠው ገንዘብ ወይም ንብረት የተረከበ፣ ወጭ ያደረገ፣ የከፈለ ወይም ለሂሣቡ ሓላፊ የሆነ ማንኛውም ሰው ሲጠየቅ ሂሣቡን ኦዲት የማስደረግ ግዴታ አለበት፡፡

፫. ኦዲት ተደራጊ መሥሪያ ቤት በአስተዳደሩ ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት በተሊኩ የኦዲት ሪፓርቶች በተገለፁ ግኝቶች ላይ ተገቢውን የእርምት እርምጃ እንዱወሰዴ በተሰጡ የማሻሻያ ሃሣቦችና አስተያየቶች መሠረት ከ፳ ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እርምጃ የመውሰዴ ግዴታ አለበት፡፡ የወሰደውን እርምጃ እና እርምጃ ለመውሰድ ካልቻለም ምክንያቱን በመግለፅ አስተዳደሩ ዋናው ኦዲተር መሥሪያ ቤት ከላይ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማሣወቅ አለበት፡፡

፬. ማንኛውም ኦዲት ተደራጊ መሥሪያ ቤት የአስተዳደሩን ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ተግባርና ሓላፊነቱን ለመወጣት ይቻለው ዘንድ የመደበው ኦዲተር ሥራውን ለማካሄድ የሚያስችለው የተሟላ ቢሮ አዘጋጅቶ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

፭. የአስተዳደሩ ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት አስተዳደሩ ምክር ቤት በሚያቀርበው ሪፓርት ዴክመት የታየበት የመንግስት መሥሪያ ቤት ሓላፊ በታዩት ድክመቶች ላይ የወሰደን

የማስተካከያ እርምጃ ለምክር ቤቱና አስተዳደሩ ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት የማሣወቅ ግዴታ አለበት፡፡

**፲፰. የማሣወቅ ግዴታ**

፩. የአስተዳደሩ ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ኦዲት ሲያከናውን በጉዳዩ ላይ ወንጀል መፈፀሙን የጠረጠረ እንደሆነ ይህንኑ ለምክር ቤት፣ ለፍትህ ቢሮ እና ጉዳዩ ለሚመለከተው ኦዲት ተደራጊ መሥሪያ ቤት ወይም ድርጅት የበላይ ሓላፊ ያሳውቃል፡፡

፪. በቀጥታ ጉዳዮ የሚመለከተው የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም በአስተዳደሩ የተወከለ አካል የሚከተለት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ሣይዘገይ አስተዳደሩ ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት የመግለፅ ግዴታ አለበት፣

ሀ በፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓት ላይ መሠረታዊ ለውጥ ሊያስከትሉ የሚችሉ ድርጅታዊ ወይም ሌሎች እርምጃዎችን በሥራ ላይ ለማዋል ሲያቅደ፣

ለ. በጀት አያያዝን፣ የንብረት አስተዳደር ወይም ከመንግሥት ገቢና ክፍያ ጋር የተያያዙ ጠቅሊሊ ደንቦች ወይም መመሪያዎችን ሲያወጡ፣

ሐ. የከተማ አስተዳደሩን የሚመለከቱ በኦዲት መሥሪያ ቤቱ ሥልጣን ሥር የሚወዴቁ ስምምነቶችና ውልች ሲፈፀሙ ወይም መሠረታዊ ለውጥ ሲደረግባቸው ወይም ሲቋረጡ፣

መ. ከከተማው አስተዳደር ውጭ ካለ አካላት ጋር የከተማውን የበጀት አስተዳደር የሚመለከቱ ስምምነቶች ሲፈፀሙ፣

**፲፱. ጥፋትና ቅጣት**

፩. ማንኛውም ሰው፡-

ሀ. በአስተዳደሩ ዋና ኦዲተር በቀጥታ ወይም በኦዲተሮቹ ወይም በወኪልች አማካይነት ለኦዲት ስራ እንዲቀርብለት የሚጠይቀውን መፅሃፍ፣ መዘክሮች፣ መዝገቦች ሰነድችና ሌሎች የጽሑፍ ወይም የቃል መረጃዎች ያለበቂ ምክንያት በወቅቱ ያሊቀረበ፣

ለ. ለመሥሪያ ቤቱ ኦዲተሮች ወይም ለወኪሎች ሀሰተኛ መሆኑን እያወቀ ሀሰተኛ መረጃ የሰጠ ወይም እውነተኛ መሆኑን ለማመን ምክንያት ሳይኖረው ማንኛውንም ዓይነት መረጃ የሰጠ፣

ሐ. የአስተዳደሩን ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ሥራ በሚገባ እንዳይከናወን ያሰናከለ፣

መ. ያለበቂ ምክንያት በአስተዳደሩ ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት በቀረበ ኦዲት ሪፓርቶች በተሰጡ የማሻሻያ አስተያየቶችና ሃሳቦች ላይ በወቅቱ እርምጃ ያልወሰደ ወይም በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት መፈፀም ሲኖርበት ለመፈፀም ፈቃደኛ ሆኖ ያልተገኘ፣

ሰ. እንደሆነ ከአምስት እስከ ሰባት ዓመት በሚደርስ እሥራት ወይም አስር ሺብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡

**፪. ማንኛውም ኦዲተር**

ሀ. የስራ ግዴታው ለመፈፀም ወይም በሓላፊነቱ ወይም በሥራ ግዴታው ማድረግ የሚገባውን ላለማድረግ ወይም ማድረግ የማይገባውን ለማድረግ ስጦታ፣ ገንዘብ ወይም ሌላ ጥቅም እንዲሰጠው የጠየቀ የተስፋ፣ ቃል የተቀበለ ወይም የቀረበለትን የወሰደ፣

ለ. ለሚያደርገው የሂሳብ ምርመራ ተመርማሪው ያቀረበለት ሰነድ ሐሰተኛ መሆኑን እያወቀ እንደ ትክክለኛ ሰነድ ከያዘለት ወይም ትክክለኛነቱን እያወቀ ላይዝለት የሚገባውን ሰነድ ሳይቀበለው የቀረ፣

ሐ. የአስተዳደሩን ገንዘብ ያጭበረበረ ወይም ሌላ ሰው እንዲያጭበረብር ሁኔታዎችን በማመቻቸት የተባበረ ወይም ያሴረ፣

መ. ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ወይም ሌላ ሰውን ለማጉዳት በማሰብ፣ በተመርማሪው የቀረበለትን መፃሕፍት፣ መዘከር፣ መዝገቦች፣ ሰነዶችና ሌሎች ማንኛውም መረጃዎች እንዲጠፉ ያደረገ ወይም ወደ ሀሰት የለወጠ ወይም እንዲለወጡ ያደረገ፣

ሰ. እንደሆነ ከአምስት እስከ አሥር በሚደርስ እሥራት ከብር አሥር ሺህ እስከ ብር አሥራ አምስት ሺህ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡

**<u>፳. የኦዲት ባለሙያዎች የሙያ ሥነምግባርና የሙያ ከለላ</u>**

፩. የመሥሪያ ቤቱ ኦዲተሮች ለዚህ አዋጅ ማስፈፀሚያ በሚወጣ የሙያ ሥነምግባር ደንብ ላይ የሚደነገጉትን ድንጋጌዎች አክብረው የመሥራት ግዴታ አለባቸው፡፡

፪. ዋና ኦዲተሩ፣ ምክትል ዋና ኦዲተሮች የአስተዳደሩ ዋና መሥሪያ ቤት እና ኦዲተሮች የሀገሪቱን ሕግና የሙያ ሥነምግባር አክብረው ለሚያከናውኑት የኦዲት ሥራዎች አይከሰሱም፡፡

፫. አስተዳደሩ ምክር ቤት በዋና ኦዲተሩ ተዘጋጅተው የሚቀርብ ሪፓርት እንደ ምክር ቤቱ ሪፓርት አካል ሆኖ ይቆጠራል፡፡ በእነኝህ ሪፓርቶች መነሻነት በዋና ኦዲተሩ ላይ ምንም ዓይነት የፍትሃብሔርም ሆነ የወንጀል ክሶች አይመሠርቱም፡፡

<u>፳፩. የመተባበር ግዴታ</u>

ማንኛውም ሰው ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም የመተባበር ግዴታ አለበት፡

**<u>፳፪. ደንብ የማውጣት ሥልጣን</u>**

የከተማ አስተዳደሩ ካቢኔ ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም የሚረዳ ደንብ ሊያወጣ ይችላል ፡፡

**<u>፳፫. የተሻሩና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች</u>**

፩. የክልል ፩፬ አስተዳደሩ የኦዲትና ቁጥጥር መሥሪያ ቤትን ለማቋቋም የወጣው አዋጅ በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

፪. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም አዋጅ፣ ደንብ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ አዋጅ ውስጥ የተደነገጉትን ጉዳዮች በተመለከተ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

**<u>፳፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በአዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ የካቲት ፲ ቀን ፪፻፬ ዓ_ም

ኩማ ደመቅሳ

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት እንደገና ለማቋቋም የወጣውን አዋጅ /ማሻሻያ/ አዋጅ ቁጥር ፳፱/፪ሺ፲፪ አጭር መግለጫ

ማውጫ

፩. አጭር ርዕስ

፪.ትርጓሜ

፫. ማሻሻያ

፬. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

<u>አጭር መግለጫ</u>

የአዲስ አበባ ከተማ ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት በከተማው የሚገኙ የመንግስት አካላት ማለትም የህግ አውጪውን፣ የፍትሕና አስፈጻሚ አካላት ላይ ግልጸኝነትና ተጠያቂነትን ለማስፈን በሚደረገው ሁሉን አቀፍ እንቅስቃሴ ላይ የሚኖረው ሚና የጎላ በመሆኑ የተቋሙን ሙያዊ ነጻነት ለማስጠበቅና ውስጣዊ አደረጃጀቱን ለማሻሻል የወጣ ሕግ ነው፡፡

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ለማቋቋም የወጣውን አዋጅ ቁጥር ፳፱/፪ሺ፬ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የአዲስ አበባ ከተማ ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት በከተማው የሚገኙ የመንግስት አካላት ማለትም የህግ አውጪውን፣ የፍትሕና አስፈጻሚ አካላት ላይ ግልጸኝነትና ተጠያቂነትን ለማስፈን በሚደረገው ሁሉን አቀፍ እንቅስቃሴ ላይ የሚኖረው ሚና የጎላ በመሆኑ የተቋሙን ሙያዊ ነጻነት ማስጠበቅ ውስጣዊ አደረጃጀቱን ማሻሻል፣ ማዘመንና ማጠናከር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ባለሙያዎች ነጻነታቸው ተጠብቆ፣ መብትና ግዴታቸውን በውል ለይተው በማወቅ ተግባርና ሀላፊነታቸውን ግልጸኝነትና ተጠያቂነት በሰፈነበት ሁኔታ መወጣት እንዲችሉ ለማድረግ፤

የኦዲት ስራውን ወቅታዊና ፈጥኖ ማስተካከያ እርምጃ ከመውሰድ አንጻር እየታየ ያለውን የመንግስት የሀብት ብክነት መልክ ለማስያዝ የሚያስችል ተደራሽ አደረጃጀት አሰራር በመዘርጋት ኃላፊነቱን መወጣት እንዲችል ለማድረግ አሁን በስራ ላይ ያለው የዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፳፱/፪ሺ፬ ማሻሻል በማስፈለጉ።

በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ (እንደተሻሻለ) አንቀጽ ፲፬ ንኡስ አንቀጽ ፩ (ሀ) መሠረት የከተማው ምክር ቤት ይህንን አዋጅ አውጥቷል።

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ “ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት እንደገና ለማቋቋም የወጣውን አዋጅ /ማሻሻያ/ አዋጅ ቁጥር ፷፱/፪ሺ፲፪ ” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### ፪. ማሻሻያ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፳፱/፪ሺ፬ እንደሚከተለው ተሻሽሏል።

፩) ከአዋጁ አንቀጽ (፬) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ አንቀጽ (፭) ተጨምሯል፡-

“፭ ስለቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ማቋቋም

፩. መስሪያ ቤቱ የኦዲት ሽፋኑን ለማሳደግ እንደ አስፈላጊነቱ በከተማው ውስጥ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ሊያቋቁም ይችላል፤

፪. የቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቱ ኃላፊ ሙያን መሰረት አድርጎ በዋና ኦዲተሩ ይመደባል፤

፫. የቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቱ ተጠሪነት ለመስሪያ ቤቱ ይሆናል።”

፪) ከአዋጁ አንቀጽ (፭) በኋላ ያሉ አንቀጾች እንደቅደመ ተከተላቸው ተሸጋሽገዋል፤

፫) የአዋጁ አንቀጽ ፲፬ (እንደተሻሻለ) ንዑስ አንቀጽ (፮) እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-

“፮. የመስሪያ ቤቱን መዋቅር፣ የደመወዝ ስኬል እና ጥቅማ ጥቅም ክፍያ በማጥናት ለከተማው ካቤኔ ያቀርባል፤ በካቢኔው ሲጸድቅ ተግባራዊ ያደርጋል።”፤

፬) ከአዋጁ አንቀጽ ፲፬ (እንደተሻሻለ) ከንዑስ አንቀጽ (፰) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፱) ተጨምሯል፡፡

"፱. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ውስጥ የተቀመጡት መሠረታዊ ዓላማዎችና መርሆዎች እንደተጠበቁ ሆነው ካቢኔው በሚያወጣው ደንብ መሠረት የመስሪያ ቤቱን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤ ያሰናብታል፡፡"

**፭. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ ከጥር ፲፮ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ጥር ፲፮ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም.

ታከለ ኡማ በንቲ

የአዲስ አበባ ከተማ ምክትል ከንቲባ

## <u>የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤቶች አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ፴፩/፲፱፻፺፱</u>

ቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤትን አደረጃጀትና አሰራርን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፲፪/፲፱፻፱፮ የታዩ ክፍተቶችን የሕግ ሽፋን መስጠት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

አዋጁ ላይ የሚታዩ ከቻርተሩ ድንጋጌዎች ጋር የሚቃረኑ ይዘቶችን ከቻርተሩ ጋር ማጣጣም አስፈላጊ በመሆኑ፣

የዳኝነት ተግባራቸውን ሲያከናውኑ ዳኞች ለሚፈጽሙት የስነ ምግባር ጉድለት የእርምት እርምጃ የሚወስድና ጥቅማጥቅማቸውንም የሚያስጠብቅ አካል ባለመኖሩ ምክንያት የተፈጠረውን ችግር ለመቅረፍ እንዲቻል ይሄንኑ ተግባር የሚወጣ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ለማቋቋም የሚያስችል የህግ መሠረት መደንገግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

ዳኞች ከችሎት እንዲነሱ ማመልከቻ ስለሚቀርብበትና የሚነሱበትን ስነ ስርዓት በህግ ውስጥ ማካተት ወሳኝ ጉዳይ በመሆኑ፣

የዳኞችን አመላመል፣ ለዳኝነት የሚያበቁ መስፈርቶችን፣ ሹመትንና ስንብትን በተመለከተ የግልጽ መደንገግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የዳኞች አስተዳደር ጉባኤን የዕለት ተዕለት ሥራ የሚከታተል፣ ምልመላቸውን የሚያከናውን፣ የስነስርዓት ጉድለት ሲፈጽሙ አቤቱታ የሚቀበል እና የሚያስወስን እንዲሁም የፍርድ ቤቶቹን ውሳኔዎች የሚያስፈጽም ጽህፈት ቤት ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የከተማው ነዋሪ በመኖሪያ አካባቢው ያለብዙ ውጣ ውረድ የዳኝነት አገልግሎት እንዲያገኝ ማድረጉ በነዋሪዎች ላይ ሊከተል የሚችለውን የሀብት ብክነትና መጉላላት የሚያስቀር ሆኖ በመገኘቱ፣

መደበኛ ፍርድ ቤቶች ይበልጥ በተወሳሰቡ ጉዳዮች ላይ ሙሉ ጊዜያቸውን በማዋል የተሻለ አገልግሎት ሊሰጡ እንደሚያስችል በመታመኑና ቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤቶች የተቀላጠፈና ውጤታማ የዳኝነት አገልግሎት የሚሰጡበትን ሁኔታ መደንገግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

ቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤቶች በተራዘመ የሥነ ሥርዓት ድንጋጌዎች ሳይታሰሩ የተቀላጠፈና ውጤታማ የዳኝነት አገልግሎት የሚሰጡበትን ሁኔታ መደንገግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ ዓ/ም አንቀጽ ፶/፫/ እና ፲፬/፩/ ረ በተደነገገው መሠረት የከተማው ባለአደራ ጊዜያዊ አስተዳደር ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ " የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤቶች አዋጅን /ለማሻሻል/ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፴፩/፲፱፻፺፱ ዓ/ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

፩. "ከተማ፣ ክፍለ ከተማ እና የቀበሌ አስተዳደር" የሚሉት ሐረጎችና ቃላት በቻርተር አዋጁ ውስጥ የተሰጣቸው ትርጉም በዚህም አዋጅ ውስጥ ይኖራቸዋል፡፡

፪. "ቢሮ" ማለት የከተማ አስተዳደር የፍትሕና ህግ ጉዳዮች ቢሮ ነው፡፡

፫. " ፍርድ ቤት" ማለት የከተማው አስተዳደር የዳኝነት አካል የሆነ፣ በእያንዳንዱ ቀበል የሚቋቋምና የዳኝነት ተግባራትን የሚያከናውን የማህበራዊ ፍርድ ቤት ነው፡፡

፬. "ሬጅስትራር" ማለት በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፯ እና በልሎችም ድንጋጌዎች የተሰጡትን ተግባራት የሚያከናውን የፍርድ ቤቱ ተቀጣሪ ሠራተኛ ነው፡፡

፭. "ቻርተር አዋጅ" ማለት የተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ እንደተሻሻለው ነው፡፡

፮. "ምክር ቤት" ማለት የፍርድ ቤቶቹን ዳኞች የሚሾም በየቀበሌው ህዝብ በሚመረጡ ተወካዮች የሚቋቋም የቀበሌ ምክር ቤት ነው፡፡ ምክር ቤቱ በሥራ ላይ በማይኖርበት ጊዜ የቃሉ ትርጕም የቀበሌ ቋሚ ኮሚቴንም ይጨምራል፡፡

፯. "ጉባዔ እና ጽሕፈት ቤት" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፪ መሠረት የተቋቋሙ አካላት ናቸው፡፡

## ፫. መቋቋም

በከተማው አስተዳደር ክልል ውስጥ በሚገኝ በማንኛውም ቀበል ውስጥ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ ሥር የተመለከተው የዳኝነት ሥልጣን የሚኖረው ፍርድ ቤት ተቋቁሟል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የፍርድ ቤቱ አደረጃጀትና የዳኝነት ስልጣን

## ፬. የፍርድ ቤቱ አደረጃጀት

፩. ማንኛውንም ፍርድ ቤት አንድ ሰብሳቢ ዳኛና ሁት ዳኞች እንዲሁም ሁት ተጠባባቂ ዳኞች ያሉት አንድ ችሎት ወይም ከአንድ በላይ ችሎቶች ሊኖሩት ይችላል፡፡

፪. እያንዳንዱ ፍርድ ቤት አንድ ሬጅስትራርና ልሎች ለስራው የሚያስፈልጉ ድጋፍ ሰጭ ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

፫. የፍርድ ቤቱ ተጠሪነት ለሚገኝበት የቀበሌ ምክር ቤት ይሆናል፡፡

## ፭. የፍርድ ቤቱ የዳኝነት ሥልጣን

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር በሚገኝ በእያንዳንዱ ቀበል ያለ ፍርድ ቤት በቻርተር አዋጁ በተደነገገውና በዚህ አዋጅ መሠረት በሚከተሉት የፍትሐብሔርና የደንብ መተላለፍ ጉዳዮች ላይ የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

፩. በህግ ለልሎች የዳኝነት አካላት የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ፍርድ ቤቱ ግምታቸው ከብር አምስት ሺህ ያልበለጡ የንብረትና የገንዘብ ክርክሮችን የመዳኘት የፍትሐብሔር ስልጣን አለው፡፡

፪. በቻርተር አዋጁ አንቀጽ ፵፩/፪/ /ለ/ እና /መ/ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ፍርድ ቤቱ የከተማውን የሃይጂንና የጤና አጠባበቅ ደንብ እና ሌሎችንም ተመሳሳይ የደንብ መተላለፍ ጉዳዮች የማየት ስልጣን ይኖረዋል፡፡

**፮. ፍርድ ቤቱን ስለመድፈር**

፩. ማንኛውም ሰው ፍርድ ቤቱ በችሎት ላይ እንዳለ የስድብ፣ የዛቻ፣ የፌዝ ወይም ሌላ ተመሳሳይ የሁከት ድርጊት ፈጽሞ ሲገኝ ፍርድ ቤቱ ቀጠሮ ሳያደርግ ወዲያውኑ ዝርዝር ሁኔታውን በያዘው መዝገብ ላይ በመመዝገብ እስከ አንድ መቶ ሀምሳ ብር (፩፻፶) በሚደርስ መቀጮ ሊቀጣው ይችላል፡፡

፪. አጥፊው ገንዘቡን ለመክፈል የማይችል ወይም የማይፈልግ በሆነ ጊዜ ፍርድ ቤቱ መቀጮውን እስከ ሰባት ቀናት ወደሚደርስ እስራት ይለውጣል፡፡

**፯. የሬጅስትራር ሥልጣንና ተግባር**

ሬጅስትራሩ በጉባዔው ጽ/ቤት በኩል በቅጥር የሚመደብ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

፩. ለፍርድ ቤቱ የሚቀርቡ የክስ አቤቱታዎችን መዝገብ ከፍቶ ለችሎት ያቀርባል፣

፪. በፍርድ ቤቱ በኩል ለእርቅ የሚመሩ ጉዳዮች ሲኖሩ በተቻለ መጠን ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ ተገቢ ድጋፍም ይሰጣል፣ ይህንን ተግባሩንም በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር ፪፻፸፬-፪፻፸፱ እና በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር ፫ሺ፫፻፯-፫ሺ፫፵፮ ባሉት ክፍሎች ግልግሎችንና እርቅን አስመልክቶ የተደነገጉ መሠረታዊ መርሆዎችን በመጠበቅ ያከናውናል፡፡

፫. በፍርድ ቤቱ በኩል መጥሪያ እና ትዕዛዞች እንዲሰጥ ሲታዘዝ ለሚመለከተው ወገን እንዲደርሰው ያደርጋል፣

፬. በፍርድ ቤቱ የሚሰጡ ትዕዛዞችና የውሳኔ ግልባጭ ወጪ በማድረግ ለሚመለከታቸው ይሰጣል፣

፭. የፍርድ ቤቱን የአስተዳደርና የዕለት ተዕለት ሥራ በቅርብ ይመራል፣ እና

፮. በፍርድ ቤቱ በኩል የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

፰. የፍርድ ቤቱ ሰብሳቢ ዳኛ ሥልጣንና ተግባር

ሰብሳቢ ዳኛው ለምክር ቤቱ ተጠሪ ሆኖ፣

፩. ፍርድ ቤቱን በፍትህና በአስተዳደር አካላት ፊት ይወክላል፣

፪. የፍርድ ቤቱን ችሎት በሰብሳቢነት ይመራል፣

፫. የፍርድ ቤቱ ስላከናወናቸው ተግባራትና ስላጋጠሙት ችግሮች በዚህ አዋጅ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ተጠሪ ለሆነበት አካል ዘገባ ያቀርባል፣

፬. የፍርድ ቤቱን ዳኞች ያስተባብራል፣ ከቋሚ ዳኞች መካከል አንዱ ለጊዜው ሳይመጣ ቢቀር ዳኛው ላልተገኘበት ጊዜ ብቻ ከተጠባባቂዎች መካከል ተክቶ ችሎቱ እንዲሟላ ያደርጋል

እንዲሁም የሬጅስትራር እና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞችን ሥራ በበላይነት ይመራል፣ ያስተዳድራል፡፡

፫. የፍርድ ቤቱ ልሎች ዳኞች ተጠሪነት ለሰብሳቢው ዳኛ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሦስት

## ስለ ችሎት አመራርና የውሳኔ አሰጣጥ

### ፱. ስለክስ አቤቱታ አቀራረብ

፩. በፍርድ ቤቱ ለሚመሠረቱ የፍትሐብሔርም ሆነ የደንብ መተላለፍ ጉዳዮች አቤቱታ ከዚህ አዋጅ ጋር ተያይዞ የተዘጋጀውን ፎርም በመሙላት ወይም ፎርሙን ጠብቆ በሚዘጋጅ ማመልከቻ በጽሑፍ ለችሎት ይቀርባል ወይም ማንበብና መፃፍ ለማይችል በሚዘጋጅ ፎርም በሬጅስትራሩ ወይም በሌላ ሰው አማካኝነት ክሱ በፎርም ላይ ተሞልቶለትና ተነቦለት በአመልካቹ ተፈርሞበት ለችሎት ይቀርባል፡፡

፪. በአዋጁ አንቀጽ ፫ ንዑስ አንቀጽ ፪ የተመለከተውን የደንብ መተላለፍ ክስ የሚያቀርበው አግባብ ባለው ህግ ስልጣን የተሰጠው ሰው ነው፡፡

፫. ከሚቀርበው አቤቱታ ጋር አመልካች አሉኝ የሚላቸውን እንደአግባቡ የጽሑፍ ማስረጃዎች ፎቶ ኮፒና የምስክሮች ዝርዝር ከነአድራሻቸው ዘርዝሮ በመግለጽ አያይዞ ማቅረብ አለበት፡፡

### ፲. አቤቱታ ከቀረበ በኋላ ስለሚፈፀሙ የመጀመሪያ ሥነ ሥርዓቶች

፩. ፍርድ ቤቱ፣ ወደ ሙሉ ክርክር ከመግባቱ በፊት በሬጅስትራሩ በኩል ተከፍቶ የቀረበለትን አቤቱታ ተመልክቶ በተከሳሽነት የሚጠራው ሰው እንዲቀርብ በማድረግ፣ ከሳሽ እና ተከሳሽ ጉዳዩን በስምምነት ወይም በእርቅ ለመጨረስ እንዲችሉ ሀሳብ ይሰጣቸዋል፡፡ ባለጉዳዮቹ ሀሳቡን ከተቀበሉት አንዳንድ አስታራቂ መርጠው ችግሩን በስምምነት ለመጨረስ መፈለጋቸውን ጠቅሰው በመፈራረም ማመልከቻ ሲያቀርቡ ፍርድ ቤቱ ሬጅስትራሩን ወይም ሌላ ግልጽ ኃላፊነት የተሰጠው ሰው በመመደብ የእርቁ ውጤት የሚቀርብበትን ቀን ይወስናል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንሁስ አንቀጽ /፩/ በተደነገገው መሠረት ሁለቱ ወገኖች ጉዳዩን በእርቅ ወይም በስምምነት ጨርሰው ከቀረቡ ፍርድ ቤቱ ስምምነቱ ለህግ ወይም ለሞራል ተቃራኒ አለመሆኑን መርምሮ በመመዝገብ መዝገቡን ይዘጋል፡፡ የተደረገው ዕርቅ ወይም ስምምነት ተፈፃሚ ስለሚሆንበት ሁኔታ እንደየአግባቡ ፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ ለመስጠት ይችላል፡፡ ሆኖም በአስታራቂዎች ክፍያ እንዲፈፀም ፍርድ ቤቱ አያዝም፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት በዳኛው የሚቀርበውን የእርቅ ሀሳብ ከሳሽና ተከሳሽ ካልተቀበሉት ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፪/ መሠረት ጉዳዩን በእርቅ ወይም በስምምነት ለመፍታት ሳይቻል መቅረቱ በተሰጠው ቀነቀጠሮ በአስታራቂነት

በተመደበው ሰው ሲረጋገጥ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ወደ ማየት ያመራል፡፡ ተከሳሽ ለተባለው ወገን መጥሪያና የቀረበው የክስ አቤቱታ ከነማስረጃው እንዲደርሰው በማድረግ መከላከያውን እንዲያቀርብ ያደርጋል፡፡

፬. በተከራካሪዎች በኩል የጽሁፍ ልውውጥ ሲጠናቀቅም ጉዳዩን መርምሮ ጭብጥ በመያዝ ማቅረብ ያለበት ወገን ማስረጃውን እንዲያሰማ ያደርጋል፡፡ የሰው ምስክሮቹ ቀርበው የሚሰጡት የምስክርነት ቃል አግባብ ባለው ሥነ-ሥርዓት ህግ ላይ በተደነገገው መሠረት ይቀበላል፡፡

**፲፩. በግልጽ ችሎት ስለመስራት**

፩. በፍርድ ቤቱ ክርክሮች የሚካሄዱትና ውሳኔዎች የሚሰጡት በግልጽ ችሎት ነው፡፡

፪. የፍርድ ቤቱ የማስቻያ ስፍራ በቀበልው አስተዳደር ክልል ውስጥ ይዘጋጃል፡፡

**፲፪. የዳኞች ከችሎት መነሳት**

፩. ማንኛውም ዳኛ ከዚህ ቀጥሎ ከተመለከቱት ምክንያቶች በአንዱ ከችሎት ይነሣል፡፡ ዳኛው፡-

ሀ/ ከተከራካሪዎች ከአንደኛው ወገን ወይም ከጠበቃው ጋር የሥጋ ወይም ጋብቻ ዝምድና ያለው እንደሆነ፣

ለ/ ከተከራካሪዎቹ ከአንደኛው ወገን ሞግዚት፣ ነገረ ፈጅ ወይም አማካሪ በሆነበት ጉዳይ ላይ የተነሳ ክርክር የሆነ እንደሆነ፣

ሐ/ ክርክር የተነሳበትን ጉዳይ አስቀድሞ በዳኝነት፣ በውሳኔ ሰጭነት፣ በእርቅ ወይም በተከራካሪነት የተሳተፈበት ሆኖ የተገኘ እንደሆነ፣

መ/ ከተከራካሪዎቹ ከአንደኛው ወይም ከጠበቃው ጋር በፍርድ ቤት የተያዘ ክርክር ወይም ሙግት ያለው እንደሆነ ወይም፣

ሠ/ ከዚህ በላይ ከ/ሀ/ እስከ /መ/ ከተመለከቱት ምክንያቶች ውጭ ትክክለኛ ፍትህ አያሰጥም የሚያሰኝ ሌላ በቂ ምክንያት ሲቀርብ፡፡

በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት ዳኛው በችሎት ሊቀመጥ የማይገባው መሆኑን ሲያውቅ ወዲያውኑ ከችሎት መነሳት አለበት፡፡

**፲፫. ዳኛ ከችሎት እንዲነሳ ስለማመልከት**

፩. ከተከራካሪዎቹ አንደኛው በአንቀጽ ፲፪ በተመለከተው በማንኛውም ምክንያት ዳኛው ከችሎት መነሳት የሚገባው መስሎ የታየው እንደሆነ እንዲነሳለት ለፍርድ ቤቱ ወይም አቤቱታ የሚቀርብባቸው ሁለት ወይም ከሁለት በላይ ከሆነ ለጉባዔው ሰብሳቢ በጽሑፍ ማመልከቻ ማቅረብ ይችላል፡፡

፪. ማመልከቻ የሚቀርበው ክርክሩ ከመጀመሩ በፊት ወይም ማመልከቻ ለማቅረብ ምክንያት መኖሩን አመልካቹ እንዳወቀ ወዲያውኑ ነገር ግን ከውሣኔ በፊት መሆን አለበት፡፡

፫. ከችሎት እንዲነሳ አቤቱታ የቀረበበት ዳኛ በልለበት በሦስት ዳኞች ማመልከቻው ታይቶ ውሳኔ ያገኛል፡፡ ሆኖም ከዳኝነት እንዲነሱ አቤቱታ የቀረበው በሁለቱ ወይም በሶስቱ ዳኞች ላይ ከሆነ በአቤቱታው ላይ ውሳኔ የሚሰጠው የጉባዔው ሰብሳቢ ይሆናል፡፡

፬. ከችሎት እንዲነሣ ማመልከቻ የቀረበው በሰብሳቢው ዳኛ ላይ ከሆነ የቀኝ ዳኛው ሰብሳቢ ሆኖ እና ከተጠባባቂ ዳኞች መካከል አንዱን በራሱ ቦታ ተክቶ ችሎቱ እንዲሟላ በማድረግ በፍርድ ቤቱ በአቤቱታው ላይ ወሣኔ ይሰጣል፡፡ እንደዚሁም፣ ከችሎት እንዲነሣ አቤቱታ የቀረበው በሰብሳቢው ዳኛ ላይ ካልሆነ ሰብሳቢ ዳኛው ፍርድ ቤቱ አቤቱታውን በሚያይበት ጊዜ በአንቀጽ ፰ /፬/ መሠረት ከተጠባባቂ ዳኞች መካከል አንድ ዳኛ ተክቶ ችሎቱ እንዲሟላ ያደርጋል፡፡

፭. የጉባኤው ሰብሳቢ ሁለቱ ወይም ሦስቱ ዳኞች ከችሎት እንዲነሱ የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ ዳኞቹ እንዲነሱ ሲወስን፣ እንደየአግባቡ ችሎት በተጠባባቂ ዳኞች ተሟልቶ ወይም ሦስቱ ዳኞች በመነሣታቸው ምክንያት ሲጓደል በክፍለ ከተማው ከሚገኝ ሌላ ፍርድ ቤት ለዚያ ጉዳይ ብቻ ዳኛ በማዛወር ችሎቱ ተሟልቶ ጉዳዩ እንዲታይ ያደርጋል፡፡

፮. በፍ/ቤቱ ወይም በጉባዔው ሰብሳቢ እንዲነሣ የሚሰጠውን ማንኛውንም ውሳኔ ዳኛው ወዲያውኑ መፈፀም አለበት፡፡

፯. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ መሠረት የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻና ይግባኝ የማይባልበት ይሆናል፡፡

## ፲፬. የፍርድ ቤቱ ችሎት የሥራ ቀናት

፩. ፍርድ ቤቱ ቢያንስ በሣምንት ሁለት ቀናት በችሎት ይሰየማል፡፡

፪. ከዳኞቹ መካከል የመንግሥት ሠራተኛ የሆነ ካለ የሚሰራበት መስሪያ ቤት የዳኝነቱን ተግባር እንዲወጣ በችሎት ለሚሰራበት ሰዓት ፈቃድ ከደሞዝ ጋር ይሰጠዋል፡፡

## ፲፭. ለፍርድ ቤቱ ዳኞች ስለሚከፈል አበል

የፍርድ ቤቱ ሰብሳቢ ዳኛ መደበኛ ደመወዝ ተከፋይ ሆኖ ልሎች ዳኞች እያንዳንዳቸው ባስቻሉበት ቀን የሚታሰብ የቀን አበል የአስተዳደሩ ካቢኔ በሚወስነው መሠረት በየወሩ ይከፈላቸዋል፡፡

## ፲፮. ስለዳኝነት አገልግሎት ክፍያ

፩. የፍትሀብሄር የክስ አቤቱታ የሚያቀርብ አመልካች አቤቱታው በፍርድ ቤቱ እንዲታይለት በሥራ ላይ ባለው ታሪፍ ልክ የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ ይከፍላል፡፡

፪. የዳኝነት ገንዘብ ለመክፈል የማይችል አመልካች ክሱ በነጻ እንዲታይለት በፍትሐብሔር ሥነሥርዓት ሕግ በተደነገገው መሠት አቤቱታ ሊያቀርብና ፍርድ ቤቱ ለሌላው ተከራካሪ

ወገን አቤቱታውን ልኮ መልስ ከመከላከያ ማስረጃ ጋር እንዲያቀርብ ዕድል በመስጠት አጣርቶ ሲፈቅድለት በደሃ ደንብ ክስ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

**፲፯. ስለ ውሳኔ አሰጣጥ እና የይግባኝ አቤቱታ**

፩. በተከራካሪዎች መካከል ያለው ክርክር ሲጠናቀቅ በሰላሳ ቀናት ውስጥ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ በጽሁፍ ይሰጣል፡፡

፪. በሙሉ ድምጽ ወሳኔ ካልተሰጠ በአብላጫ ድምጽ የተደገፈው ውሳኔ የፍርድ ቤቱ ውሳኔ ይሆናል፡፡ ሆኖም የአነስተኛው ድምጽ አስተያየት በውሳኔው ላይ መመዝገብ አለበት፡፡

፫. ማናቸውም ፍርድ ቤቱ ውሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ የፍርዱ ሀተታ የሚከተሉትን ጉዳዮች መያዝ አለበት፡፡

ሀ/ ለውሳኔ የቀረበለትን ጭብጥ ወይም ክርክር፣

ለ/ ክርክሩ በሚሰማበት ጊዜ ችሎቱ የቀረበለትን አግባብ ያላቸውን መረጃና የሰማውን የምስክሮች ቃል ፍሬ ነገርና የተገኘበትን ምንጭ፣

ሐ/ ችሎቱ ውሣኔ ላይ እንዲደርስ ያበቁትን ፍሬ ነገሮችንና ያመዛዘናቸውን ጉዳዮች፣

መ/ ለእያንዳንዱ ጭብጥ ወይም ክርክር የሰጠውን ውሳኔ፣

ሠ/ በሰጠው ውሳኔ መሠረት ሊወሰዱ የሚገባቸውን እርምጃዎች፡፡

፬. የፍርድ ቤቱ ውሳኔ ግልባጭ ውሳኔው በተሰጠ በ፭ የሥራ ቀናት ውስጥ ለተከራካሪ ወገኖች መሰጠት አለበት፡፡

፭. በፍርድ ቤቱ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ሰው ለክፍለ ከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንደየአግባቡ በፍትሀብሄር ሥነ ሥርዓት ህግና በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ህግ በተደነገገው መሠረት የይግባኝ አቤቱታውን ማቅረብ ይችላል፡፡

፮. በዚህ አዋጅ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ፍርድ ቤቱ የፍርድ ሥራውን የሚያከናውነውና የሚያስፈጽመው በፍትሐብሄር ሥነ-ሥርዓት ሕግ እና በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ እንዲሁም በልሎችም አግባብነት ባላቸው ህጐች በተደነገገው መሠረት ነው፡፡

**፲፰. ውሳኔውን የማስፈጸም ስልጣን**

፩. ፍርድ ቤቱ የሰጠውን ውሳኔ የማስፈፀም ሥልጣን አለው፡፡

፪. ፍርድ ቤቱ ውሳኔውን ሲያስፈጽም እንደአግባቡ የፖሊስ ኃይል ወይም የደንብ ማስከበር አገልግሎት ተገቢውን እንዲፈጽሙ የማዘዝና ውሣኔውን የማስፈፀም ሥልጣን አለው፡፡

፫. በፍርድ ቤቶቹ የሚሰጡ ውሳኔዎችን የሚያስፈፀም የስራ ክፍል በጉባዔው ጽሕፈት ቤት ውስጥ ይደራጃል፡፡

## ክፍል አራት

## ስለዳኞች ምርጫ፣ አሿሿምና ከስራ መነሳት

**፲፱. የዳኞች ምልመላና ሹመት**

የፍርድ ቤቱ ዳኞች በጉባዔው አቅራቢነት በምክር ቤቱ ይሾማሉ፡፡

፳. ለፍርድ ቤቱ ዳኝነት ለመሾም ስለሚያበቁ መመዘኛዎች

፩. ስለ ሰብሳቢ ዳኛ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በፍርድ ቤቱ የሚሾም ማንኛውም ዳኛ የሚከተሉትን መመዘኛዎች ማሟላት አለበት፡-

ሀ/ ዕድሜው ቢያንስ ፳፩ ዓመት የሆነና የሚሾምበት ፍርድ ቤት በሚገኝበት ቀበል አስተዳደር ክልል ውስጥ ነዋሪ የሆነ፣

ለ/ ፲ኛ ወይም ፲፪ኛ ክፍል ያጠናቀቀና በአማርኛ ቋንቋ መጻፍና ማንበብ የሚችል፣

ሐ/ በታታሪነቱ፣ በታማኝነቱ፣ በስነምግባሩና በፍትሐዊነቱ መልካም ስም ያተረፈ፡፡

፪. ሰብሳቢው ዳኛ በሕግ ሙያ ቢያንስ በዲፕሎማ የተመረቀና አግባብ ያለው የሕግ ሙያ የስራ ልምድ ያለው መሆን አለበት፡፡

፫. በፍርድ ቤቶቹ ዳኞች አመራረጥና አሿሿም ብሔራዊ ተዋጽኦ ግምት ውስጥ ገብቶ መታየቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ከዳኞች መካከል ቢያንስ እንዱ ሴት መሆን አለባት፡፡

፬. ማንኛውም የተሾመ ዳኛ የዳኝነት ሥራውን ከመጀመሩ በፊት ተገቢውን የዳኝነት ስልጠና ማግኘት አለበት፡፡

**<u>፳፩. ስለዳኞች ከሥራ መነሳት</u>**

፩. በጉባዔው መወሰኑ እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ ዳኛ ከሥራ የሚሰናበተው፡-

ሀ/ ሥራውን በገዛ ፍቃዱ ለመልቀቅ ሲፈልግ የሁለት ወር የቅድሚያ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ለጽ/ቤቱ በመስጠት፣

ለ/ በሕመም ምክንያት ተግባሩን በተገቢው ሁኔታ ማከናወን አይችልም ተብሎ በሀኪም ሲወሰን፣

ሐ/ ጉልሕ የሆነ የሥራ ችሎታና ቅልጥፍና እንሶት ሲገኝ፣

መ/ የዲሲፕሊንና የሥነ ምግባር ደንብ ተላልፎ ጥፋት በመፈፀሙ ከሥራ እንዲሰናበት ሲደረግ፣

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ /ሐ/ እና /መ/ መሠረት የሚሰጥ የዳኛ ስንብት ውሣኔ ለምክር ቤቱ ቀርቦ ሲፀድቅ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል አምስት</u>

## <u>ስለ ጉባዔ መቋቋምና አሠራር</u>

**<u>፳፪ የጉባዔው መቋቋም</u>**

፩ የራሱ ጽ/ቤት ያለውና ተጠሪነቱ ለአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት የሆነ የአዲስ አበባ ከተማ ማሕበራዊ ፍርድ ቤቶች የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ከዚህ በኋላ "ጉባዔ" እየተባለ የሚጠራ አካል ሕጋዊ ሰውነት ኖሮት በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

፪ የጉባዔውን የዕለት ተዕለት ሥራዎች የሚመራና የሚያስተባብር፣ እንዲሁም የፍርድ ቤቶቹን የአቅም ግንባታ ጉዳዮች የሚያስፈጽም የራሱ ኃላፊና አግባብ ያላቸው ሠራተኞች ያሉት ጽ/ቤት በቢሮው ይደራጃል፡፡

፫. የጽ/ቤቱ ኃላፊ ምደባም ሆነ አግባብ ያላቸው ሠራተኞች ቅጥር በመንግሥት ሠራተኞች አስተዳደር ህግ መሠረት በቢሮው ይፈፀማል፡፡

፬. የፍ/ቤቶቹ ሬጅስትራሮች ቅጥርና አስተዳደር በጽ/ቤቱ በመንግሥት ሠራተኞች አስተዳደር ሕግ መሠረት የሚከናወን ሆኖ አሁን በሥራ ላይ ያሉ ሬጅስትራሮች ወደ ጽ/ቤቱ ይዛወራሉ፡፡ ሆኖም የፍ/ቤቶቹ ሬጅስትራሮችም ሆኑ ልሎች ሠራተኞች የዕለት ተዕለት አስተዳደርና ቁጥጥርን በሚመለከት በውክልና በየፍርድ ቤቱ ሊከናወን የሚችልበት ሁኔታ ቢሮው የጋራ አስተዳደር አገልግሎት አሰጣጥ መርሆን በመከተል በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

**<u>፳፫. የጉባዔው ሥልጣንና ተግባር፡-</u>**

ጉባዔው ከዚህ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩. ለፍርድ ቤቶቹ ዳኝነት ብቁ የሆኑ ዳኞችን በመመልመል በምክር ቤቱ እንዲሾሙ ለቀበልው ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ወይም ለቀበልው ዋና ሥራ አስፈፃሚ ያቀርባል፡፡

፪. የፍርድ ቤቶችን የዳኝነት ሥራ አካሄድ በበላይነት ይመራል፣ ይከታተላል፡፡

፫. ስለ ፍርድ ቤቶቹ ዳኞች፣ የደመወዝ፣ አበል፣ የደረጃ እድገትና ምደባ በመንግሥት ፖሊሲ መሠረት ወስኖ ለካቢኔ ያቀርባል፣ ሲፀድቅም ተፈፃሚነቱን ይከታተላል፡፡

፬. ስለ ዳኞች ስንብትና የዲሲፕሊን ጥፋት የሚቀርቡ ጉዳዮችን መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ ጉዳዩ የሚመለከተው ዳኛ ከሥራና ደመወዝ ታግዶ እንዲቆይ ለማድረግ ይችላል፡፡ ዝርዝሩ በካቢኔው በሚወጣ የሥነ-ምግባርና የዲሲፕሊን አፈፃፀም የሥነ-ሥርዓት ደንብ ይወሰናል፡፡

፭. ጉባዔው የሚሰጠው ማናቸውም ውሣኔ ይግባኝ አይጠየቅበትም፣ በፍርድ ቤትም ሆነ በሌላ የፍትህ አካል ክስ ለመመስረት መነሻ አይሆንም፡፡

**<u>፳፬. የጉባዔው አባላት ፡-</u>**

፩. በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፪ ንኡስ አንቀጽ ፪ መሠረት የሚቋቋመው የጽሕፈት ቤት ኃላፊ ሰብሳቢ

፪. በቢሮው የሚወከል ፩ ከፍተኛ የህግ ባለሙያ አባልና ፀሐፊ

፫. በከተማው ባለአደራ ጊዜያዊ አስተዳደር፣ የጊዜያዊ አስተዳደሩ ሥራ ዘመን ሲያበቃ ደግሞ በከተማው ምክር ቤት የሚወከሉ ሦስት ግለሰቦች አባላት

፬. የፍርድ ቤቶች ሰብሳቢ ዳኞች በቢሮው ሰብሳቢነት ተሰብስበው የሚመርጧቸው ፬ የፍርድ ቤቶቹ ሰብሳቢ ዳኞች አባላት

፫. የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት አባል፣

፯. በከተማው አቃቤ ህግ መሥሪያ ቤት የሚወከል አንድ የህግ ባለሞያ አባል በድምሩ ፲፩ አባላት የሚኖሩት ሲሆን

፯. ሰብሳቢው በማይኖርበት ጊዜ የቢሮው ተወካይ ጉባዔውን በሰብሳቢነት ይመራል፡፡

**፹፫. ስለ ጉባዔው ስብሰባ እና ሥነ ሥርዓት ፡-**

፩. ጉባዔው በወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ይኖረዋል፡፡ ሆኖም እንደአስፈላጊነቱ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፡፡

፪. ከጉባዔው አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፡፡

፫. የጉባዔው ውሳኔዎች በድምጽ ይወክላልጫ ያልፋሉ፡፡ ሆኖም ድምጽ እኩል ከተከፈለ ሰብሳቢው ድምጽ የሰጠበት ውሳኔ የበላይነት ይኖረዋል፡፡

፬. የዲሲፕሊን ክስ የቀረበበት ማንኛውም የጉባዔ አባል የሆነ ዳኛ ጉዳዩ በሚታይበት ጊዜ በጉባዔው ስብሰባ በአባልነት መቀመጥ አይችልም፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ጉባዔው የራሱን የስብሰባ ውስጠ ደንብ ያወጣል፡፡

**፹፯. የጉባዔው ሰብሳቢ ሥልጣንና ተግባር**

ሰብሳቢው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

፩. ጽ/ቤቱን በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፡፡

፪. የጉባዔውን ስብሰባ በሊቀመንበርነት ይመራል፡፡

፫. የዕጩ ዳኞችን አጭር መግለጫ በማዘጋጀት ወይም እንዲዘጋጅ በማድረግ ለጉባዔው ያቀርባል፡፡ በጉባዔው የተመለመሉትን ዕጩ ዳኞች ለቀበል ምክር ቤት አፈ ጉባዔ፣ ወይም ለቀበልው ዋና ሥራ አስፈፃሚ ያስተላልፋል፣ የሹመት ደብዳቤ ግልባጭ ሲደርሰው የተሾመው ዳኛ በችሎት ተገኝቶ የፍርድ ቤቱን ሥራ ማከናወኑን ያረጋግጣል፡፡

**፹፯. የአቤቱታ አቀራረብ**

ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት በዳኞች አስተዳደር ጉባዔ የሚታይ አቤቱታ በዳኛ ላይ ማቅረብ ይችላል፡፡ ዝርዝሩ በካቢኔው በሚወጣው የፍ/ቤቱ ዳኞች የሥነ-ምግባርና የዲሲፕሊን አፈፃፀም ሥነ-ሥርዓት ደንብ ይወሰናል፡፡

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፹፰. የመተባበር ግዴታ**

እያንዳንዱ የቀበሌ አስተዳደር ጽሕፈት ቤት በክልሉ ለተቋቋመው ፍርድ ቤት የተቃና የሥራ አፈፃፀም አስፈላጊ የሆኑ ቁሳዊና ቴክኒካዊ ድጋፎች ያደርጋል፡፡

**፹፱. ስለ ቅጣት**

፳. በፍርድ ቤቱ ሥልጣን ሥር የተዘረዘሩት ጥፋቶች ተፈጽመው ሲገኙ፣ ጥፋቱ፣ ያደረሰውን ጉዳት ማስወገዱ ወይም ማጽዳቱ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ የተመለከተውን የገንዘብ መቀጮ እና የማረፊያ ቤት እስራት ቅጣት ፍርድ ቤቱ ይወስናል፡፡ ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ የተመለከተውን የገንዘብ መቀጮ እና የማረፊያ ቤት እስራት ቅጣት ፍርድ ቤቱ ይወስናል፡፡ ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዙት አባሪዎች ውስጥ የተዘረዘሩት የጥፋትና ቅጣት ድንጋጌዎች ሕጐቹ ሲሻሻሉ ተፈፃሚነታቸው ማሻሻያውን ተከትሎ የሚቀጥል ይሆናል፡፡

፪. በወንጀል ህግ ለተካተቱ የደንብ መተላለፎች በዳኞች የሚሰጠው ፍርድ በወንጀል ህጉ ቁጥር ፯፻፴፯ እና ፯፻፺፪ የተደነገገው የማረፊያ ቤት እስራትና የገንዘብ መቀጮ መርሆዎች ሕጉ በሚያዘው መሠረት ከልሎች የክፍሉ ድንጋጌዎች ጋር አጣጥሞ ተፈፃሚ በማድረግ ይሆናል፡፡

፫. ገንዘብ መክፈል የማይችል ሰው ጥፋት ፈጽሞ ሲገኝ፣ የቅጣቱን ገንዘብ የሚመጥን የአገልግሎት ሥራ እንዲሰራ ፍርድ ቤቱ መወሰን ይችላል፡፡

፬. ጥፋቱ ተደራርቦ ሲገኝ ቅጣቱ ከብዶ ይወሰናል፡፡

**<u>፴. ሪፖርት ስለማቅረብ ፡-</u>**

እያንዳንዱ ፍርድ ቤት ስለሥራው እንቅስቃሴ በየሩብ ዓመቱ ለቢሮው ሪፖርት ያቀርባል፡፡ ከዚህ በላይ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ቢሮው መረጃ እና ሪፖርት እንዲቀርብለት በጠየቀበት በማናቸውም ጊዜ ፍርድ ቤቱ የተጠየቀውን የመላክ ግዴታ አለበት፡፡

**<u>፴፩. ተፈፃሚነት ስለሌላቸው ሕጐች</u>**

ይህንን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የተለመደ አሰራር በዚህ አዋጅ ውስጥ የተሸፈኑ ጉዳዮችን በተመለከተ ተፈፃሚነት የለውም፡፡

**<u>፴፪ ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን ፡-</u>**

፩. ካቢኔው ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም የሚያስፈልገውን ደንብ ያወጣል፡፡

፪. ቢሮው ይህን አዋጅና በአዋጁ ላይ ተመስርቶ የሚወጣውን ደንብ ለማስፈፀም የሚያስፈልገውን መመሪያ የማውጣት ሥልጣን እና ዳኞችን የማሰልጠን ኃላፊነት አለበት፡፡

**<u>፴፫. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች ፡-</u>**

ከዚህ ቀደም በፍርድ ቤቶቹ በመታየት ላይ የነበሩ ጉዳዮች በዚህ አዋጅ መሠረት ታይተው ውሳኔ ያገኛሉ፡፡

**<u>፴፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ ከሐምል ፳፯ ቀን <u>፲፱፻፺፱</u> ዓ/ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፯ ቀን <u>፲፱፻፺፱</u> ዓ/ም

## የአዲስ አበባ ከተማ ባለአደራ ጊዜያዊ አስተዳደር

| አባሪ አንድ<br>በማህበራዊ ፍርድ ቤት የሚታዩ የደንብ መተላለፍ<br>ድንጋጌዎች የወንጀል ሕግ ቁጥሮች | |
|---|---|
| አንቀጽ<br>ቁጥር | የሕጉ ርዕስ |
| ፯፻፲፰ | የልሎችን ሥራ፣ ሰላምና እረፍት ማወክ |
| ፯፲፯ | አልኮል የሚያደርሰውን አደጋ መከላከል |
| ፯፻፲፱ | ሰክሮ ወይም አእምሮ የሚያናውጥ ነገር ቀምሶ ሕዝብን ማወክ |
| ፯፻፳ | የምግብና የመጠጥ ቤቶችን መጠበቅና መቆጣጠር |
| ፯፻፳፩ | የቲያትር ቤቶችንና የሕዝብ መደሰቻ ሥፍራዎችን መጠበቅ |
| ፯፻፳፫ | የሰዎችን ሰላማዊ ኑሮ መንካት |
| ፯፻፳፬ | በአደገኞች ሰዎች ወይም በእንስሳት ላይ ተገቢውን ቁጥጥር አለማድረግ |
| ፯፻፳፭ | የህንፃ ሥራዎችን መቆጣጠር |
| ፯፻፳፮ | መንገዶችና የሕዝብ መሰብሰቢያ ሥፍራዎችን መቆጣጠር |
| ፯፻፳፯ | የመገናኛ ደህንነት አደጋ ላይ መጣል |
| ፯፻፴ | የሕዝብ ጤናና ጤናማነትን መቆጣጠር ደንብ ቁጥር ፩/፩፱፯፮ን በተመለከተ |
| ፯፻፴፫ | ምግቦችን፣ መጠጦችንና ልሎች ሸቀጦችን መቆጣጠር |
| ፯፻፴፮ | አስከሬን ስለመቅበርና ስለማቃጠል የወጣውን ደንብ መጣስ |
| ፯፻፵፬ | በክብር ላይ የሚፈፀሙ ቀላል ጥፋቶች |
| ፯፻፵፭ | አስነዋሪ የዝሙት ጥያቄና የይወክላልግና ተግባር |
| ፯፻፶፩ | የመንግሥትና የግል ንብረቶችን መጠበቅ |
| ፯፻፶፪ | ቀላል ስርቆት |
| ፯፻፶፭ | የሌላ ሰውን ንብረት ማበላሸት ወይም ዋጋው እንዲቀንስ ማድረግ |
| ፯፻፶፮ | በሕዝብ ሐውልቶች ላይ ጉዳት ማድረስ |
| ፯፻፶፱ | ወስላታነት |
| ፻፯ | ልሎች ጥቅሞችን በማጭበርበር ማግኘት |
| ፻፯፪ | ያለፈቃድ ገንዘብ መሰብሰብ |

አባሪ ሁለት

በወንጀል ሕግ ያልተሸፈኑ የከተማ አስተዳደሩ

የሐይጅንና የአካባቢ ጤና አጠባበቅ ደንብ ቁጥር

፩/፲፱፻፹፯

| እና የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ደንብ ቁጥር ፲፫/፲፱፻፺፯ ተ/ቁ | ጥፋት | ቅጣት |
|---|---|---|
| ፩ | የደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ ሥርዓት መጣስ | ግለሰብ = ብር ፲፭<br>ድርጅት = ብር ፻ |
| ፪ | የውኃና ቆሻሻ አወጋገድ ሥርዓት በመጣስ<br>ሀ. እጣቢ ወደ መንገድ ማገናኘት ወይም ማፍሰስ<br>ለ. የሽንት ቤት ፍሳሽ ወደ መንገድ ማገናኘት ወይም ማፍሰስ<br>ሐ. መርዛማ ንጥረ ነገር ያዘለ ፍሳሽን ወደ መንገድ ማገናኘት ወይም ማፍሰስ | ብር ፳፭<br>ብር ፸፭<br>ብር ፪፻ |
| ፫ | መኪና፣ ልብስ ልሎች ዕቃዎች በመንገድ፣ በአደባባይ ወይም በልሎች ባልተፈቀዱ ቦታዎች ላይ፣<br>ሀ. ማሳጠብ<br>ለ. ማጠብ | ብር ፵<br>ብር ፭ |
| ፬ | ከመፀዳጃ ቤት ውጪ ሽንት መሽናት ወይም መፀዳዳት | ብር ፭ |

ከቆሻሻ አያያዝ፣ አሠባሰብና አወጋገድ ጋር በተገናኘ የሚፈጸሙ የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቆሻሻ አያያዝ፣ አሠባሰብና አወጋገድ ደንብ ቁጥር ፲፫/፲፱፺፯ ዓ/ም በተደነገገው የጥፋትና የቅጣት ሠንጠረዥ መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል፡

ለቀበል ማህበራዊ ፍርድ ቤት የክስ አቤቱታ የማቅረቢያ ፎርም

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

ለ ……………………………….ክ/ከተማ ቀበል ……………….. ማህበራዊ ፍርድ ቤት

አዲስ አበባ፣

ከሳሽ/ዎች ፣ ፩. ………………………………

፪. ………………………………

፫. ………………………………..

አድራሻ፣ ክልል/ከተማ………………………. ወረዳ/ክፍለ ከተማ ………………….

ቀበል/የገበሬማሕበር …………………….. የቤት ቁጥር …………………

ተከሳሽ/ዎች፣ ፩. ……………………………

፪. ……………………………

፫. ………………………………..

አድራሻ፣ ክልል/ከተማ ………………………… ወረዳ/ክፍለ ከተማ ………………

ቀበል/ገ/ማሕበር …………………….. የቤት ቁጥር ……………………………………….

የክሱ ምክንያት …………………………………………………………………………………

የገንዘቡ ልክ ………………………………………………………………………………………

ሀ. ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለመዳኘት ሥልጣን ስለመኖሩ፣

ለ. ጉዳዩ በይርጋ የማይታገድ ስለመሆኑ፣

ሐ. መጥሪያና የክስ አቤቱታ ከሳሽ የሚያደርስ ስለመሆኑ፣

መ. ከሳሽ ችሎታ ያለው ስለመሆኑና በምን ሥልጣን ክሱን እንደሚያቀርብ ይገለጽ/

ለምሣል፡- በሞግዚትነት፣ በጠባቂነት በወኪልነት ወይም በአስተዳዳሪነትና በእራስ ስም ስለመሆኑ/

ሠ. የጉዳዩ ፍሬ ነገር በዝርዝር ይገለጽ፡፡

ለምሣል ፡- ከሳሽ ከተከሳሽ ያልተከፈለው የቤት ኪራይ ሂሣብ ቢኖር መክፈል ይገባው የነበረበትን ጊዜ በማመልከት ያልተፈፀመለት መሆኑን ጠቅሶ ተፈላጊ ዝርዝሮችን ያካት

ረ. የሚጠየቀው ዳኝነት በግልጽ ይመልከት፡፡

ለምሣል፡- ያልተከፈለው ገንዘብ እንዲከፈለው፣ ወለድ የሚጠይቅ ቢሆንይህንኑ እና ልሎች ሂሳቦች ቢኖሩ በዝርዝር ማመልከት፡፡

ሰ. በግል የሚቀርብ አቤቱታ ጉዳዩ በእውነት የቀረበ መሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. ፺፪ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት ይረጋገጥ፡፡

ሸ. አቤቱታው መንግሥታዊ በሆኑና ባልሆኑ ተቋማት የሚቀርብ ሲሆን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ ፺፪ ንዑስ አንቀጽ ፪ እና ፫ መሠረት ስለትክክለኛነቱ በሚመለከተው ኃላፊ ተረጋግጦ፣ የፕሮቶኮል ቁጥር ይዞና የተቋሙ ማህተም አርፎበት በበቂ ኮፒ ይቅረብ፡፡

ሙሉ ስም ……………………………………..

ፊርማ ……………………………………....

የቀበሌ ማህበራል ፍርድ ቤት የክስ አቤቱታ የማቅረቢያ ፎርም

ቀን …………………………………..

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

ለ ………………… ክ/ከተማ ……………. ቀበል ………… ማህበራዊ ፍርድ ቤት

አዲስ አበባ፡

ከሳሽ/ዎች ፣ ፩. ………………………………

፪. ………………………………

፫. ………………………………..

አድራሻ፣ ክልል/ከተማ ……………………… ወረዳ/ክፍለ ከተማ ………………….

ቀበል/ገ/ማሕበር …………………….. የቤት ቁጥር …………………………………………

ተከሳሽ/ዎች፣ ፩. ………………………………

፪. ………………………………

፫. ………………………………..

አድራሻ፣ ክልል/ከተማ …………………………… ወረዳ/ክፍለ ከተማ …………………….

ቀበል/የገበሬ/ማሕበር …………………….. የቤት ቁጥር …………………………………………

እንደክሱ ለማስረዳት የቀረበ የማስረጃ ዝርዝር

፩. እንደክሱ ሊያስረዱ የሚችሉ ማናቸውም ሰነዶች ከነመለያ ቁጥራቸውና ቀናቸው እንዲሁም የገጽ ብዛታቸው ተዘርዝሮ በፎቶ ኮፒ አባሪ ተደርጐ ይቅረብ፡፡ ማስረጃዎቹ በከሳሽ እጅ የሚገኙ ሲሆን ትክክለኛ መገኛ ቦታቸው ይጠቀስ፡፡

፪. የሰው ምስክር የሚቀርብ ሲሆን ሙሉ ስሙ ከመገኛ ትክክለኛ አድራሻው ጋር ይገለጽ፡፡ ለቀረበው አቤቱታ ሌላ ማስረጃ የማይቀርብ ከሆነ ግለሰብ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ ፱፪ ንዑስ አንቀጽ ፩ እንዲሁም ተቋም በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ ፱፪ ንዑስ አንቀጽ ፫ መሠረት ተረጋግጦ የፕሮቶኮል ቁጥር ይዞና ማህተም አርፎበት ይቅረብ፡፡

ሙሉ ስም ……………………………………..

ፊርማ ………………………………………....

# የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአማካሪ ምክር ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ፯/፲፱፻፺፰

ጊዜያዊው የከተማው አስተዳደር ሲቋቋም ቀድሞ የነበሩት ምክር ቤቶች የፈረሱ ስለሆነ ለቀጣዩ የከተማው አስተዳደር የሕዝብ ምርጫ ነዋሪው ልምድ የሚቀስምበት መድረክ መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ፤

በከተማው መልካም አስተዳደር እና የዴሞክራሲ ግንባታ ፅኑ መሠረት ላይዝ የሚችለው በሂደቱ ነዋሪው በንቃት ሲሳተፍ በመሆኑ፤

የከተማው ልማት ሊረጋገጥ የሚችለው እና ነዋሪውም የልማቱ ተጠቃሚ የሚሆነው ነዋሪው በባለቤትነት መንፈስ ሲሳተፍ በመሆኑ፤

ለከተማው ነዋሪ የሚቀርቡ አገልግሎቶች ዓይነት፣ መጠንና ጥራት አስተማማኝ ሊሆን የሚችለው በነዋሪው ቀጥተኛ ተሳትፎ በመሆኑ፣

የአዲስ አበባ ከተማ ጊዜያዊ አስተዳደር በተሸሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፲፩/፲፱፻፺፫ አንቀጽ ፲፫/፩/ረ/ እና አንቀጽ ፷፯ (፪) እና ፷፯(፫)፩ (መ) መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአማካሪ ምክር ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፯/፲፱፻፺፰ ዓ.ም." ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ፤

፩. "ከተማ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤

፪."የከተማ አስተዳደር" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፫. "የአማካሪ ምክር ቤት" ማለት እንደአግባብነቱ የከተማ ምክር ቤት፣ የክፍለ ከተማ ምክር ቤት፣ የቀበሌ ምክር ቤት ነው፡፡

## ክፍል ሁለት

## ማቋቋም፣ ጽሕፈት ቤት፣ ከተማ፣ የክፍለ ከተማ፣ የቀበሌ፣ አማካሪ ምክር ቤት አባላትና አባልነት

### ፫. የአማካሪ ምክር ቤቶች መቋቋም

በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ምክር ቤቶች ተቋቁመዋል፤

፩. የከተማው አስተዳደር የአማካሪ ምክር ቤት፤

፪. የክፍለ ከተማ የአማካሪ ምክር ቤት፤

፫. የቀበሌ የአማካሪ ምክር ቤት፡፡

፬. <u>የጽህፈት ቤት</u>

የከንቲባው ጽሕፈት ቤት፣ የክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈፃሚ ጽሕፈት ቤት፣ የቀበሌ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ጽሕፈት ቤት እንደ ቅደም ተከተሉ የየዐማካሪ ምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤቶች ሆነው ይሰራል፡፡

፭. <u>የከተማ አማካሪ ምክር ቤት አባላት</u>

፩. የከተማ አማካሪ ምክር ቤት የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፤

፩. የከተማ ከንቲባ ................................ ሰብሳቢ

፪. የካቢኔ አባላት ................................ አባል

፫. የከተማው ሥራ አስኪያጅ.................... አባል

፬. የከተማው ምክትል ሥራ አስኪያጅ.......... አባል

፭. ምክትል የቢሮ ኃላፊዎች .................... አባሎች

፮. የከተማው አስተዳደር መሥሪያ ቤቶች ኃላፊዎች ...... አባሎች

፯. የክፍለ ከተማ ዋና ሥራ አስፈፃሚ፣ ምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚ እና ቋሚ ኮሚቴ.....አባሎች

፰. ከየቀበሌው ሁለት የነዋሪዎች ተወካይ...... አባሎች

፱. የቀበሌ ቋሚ ኮሚቴ.......................... አባል

፲. የከተማው ሴቶች ማህበር ተወካይ.......... አባል

፲፩. የከተማው ወጣቶች ማህበር ተወካይ........ አባል

፲፪. የሠራተኛ ማህበር ተወካይ.................. አባል

፲፫. የአዲስ አበባ ንግድ ምክር ቤት ተወካይ.....አባል

፲፬. የኢትዮጵያ አምራች ኢንዱስትሪ ባለሀብቶች ማህበር ተወካይ............አባል

፲፭. መምህራን ማህበር ተወካይ................. አባል

፲፮. የሙያ ማህበራት ተወካይ..................... አባል

፲፯. የኢትዮጵያ አርበኞች ማህበር ተወካይ......አባል

፲፰. የሲቪል ህብረተሰብ ማህበራት ተወካይ.....አባል

፲፱. ዩንቨርስቲ እና ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ተወካይ......................................... አባል

፳. የጤና ባለሙያዎች ማህበር ተወካይ........ አባል

፳፩. መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተወካይ...አባል

፪. የከተማ አማካሪ ክር ቤት ተወካዮች ቁጥር ከስድስት መቶ አስከ ሰባት መቶ የሚደርስ ሲሆን ዝርዝሩ በአባሪ ቁጥር ፩ የተመለከተው ይሆናል፡፡

፮. የክፍለ ከተማ አማካሪ ምክር ቤት አባላት

፩. የክፍለ ከተማ አማካሪ ምክር ቤት የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፤

፩. የክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈፃሚ............ ሰብሳቢ

፪. የክፍለ ከተማው ቋሚ ኮሚቴ........................... አባል

፫. ከየቀበሌው ሃያ የነዋሪ ተወካዮች..................... አባል

፬. የቀበሌ ቋሚ ኮሚቴዎች................................... አባል

፭. የክፍለ ከተማው መሥሪያ ቤቶች ኃላፊዎች...... አባል

፮. የክፍለ ከተማው የሴቶች ማህበር ተወካይ........... አባል

፯. የክፍለ ከተማው ወጣቶች ማህበር ተወካይ......... አባል

፰. የክፍለ ከተማው መምህራን ማህበር ተወካይ...... አባል

፱. የአዲስ አበባ ንግድ ምክር ቤት ተወካይ..............አባል

፲. የሲቪል ህብረተሰብ ማህበራት ተወካይ............. አባል

፲፩. መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተወካይ......... አባል

፪. የክፍለ ከተማ አማካሪ ምክር ቤት አባላት ቁጥር ከአምስት መቶ እስከ ሰባት መቶ የሚደርስ ሲሆን ዝርዝሩ በአባሪ ቁጥር ፪ የተመለከተው ይሆናል፡፡

፯. <u>የቀበሌ አማካሪ ምክር ቤት አባላት</u>

፩. የቀበሌ አማካሪ ምክር ቤት የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፤

፩. የቀበሌው ዋና ሥራ አስፈጻሚ..................ሰብሳቢ

፪. የቀበሌ ቋሚ ኮሚቴ..................................አባል

፫. ቀበሌ ነዋሪ ተወካዮች.............................አባል

፬. ሴቶች ማህበር ተወካዮች.............................አባል

፭. የወጣቶች ማህበር ተወካይ..........................አባል

፮. መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተወካይ......አባል

፯. የመምህራን ማህበር ተወካዮች......................አባል

፰. የህክምና ባለሙያዎች ማህበር ተወካዮች.......አባል

፱. የቀበሌ የትምህርት ዴስክ..............................አባል

፲. የቀበሌ የትምህርት አመራር ተወካዮች.........አባል

፲፩. የሲቪል ህብረተሰብ ማህበራት ተወካይ........አባል

፲፪. የአካባቢ ልማት ኮሚቴ..............................አባል

፲፫. የአካባቢ ልማት ኮሚቴ..............................አባል

፲፬. የእድሮች ተወካዮች..................................አባል

፪. ቀበሌ አማካሪ ምክር ቤት አባላት ቁጥር ከአምስት መቶ እስከ ስድስት መቶ ሆኖ ዝርዝሩ በአባሪ ቁጥር ፫ የተመለከተው ይሆናል፡፡

፰. <u>አባልነት</u>

፩. ከየቀበሌው ለከተማ ምክር ቤት እና ለክፍለ ከተማ ምክር ቤት የተወከሉ ነዋሪዎች፣ በተደራቢነት በተዋረድ በየሚመለከታቸው ክፍለ ከተማ እና ቀበል ምክር ቤት ይሳተፋሉ፡፡

፪. በማንኛውም የአማካሪ ምክር ቤት ከሚገኙ አባላት ውስጥ ሁለት ሶስተኛው የነዋሪው ተወካዮች ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>የአማካሪ ምክር ቤት ስልጣንና ተግባር የምክር በቤቱ ሰብሳቢ፣ ፀሐፊ፣ የምክር ቤቱ ኮሚቴዎች ሰብሳቢ ሥነ ሥርዓትና ቃለ ጉባኤ</u>

፱. <u>የአማካሪ ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር፤</u>

፩. ማንኛውም በዚህ አዋጅ መሠረት የተቋቋመ ምክር ቤት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

፩. በከተማው አስተዳደር ዕቅዶችና አፈፃፀማቸው ላይ ይመክራል አፈፃፀማቸውንም ይከታተላል፡፡

፪. በከተማው አስተዳር በጀት ቁጠባዊ አጠቃቀም ላይ ይመክራል፡፡

፫. የከተማው አስተዳር በሚያወጣቸው ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ላይ ምክር ይሰጣል፤

፬. በከተማው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ዕቅድ ዝግጅት ላይ ይመክራል፤

፭. በከተማው ፀጥታ ጉዳዮች ላይ ይመክራል፤

፮. በከተማው አስተዳደር ጉዳዮች ላይ ምክር ይሰጣል፤

፯. በህዝብና በከተማው አስተዳደር በጋራ ለሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ የሚውል የሕዝብ መዋጮ የሚሰበሰብበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡

፰. በህዝብና በከተማው አስተዳደር በጋራ የተሠሩ ፕሮጀክቶችን እንክብካቤ ይካተታል፡፡

፱. በከተማው ነዋሪና በከተማው አስተዳደር መካከል በልማት እና በአስተዳደር ረገድ የግንኙነት መድረክ በመሆን ያገለግላል፤

፲. የከተማው ነዋሪ በከተማው ልማትና መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን ተደራጅቶ በፈቃደኝነት ሙሉ ተሳትፎ ስለሚያሳድጋቸው ሁኔታዎች ይመከራል፤ ስልቶችን ይነድፋል፤

፲፩. ለከተማው ነዋሪ የሚቀርቡ አገልግሎቶች ዓይነት መጠንና ጥራት ደረጃውን የጠበቀና ቀጣይነት ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ይመክራል፡፡

፲፪) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ሥር የተዘረዘሩት ሥልጣንና ተግባራት እነደአግባብነቱ ለክፍለ ከተማና ለቀበል ምክር ቤቶች ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

፲. <u>አማካሪ ምክር ቤቱ ሰብሳቢ</u>

የምክር ቤት ሰብሳቢ በማይገኝበት በማንኛውም ጊዜ ምክትል ሰብሳቢ ተክቶ የሚሠራ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ አማካሪ ምክር ቤቱ ሰብሳቢ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

፩. የምክር ቤቱን ስብሰባዎች ይመራል፣ ምክር ቤቱን ይወክላል፣ ያስተባብራል፤

፪. በአማካሪ ምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ ቀርበው ማብራሪያ የሚሰጡ የሥራ ኃላፊዎች፣ ባለሙያዎች፣ ወይም አግባብነት ያላቸው ግለሰቦች እንዲገኙ ይፈቅዳል፤

፫. የአማካሪ ምክር ቤቱን ፀሐፊ ይመድባል ይህንንም ለምክር ቤቱ ያሳውቃል፤

፬. አማካሪ ምክር ቤቱ የሚስማማባቸውን የምክር አስተያየቶች በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፡፡

## ፲፩. የአማካሪ ምክር ቤቱ ፀሐፊ

የአማካሪ ምክር ቤቱ ፀሐፊ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

፩. የአማካሪ ምክር ቤቱን ጽህፈት ቤት በኃላፊነት ይመራል፣

፪. በአማካሪ ምክር ቤቱ ጽህፈት ቤት ስም ከልሎች አካላት ጋር ይፃፃፋል፤

፫. የአማካሪ ምክር ቤቱን የሥራ ፕሮግራምና የውይይት አጀንዳዎች በማዘጋጀት ረገድ ለምክር ቤቱ ሰብሳቢ ድጋፍ ይሰጣል.

፬. ቃለ ጉባኤዎች ይመዘግባል፣ ይይዛል፣

፭. ለአማካሪ ምክር ቤቱ የሚያስፈልጉት ቁሳቁሶች እንዲሟሉ ያደርጋል፡፡

፮. በአማካሪ ምክር ቤቱ ሰብሳቢ የሚሰጡትን ልሎች ተግባሮች ያከናውናል፡፡

## ፲፪. የአማካሪ ምክር ቤት ኮሚቴዎች

፩. አማካሪ ምክር ቤት እንደአግባብነቱ ኮሚቴዎች ሊሰይም ይችላል፡፡

፪. የአማካሪው ምክር ቤት ኮሚቴዎች ምክር ቤቱና ለሰብሳቢው በፖሊስ ጉዳዮች ላይ የምክር አገልግሎት ይሰጣሉ፤ የአማካሪ ምክር ቤቱን አስተያየቶች አፈፃፀም ይከታተላሉ፣ ይገመግማሉ፡፡

፫. የኮሚቴዎች አሰራር አማካሪ ምክር ቤቱ በሚያወጣው ውስጠ ደንብ ይወስናል፡፡

## ፲፫. የአማካሪ ምክር ቤት የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት

፩. የከተማው እና የክፍለ ከተማ አማካሪ ምክር ቤቶች በየሦስት ወሩ አንድ ጊዜ የሚካሄድ መደበኛ ስብሰባ ሲኖራቸው ቀበሌ አማካሪ ምክር ቤት በሁለት ወር አንድ ግዜ የሚካሄድ መደበኛ ሲኖራቸው ቀበሌ አማካሪ ምክር ቤት በሁለት ወር አንድ ጊዜ የሚካሄድ መደበኛ ስብሰባ ይኖረዋል፤ እያንዳንዱ ምክር ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው አስቸኳይ ስብሰባ ሊኖረው ይችላል፤ ዝርዝሩ በምክር ቤቱ በሚወጣ የውስጥ ደንብ ይወሰናል፡፡

፪. ምልዓተ ጉባኤ የሚኖረው ከአባላት ከግማሽ በላይ ሲገኙ ይሆናል፡፡

፫. ምልዓተ ጉባኤ መኖሩ በምክር ቤቱ ፀሐፊ ሲረጋገጥ ሰብሳቢው የአማካሪ ምክር ቤቱ ሥራውን እንዲጀምር ያደርጋል፡፡

፬. አንድ አባል በሰብሳቢው ተፈቅዶለት በመናገር ላይ እያለ ሌላ አባል ሊያቋርጠው አይችልም፤ ሆኖም ውይይቱ ፈር ለቋል ወይም ሥነ ሥርዓት ተጓድሏል ብሎ ለማመልከት ወይም መረጃ ለመስጠት የሚጠይቅ አባል "ስለ ደንብ" ወይም "ስለ መረጃ" ሲል ሰብሳቢው ተራ ጠብቆ እንዲናገር ዕድል ይሰጠዋል፣ የደንብ ጥያቄ ቅድሚያ የሚሰጠው ሲሆን መረጃና ማብራሪያ እንደ ቅደም ተከተላቸው ይቀርባሉ፡፡

፭. አማካሪ ምክር ቤቱ የሚያስተላልፈው የምክር አስተያየት በተባበረ ድምፅ ይሆናል፤ ይህ ካልተቻለ የአብዛኛው ድምፅ አስተያየት እና የአማራጭ አስተያየት ይተላለፋሉ፡፡

፮. የአማካሪ ምክር ቤቱ አስተያየት በአባላቱ ተፈርሞበት በሰብሳቢው እንደአግባብነቱ ለከተማ፣ ለክፍለ ከተማው፣ ለቀበልው ከፍተኛ የሥልጣን አካል ይቀርባል፡፡

**፲፬. <u>የአማካሪ ምክር ቤቱ ቃለ ጉባኤ</u>**

፩.የአማካሪ ምክር ቤቱ ቃለ ጉባኤ የሚከተሉትን ይይዛል፤

ሀ) የስብሰባውን ቦታ፣ ቀንና ሰዓት፣

ለ) በስብሰባው ላይ የተገኑትን አካላት ዝርዝር፤

ሐ) በስብሰባው ላይ ያልተገኙትን አባላት ዝርዝርና ያልተገኙበትን ምክንያት፣

መ) በስብሰባው ላይ የተገኙ ልሎች ሰዎች ካሉ ስማቸውንና የተገኙበትን ምክንያት፤

ሠ) ለስብሰባው የቀረበውን አጀንዳ፤

ረ) ለውይይቱ የቀረበውን ጉዳይ በአጭሩ የሚገልፅ ጽሁፍ፤

ሰ) ስብሰባው የተፈፀመበትን ሁኔታና ሰዓት፤

ሸ) ቃለ ጉባኤው ከፀደቀ በኋላ በአማካሪ ምክር ቤቱ ሰብሳቢና ፀሐፊ መፈረም ይኖርበታል፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

**፲፭. <u>ውስጥ ደንብ የማውጣት ሥልጣን</u>**

የአማካሪ ምክር ቤት ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም የውስጥ ደንብ ማውጣት ይችላል፡፡

**<u>፲፮. አዋጁ ስለሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ ከግንቦት ፮ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ

ግንቦት ፮ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም

የአዲስ አበባ ከተማ ጊዜያዊ አስተዳደር

አባሪ፩

የከተማ አማካሪ ምክር ቤት አባላት ዝርዝር እና ብዛት

| ተ.ቁ | አባላት | የሥራ ድርሻ | ብዛት |
|---|---|---|---|
| ፩ | የከተማው ከንቲባ | ሰብሳቢ | ፩ |
| ፪ | የካቢኒ አባላት | አባል | ፱ |
| ፫ | የከተማ ሥራ አስኪጅ | አባል | ፩ |
| ፬ | የከተማ ምክትል ሥራ አስኪጅ | አባል | ፩ |
| ፭ | ምክትል የቢሮ ኃላፊዎች | አባል | ፯ |
| ፮ | የከተማው አስተዳደር መሥሪያ ቤቶች ኃላፊዎች | አባል | ፰ |
| ፯ | የክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስኪያጅ ምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚ እና ቋሚ ኮሚቴ | አባል | |
| ፰ | ከቀበሌው ሁለት የነዋሪዎች ተወካይ | አባል | 280 |
| ፱ | ቀበሌ ቋሚ ኮሚቴ | አባል | 30 |
| ፩0 | የከተማ ሴቶቸ ማህበር | አባል | 50 |
| ፩፩ | የከተማ ወጣቶች ማህበር | አባል | 50 |
| ፩፪ | የሠራተኛ ማህበር | አባል | 20 |
| ፩፫ | የአዲስ አበባ ንግድ ምክር ቤት | አባል | 15 |
| ፩፬ | የኢትዮጵያ አምራች ኢንዱስትሪ ባለቤቶች ማህበር | አባል | 10 |
| ፩፭ | መምህራን ማህበር | አባል | 10 |
| ፩፮ | የሙያ ማህበራት | አባል | 10 |
| ፩፯ | አርበኞች ማህበር | አባል | ፭ |
| ፩፰ | የሲቪል ኅብረተሰብ ማህበራት | አባል | 10 |
| ፩፱ | ዩንቨርስቲና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት | አባል | ፭ |
| ፪0 | የጤና ባለሙያዎች ማህበር | አባል | ፯ |
| ፪፩ | መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች | አባል | 10 |
| | | ድምር | |

አባሪ ፪

የከተማ አማካሪ ምክር ቤት አባላት ዝርዝር እና ብዛት

| ተ.ቁ | አባላት | የሥራ ድርሻ | ብዛት |
|---|---|---|---|
| ፩ | የክፍለ ከተማው ዋና ስራ አስፈፃሚ | ሰብሳቢ | ፩ |
| ፪ | የክፍለ ከተማ ቋሚ ኮሚቴ | አባል | ፩ |
| ፫ | ከቀበሌው ሃያ ነዋሪ ተወካዮች | አባል | ፫ቱ እንደ ቀበልው ብዛት |
| ፬ | ቀበል ቋሚ ኮሚቴ | አባል | ፭ |
| ፭ | የክፍለ ከተማ መሥሪያ ቤቶች ኃላፊዎች | አባል | 30 |
| ፮ | የክፍለ ከተማ ሴቶች ማህበር ተወካዮች | አባል | 20 |
| ፯ | የክፍለ ከተማ ወጣቶች ማህበር | አባል | 20 |
| ፰ | የክፍለ ከተማው መምህራን ማህበር | አባል | 10 |
| ፱ | የአዲስ አበባ ንግድ ምክር ቤት | አባል | 10 |
| ፩0 | የሲቪል ህብረተሰብ ማህበራት | አባል | 20 |
| ፩፩ | መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች | አባል | 10 |
| | | ድምር | |

አባሪ ፫

ቀበሌ አማካሪ ምክር ቤት አባላት ዝርዝር

| ተ.ቁ | አባላት | የሥራ ድርሻ | ብዛት |
|---|---|---|---|
| ፩ | ቀበሌ ዋና ሥራ አስፈፃሚ | ሰብሳቢ | ፩ |
| ፪ | ቀበሌ ቋሚ ኮሚቴ | አባል | ፭ |
| ፫ | ቀበሌ ነዋሪ ተወካዮች | አባል | ከ300-900 |
| ፬ | የሴቶች ማህበር ተወካዮች | አባል | 20 |
| ፭ | የወጣቶች ማህበር ተወካዮች | አባል | 90 |
| ፮ | መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች | አባል | 10 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፯ | የመምህራን ተወካዮች | አባል | 20 |
| ፰ | የሕክምና ባለሙያዎች ተወካዮች | አባል | 10 |
| ፱ | ቀበሌ የትምህርት ዴስክ | አባል | 15 |
| ፩0 | ቀበሌ የትምህርት አመራር ተወካዮች | አባል | 20 |
| ፩፩ | የሲቪል ህብረተሰብ ማህበራት | አባል | 15 |
| ፩፪ | የአካባቢ ልማት ማህበር | አባል | 20 |
| ፩፫ | የእድር አመራሮች | አባል | የሁሉም እድሮች |
| ፩፬ | ቀበሌ የልማት ኮሚቴ | አባል | |
| | | ድምር | እስከ 500 |

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ፷፬/፪ሺ፲፩

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስትና በተሻሻለው ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ (እንደተሻሻለ) የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር በአግባቡ መወጣት የሚያስችል የአደረጃጀት ማሻሻያ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የከተማው አስተዳደር ለነዋሪው የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች በእኩልነት፣ በግልጽነትና በፍትሀዊነት መርህ መሰረት ለመስጠት እንዲችል የከተማ አስተዳደሩን አስፈፃሚ አካላት በተገቢው ማደራጀት በማስፈለጉ፤

በሀገራችን ብሎም በከተማችን እየተካሄደ ያለውን ለውጥ ውጤታማ፣ ዘላቂና ተቋማዊ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ (እንደተሻሻለ) አንቀጽ ፲፬ ንዑስ አንቀጽ (፩) (ሀ) መሰረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ ድንጋጌ

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን እንደገና ለማደራጀት፤ ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ፷፬/፪ሺ.ህ፲፩ ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩. "ከተማ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤

፪. "የከተማው አስተዳደር" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፫. "ከንቲባ" ማለት በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ (እንደተሻሻለ) አንቀፅ ፪ ንዑስ አንቀፅ (፫) የተመለከተውና በቻርተር አዋጁ አንቀፅ ፳፩ የተመለከቱት ስልጣንና ተግባር ያሉት የከተማውን አስተዳደር የሚመራ ዋና ስራ አስፈፃሚ ነው፤

፬."ቻርተር" ማለት የተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ (እንደተሻሻለ) ነው፤

፭."ካቢኔ" ማለት በከንቲባው አቅራቢነት በከተማው ምክር ቤት የሚሾሙ አባላት ያሉት አስፈጻሚ አካል ነው፤

፮."የከተማ ስራ አስኪያጅ" ማለት በቻርተሩ አንቀፅ ፳፬ የተመለከቱት ስልጣንና ተግባር ያሉት ነው፤

፯. "ክፍለ ከተማ" ማለት በቻርተሩ አንቀፅ ፪ ንዑስ አንቀፅ (፭) የተመለከተው የከተማው ሁለተኛ ደረጃ የአስተዳደር እርከን ነው፤

፰."ወረዳ" ማለት የክፍለ ከተማ አካል የሆነ የከተማው ሶስተኛ ደረጃ የአስተዳደር እርከን ነው፤

፱."የክፍለ ከተማ ዋና ስራ አስፈፃሚ፣ የክፍለ ከተማ ስራ አስኪያጅና የክፍለ ከተማ ቋሚ ኮሚቴ" ማለት እንደቅደም ተከተላቸው በቻርተሩ አንቀጽ ፴፬ ፣ ፴፯ እና ፴፮ የተመለከቱት አካላት ናቸው፤

፲."የወረዳ ዋና ስራ አስፈፃሚ፣ የወረዳ ቋሚ ኮሚቴ፣ የወረዳ ስራ አስኪያጅ" ማለት በቻርተሩ አንቀፅ ፴፰ ንዑስ አንቀፅ (፪) የተመለከቱት አካላት ናቸው፤

፲፩. "ቋሚ ኮሚቴ" ማለት በክፍለ ከተማና በወረዳ ደረጃ በዋና ስራ አስፈጻሚ አቅራቢነት በክፍለ ከተማ ወይም በወረዳ ምክር ቤት የሚሾሙ አባላት ያሉት የከተማ አስተዳደሩን ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ፣ ህጎችና እቅዶችን የሚያስፈጽም አካል ነው፤

፲፪. ልሎች ትርጉሞች ካቢኔ በሚያወጣው የአሰራርና አደረጃጀት ደንብ የሚቀመጥ ይሆናል፡፡

**፫. <u>የጾታ አገላለጽ</u>**

በዚህ አዋጅ ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>ስለ አስፈፃሚ አካላት</u>

## <u>ዘርፍ አንድ</u>

## <u>ስለአደረጃጀት</u>

**፬. <u>አደረጃጀት</u>**

በቻርተሩ የተደነገገው አደረጃጀት እንደተጠበቀ ሆኖ የከተማውን ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና ሕጎች የሚያስፈጽሙ አስፈጻሚ አካላት፡-

፩. ከንቲባ፤

፪. ምክትል ከንቲባ፤

፫. ካቢኔ፤

፬. የከተማ ስራ አስኪያጅ፤

፭. የክፍለ ከተማ ዋና ስራ አስፈጻሚ፤

፮. የክፍለ ከተማ ቋሚ ኮሚቴ፤

፯. የወረዳ ዋና ስራ አስፈጻሚ፤

፳. የወረዳ ቋሚ ኮሚቴ፡፡

## ዘርፍ ሁለት

## ስለከንቲባ፣ ስለምክትል ከንቲባ፣ ስለካቢኔ፣ ስለከተማ ሥራ አስኪያጅ

**፩. ስለከንቲባ**

በቻርተሩ አንቀጽ ፳፩ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከንቲባው፡-

ሀ.ተጠሪነታቸው በቀጥታ ለእርሱ የሆኑ አስፈፃሚ አካላትን በበላይነት ይመራል፤ያስተባብራል፤ ይቆጣጠራል፤

ለ. ለስራው ቅልጥፍና አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ከስልጣኑ በከፊል ለምክትል ከንቲባ፣ በቀጥታ ለራሱ ተጠሪ ለሆነ ኃላፊ ወይም አስፈፃሚ አካል በውክልና ሊሰጥ ይችላል፤

ሐ. በአስፈፃሚ አካላት ወይም በኃላፊዎቻቸው የተሰጡ ውሳኔዎች፣ የወጡ መመሪያዎችና የተሰጡ ትእዛዞች ህግን የሚፃረሩ መሆናቸውን ሲያረጋግጥ ይሽራል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እንዲስተካከሉ መመሪያ ይሰጣል፡፡

**፪. ስለምክትል ከንቲባ**

የምክትል ከንቲባ ተጠሪነት፣ ስልጣንና ተግባር በቻርተሩ አንቀፅ ፳፪ የተመለከተው ይሆናል፡፡

**፫. ስለካቢኔ**

የካቢኔው ሥልጣንና ተግባራት በቻርተሩ አንቀፅ ፳፫ የተመለከተው ይሆናል፡፡

**፳. ስለካቢኔ አባላት**

፩. የካቢኔው አባላት የሚከተሉት ናቸው፡-

ሀ. ከንቲባ፣

ለ. ምክትል ከንቲባ፣

ሐ. በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፩ ከተራ ቁጥር ፪ እስከ ፲፯ የተቋቋሙትን አስፈፃሚ አካላት የሚመሩ ኃላፊዎች፣

መ. እንደ አስፈላጊነቱ በከንቲባ የሚሰየሙ ልሎች አባላት ይኖሩታል፡፡

፪. የካቢኔ አባል በካቢኔው ስብሰባ ላይ ሊገኝ በማይችልበት ጊዜ ምክትሉ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ምክትሎች ሲኖሩ በሹመት ቅድሚያ ያለው ወይም በግልጽ ተለይቶ ውክልና የተሰጠው በካቢኔው ስብሰባ ላይ በምትክ አባልነት በመገኘት ይመክራል፤ ድምፅ ይሰጣል፡፡

**፱. ስለካቢኔ የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት**

የካቢኔው የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ካቢኔው በሚያወጣው ደንብ መሰረት ይወሰናል፡፡

**፲. ስለከተማ ስራ አስኪያጅ**

የከተማው ስራ አስኪያጅ ተጠሪነቱ ለከንቲባው ሆኖ በዚህ አዋጅ፡-

ሀ. ተጠሪነታቸው በቀጥታ ለእርሱ የሆኑ አስፈፃሚ አካላትን በበላይነት ይመራል፤ያስተባብራል፤ ይቆጣጠራል፤

ለ. ለስራው ቅልጥፍና አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ከስልጣኑ በከፊል ለምክትል ሥራ አስኪያጅ፣ በቀጥታ ለራሱ ተጠሪ ለሆነ ኃላፊ ወይም አስፈፃሚ አካል በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

## ክፍል ሶስት

## ስለአስፈፃሚ አካላት መቋቋምና ተጠሪነት

### ፲፩. የአስፈፃሚ አካላት መቋቋም

የሚከተሉት አስፈፃሚ አካላት በዚህ አዋጅ እንደገና ተቋቁመዋል፤

፩. የከንቲባ ጽህፈት ቤት፤

፪. የሰላምና ጸጥታ አስተዳደር ቢሮ፤

፫. የዐቃቤ ሕግ ቢሮ፤

፬. የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ፤

፭. የፋይናንስ ቢሮ፤

፮. የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ቢሮ፤

፯. የኮንስትራክሽን ቢሮ፤

፰. የቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ፤

፱. የትራንስፖርት ቢሮ፤

፲. የንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ፤

፲፩. የሥራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዝ ልማት ቢሮ፤

፲፪. የጤና ቢሮ፤

፲፫. የትምህርት ቢሮ፤

፲፬. የወጣቶችና በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ቢሮ፤

፲፭. የሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮ፤

፲፮. የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ፤

፲፯. የባህል፣ ኪነ ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ፤

፲፰. የፕላንና ልማት ኮሚሽን፤

፲፱. የኢንቨስትመንት ኮሚሽን፤

፳. የእሳትና አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን፤

፳፩. የአካባቢ ጥበቃና አረንጓዴ ልማት ኮሚሽን፤

፳፪. የአርሶ አደር እና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን፤

፳፫. የስፖርት ኮሚሽን፤

፳፬. የገቢዎች ባለስልጣን፤

፳፭. የመንገዶች ባለስልጣን፤

፳፮. የውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን፤

፳፯. የመሰረተ ልማት ቅንጅት፣ ግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን፤

፳፰. የትምህርትና ስልጠና ጥራት፣ ሙያ ብቃትና ምዘና ማረጋገጫ ባለስልጣን፤

፳፱. የምግብ፣መድሃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን፤

፴. የመንግስት ሕንፃና ንብረት አስተዳደርባለሥልጣን፤

፴፩. የመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለስልጣን፤

፴፪. የትራንስፖርት ባለስልጣን፤

፴፫. የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን፤

፴፬. የትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ፤

፴፭. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናኤጀንሲ፤

፴፮. የሳይንስና ቴክኖሎጂ ኤጀንሲ፤

፴፯. የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ፤

፴፰. የመሬት ልማትና ከተማ ማደስ ኤጀንሲ፤

፴፱. የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ ኤጀንሲ፤

፵. የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ኤጀንሲ፤

፵፩. የህብረት ስራ ማህበራት ኤጀንሲ፤

፵፪. የምግብ ዋስትና እና ልማታዊ ሴፍቲኔት ኤጀንሲ፤

፵፫. የወሳኝ ኩነት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ፤

፵፬. የተፋሰስና አረንጓዴ አካባቢዎች ልማት ኤጀንሲ፤

፵፭.የህዝብ ቅሬታና አቤቱታ ማስተናገጃ ጽህፈት ቤት፤

፵፮. የመሬት ባንክና ማስተላለፍ ጽህፈት ቤት፤

፵፯. የመሬት ይዞታ አስተዳደር ጽህፈት ቤት፤

፵፰. የግንባታ ዲዛይን ጽህፈት ቤት፤

፵፱. የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ህዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ጽህፈት ቤት፤

፶. የኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከያና መቆጣጠርያ ጽህፈት ቤት፤

፶፩.የቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን፤

፶፪. የኮተቤ ሜትሮፖሊታን ዩኒቨርሲቲ፤

፶፫. መለስ ዜናዊ የስራ አመራር ኢንስቲትዩት፤

፶፬. ጉለሌ የዕፅዋት ማዕከል፤

፶፭. የአዲስ ዙ ፓርክ፡፡

**፲፪. የአስፈፃሚ አካላት ተጠሪነት**

፩. የሚከተሉት አስፈፃሚ አካላት ተጠሪነት ለከንቲባ ይሆናል፡-

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፩ ከተራ ቁጥር ፪እስከ ፲፯ የተጠቀሱት ቢሮዎች፤

ለ) የከንቲባ ጽህፈት ቤት፤

ሐ) የፕላንና ልማት ኮሚሽን፤

መ) የገቢዎች ባለስልጣን፤

ሠ) የመንገዶች ባለስልጣን፤

ረ) የውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን፤

ሰ) የመሰረተ ልማት ቅንጅት፣ ግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን፤

ሸ) የትምህርትና ስልጠና ጥራት፣ ሙያ ብቃትና ምዘና ማረጋገጫ ባለሥልጣን፤

ቀ) የምግብ፣ መድሃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን፤

በ) የአካባቢ ጥበቃና አረንጓዴ ልማት ኮሚሽን፤

ተ) የኢንቨስትመንት ኮሚሽን፤

ቸ) የአርሶ አደር እና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን፤

ኀ) የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ፤

ነ) የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲ፤

ኘ) ኮተቤ ሜትሮፖሊታን ዩኒቨርሲቲ፤

አ) የህዝብ ቅሬታና አቤቱታ ማስተናገጃ ጽህፈት ቤት፤

ከ) የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ህዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ጽህፈት ቤት፡፡

፪. የሚከተሉት አስፈፃሚ አካላት እና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተጠሪነት ለከተማ ሥራ አስኪያጅ ይሆናል፡-

ሀ) የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ኤጀንሲ፤

ለ) የአዲስ ዙ ፓርክ፤

ሐ) ቄራዎች ድርጅት፤

መ) የከነማ ፋርማሲዎች ድርጅት፤

ሠ) የሸገር የብዙሀን ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት፤

ረ) የኤግዝቢሽን ማዕከልና የገበያ ልማት ድርጅት

ሸ) አንበሳ የከተማ አውቶቡስ አገልግሎት ድርጅት፤፤

፫. የሚከተሉት አስፈፃሚ አካላት ተጠሪነት ለሰላምና ፀጥታ አስተዳደር ቢሮ ይሆናል፡-

ሀ) የእሳትና አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን፤

ለ) የወሳኝ ኩነት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ፡፡

፬. የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላት ተጠሪነት ለፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ ይሆናል፡-

ሀ) የሳይንስና ቴክኖሎጂ ኤጀንሲ፤

ለ) መለስ ዜናዊ የስራ አመራር ኢንስቲትዩት፡፡

፭. የሚከተሉት አስፈፃሚ አካላት ተጠሪነት ለፋይናንስ ቢሮ ይሆናል፡-

ሀ) የመንግስት ሕንፃና ንብረት አስተዳደር ባለሥልጣን፤

ለ) የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለስልጣን፤

ሐ) የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ ኤጀንሲ፡፡

፮. የኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽህፈት ቤት ተጠሪነት ለጤና ቢሮ ይሆናል፡፡

፯. የስፖርት ኮሚሽን ተጠሪነት ለወጣቶችና በጎ- ፈቃድ ማስተባበሪያ ቢሮ ይሆናል፡፡

፰. የሚከተሉት አስፈፃሚ አካላት ተጠሪነት ለመሬት ልማትና ማኔጅመንት ቢሮ ይሆናል፡-

ሀ) የመሬት ልማትና ከተማ ማደስ ኤጀንሲ፤

ለ) የመሬት ባንክና ማስተላለፍ ጽህፈት ቤት፤

ሐ) የመሬት ይዞታ አስተዳደር ጽህፈት ቤት፡፡

፱. የሚከተሉት አስፈፃሚ አካላት ተጠሪነት ለቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ ይሆናል፡-

ሀ) የቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን፤

ለ) የግንባታ ዲዛይን ጽህፈት ቤት፤

ሐ) የግንባታ ኢንተርፕራይዝ በመንግስት የልማት ድርጅትነት ሲቋቋም ተጠሪነቱ ለቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮይሆናል፡፡

፲. የምግብ ዋስትናና ልማታዊ ሴፍቲኔት ኤጀንሲ ተጠሪነት ለስራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዝ ልማት ቢሮ ይሆናል፡፡

፲፩. የሚከተሉት አስፈፃሚ አካላት ተጠሪነት ለትራንስፖርት ቢሮ ይሆናል፡-

ሀ) የትራንስፖርት ባለስልጣን፤

ለ) የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን፤

ሐ) የትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ፡፡

፲፪. የሚከተሉት አስፈጻሚ አካላትና የመንግስት ልማት ድርጅት ተጠሪነታቸው ለንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ይሆናል፡-

ሀ) የህብረት ሥራ ማህበራት ኤጀንሲ፤

ለ) የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ክላስተር ልማት ኮርፖሬሽን፡፡

፲፫. የሚከተሉት አስፈፃሚ አካላት ተጠሪነታቸው ለአካባቢ ጥበቃና አረንጓዴ ልማትኮሚሽን ይሆናል፡-

ሀ) ጉለሌ የዕፀዋት ማዕከል፤

ለ) የተፋሰስና አረንጓዴ አካባቢዎች ልማት ኤጀንሲ፡፡

፲፬. የሲኒማ ቤቶች ድርጅት ተጠሪነት ለባህል፣ ኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ይሆናል፡፡

**፲፫. <u>የአስፈፃሚ አካላት አደረጃጀት ከክፍለ ከተማ ጋር ያላቸው ተዋረዳዊ ግንኙነት</u>**

፩.የእያንዳንዱ አስፈፃሚ አካል ኃላፊ፣ እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ኃላፊ ወይም ኃላፊዎች፣ ልሎች አግባብ ያላቸው የስራ ክፍሎችና ለስራው የሚያስፈልጉ ሰራተኞች የሚኖረው ሆኖ ይደራጃል፤

፪. አንድ አስፈፃሚ አካል ከሌላ አስፈፃሚ አካል ጋር እንደ አስፈላጊነቱ ደጋፊ ስራ ሂደት አገልግሎቶችን በጋራ ሊጠቀሙ ይችላሉ፡፡ ዝርዝሩ የከተማው ካቢኔ በሚያፀድቀው መዋቅራዊ አደረጃጀት መሰረት በከንቲባው በሚወጣ መመርያ ይወሰናል፤

፫. የየክፍለ ከተማው ጽህፈት ቤት ወይም የሌላ አስፈጻሚ የስራ ክፍል፡-

ሀ) በቻርተር አዋጁና በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሰረት ተጠሪነታቸው ለክፍለ ከተማው ዋና ስራ አስፈፃሚ ነው፤

ለ) ከከተማው ቢሮ ወይም ሌላ አስፈፃሚ አካል በእቅድ ዝግጅት፣ ክዋኔ ክትትልና ግምገማ በትስስር ይሰራል፤

ሐ) እንደየአግባቡ የሰራተኛ የውስጥ ዝውውር የደረጃ ዕድገት፣ አመዳደብ በልሎች ቴክኒካዊና ሙያዊ ጉዳዮች በየክፍለ ከተማው በተዋረድ በስራው መስክ ከተደራጀው ጽህፈት ቤት ወይም ሌላ የስራ ክፍል ጋር ቀጥተኛና መደበኛ ግንኙነት በማድረግ ይሰራል፡፡

**<u>፲፩. የአስፈፃሚ አካላት ኃላፊዎች ተጠሪነትና ሃላፊነት</u>**

፩.እያንዳንዱ የካቢኔ አባል ተጠሪነቱ ለከንቲባው ሆኖ፡-

ሀ) የሚመራውን አስፈፃሚ አካል ስለሚመለከቱ ስራዎች፣ ፕሮግራሞች፣ ፕሮጀክቶችና ህጎች አፈጻጸም ተጠሪነቱ ለካቢኔው ይሆናል፤

ለ) ኃላፊ ለሆነበት አስፈፃሚ አካል የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር በስራ ላይ ያውላል፤

ሐ) ኃላፊ ለሆነበት አስፈፃሚ አካል በተፈቀደው በጀትና የስራ ፕሮግራም መሰረት ገንዘብ ወጭ ያደርጋል፤

መ) ኃላፊ የሆነበትን አስፈፃሚ አካል ይመራል፤ ይወክላል፡፡

፪. የእያንዳንዱ ሌላ አስፈፃሚ አካል ኃላፊ፡-

ሀ) የሚመራውን አስፈጻሚ አካል ስለሚመለከቱ ስራዎች፣ ፕሮግራሞችና ህጎች አፈጻጸም ተጠሪነቱ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፪ ለተመለከተው አስፈጻሚ አካል ወይም የስልጣን አካል ይሆናል፤

ለ) ኃላፊ ለሆኑበት አስፈጻሚ አካል የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር በስራ ላይ ያውላል፤

ሐ) ኃላፊ ለሆነበት አስፈፃሚ አካል በተፈቀደው በጀትና የስራ ፕሮግራም መሰረት ገንዘብ ወጭ ያደርጋል፤

መ) ኃላፊ የሆነበትን አስፈጻሚ አካል ይመራል፤ ይወክላል፡፡

**<u>ክፍል አራት</u>**

## የአስፈፃሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር

፲፰. የወል ሥልጣንና ተግባር

እያንዳንዱ አስፈጻሚ አካል፡-

፩. እቅድን በሚመለከት፡-

ሀ) በሚደርሰው መመርያ መሰረት እቅዶችን ያዘጋጃል፤ ሲጸድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፤

ለ)የሚመለከቱትን ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ስራ ላይ ያውላል፤

ሐ) ለእቅዱ አተገባበር አስፈላጊ የሆኑትን ተግባራት በወቅቱ ይፈፅማል፤ ያስፈጽማል፤

መ) የስታትስቲክስ መረጃዎች ያሰባስባል፤ ያቀነባብራል፡፡

፪. በስራው መስክ ፖሊሲ ወይም የህግ ረቂቅ ያመነጫል፤ በጀት ያዘጋጃል፤ ሲፈቀድም በስራ ላይ ያውላል፤ ይቆጣጠራል፤ ያስተዳድራል፤

፫. በስራው መስክ፡-

ሀ) መስሪያ ቤቱን የሚመለከቱ ፖሊሲዎች፣ ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

ለ) ጥናት ያጠናል፤ በቴክኖሎጂ የታገዘ የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊ ያደርጋል፤

ሐ) ተገቢውን ስልጠና ይሰጣል ወይም እንዲሰጥ ያደርጋል፤

መ) በህግ መሰረት ውሎችንና ስምምነቶችን ያደርጋል፤

ሠ) በህግ መሰረት መመርያዎችን ያወጣል፤ በስራ ላይ ያውላል፡፡

፬. ስለስራው ክንዋኔ በወቅቱ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያቀርባል፤

፭. የመስሪያ ቤቱን ድርጅታዊ መዋቅር አግባብ ላለው አካል አቅርቦ ያፀድቃል፤

፮. የሚያዘጋጃቸው ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ የልማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የሴቶችንና የወጣቶችን ጉዳይ እንዲያካትቱ መደረጋቸውን ያረጋግጣል፤

፯. የአካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን፣ ለማህበራዊ ችግሮች ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች እና በደማቸው ውስጥ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ያለባቸው ሰዎች በሃላፊነቱ ክልል የእኩል እድል ተጠቃሚና ሙሉ ተሳታፊ የሚሆኑበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

፰. አግባብ ባለው ህግ መሰረት አስፈላጊ የሆኑ ሰራተኞችን ይቀጥራል፤ ያዘዋውራል፤ይመድባል፤ ያሰናብታል፤ ያስተዳድራል፤

፱. ተጠሪ የተደረጉለትን አስፈፃሚ አካላት አፈፃፀም በበላይነት ይመራል፤ ያስተባብራል፤አደረጃጀቶቻቸውን፣ የስራ ፕሮግራሞቻቸውን እና በጀቶቻቸውን መርምሮ ለሚመለከተው አካል እንዲቀርብ ያደርጋል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

፲. ለሚሰጠውአገልግሎት በህግ ሲፈቀድለት የአገልግሎት ክፍያይሰበስባል፤

፲፩. እንደየስራ ባህሪያቸው ህብረተሰቡን ባማከለ፣ ባሳተፈ እና ተጠቃሚ የሚያደርጉ ስራዎችን ያከናውናል፤

፲፪. የዘላቂ ልማት፣ የህብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፈቃድ ስራዎችን ለማበረታታት ሲፈቀድ ፈንድ ሊያቋቁም ይችላል፤

፲፫. በከንቲባው ወይም አግባብ ባለው ተጠሪ ኃላፊ የሚሰጡትን ልሎች ተያያዥ ተግባራትን ያከናውናል፤

፲፬. በዚህ አዋጅ የተመለከቱትንና ልሎች በህግ የተሰጡትን ተግባሮች ያከናውናል፤

፲፭. ለስራው ቅልጥፍና አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ከስልጣንና ተግባሩ በከፊል ለሌላ አስፈፃሚ አካል በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

**፲፮. ከንቲባ ጽህፈት ቤት**

ጽህፈት ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩. ለካቢኔ ስብሰባ የሚቀርቡ አጀንዳዎችን አስፈላጊነት አይቶ ውሳኔ እንዲያገኙ ያደርጋል፤ የካቢኔ ስብሰባ ቃለ-ጉባዔዎች፣ ውሳኔዎችና ሰነዶች በሚገባ ተመዝግበው እንዲጠበቁ ያደርጋል፤

፪. የከንቲባውን የዕለት ተዕለት መርሀ ግብሮችን ይከታተላል፤ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፫. የከተማ አስተዳደሩን የስራ እንቅስቃሴ የሚመለከቱ መረጃዎችን በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች በማሰራጨት የሕብረተሰቡን ተሳትፎ ያረጋግጣል፤ የተለያዩ የማስተዋወቂያ ዘዴዎችን በማዘጋጀት የከተማውን መልካም ገጽታ ይገነባል፤

፬. በከተማው አስተዳደር በየደረጃው ለሚከናወነው የመንግስት መረጃ ሥርጭትና ልውውጥ ሥራ አቅጣጫ በመስጠት ያስተባብራል፤

፭. ከልሎች የውጭ ሀገር ከተሞች፤ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር በጋራ ጉዳዮች የውጭ ግንኙነት ሥራዎችን ያስተባብራል፤

፮. ለከንቲባውና በከንቲባው ሲታዘዝ ለከተማው አስተዳደር ባለሥልጣናት የፕሮቶኮል አገልግሎት ይሰጣል፤ የውጭ ግንኙነት ስራዎችን ያስተባብራል፤

፯. በከንቲባው የሚሾሙ ወይም የሚሸለሙ ዕጩዎችን የሹመትና የሽልማት ደብዳቤ ያዘጋጃል፤ የሹመት ወይም የሽልማት ሂደቱን ያስፈጽማል፤

፰. የከተማው አስፈፃሚ አካላትን እቅድ እና የእቅዱን አፈጻጸም ይከታተላል፤ ይገመግማል፤ ግብረ-መልስ ይሰጣል፣ ወቅታዊ መረጃ ለከንቲባው ያቀርባል፤

፱. የሠላማዊ ሠልፍ ጥያቄን ከሰላምና ፀጥታ አስተዳደር ቢሮ ጋር በመነጋገር ያስተናግዳል፤

፲. ተጠሪነታቸው ለከንቲባው የሆኑ አስፈጻሚ አካላትን ከከንቲባው በሚሰጥ ውክልና መሰረት ያስተባብራል፤ ይከታተላል፤ ተገቢውን ሪፖርት ለከንቲባው ያቀርባል፤

፲፩. የካቢኔ ጉዳዮችን ስራ ያከናውናል፤

፲፪. በከንቲባው የሚሰጡ ልሎች ተዛማች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

**፲፯. የሰላምና ጸጥታ አስተዳደር ቢሮ**

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩. የእሳትና አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽንን እና የወሳኝ ኩነት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲን በበላይነት ይመራል፤ ያስተባብራል፤ ይቆጣጠራል፤

፪. የብሔራዊ የፀጥታና የሰላም ፖሊሲን መሠረት በማድረግ የከተማውን የአስተዳደርና ፀጥታ ጉዳይ ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘበ ከተማ አቀፍ ፖሊሲ ይቀርፃል፤ እስትራቴጂ ይነድፋል፤ ህግ ያመነጫል፤ ሲጸድቅም ተግባራዊ መሆኑን ይከታተላል፤ ያረጋግጣል፤

፫. በፀጥታ ጉዳዮች የከተማው አስተዳደር ዋና የፀጥታ አማካሪ ሆኖ ይሰራል፤ ለፀጥታና ሰላም አስጊ የሆኑ ጉዳዮች ላይ ተገቢ የሆነ አፋጣኝ እርምጃ ይወስዳል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም እንደ አግባብነቱ በቢሮው ወይም ከሚመለከተው አካል ጋር በመቀናጀት የእርምት እርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል፤

፬. የግጭት መንስዔዎችን በጥናት ይለያል፣ ግጭት እንዳይከሰት ይከላከላል፤ ሲከሰትም ባህላዊና ዘመናዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎችን በመጠቀም ይፈታል፤

፭. በከተማው ልዩ ልዩ ሀይማኖትና ቤተ-እምነት ተከታዮች መካከል ሰላምና መከባበር እንዲሰፍን ለማድረግና ግጭትንም ለመከላከል እንዲቻል አግባብነት ካላቸዉ የፌደራልም ሆነ የከተማው አስተዳደር መንግሥት አካላት፣ የኃይማኖት ተቋማትና ከልሎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይሠራል፤ የህግ የበላይነት እንዲረጋገጥ ያደርጋል፤

፮. በግጭት መከላከል፣ አያያዝም ሆነ አፈታት፣ በነዋሪው ደህንነት፣ ሰላም እና ፀጥታ አጠባበቅ ጉዳዮች ዙሪያ አግባብነት ካላቸው የፌደራል፣ የክልል፣ የከተማ አስተዳደር እና ልሎች አካላት ጋር የሥራ ግንኙነቶችን ያደርጋል፤ እንደአግባብነቱ ችግሮችን በተናጠል ወይም በጋራ ይፈታል፤

፯. ህግና ስርዓት መከበሩንና የህብረተሰቡ ሰላምና ደህንነት መጠበቁን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ ያረጋግጣል፤

፰. ህገ-መንግስታዊ ስርዓቱን በኃይል ለማፍረስና በስውር የህዝቡንና የመንግስትን ጥቅም ጉዳት ላይ ለመጣል የሚንቀሳቀሱ ግለሰቦችን፣ ቡድኖችንና ድርጅቶችን በመከታተል ነዋሪውንና ልሎች የሚመለከታቸውን አካላት በማሳተፍ ይከላከላል፤ ይቆጣጠራል፤

፱. የህብረተሰቡን ተሳትፎ በማጎልበት እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ወንጀል፣ የደንብ መተላለፍ እና ተያያዥ ሕገ ወጥ ተግባራት እንዳይፈፀሙ የሚመለከታቸው አካላትን በማስተባበር ይከላከላል፤ ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፣ እንዲወሰድ ያደርጋል፣ ተፈፃሚነቱን ያረጋግጣል፤ ይቆጣጠራል፤

፲. የህግ አስከባሪ አካላት በሰብዓዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብቶች አያያዝና አጠባበቅ፤ በህገ-መንግስታዊ እና በወቅታዊ ጉዳዩች ዙሪያ አቅማቸውን በመገንባት የህዝብ አገልጋይነት ሚናቸውን እንዲወጡ ያደርጋል፤

፲፩. ከጸጥታ አስተዳደር ጋር የተያያዙ ቅሬታ እና አቤቱታዎችን ይቀበላል፤ ይመረምራል፤ እንዳግባብነቱ እራሱ ወይም በተጠሪ ተቋማት ወይም በልሎች በሚመለከታቸው አካላት ቅሬታዎቹንና አቤቱታዎቹን መልስ እንዲያገኙ ያደርጋል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

፲፪. በልሎች ህጎችና አሰራሮች ያሉ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የጦር መሳሪያ ፈቃድ በሚመለከት የድጋፍ ደብዳቤ ይሰጣል፤ መረጃ ያደራጃል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል፤

፲፫. በከተማው የጦር መሳሪያ አጠቃቀምና አያያዝ በተመለከተ የምዝገባ አፈፃፀምን ይከታተላል፤

፲፬. በከተማው የሀይማኖት ተቋማት፣ ሀይማኖታዊ ማህበራትን እና ብዙሃን ማህበራት መረጃ ያደራጃል፤ ይከታተላል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተቀናጅቶ ይሰራል፤ ህገ-ወጥ ተግባራት ላይ በተሰማሩ አካላት ላይ ህጋዊ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል ወይም እዲወሰድ ያደርጋል፤

፲፭. በፌደራል መንግስት የተመዘገቡ እና ፈቃድና እድሳት የተሰጣቸውን የሀይማኖት ተቋማት እና የብዙሀን ማህበራት ይመዘግባል፤ በከተማው ህገ-መንግስቱንና ልሎች ህጎችን አክብረው ስለመስራታቸው ይከታተላል፤

፲፮.የማህበረሰብ አቀፍ ፖሊስ አገልግሎት በህብረተሰብ ተሳትፎ ላይ እና በመስፈርቱ መሰረት ስለመከናወኑ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል፤

፲፯. የፀጥታ አስተዳደር እና ልሎች ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮች ላይ ለተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎችን ይሰጣል ወይም እንዲሰጥ ያደርጋል፤

፲፰. የፀጥታ ሁኔታ መረጃ ይሰበስባል፣ ያደራጃል፣ ጥናትና ምርምር ያደርጋል፣ ውጤቱን ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፤ በሚሰጠው ውሳኔ መሠረት ተግባር ላይ እንዲውል ያደርጋል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤

፲፱. የመንግስት፣ የግል ተቋማትን እና ነዋሪውን በአካባቢያቸው የፀጥታ፣ ሰላም እና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ የሚሳተፉበትን ስልት ይቀይሳል፤ ተቋማዊ አደረጃጀት ይፈጥራል፤ ያስተባብራል፤

፳. በከተማው ክልል ውስጥ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች በሚያጋጥሙበት ወቅት ከልሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የጉዳቱ መጠን እንዳይባባስ አስፈላጊውን ሁሉ ያደርጋል፤ በአደጋው ክልል ውስጥ የሚገኙ ማህበረሰብ አካላት የህይወትና የንብረት ደህንነት እንዲጠበቅ ያደርጋል፤

፳፩. የሰላማዊ ሰልፍ፣ በአደባባይ ላይ ለሚከናወኑ የተለያዩ ፕሮግራሞች እና ስብሰባዎች ከንቲባውን ያማክራል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

፳፪. የመንግስትና የግል ተቋማት እንዲሁም የአካባቢ ቅጥር ጥበቃ የሚመሩበትን ስርዓት ስልት ይቀይሳል፤ መስፈርት ያወጣል፣ በዚሁ መሠረት ስለመፈጸሙ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

፳፫. የፀጥታ ምክር ቤት አደረጃጀትና አሰራር አጥንቶ ለከንቲባው ያቀርባል፤ ሲወሰንም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፳፬. ከሚመለከተው አካል ጋር በመተባበር ሕገ-ወጥ ግንባታ፣ በሕገ-ወጥ መንገድ መሬትን መያዝ፣ በሕገ-ወጥ መንገድ የመሬት ይዞታ ማስፋፋትን፣ ሕገ-ወጥ ማስታወቂያዎችን መለጠፍ፤ ሕገ-ወጥ የመንገድ ላይ ንግድ፣ የእንስሳትና የስጋ ዝውውር፣ ዕርድ፣ ሽያጭ፣ ልሎች የደንብ መተላለፍ ተግባራትን ይከላከላል፤ ይቆጣጠራል፣ ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፤ ያስወስዳል፤

፳፭. በህብተሰብ ተሳትፎ አቀናጅቶ የመከላከልና የመቆጣጠር ስራ በመስራት ደንብ መተላለፍን እንዲቀንስ ያደርጋል፤

፳፮. አግባብ ባለው ህግ መሰረት በገንዘብ የሚያስቀጡ የደንብ መተላለፍ ተግባራትን የቅጣት ገቢ ይሰበስባል፣ ህገወጥ ድርጊት የተፈጸመባቸዉን ንብረቶች ይወርሳል፣ ይሸጣል ወይም መሸጥ ያልቻሉትን ያስወግዳል፤

፳፮. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የመከላከልና የቁጥጥር ኦፊሰሩን፣ ባለሙያዉን፣ አመራሩን ከማዕከል እስከ ንኡስ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት በመመደብ ወይም በማዘዋወር ሊያሰራ ይችላል፤

፳፰. ፓራ ሚሊተሪ ሰራተኞችን ካቢኔው በሚያወጣው ደንብ መሰረት ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፡፡

**፲፰. <u>የዐቃቤ ሕግ ቢሮ</u>**

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩. በሕግ ጉዳዮች የከተማው አስተዳደር ዋና አማካሪና ተወካይ ሆኖ ይሠራል፤

፪. የከተማውን የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራምን ያቅዳል፤ ያስተባብራል፤ በእቅዱ መሰረት መከናወኑን ያረጋግጣል፤ ይከታተላል፤ ክፍተቶችን እየለየ ድጋፍ ያደርጋል፤

፫. የሰብዓዊ መብት የድርጊት መርሀ ግብር ይተገብራል፤ አስፈፃሚ አካላት በዋና ዕቅዳቸው ማካተታቸውን ያረጋግጣል፤ ይደግፋል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤ ለሚመለከታቸው አካላት ሪፖርት ያቀርባል፤

፬. ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውርን ለመከላከል ፕሮግራሞችን ይቀርፃል፤ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፤ ይመራል፤ ያስተባብራል፤ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤

፭. የከተማው አስተዳደር መስሪያ ቤቶች የአስተዳደሩና የነዋሪው መብትና ጥቅም ወኪል ሆኖ ይከራከራል፣ ያስከብራል፣ የሚከበሩበትን ሂደት ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

፮. የከተማው አስተዳደር የመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚያደርጉትን ውል እንደአስፈላጊነቱ ይመረምራል፤ ሕጋዊነታቸውን ያረጋግጣል፤ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፤ ተገቢው የጥንቃቄ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል ወይም ይወስዳል፤

፯. የከተማው አስተዳደር የመንግስት መስሪያ ቤትን እና የመንግስት ልማት ድርጅቶችን በመወከል በማንኛውም የዳኝነት ሥልጣን በተሰጠው አካል ወይም በግልግል ጉባኤ በመቅረብ ክስ ይመሰርታል፣ መልስ ይሰጣል፣ የጣልቃ ገብ፣ የመቃወም እና የይግባኝ አቤቱታ ያቀርባል፤

፰. የከተማ አስተዳደሩን የህዝብ መብትና ጥቅም ለማስከበር አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በማንኛውም የዳኝነት ሥልጣን በተሰጠው አካል ወይም በግልግል ጉባኤ በመቅረብ በስሙ ክስ ይመሠረታል፤ መልስ ይሰጣል፤ የጣልቃ ገብ አቤቱታ ያቀርባል፤ ይግባኝ ይጠይቃል፤

፱. የተሰጠው ውሣኔ የህዝብንና የመንግስትን ጥቅም የሚጐዳ ሆኖ ካገኘው የመቃወም አቤቱታ ያቀርባል፤ ይከራከራል፤

፲. የአስተዳደሩ ተቋማት ከአሰሪና ሰራተኛ ጋር ተያይዘው የሚቀርቡ የክርክር ጉዳዮችን ወክሎ ይከራከራል፤ ያስወስናል፤ ያስፈጽማል፤

፲፩. በከተማው አስተዳደር የመንግስት መስሪያ ቤቶች እርስ በእርሳቸው ያልተግባቡባቸው የፍትሐብሔር ጉዳዮች በፍርድ ቤት ወይም ከፍርድ ቤት ውጪ ባለ አማራጭ የክርክር መፍቻ መንገድ እንዲወሰን ውሣኔ ይሰጣል፣ በውሣኔ መሠረት መፈፀሙን ይከታተላል፤

፲፪. በካቢኔው በሚፀድቅ ወይም በፀደቀ መዋቅራዊ አደረጃጀት መሠረት የራሳቸው የሕግ አገልግሎት እንዲኖራቸው የተፈቀደላቸው አካላትን የህግ አገልግሎቶች በሚመለከት ወቅታዊ ሪፖርት እንዲቀርብለት ያደርጋል፤ የጉዳይ አያያዛቸውን ወይም ስራቸውን ይከታተላል፤ ይደግፋል፤ ይቆጣጠራል፤ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፤

፲፫. በልሎች ሕጐች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በፍርድ ቤት የተያዙ ወይም ፍርድ ቤት ከመቅረባቸው በፊት የማያዋጡ ወይም ለአላስፈላጊ ወጪ የሚዳርጉ ጉዳዮችን በአማራጭ ክርክር መፍቻ ዘዴዎች እንዲፈቱ ያደርጋል፤

፲፬. በከተማው ውስጥ ለሚኖሩ አቅም ለሌላቸው ነዋሪዎች ነፃ የህግ ምክር ድጋፍ ይሰጣል፤

፲፭. በዐቃቢያነ ሕግ የሚሰጡ ውሣኔዎች በሕግ መሠረት መከናወናቸውን ያረጋግጣል፤ ጉድለቶችን በጥናት አስደግፎ ይለያል፤ በግኝቱ መሠረትም እንዲታረሙ ያደርጋል፤ አስፈላጊ ሲሆን እርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል፤

፲፮. የሕግ ጥናትና ምርምር ያደርጋል፤ የከተማው አስተዳደር ያወጣቸው ሕጎች በአግባቡ ስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ ይጠብቃል፤ የሕግ ወይም የውል ረቂቅ ያዘጋጃል፤

፲፯. ነዋሪው በሕገ መንግስቱና በቻርተሩ የተሰጡትን መብቶችና ነጻነቶች እንዲያውቅና እንዲጠቀም ተገቢውን የሕግ ስልጠና ይሰጣል፤

፲፰. ለከተማው አስፈጻሚ አካላትና የልማት ድርጅቶች አመራሮችና ሰራተኞች የንቃተ ሕግ ስልጠና ይሰጣል፤

፲፱.አግባብ ባለው ሕግ መሰረት በከተማው ፍርድ ቤት ሥልጣን ስር የሚወድቁ የወንጀል ጉዳዮችን በተመለከተ ክስ ይመሰርታል፤ ይከራከራል፤ አግባብነት ያላቸውን ልሎች ተግባራት ያከናውናል፤

፳. ከፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ፣ ከሚመለከተው አካል ወይም በህግ በውክልና የሚሰጡትን የወንጀል ጉዳዮች ይከራከራል፤ ያስወስናል፤ ያስፈጽማል፤

፳፩. በሕግ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የደንብ መተላለፍ ጉዳዮችን በከተማው ፖሊስ ተጣርቶ ሲቀርብለት ወይም እንዲቀርብለት በማድረግ ክስ ይመሰርታል፣ ይከራከራል፤ የተጀመረ ምርመራ በሕግ መሠረት እንዲቆም ያዛል፤ ክስ ያነሣል ወይም የምርመራ መዝገቡ በሕጉ መሠረት ይዘጋል፤ ልሎች ሕጋዊ ተግባራትን ያከናውናል፤

፳፪. በከተማው አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት የሚጣሉ የደንብ መተላላፍ ቅጣቶችን ያስፈፅማል፤ ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል፤፳፫. በካቢኔ የጸደቀ ደንብ በአዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ያሳትማል፤ የከተማው ሕጎችን መሰብሰብ ማደራጀት መተንተንና ማሰራጨት የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤ ይፈጽማል፤

፳፬. የከተማው አስተዳደር የሚሰጣቸው አስተዳደራዊ ውሳኔዎች ከሕግ ጋር የተጣጣመ መሆኑን ያረጋግጣል፤ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፤ እንዲወሰድ ያደርጋል፤ ምክር ይሰጣል፤

፳፭. የዓቃብያነ ሕግ መተዳደሪያ ደንብ እና የሙያ ስነምግባር ደንብ ካቢኔው በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

## ፲፱. <u>የፐብሊክ ሰርቪስና ሰው ሀብት ልማት ቢሮ</u>

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩. የሳይንስና ቴክኖሎጂ ኤጀንሲን እና መለስ ዜናዊ የሥራ አመራር ኢንስቲትዩትን በበላይነት ያስተባብራል፤ ይመራል፤

፪. የለውጥ መሳሪያዎችን ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት አሰጣጥ በከተማ አስተዳደሩ መስሪያ ቤቶች ላይ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፤ ይከታታላል፤ አስፈላጊውን የቴክኒክና ሙያ ድጋፍ ይሰጣል፤

፫. በጥናት ላይ በመመስረት የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራሞችን ይተገብራል፤ እንዲተገበር ያደርጋል፤

፬. የአስተዳደሩ ተቋማት ውስጥ ካይዘንን ተግባራዊ በማድረግ የጥራትና ምርታማነት ማሻሻያ ሥራዎችን በማከናወን በከተማ አስተዳደሩ የሚገኙ ተቋማት ፈጣንና ውጤታማ አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ፤ ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ለማድረግ የሚያስችል ስልት ይቀይሳል፤ ተግባራዊ ያደርጋል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

፭. ለአስፈፃሚ አካላት እና የብዙሃን ማህበራት አቅም የሚገነባበት፤ ውጤታማ የስራ አመራርና የተሻለ አገልግሎት የሚሰጥበትን አሰራር ይቀይሳል፤ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

፮. የተቋማት አደረጃጀት አግባብነት ይመረምራል፤ ያፀድቃል፤ በአደረጃጀት ጥናት ላይ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤

፯. የከተማ አስተዳደሩ አስፈጻሚ አካላት እንዲታጠፍ፣ ከሌላ አስፈጻሚ አካል ጋር እንዲዋሀድ ወይም እንዲከፋፈል ለማድረግ፣ ተጠሪነቱን ወይም ስልጣንና ተግባሩ እንዲለወጥ ለማድረግ ወይም አዲስ የመንግስት መስሪያ ቤት እንዲቋቋም ለማድረግ ወይም እንደገና ለማደራጀት ጥናት በማካሄድ ለካቢኔው የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፤ ሲፀድቅም ተገቢውን ይፈፅማል፤

፰. የአስተዳደሩ አጠቃላይ ዓላማና ተግባራት ላይ በመመሰረት አደረጃጀቱን መፈተሸ፤ የተቀናጀ ስልጣንና ኃላፊነትን በግልፅ ሊያሣይ የሚችል ድርጅታዊ መዋቅር ተጠንቶ በስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤ አገልግሎት መስጠትን እስከ ማስጀመር ያለውን ሂደት ይከታተላል፤

፱. በአስተዳደሩ መስሪያ ቤቶች የሚሰጡ አገልግሎቶች ስታንዳርድ መኖሩንና ተግባራዊ መደረጉን ያረጋግጣል፤

፲. በአስተዳደሩ መስሪያ ቤቶች የዕቅድ አፈፃፀም ምዘና ስርዓት እና የመንግስት ሰራተኞች ቅሬታ አቀራረብና አፈታት ሥርዓት ግልፅነትና ተጠያቂነት ባለው መንገድ መዘርጋቱንና ተግባራዊ መደረጉን ያረጋግጣል፤ ትግበራውንና ውጤታማነቱን ይገመግማል፤

፲፩. አስፈጻሚ አካላትና የልማት ድርጅቶች ምርጥ ተሞክሮ ለመለየት፣ ለመቀመርና ለማስፋፋት የሚያስችል አቅም እንዲኖራቸው አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤

፲፪. ያልተማከለ የአስተዳደር ስርዓት ለማጠናከር የሚያስችል የማስፈፀም አቅም ግንባታ ይዘረጋል፤ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤ ይደግፋል፤

፲፫. ለሲቪል ሰርቪሱ በብቃትና በአፈፃፀም ላይ የተመሰረተ የምደባ፣ የጥቅማ ጥቅምና የማበረታቻ ስርዓት ይዘረጋል፤ ውጤታማነቱን ይገመግማል፤ አስፈላጊውን የማሻሻያ እርምጃ ይወስዳል፤

፲፬. የአስተዳደሩ ሰራተኞች የስነ-ምግባር መከታተያ ስርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል፤ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤

፲፭. ለሲቪል ሰርቪስ የስራ መደቦች የሚያስፈልጉ የትምህርት፣ የስልጠናና የስራ ልምድ አጠቃላይ መመዘኛዎች ያወጣል፤

፲፮. የአስተዳደሩን ሲቪል ሰርቪስ ሰራተኞች አቀጣጠር፣ አመዳደብ፣ የደረጃ እድገት፤ ዝውውር፣ ስልጠናና ዲሲፕላን በህግ መሰረት መፈፀሙን ያረጋግጣል፤

፲፯. በሕግ መሰረት የከተማ አስተዳደሩን ሲቪል ሰርቪስ ሰራተኞችን ከጡረታ ዕድሜ ክልል በላይ በአገልግሎት ላይ ስለማቆየት በሚቀርብ ጥያቄ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፤

፲፰. የከተማ አስተዳደሩን የሰው ሃብት መረጃዎችን በቴክኖሎጂ በታገዘ መልኩ ያደራጃል፤

፲፱. በመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ በልማት ድርጅቶችና በግሉ ዘርፍ የሰው ሃብት ልማት በቀጣይነት የሚለማበትና ጥቅም ላይ የሚውልበትን ስርዓት ይዘረጋል፤

፳. ብቃት ያለው፣ የህዝብ አገልጋይነት አስተሳሰብ ያለው አመራርና ፈጻሚ እንዲገነባ ይሰራል፤ የብቃት ማረጋገጫ ስርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤

፳፩. የሰው ሀብት ልማት ስራ ላይ በጥናት የተመሰረተ የአመለካከት እና የክህሎት ክፍተቶችን በመለየት ስልጠናዎች ይሰጣል፤ ስልጠናውን በበላይነት ያስተባብራል፡፡

## ፳. <u>የፋይናንስ ቢሮ</u>

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

፩. የመንግስት ሕንጻና ንብረት አስተዳደር ባለስልጣንን፣ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለስልጣንን እና የመንግስት ግዢና ንብረት ማስወገድ ኤጀንሲን ያስተባብራል፤ በበላይነት ይመራል፤ ይቆጣጠራል፤

፪. በከተማው አስተዳደር አካላት ተዘጋጅቶ የሚቀርብለትን የበጀት ጥያቄ እና የክፍለ ከተሞችን የበጀት ድልድል መርምሮ የተጠቃለለ ዓመታዊ በጀት በማዘጋጀት ያቀርባል፤ ሲፀድቅም በህግ መሰረት ያስተዳድራል፤

፫. የፊሲካል ፖሊሲ ያጠናል፤ እንዲጠና ያደርጋል፤ ውጤቱንም ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፤

፬. ባልተማከለ የበጀት አስተዳደር ሥርዓት መሠረት የክፍለ ከተሞችን የበጀት ድልድል ቀመር አዘጋጅቶ ያቀርባል፤ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤ ለክፍለ ከተሞች የሚሰጠውን የበጀት ድጎማ በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፤

፭. በገቢዎች ባለስልጣን የሚሰበሰበውን፣ በብድርና በእርዳታ የሚገኝ ገቢ እና ልሎች ልዩ ልዩ ገቢዎችን ያስተዳድራል፤ በአግባቡ ስራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

፮. የግብር እና የማዘጋጃ ቤታዊ ገቢ የታሪፍ ማሻሻያ እንዲሁም አዳዲስ የገቢ ምንጭ ጥናት በማዘጋጀት እና/ወይም እንዲዘጋጅ በማድረግ የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፤ ሲፀድቅ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

፯. አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ከሀገር ውስጥ ምንጮች በከተማ አስተዳደሩ ስም ይበደራል፤

፰. የቴክኒክ፣ የማቴሪያልና የገንዘብ ድጋፍ ከዕርዳታ ሰጪ አገሮች፤ (ከተሞች) እና ድርጅቶች ያፈላልጋል፤ ያስተባብራል ውል ይፈርማል አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

፱. የከተማውን የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት፣ የክፍያና የውስጥ ኦዲት ሥርዓት ይዘረጋል፤ የአፈጻጸሙን ውጤታማነት ይከታተላል፤ አለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ መሆኑን ያረጋግጣል፤

፲. ለመንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብና ገቢ ደረሰኞች፣ ቅጻቅፆች፣ መዛግብቶች ያሳትማል፤ እንዲታተም ያደርጋል፤

፲፩. የካፒታል ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ይከታተላል፤ ይገመግማል፤

፲፪. ከከተማው አጠቃላይ ሃብት ጋር የተጣጣመ የመካከለኛ ዘመን የወጪ ማዕቀፍ በማዘጋጀት ያቀርባል፤ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፲፫. መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የሚያቀርቧቸው ፕሮጀክቶችን ተቀብሎ ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን ያበለጽጋል፤ ያፀድቃል፤ ውል ይፈራረማል፤ ድጋፍ ይሰጣል፤ በበላይነት ያስተባብራል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

፲፬. የከተማው አስተዳደር ዓመታዊ ሒሳብ አጠቃሎ ይይዛል፤ በዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ያስመረምራል፤ በግኝቱ ላይ ተመስርቶ የማስተካከያ እርምጃ መወሰዱን ያረጋግጣል፤

፲፭. የከተማው የግዥና የንብረት አስተዳደር ስርዓት ይዘረጋል፤ በአግባቡ ስራ ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል፤

፲፮. የውስጥ ኦዲት በሴክተር መሥሪያ ቤቶች፣ በክፍለ ከተሞችና በወረዳዎች እንዲቋቋሙ ያደርጋል፤ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፤

፲፯. የውስጥ ኦዲት መመሪያዎች፣ ማኑዋሎችና የሙያ ሥነ-ምግባር ደንብ በማዘጋጀት ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤ የኦዲት ሪፖርቶችን ተቀብሎ ይገመግማል፤ የተገኙ ድክመቶች እንዲታረሙ ያደርጋል፤

፲፰. የከተማ አስተዳደሩ የልማት ድርጅቶች ወደ ግል ባለቤትነት ለማዛወር የሚያስፈልጉ ሰነዶችን ያዘጋጃል፤ ከሚመለከታቸው የመንግስት ተቋማት ጋር በመቀናጀት የዝውውር ሂደቱን ያሳልጣል፤

፲፱. የከተማ አስተዳደሩን አክሲዮኖች፣ የሚተላለፉና የማይተላለፉ የገንዘብ ሰነዶች እና ሌሎች ተመሳሳይ ተቀማጭ የገንዘብ ሀብቶችን ይይዛል፤ ይጠብቃል፤

**፳፩. <u>የመሬትልማትናማኔጅመንትቢሮ</u>**

ቢሮው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩. የመሬትልማትናከተማማደስኤጀንሲን፣የመሬትባንክና ማስተላለፍ ጽህፈት ቤትን እና የመሬት ይዞታአስተዳደርጽህፈት ቤትንበበላይነትይመራል፤ያስተባብራል፤

፪. ስለከተማው ቦታዎች የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች አመዘጋገብና መረጃ አያያዝ የወጡ ፖሊሲዎችና ሕጎች መፈፀማቸውን ይከታተላል፤ ከሕግ ውጪ በሚሰሩ የቦታ ማስተላለፎች፣ መረጃ አያያዞች ላይ እርምጃ ይወስዳል፤ ያስወስዳል፤

፫. የከተማዋን የመሬት ልማት እና ከተማ ማደስ አፈጻጸም ስትራቴጂዎችን ይነድፋል፤ ሲጸድቅም እንዲተገበሩ ያደርጋል፤ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

፬. የከተማዋን መዋቅራዊ እና ዝርዝር የአካባቢ ልማት ፕላኖች መሰረት በማድረግና ፍትሃዊና ኢኮኖሚያዊ የመሬት ልማትና አቅርቦት እንዲሁም የከተማ ማደስ ጥናት ስራዎችን ያከናውናል ወይም እንዲከናወን ያደርጋል፤ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

፭. የልማት ቅደም ተከተል በወጣላቸው አካባቢዎች የመልሶ ማልማት ፕሮጀክት ጥናት፣ መርሀ-ግብሮች፣ ጥቅል ዓላማዎች፣ ግቦች፣ የኢንቨስትመንት ዕቅዶች፣ በጀት፣ የዓላማ ማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎችና የጊዜ ሠልዳ መያዙን ያረጋግጣል፤ በሚመለከተው አካል እንዲጸድቅ ያደርጋል፤ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤

፮. ለመልሶ ማልማትና ለመሬት ዝግጅት ተፈላጊው መሰረተ ልማት መጠናቱን ያረጋግጣል፤ ክትትል ያደርጋል፤ ይቆጣጠራል፤

፯. ለልማት የተመረጡ አካባቢዎች በአካባቢ ልማት ፕላኑ መሰረት የተቀናጀ የከተማ ዲዛይን መዘጋጀቱን ያረጋግጣል፤ በሚመለከተው አካል ያፀድቃል፤

፰. በከተማዋ ክልል ውስጥ ለተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የልማት ስራዎች የሚውል መሬት እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤ ያረጋግጣል፤

፱. በከተማው ውስጥ የተጎዱና ያረጁ አካባቢዎችን ለማደስ እንዲቻል የካሳ ክፍያ ስርዓት ጥናት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ያከናውናል፤ በየጊዜውም እንዲሻሻል ያደርጋል፤ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤

፲. ለልዩ ልዩ የልማት ስራዎች የለማ መሬት በመሬት ባንክ መመዝገቡን ያረጋግጣል፤ ወጥ የሸንሻኖ ቁጥር መሰጠቱንም ያረጋግጣል፤ ይቆጣጠራል፤

፲፩. መሠረተ ልማት ተሟልቶላቸው የተዘጋጁ የከተማ ቦታዎች ለአልሚዎች የሚተላለፉበትን ስርዓት ይዘረጋል ወይም እንዲዘረጋ ያደርጋል፤ ለአልሚዎች የሚተላለፉ የከተማ ቦታዎችን አግባብነት ይመረምራል፤ በውል መሰረት የሊዝ ክፍያው መሰብሰቡን ይከታተላል፤ ያረጋግጣል፤

፲፪. በከተማዋ የመሬት አቅርቦትና ፍላጎት ሚዛኑን ጠብቆ መሄድ እንዲችል የተለያዩ ጥናቶችን በማከናወን የመፍትሄ እርምጃዎችን መውሰድ የሚያስችሉ የውሳኔ ሃሳብ አዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፤

፲፫. በካርታ በተደገፈ መልኩ የከተማ ቦታ ደረጃ እና የሊዝ መነሻ ዋጋ ጥናት ያካሂዳል ወይም እንዲካሄድ ያደርጋል፤ ወቅታዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፤ ጥናቱን በመገምገም የመነሻ ዋጋውን አንዲጸደቅ ያደርጋል፤ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤

፲፬. የመሬት ልማትና ማኔጅመንት አፈፃፀምና መሬት ለተጠቃሚዎች የሚፈቀድባቸው ሥርዓቶች የሚመሩባቸውን የአገልግሎት አሰጣጥ መመሪያዎች በጥናት ወቅታዊ ያደርጋል፤ ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፤

፲፭. በከተማው የተጎዱና ያረጁ አካባቢዎችን የሕዝቡን ተጠቃሚነት በሚያረጋግጥ ሁኔታ ስታንዳርዱን ጠብቆ መልሶ ማልማት የሚያስችል ስርዓት ይዘረጋል፤

፲፮. የልማት ተነሺዎች ከመነሳታቸው ቀደም ብሎ አግባብ ባለው ሕግ የምትክ ቦታ፣ ቤት፣ ተመጣጣኝ ካሳ እና ልሎች ክፍያዎች ማግኘት የሚችሉበትን ስርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

**፳፪. <u>የኮንስትራክሽን ቢሮ</u>**

ቢሮው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖረዋል፡-

፩. የግንባታውን ኢንዱስትሪ ለማዘመን የሚያስችሉ በዲዛይን፣ በኮንስትራክሽን ግብዓትና ግንባታ ወጪ ቆጣቢ የሆኑ አዳዲስ አማራጭ ቴክኖሎጂዎችን ያጠናል፤ ሲፈቀድም ይተገብራል፤

፪. በግንባታው ዘርፍ የተሰማሩ የስራ ተቋራጮች፣ አማካሪዎችና ባለሙያዎች፣ ጥቃቅንና አነስተኛ ድርጅቶችን አቅም ይገነባል፤

፫. የግንባታ ግብዓትና የጉልበት የገበያ ዋጋ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በማጥናት የዋጋ ተመን ያወጣል፤ ሲጸድቅ ለዘርፉ ተጠቃሚ አካላት ያሰራጫል፤

፬. በግንባታና ዲዛይን እና የግንባታ ግብአት ማምረት ላይ የሚሳተፉ የስራ ተቋራጮች፣ አማካሪዎችን፣ ባለሙያዎችን፣ ግብዓት አምራችና አቅራቢዎችን፣ የግንባታ መሳሪያ አከራዮችን ይመዘግባል፤ የሙያና የብቃት ማረገገጫ ፈቃድ ይሰጣል፤ ይሰርዛል፤ ዕድሳት ያደርጋል፤ ህጋዊ ፈቃድ ይዘው መስራታቸውን ያረጋግጣል፤

፭. የግንባታ ግብአት ናሙናዎችን ከማምረቻ ቦታዎች፣ ግንባታ ከሚከናወንባቸው አካባቢዎች ናሙና በመውሰድ በላቦራቶሪ ጥራታቸውን ያረጋግጣል፤ ችግር በታየባቸው ላይ አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፤ በተጠየቀ ጊዜ ከልሎች ተቋማትና ግለሰቦች አስፈላጊውን ክፍያ በማስከፈል የግንባታ ግብዓት የጥራት ምርመራ ያካሂዳል፤ ውጤቱን ያሳውቃል፤

፮. የዲዛይንና ግንባታ ስታንዳርዶችን ያዘጋጃል፤ እንዲዘጋጁ ያደርጋል፤ ሲጸድቅም መተግበራቸውን ይከታታላል፤ ይቆጣጠራል፤

፯. የግንባታ ግብዓት ሀብት ጥናት አቅም ያጠናል፤ ለሚመለከታቸው አካላት ያሳውቃል፤

፰. በግንባታው ዘርፍ ከውል ጋር ተያይዞ የሚከሰቱ አለመግባባቶችን በስምምነት እንዲፈቱ ድጋፍ ያደርጋል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

፱. የኮንስትራክሽን ዘርፍ የመረጃ መረብና ማዕከል እንዲኖር ያደርጋል፤ መረጃዎችን ይመዘግባል፤ ወቅታዊ ያደርጋል፤ ይተነትናል፤ ያሰራጫል፤

፲. ለግንባታ የሚከፈሉና የተከፈሉ ክፍያዎችን እና የተከናወኑ የግንባታ ሥራዎች ህጋዊነታቸውንና ትክክለኛነታቸውን ኦዲት ያስደርጋል፤ በግኝቱ መሰረት የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፤

፲፩. ማንኛውንም የአስተዳደሩ የህንጻና ተመሳሳይ የግንባታ ስራዎችን የከተማ አስተዳደሩን ወክሎ አግባብ ባለው ህግ መሰረት ውል ይፈጽማል፣ ኮንትራት ያስተዳድራል፣ ግንባታው ሲጠናቀቅም በውሉ መሠረት መከናወኑን ተቆጣጥሮ ይረከባል፣ ህንጻው ወይም ግንባታው ለተከናወነለት ተቋም በሰነድ ያስረክባል፣

፲፪. የህዝብ መጸዳጃ ቤት እንዲገነባ ያደርጋል፣ ግንባታው ሲጠናቀቅ ለተፋሰስና አረንጓዴ አካበቢዎች ልማት ኤጀንሲ ያስተላልፋል፣

፲፫. ከጥቃቅንና አነስተኛ ወደ መካከለኛ ኮንትራክተርነት የተሸጋገሩ ኢንተርፕራይዞችን እንደ ባለቤትነት ተረክቦ የድጋፍ ማዕቀፍ በማዘጋጀት ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት ይደግፋል፣ ያበቃል፡፡

## ፳፫. የቤቶችልማትና አስተዳደር ቢሮ

ቢሮው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖረዋል፡-

፩. የቤቶች ልማት ኮርፖሬሽንን እና የግንባታ ዲዛይን ጽህፈት ቤትን በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣

፪. አገራዊ የቤቶች ልማትና አስተዳደርን የሚመለከቱ ፖሊሲዎች፣ ዝርዝር የህግ ማዕቀፎች እንዲሁም ስታንዳርድ በከተማዋ ተፈጻሚ መሆናቸውን ያረጋግጣል፣ የማሻሻያ ግብዓቶች ያሰባስባል፣ ለሚመለከተው አካል ያስተላልፋል፣ ተግባራዊነቱንምይቆጣጠራል፣

፫. በከተማዋ የጋራ መኖሪያ ቤቶችንና ንግድ ቤቶችን ለማስተላለፍ፣ ለማከራየትና ለማስተዳደር እንዲሁም ልሎች የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት፣ የግል ቤት አልሚዎች እና ሪል ስቴቶችን ለመምራት የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ፣ ስልትና ስታንዳርድ ያዘጋጃል፣ ይተገብራል፣ የመኖሪያ ቤት አይነቶችን መደብና ደረጃ ያወጣል፣ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ይሰጣል፣

፬. በከተማ አስተዳደሩ ለጋራ መኖሪያ ቤቶች ግንባታ ከባንክ የተገኘው ብድር፣ ቤቶቹ ሲተላለፉ የተገኘው ገቢ፣ የተመለሰው የብድር መጠን እና ወለድ የቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን በአግባቡ እየመዘገበ ወቅታዊ ማድረጉን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

፭. በአነስተኛና መካከለኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ያሉ ነዋሪዎች በተለይም ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞችና የልማት ተነሺዎች በቤት ልማት ፍትሐዊ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፣

፮. የቤት ልማት ግንባታ ወጪ- ቆጣቢ፣ ጥራትና ዘመናዊነትን የተከተለ መሆኑን ያረጋግጣል፣

፯. የቤት ልማቱ ስራ ከድህነት ቅነሳ እና ከስራ እድል ፈጠራ ጋር የተቀናጀ እንዲሆን ያደርጋል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣

፰. የከተማ ነዋሪ ከአቅሙ ጋር የተመጣጠነ መኖሪያ ቤት እንዲሠራ አጠቃላይ አቅጣጫ ለመቀየስ የሚያስችሉ ጥናቶችን ያካሂዳል፣ አግባብ ባለው ህግ መሰረት መንግሥትና

የግል ባለሃብቶች በአጋርነት የቤት ልማት ማካሄድ የሚችሉበት ሥርዓት ይዘረጋል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

፱. በበጎ አድራጊ ወይም በሌላ የከተማውን ህብረተሰብ የቤት ችግር ለመቅረፍ የሚሰሩ የቤት ልማቶች በከተማው አጠቃላይ የቤቶች ልማትና አስተዳደር ፕሮግራም ጋር የተጣጣሙና የተቀናጁ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

፲. በቤት ልማት ዘርፍ የሚሰማሩ አካላት ተቀናጅተው የሚሰሩበትን አሰራር ስርዓት ይዘረጋል፤ ድጋፍ ያደርጋል፤ አፈፃፀሙን ይቆጣጠራል፤

፲፩. ከቤት ሽያጭ፣ ኪራይና የመሳሰሉት ተግባራት ላይ ጤናማ የገበያ ስርዓት እንዲኖር የሚያስችል ጥናቶችን ያጠናል፤ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፲፪. የጋራ መኖሪያ ቤት ማህበራት እንዲመሰረቱና በህግ አግባብ ተልእኳቸውን እንዲወጡ ያበረታታል፣ በጋራ መኖሪያ ቤቶች የማህበራት አደረጃጀት ላይ የሚታዩ ችግሮችን በማጥናት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ክፍተቶችን የሚሞላ ስርዓት ይዘረጋል፤ ክትትል ያደርጋል፤

፲፫. በቤትልማት ፖሊሲውና ስታንዳርድ መሰረት የሚከናወኑ የቤት ልማት ስራዎች በጥራትና በጊዜው የሚጠናቀቁበት የቁጥጥርና ክትትል ስርዓት ይዘረጋል፤ ይተገበራል፤

፲፬. የቤት ፍላጎትና አቅርቦት መለየት የሚያስችል ዝርዝር ጥናት ያከናውናል፤ የቤት አቅርቦት ክፍተቶችን መድፈን የሚያስችል የመፍትሔ ኃሳቦችን ያመነጫል፤ ለሚመለከተው አካል በማቅረብ ያስወስናል፤ ይተገበራል፤ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤

፲፭. ወቅታዊ የቤት ፍላጎት፣ አቅርቦት እና አጠቃላይ የቤት መረጃ በዝርዝር ይይዛል፤ ወቅታዊ ያደርጋል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ጥቅም ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

፲፮.በጋራ መኖሪያ ቤቶች ህብረተሰቡን የሚያውኩ እና ህገ-ወጥ ተግባራትን የሚፈፅሙ አካላትን ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ቁጥጥር ያደርጋል፤ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

፲፯. የከተማ አስተዳደሩ ንብረት የሆኑ የመኖሪያ፣ ንግድና ልሎች ቤቶችን በፍትሐዊነት ያስተዳድራል፤ ቤቶችን በህግ መሠረት ያከራያል፤ የተለያዩ አማራጭ የኪራይ ተመን ያጠናል፤ ሲጸድቅ ይተገበራል፤ ወርሃዊ የቤት ኪራይ ይሰበስባል፤ መሰብሰቡን ይከታተላል፤

፲፰. ኢ-መደበኛ የሆኑ የመኖሪያ ቤት አቅርቦቶች መረጃ ይሰበስባል፤ በመደበኛው የቤቶች ልማት ፕሮግራም ላይ ያላቸውን ተጽዕኖ በማጥናት ወደ መደበኛው ፕሮግራም የሚገቡበት የመፍትሔ ሀሳብ ለሚመለከታቸው አካላት ያቀርባል፤ የመፍትሔ ሀሳቡ ተቀባይነት ሲያገኝ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፲፱. ቤቶቹ በልማት ምክንያት በሚፈርሱበት ወቅት አስፈላጊውን መረጃ ለሚመለከተው አካል ያስተላልፋል፤ በቤቱ ውስጥ ነዋሪ የሆኑ ሰዎች ምትክ ቤት የሚያገኙበትን አግባብ ያመቻቻል፤

፳. የግል መኖሪያ ቤት ያላቸው ነዋሪዎችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመለየት ከጋራ መኖሪያ ቤት እጣ ውጪ እንዲሆኑ ያደርጋል፤ ቅድመ ጥንቃቄ እርምጃዎችን ይወስዳል፤ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

፳፩. የመንግስት የመኖሪያና የንግድ ቤቶችን በህገ-ወጥ መንገድ ከያዙት አካላት ያስለቅቃል፤

፳፪. የሚያስተዳድራቸውን ቤቶች መረጃ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ይይዛል፤ ለቤቶቹ ጥገናና እድሳት ያደርጋል፡፡

**፳፬. <u>የትራንስፖርት ቢሮ</u>**

ቢሮው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩. የትራንስፖርት ባለሥልጣንን፣ የትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲን እና የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣንን በበላይነትይመራል፤ያስተባብራል፤

፪. የትራንስፖርት ማስተር ፕላን ያዘጋጃል፤ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤ ሲጸድቅም አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

፫. የከተማዋን የትራንስፖርት መሠረተ ልማት የመገንባት፣ የማስፋፋት፣ የመጠገንና የማስተዳደር ስራ እንዲሳለጥ የሚያግዙ የአሰራር ሥርአት ይዘረጋል፤

፬. የተቀናጀ የሕዝብና የጭነት ትራንስፖርት አገልግሎት እንዲኖር የሚያግዙ የከተማ ትራንስፖርት ደንብ፣ ደረጃዎች እና የአሰራር ሥርዓቶች፣ ያዘጋጃል፤ ሲጸድቁም ተግባራዊ ያደርጋል፤ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፤

፭. የትራንስፖርት መሠረተ ልማት ለማቀናጀት፤ የትራንስፖርት ፍላጎትና አቅርቦት፣ የትራፊክ አመራር፣ የአሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር፣ አማራጭ የትራንስፖርት አገልግሎት ዘዴዎችን ለማስፋት፣ የመንገድ ኔትዎርክ ለማሻሻል እና አገልግሎቱን ለማሳለጥና ለማዘመን የሚረዱ ጥናቶች ያደርጋል፤ ሲፀድቅም ሥራ ላይ ያውላል፤

፮. የአየር ብክለት የሚቀንሱና ለአየር ንብረት ምቹ የሚሆኑ የትራንስፖርት ዓይነቶችን መጠቀምን ለማበረታታት የሚያስችሉ መመሪያ በማውጣትና ተግባራዊነቱን በመከታተል ከተማዋን ከብክለት ይከላከላል፤ ከሚመለከተው አካል ጋር በቅንጅት ይሰራል፤

፯. በከተማዋ የትራንስፖርት ማሰተር ፕላን መሠረት የሚገነቡትን የመንገድ፣ የፓርኪንግ ቦታዎች፣ መናሃሪያዎች፣ ዴፖዎች እና ተርሚናሎች መለየታቸውን ያረጋግጣል፤

፰. የትራንስፖርት መሠረተ ልማት ግንባታ ፕሮግራሞች፣ ዕቅዶችና ዲዛይኖች ሲዘጋጁ ከልሎች የከተማው መስረተ ልማት አውታሮች ጋር የተናበቡ መሆናቸውን ይከታተላል፡፡

**፷፳. የንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ**

ቢሮው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩. የህብረት ስራ ማህበራት ኤጀንሲን እና አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪነግ ክላስተር ኮርፖሬሽን በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፣

፪. የአገራችንን የንግድና ኢንዱስትሪ ፖሊሲናሕግመሰረት እንዲሁምየከተማችንን ተጨባጭ ሁኔታ ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ተስማሚ የንግድና ኢንዱስትሪፕሮጀክቶችን በመቅረፅ ያስተዋውቃል፣ ያበረታታል፣ ንግድ፣ ኢንዱስትሪናዕደ-ጥበብእንዲስፋፉ ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፣

፫. የከተማው የምርት ውጤቶች እንዲታወቁ ያደርጋል፣ አውደ-ርዕይ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ ይሳተፋል፣ ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፣

፬. የአገር ውስጥ ባለሃብቶች በከተማው ውስጥ በንግድና ኢንዱስትሪ ስራ ላይ በሰፊው እንዲሰማሩ ያበረታታል፣ የቴክኒክና የምክር አገልግሎቶችን ይሰጣል፣ በንግድ ስራ ለሚሰማሩና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎችን ለሚያቋቁሙ የሃገር ውስጥ ባለሃብቶች የንግድ ፍቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፣

፭. በከተማው ውስጥ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት እንዲቋቋም ያበረታታል፣ ድጋፍ ይሰጣል፣

፮. የከተማውን የንግድ መዝገብ ያቋቁማል፣ የንግድ ስም ምዝገባ ያከናውናል፣ ያስተዳድራል፣ የንግድ ማህበራትን በህግ መሠረት በመመዝገብ ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ያግዳል፣ ይሰርዛል፣

፯. የዋስትና መያዣ በሕግ መሠረት በንግድ መዝገብ ይመዘግባል፣ ይሰርዛል፣ ለሃራጅ ሽያጭ አፈጻጸም የሚረዱ ስራዎችን በሕግ መሰረት ያከናውናል፣

፰. የገበያ ማዕከላት ያለማል፣ ደረጃ ያወጣል፣ ደረጃቸውን የጠበቁ የገበያ ማዕከላት መገንባታቸውን ይቆጣጠራል፣ የሚስፋፉበትንና የሚያድጉበትን ስልት ይቀይሳል፣

፱. በከተማው ውስጥ የመሠረታዊ ንግድ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ስርጭት የገበያ ህግና ስርዓትን መከተሉን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

፲. ለገበያ የሚቀርቡ ምርቶችና አገልግሎቶች ጥራትና ደረጃቸውን የጠበቁ መሆኑን እና ጥራትና ደረጃቸውን ያልጠበቁ ወይም ጊዜ ያለፈባቸው ምርቶች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን እንዲወገዱ ያደርጋል፣

፲፩. የፍጆታ ምርቶችን የአገልግሎት ዘመንና የተዘጋጁባቸውን ንጥረ-ነገሮች ይዘት ሸማቹ ማወቅ በሚችልበት ሁኔታ መሆኑን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

፲፪. በገበያው ውስጥ በቂ አቅርቦት መኖሩንና ግዥና ሽያጩ በተረጋጋ ሁኔታ እየተከናወነ መሆኑን ያረጋግጣል፤ ለነጻ ገበያ ውድድር እንቅፋት የሆኑ ድርጊቶችና ተገቢ ያልሆኑ የንግድ ስራዎች እንዳይፈጸሙ በመከላከልና በማስወገድ የከተማውን ነዋሪዎች ጥቅም ያስጠብቃል፤

፲፫. የገበያ ዋጋ መረጃ የመሰብሰብ፣ የመተንተን እና የማቀነባበር ተግባራትን ያከናውናል፤ እንዳስፈላጊነቱ በጥቅም ላይ ያውላል፤

፲፬. የልኬት መሳሪያዎችንና መስፈሪያዎችን ትክክለኛነት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ያረጋግጣል፤ ይቆጣጠራል፤ ትክክለኛ ሆነው ያልተገኙ የልኬት መሳሪያዎችንና መስፈሪያዎችን እንዲወገዱ ያደርጋል፤

፲፭. ለገበያ አገልግሎት እንዲውሉ የተዘጋጁ ቦታዎችን ይቆጣጠራል፤ ያስተዳድራል፤ የአገልግሎት አስጣጡን በተመለከተ መመሪያ ያወጣል፤

፲፮. በኢንደስትሪ ዞን ገብተው ምርት ማምረት የሚገባቸውን ፕሮጀክት አይነቶች የአገራችንን የኢንዱስትሪ ፖሊሲና ስትራቴጂ፣ የከተማዋን ተጨባጭ ሁኔታ መሠረት በማድረግ የመግቢያ መስፈርት ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ያዘጋጃል፤ ይተገብራል ወይም ተግባራዊ መሆኑን ይከታተላል፤

፲፯. ከጥቃቅንና አነስተኛ ወደ ታዳጊ መካከለኛና መካከለኛ ለሚሸጋገሩ ባለሀብቶች የመስሪያ ቦታና መሰረተ ልማት እንዲሟላላቸው ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ይሰራል፤ የፕሮጀክቶች ዝግጅት፣ አዋጭነት ጥናት ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤

፲፰. ኢ-መደበኛ ንግድ ወደ መደበኛ ስርዓት የሚገባበትን አሰራር ስርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤

፲፱. ሕገ-ወጥ ንግድን ከሚመለከተው አካል ጋር በመተባበር ይከላከላል፤ ይቆጣጠራል፤ እርምጃ ይወስዳል፤ እንዲወሰድ ያደርጋል፡፡

## ፳፯. የሥራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዝ ልማት ቢሮ

ቢሮው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩. የምግብ ዋስትና እና ልማታዊ ሴፍቲኔት ኤጀንሲን በበላይነት ይመራል፤ ያስተባብራል፤ ይቆጣጠራል፤

፪. የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርኘራይዝ እንዲስፋፋ አስፈላጊውን ሁሉ ያደርጋል፤ ከመንግስታዊ፣ መንግስታዊ ካልሆኑ እና ከግል ድርጅቶች ጋር ትስስር በመፍጠር ድጋፍ እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤ የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፤ ተፈጻሚነቱን ያረጋግጣል፤

፫. በከተማችን ውስጥ የሚገኙ ነዋሪዎች የስራ ዕድል መፍጠር እንዲችሉ ስልጠናዎችን በማዘጋጀት ይሰጣል፤ ተሞክሮዎችን በመለየትና በመቀመር ዕውቀትና ክህሎት እንዲቀስሙ ያደርጋል፤ ያበረታታል፤ የንግድ ስራ ክህሎት የምክር አገልግሎት ይሰጣል፤

፬. ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የንግድ ስራቸውን በአግባቡ መምራት እና ምርትና ምርታማነታቸውን ማሳደግ እንዲችሉ ሙያዊ ድጋፍና ክትትል አገልግሎት ይሰጣል፤ የአንድ ማዕከል አገልግሎትን ያደራጃል፤ ያስተባብራል፤ ይቆጣጠራል፤

፭. በከተማው ውስጥ የሚገኙትን ነዋሪዎች አምራች ዜጋ ለማድረግ የሚያስችሉ የጥቃቅንና አነስተኛ ፕሮጀክቶችን ያጠናል፤ ፕሮጀክት ፕሮፋይል በማዘጋጀት ፍላጎቱ ላላቸው ስራ አጥ ወጣቶች ያስተዋውቃል፤ በስራው እንዲሰማሩ ያበረታታል፤

፮. የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የተሰማሩበትን የስራ ዘርፍ በአግባቡ ማካሄድ የሚያስችላቸው የፋይናንስ ብድር አገልግሎት የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

፯. የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርኘራይዝ ማምረቻ፣ ማሳያ እና መሸጫ ማዕከላትን ማስገንባት እንዲቻል ከሚመለከተው አካል መሬት ይረከባል፤ ካርታ የሌላቸው ነባር ይዞታዎችን ካርታ እንዲሰራላቸው ያደርጋል፤ የማምረቻ፣ ማሳያ እና መሸጫ ማዕከላትን የከተማዋን ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘበና ለስራ ተስማሚ በሆነ ዲዛይን በባለቤትነት ያስገነባል፤

፰. በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ላይ የተሰማሩ አንቀሳቃሾች የማምረቻ፣ ማሳያ እና የመሸጫ ቦታዎች በኪራይ እንዲያገኙ ያደርጋል፤ የጥሬ ዕቃ፣ የማምረቻ መሳሪያዎች እና የመሰረተ ልማት አውታሮች የሚሟላበት ሁኔታ ያመቻቻል፤

፱. የማምረቻ፣ ማሳያ እና መሸጫ ማዕከላትን አጠቃቀምና አስተዳደር የሚመለከት መመሪያ ያወጣል፤ ያስተዳድራል፤

፲. የማምረቻ፣ ማሳያ እና መሸጫ ማእከላትን እና መስሪያ ቦታዎች በህገወጥ መንገድ እንዳይተላለፉ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤ ተላልፈውም ሲገኝ ሁኔታውን በአግባቡ በማጣራት በፈጻሚዎቹ ላይ ተገቢውን ህጋዊ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል፤

፲፩· የማምረቻ፣ ማሳያ እና መሸጫ ማዕከላትን በተመለከተ የተደራጀ መረጃ በመመዝገብ ይይዛል፤ ለተጠቃሚዎች በውል መሠረት በኪራይ ያስተላልፋል፤ በተገቢው ጥቅም ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ የውል ዘመኑ ሲያበቃ ተከታትሎ ይረከባል፤

፲፪· የማምረቻ፣ ማሳያና መሸጫ ማዕከላት እድሳት እንዲያገኙ ያደርጋል፤

፲፫· ለጥቃቅንና አነስተኛ አገልግሎት እንዲውሉ የተዘጋጁ ቦታዎችን፣ ሼዶች፣ ተለጣፊ ሱቆችን፣ በመንግስትና በተለያዩ በጎ አድራጎት የተገነቡ መደብሮችን ይቆጣጠራል፤ ያስተዳድራል፤

፲፬· በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርኘራይዝ ለተሰማሩ የህብረተሰብ ክፍሎች የሙያ ማበልጸጊያ ስልጠናዎችና አውደ ርዕዮች እንዲዘጋጁ ያደርጋል፤ ያስተባብራል፤

፲፭· የአንቀሳቃሾችን የገበያ ችግር ለመቅረፍ ከተለያዩ አካላት ጋር የገበያ ትስስር እንዲፈጠርላቸው ያደርጋል፤ ምርቶቻቸውንና አገልግሎታቸውንለተጠቃሚው ለማስተዋወቅ እንዲችሉና የገበያ ዕድላቸውን ለማስፋት ኤግዚቢሽንና ባዛሮች እንዲዘጋጁ ያደርጋል፤

፲፮· የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ አንቀሳቃሾች በግል ንግድ፣ በሽርክና እና በህብረት ስራ ማህበር እንዲደራጁ ያመቻቻል፤ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፤ ያበረታታል፤

፲፯· ኢንተርፕራይዞቹ አግባብ ባለው ህግ መሠረት ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ ኢንተርኘራይዝ መሸጋገር የሚገባቸውን በመለየት ኢንዲሸጋገሩ ያደርጋል፤

፲፰· የመረጃና የምክር አገልግሎት ለተጠቃሚዎች የሚሰጥበትን ስርዓት ይዘረጋል፡፡

**፳፯·<u>የጤና ቢሮ</u>**

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩· ኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽህፈት ቤትን፣ በከተማው አስተዳደር ስር የሚገኙ ጤና ተቋማትን እና የካቲት ፲፪ ሜዲካል ኮልጅን በሕግ መሠረት ያስተዳድራል፤ ይመራል፤

፪· የሀገሪቱን የጤና ፖሊሲና ደረጃ በማገናዘብ የከተማውን የጤና አገልግሎት ደረጃ ያወጣል፤ ተግባራዊነቱን ያረጋግጣል፤ በጤና ጉዳዮች ላይ የግንዛቤ ማስፋፊያ ትምህርት ለነዋሪው አመቺ በሆነ ዘዴ ይሰጣል ወይም እንዲሰጥ ያደርጋል፤

፫· አጠቃላይ የሆነ የተላላፊ በሽታዎች ቁጥጥርና ቅኝት ያደርጋል፤ ይቆጣጠራል፤ ይከላከላል፤ መረጃዎችን ያሰባስባል፤ ወረርሽኝ ሲነሳ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይከላከላል፤

፬· የእናቶችና ህፃናት ጤና ክብካቤ አገልግሎት ይሰጣል ወይም እንዲሰጥ ያደርጋል፤ ይቆጣጠራል፤

፭· ከፌደራል መንግሥት እና ከዕርዳታ ሰጭ ድርጅቶች ለተለያዩ ፕሮግራሞች ማስፈጸሚያ የሚሰጡ መድኃኒቶችንና የሕክምና መሳሪያዎችን ያሰራጫል፤ ስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

፮· የጤና አገልግሎት ፕሮግራሞችን ከሚያካሂዱ መንግሥታዊ ያልሆኑ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ጋር ሕጋዊ ስምምነቶችና ውሎች ይፈጽማል፤ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፤

፯· በከተማው ውስጥ የሚከናወኑ የኤች አይ ቪ ኤድስና ልሎች በሽታዎች ቁጥጥር መረጃ ያጠናቅራል፤ በአግባቡ በመተንተን ለሚመለከታቸው ያቀርባል፤

፰· የጤና አጠባበቅ የምክርና የመረጃ አገልግሎት ያደራጃል፤ ይሰጣል፤

፱· መንግስታዊ ጤና ተቋማት የሚሰጡትን የሕክምና መረጃዎች ያረጋግጣል፤ ይከታተላል፤ እንደ አስፈላጊነቱም እርምጃ ይወስዳል፤

፲· ደረጃውን የጠበቀ የቅድመ ሆስፒታል አምቡላንስ አገልግሎት እንዲሰጥ ያደርጋል፤ በበላይነት ይመራል ያስተዳድራል ፡፡

**፳፰·<u>የትምህርት ቢሮ</u>**

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩. የትምህርት ተደራሽነትን ማረጋገጥ እንዲቻል ትምህርት ቤቶችን ያስፋፋል፤ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን እንዲጠገኑ እና መሰረተ ልማታቸው በአግባቡ እንዲሟላ ያደርጋል፤

፪· የሀገሪቱን የትምህርት ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና ደረጃ በመጠበቅ የከተማውን አስተዳደር ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘበ ጥናትና ምርምር ያደርጋል፤ መደበኛ ያልሆኑ፣ ቅድመ መደበኛ እና መጀመርያ ደረጃ ሥርዓተ ትምህርት ያዘጋጃል፤ መጻህፍት ያሳትማል፤ የትምህርት ግብዓት መሟላታቸውን ያረጋግጣል፤

፫· በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚወጣውን መስፈርት መሠረት በማድረግ በከተማው ውስጥ የሚገኙትን ትምህርት ቤቶች ደረጃ እንዲሻሻል ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤

፬· የመምህራንና የትምህርት ባለሙያዎችን የአቅም ግንባታ ስራ ያከናውናል፤

፭· በከተማው ውስጥ አገር አቀፍ ፈተናዎችን ያስፈፅማል፤ በከተማው ውስጥ በሚገኙ የመጀመሪያና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተዘጋጅተው የሚሠጡ ፈተናዎችንና የምስክር ወረቀቶችን ህጋዊነት ያረጋግጣል፤

፮· ከተማ አቀፍ የሆኑ ፈተናዎችን ያዘጋጃል፣ ያስፈፅማል፤

፯· በመገናኛ ዘዴዎች የተደገፉ የትምህርት ፕሮግራሞች እንዲሰጡ ያደርጋል፤ መደበኛና ኢ-መደበኛ የትምህርት ፕሮግራሞች የሚስፋፉበትን ሁኔታ ይቀይሳል፤ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

፰· ለሴቶች፣ ለህፃናት፣ ለጎልማሶችና ልዩ የትምህርት ፍላጎት ላላቸው ዜጎች ለሚሰጡ የትምህርት አገልግሎቶች ልዩ ድጋፍ እንዲሰጥ ያደርጋል፤

፱· በሀገር አቀፍ ደረጃ በሚወጡ የብቃት መመዘኛዎች መሠረት መምህራንና ልሎች የትምህርት ባለሙያዎችን ያሰለጥናል፣ እንዲሰለጥኑ ያደርጋል፤ ሙያ ድጋፍ ይሰጣል፤

፲· ትምህርት ቤቶችን ማቋቋምና ማስፋፋት ለሚፈልጉ አካላት የመረጃ አገልግሎትና ድጋፍ ይሰጣል፤

፲፩· በከተማው ውስጥ የሚገኙ መንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት የሚተዳደሩ ትምህርት ቤቶች የመማርና ማስተማር ሂደት በበላይነት ይመራል፤ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፡፡

**፳፱·<u>የወጣቶችና በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ቢሮ</u>**

ቢሮው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡-

፩· የስፖርት ኮሚሽንን በበላይነት ይመራል፤ ያስተባብራል፤

፪· በከተማ አስተዳደሩ ህጎች ሲተገበሩ የወጣቶችን ሁለንተናዊ መብትና ጥቅም የሚጠብቁ መሆናቸውን ይከታተላል፤ ሁሉም አስፈፃሚ አካላት የወጣቶችን ጉዳይ በዕቅዳቸው ማካተታቸውን ይከታተላል፤ መፈጸሙን ያረጋግጣል፤

፫· የወጣቶች መብት ስለመጣሳቸው መረጃ ሲደርሰው ጉዳዩን ከሚመለከተው አካል ጋር በማጥናትና በማጥራት የህግ ከለላ ማግኘት እንዲችሉና ተገቢው መፍትሔ እንዲሰጥ ያደርጋል፤

፬· የወጣቶችን አቅም የሚያጎለብቱ ትምህርታዊ፣ ሙያዊና የተጨማሪ ክህሎት ስልጠናዎችን ያዘጋጃል፤ ያመቻቻል፤ ይሰጣል፤

፭· ወጣቶች ከሚመለከተው አካል ጋር በመቀናጀት በተለያዩ በኪነ-ጥበብ በቴክኖሎጂ የፈጠራ ስራዎች ላይ እንዲሰማሩ ያበረታታል፤ ድጋፍ ያደርጋል፤

፮· አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባባር ወጣቶች በማህበር እንዲደራጁ፣ የመስሪያ ቦታ እንዲመቻችላቸው፣ የማምረቻ መሳሪያ አቅርቦት፣ የብድርና የቁጠባ አገልግሎት እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

፯· ለወጣቶች መብት፣ ጥቅም እና ደህንነት የሚሰሩ ማህበራት እንዲደራጁና እንዲጠናከሩ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፤

፰· ወጣቶች በከተማው አስተዳደር የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በንቃት እንዲሳተፉና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጥምረት ይሰራል፤

፱· የወጣቶችን የስራ ዕድል ፈጠራና ተጠቃሚነት ማረጋገጥ የሚችል ከልማት ስትራቴጂ ጋር የተጣጣመ ተቋማዊ አሰራር፣ አደረጃጀትና ግንባታ ስርዓት ከሚመለከታቸው ጋር ይዘረጋል፤ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

፲· ወጣቶችን በሚመለከት ከልማት ስትራቴጂ አኳያ ተቃኝቶ በወጣ ፕሮጀክት ላይ በከተማው ውስጥ ከሚሰሩ የተለያዩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር ስምምነት ይመሰርታል፣ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፣ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያቀርባል፤

፲፩· የወጣቶች ማህበራዊ ችግሮች በሁሉም በተባበረ ጥረት መፍትሄ እንዲያገኝ ያስተባብራል ተፈፃሚነቱን ይከታተላል፤

፲፪· ለአካል ጉዳተኛ ወጣቶች ልዩ ትኩረት በመስጠት በሁሉም የልማት ስራዎች ከግምት ውስጥ እንዲገቡ ለማድረግ፣ ከተለያዩ ጥቃት መከላከል፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጥቅሞቻቸው ለማስከበር ከሌሎች አካላት ጋር በትብብር ይሰራል፤

፲፫· የወጣት ማዕከላት እንዲገነቡ ያደርጋል፤ ያስተዳድራል፤ ይመራል፤ እንዲስፋፉና አቅማቸው እንዲገነባ ያደርጋል፤

፲፬· የበጎ ፈቃድ አገልግሎት በራስ መልካም ፈቃድ፣ ተነሳሽነት እና ያለማንም አስገዳጅነት ለሚሳተፉ ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፤ ያስተባብራል፤ ይመራል፤

፲፭· በበጎ ፈቃድ አገልግሎት ላይ ለሚሰማሩ ወጣቶችና ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች የዕውቅና የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤ ያበረታታል፤

፲፮· ወጣቶች ያላቸውን እውቀት፣ አቅም፣ ችሎታና ተሰጥኦ በልማት፣ በዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ተግባሮች ላይ አውለው ለህብረተሰቡ ጠቃሚ የሆኑ አገልገሎቶች ለማበርከት የሚያስችላቸው የበጎ ፈቃደኝነት ባህል እንዲያጎለብቱ ያበረታታል፤

፲፯· በከተማችን የሚገኙ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት የበጎ ፈቃድ አገልግሎትን በእቅዶቻቸውና በፕሮግራሞቻቸው ውስጥ አካትተው እንዲሰሩ ያደርጋል፤ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤

፲፰· በከተማችን ዘላቂ የበጎ ፈቃድ ፍኖተ ካርታ ያዘጋጃል፤ ግብረ-ኃይል እንዲደራጅ ያደርጋል፤ ግብረ-ኃይሉ የሚሳተፍበትን የአገልገሎት መስኮች ይለያል፤ ስልጠና ይሰጣል፤ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፡

**፴·<u>የሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮ</u>**

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-፩· ሴቶች በከተማው አስተዳደር የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በንቃት እንዲሳተፉና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጥምረት ይሰራል፤

፪· በከተማ አስተዳደሩ የሚተገበሩ ህጎች የሴቶችና ህጻናት ሁለንተናዊ መብትና ደህንነት የሚጠብቁ መሆናቸውን ይከታተላል፤

፫· በሁሉም አስፈፃሚ አካላት፣ በልማት ድርጅቶችና ልሎች የአስተዳደሩ አካላት የስርአተ ፆታን ጉዳይ በዕቅዳቸው ላይ ማካተታቸውን ይከታተላል፤

፬· የሴቶችና ህጻናት መብቶች ስለመጣሳቸው መረጃ ሲደርሰው ጉዳዩን ከሚመለከተው አካል ጋር በማጥናትና በማጥራት ተገቢው መፍትሔ እንዲሰጥ ያድርጋል፤

፭· በሴቶችና ህጻናት ጉዳይ እና በስርዓተ ፆታ እኩልነት ዙሪያ ግንዛቤና ንቅናቄ እንዲፈጠር ይደረጋል፤

፮· የሴቶችን አቅም የሚያጎለብቱ ትምህርታዊ፣ ሙያዊና የተጨማሪ ክህሎት ሥልጠናዎችን ያዘጋጃል፤ ይሰጣል፤

፯· አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ሴቶች በማህበራት እንዲደራጁና የብድርና የቁጠባ አገልግሎት እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

፰· ለሴቶችና ህጻናት መብት፣ ደህንነትና ጥቅም የሚሰሩ ማህበራት እንዲደራጁና እንዲጠናከሩ አስፈላጊውን ድጋፍ ያድርጋል፤

፱· የሴቶችና ህጻናት በሚመለከት ከልማት ስትራቴጂ አኳያ ተቃኝቶ በወጣ ፕሮጀክት ላይ በከተማው ውስጥ ከሚሰሩ የተለያዩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር ስምምነት ይመሰርታል፤ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፤ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያቀርባል፤

፲· የሴቶችና ህጻናትን ማህበራዊ ችግሮች በሁሉም የተባበረ ጥረት መፍትሄ እንዲያገኝ ያስተባብራል፤ ተፈፃሚነቱን ይከታተላል፤

፲፩· ለአካል ጉዳተኛ ሴቶችና ህጻናት ልዩ ትኩረት በመስጠት በሁሉም የልማት ሥራዎች ውስጥ ፍላጎቶቻቸው እንዲካተት ለማድረግ፣ ከተለያዩ ጥቃት መከላከል፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጥቅሞቻቸው ለማስከበር ከልሎች አካላት ጋር በትብብር ይሰራል፤

፲፪·በአስተዳደሩ ውስጥ የሴቶች ልዩ ድጋፍ መብት በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውል ሥልት ይቀይሳል፤ አፈጻፀሙን ይከታተላል፤

፲፫.ሴቶች ያላቸውን ዕውቀት፣ አቅም፣ ችሎታና ተስጥዖ በልማት፣ በዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታና በመልካም አስተዳደር ተግባሮች ላይ አውለው ለህብረተሰቡ ጠቃሚ የሆኑ አገልግሎቶች ለማበርከት የሚያስችላቸው የበጎ ፈቃደኝነት ባህል እንዲያጎለብቱ ያበረታታል፤

፲፬.ለችግር ተጋላጭ የሆኑ ሴቶችና ህጻናት የኑሮ ሁኔታ የሚሻሻልበትን ሁኔታ ያጠናል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ተግባራዊ ያደርጋሉ፤

፲፭.የአስተዳደሩን የህፃናት ማሳደግያ ተቋማትን ያስተዳድራል፤ ይመራል፤ አቅማቸው እንዲገነባ ያድርጋል፤

፲፮. በየደረጃው ያሉ የሕፃናት አደረጃጀቶችን አቅም በማጎልበት የሕፃናት ተሳትፎ እንዲያድግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ይሠራል፡፡

## ፴፩.<u>የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ</u>

ቢሮው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩. የማህበራዊ ጥበቃ ሥርዓትን በማጠናከር የነዋሪዎች ማኀበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደህንነት እና ዋስትና የሚሻሻሉባቸውና የሚጠበቁባቸው አሰራር ይዘረጋል፤ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፪.የማኀበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ለመከላከልና በችግሩ ውስጥ የሚገኙ የኅብረተሰብ ክፍሎች የተለያዩ አገልግሎት እንዲያገኙ፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይሰራል፤ በተለይም፡-

ሀ) የአካል ጉዳተኞች እኩል ዕድል ተጠቃሚና ሙሉ ተሳታፊ እንዲሆኑ፣

ለ) አረጋዊያን እንክብካቤና ድጋፍ እንዲያገኙ ተሳትፎአቸው እንዲጎለብት፣

ሐ) በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ለሚገኙ ወጣቶች የተሃድሶ አገልግሎት እንዲያገኙ ያደርጋል፤

፫.የማህበረሰብ አቀፍ ድጋፍና ክብካቤ ጥምረት ምክር ቤቶች እንዲቋቋሙ በማድረግ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ለሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎች በማህበረሰብ አቀፍ የተሀድሶ አገልገሎት እንዲታቀፉ ሙያዊ ድጋፍ ያደርጋል፤ ይከታተላል፤

፬.በማህበረሰብ አቀፍ ሊታቀፉና ሊደገፉ ያልቻሉ ጧሪና ደጋፊ የሌላቸው አረጋዊያን፣ አካል ጉዳተኞች እና ሰርቶ ለማደር አቅም በሚነሱ ደዌዎች የተጠቁ የማህበረሰብ ክፍሎች በአስተዳደሩና መንግስታዊ ባልሆኑ ማዕከላት ውስጥ ክብካቤና ድጋፍ እንዲያገኙ ያደርጋል፤ የክብካቤ መስጫ ማዕከላትን ያስተዳድራል፤ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

፭ የማህበራዊ ልማት ፈንድ የሚያስገኝፕሮጀክት ያዘጋጃል፤ ሲፈቀድ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፮.መስራት የማይችሉና ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን የህብረተስብ ክፍሎች በሴፍቲኔት ቀጥታ ድጋፍ ማዕቀፍ ውስጥ ተጠቃሚ ያደርጋል፤ ይከታተላል፤ ይደግፋል፤ ያስተባብራል፤

፯.በአሰሪና ሠራተኛ ወገኖች መካከል የሥራ ቦታ ሰላም እንዲሰፍን የትምህርትና የሥልጠና አገልግሎት ይሰጣል፣ የሙያ ምክር አገልግሎት ስለሚስፋፋበት፣ ክፍት የሥራ መደቦች

ስለሚመዘገቡበትና ሥራና ሠራተኛ ስለሚገናኙበት ዘዴ ይቀይሳል፣ ሲጸድቅም ተግባራዊ መሆኑን ያረጋግጣል፣

፫.የከተማውን የስራ ሰምሪት እንዲሁም የሙያ አመዳደብ ጥናት ያደርጋል፣

፱.በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ህግ በተደነገገው መሰረት በከተማው ውስጥ የሚደራጁ የአሰሪና ሰራተኛ የሙያ ማህበራትን ይመዘግባል፣ ድጋፍ ይሰጣል፣ ሲፈርሱ ምዝገባውን ይሰርዛል፣

፲.በአሰሪና ሠራተኛ ወገኖች ድርድር ወቅት የሚቀርቡ የኅብረት ስምምነት ድርድር ልዩነቶች በመግባባት እልባት እንዲያገኙ ለማድረግ አስማሚዎችን በመመደብ ጥረት ያደርጋል፣ የሕብረት ስምምነት በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ህግ መሰረት መፈፀማቸውን በማረጋገጥ የህብረት ስምምኖችንና ማሻሻያቸውን ይመዘግባል፣

፲፩.የወል የሥራ ክርክሮችን በሚመለከት ተከራካሪ ወገኖችን ለማስማማት ጥረት ያደርጋል፣

፲፪.አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር በከተማው ውስጥ በሥራ ላይ ስለተሰማራውና ሥራ አጥ ስለሆነው የሰው ኃይል እንዲሁም ስለሙያ መደብ ጥናትና ምርምር ያደርጋል፣ መረጃዎችን ይይዛል፣

፲፫.ድርጅቶች የስራ ሁኔታን፣ የሙያ ደህንነትና ጤንነትንና የስራ አካባቢን ለመጠበቅ የወጡ የስራ ሁኔታ ደረጃዎችና የመከላከያ ዘዴዎች በሥራ ላይ ማዋላቸውን ይቆጣጠራል፣

፲፬.በከተማው ውስጥ ሥራና ሠራተኛ ለሚያገናኙ ኤጀንሲዎች የብቃት ማረጋገጫ በህግ መሰረት ይሰጣል፣ ድጋፍ ያደርጋል፣ በሕግ መሰረት መሥራታቸውን ያረጋግጣል፣ ይሰርዛል፣

፲፭.በስራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ እና በሠራተኛ መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶች በስምምነት እንዲያልቁ ሙያዊ ድጋፍ ያደርጋል፣

፲፮. በአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ህግ መሰረት የከተማው አስተዳደር የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ አባሎችን ይሾማል፣ ያሰናብታል፣ ተግባርና ኃላፊነታቸውን ይከታተላል፣

፲፯.በዘላቂ ማረፊያ የሚፈፀሙ ቀብሮችን መረጃ ይይዛል፣ ያጠናቅራል፣ የቀብር ምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ የአፅም ዝውውር ፈቃድ ይሰጣል፣ የባይተዋር ቀብር ያስፈፅማል፣

፲፰.በበጎ አድራጎት ማህበር ወይም ድርጅት ውስጥ ቆይተው በሞት የተለዩ እና ቀባሪ የሌላቸው ባይተዋሮች አስክሬኖች በአግባቡ እንዲከፈኑ፣ እንዲቀበሩ መረጃዎች እንዲሰጡ ያደርጋል፣

፲፱.የዕድር ምክር ቤቶች በዘላቂ ማረፊያ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የህብረተሰቡን ፍላጎት መነሻ ያደረገ ጥናት እንዲያደርጉ ይደግፋል፣ ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ዘዴዎችን በመጠቀም የቀብር አገልግሎት ጥያቄ ከተሟላ መረጃ ጋር እንዲቀርብ እና አገልግሎቱ እንዲሰጥ ያደርጋል፣

፳.ህብረተሰቡ በመረዳጃ ዕድር ተደራጅቶ የመረዳዳት ወግና ባህሉን እንዲጠናከር በከተማው ውስጥ ያሉትን መሠረታዊ እድር እና በየደረጃው የሚገኙት የእድር ምክር ቤቶችን ይመዘግባል፣ ፈቃድ ይሰጣል፣ ባህላዊና ታሪካዊ እሴታቸው ጠብቀው እንዲሄዱ ድጋፍ ያደርጋል፣ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ላይ ያላቸውን ተሳትፎ እንዲያጠናክሩ ያበረታታል፣

፳፩·በከተማው ውስጥ መደበኛ በሆነና መደበኛ ባልሆነ ስራ ላይ የተሰማራውንና በስራ አጥነት ስለሚገኘው የሰው ኃይል፣ የስራ ስምሪት እንዲሁም ስለሙያ መደብ ጥናት ያደርጋል፡፡ የስራ ገበያ መረጃዎች ስርዓት ይዘረጋል፣ ይሰበስባል፣ ያጠናክራል፤ ያሰራጫል፤

፳፪·ለሥራ ወደ ውጭ አገር ለመሄድ ፍላጎት ላላቸው ዜጎች ስለተቀባይ አገር ሁኔታ፣ በሚሰማሩበት የሥራ መስክ ሊኖራቸው ስለሚገባ ክህሎት፣ ስለመብታቸውና ኃላፊነታቸው እና ስለመሳሰሉት ጉዳዮች የቅድመ-ስምሪትና የቅድመ-ጉዞ ግንዛቤ ማሳደጊያ ሥልጠና እንዲያገኙ ያደርጋል፤

፳፫·የከተማ ነዋሪ ስለ ውጭ አገር ሥራ ስምሪት ተጨባጭ ሁኔታ ትክክለኛ እና ወቅታዊ መረጃ እንዲያገኝ የመገናኛ ብዙኃንንና ልሎች አማራጭ ዘዴዎችን በመጠቀም ቀጣይነት ያለው ከተማ አቀፍ የግንዛቤ ማሳደጊያ ሥራዎችን ያከናውናል፡፡

**፴፪·<u>የባህል፣ ኪነ ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ</u>**

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩· የአዲስ አበባ ትያትርና ባህል አዳራሽ፣ የራስ ቲያትር፣ የሀገር ፍቅር ቲያትርና የህፃናትና ወጣቶች ትያትር ቤቶችን እና የሲኒማ ቤቶች ድርጅት በበላይነት ይመራል፤ የስተባብራል፤

፪· በከተማዋ ውስጥ የሚገኙ ታሪካዊ ቅርሶችን ያጠናል፤ በሕግ መሠረት ይጠብቃል፤ ያስጠብቃል፤ የሀገሪቱን ብሔር ብሔረሰቦች ታሪክና ባህል ተመዝግቦ እንዲያዝ ያደርጋል፤ የባህል ሙዝየሞችን ያደራጃል፤ ያስተዳድራል፤ ቋንቋዎችና ሥነ ፅሑፎች እንዲዳብሩ ያደርጋል፤

፫· በባህል ተፅዕኖ ሳቢያ ማህበራዊ ዕድገትን የሚያጓትቱ አመለካከቶችን፣ እምነቶችንና ልማዳዊ አሠራሮችን የመለወጥ ተግባሮችን ያከናውናል፤

፬· የባህል ዘርፍ ልማዳዊ አስተዋጽኦ እንዲስፋፋ ያድርጋል፤ ባህል፣ ኪነጥበብ፣ ሥነ ጥበብ እና የፈጠራ ችሎታ በከተማው ውስጥ እንዲዳብርና እንዲስፋፋ ያደርጋል፤ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና ግብረ-ገባዊ ያልሆኑ ድርጊቶችን የሚያራምዱና የሚያስፋፉ እንቅስቃሴዎችን ይከታተላል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ሕጋዊ እርምጃ እንዲወስድ ያደርጋል፤

፭· በከተማው አስተዳደር ሥር የሚገኙ ቤተ መጽሐፍትን፤ ቤተመዛግብትና አብያተ-መዘክርን ያስተዳድራል፣ ይመራል፤ እንዲቋቋሙና እንዲስፋፉ ያደርጋል፤ በባህል ዘርፍ የህዝብን ተሳትፎ መሠረት ለማስያዝ ልሎች የባህል ተቋማት እንዲስፋፉ ያድርጋል፤

፮· የከተማውን የቱሪዝም መስህቦችና መልካም ገጽታ ለሀገር ውስጥና ለውጪ እህት ከተሞች የቱሪዝም ገበያ በስፋት ያስተዋውቃል፤

፯· የከተማው የቱሪስት መስህቦችና መዳረሻዎችን ተለይተው እንዲታወቁና ለቱሪዝም አመቺ ሆነው እንዲለሙና እንዲደራጁ፤ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች እንዲስፋፉ፣ የከተማው ነዋሪም ከቱሪዝም ጥቅሞች ተካፍይ እንዲሆን ያድርጋል፤

፰· ለቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሙያ ፍቃድ ይሰጣል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

፱· የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ደረጃዎችን ይወስናል፤ ተፈፃሚነቱን ይቆጣጠራል፤

፲· በቱሪዝም የሰመረ አገልግሎት እንዲኖርና የቱሪስቶችም ደህንነት እንዲረጋገጥ ከሚመለከታቸው ጋር ይሠራል፤

፲፩· የቱሪዝም ሴክተር የማስፈፀም አቅም ይገነባል፤

፲፪· የባህልና ቱሪዝም መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያጠናቅራል፣ ያሠራጫል፤

፲፫· በከተማው ውስጥ የሚንቀሳቀሱ የኪነ ጥበብና የቱሪዝም ተቋማትን፣ ማህበራትን፣ ክበባትን፣ ሞያተኞችን በሕግ መሠረት ይመዘግባል፤ ፈቃድ ይሰጣል፤ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፤ በባህልና ቱሪዝም ዘርፍ የተሰማሩ መንግስታዊና መንግስታዊ ላልሆኑ ተቋማት ድጋፍ ያደርጋል፡፡

<u>፴፫·የፕላንና ልማት ኮሚሽን</u>

ኮሚሽኑየሚከተሉትስልጣንናተግባራትይኖሩታል፡-

፩· የከተማውን የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ እቅድ ያዘጋጃል፤ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤ ግብረ መልስ ይሰጣል፤ ይገመግማል፤ ሪፖርት ለሚመለከተው ያቀርባል፤

፪· የከተማውን መዋቅራዊ ፕላን ያዘጋጃል ፤ ሲፀድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፫· የአካባቢ ልማት ፕላን ያዘጋጃል፤ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤ ሲፀድቅ ተግባራዊ መሆኑን ያረጋግጣል፤

፬· የተቀናጀ የመሰረተ ልማት ፕላን ያዘጋጃል፤ያፀድቃል፤ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤

፭· የፕላን ዝግጅትና አተገባበር የጥናትና ምርምር ሥራዎች ያከናውናል ፣መረጃዎችን ይሰበስባል ፣ያቀነባብራል፤ያሰራጫል፤

፮· የሕዝብ ተግባቦትና ስርፀት ስራዎችን ያከናውናል፤ ተደራሽ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመጠቀም የመረጃ ስነድና ስርጭት ቋት ያደራጃል ፣ ጥቅም ላይ ያውላል፤

፯· የከተማው አስተዳደር ፕላን ፈፃሚና አስፈፃሚ አካላት ድጋፍና ምክር ይሰጣል፤

፰· በሚያመነጫቸው ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ ፕላኖች፣ የልማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች አካል ጉዳተኞች፣ አረጋዊያን፣ የሴቶችንና የወጣቶች ጉዳዮች እንዲካተቱ መደረጋቸውን ያረጋግጣል፤

፱· ፕላን በሚጥስ ማናቸውም አካል ላይ በሕግ መሠረት እርምጃ ይወስዳል፤ ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል፤

፲·አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ላሉ የከተማው አስተዳደር አካል በውክልና ሊሰጥ ይችላል፤

፲፩·ከተማ ፕላን ለማዘጋጀት የሚያስችል መሠረታዊ የከተማ ካርታ ከሀገሪቱ ጂኦዳቲክ ካርታ ጋር በተገናዘበ መልኩ ያዘጋጃል፤እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤ ያደራጃል፤ ያሰራጫል፤

፲፪·የፀደቀ ፕላን በሕግ መሠረት እንደ የአግባቡ ያሻሽላል፤ ያጣጥማል፤

፲፫· የፕላን፣ የዲዛይንና የግንባታ ፈቃድ ደረጃዎችን አፈፃፀም የሚመለከቱ ወቅታዊ ሪፖርቶችን ፕላንፈፃሚና አስፈፃሚ አካላት እንዲያቀርቡና የመስክ ምልከታ እና ጥናት በማድረግ ሪፖርት ያቀርባል፤

፲፬· የከተማውን ዝርዝር የሥነ ህዝብ ጥናትና ትንበያ ያካሂዳል፣ ውጤቱንም ለከተማው አስተዳደር አካላትና የልሎች ባለድርሻ አካላት ያሰራጫል፤ የስነ ህዝብ ፖሊሲ በከተማው ውስጥ ይፈፅማል፤ ያስፈፅማል፤

፲፭· የከተማውን አመታዊ አጠቃላይ የምርት እድገት ለማስገኘት የሚያስፈልገውን የካፒታልና የምርታማነት እድገት መነሻዎችን ይገምታል፤ ውጤቱንም ለሚመለከታቸው የከተማው አስተዳደር አካላትና ለባለድርሻ አካላትያሰራጫል፤

፲፮· የከተማውን የምርት እድገት ግቦች የፖሊሲና የህግ ሪፎርም እርምጃዎች ጋር የተጣጣሙ የቁጠባ፣ የኢንቨስትመንትና የወጪና የገቢ ንግድ ከተማ አቀፍ የማክሮ ኢኮኖሚ ግቦችን ያዘጋጃል፤ ሲፀድቅም ተግባራዊ መሆኑን ይከታተላል፤

፲፯·ከአጠቃላይ ከተማ አቀፍ ምርት የኢንዱስትሪ፣ የአገልግሎት ዘርፎችና የከተማ ግብርና የተናጠል ድርሻን ይለያል፤ ውጤቱንም ለሚመለከታቸው የከተማው አስተዳደር አካላትና ለባለድርሻ አካላት ያሰራጫል፤

፲፰· የከተማውን በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪና በአገልግሎት ዘርፎች መካከል የሚኖረውን የግብዓት አቅርቦት ፍላጎት ይተነትናል ፤ውጤቱንም ለሚመለከታቸው የከተማው አስተዳደር አካላትና ለባለድርሻ አካላት ያሰራጫል፤

፲፱·ለሬዚለንት ስትራቴጂ ትግበራ ከተለያዩ የሀገር ውስጥ፣ የክልል እና የውጭ ሀገር የግል ዘርፍ አካላት ጋር አጋርነትን ይመሰርታል፤

፳· ለሁሉም ዘርፎች የሬዚሊየንስ ስትራቴጂ ለማስፈፀም አዋጭ ፕሮጀክቶችን ያሰናዳል፣ ለተፈፃሚነታቸውም ተዛማች የሆነ የገንዘብ ምንጭ መገኘቱንና ለታለመለት ዓላማ መሰራጨቱን ያረጋግጣል፤

፳፩· በሬዚሊየንስ አግባብ ፍላጎት መርና ችግር ፈቺ የሆነ ጥናት የተፅእኖ ዳሰሳ ከዩኒቨርሲቲ፣ ከምርምር ማዕከላትና ከልሎች ትምህርታዊ አካላት ጋር በመተባበር ያከናውናል፤

፳፪· ከሚመለከታቸው የከተማው አስተዳደር አካላት ጋር ተከታታይ ምክክር በማድረግ የሚተገበሩ ፕሮግራሞችንና ፕሮጀክቶችን እንዲሁም ሊወሰዱ የሚገባቸውን የፖሊሲና የህግሪፎርም እርምጃዎችን የሚዘረዝር የመካከለኛና የረጅም ጊዜ ማህበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ የዘርፍ ፕላን ያዘጋጃል፤ ሲፀድቅም ተግባራዊ መሆኑን ይከታተላል፤

፳፫· ተዋረዳዊ አደረጃጀት ያላቸው የከተማው አስተዳደር ተቋማት አጠቃላይ ፕላን ተመጋጋቢ በሆነ መንገድ ተግባራዊ ማድረግ፤ የሚፈፅሟቸውን ተግባራት የሚያሳይ የተቀናጀ የመካከለኛና

የረጅም ጊዜ ማህበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ ልማት ፕላን አፈፃፀም መርሀ-ግብር ያዘጋጃል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ መሆኑን ይከታተላል፡፡

፴፬·የኢንቨስትመንት ኮሚሽን

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

፩·የኢንቨስትመንት አመችነትን ያጠናል፣ ያስተዋውቃል፣ ያስተባብራል፣ ያስፋፋል፣ ምክርና የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፣

፪·የኢንቨስትመንት ጥያቄዎች ሲቀርቡለት በህግ መሰረት መርምሮ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ማግኘት የሚገባቸውን በማረጋገጥ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ የንግድ ወይም ኢንዱስትሪ ፈቃድ ማግኘት እንዲችሉ አግባብ ወዳለው አካል ያስተላልፋል፣

፫·ለኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የማምረቻና የመሸጫ ቦታዎች፣ የፋይናንስና የብድር አገልግሎቶች፣ የጥሬ ዕቃና የማምረቻ መሳሪያዎች የማግኘት ዕድልና የተለያዩ የመሰረተ ልማት አውታሮች የሚሟሉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣

፬·ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋትና ለማበረታታት እንዲሁም የከተማውን መልካም ገጽታ ለመገንባት የሚረዱ ጽሑፎችን ያዘጋጃል፣ ያሠራጫል፣ ዓውደ ርዕዮችን፣ ዓውደ ጥናቶችንና ሴሚናሮችን ያዘገጃል፣

፭· ኢንቨስትመንትን ለማስፋት በባለሀብቶች፣ በመንግስታዊ መሥሪያ ቤቶችና በሌሎች ኢንቨስትመንትን በተመለከተ አግባብነት ባላቸው አካላት መካከል ግንኙነት እንዲኖር ያደርጋል፣ ያስተባብራል፣

፮·የኢንቨስትመንት ፈቃድ የሰጣቸውን ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች አፈፃፀም ይከታተላል፣ የኢንቨስትመንት ፈቃዱ የያዛቸው ሁኔታዎች መከበራቸውንና ማበረታቻዎች ለታለመላቸው ዓላማ መዋላቸውን ያረጋግጣል፣ ከህግ አግባብ ውጪ ሆነው ሲገኙ ይሰርዛል፣

፯·የድህረ-ኢንቨስትመንት የድጋፍና ክትትል ሥራን ለዚህ ዓላማ ከተቋቋሙ አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል፣

፰·የኢንቨስትመንት ፈቃድ ላወጡ ባለሀብቶች የአንድ መስኮት አገልገሎት የሚያገኙበትን አሰራር ስርዓት ይዘረጋል፣

፱·እንደ ኢንቨስትመንቱ ዓይነት ለፕሮጀክቱ የሚያስፈልገውን መሬት አግባብ ካለው አካል ጋር በመቀናጀት ለከተማው አስተዳደር አቅርቦ ያስወስናል፣ ተፈፃሚ እንዲሆኑ ይከታተላል፣ ይዋዋላል፣ ከህግ አግባብ ውጪ ሆነው ሲገኙ ይሰርዛል፡፡

፴፭·የእሳትና አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

፩.የመረጃና ቴክኖሎጂ ማዕከል በማቋቋም ከአደጋ በፊትም ሆነ በአደጋ ጊዜ እና በኃላ የተማከለ የመረጃ ልውውጥ ስርዓት እንዲኖር ያደርጋል፣ በከተማ ደረጃ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር የመረጃ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፤

፪.የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች መንስኤና የተጋላጭነት ደረጃና ትንናት መረጃ ያሰባስባል፤ የቅድመ አደጋ ጠቋሚ ጥናቶችን በማካሄድ አስፈላጊውን የቅድመ ማስጠንቀቂያ እርምጃዎችን ይወስዳል፤ እንዲወሰድ ያደርጋል፤ ይከታተላል፤

፫.በሰው ሰራሽም ሆነ በተፈጥሮ ሊከሰት የሚችል አደጋን የመከላከል እና የአደጋ ጉዳት ቅነሳና የማጣጣም ስራን ይሰራል፤ልሎች ተቋማትም እንዲሰሩ ያደርጋል፤

፬.በከተማዋ የሚገኙ ተቋማት የአደጋ ስጋት ቅነሳ እቅድን በልማት እቅዶቻቸው ውስጥ እንዲያካትቱ ያደርጋል፤ ተግባራዊ እንዲሆኑ ይከታተላል፤

፭.የተቋሙ ባለሙያዎች፣ ልዩ ልዩ ተቋማትና ህብረተሰቡ ስለ አደጋ ስራ አመራር ስልጠና የሚያገኙበት የስልጠና ማእከል ያደራጃል፤

፮.በተከታታይ ወይም በዕቅድ ላይ ተመስርቶ የናሙና ልምምዶች ያከናውናል፤ እንዲከናወኑም ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤ በአደጋ ምላሽ እቅድ ላይም የማስተካከያ እርምጃዎችንም ይወስዳል፤

፯. የአደጋ መከላከያና መቆጣጠሪያ መሳሪያዎችን፣ የአደጋ ጊዜ ማምለጫ ደረጃዎች፣ የእሳትና የጭስ፣ የነበልባል እና ልሎች አደጋ ጠቋሚ መሳሪያዎች በአገልግሎት መስጫ ልዩ ልዩ ተቋማት መተከላቸውንና በአግባቡ መስራታቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ እርምጃ ይወስዳል፤ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

፰.ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ ለህዝቡ ለማድረስ ሁሉን አቀፍ የቅድመ አደጋ ማስጠንቀቂያ ስርዓት ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤ ለህብረተሰቡ የቅድመ አደጋ ማስጠንቀቂያ መረጃዎችን፤ በአደጋ ወቅት መውሰድ ያለባቸውን እርምጃዎች እና የደረሰውን አደጋ በተመለከተ ወቅታዊ መረጃዎችን የማሰራጨት ተግባር ያከናውናል፤

፱.በአደጋ የተጎዱና የተፈናቀሉ አካላት አጠቃላይ የጉዳት መጠን፣ ክስተትና ፍላጎት መረጃ በማሰባሰብ ይተነትናል፤ ያደራጃል፤ ለሚመለከተው አካል የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፤ ሲወሰንም ተከታትሎ ይፈጽማል፤ ያስፈጽማል፤

፲.በከተማው የአደጋ ተጎጂዎችና ተፈናቃዮች ወቅታዊና ተደራሽ የሆነ የአደጋ ምላሽና መልሶ ማቋቋም የአደጋ ምላሽ አሰጣጥ ስራ አመራር ስርዓት ይዘረጋል፤

፲፩.በተከሰቱ አደጋዎች ምክንያት የተፈጠሩ ተጎጂዎችና ተፈናቃዮች መጠን የአፋጣኝ መረጃ ትንተና መሰረት በማድረግ በከተማ ደረጃ የአደጋ ጊዜ አስቸኳይ አዋጅ የሚያስፈልጋቸው ሲሆን ለሚመለከተው አካል የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፤

፲፪·በአደጋ ክስተት ወቅት የሚመለከታቸውን መስሪያ ቤቶችና ነዋሪዎችን በማስተባበር ፈጣን ምላሽ ማለትም የነፍስ አድን እርዳታ ያደርጋል፤ ለድንገተኛ አደጋዎች የቅድመ ሆስፒታል ህክምና እና አምቡላንስ አገልግሎት ይሰጣል፤

፲፫·መንግስታዊ፣ መንግስታዊ ያልሆኑና የግል ድርጅቶችን እንዲሁም ሌሎች በከተማው ውስጥ በአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ አቅርቦትና መልሶ ማቋቋም ተግባራት ላይ ሚና ያላቸው ተቋማት ያስተባብራል፤

፲፬·የአደጋ ስጋት ስራ አመራር መሰረተ ልማቶችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ያዘጋጃል፤ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፲፭·በአደጋ ምክንያት ከቤት ንብረታቸው የተፈናቀሉ የህብረተሰብ ክፍሎች ጊዜያዊ ድጋፍና መልሶ የማቋቋም ተግባር ያከናውናል፤

፲፮·ለአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ አቅርቦት ምላሽ ስራ ብቻ የሚውል የአደጋ ጊዜ ፈንድ፣ ምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆነ ቁሳቁስ በመጠባበቂያነት ይይዛል፤ ያደራጃል፤ ያስተዳድራል፤ ያሰራጫል፤

፲፯·አደጋ ስጋት ቅነሳ ስራዎች እና በአደጋ ወቅት የአስቸኳይ ጊዜ ምላሽና እርዳታ አቅርቦት አገልግሎቶች ላይ የሚሳተፉ በጎ ፍቃደኞችን በመመልመል፣ በማደራጀትና ሙያዊ ስልጠናዎች በመስጠት የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ተግባራት ላይ ተባባሪ እንዲሆኑ ይሰራል፣

፲፰·በአደጋ ስራ አመራር ሥርዓት ውስጥ ተሳታፊ በሚሆኑ ባለድርሻ አካላት መካከል ቅንጅታዊ አሰራርን ለማስፈንና ውጤታማነታቸውን ለማረጋገጥ የጋራ መድረኮች ይመሰርታል፣ ያስተባብራል፤

፲፱·አግባብ ባለው ህግ መሰረት አደጋ በይፋ መገለጹን ተከትሎ አግባብ ባለው አካል ሲወሰን ከተለያዩ አካላት ለምላሽ ስራ የሚውል ሀብት ያሰባስባል፣ ያስተዳድራል፣ በባለድርሻ ተቋማትና በራሱ አማካኝነት ለምላሽ ስራ ጥቅም ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

፳·ፓራሚሊተሪ ሰራተኞችን ካቢኔ በሚያወጣው ደንብ መሠረት ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፡፡

**፴፮·የአካባቢ ጥበቃና አረንጓዴ ልማት ኮሚሽን**

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩·የተፋሰስና አረንጓዴ አካባቢዎች ልማት ኤጀንሲን እና ጉለሌ የእፅዋት ማዕከልን በበላይነት ያስተባብራል፤ ይመራል፤

፪·የአካባቢ ጥበቃ ስታንዳርድ ያዘጋጃል፤ አካባቢ እንዳይበከል የመከላከያ ስልት ይቀይሳል፣ አግባብ ያላቸውን አካላት ከአካባቢ ጥበቃ አንፃር ያስተባብራል፤

፫·የአካባቢ ጥበቃ፣ የተፈጥሮ ሃብት የዘለቄታ አጠቃቀም እንዲኖርና እንዳይባክን ተገቢ ግንዛቤ ይፈጠራል፤ ስለ አካባቢ ጥበቃ በተለያዩ መድረኮች፣ አደረጃጀቶች እና በመገናኛ ብዙሃን ትምህርት ይሰጣል፤

፬.ከኢንዱስትሪ ከልሎች አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚመነጩ ዝቃጭ፣ ተረፈ ምርት፣ ቆሻሻ በሕግ መሠረት መወገዱን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ በህግ አግባብ እርምጃ ይወስዳል፤ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

፭.ከተለያዩ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚመነጩ የድምጽ እና የአየር ብክለት በህግ መሰረት ይቆጣጠራል፤ እርምጃ ይወስዳል፤ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

፮.የአካባቢ ጥበቃ ሕጎችን መሠረት በማድረግ የማምረቻና የአገልግሎት መስጫ ተቋማት እና ልሎች አካባቢ ላይ ተፅእኖ የሚያሳድሩ አካላት የብክለት መከላከል የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤

፯. የከተማው የካባና ልሎች ተቆፋሪ ማዕድናት ሥፍራዎች ያላቸውን የማዕድን ክምችት መጠን ይለያል፤ ለልማት ያዘጋጃል፤ ከአደጋ ነጻ መሆኑን ያረጋግጣል፤

፰.የካባ ማምረት ሥራ ለሚያካሂዱ ፈቃድ ይሰጣል፤ ቁጥጥር ያደርጋል፤

፱.የተለያዩ ዕፅዋት የሚተከሉበትን ቦታና የሚሰጡትን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ባህላዊና አካባቢያዊ ጠቀሜታ በማጥናት ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፤ በከተማው መሪ ፕላን ለመናፈሻ፣ ለደን፣ ለወንዝ ዳርቻና ለሌላ አረንጓዴ ቦታ ልማት በተከለለ ቦታዎች ላይ የሚተከሉትን ዕፅዋት አይነት በሚመለከት ያማክራል፤ ያስተዋውቃል፤

፲.ያልተሞከሩና የማይታወቁ ከአካባቢ ጋር ተስማሚና ጠቃሚ የሆኑ የዕፅዋት ዝርያዎች በከተማው ማልማት ለሚፈልጉ ሰዎች ፈቃድ ይሰጣል፤

፲፩.በመንግስትም ሆነ በግል የይዞታ ክልል የለሙ ዛፎችን ለመቁረጥ ሲፈለግ ፈቃድ ይሰጣል፣ ከባለስልጣኑ ዕውቅናና ፈቃድ ውጭ እንዳይቆረጡ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤

፲፪.በአስተዳደሩ ይዞታ ስር የሚገኙ ጥብቅ ደኖች በሥርዓት መጠበቃቸውን ያረጋግጣል፤

፲፫.የደን ቦታዎች፣ የወንዝ ዳርቻዎች፣ የጋራ መገልገያ አረንጓዴ ቦታዎች ለታለመላቸው ዓላማ መዋላቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

፲፬.በተፋሰስና በአረንጓዴ አካባቢዎችልማትና አገልግሎት ዘርፎች መሠማራት ለሚፈልጉ የግል ባለሀብቶች፣ የሃይማኖት ድርጅቶች፣ የሰፈር ነዋሪዎች ወይም ልሎች አካላት በየበኩላቸው የሚያቀርቡትን ጥያቄና የልማት ዕቅድ መርምሮ ፈቃድ ይሰጣል፤ የአረንጓዴ ልማት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፡፡

**፴፮.<u>የአርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን</u>**

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩.የግብርና ምርት በጥራት የሚመረትበት፣ ለገበያ የሚቀርብበትን እና የግብርና ልማት የሚጎለብትበት ስልት ይቀይሳል፤ ያስፈጽማል፤

፪.የከተማው ነዋሪ በከተማ ግብርና እንዲሳተፉ ያበረታታል፤ ሙያዊ ድጋፍና አስፈላጊ ግብዓቶችን ያቀርባል፤

፫.በግብርናው ዘርፍ መረጃዎችን በማሰባሰብ፣ በማጠናቀርና በመተንተን ለተጠቃሚዎች ያሰራጫል፤

፬.የእንስሳት በሽታዎች ስርጭትን ያጠናል፤ በበሽታ ስርጭት የተነሳ መወሰድ ያለባቸውን እርምጃዎች ለመንግስትና ለአርቢዎች ያሳውቃል፤ ለእንስሳት አርቢዎች የእንስሳት ህክምናና የክትባት አገልግሎት ይሰጣል፤ እንዲሰጥ ያደርጋል፤ የዕብድ ውሻ በሽታ መከላከያ ክትባት ይሰጣል፤ ባለቤት የሌላቸውን ውሾች ያስወግዳል፤

፭.ለእንስሳት አርቢዎች የማዳቀል አገልግሎት ይሰጣል፤ የተሻሻለ የግብርና ቴክኖሎጂ ውጤቶች፣ ምርጥ ዘርና ማዳበሪያ ለአርሶ አደር እንዲዳረስ ያደርጋል፤ ውጤታማነታቸውንም ይከታተላል፤ ለገበሬዎች ትምህርትና ሥልጠና እንዲሁም የሙያ ድጋፍ ይሰጣል፤

፮.የእንስሳት ማራቢያና ማባዣ ማዕከላትን ያቋቁማል፤ ያስፋፋል፤ ያስተዳድራል፤

፯.የእንስሳትና የእጽዋት የኳራንቲን አገልግሎት ይሰጣል፤ በከተማው ውስጥ አገልግሎት ላይ ሊውሉ የሚችሉ የእንስሳት መድሃኒቶች ጥራት ደረጃቸውን የጠበቁና የአገልግሎት ዘመናቸው ያላለቀ መሆኑን ያረጋግጣል፤ የአገልግሎት ዘመናቸው ያለፈ መድሃኒቶችን ያስወግዳል፤

፰.በመዋቅራዊ ፕላኑ ለእንስሳት፣ ለሰይወክላል፣ ለአትክልትና ፍራፍሬ ገበያዎችና ለከተማ ግብርና የተከለሉ ቦታዎችን ከሚመለከተው አካል ጋር በመቀናጀት እንዲዘጋጁና በዘመናዊ መንገድ እንዲሰሩ ያደርጋል፤

፱.በግል የሚቋቋሙትን የእንስሳት ጤና ክሊኒኮች፣ ላብራቶሪዎች፣ የቆዳና ሌጦ መጋዘኖች፣ ጸረ-ተባይ ማከማቻ መጋዘኖችና መሸጫ መደብሮች ደረጃና ጥራት ጠብቀው መስራታቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

፲.በህግ በሌላ ሁኔታ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በመንግስት፣ በማህበራት እና በግል ቄራ ድርጅቶች የሥጋ ምርመራ አገልግሎት ይቆጣጠራል፤ ጤናማ ሥጋ ለተጠቃሚዎች መቅረቡን ያረጋግጣል፤ ሕገወጥ የእንስሳት እርድና በሕገወጥ መንገድ የታረዱ ስጋ ዝውውርን ይቆጣጠራል፤ በስጋ ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎች የምርት ጥራትና የሐይጅን ቁጥጥር ያካሂዳል፤

፲፩.ለልማት ይዞታቸውን የለቀቁ አርሶ አደሮች ወቅታዊና ተመጣጣኝ ካሳ መከፈሉን፣ የይዞታ ማረጋገጫ እና መሠረተ ልማት የተሟላለት ምትክ ቦታ ማግኘታቸውን ያረጋግጣል፤

፲፪.መጠለያ ለሌላቸዉ ለልማት ይዞታቸውን የለቀቁ አርሶ አደሮች ከሚመለከታቸው የአስተዳደሩ አካላት ጋር በመቀናጀት የመኖሪያ ቤት እንዲያገኙ ያደርጋል፤ የመኖሪያ ቤቱ እስኪዘጋጅ ድረስ የቤት ኪራይ እንዲሰጥ ያደርጋል፤

፲፫.በልማት ምክንያት ከመኖሪያ አካባቢያቸው የተነሱ አርሶ አደሮችን ቋሚና ጊዜያዊ የሥራ እድል ፈጠራ ፕሮግራሞች ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ የክህሎት ሥልጠና እንዲያገኙ ያደርጋል፤ በተሰጣቸው የክህሎት ሥልጠና መሠረት በአካባቢው በሚፈጠሩ የሥራ ዕድሎች ቅድሚያ ተጠቃሚ መሆናቸውን ይከታተላል፤

፲፬·የአርሶ አደሮችን የኑሮ ሁኔታ በዘላቂነት ለማሻሻል የሚያስችሉ አዳዲስ ፕሮጀክቶችን ይቀርፃል፣ ለፕሮጀክቱ የሚያገለግሉ የማምረቻ እና የመሸጫ ማእከላትን እንዲያገኙ ያደርጋል፣

፲፭·በከተማው በተለያዩ የግብርና ዘርፍ ለተሰማሩ አካላት ምርትና ምርታማነታቸዉ እንዲጨምር ዘመናዊ የግብርና ግበአት እንዲቀርብላቸው፣ ሙያዊ ድጋፍና ምክር እንያገኙ ያደርጋል፣

፲፮·በከተማዉ አስተዳደር ክልል ዉስጥ የሚኖሩና ኑሮአቸዉ በግብርና ስራ ላይ የተመሠረተ አርሶ አደሮች የያዙት መሬት መጠን ልኬት እንዲወሰድና የመጠቀሚያ ፈቃድ እንዲሰጣቸዉ ከሚመለከተው አካል ጋር ይሰራል፣

፲፯·ምንም ገቢ የሌላቸዉና መስራት የማይችሉ አርሶ አደሮች ከሚመለከተው አካል ጋር በመቀናጀት የማህበራዊና የቀጥታ ድጋፍ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፣

፲፰·ለልማት ይዞታቸውን የለቀቁ አርሶ አደሮች የተሰጣቸውን ካሳ አቀናጅተው ወደ ተሻለ ልማትና የኢንቨስትመንት አማራጮች የሚሰማሩበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ ይደግፋል፣ይከታተላል፣

፲፱·ለልማት ይዞታቸውን የለቀቁ አርሶ አደሮችን መረጃ አደራጅቶ ይይዛል፣

፳· የተሻለ ልምድና ሀብት ያለቸዉ ለልማት ይዞታቸውን የለቀቁ አርሶ አደሮችና ቤተሰቦችን በመለየት አዋጭ በሆኑ የኢንቨስትመንት አማራጮች ላይ በግል ይዞታቸው ወይም ተደራጅተዉ የሚሰማሩበትን ስልት ይቀይሳል፣ ተግበራዊ ያደርጋል፣ ይደግፋል፣ ይከታተላል፣

፳፩· በህብረት ስራ ማህበራት ህግ እና በልሎች አግባብነት ባለዉ የንግድ ህግ መሰረት ለልማት ይዞታቸውን የለቀቁ አርሶ አደሮች እንዲደራጁ በማድረግ ያቋቁማል፣ ይከታተላል፣ ይደግፋል፡፡

## ፴፰·<u>የስፖርት ኮሚሽን</u>

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩·የከተማ አስተዳደሩን የስፖርት ትምህርትና ሥልጠና ማዕከላትን ያስተዳድራል፣ ይመራል፣ እንዲስፋፉና አቅማቸው እንዲገነባ ያደርጋል፣

፪·የከተማው ነዋሪ በስፖርት ለሁሉምና በባህላዊ ስፖርት ተሣታፊና ተጠቃሚ የሚሆንበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣

፫·በስፖርት የሠለጠነ የሰው ኃይል ለማፍራት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ይሰራል፣

፬·የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎችንና ማበልፀጊያ ማዕከላት እንዲገነባ ያደርጋል፣ ያስተዳድራል፣

፭·ለስፖርት ተግባራት የሚውሉ የስፖርት ትጥቆችና መሣሪያዎች አቅርቦት የሚሟላበትን ሁኔታ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ያመቻቻል፣

፮·አግባብ ባለው ህግ የስፖርት ህክምና አገልግሎት መደራጀቱን፣ በስፖርት አበረታች መድሃኒቶችና ዕፆች መጠቀምን ለመከላከል የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋቱን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣

፯.የስፖርት ማህበራት ስለሚቋቋሙበትና ማዘውተሪያ ስፍራ አጠቃቀምና አሰራር ሁኔታ መመሪያ ያወጣል፤ የስፖርት ማህበራትንና ክለቦችን እንዲሁም ጅምናዚየሞችን ይመዘግባል፤ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤

፰.በሳይንሳዊ ጥናት ላይ የተመሰረቱ የአካል ብቃት ማሰልጠኛ ዘዴዎችን በማዘጋጀት ስፖርተኞች፣ አሰልጣኞች የስፖርት ዳኞችና የመሳሰሉት እንዲሰለጥኑ ያደርጋል፤

፱.የከተማውን ነዋሪ የስፖርት ተሳትፎ ለማጎልበት ያቅዳል፤ ስፖርት ውድድሮች ያዘጋጃል፤ ይመራል፤ ከሚመለከተው ጋር በመተባበር የትምህርት ቤቶች የስፖርት ውድድር እንዲስፋፋና እንዲጠናከር ያደርጋል፤

፲. በውጭ ኦዲተር የተመረመረ የሂሳብ ሪፖርት ከማህበሩ እንዲቀርብለት በማድረግ የስፖርት ማህበራት ገቢ ለአላማቸው ብቻ መዋሉን ያረጋግጣል፤

፲፩.የአስተዳደሩን ስፖርት ምክር ቤት በየደረጃው በማቋቋም አግባብ ባለው ህግ አደረጃጀቱን ያጠናክራል፤ ይመራል፤ ይቆጣጠራል፡፡

**<u>፴፱.የገቢዎች ባለስልጣን</u>**

ባለስልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

፩. ዘመናዊ የገቢ አወሳሰንና አሰባሰብ ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ያደርጋል፤

፪. ፍትሐዊ፣ ቀልጣፋና ጥራት ያለው አገልግሎት ይሰጣል፤ ኢንቬስትመንትን ለማበረታታት ለባለሃብቶች የተሰጡ የታክስና የቀረጥ ነጻ መብቶች በህግ አግባብ እንዲፈፀሙ ያደርጋል፤ ለታሰበው ዓላማ መዋላቸውን ይከታተላል፤

፫. ታክስ ከፋዮች በፈቃደኝነት ታክስ የመክፈል ባሕልን እንዲያዳብሩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራሞች ተግባራዊ ያደርጋል፤

፬. የታክስ መመሪያዎችን አፈፃፀም ለማሻሻል እና ገቢ በአግባቡ እንዲሰበሰብ ለማድረግ የጥናትና የምርምር ሥራዎችን ያካሂዳል፤

፭. ለግብር እና ለልዩ ልዩ ገቢዎች አወሳሰን የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ይሰበስባል፤ ይተነትናል፤ በመስኩ ስለሚፈጸሙ ወንጀሎች የተሟላ የስታትስቲክስ መረጃ ያጠናቅራል፤ ለሚመለከተው አካል ያሳውቃል፤

፮. በከተማ የሚሰበሰቡ ገቢዎችን ወስኖ፣ ውሳኔዎችን ለግብር ከፋዮች በጽሁፍ ያሳውቃል፤ ብቃት ባለው መልኩ ለማከናወን የሚያስችሉ የአሰራር ዘዴዎችን በመቀየስ ገቢ ይሰበስባል፤

፯. በተዋረድ ባሉ የባለስልጣኑ አደረጃጀት የሚሰበሰቡ ገቢዎች ለፋይናንስ ቢሮ በወቅቱ ፈሰስ ያደረጋል፤

፰. ግብር ከፋዮች ደረሰኝ እንዲያሳትሙ ይፈቅዳል፤ ይቆጣጠራል፤ አግባብ ባለው ህግ መሰረት የታክስ ህጎችን ያስከብራል፤

፱. የቀን ገቢ ግምት ጥናት አግባብ ባለው ህግ መሰረት ያከናውናል፤

፲. አግባብነት ካላቸው አካላትና የከተማ ነዋሪዎች እና ግብር ከፋዮች ጋር በአጋርነት ለመስራት የሚያስችል ስልቶች በመቀየስ ተግባራዊ ያደርጋል፣

፲፩.የባለስልጣኑን ሰራተኞች ካቢኔው በሚያወጣው ደንብ መሰረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፡፡

፵.<u>የመንገዶች ባለስልጣን</u>

ባለስልጣኑየሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩.የመንገድ ኔትዎርክን፣ የመንገድ ስራን፣ የመንገዶችን አጠባበቅና አጠቃቀም ህግ ያዘጋጃል፣ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፣

፪.የመንገድና ድልድይ ዲዛይን ደረጃ ያወጣል፣ ያሻሽላል፣ የጥገና ስታንዳርድ ያወጣል፣ የመንገድ ደረጃ አመዳደብ መመሪያ ያወጣል፣ አተገባበራቸውንም ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

፫.የመንገድና ድልድይ ዲዛይን ከመጽደቁ በፊት በትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ አስተያየት እንዲሰጥበት ያደርጋል፣

፬.የመንገድ እና የድልድይ ዲዛይን፣ ግንባታ፣ ጥገና ስራዎችን በራስ አቅም ያከናውናል፣ እንዲከናወን ያደርጋል፣

፭.ለመንገድ ሥራ የአዋጭነት ጥናት፣ የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ፣ የመንገድ ዲዛይን እና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸውን ጥናቶች ያካሂዳል፣ እንዲካሄድ ያደርጋል፣

፮.ለመንገድ ሥራው የሚያስፈልገውን ቦታ አግባብ ባለው ህግ መሰረት እንዲለቀቅ ያደርጋል፣

፯.አግባብ ባለው ህግ መሠረት የመንገድ ዲዛይን የሚሰሩ፣ የግንባታ ቁጥጥርና ሌሎች ተዛማጅ አገልግሎቶችን የሚሰጡ አማካሪዎችን፣ በመንገድ ግንባታዎች ላይ የሚሰማሩ ሥራ ተቋራጮች የሚመረጡበትን ዘዴ ይወስናል፣

፰.ግንባታቸው የተጠናቀቀ መንገዶችና ሥራዎች በውሉ መሠረት በተፈለገው ጥራትና ደረጃ መከናወናቸውን በማረጋገጥ ይረከባል፣ እንዲረከብ ያደርጋል፣

፱.የመንገድ ፕላን መሰረት አዲስ ለሚገነቡ ለእግረኛ መተላለፊያ መንገድ የሚያስፈልገውን የመሬት ስፋትና አሰራር፣ የመንገድ ተጠቃሚ ተሽከርካሪዎችን ክብደት፣ ዓይነት ወሰን፣ ለተለያዩ የመንገድ ተጠቃሚዎች የሚውሉ መንገዶችን ለይቶ ይወስናል፣ የመንገድ ምልክቶችን ይተክላል፣

፲. ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በመንገዶች ዳር እና መካከል የሚተከሉ የዛፍ ዓይነቶችና መጠን ይወሰናል፣ መተግበሩንም ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

፲፩.በዋና መንገዶች እና በመለስተኛ ዋና መንገዶች ግራ እና ቀኝ ዳርቻዎች፣ አካፋዮችና አደባባይ ላይ የአረንጓዴ ልማት ስፍራዎች ዲዛይን የመንገድ ግንባታ ፕላን አካል አድርጎ ያዘጋጃል ወይም እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ መትከያ ስፍራዎችን ዝግጁ ያደርጋል፣ አስፈላጊውን መረጃ በወቅቱ ለተፋሰስና አረንጓዴ አካባቢዎች ልማት ኤጀንሲ መረጃ ይሰጣል፣

፲፪.የአካባቢውን የውሃ ፍሰት መጠን ያገናዘበ የመንገዶችን ፍሳሽ ማስወገጃ ስርዓት ይገነባል፤ ያስገነባል፤ ይጠግናል፤ ያሻሽላል፤

፲፫.መንገዶችን የፍሳሽ ማስወገጃ ቱቦዎቹን ጨምሮ ከደለል፣ ከሌላ ጉዳትና አለአግባብ ከመጠቀም ይጠብቃል፤ በመንገዶች ላይ የሚከሰቱ መሰናክሎችን ያስወግዳል፤ ወይም እንዲወገዱ ያደርጋል፤ በተገቢው መንገድ ያስተዳድራል፤

፲፬.በመንገድ ላይ ለሚከናወኑ የተለያዩ የመሰረተ ልማት ዝርጋታ እና ቁፋሮዎች ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ፈቃድ ይሰጣል፤

፲፭.ከሚለከታቸው የባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በመንገዶች ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ወይም ማናቸውንም መሰናክሎች የሚያስቀምጡ ወይም ነዳጅና ቅባት ነክ ፈሳሾችን የሚያፈሱ ሰዎችን አግባብ ባለው ህግ መሠረት እንዲጠየቁ ያደርጋል፤

፲፮.በህብረተሰቡ፣ በቡድን፣ በግል ወይም በመንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች አማካኝነት ለሚሰሩ መንገዶች ስታንዳርድ ያወጣል፤ ፈቃድ ይሠጣል፤ ይቆጣጠራል፤ እንዳስፈላጊነቱም በሚወጣው መመሪያ መሠረት ተገቢውን የቴክኒክ ድጋፍ ያደርጋል፤

፲፯.ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር በኮይወክላልሰቶን መሰራት የሚገባቸውን መንገዶች ይለያል፤ በዕቅድ ውስጥ ያካትታል፤ የኮይወክላል ስቶን የሚጠርቡ ማህበራትን የአቅም ክፍተት በመለየት ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤

፲፰.የመንገድ ላብራቶሪ ምርመራና ፍተሻ ስራዎችን ያከናውናል፤ ውጤቶችንም በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

፲፱.መንገዶች አግባብ ባለው አካል እንዲሰየሙ ሃሳብ ያቀርባል፤ ሲፈቀድም ይተገብራል፤

፳.ለአረንጓዴ ልማት በከተማው ፕላን በተመለከተው መሰረት በቂ ስፍራ እንዲዘጋጅ እና እንዲከልል ያደርጋል፤

፳፩.የመንገድ አካፋዮችና ዳርቻዎች፣ የመከለያ አጥሮች ደረጃ እና ዲዛይን ያዘጋጃል፤

፳፪.ለጎርፍ የተጋለጡ የከተማ ክፍሎችን በተመለከተ ከሚመለከተው አካል ጋር በመቀናጀት ጥናት ያደርጋል፤ የመከላከያ ሥራ መስራት የሚያስችል ዲዛይን ያዘጋጃል ወይም እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤ በህግ አግባብ ከስራ ተቋራጮች እና ከአማካሪዎች ጋር ውል በመዋዋል ግንባታው እንዲከናወን ያደርጋል፡፡

**<u>፵፩.የውሃና ፍሳሽ ባለሰልጣን</u>**

ባለስልጣኑ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖረዋል፡-

፩. የውሃ አቅርቦት እና ፍሳሽ ማስወገድ ፍላጎት ያጠናል፤ የውሃ አቅርቦት እና የፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ ማስተር ፕላን፣ የአጭር፤ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ ዕቅድን ያዘጋጃል፤ ሲጸድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፪.የውሃ አቅርቦት እና ፍሳሽ ማስወገድ ፍላጎትን የሚያሟሉ ፕሮጀክቶችን ይነድፋል፤ ፕሮጀክቶች በወጣላቸው ስታንዳርድ፣ ዕቅድና የውል ስምምነት መሠረት ተጠናቀው ለህብረተሰቡ አገልግሎት እንዲሰጡ ያደርጋል፤

፫.የውሃ መገኛ፣ የውሃ ማጣሪያ ጣቢያዎች፣ የማሰባሰቢያና መስመር ዝርጋታ ጥናቶችን ያካሂዳል፤

፬.የውሃ አቅርቦት እና ፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ መሰረተ ልማት ዲዛይን ያዘጋጃል፤ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤ በተዘጋጁ ዲዛይኖች መሰረት አግባብ ባለው ህግ ያስገነባል፤ ያስተዳድራል፤

፭.የአገልግሎት ክልል በሚመለከት አግባብ ካለው ክሌላዊ መንግስት ጋር ግንኙነት ያደርጋል፤ የውሀ መሰብሰቢያ ስፍራዎችን ይለያል፤ ስምምነት ላይ ሲደረስ ስራ ላይ ያውላል፤

፮.አግባብ ባለው ሕግ መሰረት ለውሃ አቅርቦት እና ፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ልማት ለሚለቀቅ ንብረት ተገቢውን ካሳ ይከፍላል፤ ይይዛል፤ ያስተዳድራል፤

፯.የውሀ ምንጭ ሀብት ግድብ፣ የገጸ ምድርና የከርሰ ምድር ውሃ ምንጭ፣ የግድብ ተፋሰስ ይንከባከባል፤ ያስተዳድራል፤

፰. ባለስልጣኑ አጣርቶ የሚያቀርበውን ውሀ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አጠቃቀሙን ሊወስን ወይም ሊገድብ ይችላል፤

፱. የውሀ ማጣራት፤ ማከፋፈል፤ መሸጥ፣ የፍሳሽ መስመር መዘርጋት፣ መስመር የማስቀጠያና የመገልገያ ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፤

፲.የፍሳሽ ማጣሪያ ጣቢያዎችን፤ የቅብብሎሽ ጣቢያዎችን ይገነባል፤ ያስገነባል፤ ያስተዳድራል

፲፩.ለውሃው አቅርቦት እና ፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ልማት ስራ ማስፈጸሚያ የሚውል ገንዘብ ከተለያዩ የገንዘብ ምንጮች ያፈላልጋል፤ ሲፈቀድ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፲፪.ለውሀ ስርጭት እገዛ የሚያደርጉ የኤልክትሮ ሜካኒካል ስራዎችን ያከናውናል፤

፲፫.በግል የውሃና ፍሳሽ መስመር ዝርጋታ ስራዎች ላይ መሰማራት ለሚፈልጉ ባለሙያዎችና ተቋማት እንደአስፈላጊነቱ የአጭር ጊዜ ስልጠናና የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፤ ያድሳል፤ ይቆጣጠራል፤

፲፬.የፍሳሽ ቆሻሻን በተሽከርካሪ በመሰብሰብ፣ በማጓጓዝ እና በማስወገድ ተግባር ላይ መሰማራት ለሚፈልጉ ባለሃብቶች አግባብ ባለው ህግ የእውቅና ምስክር ወረቀት ይሰጣል፤ ይቆጣጠራል፤

፲፭.የባዮጋዝና የተፈጥሮ ማዳበሪያ ማምረቻ ቦታዎችን ያዘጋጃል፤ ያመርታል፤ ያስተዳድራል፤

፲፮.የከርሰ ምድር ውሃ ቁፋሮ ማከናወን ለሚፈልጉ አካላት የቁፋሮ ፈቃድ ይሰጣል፤ ያድሳል፤ ይቆጣጠራል፤

፲፯.የውሀ መስመሮችን እና ፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ መስመሮችን በየወቅቱ ያድሳል፤ በሚበላሹበትም ወቅት አስፈላጊውን ጥገና ያከናወናል፤ የውሀ ስርጭትን ያከናውናል፤

፲፰·ውሃን ከምርት ጀምሮ ተጠቃሚው ጋር እስኪደርስ ድረስ ባሉ ሂደቶች የወጣውን የጥራት ስታንዳርድ መጠበቁን ያረጋግጣል፤ ይቆጣጠራል፤ ፍሳሾች በተዘረጋ የፍሳሽ መስመርና በተሽከርካሪ ያስወግዳል፤

፲፱·ፍሳሽን ያጣራል፤ የተጣራ የፍሳሽ ውሀንና ዝቃጩን መልሶ በመጠቀም በልዩ ልዩ አገልግሎት ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

፳·የውሀ ቆጣሪ የማስመጣት ብቸኛና ልዩ ስልጣን ይኖረዋል፤ የቆጣሪና የላብራቶሪ ምርመራ ያካሂዳል፤ በምርመራው ውጤት መነሻነት ተገቢውን አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል፤

፳፩·ውሃና ፍሳሽን በተመለከተ ለህብረተሰቡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ይሰጣል፤ ህብረተሰቡን በተለያየ የውሃና ፍሳሽ ስራዎች እንዲሳተፉ ያስተባብራል፡፡

፵፪·የመሰረተ ልማት ቅንጅት፣ ግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን

ባለስልጣኑ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩·የመሠረተ ልማት ግንባታ ስራዎችን በቅንጅት ለመስራት ፣ዲዛይን ለማዘጋጀት፣ የግንባታ ፈቃድ፣ ቁጥጥር እና መጠቀሚያ ፈቃድ ለመስጠት እንዲሁም የግንባታ ስራ ቁጥጥር ለማድረግ የሚያስችል፡-

ሀ) የግንባታ ዕቅድና የዲዛይን ማቅረቢያ መመሪያ ያዘጋጃል፤ ያሰራጫል፤ ስለአጠቃቀሙም ስልጠና ይሰጣል፤

ለ) የግንባታ ቅንጅት ለማጎልበት የሚያስችል ጥናት ያካሄዳል፤ ግንባታ የሚያካሄዱ አካላት ተቀናጅተው እንዲሰሩ ያደርጋል፤

፪·በጸደቀ የከተማ ፕላን መሠረት የፕላን ስምምነት መረጃ በጽሁፍ ይሰጣል፤ የማይሰጥበት ሕጋዊ ምክንያት በሚኖርበት ጊዜ በህግ መሠረት ውሳኔውን ለባለጉዳዩ በጽሁፍ ያሳውቃል፤

፫·የመንግስትም ሆነ የግል የህንጻወይምየመሠረተ-ልማት አዲስ ግንባታ፣ የግንባታ ማሻሻያ ወይም እድሳት ፈቃድ፣ ለህዝብ ግልጋሎት ለሚውል የተጠናቀቀ ግንባታ መጠቀሚያ ፈቃድ እንዲሁም ግንባታ የማፍረስ ፈቃድ በሕግ መሠረት ይሰጣል፤

፬·የግንባታ ዲዛይን በከተማ ፕላን፣ በሕግና በሕንጻ ደረጃ መሠረት በመመርመር ያጸድቃል፤ ዲዛይን በሚመረመርበትም ሆነግንባታ ፈቃድ በሚሰጥበት ጊዜ የሚከተሉት መሟላታቸውን ያረጋግጣል፡-

ሀ) ለጸደቀ የመሠረተ-ልማት ቅንጅት መሪ ዕቅድ ዝርዝር ዲዛይን፣ የአጭር ጊዜ ዕቅድ፣መርሃ-ግብር እና/ወይም ፕሮጀክት እንደየአግባቡ ተዘጋጅቶ መቅረቡን፤

ለ) በከተማው ውስጥ በአንድ አካካቢ ወይም የልማት ቀጠና የሚከናወኑ አዳዲስ የግንባታ ልማቶች፣ ማሻሻያዎች ወይም እድሳቶች ያሐቸው ዲዛይኖችና የድርጊት መርሃ-ግብሮቻቸው ተጣጥመው፣ ተደጋግፈውና ልማት በሚያፋጥን መልኩ እንደየአግባቡ ተቀናጅተው መዘጋጀቸውን፤

ሐ) ከአንድ ህንጻ በላይ ያላቸው ሰፋፊ ግንባታ ልማት ሥራዎች ዝርዝር ዲዛይን ተዘጋጅቶላቸው መቅረቡን፤

መ) የመንገድ፣ የድልድይ ወይም የሌላ መሰረተ-ልማት አገልግሎት መስመር ዲዛይን ተቀናጅቶ መዘጋጀቱንና እንደየአግባቡ በተፋፈሰስ ላይ መከናወን ስላለበት ማሻሻያ ስራጥናትና ዲዛይን ተዘጋጅቶ መቅረቡን፤እና

ሠ) ማናቸውም የግንባታ ዲዛይን የማህበረሰብ ደህንነት፣የድንገተኛአደጋዎች፣ የአካባቢ ጥበቃና ሌሎች ህግጋትን እንደ የአግባቡ ተከትሎ መዘጋጀቱን፤

፫.ከቴክኒካዊ አቅሙብላይ የሆነ ዲዛይን ሲቀርብለት አግባብያላቸው ባለሙያዎችን በመሰየም ወይም አግባብ ያለው ስልት በመጠቀም ዲዛይን መርምሮ የቀረበለትን የግንባታ ፈቃድ ጥያቄ ይወስናል፤

፮.የመኖሪያ ግንባታን ከመኖሪያ ውጪ ወደ ሆነሌላ አገልግሎት መቀየር የሚፈልግ ሰው በጽሁፍ ሲጠይቅ እና የግንባታው ዲዛይን ለተለወጠው አገልግሎት መዋል የሚችል ሆኖ ሲገኝ፣ ንግድ ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት የመጠቀሚያ ፈቃድ ይሰጣል፤ እንዲሁም የመጠቀሚያ ፈቃድ ሳይሰጠው በመኖሪያ ግንባታ ንግድ ፈቃድ አውጥቶ የሚሰራ ማናቸውም ሰው በሚወጣ መመሪያ በሚወሰነው መሠረት የመጠቀሚያ ፈቃድ ማውጣቱን ያረጋግጣል፤

፯. የማስታወቂያ ሰልዳዎች፣ ባነሮችና ፅሑፎች የሚተከልባቸውንና የሚለጠፍባቸውን ቦታዎች፣ ግንባታዎችና ሌሎች ቋሚ ነገሮች ደረጃ አውጥቶ ይወስናል፤

፰.የማስታወቂያ ሰልዳ ወይም በሌላ ዘዴ የተዘጋጀ ማስታወቂያ ለመትከል፣ በህንጻ ወይም በሌላ ቋሚ ነገር ላይ ለሚለጠፍ ወይም ለማንጠልጠል ጥያቄ ሲቀርብለት፣ በህግና በማስታወቂያ ደረጃ መሠረት ፈቃድ ይሰጣል፤ ይቆጣጠራል፤ የተፈቀደው ጊዜ ሲያበቃ መነሳቱን ያረጋግጣል፤

**__፵፫.የትምህርትና ስልጠና ጥራት፣ ሙያ ብቃትና ምዘና ማረጋገጫ ባለስልጣን__**

ባለስልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩. በአጠቃላይ ትምህርት እና በቴክኒክና ሙያ ተቋማት የሚሠጥ ትምህርትና ስልጠና ከሀገሪቱና ከከተማ አስተዳደሩ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ፍላጎትና አግባብነት ካላቸው ሥርዓተ ትምህርት፣ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ጋር መገናዘባቸውን ያረጋግጣል፣ ይቆጣጠራል አስፈላጊ እርምጃዎችን ይወስዳል፤

፪. አጠቃላይ የትምህርትና በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት በህግ የተቀመጠውን የትምህርትና ስልጠና ስታንዳርድ፣ የትምህርትና ስልጠና አገልግሎት አሰጣጥ መስፈርት ማሟላታቸውን፤ አግባብነቱና ጥራቱ ደረጃውን ጠብቆ ስለመፈፀሙ ይከታተላል፤ይቆጣጠራል፤

፫. አጠቃላይ የትምህርት እና ስልጠና ተቋማት የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ያግዳል፣ ይሰርዛል፤ ለሰልጣኞች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምዘና ይሰጣል፤ ብቁ ሆኖ ለተገኘ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤

፬. አጠቃላይ የትምህርት እና ስልጠና ተቋማትን እና የሙያ ብቃትን መረጃ ያደራጃል፤ ያሰራጫል፤

፭. የአጠቃላይ የትምህርት እና ስልጠና ተቋማት ብቃት እና ምዘና መከታተያና መገምገሚያ ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፮. ፍቃድ ያላቸው የትምህርት እና ስልጠና ተቋማት ጥራታቸው ከስታንዳርድ በታች በሆኑ ተቋማት ላይ የሙያ ብቃት ማረጋገጫውን እስከመሰረዝና እስከ ማሸግ የሚደርስ እርምጃ ይወስዳል፤

፯.በሕገ ወጥ መንገድ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ፍቃድ ያገኙ የትምህርትና ስልጠና ተቋማት ላይ የሙያ ፈቃዳቸውን ይሰርዛል፣ ተቋሙንም ያሽጋል፤ አግባብ ባለው የወንጀል ሕግ እንዲጠየቁ ስልጣን ላለው አካል ያሳውቃል፤

፰.የሙያ ብቃት ፍቃድ እያላቸው አግባብ ያለው ህግ በሚጥሱ አካላት ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፤ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

፱.የሙያ ብቃት ፍቃድ ሳያገኙ ወይም በልሎች ተቋማት የሙያ ብቃት ፈቃድ የሚሰሩ የትምህርት እና ስልጠና ተቋማትን ያሽጋል፤ አግባብ ባለው የወንጀል ሕግ እንዲጠየቁ ሥልጣን ላለው አካል ያሳውቃል፤

፲.ለትምህርት እና ስልጠና ተቋማት ዕውቅና ይሰጣል እውቅና አግኝተው የሚሠሩ ትምህርት ቤቶች በሀገር ደረጃም ሆነ በከተማ ደረጃ በሚወጡ ህጎች የተቀመጡ የስርዓተ ትምህርት፣ የትምህርት አግባብነትና ጥራት ደረጃዎችን ማሟላታቸውን ያረጋግጣል፤

፲፩.በትምህርት ተቋማት የህብረተሰቡን ተሳትፎ ሊያረጋግጡ የሚችሉ አደረጃጀቶች፣ የወላጅ፣ የተማሪ፣ የመምህራን ፎረም፣ የተማሪ ክበባት ስለመኖራቸው ያረጋግጣል፤ እንዲሁም የትምህርት አገልግሎት ክፍያዎች የወላጆችን የመክፈል አቅም ያገናዘበ እንዲሆን ከተቋማቱ ጋር ይመክራል፤

፲፪. ከሥራ ዓለምና ከተቋማት የሙያ ብቃት ምዘና ወስደው ብቁ ሆነው ለተገኙ ተመዛኞች የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤

፲፫. በምዘና ጣቢያነት አገልግሎት መስጠት የሚችሉ እንዱስትሪዎችን ይለያል፤ ለምዘነና ምቹ ሆነው እንዲደራጁ ያደርጋል፤ የምዘና ስራ ይከታተላል፤ በበላይነት ይመራል፤

፲፬. ከባለስልጣኑ ውጭ በከተማው አስተዳደር ከሚገኙ ተቋማት ወይም ኢንዱስትሪዎች ውስጥ የምዘና አገልግሎት መስጠት የሚችሉ አካላትን በመምረጥ ዕውቅና ይሰጣል፤

፲፭. የሙያ ብቃት ምዘና ማዕከላት፣ የኢንዱስትሪ መዛኞች እና ሱፐርቫይዘሮች አሰራር ለመከታተል የሚያስችሉ የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

፲፮. ከባለስልጣኑ ባለሙያዎች በመረጃ አያያዝና አደረጃጀት ዙሪያ የሚቀርቡትን የጥናት ፕሮጀክቶች፣ ፕሮፖዛሎችንና ሪፖርቶችን በመገምገም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፲፯· መንግስታዊ ወይም መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ብቃት ያላቸው ሰራተኞች በሚፈለጉበት ወቅት የሙያ ብቃት ምዘና በመስጠት ብቃታቸውን ያረጋግጣል፡፡

**፵፬·<u>የምግብ፣ መድሃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን</u>**

ባለስልጣኑ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩·የምግቦችን ደህንነትና ጥራት፣ የመድኃኒቶችን ደህንነት፣ ፈዋሽነት፣ ጥራትና አግባባዊ አጠቃቀም የህክምና ባለሙያዎችን ብቃትና አሰራር፣ የኃይጅን፣ የአካባቢ ጤናን እና የጤና ነክ ቁጥጥር የሚደረግበት ተቋማት የቁጥጥር ደረጃዎች ማሟላታቸውን ያረጋግጣል፤

፪·ለጤና ተቋማት፣ የመድኃኒት አከፋፋዮችና ማከማቻዎች፣ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፤ ያድሳል፤ ያግዳል፤ ይሰርዛል፤

፫·ለጤና ነክ ተቋማት የሙያ ፈቃድ ይሰጣል፤ የንጽህናና የጤና ደረጃዎችን ማሟላታቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

፬·የህጻናት ማቆያዎችን የሙያ ደረጃ ፈቃድ ይሰጣል፣ የንጽህና፣ የጤንነትና ተስማሚነት ደረጃዎችን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

፭·የምግብ፣ የመድኃኒት የአካባቢ ጤና አጠባበቅ፣ የጤና ባለሙያዎች እና የጤናና ጤና ነክ ቁጥጥር የሚደረግባቸው ተቋማትን በሚመለከት የመረጃ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፤

፮·በምግብ ወይም በመድኃኒት መመረዝ ወይም መበከል ምክንያት ለሚደርስ ሞት፣ የጤንነት መታወክ መንስኤ የሆነውን ንጥረ ነገር ልዩ ልዩ ናሙናዎች በመውሰድ ምንነታቸው እንዲረጋገጥ ያደርጋል፤ እርምጃ ይወስዳል፤

፯·አግባብ ባለው ህግ መሰረት የባህል መድሀኒት አዋቂዎች በባህል ህክምና ዘርፍ ላይ እንዲሰማሩ ፈቃድ ይሰጣል፤ የባህል መድሀኒቱ ምን አይነት ይዘት እንዳለው በላብራቶሪ እንዲመረመር ያደርጋል፤ ያረጋግጣል፤ ይቆጣጠራል፤

፰·በደረጃው የተፈቀደለት የጤና ባለሙያዎች የሙያ ፈቃድ ይሰጣል፤ ያድሳል፤ ያግዳል ይሰርዛል፤ የባህል ሕክምና ከዘመናዊ ሕክምና ጎን ተጠናክሮ የሚሄድበትን ሥልት ይቀይሳል፤

፱·በባለስልጣኑ ቁጥጥር የሚደረግባቸው ተቋማት ላይ የአገልግሎት ጊዜያቸው ያበቃ ምግቦች፣ መድኃኒቶችና ጥሬ ዕቃዎችቻቸው በአግባቡ መወገዳቸውን ያረጋግጣል፤

፲·ሕገወጥ ምግቦችን፣ መድኃኒቶችና፣ የጤና አገልግሎቶችን ይቆጣጠራል አስፈላጊ እርምጃዎችንም ይወስዳል፤

፲፩·አስተዳደሩ በሚቆጣጠራቸው የጤና ተቋማት አበረታች መድሀኒቶች፣ የናርኮቲክ መድኃኒት፣ ሳይኮትሮፒክ ንጥረ ነገሮች እና ፕሪከርሰር ኬሚካሎች ለህሙማን ማዘዝን፣ ማደልን፣ አጠቃቀምን፣ መመዝገብንና ሪፖርት ማድረግን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ አስፈላጊ ሲሆን ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፤

፲፪.በከተማው አስተዳደር ሥር ያሉ ጤና ነክ ቁጥጥር የሚደረግባቸው ተቋማት ተገቢውን የሐይጅንና አካባቢ ጤና አገልግሎት መስፈርት ማሟላታቸውን ያረጋግጣል፤

፲፫.የስነምግባር ግድፈት በሚያሳዩ የጤና ባለሙያዎች ላይ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፤

፲፬.ለሥራው አስፈላጊ የሆኑትን የጥራት ምርመራ ላቦራቶሪ ያደራጃል፤ለሚሰጠው አገልግሎት በህጉ ክፍያ ያስከፍላል፡፡

**፵፰.<u>የመንግስት ሕንጻና ንብረት አስተዳደር ባለስልጣን</u>**

ባለስልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

፩.በመንግስት ህንጻና ንብረት አስተዳደር ላይ ለከተማ አስተዳደሩ የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፤ ያማክራል፤

፪.ስልጣኑ በህግ ለሌላ አካል ወይም ለሌላ የመንግስት መስሪያ ቤት ካልተሰጠ በቀር የከተማውን አስተዳደር ህንፃዎችንና ቋሚ ንብረቶችን ይመዘግባል፤ በበላይነት ያስተዳድራል፤ ያድሳል፤ ጥገና የሚያስፈልጋቸውን ህንፃዎች በመለየት እንዲጠገን ያደርጋል፤

፫.የህንጻና ንብረት አስተዳደር እና አጠቃቀም ዘመናዊ ስርዓትን ይዘረጋል፤ ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ያረጋግጣል፤ ምድረ ግቢን ውብና ማራኪ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

፬.የመንግስት ህንፃዎች አጠቃቀም፣ ለተጠቃሚው ያላቸው ተደራሽነት እና ከወጪ አንፃር ውጤታማ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

፭.የተቋማትን ፍላጎት፣ የስራ ባህሪይ እና የተገልጋይ ሁኔታን በማጥናት የተቋማትንና የስራ ክፍሎችን የስራ ቦታ ይደለድላል፤

፮.የከተማ አስተዳደሩ የመንግስት ተቋማት ለአገልገሎት አሰጣጥ የሚያስፈልጋቸውን ህንፃዎች የኪራይ ደረጃ አጥንቶ ይወስናል፤ ለመንግስት አገልግሎት የሚውሉ ህንፃዎች እንዲገነቡ ያደርጋል፤

፯.በከተማው ውስጥ ባለቤት የሌላቸው ህንጻና ንብረቶችን አግባብ ባለው ህግ መሰረት ተረክቦ ያስተዳድራል፤

፰.መንግስት ህንፃዎች ወጥ የሆነ ስታንዳርድ እና ዲዛይን እንዲኖራቸው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ይሰራል፤ ያስገነባል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

፱.የህንጻ አስተዳደር ሥራዎች የተቀላጠፉና ውጤታማ እንዲሆኑ የውስጥ አደረጃጀት እና የቢሮ ቁሳቁስ ስታንዳርድ ያዘጋጃል፤ እንዲተገበር ያደርጋል፤

፲. መንግስት የንብረት አያያዝ ስርዓት መሰረት የመንግስት ንብረቶች በአግባቡ ስለመያዛቸው እና ጥቅም ላይ ስለመዋላቸው የንብረት ኦዲት ያደርጋል፤

፲፩.ባለስልጣኑ የህንጻና የንብረት ኦዲት ውጤት መሰረት ተገቢው የእርምት እርምጃ ያልወሰዱ የመንግስት መስሪያ ቤቶችን ለይቶ ተጠሪ ለሆነለት ቢሮና ለሚመለከተው አካል ያሳውቃል፤

፲፪.አግባብ ባለው ህግ ቋሚ ንብረቶች ዋጋ እንዲወጣላቸው እና በየዓመቱ የዕልቀት ዋጋ እንዲሰላላቸው በማድረግ መንግስት የቋሚ ንብረቶች የያዙትን ዋጋ እንዲያውቅ ያደርጋል፤

፲፫.ለስልጣኑ በሚያስተዳድራቸው ንብረቶች ላይ የሚፈጸሙ ህገወጥ ድርጊቶችን ይከላከላል፤ ተፈጽሞም ሲገኝ ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል፤

፲፬.የመንግስት ህንፃዎች የሚገነቡበት ቦታ ያስፈቅዳል፤ ይመዘግባል፤ ተገቢውን የይዞታ ማረጋገጫ እና የግንባታ ፈቃድ እንዲሰጥ ያደርጋል፤ ይጠብቃል፤

፲፭.የመንግስት ህንፃዎች የሰራተኞች ካፍቴሪያ፣ የጽዳትና ውበት፣ የጥበቃ፣ የመጀመሪያ ህክምና፣ የመንግስት ተሽከርካሪዎች ማቆሚያ፣ የመኪና እጥበት እና የህፃናት ማቆያ አገልግሎቶች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

<u>፵፮.የመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለስልጣን</u>

ባለስልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩.ተጠሪነታቸው ለሌላ አስፈጻሚ አካል የሆኑ የልማት ድርጅቶችን የኮርፖሬት አስተዳደር እና የፋይናንስ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

፪.የልማት ድርጅቱን መነሻ ካፒታል ለፋይናንስ ቢሮ በማቅረብ በከተማ አስተዳደሩ እንዲፀድቅ ያደርጋል፤

፫.የልማት ድርጅቶችን የኢንቨስትመንት እቅድ እና ዓመታዊ ዕቅድ እንዲያዘጋጁ ያደርጋል፤ ሲጸድቅ አፈፃፀማቸውንም ይከታተላል፤

፬.በኢኮኖሚው ውስጥ ተገቢ ድርሻቸውን ለመወጣት የሚያስችላቸው ዘመናዊ የኮርፖሬሽን አስተዳደር አሰራር ስርዓት ይዘረጋል፤

፭.አግባብ ባለው ህግ የከተማው ዕቅድ ላይ በመመስረት ድርጅቶቹ ቦንድ የሚሸጡበትን፣ የሚገዙበትንና ብድር የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

፮.የልማት ድርጅቱ ካፒታል እንዲቀንስ፤ እንዲጨምር ለሚመለከተው አካል የውሳኔ ሀሳብ በማቅረብ እንዲወሰን ያደርጋል፤

፯.እያንዳንዱ የልማት ድርጅት የተፈቀደ ካፒታል መጠን የሚከፈልበትን አሰራር ይዘረጋል፤ የመጠባበቂያ ሂሳቦች እንዲያዙ ያደርጋል፤

፰.ከተጣራው ትርፍ ውስጥ በየዓመቱ ለከተማ አስተዳደሩ ፈሰስ ሊደረግ የሚገባውን መጠን አግባብ ባለው ህግ ይወስናል፤

፱.የውጭ ኦዲተሮችን ይሰይማል፤ የልማት ድርጅቱን የሂሳብ ሪፖርትና የውጭ ኦዲተር ሪፖርት ያፀድቃል፤

፲.አስፈላጊ ሲሆን የልማት ድርጅት እንዲፈርስ ከሌላ የልማት ድርጅት ጋር እንዲዋሀድ ወይም እንዲከፋፈል ወይም እንዲሸጥ ለሚመለከተው አካል ሃሳብ እያቀረበ ያስወስናል፤

፲፩.የልማት ድርጅቶችን የባለቤትነት መብት ለማስከበር የሚያስፈልጉ ልሎች ተግባሮችን ያከናውናል።

፲፪.የሶስተኛ ወገኖችን መብት ሳይነካ፡-

ሀ. ማናቸውም የልማት ድርጅት በንግድ ሕግ መሰረት የንግድ ማህበር ሆኖ እንዲቋቋም የውሳኔ ሀሳብ ለፋይናንስ ቢሮ ያቀርባል። ሲጸድቅ አፈጻጸሙን ይከታተላል።

ለ. ማንኛውም የልማት ድርጅት እንዲሸጥ ወይም በሌላ አኳኋን የልማት ድርጅቱ ወይም ማኔጅመንቱ እንዲተላለፍ የውሳኔ ሀሳብ ለፋይናንስ ቢሮ ያቀርባል። ሲፀድቅም ተግባራዊነቱን ይከታተላል።

፲፫.በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፲፪(ሀ) መሰረት በሚቋቋም የንግድ ማህበር በመንግስት የተያዘ አክስዮን እንዲሸጥ የውሳኔ ሀሳብ ለፋይናንስ ቢሮ ያቀርባል። ሲፀድቅም ተግባራዊነቱን ይከታተላል።

፲፬.በእያንዳንዱ የልማት ድርጅት ገንዘብ ወጪ የሚደረግበትንና ሽያጭም ሆነ ግዢ በመመሪያ ይወስናል።

፲፭.የልማት ድርጅት ሥራ ክትትል እና ማስተባበር በተለየ ክፍል እንዲካሄድ ያደርጋል። የክፍሉን ዝርዝር ኃላፊነትና ተግባር በመመሪያ ይወስናል።

፲፯.የልማት ድርጅቶች የቦርድ አባላት ብዛትና ስብጥር አጥንቶ ያቀርባል። ሲፀድቅ ተግባራዊ መሆኑን ይከታተላል፡፡

፵፯.<u>የትራንስፖርት ባለስልጣን</u>

ባለስልጣኑ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩.የከተማውን የተማከለ የብዙሃን ትራንስፖርት ሥርዓት ይዘረጋል። የሥምሪት ድልድል ያዘጋጃል። ታሪፍ አጥንቶ ለሚመለከተዉ አካል ያቀርባል። ሲጸድቅ ተግባራዊ ያደርጋል። ለአፈፃፀም የሚረዳ የቴክኖልጂ አውታሮችንም ይዘረጋል።

፪.በትራንስፖርት አገልግሎቱ ውስጥ የግሉ ዘርፍ እንዲሳተፍ የሚያበረታታ ሥርዓት ይዘረጋል። የትራንስፖርት ማህበራትን ያደራጃል። ያሉትም እንዲጠናከሩ ያደርጋል።

፫.የከተማውን የብዙሃንና የጭነት ትራንስፖርት አቅርቦት ፍላጎት ያጠናል። አማራጭ መፍትሂዎችን በማቅረብ ለአቅርቦት መጣጣም ፕሮግራሞችን በመቅረጽ ይሠራል።

፬.የከተማውን የትራንስፖርት መሠረተ ልማት ማለትም ለህዝብና ለጭነት ተሽከርካሪዎች አገልግሎት የሚውሉ መናኸሪያዎችን፣ ፌርማታዎችን፣ መጋዘኖችና ዴፖዎችን ይገነባል። ያስተዳድራል።

፭.የከተማውን የትራንስፖርት አቅርቦትና ፍላጎት በመለየት። የህዝብ፣ ደረቅና ፍሳሽ ጭነት ተሽከርካሪዎች ስምሪት ስርዓት ይዘረጋል። አዳዲስ የትራንስፖርት መስመሮችን ይከፍታል። ተግባራዊነቱን ይከታተላል።

፯.በከተማውየሚንቀሳቀሱየብዙሃንናየጭነትትራንስፖርትአገልግሎትሰጪአካላትአጠቃላይየኦፕሬሽን ሥርዓታቸውንበበላይነትይቆጣጠራል፤ ይመራል፤ ፈቃድይሰጣል፤ያግዳል፤

፯.አጠቃላይ የከተማውን የብዙሃንና የጭነት ትራንስፖርት በተመለከተ መመሪያዎችን ያወጣል፤ ተፈጻሚ ያደርጋል፤

፰.ለሕብረተሰቡ ተደራሽ የሆነ የትራንስፖርት መረጃ አገልግሎት ያደራጃል፤ ያሰራጫል፤ የከተማው የትራንስፖርት አገልግሎት በቅንጅት እንዲሰሩ ዕቅድ ያወጣል፤

፱.የከተማውን የብዙሃንና የጭነት ትራንስፖርት መመዘኛ መስፈርቶች፣ ማንዋሎችና ደረጃዎች ያወጣል፤ ለተፈፃሚነቱ ይሰራል፤

፲.ትራንስፖርት ደንብና ህግ የሚተላለፉ አሽከርካሪዎች ላይ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፤

፲፩.ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በብዙሃንና በጭነት ትራንስፖርት ዘርፍ የሚሰሩ ኦፕሬተሮች፣ ማኅበራት፣ ድርጅቶችና ግለሰቦች እንዲደራጁና እንዲጠናከሩ ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል፤ ለከተማው ትራንስፖርት ቅልጥፍናና ደህንነት መሥራታቸውንም ያረጋግጣል፡፡

፵፰.<u>የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን</u>

ባለስልጣኑ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

፩. አግባብ ባለው ህግ መሰረት ተሽከርካሪዎችን ይመዘግባል፤ የስም ዝውውር አገልግሎቶችን ይሰጣል፤ እዳና እገዳ አገልገሎት ይሰጣል፤

፪. የተሽከርካሪ አመታዊ ምርመራ በራሱ ወይም በህግ አግባብ ውክልና በሰጠው አካል ያከናውናል፤ ምርመራውን ያላለፉ ወይም በወቅቱ ያልተመረመሩ ተሽከርካሪዎች አገልግሎት እንዳይሰጡ ያደርጋል፤

፫. አግባብ ባለው ህግ መሰረት የአሽከርካሪነት ብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፤ ያድሳል፤ ምትክ ይሰጣል፤ ህጋዊነቱን ያረጋግጣል፤

፬. የተሽከርካሪ ስታንዳርዳይዜሽን፣ ምዝገባና ስረዛ፤ የተሽከርካሪ ዋጋ ግምት ይሰጣል፤

፭. የባለሞተር ተሽከርካሪዎችን የማሽከርከር ስልጠና የሚሰጡ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች የስራ ፍቃድ ይሰጣል፤ ይቆጣጠራል፤ አግባብነት የሌለው ተግባር ሲፈጽሙ ተገቢውን የእርምት እርምጃ ይወስዳል፤

፮. በተሽከርካሪ ምርመራ አገልግሎት፣ በአሽከርካሪ ማሰልጠኛ፤ በጋራዥ፣ በጎሚስታ እና መሰል አገልግሎቶች ላይ ለሚሰማሩ ተቋማትና ግለሰቦች የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይሰጣል፤ አስፈላጊውን ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤

፯. የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ መረጃዎችን በተመራጭ ቴክኖሎጂ በመታገዝ ያደራጃል፣ ያሰራጫል፣ እንደ አስፈላጊነቱም ስራ ላይ እንዲ ውሉ ያደርጋል፤

፰. ከአሽከርካሪና ከተሽከርካሪ ጋር ተያይዞ ያሉ አገልግሎቶችን ሊያሻሽሉ የሚችሉ የጥናትና ምርምር ስራዎችን ያከናውናል፤ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

፵፱.<u>የትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ</u>

ኤጀንሲው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖረዋል፡-

፩. የትራፊክ አመራርና አስተዳደር ሥራ በበላይነት ይመራል፤ ይቆጣጠራል፤ ለአገልግሎቱ ሥልጠት የሚያግዝ ስልት ይቀይሳል፤ ይተገብራል፤

፪. ትራፊክን ማሳለጥ የሚያስችሉ ተግባራትን ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መንገዶች ባለሥልጣን፣ ትርንስፖርት ባለስልጣን እና ከልሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይሰራል፤

፫. የመንገድ ትራፊክ ፍሰቱን በማሳለጥ ደህንነቱ የተጠበቀ የትራፊክ እንቅስቃሴ እንዲኖር የሚያስችል የትራፊክ ሥርዓት ይዘረጋል፤ ስታንዳርዶችን ያዘጋጃል፤ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

፬. የትራፊክ ፍሰትና ደህንነትን ለማሻሻልና ለመቆጣጠር የሚያስችል ዘመናዊ የቴክኖሎጂ ሥርዓት ይዘረጋል፤ የመረጃ ሥርዓቱን በመጠቀም የትራፊክ ደህንነቱንና ፍሰቱን ይከታተላል፤ መረጃዎችን ይሰበስባል፤ ያቀናጃል፤ እንደአስፈላጊነቱ በግብዓትነት ይጠቀማል፤

፭. በትራንስፖርት አገልግሎት እና በትራፊክ ሥርዓት ዙሪያ ግንዛቤ ይፈጥራል፤

፮. የትራፊክ ምልክቶችና ማመላከቻዎች፣ የመንገድ ላይ ቅቦች፣ የትራፊክ መብራቶች እና ልሎች የትራፊክ መቆጣጠሪያ ዘዴዎችን ይተገብራል፤ ያስተዳድራል፤

፯. ከመንገድ ትራፊክ እንቅስቃሴ አንፃር ሊገነቡ የሚገባቸውን መንገዶች ይለያል፤ የመንገዶች ባለስልጣን የመንገድ ዲዛይን ሲሰራ ወይም ሲያሰራ ትራፊኩን ከማሳለጥ አኳያ አግባብነቱን ይገመግማል፤ ያረጋግጣል፤

፰. ለህዝብና ለጭነት ተሽከርካሪዎች አገልግሎት የሚውሉ መናኸሪያዎች፣ ፌርማታዎች፣ ፓርኪንግ እና ዴፖዎች በከተማዋ መዋቅራዊ ፕላን መሠረት በሚመለከተው አካል መገንባታቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

፱. ከትራንሰፖርት ባለስልጣን ጋር በመተባበር የከተማዋን ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘበ የጭነት ተሽከርካሪዎች መንቀሳቀሻ ፈቃድ ቁጥጥር ሥርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊ መሆኑንም ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

፲. መንገድ ለመዝጋትና ልሎች ተዛማጅ ተግባራትን ወይም ከታለመለት ዓላማ ውጪ ለመጠቀም ለሚቀርብ ጥያቄ ፈቃድ ይሰጣል፤ ያድሳል፤ የመንገድ ላይ ኩነቶችን ያስተዳድራል፤ ህግን በሚተላለፉ ላይ ህጋዊ እርምጃ ይወሰዳል፤ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

፲፩. የትራፊክ ደንቦች መከበራቸውን ቁጥጥር ያደርጋል፤ አግባብ ባለው ህግ ደንብ ተላላፊዎችን ላይ እርምጃ ይወስዳል፤ የማስፈፀሚያ ስልቶችን ይዘረጋል፤ ተግባራዊነታቸውን ያረጋግጣል፤

፲፪. በከተማው ውስጥ የተሽከርካሪ የፍጥነት ወሰን ይወስናል፤ ለተለያዩ የመንገድ ተጠቃሚዎች የሚውሉ መንገዶች ለይቶ ይወስናል፤

፲፫. የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልገሎት ክፍያ ያጠናል፣ ሲፈቀድ ተግባራዊ ያደርጋል፣

፲፬. የአሽከርካሪ የርቀት እይታ የሚጋርድ ወይም የደረቁ የመንገድ ዳርና የአደባባይ ዕጽዋት እንደአስፈላጊነቱ በተፋሰስና አረንጓዴ አካባቢዎች ልማት ኤጀንሲ መወገዳቸውን ወይም መመልመላቸውን ያረጋግጣል፣

፲፭. የሕዝብ የብዙኃን ትራንስፖርት፣ አንቡላንስና የእሳት አደጋ አገልግሎት የሚሰጡ ተሽከርካሪዎችና የመሳሰሉት የመንገድ ቅድሚያና ያልተቋረጠ የትራፊክ አቅጣጫ የሚያገኙበትን ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊ መሆኑንም ይከታተላል፣

፲፮. የተሽከርካሪ ማቆሚያ ቦታ ፍላጎትና አቅርቦት ጥናት አጥንቶ አማራጭ የመፍትሔ ሃሳቦችን ያቀርባል፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር ይተገብራል፣ የፓርኪንግ ቦታዎች ለታለመላቸው ዓላማ መዋላቸውን ያረጋግጣል፣ ይቆጣጠራል፣

፲፯. በትራፊክ ደንብ ተላላፊዎች ላይ የሚጣል ቅጣት አግባብ ባለው ህግ ይሰበስባል፣

፲፰ የፓርኪንግ ቦታ ግንባታ ወይም አገልግሎት መስጠት ለሚፈልጉ የመንግስትና የግል ተቋማትና ግለሰቦች ፍቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፡፡

፱.<u>የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲ</u>

ኤጀንሲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩.የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ማሰልጠኛ ኮልጆችንና ማዕከላትን በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፣

፪.የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና አሠልጣኞች እና ቴክኒሺያኖችን የክህሎት ክፍተት በመለየት በክህሎትና በቴክኖሎጂ ብቃት ለማሳደግ አጫጭር ስልጠና የሚያገኙበትን ሥልት ይቀይሳል፣ ተግባራዊ ያድርጋል፣

፫.መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሰራተኞችና የግል አመልካቾች የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና የሚያገኙበትን አሰራር ይዘረጋል፣

፬.የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና አሰልጣኞችን የአሰልጣኝነት ብቃት እንዲሻሻል ያደርጋል፣ የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማትን ምርታማነት ተወዳዳሪነት የሚያጎለብትበት የቴክኖሎጂ ሽግግር ይደግፍል፣ ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፣

፭.የሀገሪቱን የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ስትራቴጂና መርሃ ግብር ለማስፈፀም የሚያስችል የአሰራር ሥርዓቶችን ይዘረጋል፣ ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

፮.በፌደራል የቴክኒክ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ የሚዘጋጁ ሥርዓተ ሥልጠናዎች በከተማው ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፣

፯.ማሰልጠኛ ተቋማት የቴክኖሎጂ ሽግግርና የምርምር ማዕከላት እንዲሆኑ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ተገቢውን እገዛ ያደርጋል፣

፰.ማሰልጠኛ ተቋማት ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የተሟላ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ድጋፍ እንዲሰጡ ያድርጋል፤ አፈፃፀሙን ይቆጣጠራል፤ ይከታተላል፤

፱.የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ከማምረቻና ከአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችና ተቋማት ጋር ተቀናጅተው የትብብር ሥልጠና፣ የኢንዱስትሪ ውስጥ ሥልጠና ወይም የሥራ ላይ ልምምድ በተገቢው መንገድ እንዲተገበር አስፈላጊውን እገዛ ያደርጋል፤ ያስተባብራል፤

፲.የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች ከከተማው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የሰው ኀይል ፍላጎት ጋር እንዲጣጣም ለማድረግ የሚያስችሉ የገበያው የሙያ ፍላጎትና ልሎችንም ጥናትና ምርምሮች ያካሄዳል፤ እንዲካሄዱ ያደርጋል፤ ያስተዋውቃል፤ የጥናትና ምርምር ውጤቶች መረጃ ያደራጃል፤ ለተጠቃሚዎች ክፍት ያደርጋል፤

፲፩.የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞችና ልዩ ፍላጎት ያላቸውና ልሎች ትኩረት የሚሹ ዜጎች ትኩረት እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤ በዚህ ረገድ የሚቀየሱ አገር አቀፍ ሥርአቶች በከተማው ውስጥ ተግባራዊ መደረጋቸውን ያረጋግጣል፤

፲፪.የማሰልጠኛ ተቋማትን አደረጃጀትና አስተዳደራቸውን እያጠና እንዲሻሻል ለሚመለከታቸው አካላት ያቀርባል፤ ግብረ መልስ ይሰበስባል፤ የሥልጠና አካሄዳቸውንም ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

፲፫.የማሰልጠኛ ተቋማት የሥራ ኃላፊዎችን የትምህርት ዝግጅት፣ የሥራ ልምድና የሥራ ብቃትን በመገምገምና በማወዳደር ይመድባል፤ የሥራ አፈፃፀም ብቃት ማነስ ወይም የሙያ ሥነ - ምግባር ጉድለት በታየባቸው ላይ ተገቢውን ማጣራት በማድረግ ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፤

፲፬.የቴክኒክና ሙያ ምሩቃን በሙያቸው ተደራጅተው ወደ ሥራ በሚገቡበት ጊዜ ያላቸውን የሙያ ክፍተት በመለየት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት በየደረጃው ሙያዊ እገዛ እንዲደረግላቸው አስፈላጊውን የሥራ ትብብር ያደርጋል፤

፲፭.የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናን አስመልክቶ ለሕብረተሰቡ የተለያዩ የግንዛቤ ማሰጨበጫ መድረኮችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ያዘጋጃል፤ ያስተባብራል፤

፲፮.በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዘርፍ መሰማራት የሚፈልጉትን የግል ባለሀብቶች ይደግፋል፤ መንግስታዊ ከሆኑ እና ካልሆኑ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ማሰልጠኛ ተቋማት ጋር ጠንካራ ግንኙነት ይፈጥራል፤

፲፯.የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ማሰልጠኛ ተቋማት ስርጭት የተመጣጠነ መሆኑን ይከታተላል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር ተጨማሪ ማሰልጠኛ ተቋማት የሚቋቋሙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

፲፰.የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ማሰልጠኛ ተቋማት እንዲሁም ከሀገር ውስጥና በውጪ ከሚገኙ ማሰልጠኛ ተቋማት ጋር ግንኙነትን በመፍጠር የልምድ ልውውጥ ያደርጋል፤

፲፱.የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ማሰልጠኛ ተቋማት ከተለያዩ መንግስታዊ ከሆኑና ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር የትብብር ሥልጠና እንዲፈራረሙ ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል፣ ይከታተላል፤

፳.በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዘርፍ ለተዘጋጁ ለሀገር አቀፍ ደረጃዎች፣ መመሪያዎች፣ ስትራቴጂዎችና መርሃ ግብሮች ለተቀናጀ አፈፃፀምና አተገባበር የአሰተዳደሩን ድርሻ በሚመለከት ከፌደራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ ጋር ተቀናጅቶ ይሰራል፤

፳፩.በከተማ ደረጃ የቴክኖሎጂ ምርምርና ሽግግር፣ የኢንኩቤሽን፣ የክህሎት፣ የብየዳ፣ የሥራ ፈጠራ ማዕከል ያደራጃል፤ ይመራል፤ ያስተባብራል

፳፪.በማስልጠኛ ተቋማት፣ በምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ማዕከላትና በሥራ ፈጠራ ማዕከላት መካከል የምርምርና የፈጠራ ክህሎት ውድድር በማዘጋጀት ዘርፉን ያበረታታል፡፡

፶፩.<u>የሳይንስና ቴክኖሎጂ ኤጀንሲ</u>

ኤጀንሲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩.የልማት ፍላጐት መሰረት ያደረገ የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ ምርምርና ልማት እቅዶች ያዘጋጃል፤ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፪.የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን እንቅስቃሴዎችን በበላይነት ያስተባብራል፤ በኢንዱስትሪዎች፣ ዩኒቨርስቲዎች፣ የምርምር ተቋማት እና ቴክኒክና ሙያ ተቋማት መካከል ጠንካራ ትስስርና ትብብር እንዲፈጠር ያደርጋል፤

፫.የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ልማትን አስመልክቶ ተገቢውን መረጃ መከታተል፣ ማሰባሰብና መተንተን የሚያስችል ሥርአትና ከተማ አቀፍ አቅምን ይገነባል፤

፬.የአስፈፃሚ ተቋማት አገልግሎት አሰጣጣቸው በኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ የተደገፈ እንዲሆን ያደርጋል፤ ደረጃ በደረጃም ለተጠቃሚዎች በቀጥታ አገልግሎት ሊሰጥ በሚችሉበት ሁኔታ መመቻቸታቸውን ያረጋግጣል፤

፭.የኢንፎርሜሽን ከሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት ክፍተትን ይለያል፤ አስፈላጊ መስፈርቶችን በማዘጋጀት ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፤ ሲፈቀድም ይዘረጋል፤ እንዲዘረጋም ያደርጋል፤

፮.ደረጃ አውጥቶ ወይም በወጣው ደረጃ መሰረት ሃርድዌርና ሶፍትዌር ያዘጋጃል፤ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤ ለአስተዳደሩ መስሪያ ቤቶች ያቀርባል፣ ተግባራዊ መሆኑን ይከታተላል፤ በዚህ መልኩ ለሚያዘጋጃቸው የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ስም ይሰጣል አጠቃቀም ጋር በተያያዘ የአስተዳደሩን መስሪያ ቤቶች ያማክራል፤

፯.የከተማ አስተዳደሩ ተቋማት የኮምፒውተር መረቦችና አፕሊኬሽኖች እንዲቀናጁና እንዲናበቡ ያደርጋል፤ ያረጋግጣል፤

፰.የከተማ አስተዳደሩን የመረጃ ስርዓት ያደራጃል፤ ጥራቱ፣ ደህንነቱና አስተማማኝነቱን ይጠብቃል፤

፱.በከተማው ውስጥ የኮፒውተር መረብ ዝርጋታ ስራዎችን ለሚሰሩ አካላት በጥናት ላይ የተመሰረተ ፈቃድ ይሰጣል፤

፲.ከሚመለከታቸው ልሎች አካላት ጋር በመተባበር በከተማ አስተዳደሩ የቴክኖሎጂ ፖርኮች እንዲቋቋሙ ያደርጋል፤

፲፩.የሳይንስና ቴክኖሎጂ እንቅስቃሴዎች የገንዘብና የዓይነት የማቴሪያልና የቴክኒክ ድጋፎች የሚያገኙበትን ስርዓት ይዘረጋል፤

፲፪.የአዕምሯዊ ንብረት መብት ጥሰቶችን ለመከላከልና የህብረተሰቡ ግንዛቤ ለማሳደግ ከሚመለከታቸው የፌደራል አካላት ጋር በመተባበር ይሰራል፤

፲፫.የጥራት መሰረተ ልማትና የጨረራ እና ጨረራ አመንጪ መከላከያ እንቅስቃሴዎችን ያስተባብራል፤ ለተግባራዊነቱም የበኩሉን ጥረት ያደርጋል፤

፲፬.የምርምር ፕሮቶኮሎች ሥነ-ምግባርን ተከትለው መካሄዳቸውን ይከታተላል፤ የሥነ-ምግባር ጉድለት ሲያጋጥም አስፈላጊ የሆኑ ሕጋዊ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ጥረት ያደርጋል፤

፲፭.የምርምር ሥራዎች (ፕሮቶኮሎች) እና የባዮኢቲክስ ምርምሮች ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዲተገበሩ ለማድረግ እንዲቻል ሥራውን በበላይነት የሚመራ አካል እንዲቋቋም ሀሳብ ያቀርባል፡፡

**<u>፶፪.የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ</u>**

ኤጀንሲው የሚከተሉትስልጣንናተግባራትይኖሩታል፡-

፩. አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የመሬት ይዞታን በተመለከተ የመብት፣ ክልከላ እና ኃላፊነት መረጃን ምዝገባ፣ ስረዛ፣ እድሳት፣ ማስተካከያ ልሎች የመሬት ይዞታ አገልግሎቶችን ባአግባቡ መሰጠታቸውን ያረጋግጣል፣ ይቆጣጠራል፤

፪. አግባብ ባለው ህግመሰረት ለተመዘገበ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት መሰጠቱን ያረጋግጣል፣ ይቆጣጠራል፤

፫. በሥልታዊ ዘዴ ወይም በአልፎ አልፎ ዘዴ የመሬት ይዞታን የማረጋገጥ ሥራዎች መከናወናቸውን ያረጋግጣል፤ ይቆጣጠራል፤

፬. ሀገራዊ ደረጃን መሰረት ያደረገ የቁራሽ መሬት ልዩ መለያ ኮድ ይሰጣል፤ ተግባራዊነቱንም ያረጋግጣል፤

፭. የመሰረታዊና የህጋዊ ካዳስተር ካርታ ያዘጋጃል፣ ወቅታዊ ያደርጋል፤

፮. የመሬት ይዞታ ምዝገባ መረጃን በዲጂታል እና በወረቀት ይይዛል፤ ያደራጃል፤ ይተነትናል፤ ወቅታዊ ያደርጋል፤ እንዲሁም መረጃውን ይጠቀማል፤ ጥሬና የተቀናጀ ወይም የተተነተነ መሬትና መሬት ነክ መረጃዎችን ያሰራጫል፤

፯. ወቅታዊ የከተማ መሬት፣ የፊዝካል መሠረተ ልማትና የማህበራዊ ተቋማት የስፓሻልና ስፓሻል ያልሆኑ መረጃዎችንና ጥናቶችን ከሚመለከታቸዉ ተቋማት ይሰበስባል፣ በጂ.አይ.ኤስና በካርቶግራፊ በማደራጀት ዳታ ባንክ ያዘጋጃል፣ ያስተዳድራል

፰. እንደአስፈላጊነቱ ከተማዋን ሙሉ በሙሉ የሚሸፍን እና ለተለያዩ ተቋማት የሚያገለግሉ የሪሞት ሴንሲንግ ቴክኖልጂ ማለትም የአየር ፎቶ፣ የሳተላይት ምስሎችንና የራዳር ፎቶዎችን በመጠቀም የግንባታዎችን፣ የመሬት አጠቃቀምና ልሎች የከተማ ለውጦችን በመለየት ለሚመለከታቸው አካላት ውሳኔ እንዲሰጡበት ያስተላልፋል፣ እንደአስፈላጊነቱ ጥሬ መረጃዎችን ለተለያዩ አካላት በሚያቀርቡት ጥያቄ መሠረት ይሰጣል፤

፱. ከሚመለከተው ባለድርሻ አካል ጋር በመሆን የአዲስ አበባ ከተማ ህጋዊ ካዳስተር መረጃ ሥርዓት ላይ መደበኛ የሆነ የስጋት እና የደህንነት ቁጥጥር ያደርጋል፤

፲. የህጋዊ ካዳስተር ቴክኖሎጂ ስርዓትን እና የኔት ወርክ መሰረተ-ልማትን ያሻሽላል፤ ወቅታዊ ያደርጋል፤ ያስተዳድራል፤

፲፩. በህግ መሰረት የሕጋዊ ካዳስተር መረጃን ለህዝብ ክፍት ያደርጋል፤

፲፪. ተግባሩን በሚመለከት የሚቀርቡ ቅሬታዎችን ይመረምራል፣ ውሳኔም ይሰጣል፤

፲፫. የሚሰሩ ሥራዎች እና የሚሰጡ አገልግልቶች ግልጽነት ያለውና ፈጣን እንዲሆኑ የሚያስችል የአሰራር ማንዋልችን ያወጣል፤ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ያከናውናል፤

፲፬. ኤጀንሲው በራሱ በሰጠው የምዝገባ ማስረጃ ምክንያት በቅን ልቦና ጉዳት ለደረሰባቸው ሶስተኛ ወገኖች በፍርድ ቤት ተጠያቂ ሆኖ ሲገኝ ክፍያ ይፈጽማል፤ የሚከፍለው የዋስትና ፈንድ በከተማው አስተዳድር እንዲቋቋም ክትትል ያደርጋል፤

፲፭.የመሬት መቆጣጠሪያ ነጥቦችን ሀገራዊ ስታንዳርዶችን መሠረት በማድረግ ያስተክላል፣ እንዲናበቡ ያደርጋል፤ ዘመናዊ ያደርጋል፤እንዲሁም ያስተዳድራል፤

፲፮. በሦስተኛ ደረጃ የሚተከል የመሬት የመቆጣጠሪያ ነጥቦችን የማብዛት ስራ ይሰራል፤

፲፯. መረጃ ለመሰብሰብ፣ ለማደራጀትና ለማሠራጨት እንዱሁም የአድራሻ ሥርዓት ለመዘርጋት፣ ለማስተዳደር እና የቤት ቁጥር ለመስጠት የሚያገለግል የህግ ማዕቀፎችንና ስታንዳርዶችን ያዘጋጃል፣ በሚመለከታቸዉ አካላት ያስጸድቃል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤ የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ይተገብራል፤ እንዲተገበር ሥልጠናና ድጋፍ ይሰጣል፤

፲፰.ለአድራሻ ሥርዓት የሚሆኑትን የመንገድ፣ የፓርሴልና የቤት ቁጥር በመስጠት እና ልሎች አስፈላጊ መረጃዎችን በመሰብሰብና በማደራጀት የአድራሻ ሥርዓትን ይዘረጋል፤ ዘመናዊ ያደርጋል፤ ያስተዳድራል፤

፲፱.የመሬት መረጃ አያያዝና አጠቃቀም እንዲሁም የአድራሻ ሥርዓትን በሚመለከት በፌደራልና በከተማ አስተዳደሩ ደረጃ የሚወጡ አግባብነት ያላቸዉ ህጎች ተግባራዊ መሆናቸውን ያረጋግጣል፡፡

፶፫.<u>የመሬት ልማትና ከተማ ማደስ ኤጀንሲ</u>

ኤጀንሲዉየሚከተሉት ስልጣንና ተግባራትይኖሩታል፡-

፩.የከተማዋን መዋቅራዊ ፕላን እና ዝርዝር የአካባቢ ልማት ፕላኖች መሰረት በማድረግና ፍትሃዊና ኢኮኖሚያዊ የመሬት ልማትና አቅርቦት፣ የከተማ ማደስ ጥናት ስራዎችን ያከናውናል፤ ይተገብራል፤

፪.የልማት ቅደም ተከተል በወጣላቸው አካባቢዎች የመልሶ ማልማት ፕሮጀክት ጥናት ያካሂዳል፤ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፫.ለልማት የተመረጡ አካባቢዎች በአካባቢ ልማት ፕላኑ መሰረት የተቀናጀ የከተማ ንድፍ ያዘጋጃል፤ ለሚመለከተው አካል በማቅረብ ያፀድቃል፤

፬.ለመልሶ ማልማትና ለመሬት ዝግጅት ተፈላጊውን መሰረተ ልማት ያጠናል፤ ለሚመለከታቸው ያሳውቃል፤ ከገንቢዎች በሚገኝ ግብዓት የግንባታ ቅንጅት እቅድና በጀት ያዘጋጃል፤ ሲፈቀድም ያስገነባል፤

፭.ለተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶች የሚውል መሬት ወሰን ያስከብራል፤አዘጋጅቶ ያቀርባል፤

፮.የተጎዱና ያረጁ አካባቢዎችን ይለያል፤ የሕዝቡን ተጠቃሚነት ባረጋገጠ ሁኔታ ፕላኑን ጠብቆ መልሶ እንዲለማ ያደርጋል፤

፯.ለልማት ይዞታቸውን የሚለቁ ባለይዞታዎች ከመልቀቃቸው በፊት አግባብ ባለው ህግ መሰረት የይዞታ ማስለቀቅ ሂደቱን ይተገብራል፤

፰.ለመሠረተ ልማት አውታር፤ ለመናፈሻ፣ ለአረንጓዴ ልማት እና ለሕዝብ መሰብሰቢያ ፕላዛዎች በፕላኑ መሠረት ቦታ መወሰኑን ይከታተላል፤ የወሰን ማስከበር ሥራዎች ያከናውናል፤ የይዞታ የምስክር ወረቀት እንደየአግባቡ እንዲሰጥ ለሚመለከተው አካል ያስተላልፋል

፱.የማዕድን ማውጫ ቦታዎችን ማለትም የድንጋይ፣ የጠጠር እና የገረጋንቲ ቦታዎች በፕላኑ መሠረት ከልሎ በማስቀመጥ ለመሬት ባንክና ማስተላለፍ ጽህፈት ቤት ያስረክባል፤ የቦታዎቹ ጠቀሜታ ሲያበቃም ተከታትሎ በመረከብ ለዳግም ልማት ያዘጋጃል፤

፲.በልማት ስራዎች እና መልሶ ማልማት ተነሽ ለሆኑት ተገቢውን የካሳ ግምት ይተምናል፤ የካሳ ክፍያ ይፈጽማል፤ ምትክ ቦታ ያዘጋጃል፤ ይሸነሽናል፤ የምትክ ቤት መቀበያ ሰርተፊኬት ይሰጣል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

፲፩.የምትክ ቤት ፍላጎትን ያጠናል፤ ለሚመለከተው ያሳውቃል፤ ሲፈቀድም ለተነሽዎች ምትክ ቤት ድልድል በማድረግ እንዲሰጣቸው ለሚመለከተው አካል ያስተላልፋል፤ ያረጋግጣል፤

፲፪.በከተማ ማደስና በተለያዩ ምክንያቶች የተረከባቸውን የከተማ ቦታዎች ለመሬት ባንክና ማስተላለፍ ጽህፈት ቤት በሰነድ ያስረክባል፤

፲፫· ለግንባታ ተረፈ ምርት መድፊያነት አገልግሎት የሚሰጡ ቦታዎችን ከልሎ ለመሰረተ ልማት ቅንጅት፣ ግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን ያሳውቃል፤ ያስተዳድራል፤ በባለስልጣኑ በተሰጠው ፈቃድ መሰረት በተገቢው የተደፋ መሆኑን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፡፡

**፺፬·<u>የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ ኤጀንሲ</u>**

ኤጀንሲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩·ዝርዝራቸው በኤጀንሲው መመሪያ የሚወሰኑ የመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚጠቀሙባቸውን ተመሳሳይ ዕቃዎች፣ አገልግሎቶችና ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ ያላቸው ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ ያከናውናል፤

፪·በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ ፩ላይ የተገለፀው ቢኖርም በመንግስት ለሚከናወኑ የግንባታ ስራዎች ግዥ ግንባታውን እንዲያስፈፅም ስልጣን በተሰጠው አካል ተፈፃሚ ይሆናል፤

፫·ግምታቸው አግባብ ባለው ህግ መሰረት ከሚወሰን የገንዘብ መጠን በላይ የሆኑ በአስተዳደሩ መስሪያ ቤቶች ኃላፊነት ስር ያሉ ንብረቶች እንዲወገዱ ውሳኔ የተሰጠባቸውን ንብረቶች ይሸጣል፤

፬·ለመንግስት የልማት ድርጅቶችና ለግሉ ዘርፍ በወቅታዊ የገበያ መረጃ ላይ የተመሰረተ የአገር ውስጥና የዓለም አቀፍ የግዥ አገልግሎቶችን ይሰጣል፤

፭·ለከተማ አስተዳደሩ መሥሪያ ቤቶች ግዥን በተመለከተ የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፤

፮·በከተማው አስተዳደር ለሚገኙ መንግስት መስሪያ ቤቶች፤ ለልማት ድርጅቶች እና ለግሉ ዘርፍ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች ተመጣጣኝ ዋጋ ያስከፍላል፤

፯·በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፩ እና ፪ የተመለከቱትን ሥልጣንና ተግባሮች በስራ ላይ ሲያውል፡-

ሀ. የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገዱ ተግባር አግባብ ባለው ህግ መሰረት መፈጸሙን ያረጋግጣል፤

ለ. ግዥ የተፈጸመላቸው የመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚጠቀሙባቸው ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የአገር ውስጥ ግዥ ሂደት አጠናቆ የማዕቀፍ ስምምነት በመፈራረም ይህንኑ የመንግስት መሥሪያ ቤቶች እንዲያውቁት ያደርጋል፤

ሐ. የመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚጠቀሙባቸው ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ዓለም አቀፍ ግዥ፤ ከተማዊ ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ ያላቸውን ዕቃዎችና አገልግሎቶች የግዥ ሂደት በማጠናቀቅ ዕቃዎቹና አገልግሎቶቹ ለተጠቃሚ እንዲደርስ ያደርጋል፤

መ. ልዩ ሙያዊ እውቀት በሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች አግባብነት ካላቸው መንግስታዊ ተቋማት መጠየቅና ማግኘት ይኖርበታል፡፡

**፺፭·<u>የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ኤጀንሲ</u>**

ኤጀንሲው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖረዋል፡-

፩.የከተማው የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ፣ አሰባሰብ፣ አጓጓዝና አወጋገድ የህዝብ ጤናን በማይጎዳና የአካባቢ ብክለትን በማይፈጥር መንገድ ለማከናወን የሚያስችል ቀልጣፋና ውጤታማ አሰራር ይዘረጋል፤ ይተገብራል፤ እንዲተገበር ያደርጋል፤ ይቆጣጠራል፤

፪. በህብረተሰቡ ዘንድ የአመለካከትና የባህሪይ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችሉ የትምህርትና ግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን በየደረጃው ያከናውናል፤ ልዩ ልዩ ስልጠናዎችንም ይሰጣል፤ እንዲሰጥም ያስተባብራል፤

፫.የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ስራዎችን ለመተግበር በከተማ ደረጃ የወጡና የፀደቁ ፖሊሲና ህጎች በየደረጃው እንዲፈፀሙ ያደርጋል፤ይከታተላል፤ይቆጣጠራል፤

፬. የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራት እና የግል የጽዳት ድርጅቶች በከተማው የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ስራዎች የሚሳተፉበትን አማራጮች በማጥናት እንዲተገበር ያደርጋል፤

፭.ደረቅ ቆሻሻ ከምንጩ የሚቀንስበትንና የሚለይበትን ስርዓት ይዘረጋል፤ የደረቅ ቆሻሻ የመልሶ መጠቀምና ማስወገድ ስራዎች በአግባቡ መፈፀማቸውንም ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

፮.ለአገልግሎቱ የሚወጣው ወጪ በተገልጋዮች የሚሸፈንበትን የታሪፍና የክፍያ ስርዓት አጥንቶ ያቀርባል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፯.የግል ባለሀብቶችና የግል ጽዳት ድርጅቶች የሚያቀርቡትን የፕሮጀክት ፕሮፖዛል ይገመግማል፤ የብቃት ማረጋገጫ፤ የምስክር ወረቀትና የስራ ፍቃድ ይሰጣል፤ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ እርምጃ ይወስዳል፤

፰.የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ማዕከላትንና ስፍራዎችን ያስተዳድራል፤ ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል የማሻሻያ ስራዎችን በማከናወን የማስወገጃ ቦታው በህዝብ ጤና እና በአካባቢ ላይ አሉታዊ ተፅእኖ በማያስከትል መንገድ አገልግሎት እንዲሰጥ ያደርጋል፤ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

፱. የመልሶ መጠቀሚያ ማዕከላትና የማስወገጃ ቦታ የደረቅ ቆሻሻ በክብደት ሚዛን የሚመዘንበትንና ትክክለኛ መጠኑ የሚታወቅበትን ስርዓት ይዘረጋል፤ መረጃዎችን መዝግቦ ይይዛል፤ ያሰራጫል፤ እንዲሁም የከተማዋን የደረቅ ቆሻሻ አጠቃላይ ሁኔታ ከመረጃው ተነስቶ ማስተካከያ የሚደረግባቸውን መረጃዎች በማደራጀት ለወሳኝ አካል ያቀርባል፤

፲.የደረቅ ቆሻሻ ጊዜአዊ ማስቀመጫ ቦታዎችን በከተማው የተለያዩ አቅጣጫዎች በማጥናት እንዲገነቡና ጥቅም እንዲውሉ ያደርጋል፤

፲፩. የመልሶ መጠቀምና የቀልዝ (የብስባሽ ማዳበሪያ) ማዕከላትን በማስፋፋት ደረቅ ቆሻሻ መልሶ ጥቅም ላይ የሚውልበትን፣ ጠቃሚ ውጤት የሚያስገኝበትን የተለያዩ የቴክኖሎጂ አማራጮች በማጥናት እንዲተገበሩ ያደርጋል፤ ውጤታቸውንም ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

፲፪· መልሶ መጠቀሚያ ማዕከላትና ማስወገጃ ቦታ የአገልግሎት ክፍያ ታሪፍ በማጥናት ያቀርባል፣ ሲፀድቅ ይተገብራል፤

፲፫· የአዲስ ሳኒተሪ ላንድፊል ቦታ መረጣ፣ የጥናትና የማልማት ስራዎችን በበላይነት ይመራል፤ ያስተባብራል፤ ይቆጣጠራል፤

፲፬· የደረቅ ቆሻሻ ማንሻ ተሽከርካሪዎችን እንዲሁም ማሽነሪዎችን ያሰማራል፣ ያስተዳድራል፡፡

**፶፮·የህብረት ስራ ማህበራት ኤጀንሲ**

ኤጀንሲው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩·አግባብ ባለው ህግ መሰረት የህብረት ስራ ማህበራትንና የጋራ ህንፃ ባለቤቶች ማህበራትን ያደራጃል፤ ይመዘግባል፤ ያስፋፋል፤ የሕጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ ማህበሩ ሲፈርስ ከመዝገብ ይሰርዛል፤

፪·የህብረት ስራ ማህበራት በዩኒየንና በፌዴሬሽን ደረጃ እንዲደራጁ ያበረታታል፤ የህብረት ስራ ማህበራት ባንክ የሚቋቋምበትን መንገድ ያጠናል፤ለገንዘብና ቁጠባና ብድር ህብረት ስራ ማህበራት የተደራጁትን አባላት ቁጠባ ባህል እንዲዳብር እና ቁጠባ ድርሻቸውን ከፍ በማድረግ ወደ ኢንቨስትመንት የሚሸጋገሩበትን አሰራር ስርዓት ይዘረጋል፤

፫·ባህላዊና አገር በቀል የራስ አገዝ ማህበራት ወደ ዘመናዊ የህብረት ስራ ማህበራት የሚያድጉበትን ጥናትና ምርምር ያደርጋል፤ የጥናቱንም ውጤት ያስተዋውቃል፤ ያሰራጫል፤ ለተግባራዊነቱም ይሰራል፤

፬·የህብረት ስራ ማህበራት ስራ አመራርና የሂሳብ አያያዝ ዘመናዊ አሰራርን እንዲከተል አስፈላጊውን የስልጠና ፕሮግራም ያዘጋጃል፤ ይሰጣል፤

፭·የህብረት ሥራ ማህበራትን ሂሳብ ይመረምራል፤ ሂሳብ አጣሪም ይመድባል፤ ሲፈርሱም ከመዝገብ ይሰርዛል፤ አግባብ ባለው ህግ የህብረት ሥራ ማህበራት የሚከተሉትን የሂሳብ አያያዝና ምርመራ ስርዓት ይከታተላል፤

፮·የህብረት ስራ ማህበራት የገበያ መሰረተ ልማት እንዲሟላላቸው አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፤ ይከታተላል፤ የመስሪያ ቦታ፣ የመሸጫ ቦታ እና ልሎች መሰል ተቋማት አስተዳደርና አጠቃቀምን በሚመለከት አግባብነት ባለው ህግ መሰረት ችግሮቻቸው የሚፈቱበትን አግባብ ያመቻቻል፤ የምክር አገልግሎት ይሰጣል

፯·የህብረት ሥራ ማህበራት ምርቶች ገበያ እንዲገኙ ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል፤ በአገር ውስጥ ሸማቹና አምራቹ በቀጥታ ሚገናኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

፰·በከተማዋ የሚገኙ የህብረት ስራ ማህበራት ምርቶች ተጨማሪ እሴት ወይም ዋጋ እንዲኖራቸው፣ ወደ ኢንዱስትሪ ምርታማነት እንዲለወጡ እና የእደ-ጥበብ ምርቶች እንዲያድጉ የሙያና የቴክኒክ ድጋፍ ያደርጋል፤

፲.የህብረት ስራ ማህበራትን ለማስፋፋትና ለማጠናከር የሚረዳ የገበያ ጥናት በማድረግ አስፈላጊ መረጃዎችን ያጠናቅራል፤ ያሰራጫል፤ አግባብ ባለው ህግ ለህብረት ስራ ማህበራት የሚሰጡ ማበረታቻዎችን ያጠናል፤ ሲፈቀድም ተግባራዊ መሆኑን ያረጋግጣል፤

፲፩.ከተማዋን ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘበ እና ለህብረት ሥራ ማህበራት እድገት የሚበጁ ልዩ ልዩ የፕሮጀክት ሃሳብን በማመንጨት፣ አዋጭነታቸውን በማጥናት እና በማዘጋጀት ማህበራት እንዲሰማሩባቸው ያበረታታል፤

፲፪.የህብረት ስራ ማህበራት ሞዴል የመተዳደሪያ ደንቦችን ያዘጋጃል፡፡

## ፶፯.የምግብ ዋስትና እና ልማታዊ ሴፍቲኔት ኤጀንሲ

ኤጀንሲው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖረዋል:-

፩.መስራት እየቻሉ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ምክንያት ሥራ ሳይኖራቸው በከፋ ድህነት ላይ የሚኖሩ የከተማ ነዋሪዎችን መረጃ ያሰባስባል፤ ይለያል፤ ያደራጃል፤ ይተነትናል፤ ሲፈቀድለትም በማህበረሰብ አቀፍ ልማት ስራዎችና በዘላቂ ኑሮ ማሻሻያ ፕሮግራም ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

፪.በማህበረሰብ አቀፍ ልማት ስራዎች እና በኑሮ ማሻሻያ ፕሮግራሞች ለሚታቀፉ ተጠቃሚዎች እና ልሎች ተያያዥ ስራዎችን ለማከናወን እንዲያስችል ዘመናዊ የመረጃ ስርዓት ይዘረጋል፤ መረጃዎችን ያደራጃል፤ ይተነትናል፤ ያሰራጫል፤ ጥበቃ ያደርጋል፤

፫.በፕሮግራሙ የታቀፉ ግለሰቦችና ቤተሰቦች ድጋፍና ክትትል በማድረግ የተጠቃሚነት ጊዜያቸው ሲያበቃ የማስመረቅ ስራ ይሰራል፤

፬.ስለ ልማታዊ ሴፍቲኔት እና ምግብ ዋስትና ሁለንተናዊ ጠቀሜታ፣ ስለ ህብረተሰቡ ሚና፣ ስለሀብት አሰባሰብና አጠቃቀም በተመለከተ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን ይሰራል፤

፭.አግባብ ባለው ህግ ሀብት የሚገኝበትን ስልት ይቀይሳል፤ ያጠናል፤ ፕሮጀክቶችን ቀርጾ ሀብት ያፈላልጋል፤ ሲፈቀድለትም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፮.ለኤጀንሲው መግባት የሚገባው ሀብትና ገንዘብ በወቅቱ ገቢ መደረጉን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፡፡

## ፶፰.የወሳኝ ኩነት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ

ኤጀንሲውየሚከተሉትሥልጣንናተግባራትይኖሩታል፡-

፩. በከተማ አስተዳደሩ የወሳኝ ኩነት ምዝገባን በበላይነት ይመራል፤ ያስተባብራል፤ ይመዘግባል፤ መመዝገቡን ይቆጣጠራል፤ ይከታተላል፤

፪. የነዋሪነት መታወቂያና ልሎች የነዋሪዎች አገልግሎቶችን ይሰጣል፤

፫. የክብር መዝገቦች ዝግጅትና ስርጭትን፣ የመረጃ አጠቃቀም ሥርዓት አግባብ ካለው የፌዴራል አካል ጋር በመተባበር ይሰራል፤ ድጋፍ ይሰጣል፤ የክብር መዝገቦች ለሁሉም ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች መሰራጨታቸውን ያረጋግጣል፤

፬· የወሳኝ ኩነት ምዝገባ አስፈላጊነትን አስመልክቶ የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ስልጠናዎች ይሰጣል ወይም እንዲሰጥ ያደርጋል፤

፭· የወሳኝ ኩነት ምዝገባ የጥራትና የሽፋን ደረጃ ለመገምገምና ለመቆጣጠር የሚያስችል ጥናት ያካሂዳል፤ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፮· በወሳኝ ኩነት ምዝገባ እና የብሔራዊ መታወቂያ አዋጅ መሠረት የተሰበሰቡ መረጃዎችን አግባብ ላለው የፌደራል አካል በወቅቱ ያስተላልፋል፤

፯· የወሳኝ ኩነት ምዝገባና የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት በቴክኖሎጂ የታገዘ እንዲሆን ያደርጋል፤

፰· መንግስታዊ ተቋማት፣ ማህበራት እና የበጎ አድራጎት ድርጅቶች የሚደረገው የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ሥርዓት የተሟላ እንዲሆን ተገቢውን ድጋፍ እንዲያደርጉ ያስተባብራል፡፡

**፶፱·የተፋሰስና አረንጓዴ አካባቢዎች ልማት ኤጀንሲ**

ኤጀንሲውየሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖረዋል፤

፩· በፕላኑ የተመላከቱ አረንጓዴ አካባቢዎችን ይለያል፤ የይዞታ ማስረጃ ሊወጣላቸው የሚችሉትን በሚመለከተው አካል በስሙ በማስመዝገብ የይዞታ ምስክር ወረቀት ያወጣል፤

፪· ተፋሰሶችን እና አረንጓዴ አካባቢዎችን ያስከብራል፤ ይጠብቃል፤ በተፋሰሶች እና በአረንጓዴ አካባቢዎች በፕላንና በዲዛይን ያልተደገፈ ልማት እንዳይካሄድ ይከላከላል፤ የተካሄደም ካለ በሕግ መሰረት እንዲወገድ ያደርጋል፤

፫· የተፋሰሶችን እና የአረንጓዴ አካባቢዎችን ቅደም ተከተል በማውጣት የልማት ወይም መልሶ የማልማት ዝርዝር ፕሮጀክት ያዘጋጃል፤ የተቀናጀ የአረንጓዴ ልማት ቦታ አቀማመጥ ዲዛይን በማዘጋጀት ለፕላንና ልማት ኮሚሽን ያቀርባል፤ ሲጸድቅም ይተገብራል ወይም እንዲተገበር ያደርጋል፤

፬· የአረንጓዴ ሽፋን ምጣኔ መሰረት የልማት ደረጃ ጠብቆ ወይም አስጠብቆ ያለማል፤ ወይም እንዲለማ ያደርጋል፤ ለወንዝና ለደን ስፍራነት መዋል የሚገባቸው ተጨማሪ ቦታዎች በማጥናት ያቀርባል፤ ሲወሰንም እንዲለሙ ያደርጋል፤ ዘላቂ ማረፊያ ቦታዎችን ከሚመለከተው አካል ጋር በመቀናጀት የማስዋብ ስራ ያከናውናል፤ ያስተዳድራል፤

፭· የአዲስ አበባ መንገዶች ባለስልጣን የመንገድ ግንባታ ዲዛይን አካል አድርጎ በሚያዘጋጃቸው የመትከያ ስፍራዎች ዲዛይን መሰረት በዋና መንገዶች እና በመለስተኛ ዋና መንገዶች ግራና ቀኝ ዳርቻዎች፣ አካፋዮች እና አደባባዮች ከልሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር አግባብ ያላቸውን የጥላ ዛፎች ይተክላል፤ ወይም እንዲተከሉ ያደርጋል፤ ይንከባከባል፤ ይጠብቃል፤

፮· የአሽከርካሪዎችን የርቀት እይታ የሚጋርዱ ወይም የደረቁ የመንገድ ዳር፣ አካፋይ እና የአደባባይ ዕጽዋት እንደአስፈላጊነቱ ያስወግዳል ወይም ይመለምላል፤

፯.የከተማውን አየር ሚዛን የሚጠብቁ እንዲሁም ለከተማው ውበትና መናፈሻ ልማት የሚውሉ የእፅዋት ችግኝ ጣቢያዎችን ያስፋፋል፣ ያስተዳድራል፣ ችግኞችን ለተጠቃሚዎች አግባብ ባለው በህግ ያቀርባል፣

፰. በከተማው ውስጥ መልማት ያለባቸው በላቀ ሁኔታ ውጤታማ የሆኑና ያልታወቁ ወይም ያልተሞከሩ የውጭ እና ሀገር በቀል የዕፅዋት ዝርያዎችን በማጥናት የሚለሙበትን አግባብ በሕግ መሰረት ያስተዋውቃል፣

፱. የለሙ ተፋሰሶችንና አረንጓዴ አካባቢዎችን ይንከባከባል፣ ያስተዳድራል፣

፲. በአካባቢ ልማት ፕላን መሰረት የሠፈር ቁርጥራጭ ክፍት ቦታዎች በሠፈሩ ነዋሪዎችና እንደየአግባቡ በልሎች ባለድርሻዎች ቀጥተኛ ተሳትፎ የከተማው አረንጓዴ ልማት አካል ሆነው እንዲለሙ ያደርጋል፣ ይንከባከባል፣ ይጠብቃል፣ ያስጠብቃል፣

፲፩. የዝናብ ውሃ በተፋሰስ መነሻ ጥቅም ላይ እንዲውል ወይም እንዲሰርግ ለማድረግ የሚያስችል ጥናት ያካሂዳል፣ ይተገብራል፣

፲፪. የህዝብ መጸዳጃ ቤቶች እንዲገነቡ ያደርጋል፣ ያለማል፣ ያስተዳድራል፣ የግል ባለሀብቶች በዘርፉ እንዲሰማሩ ያበረታታል፣

፲፫. የለሙ ወይም በቀጣይ የሚለሙ የተፋሰስና የአረንጓዴ ልማት ማዕከላት በቂ ገቢ በማመንጨት ወጪያቸውን መሸፈን እንዲችሉ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፣

፲፬. ለሥራው እንቅስቃሴ ስኬታማነት ድጋፍ ሊያደርጉ ከሚችሉ የፌዴራልና የክልል አግባብ ያላቸው ተቋማት እንዲሁም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና የመስኩ የምርምርና ስርፀት ተቋማት ጋር በመተባበር ይሰራል፡፡

## ፳. <u>የህዝብ ቅሬታና አቤቱታ ማስተናገጃ ጽህፈት ቤት</u>

ጽህፈት ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩.የከተማ አስተዳደሩ ካወጣው አዋጅ ደንብና መመሪያ ውጪ በተሰጠ የአገልግሎት አሰጣጥ ምክንያት በመንግሥት መሥሪያ ቤት፣ በኃላፊ እና በሠራተኛ ላይ የሚቀርብለትን ጥቆማ፣ አቤቱታና ቅሬታ ይቀበላል፣ ያጣራል፣ ውሳኔ ይሰጣል፣ ውሣኔውን ለአቤት ባይ በጽሑፍ ያሣውቃል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣

፪.በውሣኔው መሠረት እንዲፈፀም ውሣኔውን በሾኚ ደብዳቤ ለሚመለከተው የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ይልካል፣ በውሣኔው መሠረት መፈፀሙን ይከታተላል፣

፫.የቀረበለትን አቤቱታ ወይም በከንቲባ የተመራለትን ጉዳይ ለማጣራት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ማንኛውንም ሰነድ ወይም መረጃን ያስቀርባል፣ ያጣራል፣ የሚመለከተው ባለሥልጣን ወይም ሌላ ግለሰብ ጠርቶ በቃል ወይም በጽሑፍ እንዲያስረዳ ያደርጋል፣

፬.ከከንቲባው የሚመራ ጉዳይን በማጣራት የውሳኔ ሃሳብ ለከንቲባው ያቀርባል፣

፳.አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ ያልወጣለትና ግልፅነት የጎደለውን ጉዳይ፣ ከነዋሪው ህብረተሰብና ከሌላ አካል የሚቀርቡ አቤቱታ እና ቅሬታን ተቀብሎና አጣርቶ የውሳኔ ሃሳብ ለከንቲባው ያቀርባል፤ ሲወሰን እንዲፈጸም ያደርጋል፤

፳፩.ጽህፈት ቤቱ በመንግስት መስሪያ ቤት ላይ ወይም የመስሪያ ቤት ኃላፊ ወይም ሰራተኛ ላይ የቀረበውን ቅሬታና አቤቱታ በዝርዝር ካጣራ በኋላ ለችግሩ አግባብነት ያለው የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ በሚከተለው አግባብ እንዲተገበር ያደርጋል፡-

ሀ. በከተማ፣ በክፍለ ከተማ ወይም በወረዳ ምክር ቤት በተሾሙ፣ በከተማ ከንቲባ በተሾመ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ኃላፊ ላይ ከሆነ አቤቱታውን አጣርቶ ለሾመው አካል የውሣኔ ሃሣብ ያቀርባል፤

ለ. ጥፋቱን የፈጠረው የመንግስት ሰራተኛ ከሆነ ለሚመለከተው መስሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ አግባብ ባለው ህግ መሰረት በዲሲፕላን እንዲጠየቅና ወሳኔ እንዲሰጥበት የተጣራውን ማስረጃ አያይዞ ያቀርባል፤ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤

ሐ. ጥፋቱ በወንጀል ወይም በፍትሀ ብሔር ህግ የሚያስጠይቅ ከሆነ ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ በየደረጃው ለሚመለከተው ፍትህ አካላት ይልካል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤

መ. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፳፩ (ሀ) እና (ለ) መሰረት በህግ አግባብ አስተዳደራዊ እርምጃ የማይወስድ እና ውሳኔው የማይፈፀምለት ከሆነ ጽህፈት ቤቱ ውሳኔውን ለመፈፀም ፍቃደኛ ያልሆነውን ኃላፊ ወይም ሠራተኛ አግባነት ባለው ህግ እንዲጠየቅ ያደርጋል፤

፳፪.በመስሪያ ቤት ላይ የሚታይ የቅሬታና አቤቱታ መንስኤ ሳይንሳዊ በሆነ ጥናት እየለየ ለችግሩ ተገቢውን የመፍትሄ ሃሳብ ለከንቲባው በማቅረብ ቅሬታው ከምንጩ የሚቀንስበትን ተግባር ያከናውናል፤

፳፫.የጥቆማ፣ ቅሬታና አቤቱታ ማስተናገጃ ስርዓቱን ለመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ ለኃላፊዎቻቸው፣ ለሠራተኞች እና ለከተማው ነዋሪዎች በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች በመጠቀም ግንዛቤ እና ስልጠና ይሰጣል፤

፳፬.የጥቆማ፣ ቅሬታና አቤቱታ አቀራረብና አወሳሰን ስርዓቱን ቀልጣፋና ዘመናዊ ያደርጋል፤ መረጃን ይይዛል፤

፳፭.በእያንዳንዱ መንግስት መስሪያ ቤት የተዘረጋውን የቅሬታና አቤቱታ መቀበያ ስርዓት በተቀመጠለት አሰራር መሰረት እየሰራ መሆኑና ተገልጋዩን በአግባቡ እያገለገለ መሆኑን በቅርብ ይከታተላል፤ ውጤታማ እንዲሆን ድጋፍ ያደርጋል፡፡

## ፷፩.<u>የመሬት ባንክና ማስተላለፍ ጽህፈት ቤት</u>

ጽህፈትቤቱየሚከተሉት ስልጣንና ተግባራትይኖሩታል፡-

፩.ከመሬት ልማትና ከተማ ማደስ ኤጀንሲ የለማ መሬትን በሰነድ በመረከብ በመሬት ልማት ባንክ ይመዘግባል፤ በዲጂታል እና በፕላን ፎርማት ተገቢውን መረጃ ይይዛል፤የ ቦታውንም አገልግሎት ደረጃ እና አስፈላጊ መግለጫዎችን የያዘ የመለያ ሰልዳይተክላል፤ቦታዎቹ ለህገወጥነት እንዳይጋለጡ ይከላከላል፤

፮.አግባብ ባለው ህግ መሬት ያስተላልፋል፤ የሊዝ ውል ይዋዋላል፤ ቦታ ያስረክባል፤ በውሉ መሰረት የሊዝ ክፍያ ይሰበስባል፤ በወቅቱ ፈሰስ ያደርጋል፤

፯.በተፈረመው የሊዝ ውል መሠረት ግንባታ መከናወኑን ያረጋግጣል፤ በሕግና በውል በተወሰነው ጊዜና ሁኔታ ግንባታ ካልተጀመረ ወይም ካልተጠናቀቀ አግባብ ባለው ህግ ተገቢውን ዕርምጃ ይወስዳል፤ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

፰.ባንክ የተደረጉ ክፍት መሬቶችን ወይም ይዞታዎችን እንዲመዘገቡ ለመሬት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ያስተላልፋል፤ በከተማ ልማትን በአግባቡ ለማመጣጠን የመሬት አቅርቦትንና ፍላጎትን ይመራል፡፡

፹፪.<u>የመሬት ይዞታ አስተዳደር ጽህፈት ቤት</u>

ጽህፈትቤቱየሚከተሉት ስልጣንናተግባራትይኖሩታል፡-

፩.የከተማው ቦታ ይዞታ አመዘጋገብና የመረጃ አያያዝ እንዲሁም የይዞታ እና ወይም የባለቤትነት ስም ዝውውር በወጡ ፖሊሲዎችና ህጎች መሰረት ያከናውናል፤አፈጻጸሙንም ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያደርጋል፤ ከፖሊስና ከህግ ውጪ የሆኑ የይዞታ አስተዳደር አፈፃፀም ሲከሰት የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፤

፪.የይዞታ እና የማይንቀሳቀስ ንብረት መዝገቦ ለመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ እስኪተላለፍ ጥበቃ ያደርጋል፤ የቦታ ይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤

፫.የመሬት ይዞታ እና የቤት አጠቃቀም ዓይነትና የባለይዞታዎች መረጃዎች ይይዛል፤ ይጠብቃል፤ አግባብ ባለው ህግ ለህጋዊ ባለይዞታዎች የቦታ አገልግሎት ለውጥ ጥያቄዎች መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፤

፬.ስለይዞታ አስተዳደር የሰጠውን አገልግሎት የሚመለከቱ መረጃዎችን በአግባቡ ይይዛል፤ ያደራጃል፤ መረጃውን ለመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ያስተላልፋል፤

፭.የቦታ ኪራይና የቤት ግብር ተመን አስልቶ ለሚመለከተው አካል በወቅቱ ያስተላልፋል፤

፮.ከካሳ ጉዳይ በስተቀር ለግብር ሰብሳቢ ተቋማት፣ ለፍርድ ቤቶችና ለልሎች ለሚመለከታቸው አካላት የንብረት ግምት አገልግሎት ይሰጣል፤ በመሬት ይዞታና ምዝገባ መረጃ ኤጀንሲ በተመዘገቡ ይዞታዎች ላይ የቤት ግምት አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም ወይም አደረጃጀት እስኪፈጠር ድረስ የግምት አገልግሎት ይሰጣል፤

፯.በህግ የሚቀመጠውን የአሰራር ስርአት ተከትሎ እና በከተማ አስተዳደሩ ለሚፈቀድላቸው፣ ለሰነድ አልባ ይዞታዎች የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ይሰጣል፤ ማህደራቸውን ያደራጃል፤

፰.በካርታ ዝግጅት ወቅት የሚታዩትን የሽንሻኖ ጉድለት በየጊዜው በመገምገም የጥራት ቁጥጥር ያካሂዳል፤

፱.የመሬት አጠቃቀም አይነትና የባለይዞታዎች መረጃዎችን ይይዛል በህግ መሰረት ለህጋዊ ባለይዞታዎች የቦታ አገልግሎት ለውጥ ጥያቄዎች አጣርቶ ውሳኔ ይሰጣል፤

፲.ለሰነድ አልባ ይዞታዎችና አግባብ ባለው አካል ሳይፈቀድ ለተያዙ ይዞታዎች የሽንሻኖ ማስተካከል ፕላን ያዘጋጃል፤ ሲፈቀድም የይዞታ ማስረጃ በተስተካከለዉ አግባብ ይሰጣል፡፡

፳፫.<u>የግንባታ ዲዛይን ጽህፈት ቤት</u>

ጽህፈት ቤቱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖረዋል፡-

፩.የጋራ መኖሪያ ቤቶች እና ቤቶች፣ ህንጻ፣ ድልድይ፣ ግድብ፣ መንገድ፣ ፍሳሽ ማስወገጃ እና ተዛማጅ ግንባታዎችን ዲዛይን ፍላጎት ጥናት ያከናውናል፤ ዲዛይን ያዘጋጃል፤ በዲዛይኑ መሠረት የቅየሳ ስራ ያከናውናል፤ ውል ያስተዳድራል፤

፪.መሠረተ-ልማት ግንባታ ዘርፍ ለጥናት፣ ዲዛይን እና ግንባታ ቁጥጥር የሚያስፈልጉ ደረጃዎች ዝግጅት አገልግሎት ይሰጣል፤

፫.ለቴክኖሎጂ ሽግግር የሚያግዙ የዲዛይን፣ ሱፐርቪዥን እና መሰል አገልግሎቶች ላይ የምክር አገልግሎት ይሰጣል፤

፬.በግንባታ ዘርፍ የዲዘይን ስራዎችን በሚመለከት የጨረታ ሰነድና ውል በማዘጋጀት ከሚመለከተው አካል ጋር አማካሪዎችን እና ተቋራጮችን የመምረጥ አገልግሎት ይሰጣል፤

፭.ግንባታው ከሚከናወንላቸው ተቋማት ጋር በመሆን የዲዛይኑን ወይም የግንባታውን ስፔስፊኬሽን ያዘጋጃል፤ ተግባራዊነቱን ይከታተላል ይቆጣጠራል፤ ተገቢውን ሕጋዊ እርምጃ ይወስዳል፤ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

፮.በአስተዳደሩ በጀትና በህብረተሰብ ተሳትፎ ለሚሰሩ የግንባታ ስራዎች ዲዛይኖች፣ የስራ ዝርዝሮች እና ልሎች የግንባታ ውሎች ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን ያዘጋጃል፤ እንዲዘጋጁ ያደርጋል፤

፯.በአስተዳደሩ በጀት የሚከናወኑ ግንባታዎች በአግባቡ እየተገነቡ መሆኑን ለማረጋገጥ አስፈላጊውን ቁጥጥር ያደርጋል፤ ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፤ እንዲወሰድ ያደርጋል፡፡

፳፬.<u>የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ህዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ጽህፈት ቤት</u>

በዚህ አዋጅ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ህዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ጽህፈት ቤት በተቋቋመበት ህግ በተሰጠው ሥልጣንና ተግባር መሰረት ስራውን ይቀጥላል፡፡

፳፭.<u>የኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከያና መቆጣጠርያ ጽህፈት ቤት</u>

በዚህ አዋጅ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኤችአይ ቪኤድስመከላከያናመቆጣጠሪያጽህፈት ቤት በራሱ ህግ በተሰጠው ሥልጣንና ተግባር መሰረት ስራውን ይቀጥላል፡፡

፫፮.የቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን

ኮርፖሬሽኑ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖረዋል፡-

፩.በቢሮ የሚቀርበውን መረጃ መሠረት በማድረግ የሚገነቡ የጋራ መኖሪያ ቤቶችን የስትራቴጂያዊና ዓመታዊ የፊሲካልና የፋይናንሻል ዕቅድ ያዘጋጃል፤ ከባለድረሻ አካላት ጋር ውይይት በማድረግ ያዳብራል፤ በሚመለከተው አካል አጸድቆ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፪.ለጋራ መኖሪያ ቤቶቹ ግንባታ የሚያስፈልገውን የለማ መሬት ለሚመለከተው አካል ጥያቄ ያቀርባል፤ ሲፈቀድ ይረከባል፤

፫.ለቤቶች ግንባታ የሚያስፈልገውን ዝርዝር የአካባቢ ልማት ፕላን እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤

፬የሚገነቡ ቤቶችን የታይፖሎጂ ዲዛይንና ዝርዝር ዲዛይን እንዲሁም ስፔስፊኬሽን እና የስራ ዝርዝር ይሰራል ወይም እንዲሰራ ያደርጋል፤ የተዘጋጁ ዲዛይኖችን ከግንባታ ሳይቶች ጋር የማጣጣም ስራ ይሰራል ወይም እንዲሰራ ያደርጋል፤

፭.የፕላን ስምምነትና የግንባታ ፈቃድ ለሚመለከተው አካል ጥያቄ በማቅረብ ያስፈጽማል፤ ይረከባል፤

፮.ኮርፖሬሽኑ ለቤቶቹ ልማት የሚያስፈልገውን ገንዘብ በከተማ አስተዳደሩ ዋስትና ከአበዳሪው ባንክ ይበደራል፤ በቤት ልማት ፕሮግራሙ ተጠቃሚ ለመሆን የተመዘገቡና በባንክ የሚቆጥቡ ነዋሪዎችን ቁጠባ ኮርፖሬሽኑ ለመጠቀም የብድር ወለድ ምጣኔውን በተመለከተ ከባንኩ ጋር ድርድር ያደርጋል፤

፯.ለጋራ መኖሪያ ቤቶች ግንባታ ከባንክ የተገኘው ብድር፣ ቤቶቹ ሲተላለፉ የተገኘው ገቢ፣ የተመለሰው የብድር መጠን እና ወለድ በአግባቡ ይመዘግባል ወቅታዊ የሂሳብ ሪፖርት ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፤

፰.ግንባታውን የሚያከናውኑ አማካሪዎችንና ስራ ተቋራጮችን አግባብ ባለው ህግ ይመዘግባል፤ ይመለምላል፤ ወደ ስራ ያሰማራል፤

፱.የቤቶች ልማትን ማካሄድ የሚያስችሉ ውሎችን ያዘጋጃል፤ ይዋዋላል፤ ውሉንም ያስተዳድራል፤

፲.ለግንባታና ግንባታው ከተጠናቀቀ በኋላ የሚያስፈልገውን መሠረተ-ልማት እንዲሟላ ለሚመለከተው አካል ጥያቄ ያቀርባል፤ መሟላቱንም ይከታተላል፤ ያረጋግጣል፤

፲፩.የጋራ መኖሪያ ቤቶች ግንባታ በተገባው ውል መሠረት፣ የጥራት ደረጃ፣ የጊዜና የዋጋ ገደብ ተጠብቆ መሠራቱን ለማረጋገጥ የሚያስችል የቁጥጥር ስርዓት ይዘረጋል፤ በበላይነትም ይቆጣጠራል፤ ግንባታቸው ሲጠናቀቅ ርክክብም ይፈጽማል፤

፲፪.የህንጻው ግንባታ ሲጠናቀቅ ኮርፖሬሽኑ ለመሰረተ ልማት ቅንጅት፣ ግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን እንዲሁም ለልሎች የሚመለከታቸው ተቋማት የመጠቀሚያ ፈቃድ እንዲሰጠው ጥያቄ ያቀርባል፤ ክትትል በማድረግም ፈቃዱን ይረከባል፤

፲፫.ግንባታቸው የተጠናቀቁና የመጠቀሚያ ፈቃድ ያገኙ የመኖሪያ ቤቶችን የማስተላለፊያ ዋጋ በማጥናት እንዲጸድቅ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፤

፲፬.ግንባታቸው ተጠናቆ የመጠቀሚያ ፈቃድ ያገኙ የመኖሪያ ቤቶችን በማስተላለፊያ ዋጋቸው መሠረት ለተጠቃሚዎች በእጣ ያስተላልፋል፤ የቤቶቹን አስፈላጊ ሰነዶች በሙሉ እጣው ለደረሳቸው ባለመብቶች በወቅቱ ያስረክባል፤

፲፭.በሚገነቡ የጋራ ህንጻዎች ለንግድ አገልግሎት የሚውሉትን ቤቶች በጨረታ ይሸጣል፤

፲፮.በኮርፖሬሽኑ ለሚከናውኑ ግንባታዎች እና በገበያው ተፈላጊ የሆኑ የግንባታ ግብዓቶችን በማምረት በሽያጭ ያቀርባል፤ አዳዲስ የግንባታ ግብዓት ማምረቻ ተቋማትን ያስፋፋል፤

፲፯.የሚያስገነባቸው ቤቶች ወጪ ቆጣቢና ጥራታቸው የተጠበቁ እንዲሆኑ ያደርጋል፤ ከልሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ ይሰራል፤

፲፰.ከአበዳሪው ባንክ እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ወቅታዊና መሠረታዊ የመረጃ ልውውጥ ለማድረግ የሚያስችል ስርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊም ያደርጋል፤

፲፱.በውሉ መሰረት ባልተፈጸሙ፣ በሚታዩ ጉድለቶችንና ጥፋቶች ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፤ እንዲወሰድ ያደርጋል፡፡

፳፯.<u>ስለኮተቤ ሜትሮፖሊታን ዩኒቨርስቲ</u>

በዚህ አዋጅ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የኮተቤ ሜትሮፓሊታን ዩንቨርሲቲ በተቋቋመበት ሕግ በተሰጠው ሥልጣንና ተግባር መሰረት ስራውን ይቀጥላል፡፡

፳፰. <u>መለስ ዜናዊ የስራ አመራር ኢንስቲትዩት</u>

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩.የከተማ አስተዳደሩን የስልጠና ፍላጎት መሰረት በማድረግ ሰው ሀብት በብቃት ማፍራት የሚያስችል የአጭርና የመካከለኛ ጊዜ ስልጠናዎችን ይሰጣል፤

፪.የስልጠና መርሀ ግብር ይቀርፃል፤ ሞጁሎች ያዘጋጃል፤ ሲፀድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፫.የአመራሩንና የባለሙያውን የማስፈፀም አቅም ለመገንባት የሚረዱ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን ይሰራል፤ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፬.ከመንግስታዊ መስሪያ ቤቶች ወይም የግል ድርጅቶች በሚቀርብለት ጥያቄ መሰረት ለአመራርና ባለሙያ የሥልጠና፣ የምክርና የማህበረሰብ አገልግሎት ይሰጣል፤

፭.ሥልጠና ጨርሰው በስራ የተሰማሩ አካላትን የስልጠና ዉጤታማነት ጥናት ያካሂዳል፤ ከጥናቱ በመነሳት የተሻሉ የአሰራር ስልቶችን ይቀይሳል፤

፮.የተለያዩ ሴሚናሮችን፣ ወርክ ሾፖችን፣ ኮንፈረንሶችንና አውደ ጥናቶችን ያዘጋጃል፤ ያካሂዳል፤ በልሎች ተመሳሳይ ፕሮግራሞች ላይ ይሳተፋል፤

፯.ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ስልጠናውን ላጠናቀቁ ሰርተፍኬት ይሰጣል፤

፰.የሥራ አመራር ሥልጠና፣ የምክር አገልገሎትና የጥናት ፕሮጀክቶችን በማዘጋጀት ገቢ የሚያገኝባቸዉን ሁኔታዎች ያመቻቻል፡፡

፳፱.<u>የጉለሌ የዕፅዋት ማዕከል</u>

በዚህ አዋጅ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የጉለሌ የዕፅዋት ማዕከል በተቋቋመበት ሕግ በተሰጠው ሥልጣንና ተግባር መሰረት ስራውን ይቀጥላል፡፡

፴.<u>የአዲስ ዙ ፓርክ</u>

ፓርኩ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩.በዱር እንስሳት አረባብ፣ ጥበቃ፣ ጤና፣ አመጋገብ፣ አኗኗር እንዲሁም ተያያዥ በሆኑ ሥነ-ሕይወታዊና ሥነ-አካላዊ ጉዳዮች ላይ የጥናትና የምርምር ሥራዎችን ያካሄዳል፤

፪.ለማዕከሉ በተከለለ ቦታ ላይ በዙ-ማስተር ፕላን መሠረት የመሬት አጠባበቅና ዲዛይን ስራዎችን ያከናውናል፤

፫.የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎችን ያለማል፣ ያስተዳድራል፣ ህገወጥ ተግባራት እንዳይፈፀሙባቸው ይከላከላል፤

፬.ለነዋሪዎች የመዝናኛ አገልግሎት ይሰጣል፤

፭.ጎብኚዎችን በመሳብ የቱሪዝም ኢኮኖሚ እንዲጠናከር ያደርጋል፤

፮.ውበትና ጥምር ጥቅም ያላቸው ዕፅዋትን ይመርጣል፣ ያራባል፣ ያስፋፋል፣ ይንከባከባል፣ ለመሰል ፓርኮችም ተሞክሮውን ያካፍላል፤

፯.በዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ የቴክኒክ እርዳታና ሌላም ድጋፍ ሊሰጡ ከሚችሉ አካላት ጋር ግንኙነት ይመሰርታል፤

፰.በማዕከሉ የሚፈጠረዉን የእንስሳት ፍግና የዕፅዋት ተረፈ ምርቶችን ወደ ተፈጥሮ ማዳበሪያና ቀልዝ በመለወጥ ጥቅም ላይ እንዲዉል ያደርጋል፤

፱.የማዕከሉን የአጭር፣ መካከለኛና የረዥም ጊዜ የልማት ፕሮጀክቶችንና የድርጊት መርሐ ግብሮችን በመቅረፅ ሲፀድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፲.ተግባራቱ ከአካባቢዉ ሥነ ምህዳር የሚስማሙ፣ የአገራችንን ሥነ ምህዳር የሚወክሉና ከአካባቢ ጥበቃ ዓላማዎች ጋር እንዲስማሙ አድርጎ ይፈጽማል፡፡

፴፩.<u>ስለከተማው አስተዳደር የልማት ድርጅቶች</u>

፩.በዚህ አዋጅ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት የከተማው አስተዳደር የልማት ድርጅቶች በተቋቋሙበት ህግ መሰረት ስራቸውን ይቀጥላሉ፡-

ሀ. ቄራዎች ድርጅት፤

ለ. አንበሳ የከተማ አውቶቡስ አገልግሎት ድርጅት፤

ሐ. ሸገር የብዙሀን ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት፤

መ. የኢግዝቢሽን ማእከልና የገበያ ልማት ድርጅት፤

ሠ. አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ክላስተር ልማት ኮርፖሬሽን፤

ረ. የሲኒማ ቤቶች አስተዳደር፤

ሰ. ከነማ ፋርማሲዎች ድርጅት፡፡

፪.የግንባታ ኢንተርፕራይዝ በዚህ አዋጅ መሰረት በልማት ድርጅትነት ይቋቋማል፡፡

፫.በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሱት የልማት ድርጅቶች ስምና አደረጃጀት ካቢኔው በሚያወጣው ደንብ ሊሻሻል ወይም ሊቀየር ይችላል፡፡

፴፪.ስለከተማው አስተዳደር ጤና ተቋማት፣ ኮሌጆችና ማዕከላት

በዚህ አዋጅ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር የሚተዳደሩ የጤና ተቋማት፣ ቴክኒክና ሙያ ኮሌጆችና ማዕከላት በየራሳቸው ህጎች መሰረት ስራቸውን ይቀጥላሉ፡፡

፴፫.ስለ አዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን

፩.አግባብ ባለው ህግ ፖሊስ ኮሚሽኑ ተጠሪነት ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሲዛወር የሰላምና ፀጥታ አስተዳደር ቢሮ ኮሚሽኑን በበላይነት ይመራል፤ ይቆጣጠራል፤

፪.በዚህ አንቀጽ ንዑስ (፩) የተደነገገው እስከሚፈፀም የሰላምና ፀጥታ አስተዳደር ቢሮ ከኮሚሽኑ ጋር በመተባበርና በመቀናጀት ይሰራል፡፡

## ክፍል አምስት

## የክፍለ ከተማ መቋቋምና ልሎች የአደረጃጀት ሁኔታዎች

### ምዕራፍ አንድ

### የክፍለ ከተማ መቋቋምና አደረጃጀት

፴፬. የክፍለ ከተማ የአከላለል መሠረት

የክፍለ ከተማ አከላለል የቆዳ ስፋትን፣ መልክዓ-ምድራዊ አቀማመጥን፣ የነዋሪ ብዛትን፣ የልዩ ልዩ አገልግሎት ተደራሽነትትና የሀብት ስርጭትንና የአስተዳደር አመችነትን መሠረት ያደረገ ነው፡፡

፴፭.ስለ ክፍለ ከተማ መቋቋም

በከተማው ውስጥ ቀጥሎ የተዘረዘሩት አሥር ክፍለ ከተማ ሕጋዊ ሰውነት ኖሮአቸው እንደገና ተቋቁመዋል፡-

፩.አራዳ ክፍለ ከተማ፤

፪.አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ፤

፫.ልደታ ክፍለ ከተማ፤

፬.ቂርቆስ ክፍለ ከተማ፤

፭.የካ ክፍለ ከተማ፤

፮.ቦሌ ክፍለ ከተማ፤

፯.አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ፣

፰.ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ፣

፱.ኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ፣

፲ጉለሌ ክፍለ ከተማ፡፡

፴፮.<u>የክፍለ ከተማ ወሰን</u>

የክፍለ ከተማ ወሰን በአዲስ አበባ ከተማ የአከላለል ካርታ ላይ ተለይቶ በተገለፀው መሠረት የተወሰነው ይሆናል፡

፴፯.<u>የክፍለ ከተማ አስተዳደር ተጠሪነት</u>

የክፍለ ከተማ ተጠሪነት ለነዋሪውና ለከተማው አስተዳደር ይሆናል፡፡

<u>ምዕራፍ ሁለት</u>

<u>የክፍለ ከተማ የሥልጣን አካላት ሥልጣን፣ ተግባር እና ተጠሪነት</u>

፴፰.<u>የክፍለ ከተማ አስፈጻሚ አካላት ሥልጣንና ተግባራት</u>

ክፍለ ከተማው ከከተማው አግባብ ያለው አስፈጻሚ አካል ሥልጣንና ተግባር አኳያ በተዋረድ በተደራጀ ወይም በሚደራጅ አስፈጻሚ አካል የሥራ መስክ ተከፋፍሎ የሚከናወኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩.የክፍለ ከተማውን አጠቃላይ ዕቅዶች፣ መርሐ-ግብሮችና ፕሮጀክቶች ያዘጋጃል፣ በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

፪.ፖሊሲ፣ ሕግ፣ ደረጃና የአስተዳደሩ የበላይ አካላት ውሣኔዎች በክፍለ ከተማው ተግባራዊ መሆናቸውንና የክፍለ ከተማው ሰላምና ፀጥታ መጠበቁን ያረጋግጣል፣

፫.የተፈቀደለትን በጀት ይደለድላል፣ በሥራ ላይ ያውላል፣ አፈጻጸሙ በከተማው አስተዳደር የፋይናንስ አስተዳደር ሕግ መሠረት መሆኑን ይከታተላል፣ አግባብ ባለው ህግ ግብር፣ ቀረጥና የአገልግሎት ክፍያ ይሰበስባል፣ የክፍለ ከተማው ገቢ የሚያድግበትን ሁኔታ ያጠናል፣ ሲፈቀድ ተግባራዊ ያደርጋል፣

፬.የክፍለ ከተማው አስፈጻሚ አካላት ሥራን ይመራል፣ ያስተባብራል፣ የአገልግሎት አሰጣጥ እንዲሻሻል ያደርጋል፣

፭.የክፍለ ከተማውን የመንግሥት ሠራተኞች አግባብ ባለው ሕግ ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ያሰናብታል፣

፮.በክፍለ ከተማው ውስጥ የሕዝብን ተሳትፎ ያሳድጋል፣ የብዙሃን ማህበራትን አቅም ይገነባል፣

፯.አነስተኛ ነጋዴዎችን፣ የዕደ ጥበብ ባለሙያዎችን እና ልሎች አካላት በማህበር እንዲደራጁ ድጋፍ ይሰጣል፣ አሠራራቸውንም ይቆጣጠራል፣

፰.የትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ፓኬጅ ይተገብራል፡ የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት እንዲሰጥ ያደርጋል፣ ያስተባብራል፣ ተገቢውን ክትትል ያደርጋል፣

፱.የመንግስትና የግል የትምህርት ቤቶችን እና የቴክኒክና የሙ.ያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማትን በበላይነት ይመራል፤ ይቆጣጠራል፤

፲.በክፍለ ከተማው የመንግሥት ፖሊሲና ሕጐች እንዲሁም የአስተዳደሩ የሥራ እንቅስቃሴ እንዲተዋወቁ ያደርጋል፤

፲፩.ታሪካዊ ቅርሶችን ይጠብቃል፤ ባህል፣ ኪነ-ጥበብና ሥነ-ጥበብ እንዲበለጽጉ ያደርጋል፤

፲፪.የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎችን ያስተዳድራል፤ ስፖርት እንዲስፋፋ ያደርጋል፤ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ያስፋፋል፤ ወጣቶች ተገቢውን ሥልጠና እንዲያገኙ ያደርጋል፤

፲፫.በልማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የሴቶችና የወጣቶ ተሳታፊነትና ተጠቃሚነትን ያረጋግጣል፤

፲፬.የአካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን፣ የማህበራዊ ችግሮች ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች እና በደማቸው ውስጥ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ያለባቸው ሰዎች በኃላፊነቱ ክልል የእኩል እድል ተጠቃሚና ሙሉ ተሳታፊ የሚሆኑበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

፲፭.ጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጅ ተግባራዊ ያደርጋል፤ የበሽታ መከላከልና ቁጥጥር ተግባራትን ያከናውናል፤ በክፍለ ከተማው የሚገኙ የአስተዳደሩን ጤና ጣቢያዎችንና ክሊኒኮችን ያስተዳድራል፣ የግል ክሊኒኮችን ይቆጣጠራል፤

፲፮.ኤች.አይ.ቪ. ኤድስን ለመከላከል የሚንቀሳቀሱ ተቋማትን ያስተባብራል፣ ድጋፍ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፤

፲፯.የመሠረተ ልማት አገልግሎቶች ለነዋሪው እንዲዳረሱ ያደርጋል፤ ያስተዳድራል፤ ተገቢውን ጥበቃና ቁጥጥር ያደርጋል፤ የመንገድ ግንባታና ጥገና ሥራዎች እንዲካሄድ ያደርጋል፤ የትራፊክ ደህንነትን ያስጠብቃል፤

፲፰.ሕገወጥ ግንባታዎችን ይከላከላል፤ ያስወግዳል፤ በክፍለ ከተማው ባለቤትነት ሥር ያሉ ቤቶችን ያስተዳድራል፤ ይቆጣጠራል፤

፲፱. ሕገ ወጥ ተግባራትን ይከላከላል፤ ይቆጣጠራል፤ እርምጃ ይወስዳል፤ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

፳.የክፍለ ከተማው ነዋሪዎች የስራ ዕድል መፍጠር እንዲችሉ ስልጠናዎች ይሰጣል፤ ተሞክሮዎችን በመለየትና በመቀመር ዕውቀትና ክህሎት እንዲቀስሙ ያደርጋል፤ ያበረታታል፤ የንግድ ስራ ክህሎት የምክር አገልግሎት ይሰጣል፤ የስራ ዕድል እንዲፈጠር ያመቻቻል፤

፳፩. የአካባቢ ጥበቃ ሕጎችን መሠረት በማድረግ የማምረቻና የአገልግሎት መስጫ ተቋማት እና ሌሎች አካባቢ ላይ ተፅእኖ የሚያሳድሩ አካላትን ይቆጣጠራል፤ የአካባቢ ንጽህ እና ውበት እንዲጠበቅ ያደርጋል፤

፳፪.የይዞታ አስተዳደርን በተመለከተ፡-

ሀ) በከተማው መዋቅራዊ ኘላንና በአካባቢ ልማት ኘላን ሕጐች መሠረት የቦታ ይዞታ እና/ወይም የቤት ባለቤትነት ማስረጃ ካርታ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤ በቋሚ ንብረት መዝገብ በመመዝገብ ለባለይዞታው ወይም ለቤት ባለንብረቱ ይሰጣል፤ ከሕግ ውጪ

የተሰጠ የቦታ ይዞታ ወይም የቤት ባለቤትነት ማስረጃ አግባብ ባለው ሕግ መሰረት ያግዳል፣ እንደአስፈላጊነቱ ይሰርዛል፤

ለ) የቦታ ይዞታ ወይም የቤት ባለቤትነት ስም ዝውውር አግባብ ባለው ሕግ መሠረት እንዲፈፀም ያደርጋል፤

ሐ) የቦታ ይዞታ ወይም የቤት ባለቤትነት መያዣ ዋስትና፣ እንዲሁም የፍርድ ቤት ወይም ሥልጣን ባለው አካል የተሰጠ ዕግድ ትዕዛዝ መመዝገብና ዋስትናው ወይም የዕግድ ትዕዛዙ ሳይነሳ ወይም ጊዜው ሳያበቃ የስም ዝውውር እንዳይፈፀም ያደርጋል፤

መ) በባንክ በዋስትና የተያዘ ይዞታን ወይም የማይንቀሳቀስ ንብረትን በሚመለከት በባንክ በመያዣ ስለተያዘ ንብረት በወጣው አዋጅ ቁጥር (፺፯/፲፱፺፯)( (እንደተሻሻለ) መሠረት ሬጅስትራር ሆኖ ይሠራል፤

ሠ) በባለይዞታዎች መካከል የወሰን ክርክሮች ሲከሰቱ በፕላኑ መሠረት አስተዳደራዊ ውሣኔ በመስጠት ይፈጽማል፤

ረ) የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈል ለጠያቂዎች የቦታ ይዞታና/ወይም የቤት ባለንብረትነትን በተመለከተ የመረጃ አገልግሎት ይሰጣል፤

ሰ) በቦታ ይዞታው እና/ወይም በቤት ባለቤትነት መረጃ ላይ የተደረጉ ለውጦች ሕጋዊ መሆናቸውንና በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል ፀድቀው የተፈፀሙ መሆናቸውን በየወቅቱ ያረጋግጣል፤

ሸ) የቦታ ይዞታ እና/ወይም የቤት ባለቤትነት አስተዳደር ሥራዎች አግባብ ባለው ህግ እንዲከናወኑ ያደርጋል፤

ቀ) የቦታ ይዞታ እና/ወይም የቤት ባለቤትነት ማህደሮችን ማደራጀት፣ መጠበቅና ለከተማው ይዞታ አስተዳደር ጽህፈት ቤት የአዳዲስ ይዞታ ማኅደራት ሠነዶች ግልባጮችን በወቅቱ ያስተላልፋል፤

በ) የሕንፃ ግብርና የቦታ ኪራይ ማስከፈያ ቅጽ በማዘጋጀት ለየወረዳው ያስተላልፋል፣ ይከታተላል፤

ተ) በካዳስተር መረጃ የተመዘገበ ቦታና ቤት ይለካል፤ የአዲሱን ልኬት መረጃ ወደ ኮምፒውተር ያስገባል፤ የቦታ ቤዝ ማኘ ያደራጃል፤ ይመዘግባል፡፡

<u>፳፫.በክፍለ ከተማው የሚገኙ ቦታዎችን የሚያስተዳድር ሆኖ፤</u>

፩) የመሬት ልማትን በተመለከተ፡-

ሀ) የከተማውን መዋቅራዊ ኘላን መሠረት በማድረግ የአካባቢ ልማት ኘላን ያጠናል፤ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤ የመሬት ልማት ሥራ ያከናውናል፤ እንደአስፈላጊነቱ የመሬት ልማት ሥራዎችን ከሚያከናውኑ መንግሥታዊ ወይም የግል ድርጅቶች ጋር አግባብ ባለው ህግ ይዋዋላል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

ለ) የአካባቢ ልማት ፕላኖችን ከተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ የክፍለ ከተማው መሬት የሚለማበትን ዝርዝር የአፈጻጸም ስትራቴጂ ይነድፋል፤ ሲጸድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፤

ሐ) በከተማው አስተዳደር ለሚቀርቡ የቦታ ጥያቄዎች አግባብ ባለው ሕግ ቦታ ማስለቀቅና እንደየሥልጣኑ አግባብ በከተማው ማዕከል ወይም በክፍለ ከተማው በሚወሰነው መሠረት ምትክ ቦታ ይሰጣል፤ ካሣ እና ልሎች ክፍያዎችን ይፈፅማል፣ ምትክ ቤት ይሰጣል፤

መ) የካሣ ክፍያ በተከፈለባቸውና በተለቀቁ ወይም በክፍት አካባቢዎች ላይ የቅየሳና የፕላን አፈጻጸም ሥራዎች ያከናውናል፤ ቦታዎቹን ለልማት ዝግጁ ያደርጋል፤ የአፈጻጸም ሪፖርትና ለመሬት ዝግጅት የሚያስፈልግ በጀትና ሪፖርት አዘጋጅቶ ያቀርባል፣ ሲጸድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፤

ሠ) መረጃ በመሰብሰብ በልማት ምክንያት ለሚነሱ ቤቶች የካሣ ክፍያ ሠነድ አዘጋጅቶ ያቀርባል፤ ሥልጣን ባለው አካል በሚወሰነው መሠረት ካሣ ክፍያ የተፈፀመባቸውን ንብረቶች እንዲነሱ ያደርጋል፤

ረ) ምትክ ቦታ፣ በምትክ መኖሪያ ቤት እና/ወይም በጥሬ ገንዘብ ለሚከፈል ካሣ የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ይሰበስባል፤ ያጠናቅራል፤ ተንትኖም ያቀርባል፤ ሲወሰንም ተግባራዊ ያደረጋል፤

ሰ) ምትክ ቦታ ለሚገባቸው ተነሺዎች ምትክ ቦታ ማዘጋጀትና የይዞታ ማስረጃ/ካርታ በማዘጋጀት ያስረክባል፤

ሸ) ምትክ የመኖሪያ ቤት ለሚገባቸው ተነሺዎች ቤት በማዘጋጀት ያስረክባል፡፡

፪. የሊዝ አፈጻጸምን በተመለከተ፡-

ሀ) በከተማው ካቢኔ በሚወሰነው መሠረት ለማናቸውም ግንባታ የሚውል ቦታ አግባብ ባለው ህግ ያስተላልፋል፤ ውል ይዋዋላል፤ ቦታውን ያስረክባል፤

ለ) በተፈረመው የሊዝ ውልና በተፈቀደው የግንባታ ፕላን መሠረት ግንባታ መከናወኑን ያረጋግጣል፤ አግባብ ባለው ሕግና በውሉ በተወሰነው ጊዜና ሁኔታ ግንባታ ካልተጀመረ ወይም ካልተጠናቀቀ በቦታ ሊዝ ሕግ መሠረት ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፤

ሐ) በተፈረመው የሊዝ ውል መሠረት ክፍያ በአግባቡና በወቅቱ መፈፀሙን ያረጋግጣል፤

መ) በሊዝ ለልማት የሚመደቡ ቦታዎችን በተመለከተ የአፈጻጸም ሪፖርት ያቀርባል፤

ሠ) በክፍለ ከተማው የሚገኙ ወረዳዎችን በበላይነት ይመራል፤ ያስተባብራል፤ የማስፈጸም አቅም ይገነባል፡፡

፸፱.<u>የክፍለ ከተማ የሥልጣን አካላት</u>

፩.እያንዳንዱ ክፍለ ከተማ የሚከተሉት የሥልጣን አካላት ይኖሩታል፡-

ሀ. የክፍለ ከተማ ዋና ሥራ አስፈጻሚና ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚ፤

ለ. የክፍለ ከተማ ቋሚ ኮሚቴ፡፡

፪.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ሥር የተዘረዘሩት አካላት በዚህ አዋጅ የተሰጡት ስልጣንና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆኖ በቻርተሩ አንቀጽ ፴፬ እስከ ፴፮የተመለከቱትን ስልጣንና ተግባራት ያከናውናሉ፡፡

## ምዕራፍ ሦስት

## ስለ ክፍለ ከተማ ቋሚ ኮሚቴ አባላት፣ ስለ ልሎች አስፈጻሚ አካላት

### ፹.የክፍለ ከተማ ቋሚ ኮሚቴ አባላት

፩.የሚከተሉት የክፍለ ከተማ ቋሚ ኮሚቴ አባላት ይሆናሉ፤

ሀ. የክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈጻሚና ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚ፤

ለ. በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፩ ከተራ ቁጥር ፪ እስከ ፲፯ የተቋቋሙት አስፈፃሚ አካላት በክፍለ ከተማ ደረጃ ከተደራጁ የአስፈጻሚ አካላት ኃላፊዎች፤

ሐ. ዋና ሥራ አስፈጻሚው እንደአስፈላጊነቱ በአባልነት እንዲሳተፉ የሚመርጣቸው የክፍለ ከተማው ልሎች ኃላፊዎች፡፡

፪.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ ፩ (ለ) ሥር የተጠቀሰው አስፈጻሚ አካል ኃላፊ በቋሚ ኮሚቴ ስብሰባ ላይ ሊገኝ በማይችልበት ጊዜ በግልጽ ተለይቶ ውክልና የተሰጠው ኃላፊ በተተኪ አባልነት በቋሚ ኮሚቴ ስብሰባ ላይ ይሳተፋል፡፡

### ፹፩.የክፍለ ከተማ አስፈጻሚ አካላት

፩.በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፫ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለዋና ሥራ አስፈጻሚው ተጠሪ የሆኑና የክፍለ ከተማው ቋሚ ኮሚቴ አባላት የሚሆኑ ጽህፈት ቤቶች ባልተማከለ መርህ መዋቅራዊ የሥራ ክፍፍል በሚወሰነው መሠረት የአስፈጻሚ አካላት ተዋረዳዊ አደረጃጀት አካል ሆነው ይደራጃሉ፡፡

፪.በዚህ አዋጅ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት ለማስፈጸም በጸደቀ መዋቅራዊ አደረጃጀት ተዋረዳዊ ኃላፊነት ይኖሩታል፡-

ሀ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚደራጅ እያንዳንዱ ጽህፈት ቤት እንደአግባቡ ለክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ተጠሪ ይሆናል፤

ለ) የእቅድና በጀት ዝግጅት፣ የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ፣ የሠራተኞች ውስጥ ዝውውርና የደረጃ ዕድገትን ጨምሮ ልሎች ሙያዊና ቴክኒካዊ ጉዳዮችን በሥራው መስክ ለሚመለከተው ቢሮ ተጠሪ መሆኑን እንደተጠበቀ ሆኖ የከተማው ማዕከል ተከትሎ በሥሩ የሚደራጁትን ልሎች ጽህፈት ቤቶች፣ ዳይሬክቶሬቶች ወይም የሥራ ክፍሎች በበላይነት ይመራል፤ ያስተባብራል፤

ሐ) እያንዳንዱ ጽሕፈት ቤት ወይም በክፍለ ከተማው ደረጃ የሚቋቋም የአስፈጻሚ አካል ኃላፊ፣ የሥራ ክፍሎችና ሠራተኞች ይኖሩታል፤

መ) የክፍለ ከተማ ጽሕፈት ቤቶች ከሚያስተባብሯቸው አስፈጻሚ አካላት ድጋፍ ሰጪ አገልግሎቶችን በጋራ ሊጠቀሙ ይችላሉ፤ ዝርዝሩ ካቢኔው በሚያፀድቀው መዋቅራዊ አደረጃጀት መሠረት በከንቲባው በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፤

ሠ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እስከ (፪) እና በሕግ በሌላ ሁኔታ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክፍለ ከተማ ዋና ሥራ አስፈጻሚ፣ ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚ እና የአስፈፃሚ አካላት ኃላፊዎች የሥራ ሁኔታ ካቢኔው በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡

ረ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፹፪ ንኡስ አንቀጽ ፩መሰረት የተደራጁ የክፍለ ከተማ አስፈጻሚ ተቋማት የራሳቸውን በጀት ጥያቄ አዘጋጅተው ለዋና ስራ አስፈጻሚ ያቀርባሉ፤ ሲፈቀድላቸው በህግ አግባብ ስራ ላይ ያውላሉ፤ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋሉ፡፡

፹፪·የክፍለ ከተማ ሥራ አስኪያጅ

የክፍለ ከተማ ሥራ አስኪያጅ፡-

፩·ከከተማው ሥራ አስኪያጅ ጋር በመመካከር የክፍለ ከተማውን ሥራ አስኪያጅ ጽህፈት ቤት ያደራጃል፤ በበላይነት ያስተዳድራል፤

፪·ተጠሪ የሆኑለትን የክፍለ ከተማ አስፈፃሚ አካላት ዕቅድና በጀት ከከተማው ሥራ አስኪያጅ ጋር በመመካከር በማዘጋጀት ለክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ያቀርባል፤ ሲፀድቅም ተግባራዊ መሆኑን ያረጋግጣል፤ የሥራ አፈጻጸም ሪፖርቱን አዘጋጅቶ ለከተማው ሥራ አስኪያጅና ለክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ያቀርባል፡፡

## ክፍል ስድስት

## ምዕራፍ አንድ

## የወረዳ መቋቋም፣ ተጠሪነት እና ስልጣንና ተግባር

፹፫·ስለወረዳ መቋቋም

፩·የከተማው አስተዳደር የክፍለ ከተማ አካል የሆኑ ወረዳዎች በዚህ አዋጅ እንደገና ተቋቁመዋል፡፡ ዝርዝራቸውም ከዚህ አዋጅ ጋር ተሻሽሎ በተያያዘው አባሪ የተመለከተው ይሆናል፡፡ በአባሪው የተመለከቱት ወረዳዎች መለያ ስም እንደአስፈላጊነቱ ሊሻሻል ይችላል፡፡

፪·በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም የወረዳ አስተዳደሮች ቁጥር እንደ አስፈላጊነቱ ሊቀንስ ወይም ሊጨምር ይችላል፡፡

፫·የወረዳዎች አስተዳደር አከላለል በከተማው የአከላለል ካርታ ላይ ተለይቶ በተገለፀው መሠረት ይሆናል፡፡

፹፬·የወረዳ ተጠሪነት

እያንዳንዱ ወረዳ ተጠሪነቱ ነዋሪውና ወረዳው ለሚገኝበት ክፍለ ከተማ ይሆናል፡፡

፹፭·የወረዳ ሥልጣንና ተግባር

ወረዳው ከክፍለ ከተማው አግባብ ያለው አስፈጻሚ አካል ሥልጣንና ተግባር አኳያ በተዋረድ በተደራጀ ወይም በሚደራጅ አስፈጻሚ አካል የሥራ መስክ ተከፋፍሎ የሚከናወኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩.የወረዳውን በጀትና ዕቅድ በማዘጋጀት ለክፍለ ከተማው አስተዳደር ያቀርባል፤ የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮችን ግብር ይሰበስባል፤ አግባብ ባለው ህግ የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት ክፍያዎች ይሰበስባል፤

፪.ወረዳዎች የልማትና የአገልግሎት መስጫ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፤

፫.የህብረተሰቡን ቀጥተኛ ተሳትፎ በማጠናከር በልማት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

፬.በወረዳ ደረጃ የሚሰጡ አገልግሎቶች ግልጽ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

፭..የአካባቢው የልማት ሥራዎች የከተማውን ፕላን፤ የግንባታ ሕጎችንና ደረጃዎችን ጠብቀው መሠራታቸውን እንዲሁም ሕገ ወጥ ግንባታዎችን ይቆጣጠራል፤

፮.ነዋሪውን በኮሚኒቲ ፖሊሲንግ እንዲሳተፉ ያደርጋል፤ ሕገ ወጥ ድርጊቶች እንዳይካሄዱ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤ ፀጥታ ሥራዎችን ይከታተላል፤

፯.ነዋሪው የአካባቢውን ጽዳት እንዲጠብቅና እንዲያስውብ ያስተባብራል፤ ይቆጣጠራል፤

፰.የነዋሪዎችን ተሳትፎ ለማጐልበት የተለያዩ ብዙሃን ማኀበራትና ማኀበራዊ ተቋማት እንዲደራጁ ድጋፍ ይሰጣል፤ ያስተባብራል፤

፱.በስራ ዕድል ፈጠራና በዕደ-ጥበብ ሥራ ላይ የተሰማሩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን በማኀበር እንዲደራጁ ያበረታታል፣ ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል፤

፲.ጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ለማስወገድ፣ ኤች አይ ቪ ኤድስን ለመከላከል፣ የበሽታ መከላከልና የመሠረተ ጤና ትምህርትንና ልሎች ተዛማጅ ጉዳዮችን በተመለከተ ለነዋሪው ኀብረተሰብ የትምህርትና ቅስቀሳ ተግባራትን ያከናውናል፤ ይከታተላል፤ የጤና ጣቢያዎችን ያስተዳድራል፤

፲፩.አፀደ ሕፃናትንና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ መሠረተ-ትምህርት እንዲስፋፋ ያደርጋል፤

፲፪.ክፍት ቦታዎችና የመሬት ይዞታ ሁኔታ የተሟላ መረጃ ይይዛል፤ በከተማው አስተዳደር ባለቤትነት ሥር ያሉ ቤቶች በቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ በሚቀርበው ሠነድ መሠረት ያስተዳድራል፤

፲፫.በይዞታነት ለማንም አካል ያልተላለፉ የተዘጋጁና ያልተዘጋጁ ቦታዎችን ይጠብቃል፤ ህገወጥነት ተፈፅሞ ሲገኝም ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፤ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

፲፬.የከተማ ማደስ ስራዎች በሚሰሩበት ወቅት የወረዳው አስፈጻሚ አካላት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር አስፈላጊውን ሁሉ ይፈጽማሉ፤

፲፭.ፓርኮችንና መዝናኛ ሥፍራዎችን ይጠብቃል፤ ይቆጣጠራል፤

፲፮.የወረዳውን የተደራጀ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ መረጃ ይይዛል፤ ለሚመለከተው አካል ሲጠየቅ ያቀርባል፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## የወረዳ አስፈጻሚ አካላት

## ሥልጣንና ተግባር

**፹፮.የወረዳ አስፈጻሚ አካላት የወል ሥልጣንና ተግባራት**

እያንዳንዱ ወረዳ ዋና ሥራ አስፈጻሚና ቋሚ ኮሚቴ ይኖሩታል፡-

፹፯.ስለወረዳ ዋና ሥራ አስፈጻሚ

፩.የወረዳው ዋና ሥራ አስፈፃሚ ከወረዳ ምክር ቤት አባላት ውስጥ ይመረጣል፤ የሥራ ዘመኑም የምክር ቤቱ የስራ ዘመን ይሆናል፤ ሆኖም በራሱ ፈቃድ ሲለቅ ወይም በምክር ቤቱ ከኃላፊነት ሲታገድ የስራ ዘመኑ ሳያልቅ ከኃላፊነት ሊሰናበት ይችላል፡፡

፪.የወረዳው ዋና ሥራ አስፈፃሚ ተጠሪነቱ ለወረዳው ምክር ቤትና ለክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሆኖ ወረዳውን ይመራል፤

፫.የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ሥራ አስፈጻሚው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ. የቋሚ ኮሚቴ አባላትን ከምክር ቤት አባላት ወይም የምክር ቤት አባላት ካልሆኑት መካከል መርጦ ለወረዳው ምክር ቤት በማቅረብ ሹመታቸውን ያፀድቃል፤

ለ. የወረዳው ዓመታዊ ዕቅድና የበጀት ድልድል ሃሳብ በወረዳው ቋሚ ኮሚቴ ከተመከረበት በኋላ ለወረዳው ምክር ቤት ያቀርባል፣ የወረዳውን የገቢ ማሰባሰብ በበላይነት ይመራል፤

ሐ. የወረዳውን ቋሚ ኮሚቴ ይሰበስባል፤

መ. በወረዳው ሕግና ሥርዓትን ያስከብራል፤ የወረዳውን የፀጥታ ሥራዎችን በበላይነት ይመራል፤ ከወረዳው አቅም በላይ የሆነ የፀጥታ ችግር ሲያጋጥም ለክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ያሳውቃል፤

ሠ. የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት በወረዳው ቋሚ ኮሚቴ እንዲገመገም ያደርጋል፤ ውጤቱን ለወረዳው ምክር ቤት  እና ለክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሪፖርት ያደርጋል፤

ረ. በብሔራዊና በሕዝብ በዓላት ሥነ-ሥርዓቶች ላይ እንደአስፈላጊነቱ ወረዳውን ይወክላል፤

ሰ. ዓመታዊና ወቅታዊ ሪፖርት ለክፍለ ከተማው ሥራ አስፈጻሚና ለወረዳው ምክር ቤት ያቀርባል፤

ሸ. በወረዳው ምክር ቤትና በክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈጻሚ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

፹፰.ስለወረዳ ምክትል ዋና ስራ አስፈፃሚ

፩.የወረዳ ምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚ ከወረዳ ምክር ቤት አባላት ወይም ከምክር ቤት አባላት ውጪ ሊመረጥ ይችላል፡፡

፪.የወረዳ ምክትል ዋና ስራ አስፈፃሚ የስራ ዘመን የምክር ቤቱ የስራ ዘመን ይሆናል፤ ሆኖም በራሱ ፈቃድ ሲለቅ ወይም በምክር ቤቱ ከኃላፊነት ሲታገድ የስራ ዘመኑ ሳያልቅ ከኃላፊነት ሊሰናበት ይችላል፡፡

፹፱·<u>ስለወረዳ ምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚ ሥልጣንና ተግባር</u>

፩·ከወረዳው ዋና ሥራ አስፈፃሚ የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

፪·የወረዳው ዋና ስራ አስፈፃሚ በማይኖርበት ወቅት ተክቶት ይሰራል፡፡

፺·<u>ስለወረዳ ቋሚ ኮሚቴ አባላት</u>

፩· የወረዳ ቋሚ ኮሚቴ ተጠሪነት ለወረዳው ዋና ሥራ አስፈጻሚ እና በጋራ ለሚወስነው ውሣኔ ለወረዳው ምክር ቤት ሆኖ የወረዳ ቋሚ ኮሚቴ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፣

ሀ) የወረዳው ዋና ሥራ አስፈጻሚና ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚ፤

ለ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፩ ከተራ ቁጥር ፪ እስከ ፲፯ የተቋቋሙት የአስፈፃሚ አካላት በወረዳ ደረጃ የተደራጁ አስፈጻሚ አካላት ኃላፊዎች፤

ሐ) ሥራ አስፈጻሚው እንደአስፈላጊነቱ በአባልነት እንዲሳተፉ የሚመርጣቸው የወረዳው ልሎች ኃላፊዎች፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ ፩ (ለ) ሥር የተጠቀሰው አስፈጻሚ አካል ኃላፊ በቋሚ ኮሚቴ ስብሰባ ላይ ሊገኝ በማይችልበት ጊዜ በግልጽ ተለይቶ ውክልና የተሰጠው ኃላፊ በተተኪ አባልነት በቋሚ ኮሚቴ ስብሰባ ላይ ይሳተፋል፡፡

፺፩·<u>ስለወረዳ ቋሚ ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባር፤</u>

፩·የወረዳ ቋሚ ኮሚቴ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ. በወረዳው ዕቅድና የበጀት ድልድል ሃሳብ ላይ ይመክራል፤

ለ. በወረዳው ውስጥ ፖሊሲዎች፣ አዋጆች፣ ደንቦችና የከተማው የበላይ አካላት ውሣኔዎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

ሐ. በወረዳው ምክር ቤትና በዋና ሥራ አስፈጻሚው የሚሰጡት ልሎች ተግባራት ያከናውናል፤

፪·የወረዳው ቋሚ ኮሚቴ የሥራ ዘመን የወረዳው ምክር ቤት የሥራ ዘመን ይሆናል፡፡

፺፪·<u>ስለወረዳ አስፈጻሚ አካላት</u>

፩·እያንዳንዱ ወረዳ በከተማው ካቢኔ በሚፀድቀው መዋቅራዊ አደረጃጀት መሠረት ሥልጣንና ተግባራቸው የሚወሰንላቸው አስፈጻሚ አካላት ይኖሩታል፤

፪·ወረዳዎች በዚህ አዋጅ የተሰጣቸውን ሥልጣንና ተግባር ሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችላቸው ልሎች የሥራ ክፍሎችና እንደአስፈላጊነቱም ነዋሪውን የሚያሳትፉ የበጐ ፈቃደኞች ኮሚቴዎች፣

እና የተለያዩ አገልግሎቶች የሚሰጡባቸውን ማዕከላት በከተማው ካቢኔ በሚፀድቀው መዋቅራዊ አደረጃጀትና የሥራ ድርሻ ዝርዝር መሠረት ለማደራጀት ይችላል፣

፫.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚደራጅ እያንዳንዱ ጽሕፈት ቤት በአጠቃላይ ለወረዳው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ተጠሪ ይሆናል፡፡ የዕቅድና በጀት ዝግጅት የዕቅድ አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ፣ የሠራተኞች የውስጥ ዝውውርና የደረጃ ዕድገትን ጨምሮ ልሎች ሙያዊና ቴክኒካዊ ጉዳዮችን በተመለከተ ደግሞ በሥራው መስክ ለሚመለከተው የክፍለ ከተማ ጽሕፈት ቤት ተጠሪነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ የከተማው ማዕከል ቢሮዎችና የሚያስተባብሯቸው ልሎች አስፈጻሚ አካላትን አደረጃጀት ተከትሎ በሥሩ የሚደራጁትን ልሎች ጽሕፈት ቤቶች መምሪያዎች ወይም ልሎች የሥራ ክፍሎች በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል::

፬.የወረዳ ጽሕፈት ቤቶች ከሚያስተባብሯቸው አስፈጻሚ አካላት ጋር እና ጽሕፈት ቤቶቹ በአንድ ላይ ደጋፊ የሥራ ሂደቶችን በጋራ ሊጠቀሙ ይችላሉ፡፡ ዝርዝሩ የከተማው ካቢኔ በሚያፀድቀው መዋቅራዊ አደረጃጀት መሠረት በከንቲባው በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፣

፭.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩ እስከ ፬) እና በሕግ በሌላ ሁኔታ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የወረዳ ዋና ሥራ አስፈጻሚዎችና ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚዎች እንዲሁም የጽሕፈት ቤትና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት ኃላፊዎች የሥራ ሁኔታ በከተማው ካቢኔ በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፣

፺፫.<u>ስለወረዳ ሥራ አስኪያጅ</u>

፩.የወረዳ ሥራ አስኪያጅ ተጠሪነቱ ለክፍለ ከተማው ሥራ አስኪያጅና ለወረዳው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሆኖ የወረዳው ማዘጋጃ ቤት አገልግሎቶች አስፈጻሚ በመሆን ይሠራል፣

፪.የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ የወረዳው ሥራ አስኪያጅ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ. በወረዳው የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አሰጣጥ ስሉጥ ውጤታማና ፍትሐዊ እንዲሆን ኃሳብ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፣

ለ. የወረዳው ማዘጋጃ ቤት አገልግሎት ሠራተኞችን አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ያስተዳድራል፣

ሐ. ከወረዳው ማዘጋጃ ቤት አገልግሎት ሰጪ አካላት ኃላፊዎች የተውጣጣና በከተማ ሥራ አስኪያጅ በሚወሰነው መሠረት የሚሠራ የሥራ አመራር ኮሚቴ ያቋቁማል፣ ይመራል፣

መ. በወረዳ የሚገኘውን የጽዳት ሥራ፣ የመሠረተ ልማት ጉዳዮችን ይከታተላል፣ ያስፈጽማል፣ የማዘጋጃ ቤት አገልግሎትን የሚመለከቱ ፖሊሲዎች ሕጐችና ውሣኔዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፣

ሠ. ስለሥራው አፈጻጸም ለክፍለ ከተማው ሥራ አስኪያጅና ለወረዳው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወቅታዊና ዓመታዊ ሪፖርት ያቀርባል፣

ረ. ከክፍለ ከተማው ሥራ አስኪያጅና ከወረዳው ዋና ሥራ አስፈጻሚ የሚሰጡትን ልሎች ተግባራት ያከናውናል፤

፫.የወረዳው ሥራ አስኪያጅ በወረዳ ቋሚ ኮሚቴ ስብሰባዎች ላይ ያለድምጽ መሳተፍ ይችላል፡

፺፩. ስለ ቦርድ፣ አማካሪ ምክር ቤት፣ ጠቅላላ ጉባኤ፣ ምክክር መድረክ

፩. በተለያዩ የከተማው አስተዳደር ሕጎች የተቋቋሙ ቦርድ፣ አማካሪ ምክር ቤት፣ ጠቅላላ ጉባኤ፣ምክክር መድረክ በዚህ አዋጅ ፈርሷል፤

፪. በከንቲባው አቅራቢነት ለአስፈፃሚ አካላት እና ለልሎች የከተማው ተቋማት የስራ አመራር ቦርድ፣ አማካሪ ምክር ቤት፣ ጠቅላላ ጉባኤ ወይም የምክክር መድረክ ካቢኔው በደንብ ሊያቋቁምላቸው ይችላል፤

፫. የዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (፩) ድንጋጌ የከተማ አስተዳደሩ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ እና በልማት ድርጅቶች ቦርድ ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

፺፪.የአስፈፃሚ አካላት እና የልማት ድርጅት ስለ ማቋቋምና ማደራጀት

፩. ለከተማው ምክር ቤት ወይም ለከንቲባ ተጠሪ የሆኑትን አስፈፃሚ አካላት ሳይጨምር ካቢኔው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ደንብ በማውጣት ሌላ አስፈጻሚ አካል እንዲታጠፍ፤ ከሌላ አስፈፃሚ አካል ጋር እንዲዋሀድ፣ እንዲከፋፈል ወይም ተጠሪነቱ ወይም ሥልጣንና ተግባሩ እንዲለወጥ በማድረግ፤ ወይም አዲስ አስፈፃሚ አካል እንደገና የማቋቋምና የማደራጀት፤ የከተማውን የልማት ድርጅት የማቋቋም እና የማደራጀት ሥልጣን ተሰጥቶታል፡

፺፫.የአስፈፃሚ አካላትን አደረጃጀትና አሰራር ስለመወሰን

ካቢኔው አስፈላጊነቱን ሲያምንበት የአስፈፃሚ አካላትን አደረጃጀትና አሰራር ለመወሰን ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ክፍል ሰባት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፺፬.ደንብ የማውጣት ሥልጣን

ካቢኔው ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፺፭.ስለ ማህበራዊ ፍርድ ቤቶች የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ጽህፈት ቤት

፩.የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የማህበራዊ ፍርድ ቤቶች የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ጽህፈት ቤት ተጠሪነት ለአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ይሆናል፤

፪.በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ጽህፈት ቤቱ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የማህበራዊ ፍርድ ቤቶች አዋጅ የተደነገገው ስልጣንና ተግባር ይኖረዋል፡፡

፺፮. የመብቶችና ግዴታዎች መተላለፍ

፩.የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የማዕከላትና ኮሪደሮች ልማት ኮርፖሬሽን መብት እና ግዴታ ለመሬት ልማትና ከተማ ማደስ ኤጀንሲ ተላልፏል፤

፪.የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ መብት እና ግዴታ ለሥራ ዕድል ፈጠራ ኢንተርፕራይዝ ልማት ቢሮ ተላልፏል፤

፫.የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የመስሪያ ቦታዎች ልማት እና አስተዳደር ኤጀንሲ መብት እና ግዴታ ለሥራ ዕድል ፈጠራ ኢንተርፕራይዝ ልማት ቢሮ ተላልፏል፤

፬.የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የስራ ዕድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ መብት እና ግዴታ ለምግብ ዋስትና እና ልማታዊ ሴፍቲኔት ኤጀንሲ ተላልፏል፤

፭.የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የካይዘን ኢንስቲትዩት መብት እና ግዴታ ለፐብሊክ ሰርቪስ እና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ ተላልፏል፤

፮.የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቤቶች ግንባታ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት መብት እና ግዴታ ለቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን ተላልፏል፤

፯.የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቁጠባ ቤቶች ልማት ኢንተርፕራይዝ መብት እና ግዴታ ለቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን ተላልፏል፤

፰.የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የወጣቶችና ስፖርት ቢሮ የወጣቶች ዘርፍ መብት እና ግዴታ ለወጣቶች እና በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ቢሮ ተላልፏል፤

፱.የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የወጣቶችና ስፖርት ቢሮ የስፖርት ዘርፍ መብት እና ግዴታ ለስፖርት ኮሚሽን ተላልፏል፤

፲.የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የማህበራዊ ጥበቃ ፈንድ እና ሴፍቲኔት ኤጀንሲ የማህበራዊ ፈንድ ዘርፍ መብት እና ግዴታ ለሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ተላልፏል፤

፲፩.የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመለስ ዜናዊ መታሰቢያ የምርምር፣ ሽግግርና ኢንኩቤሽን ማዕከል መብት እና ግዴታ ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲ ተላልፏል፤

፲፪.የምርታማነት ማሻሻያ ማዕከል መብት እና ግዴታ ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲ ተላልፏል፤

፲፫.የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የእሳትና ድንገተኛ አደጋዎች መከላከል እና መቆጣጠር ባለሥልጣን መብት እና ግዴታ ለእሳትና አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ተላልፏል፤

፲፬.የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቤቶች አስተዳደር ኤጀንሲ መብት እና ግዴታ ለቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ ተላልፏል፤

፲፭.የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተቀናጀ የመሬት መረጃ ማዕከል መብት እና ግዴታ ለመሬት ይዞታ ምዝገባ እና መረጃ ኤጀንሲ ተላልፏል፤

፲፮.የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የደንብ ማስከበር አገልግሎት ፅህፈት ቤት መብት እና ግዴታ ለሰላም እና ፀጥታ አስተዳደር ቢሮ ተላልፏል፤

፲፯.የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ተቆጣጣሪ ባለስልጣን የንብረት አስተዳደር የሚመለከት መብት እና ግዴታ ለመንግስት ሕንጻና ንብረት አስተዳደር ባለስልጣን ተላልፏል፡፡

፲፰.የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግስት ግዢና ንብረት አስተዳደር ተቆጣጣሪ ባለስልጣን የግዥ ቁጥጥር የሚመለከት መብት እና ግዴታ ለፋይናንስ ቢሮ ተላልፏል፤

፲፱. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአደጋ ዝግጁነት፣ ምላሽ እና መልሶ ማቋቋም ኤጀንሲ መብት እና ግዴታ ለእሳትና አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ተላልፏል፤

፳.የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የወንዞችና ወንዝ ዳርቻዎች ልማትና የአየር ንብረት ለውጥ ማጣጣሚያ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት መብት እና ግዴታ ለተፋሰስና አረንጓዴ አካባቢዎች ልማት ኤጀንሲ ተላልፏል፤

፳፩.የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሪዚሊየንስ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት መብት እና ግዴታ ለፕላንና ልማት ኮሚሽን ተላልፏል፤

፳፪.የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የልማት ተነሽ አርሶ አደሮች መልሶ ማቋቋሚያ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት መብት እና ግዴታ ለከተማ ግብርና እና አርሶ አደር ልማት ኮሚሽን ተላልፏል፤

፳፫.የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የእንጦጦና አካባቢው የቱሪስት መዳረሻ ልማት ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት መብት እና ግዴታ ለተፋሰስና አረንጓዴ አካባቢዎች ልማት ኤጀንሲ ተላልፏል፡

፳፬.የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአስፈፃሚ አካላት አደረጃጀትና የመዋቅር ጥናት ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት መብት እና ግዴታ ለፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ ተላልፏል፤

፳፭.የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትራንስፖርት ፕሮጀክቶች ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት መብት እና ግዴታ ለትራንስፖርት ቢሮ ተላልፏል፤

፳፮.የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመናፈሻዎች ልማት ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት መብት እና ግዴታ ለተፋሰስና አረንጓዴ አካባቢዎች ልማት ኤጀንሲ ተላልፏል፤

፳፯.የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ልማት ኤጀንሲ መብት እና ግዴታ ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ኤጀንሲ ተላልፏል፤

፳፰.የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ መብት እና ግዴታ ለንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ተላልፏል፤

፳፱.የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የንግድ ቢሮ መብት እና ግዴታ ለንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ተላልፏል፤

፴.የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የህበረተሰብ ተሳትፎ ልማት ኤጀንሲ መብት እና ግዴታ ለኮንስትራክሽን ቢሮ ተላልፏል፤

፴፩.የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትራንስፖርት ፈንድ ጽህፈት ቤት መብት እና ግዴታ ለትራንስፖርት ቢሮ ተላልፏል፤

፴፪. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሙያ ብቃት ምዘናና ማረጋገጫ ማዕከል መብትና ግዴታ ለትምህርትና ስልጠና ጥራት፣ ሙያ ብቃትና ምዘና ማረጋገጫ ባለስልጣን ተላልፏል፤

፴፫.የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አጠቃላይ የትምህርት ጥራትና አግባብነት ሬጉላቶሪ ኤጀንሲ መብትና ግዴታ ለትምህርትና ስልጠና ጥራት፣ ሙያ ብቃትና ምዘና ማረጋገጫ ባለስልጣን ተላልፏል፤

፴፬.የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፍትህ ቢሮ መብትና ግዴታ ለአቃቤ ህግ ቢሮ ተላልፏል፤

፴፭.የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ መብትና ግዴታ ለፋይናንስ ቢሮ ተላልፏል፤

፴፮.የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ መብትና ግዴታ ለትራንስፖርት ቢሮ ተላልፏል፤

፴፯.የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኮሚኒኬሽን ቢሮ መብትና ግዴታ ለከንቲባ ጽህፈት ቤት ተላልፏል

፴፰.የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ቢሮ መብትና ግዴታ ለባህል፣ ኪነ ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ተላልፏል፤

፴፱.የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፕላን ኮሚሽን መብትና ግዴታ ለፕላንና ልማት ኮሚሽን ተላልፏል፤

፵.የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን መብትና ግዴታ ለአካባቢ ጥበቃና አረንጓዴ ልማት ኮሚሽን ተላልፏል፤

፵፩.የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኢንቨስትመንት አጀንሲ መብትና ግዴታ ለኢንቨስትመንት ኮሚሽን ተላልፏል፤

፵፪.የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ቢሮ መብትና ግዴታ ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲ ተላልፏል፤

፵፫.የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የይዞታ አስተዳደር ሽግግር ጊዜ አግልግሎት ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት መብትና ግዴታ ለመሬት ይዞታ አስተዳደር ጽህፈት ቤት ተላልፏል፤

፵፬.የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መለስ ዜናዊ አመራር አካዳሚ መብትና ግዴታ ለመለስ ዜናዊ ስራ አመራር ኢንቲትዩት ተላልፏል፡፡

፪.<u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች</u>

፩. በዚህ አዋጅ ያልተካተቱ አስፈጻሚ አካላት ከዚህ አዋጅ ጋር ባልተቃረነ መልኩ በተቋቋሙበት ህግ ስራቸውን ይቀጥላሉ፤

፪. የአስፈፃሚ አካላትን አደረጃጀትንና አሰራር ለመወሰን ካቢኔው ያወጣቸው ልዩልዩ ደንቦች የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች እስካልተቃረኑ እና በዚህ አዋጅ መሰረት በሚወጡ ደንቦች እስከሚተኩ ድረስ ተፈፃሚነታቸው ይቀጥላል፤

፫. የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፬ ድንጋጌ ቢኖርም በዚህ አዋጅ መሰረት የአደረጃጀት ማሻሻያ እስከሚደረግ ድረስ በከተማ፣ በክፍለ ከተማ እና በወረዳ ደረጃ ተደራጅተው በመስራት ላይ የሚገኙ አስፈፃሚ አካላት በተደራጁበት ህግና አግባብ ስራቸውን ይቀጥላሉ፤

፬. በዚህ አዋጅ የታጠፉ አስፈፃሚ አካላት በመከናወን ላይ ያሉ ስራዎችን እያከናወኑ ለርክክብ ዝግጁ ያደርጋሉ፤ በከንቲባው በሚወጣ መመሪያ በሚወሰነው መሰረት በዚህ አዋጅ ለተቋቋሙ አስፈፃሚ አካል ያስረክባሉ፡፡

፶፩. <u>ስለተጠያቂነት</u>

በዚህ አዋጅና በልሎች ህጎች በተሰጠው ስልጣንና ተግባር ኃላፊነቱን ያልተወጣ ኃላፊ ወይም ሰራተኛ አግባብነት ባለው ህግና አሰራር ተጠያቂ ይሆናል፡፡

፶፪.<u>የተሻሻለ ሕግ</u>

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቴክኒክ እና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ቢሮና የማሰልጠኛ ተቋማት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፵፱/፪ሺህ፱ የማሰልጠኛ ተቋማት ተጠሪነት ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲ ይሆናል፡፡

፶፫.<u>የተሻሩ ሕጎች</u>

ከዚህ የሚከተሉት ሕጎች ተሽረዋል፡፡

፩.የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምግብ፣ የመድሀኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፴/፪ሺህ፬፤

፪.የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚና ማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፴፭/፪ሺህ፬ ከነማሻሻያዎቹ፤

፫.የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፵፩/፪ሺህ፯፤

፬.የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቴክኒክ እና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ቢሮና የማሰልጠኛ ተቋማት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፵፱/፪ሺህ፱:-

ሀ. ከአንቀፅ ፯ እስከ አንቀፅ ፲፩፣ እና

ለ. በልሎች የአዋጁ ድንጋጌዎች ውስጥ "ቢሮ" የሚል ቃል፤

፭.የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፕላን ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፵፰/፪ሺህ፱፤

፮.የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሰረተ ልማት ቅንጅት፣ የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፶፫/፪ሺህ፱፤

፯.የአዲስ አበባ ማእከላትና ኮሪደሮች ልማት ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፶፬/፪ሺህ፱፤

፰.የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተፋሰስና አረንጓዴ አካባቢዎች ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፰፪/፪ሺህ፲፤

፱.የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የስራ እድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፹/፪ሺህ፱፤

፲.የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የህብረት ስራ ማህበራት ኤጀንሲ ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፹፭/፪ሺህ፱፤

፲፩.የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መንገዶች ባለስልጣን ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፯/፲፱፻፺፩፤

፲፪. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቁጠባ ቤቶች ልማት ኢንተርፕራይዝ ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፶፰/፪ሺህ፤

፲፫. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የግዥና ንብረት ማስወገድ ኤጀንሲ ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፶፭/፪ሺህ፭፣

፲፬. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲ ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፷፫/፪ሺህ፯፣

፲፭. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአጠቃላይ ትምህርት ጥራትና አግባብነት ሬጉላቶሪ ኤጀንሲ ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፷፰/፪ሺህ፯፣

፲፮. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር  የእንጦጦና አካባቢው የቱሪስት መዳረሻ ልማት ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፷፱/፪ሺህ፰፣

፲፯. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር  የወንዞችና የወንዝ ዳርቻዎች ልማትና የአየር ንብረት ለውጥ ማጣጣም ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር  ፸፭/፪ሺህ፰፣

፲፰. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የመስሪያ ቦታዎች ልማትና አስተዳደር ኤጀንሲ ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፸፮/፪ሺህ፰፣

፲፱. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካይዘን ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፸፯/፪ሺህ፰፣

፳. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር  የቅሬታ እና አቤቱታ አቀራረብ ምርመራ፣ አወሳሰን እና የተጠያቂነት ደንብ ቁጥር ፸፰/፪ሺህ፰፣

፳፩. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የልማት ተነሺ አርሶ አደሮች መልሶ ማቋቋሚያ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት ደንብ ቁጥር ፸፱/፪ሺህ፰፣

፳፪. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የማህበራዊ ጥበቃ ፈንድ እና ሴፍቲኔት ኤጀንሲ ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፹፩/፪ሺህ፱፣

፳፫. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሬዚሊየንስና ፕ/ጽ/ቤት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፹፱/፪ሺህ፲፣

፳፬. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመለስ ዜናዊ መታሰቢያ የቴክኖሎጂ ምርምር ሽግግርና የኢንኩቤሽን ማእከል ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፺፭/፪ሺህ፲፣

፳፭. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የግዥና ንብረት አስተዳደር ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፺፯/፪ሺህ፲፣

፳፮. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአደጋ ዝግጁነት፣ ምላሽና መልሶ ማቋቋም ኤጀንሲ ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፺፰/፪ሺህ፲፣

፳፯ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአዲስ ዙ ፓርክ ማዕከል ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፶፪/፪ሺህ፭፣

፳፰. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመለስ ዜናዊ የአመራር አካዳሚ ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፷፯/፪ሺህ፯፣

፳፱. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትራንስፖርት ፈንድ ጽህፈት ቤት አደረጃጀትና አሰራር ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር ፺፩/፪ሺህ፲፣

፴. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፲/፲፱፻፺፯ ከነማሻሻያዎቹ ፣

፴፩. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርየትራንስፖርት ፕሮጀክቶች ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፶/፪ሺህ፣

፴፪. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሳይንስና ቴክኖሎጂ ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፶/፪ሺህ፣

፴፫. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመናፈሻ ልማት ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፹፬/፪ሺህ፱፣

፴፬. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአስፈፃሚ አካላትና አደረጃጀትና የመዋቅር ጥናት ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፶፱/፪ሺህ፯፣

፴፭. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሞያ ብቃት ምዘናና ማረጋገጫ ማዕከል አደረጃጀትና አሰራር ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር ፷፬/፪ሺህ፯፣

፴፮. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽህፈት ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፲፩/፲፱፻፺፭አንቀፅ ፫ ንዑስ-አንቀፅ (፪)፣

፴፯. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሸገር የብዙሀን ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፸/፪ሺህ፰ አንቀፅ ፫ ንዑስ-አንቀፅ (፫)፤

፴፰. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንደስትሪ ክላስተር ልማት ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፹፫/፪ሺህ፱ አንቀፅ ፬ ንዑስ-አንቀፅ (፪)፤

፴፱. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤቶች አዋጅን (ለማሻሻል) የወጣ አዋጅ ቁጥር ፴፩/፲፱፻፺፱:-

አንቀፅ ፪፪ "ቢሮ"፤

አንቀፅ ፫፪ "ቢሮ" እና

በአዋጁ ልሎች አንቀጾች "ቢሮ" የሚለውቃል፤

፵.ጉለሌ የዕፅዋት ማዕከል ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፲፰/፪ሺህ፪ አንቀፅ ፫ ንዑስ-አንቀፅ (፪)፤

፵፩.የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኮተቤ ሜትሮፖሊታን ዩኒቨርሲቲን ለማቋቋም የወጣ ደንብ ቁጥር ፹፪/፪ሺህ፱ አንቀፅ፫ንዑስ-አንቀፅ (፫) "ዩኒቨርሲቲው ተጠሪነቱ ለከተማው አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ይሆናል" የሚለው ዐረፍተ-ነገር፡፡

፻፬.ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረኑ የከተማው አስተዳደር አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ እና ልማዳዊ አሰራር በዚህ አዋጅ የተደነገጉትን ጉዳዮች በሚመለከት ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

፻፭. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከታህሳስ ፳፯ ቀን ፪ሺህ፲፩ ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ታህሳስ ፳፯ ቀን ፪ሺህ፲፩ዓ.ም.

ታከለ ኡማ

የአዲስ አበባ ከተማ ምክትል ከንቲባ

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚ አካላትን እንደገና ለማደራጀት፣ ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣ ማሻሻያ አዋጅ ፷፯/፪ሺ፲፪

የአዲስ አበባ ከተማ ከጊዜ ወደ ጊዜ በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊና ፖለቲካዊ ረገድ እድገት እያስመዘገበ በመሆኑና ከሚመዘገበው ለውጥ ጋር አብሮ የሚሄድ የከተማው አስተዳደር የአስፈጻሚና ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት አካላትን አደረጃጀት መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ፤ እንዲሁም በተለያዩ መስኮች የሚታዩ የአሰራር ክፍተቶችንና ችግሮችን ለመቅረፍ አንዱ መፍትሄ የተቋማትን አደረጃጀት እንዲሁም ሥልጣንና ተግባራቸውን መወሰን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1905 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 16 ንዑስ-አንቀጽ 1(ሀ) መሠረት ይህን ማሻሻያ አዋጅ አውጥቷል፡፡

1. አጭር ርዕስ

   ይህ አዋጅ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚ አካላትን እንደገና ለማደራጀት፣ ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣ" አዋጅ ቁጥር ፷፯/፪ሺ፲፪ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ትርጓሜ

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-
   በአዋጁ የተተረጎሙ ቃላትና ሐረጎች በዚህ አዋጅ ውስጥም ተፈጻሚነት አላቸው፡፡

3. ማሻሻያ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚ አካላትን እንደገና ለማደራጀት፣ ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር ፷6/20111 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፤

ከአዋጁ አንቀጽ 10 ተራ ፊደል /ለ/ ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ተራ ፊደል /ሐ/ ተጨምሯል፤

" ሐ. ለህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚውሉ የከተማውን ዴፖዎችን፣ መናኸሪያዎችን፣ ፌርማታዎችን እና መጋዘኖችን ያስተዳድራል፤ ይገነባል ወይም ያስገነባል፡፡" ፤

በአዋጁ አንቀጽ 11 ንዑስ-አንቀጽ /10/ "የንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ" የሚለው ተሰርዞ "የንግድ ቢሮ" በሚል ተተክቷል፤

በአዋጁ አንቀጽ 11 ንዑስ-አንቀጽ /26/ "የገቢዎች ባለስልጣን" የሚለው ተሰርዞ "የገቢዎች ቢሮ" በሚል ተተክቷል፤

በአዋጁ አንቀጽ 11 ንዑስ-አንቀጽ /39/ "የመንግስት የግዥና ንብረት ማስወገድ ኤጀንሲ" የሚለው ተሰርዞ "የመንግስት የግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት" በሚል ተተክቷል፤

በአዋጁ አንቀጽ 11 ንዑስ-አንቀጽ /68/ "የግንባታ ዲዛይን ጽህፈት ቤት" የሚለው ተሰርዞ "የግንባታ ዲዛይን ኤጀንሲ" በሚል ተተክቷል፤

በአዋጁ አንቀጽ 11 ንዑስ-አንቀጽ /52/ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ-አንቀጽ /52/ ተተክቷል፤

"52. የኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ"፤

ከአዋጁ አንቀጽ 11 ንዑስ-አንቀጽ /55/ ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ-አንቀጽ /56/ ተጨምሯል፤

"56. የመሥሪያ ቦታዎች ልማትና አስተዳደር ኤጀንሲ"፤

በአዋጁ አንቀጽ 12 ንዑስ-አንቀጽ /1/ ተራ ፊደል "ሀ" "ከተራ ቁጥር 2 እስከ 13 የተጠቀሱት ቢሮዎች" የሚለው "ከተራ ቁጥር 2 እስከ 13፣ 26 እና 52 የተጠቀሱት ቢሮዎች" በሚል ተተክቷል፣

የአዋጁ አንቀጽ 12 ንዑስ-አንቀጽ /1/ ተራ ፊደል "መ" ፣ "ነ" እና "ኘ" ተሠርዘዋል፤

ከአዋጁ አንቀጽ 12 ንዑስ-አንቀጽ /1/ ተራ ፊደል (ሐ) በኋላ የቀሩት ተራ ፊደሎች እንደቅደም ተከተላቸው ተሸጋሽጓል፤

ከአዋጁ አንቀጽ 12 ንዑስ-አንቀጽ /2/ ተራ ፊደል (ረ) ተሠርዟል፤

የአዋጁ አንቀጽ 12 ንዑስ-አንቀጽ /2/ ተራ ፊደል (ሸ) ተራ ፊደል (ረ) ሆኗል፤

በአዋጁ አንቀጽ 12 ንዑስ-አንቀጽ /5/ ተራ ፊደል "ሐ" "የመንግሥት የግዥና ንብረት ማስወገድ ኤጀንሲ" የሚለው ተሠርዞ " የመንግሥት የግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት" በሚል ተተክቷል፤

በአዋጁ አንቀጽ 12 ንዑስ-አንቀጽ /9/ ተራ ፊደል "ለ" "የግንባታ ዲዛይን ጽሕፈት ቤት" የሚለው ተሠርዞ "የግንባታ ዲዛይን ኤጀንሲ" በሚል ተተክቷል፤

የአዋጁ አንቀጽ 12 ንዑስ-አንቀጽ /10/ ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ-አንቀጽ /10/ ተተክቷል፤

"10. የሚከተሉት አስፈፃሚ አካላት ተጠሪነት ለሥራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዝ ልማት ቢሮ ይሆናል፡-

ሀ/ የምግብ ዋስትናና ልማታዊ ሴፍቲኔት ኤጀንሲ፤

ለ/ የመሥሪያ ቦታዎች ልማትና አስተዳደር ኤጀንሲ፤

ሐ/ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጣና አጀንሲ፡፡ "

የአዋጁ አንቀጽ 12 ንኡስ-አንቀጽ 12 "ለንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ" የሚለው ሀረግ ተሰርዞ "ለንግድ ቢሮ" በሚል ሀረግ ተተክቷል፤

የአዋጁ አንቀጽ 12 ንዑስ-አንቀጽ /12/ ተራ ፊደል "ለ" ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ተራ ፊደል (ለ) ተተክቷል፤

"ለ. የኤግዚቢሽን ማዕከልና የገበያ ልማት ድርጅት፡፡"

የአዋጁ አንቀጽ 15 ንዑስ-አንቀጽ /11/ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ-አንቀጽ /11/ ተተክቷል፤

"11. እንደየሥራ ባህሪያቸው የሕብረተሰብ ተሣትፎን ያጎለብታል፣ ያሳትፋል፣ ተጠቃሚ ያደርጋል፤ እንዲሁም ከአስተዳደሩ አካላት አግባብነት ባላቸው ጉዳዮች ላይ በመተባበር፣ በመደጋገፍ እና በመቀናጀት ሥራዎችን ያከናውናል፤ ከልሎች አስፈጻሚ አካላት ጋር ስራዎችን በቅንጅት ለመስራት የሚያስችሉ ትስስርና ትብብር ያደርጋል፤"

የአዋጁ አንቀጽ 20 ንኡስ-አንቀጽ /1/ "የመንግስት ግዢና ንብረት ማስወገድ ኤጀንሲ" የሚለው "የመንግስት ግዢና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት" በሚል ተተክቷል፤

የአዋጁ አንቀጽ 22 ንዑስ-አንቀጽ /13/ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ-አንቀጽ /13/ ተተክቷል፣

"13 በመንግሥት ወጭ የሚገነቡ ሕንፃዎችና መሰል ግንባታዎች በተመለከተ የግንባታ ፈቃድ ያወጣል፣ ያድሣል፣ የግንባታ ዲዛይን ይሠራል፡፡"፤

የአዋጁ አንቀጽ 23 ንዑስ-አንቀጽ /1/ "የግንባታ ዲዛይን ጽህፈት ቤት" የሚለው ተሰርዞ "የግንባታ ዲዛይን ኤጀንሲ" በሚል ተተክቷል፤

የአዋጁ አንቀጽ 23 ንዑስ-አንቀጽ /16/፣ /18/፣ /19/፣ /21/ እና /22/ ተሰርዟል፤

የአዋጁ አንቀጽ 23 ከንዑስ-አንቀጽ /16/ ጀምሮ ያሉት ንዑስ-አንቀጾች እንደቅደም ተከተላቸው ተሸጋሽገዋል፤

የአዋጁ አንቀጽ 25 ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 25 ተተክቷል፤

25. የንግድ ቢሮ

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

የህብረት ስራ ማህበራት ኤጀንሲን እና የኤግዚብሽን ማዕከልና የገበያ ልማት ድርጅትን በበላይነት ይመራል፤ ያስተባብራል፤

የንግድና ገበያ ልማት ተወዳዳሪነትን በቀጣይነት የሚያረጋግጡ ከተማ አቀፍ ፖሊሲዎችን ይቀርጻል፣ በሚመለከተው አካል ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

የከተማው የምርት ውጤቶች እንዲታወቁ ያደርጋል፤ አውደ-ርዕይ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤ ይሳተፋል፤ ፈቃድ ይሰጣል፤ ይቆጣጠራል፤

የአገር ውስጥ ባለሃብቶች በከተማው ውስጥ በንግድና ገበያ ልማት ስራ ላይ በሰፊው እንዲሰማሩ ያበረታታል፤ የቴክኒክና የምክር አገልግሎቶችን ይሰጣል፤ በንግድ ስራ ለሚሰማሩና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎችን ለሚያቋቁሙ የሃገር ውስጥ ባለሃብቶች የንግድ ፍቃድ ይሰጣል፤ ይቆጣጠራል፤

በከተማው በውስጥ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት እንዲቋቋም ያበረታታል፤ ድጋፍ ይሰጣል፤ የከተማውን የንግድ መዝገብ ያቋቁማል፤ የንግድ ስም ምዝገባ ያከናውናል፤ ያስተዳድራል፤ የንግድ ማህበራትን በህግ መሠረት በመመዝገብ ፈቃድ ይሰጣል፤ ያድሳል፤ ያግዳል፤ ይሰርዛል፤

የዋስትና መያዣ በሕግ መሠረት በንግድ መዝገብ ይመዘግባል፤ ይሰርዛል፤ ለሃራጅ ሽያጭ አፈጻጸም የሚረዱ ስራዎችን በሕግ መሰረት ያከናውናል፤

የገበያ ማዕከላት ያለማል፤ ደረጃ ያወጣል፤ ደረጃቸውን የጠበቁ የገበያ ማዕከላት መገንባታቸውን ይቆጣጠራል፤ የሚስፋፉበትንና የሚያድጉበትን ስልት ይቀይሳል፤

በከተማው ውስጥ የመሠረታዊ ንግድ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ስርጭት የገበያ ህግና ስርዓትን መከተሉን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

ለገበያ የሚቀርቡ ምርቶችና አገልግሎቶች ጥራትና ደረጃቸውን የጠበቁ መሆኑን ይቆጣጠራል፤ እንዲሁም ጥራትና ደረጃቸውን ያልጠበቁ ወይም ጊዜ ያለፈባቸው ምርቶች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን እንዲወገዱ ያደርጋል፤

የፍጆታ ምርቶችን የአገልግሎት ዘመንና የተዘጋጁባቸውን ንጥረ-ነገሮች ይዘት ሸማቹ ማወቅ በሚችልበት ሁኔታ መሆኑን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

በገበያው ውስጥ በቂ አቅርቦት መኖሩንና ግዥና ሽያጩ በተረጋጋ ሁኔታ እየተከናወነ መሆኑን ያረጋግጣል፤ ለነጻ ገበያ ውድድር እንቅፋት የሆኑ ድርጊቶችና ተገቢ ያልሆኑ የንግድ ስራዎች እንዳይፈጸሙ በመከላከልና በማስወገድ የከተማውን ነዋሪዎች ጥቅም ያስጠብቃል፤

የገበያ ዋጋ መረጃ የመሰብሰብ፣ የመተንተን እና የማቀነባበር ተግባራትን ያከናውናል፤ እንዳስፈላጊነቱ በጥቅም ላይ ያውላል፤

የልኬት መሳሪያዎችንና መስፈሪያዎችን ትክክለኛነት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ያረጋግጣል፤ ይቆጣጠራል፤ ትክክለኛ ሆነው ያልተገኙ የልኬት መሳሪያዎችንና መስፈሪያዎችን እንዲወገዱ ያደርጋል፤

ለገበያ አገልግሎት እንዲውሉ የተዘጋጁ ቦታዎችን ይቆጣጠራል፤ ያስተዳድራል፤ የአገልግሎት አሰጣጡን በተመለከተ መመሪያ ያወጣል፤

ኢ-መደበኛ ያልሆነ ንግድ ወደ መደበኛ ስርዓት የሚገባበትን አሰራር ስርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤

ሕገ-ወጥ ንግድን ከሚመለከተው አካል ጋር በመተባበር ይከላከላል፤ ይቆጣጠራል፤ እርምጃ ይወስዳል፤ እንዲወሰድ ያደርጋል፡፡"፤

የአዋጁ አንቀጽ 26 ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 26 ተተክቷል፤

"26. <u>የስራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዝ ልማት ቢሮ</u>

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

የምግብ ዋስትናና ልማታዊ ሴፍቲኔት ኤጀንሲን፣ የመስሪያ ቦታዎች ልማትና አስተዳደር ኤጀንሲን እና የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲን በበላይነት ይመራል፤ ያስተባብራል፤

የጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርኘራይዞችን ልማት ለማፋጠን የሚረዱ ተቋማዊ ስትራቴጂዎች፣ ስልቶችን፣ ኘሮግራሞችን፣ ኘሮጀክቶችን፣ መመሪያዎችንና እቅዶችን ያዘጋጃል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤

የጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርኘራይዞችን ልማት ለማፋጠን የሚረዱ የድጋፍ ማእቀፎች ይቀርፃል፤ ተግባራዊ ያደርጋል፤

በከተማው ውስጥ የሚገኙትን ነዋሪዎች አምራች ዜጋ ለማድረግ የሚያስችሉ አዳዲስ የስራ እድል አማራጮችን ይለያል፣ ያጠናል፣ ያስጠናል፤ ኘሮጀክት ኘሮፋይል ያዘጋጃል፣ የአዋጭነት ጥናቶችን ያጠናል፣ ያስተዋውቃል፣ ወደስራ እንዲገቡ ያበረታታል፤

ጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርኘራይዞች በንግድ ህጉና አግባብ ባለው ሌላ ህግ መሰረት እንዲደራጁ ያመቻቻል፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፣ ያበረታታል፤

የጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርኘራይዞች እንዲስፋፉ አስፈላጊውን ሁሉ ያደርጋል፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ እና ከግል ድርጅቶች ጋር ትስስር በመፍጠር ድጋፍ እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፣ ተፈጻሚነቱን ያረጋግጣል፤

የጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርኘራይዞች የተሰማሩበትን የስራ ዘርፍ በአግባቡ ማካሄድ የሚያስችላቸው የስራ ማስኬጃ ብድር፣ የካፒታል ሊዝ ፋይናንስ አገልግሎት ያመቻቻል፤ የመስሪያ ቦታ እንዲያገኙ ድጋፍ ያደርጋል፤

ጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርኘራይዞች የንግድ ስራቸውን በአግባቡ መምራት እና ምርትና ምርታማነታቸውን ማሳደግ እንዲችሉ ሙያዊ የድጋፍና ክትትል አገልግሎት ይሰጣል፤

በጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርኘራይዝ ለተሰማሩ አንቀሳቃሾች የሙያ ማበልጸጊያ ስልጠናዎችና አውደ-ርዕዮች እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ ያስተባብራል፤

የጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርኘራይዞች የገበያ ችግር ለመቅረፍ ከተለያዩ አካላት ጋር የገበያ ትስስር እንዲፈጠርላቸው ያደርጋል፣ ምርቶቻቸውንና አገልግሎታቸውን ለተጠቃሚው ለማስተዋወቅ እንዲችሉና የገበያ ዕድላቸውን ለማስፋት ኤግዚቢሽንና ባዛሮች እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ በውጭ ሀገር በሚካሄዱ ኤግዚቢሽንና ባዛሮች እንዲሳተፉ ያመቻቻል፤

ለጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርኘራይዞች ልማት ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር ይሰራል፣ ለተወዳዳሪነታቸው እንቅፋት የሆኑ ጉዳዮችን በጥናት በመለየት መፍትሄ እንዲያገኙ ያደርጋል፤

የጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ሊያፋጥኑና ተወዳዳሪ ሊያደርጉ የሚችሉ ምርጥ ተሞክሮዎችን ከሀገር ውስጥና ከውጭ ሀገር ለይቶ ያጠናል ይቀምራል፣ ያስተገብራል፤ ውጤታማነቱን ይከታተላል፤

የኢንተርኘራይዞች የእርስ በእርስ እና ከከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ጋር በግብዓት አቅርቦት፣ በምርትና በቴክኖሎጂ ትስስር እንዲፈጥሩ ያደርጋል፤ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር የገበያ ትስስር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደግፋል፤

የጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርኘራይዞች ምርታማነታቸውን ለማሳደግ፣ የሚያመርቷቸው ምርቶች የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁ እና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ከዩኒቨርሲቲዎች፣ ከጥናትና ምርምር ተቋማት፣ ከከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች እና ከልሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል፣ ቁርኝቱን ያጠናክራል፤ ያስተባብራል፤

ለጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የመረጃ፣ የቴክኖሎጂ መረጣ፣ የድርድር፣ የግንባታ፣ የኮሚሽኒንግ ድጋፍ ይሰጣል፤ ውጤቱንም ይገመግማል፤

የጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ አምራች ኢንተርፕራይዞች የሀገሪቱን አምራች ኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ፣ ህግና ደንብ መሰረት አድርገው እንዲሰሩ ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ ይሰራል፤ አፈፃፀሙን እየተከታተለ ድጋፍ ያደርጋል፤

የጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርኘራይዞች የብቃት ማረጋገጫ እንዲሁም የደረጃ እና የጥራት ሰርቲፊኬሽን እንዲያገኙ ድጋፍ ያደርጋል፤

ኢንተርኘራይዞችን ከጥቃቅን ወደ አነስተኛ፣ ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ እና ከመካከለኛ ወደ ከፍተኛ የእድገት ደረጃ እንዲሸጋገሩ ያደርጋል፤

ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር የግልና የመንግስት ተቋማት የሚገኙ ድጋፎችን ያስተባብራል፣ ተግባር ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤

የጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርኘራይዞች ተወዳዳሪ ለማድረግ በጥናት ላይ የተመሰረተ የማበረታቻ፣ የእውቅና እና ሽልማት ስርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል፣ ተፈጻሚነቱን ያረጋግጣል፤

ኢንተርኘርነሮች እና ኢንተርኘራይዞችን ውጤታማ የሚያደርጉ የኢንኩቤሽን እና አክስለሬሽን ማዕከላትን ያቋቁማል፤ ያደራጃል፣ ያስተዳድራል፤

የጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርኘራይዞች የአንድ ማእከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎችን ያቋቁማል፣ ያስተባብራል፤ ይቆጣጠራል፤

ኢንተርኘራይዞች በዘርፍ ማህበራት እንዲደራጁና ውጤታማ እንዲሆኑ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፣

የኢንተርፐራይዞችንና የስራ ፈላጊዎችን መረጃ ይሰበስባል፣ ይተነትናል፣ ያደራጃል፤ ጥቅም ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ልሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፡፡"

ከአዋጁ አንቀጽ 31 ንዑስ-አንቀጽ /23/ ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ-አንቀጽ /26/ ተጨምሯል፤

"26. ስለ ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ግንዛቤ ያስጨብጣል፤ ከስደት ተመላሽ ሰዎችን እንዲቋቋሙ ያደርጋል፡፡"፤

የአዋጁ አንቀጽ 36 ንዑስ-አንቀጽ /9/ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ-አንቀጽ /9/ ተተክቷል፤

"9. እንደ ኢንቨስትመንቱ ዓይነት ለፕሮጀክቱ የሚያስፈልገውን የመሬት ፍላጎት ገምግሞ የመሬት ዝግጅት እንዲደረግ ለሚመለከተው አካል ያስተላልፋል፡፡"

በአዋጁ አንቀጽ 39 "የገቢዎች ባለስልጣን "የሚለው ስም "የገቢዎች ቢሮ" በሚል ስም ተተክቷል፤ ባለስልጣኑ የሚለው ቃል "ቢሮው" በሚለው ተተክቷል፤

የአዋጁ አንቀጽ 60 ንዑስ-አንቀጽ /20/ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ-አንቀጽ /20/ ተተክቷል፤

"20. በአሠሪና ሠራተኛ ሕግ መሠረት ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፤"፤

ከአዋጅ አንቀጽ 61 ንዑስ-አንቀጽ /21/ ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ-አንቀጽ /22/ ተጨምሯል

"22. በአሠሪና ሠራተኛ ሕግ መሠረት ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፤"፤

በአዋጅ አንቀጽ 53 ንዑስ-አንቀጽ /11/ ውስጥ "ድልድል በማድረግ" የሚለው ሐረግ ተሰርዟል፤

የአዋጁ አንቀጽ 56 "የመንግሥት ግዥና የንብረት ማስወገድ ኤጀንሲ" የሚለው ርዕስ ተሰርዞ "የመንግሥት የግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት "በሚል ተተክቷል፤ ኤጀንሲው የሚለው ቃል "አገልግሎቱ" በሚለው ተተክቷል፤

ከአዋጁ አንቀጽ 59 ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ አንቀጽ 60 ተጨምሯል፤

"60. <u>የመሥሪያ ቦታዎች ልማትና አስተዳደር ኤጀንሲ</u>

ኤጀንሲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ለጥቃቅን እና አነስተኛ አገልግሎት እንዲውሉ የተዘጋጁ ነባር የመስሪያ ቦታ የሆኑ ሼዶችን፣ ህንጻዎችን፣ ተለጣፊ ሱቆችን፣ እና ኮንቴነሮችን እንዲሁም በመንግስት፣ በግል እና በተለያዩ በጎ አድራጎት ድርጅቶች የተገነቡ መደብሮችን ያስተዳድራል፤

ለጥቃቅንና አነስተኛ መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ ማምረቻ፣ ማሳያ እና መሸጫ ሼድና ህንጻ በኢንዱስትሪ መንደሮች፣ በክላስተር ማዕከላትና በገበያ ማዕከላት ማስገንባት እንዲችል ከሚመለከተው አካል የለማ መሬት ይረከባል፤ ካርታ የሌላቸው ነባር ይዞታዎች ካርታ እንዲሰራላቸው ያደረጋል፤

ለጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ የማምረቻ፣ ማሳያና መሸጫ ሼዶችና ህንጻዎች በኢንዱስትሪ መንደሮች፣ በክላስተር ማዕከላት፣ በገበያ ማዕከላት እና በኢንፖሪየም ማዕከላት በማደራጀት እንዲገነቡ ያደርጋል፤ የመሠረተ ልማት አውታሮችም እንዲሟላላቸው ይደግፋል፤ ይከታተላል፤

ለነባር እና አዲስ የመስሪያ ቦታ ማዕከላት ስታንዳርድ ያወጣል፣ ይተገብራል፣ ይቆጣጠራል፤ የመስሪያ ቦታ አሰጣጥ፣ አጠቃቀም እና አስተዳደር ዝርዝር አፈጻጸም በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፤

የማምረቻ፣ ማሳያና መሸጫ ሼዶችና ህንጻዎችን የተደራጀ መረጃ ይይዛል፣ ተጠሪ ከሆነበት ቢሮ ተለይተው ለሚቀርቡ የጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች በኪራይ ውል ያስተላልፋል፤ ኪራይ እንዲሰበሰብ ያደርጋል፤

የመስሪያ ቦታ ተጠቃሚ የሆኑ ኢንተርፕራይዞች በውላቸው መሠረት ለታለመለት ዓላማ እየተጠቀሙበት ስለመሆኑ ይቆጣጠራል፣ ከዚያ ውጭ በሆኑት ላይ እርምጃ ይወስዳል፤

በህገ-ወጥ መንገድ የማምረቻ፣ ማሳያና መሸጫ ቦታ እንዳይተላለፍ ይከታተላል፣ ፈጽመው በተገኙ አስተላላፊ አካልም ሆነ የተላላፊለት ላይ እርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል፤

ዕድሳት እና ጥገና የሚያስፈልጋቸው ነባር መስሪያ ቦታዎች በጥናት በመለየት እድሳት እና ጥገና እንዲደረግላቸው ያደርጋል፤

የአካባቢ ብክለትን ሊያስወግዱ የሚችሉ አሰራሮችና የስራ ላይ ደህንነቶች እንዲተገበሩ በማድረግ የመስሪያ ቦታዎች ደህንነታቸው የተረጋገጠና ምቹ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

የክላስተር ማዕከላት ልማት ከኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ ጋር የተጣጣመ እና ወቅታዊ መሆኑን በየጊዜው ያረጋግጣል፤ ስራ ላይም ያውላል፡፡”

ከአዋጁ አንቀጽ 59 ጀምሮ ያሉት አንቀጾች እንደቅደም ተከተላቸው ተሸጋሽገዋል፡፡

የአዋጁ አንቀጽ 63 “የግንባታ ዲዛይን ጽሕፈት ቤት” የሚለው ስም ተሰርዞ “የግንባታ ዲዛይን ኤጀንሲ” በሚል ተተክቷል፤ ጽህፈት ቤቱ የሚለው ቃል “ኤጀንሲው በሚለው ተተክቷል፡፡

የአዋጁ አንቀጽ 63 ንዑስ-አንቀጽ /5/፣ /6/ እና /3/ ተሰርዘው በሚከተሉት አዲስ ንዑስ- አንቀጽ /5/፣ /6/ እና /3/ ተተክቷል፤

“5. የቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን ለሚያስገነባቸው ቤቶችና ተያያዥ ግንባታዎች ዲዛይን ወይም የግንባታውን ስፔሲፊኬሽን ያዘጋጃል፤ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፣ ተገቢውን ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፤ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

6. የቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን ለሚያስገነባቸው ቤቶችና ተያያዥ ግንባታዎች ዲዛይኖች፣ የስራ ዝርዝሮች እና ሌሎች የግንባታ ውሎች ያዘጋጃል ወይም እንዲዘጋጁ ያደርጋል፤”

3. የቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን ለሚያስገነባቸው ቤቶችና ተያያዥ ግንባታዎች በአግባቡ እየተገነቡ መሆኑን ለማረጋገጥ አስፈላጊውን ቁጥጥር ያደርጋል፤ ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፣ እንዲወሰድ ያደርጋል።”፤

የአዋጁ አንቀጽ 66 ንዑስ-አንቀጽ /16/ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ-አንቀጽ /16/ ተተክቷል፤

“16. ግንባታቸው ተጠናቆ የመጠቀሚያ ፈቃድ ያገኙ የመኖሪያ ቤቶችን በማስተላለፊያ ዋጋቸው ለተጠቃሚዎች በዕጣ ወይም በምደባ ያስተላልፋል፤ የቤቶቹን አስፈላጊ ሰነዶች በሙሉ ቤቱ ለደረሳቸው ባለመብቶች በወቅቱ ያስረክባል፤”፤

የአዋጁ አንቀጽ 66 ንዑስ-አንቀጽ /16/ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ-አንቀጽ /16/ ተተክቷል፤

“16. ለኪራይ አገልግሎት የሚውሉ ቤቶችን ያስገነባል፤ ያከራያል፣ ያስተዳድራል፤”፤

የአዋጁ አንቀጽ 63 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 63 ተተክቷል፤

“63. የኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

የከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ልማት ለማፋጠን እና ተወዳዳሪነታቸውን ለማረጋገጥ የሚረዱ የድጋፍ ማዕቀፎችን፣ መመሪያዎችን፣ ደንቦች እና አሰራሮችን ይቀርፃል፤ ተግባራዊ ያደርጋል፤ እንዲሁም በኢንዱስትሪው መስክ ቀጣይነት ያለው እድገት ለማረጋገጥ የፖሊሲ ግብአቶች የሚሆኑ ጥናቶች ያካሂዳል፤ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች በኢንዱስትሪው ዘርፍ እንዲሰማሩ የፕሮሞሽን ስራ ይሰራል፤ የኢንዱስትሪ መረጃዎችን ይሰበስባል፤ ያደራጃል፤ ይተነትናል፤ ለመረጃ ማዕከላትና ተጠቃሚዎች ያሰራጫል፤

በከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ለተሰማሩ እና ለሚሰማሩ ባለሃብቶች የፕሮጀክት ዝግጅትና አዋጭነት ጥናት ያካሂዳል፤ ስለቴክኖሎጂ መረጣ ምክር ይሰጣል፣ የፕሮጀክት ፕሮፋይሎችን ያዘጋጃል፤ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤

ወደ ኢንዱስትሪ መንደሮች የሚገቡ ፕሮጀክቶች የሀገሪቱን የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ ህጐችና ደንቦች መሰረት ያደረጉ እንዲሆኑ ያደርጋል፤ ከኢንዱስትሪ አልሚዎች ጋር ውል ይፈፅማል፤ በውሉ መሰረት መፈፀሙን ይቆጣጠራል፤

የኢንዱስትሪው ዘርፍ ልማት ለማፋጠንና ምርትና ምርታማነትን እንዲሁም የምርት ጥራትን ለማሣደግ የሚያስችል ጥናት ያካሂዳል፤ የቴክኖሎጂ ድጋፍ እንዲያገኙ ያመቻቻል፤ ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመሆን የደረጃ እና የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬቶች እንዲኖራቸው ይሰራል፤

በከፍተኛ ኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማሩት ባለሀብቶችና ተቋማት ስራቸው ውጤታማ በሆነ መልኩ ማካሄድ እንዲችሉ እና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የሚያስችላቸውን የፋይናንስ፣ የመሰረተ ልማት፣ የግብአት፣ የመስሪያ ቦታ፣ የሰለጠነ የሰው ሃይልና የገበያ ትስስር የሚያገኙበት ሁኔታ ያመቻቻል፣ ያስተባብራል፣ ስርዓት ይዘረጋል፣ ይመራል፤

የኢንዱስትሪዎችን የገበያ ችግር ለመቅረፍ ከተለያዩ አካላት ጋር የገበያ ትስስር እንዲፈጠርላቸው ያደርጋል፤ አውደ-ርዕይና ባዛሮችን በማዘጋጀትና በልሎች አካላት እንዲዘጋጁ በማድረግ ምርቶቻቸውንና አገልግሎታቸውን በከተማ ውስጥና ከሀገር ውጪ ለማስተዋወቅ እንዲችሉ ያደርጋል፤ እርስ በእርስ በግብአት አቅርቦት በምርትና በቴክኖሎጂ ትስስር እንዲፈጥሩ ያደርጋል፤

ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎችን ለማበረታታትና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ለማድረግ በጥናት ላይ የተመሰረተ የማበረታቻ፣ የዕውቅና እና የሽልማት ስርአት እንዲዘረጋ ያደርጋል፣ ተፈፃሚነቱን ያረጋግጣል፤

የኢንዱስትሪውን ምርትና ምርታማነት በቀጣይነት ሊያሣድጉ የሚችሉ የአቅም ግንባታ እና ችግር ፈቺ የጥናት ስራዎችን ያከናውናል፤ እንዲሁም የሰራተኞች የስራ ላይ ደህንነት፣ የአካባቢ ጥበቃና የኢንዱስትሪ ሰላም የሚያስጠብቁ ተግባራትን ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በጋራ ይሰራል፤ ያስተባብራል፤

ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ስትራተጂያዊ ጠቀሜታቸው ጉልህ የሆኑ ምርቶችን በአገር ውስጥ እንዲያመረቱ እንዲሁም የኤክስፖርት ምርቶችን እንዲያሳድጉ ድጋፍ ያደርጋል፤ ከሚመለከታቸው አካላትጋር በጋራ ይሰራል፤

የኢንዱስትሪ ዞኖች፣ ፓርኮች እንዲሁም ክላስተሮች እንዲለሙ እና እንዲስፋፉ ከሚመለክታቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ አካላት ጋር በጋራ ይሰራል፤

የውጪ ሀገር ኢንቨስተሮች ከሀገር ውስጥ ከፍተኛ ኢንዱስትሪ ባለሀብቶች ጋር ተቀናጅተው የሚሰሩበት ሁኔታ ያመቻቻል፤ የእውቀት፣ የክህሎት እንዲሁም የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲኖር የሚያስችሉ የአሰራር ሰርዓቶች ይዘረጋል፤ ያግዛል፣ ያስተባብራል፣ ይመራል፤

ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎችን ተከትለው ሊስፋፉ የሚችሉ ተያያዥ ኢንዱስትሪዎች በጥናት ይለያል፤ ያስተዋውቃል፤ የጥናቱን ውጤት ለሚመለከተው አካል ያሰራጫል፤

ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ለከፍተኛ ኢንዱስትሪ ዘርፍ አስፈላጊ የሆነ የስለጠነ የሰው ኃይል እና የግብዓት አቅርቦት አስተማማኝ በሆነ መልኩ ለማሟላት የሚያስችል ስልት ይቀይሳል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ተግባራዊ ያደርጋል።”

የአዋጁ አንቀጽ 31 ንዑስ-አንቀጽ /1/ ተራ ፊደል “ሠ” ተሠርዟል፤ የዚሁ ንዑስ-አንቀጽ (1) ተራ ፊደል (ረ) እና (ሰ) እንደቅደም ተከተላቸው ተራ ፊደል (ሠ) እና (ረ) ሆነዋል፤

የአዋጁ አንቀጽ 95 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፤

“ለከተማው ምክር ቤት ተጠሪ የሆኑት እና በከተማው ምክር ቤት በተሾሙ ኃላፊዎች የሚመሩ አስፈፃሚ አካላት ሣይጨምር ካቢኔው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ደንብ በማውጣት ሌላ አስፈፃሚ አካል እንዲታጠፍ፣ ከሌላ አስፈፃሚ አካል ጋር እንዲዋሃድ፣ እንዲከፋፈል ወይም ሥልጣንና ተግባሩ እንዲለወጥ በማድረግ፣ ወይም አዲስ አስፈፃሚ አካል የማቋቋምና የማደራጀት፣ የከተማውን የልማት ድርጅት የማቋቋምና እንደገና የማደራጀት፣ የማፍረስ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡”፤

በአዋጁ አንቀጽ 100 ንዑስ-አንቀጽ (3) ውስጥ “አንቀጽ 106” የሚለው “አንቀጽ 103” ተብሎ ይነበብ፤

በአዋጁ አንቀጽ 103 ንዑስ-አንቀጽ (11) ውስጥ “ ደንብ ቁጥር 3/1994” የሚለው “ ደንብ ቁጥር 3/1990 ” ተብሎ ይነበብ፤

በአዋጁ አንቀጽ 103 ንዑስ-አንቀጽ (30) ውስጥ “ አዋጅ ቁጥር 10/1993” የሚለው “ አዋጅ ቁጥር 10/1983 ” ተብሎ ይነበብ፤

68.የመብቶችና ግዴታዎች መተላለፍ

የንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ የንግድ ዘርፍን የሚመለከት መብትና ግዴታ ለንግድ ቢሮ፤ አነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስተሪዎችን የሚመለከት መብትና ግዴታ ለሥራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዝ ልማት ቢሮ፤ ከፍተኛ ኢንዱስትሪ ዘርፍን የሚመለከት መብትና ግዴታ ለኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ፤ እንዲሁም

በአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ ደንብ ቁጥር 83/2009 የተቋቋመው የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ክላስተር ልማት ኮርፖሬሽን መብትና ግዴታ ለመስሪያ ቦታዎች ልማትና አስተዳደር ኤጀንሲ፤

በዚህ አዋጅ ተላልፏል፡፡

69.አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከህዳር 20 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ህዳር 20 ቀን 2012 ዓ.ም

ታከለ ኡማ በንቲ

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚ አካላትን እንደገና ለማደራጀት፣ ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ፷፬/፪ሺ፲፩ን እንደገና ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር ፸/፪ሺ፲፪

<u>ማውጫ</u>

፩. አጭር ርዕስ

፪. ትርጓሜ

፫. ማሻሻያ

፬. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

<u>አጭር መግለጫ</u>

በከተማው ህዝባዊ መሠረት ያለው የስፖርትና የመዝናኛ ስፖርት አግልግሎት አደረጃጀትን በማጠናከር ፣ የስፖርትና መዝናኛ ቦታዎችን በማሟላት የህብረተሰቡን የስፖርትና የመዝናኛ ተሳትፎና ተጠቃሚነትን በማረጋገጥ በአካልና በአምዕሮ የዳበረ ጤናማ ዜጋ ለማፍራት የሚያስችል ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር የወጣ አዋጅ ነው፡፡

# አዋጅ ቁጥር ፸/፪ሺ፲፪
# የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚ አካላትን እንደገና ለማደራጀት፣ ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ቁጥር ፷፬/፪ሺ፲፩ እንደገና ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አጠቃላይ ሀገራዊ ለውጡን ተከትሎ አዳዲስ አሰራሮችን በመዘርጋት የነዋሪውን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ የተለያዩ ተግባራትን እያከናወነ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ የስፖርትና የመዝናኛ ስፖርት ተግባራትን ቀጣይነት እና ተቋማዊ አደረጃጀት ኖሯቸው ተጠናክረው እንዲንቀሳቀሱ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በከተማው ህዝባዊ መሠረት ያለው የስፖርትና የመዝናኛ ስፖርት አግልግሎት አደረጃጀትን በማጠናከር ፣ የስፖርትና መዝናኛ ቦታዎችን በማሟላት የህብረተሰቡን የስፖርትና የመዝናኛ ተሳትፎና ተጠቃሚነትን በማረጋገጥ በአካልና በአምዕሮ የዳበረ ጤናማ ዜጋ ለማፍራት የሚያስችል ምቹ ሁኔታ መፍጠር በማስፈልጉ፤

የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ ዓ.ም (እንደተሻሻለ) አንቀጽ ፲፬ ንዑስ አንቀጽ (፩) (ሀ) መሠረት ይህን ማሻሻያ አዋጅ አውጥቷል፡፡

፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ " የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚ አካላትን እንደገና ለማደራጀት፣ ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ፷፬/፪ሺ፲፩ን እንደገና ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር ፸/፪ሺ፲፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩) "አዋጅ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚ አካላትን እንደገና ለማደራጀት፣ ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ፷፬/፪ሺ፲፩ (እንደተሻሻለ) ነው፤

፪) በአዋጁ የተተረጎሙ ቃላትና ሐረጎች በዚህ አዋጅ ውስጥም ተፈጻሚነት አላቸው፡፡

፫. <u>ማሻሻያ</u>

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚ አካላትን እንደገና ለማደራጀት፣ ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር ፷፬/፪ሺ፲፩ (እንደተሻሻለ) እንደገና እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-

፩. ከአዋጁ አንቀጽ ፲፪ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተራ ፊደል (ከ) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ተራ ፊደል (ኸ) ተጨምሯል፤

"ኸ) የስፖርት ኮሚሽን "፡፡"፤

፪. የአዋጁ አንቀጽ ፲፪ ንዑስ አንቀጽ (፯) ተሰርዟል፤

፫. የአዋጁ አንቀጽ ፲፪ ከንዑስ አንቀጽ (፯) ጀምሮ ያሉት ንዑስ አንቀጾች እንደቅደም ተከተላቸው ተሸጋሽጓል፤

፬. የአዋጁ አንቀጽ ፳፱ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተሰርዟል፤

፭. የአዋጁ አንቀጽ ፳፱ ከንዑስ አንቀጽ (፪) ጀምሮ ያሉት ንዑስ አንቀጾች እንደቅደም ተከተላቸው ተሸጋሽገዋል፤

፮ የአዋጁ አንቀጽ ፴፰ ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፴፰ ተተክቷል፤

"፴፰. <u>የስፖርት ኮሚሽን</u>

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩) የከተማ አስተዳደሩን የስፖርት ትምህርትና ሥልጠና ማዕከላትን ያስተዳድራል፤ ይመራል፤ እንዲስፋፉና አቅማቸው እንዲገነባ ያደርጋል፤

፪) የከተማው ነዋሪ በስፖርት ለሁሉምና በባህላዊ ስፖርት ተሣታፊና ተጠቃሚ የሚሆንበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

፫) በስፖርት የሠለጠነ የሰው ኃይል ለማፍራት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ይሰራል፤

፬) የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎችንና ማበልፀጊያ ማዕከላት እንዲገነባ ያደርጋል፤ ያስተዳድራል፤

፭) ለስፖርት ተግባራት የሚውሉ የስፖርት ትጥቆችና መሣሪያዎች አቅርቦት የሚሟላበትን ሁኔታ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ያመቻቻል፤

፮) አግባብ ባለው ህግ የስፖርት ህክምና አገልግሎት መደራጀቱን፣ በስፖርት አበረታች መድሃኒቶችና ዕፆች መጠቀምን ለመከላከል የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋቱን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፤

፯) የስፖርት ማህበራት ስለሚቋቋሙበትና ማዘውተሪያ ስፍራ አጠቃቀምና አሰራር ሁኔታ መመሪያ ያወጣል፤ የስፖርት ማህበራትንና ክለቦችን እንዲሁም ጅምናዚየሞችን ይመዘግባል፤ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤

፰) በሳይንሳዊ ጥናት ላይ የተመሰረቱ የአካል ብቃት ማሰልጠኛ ዘዴዎችን በማዘጋጀት ስፖርተኞች፣ አሰልጣኞች የስፖርት ዳኞችና የመሳሰሉት እንዲሰለጥኑ ያደርጋል፤

፱) የከተማውን ነዋሪ የስፖርት ተሳትፎ ለማጎልበት ያቅዳል፤ ስፖርት ውድድሮች ያዘጋጃል፤ ይመራል፤ ከሚመለከተው ጋር በመተባበር የትምህርት ቤቶች የስፖርት ውድድር እንዲስፋፋና እንዲጠናከር ያደርጋል፤

፲) በውጭ ኦዲተር የተመረመረ የሂሳብ ሪፖርት ከየማህበሩ እንዲቀርብለት በማድረግ የስፖርት ማህበራት ገቢ ለአላማቸው ብቻ መዋሉን ያረጋግጣል፤

፲፩) የአስተዳደሩን የስፖርትና የመዝናኛ ምክር ቤት በየደረጃው በማቋቋም አግባብ ባለው ህግ አደረጃጀቱን ያጠናክራል፤ ይመራል፤ ይቆጣጠራል፤

፲፪) በከተማ ደረጃ የብዙሃን የአካል እንቅስቃሴ እና የስፖርት መዝናኛ አግልግሎቶች እንዲስፋፉ ያደርጋል፣ ያስተባብራል፤ ይመራል፤

፲፫) በስፖርትና በመዝናኛ ስፖርቶች አግልግሎት ዙሪያ ጥናትና ምርምር ያደረጋል፤ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፤ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፲፬) የመዝናኛ ፓርኮችን ከሚመለከተው አካል ጋር በመቀናጀት ለመዝናኛ ስፖርቶች በሚያመች ሁኔታ ያለማል፤ ጥቅም ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

፲፭) በተለያዩ ስፍራዎች የስፖርትና የመዝናኛ ትርዒቶች የሚከናወኑበትን ስልት ይቀይሳል፤ አደረጃጀት ይፈጥራል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፲፮) በከተማ ውስጥ በስፖርትና መዝናኛ ስፖርት አግልግሎት ለሚሰማሩ አካላትን ያበረታታል፤ የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፤

፲፯) የአካል ወይም የአምሮ ጉዳተኞች እና አረጋውያን የስፖርት እና የስፖርት መዝናኛ አግልግሎት እንደያገኙ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል፤

፲፰) ነዋሪው የመዝናኛ ስፖርቶችን ጠቀሜታ እንዲገነዘብ እና እንዲጠቀም ያበረታታል፤ ምቹ ሁኔታዎች ይፈጥራል፣

፲፱) በከተማው ደረጃ የስፖርት ልማት ፈንድ የሚቋቋምበትን ስልት ይቀይሳል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

፬. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከ ጥር ፲፮ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ጥር ፲፮ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም.

ታከለ ኡማ በንቲ

የአዲስ አበባ ከተማ ምክትል ከንቲባ

# የአዲስ አበባ ከተማ የትራንስፖርት ባለስልጣን አደረጃጀትና አሠራርን ለመወሰን የወጣ ደንብ ፸፩/፪ሺ፰ አጭር መግለጫ

<u>ማውጫ</u>


፩. አጭር ርዕስ

፪. ትርጓሜ

፫. የተፈፃሚነት ወሰን

፬. ዓላማዎች

፭. አደረጃጀት

፮. የትራንስፖርት ባለስልጣን ስልጣንናተግባር

፯. የቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ሥልጣንና ተግባር

፰. የዋና ሥራ አስኪያጁ ስልጣንና ተግባር

፱. የምክትል ሥራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባር

፲.የዋና ሥራ አስኪያጁ እና የምክትል ሥራ አስኪያጆች አሿሿም

፲፩. የመተባበር ግዴታ

፲፪. የበጀት ምንጭ

፲፫. የሂሳብ መዛግብት አያያዝ

፲፬. መመሪያ የማውጣት ስልጣን

፲፭. ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ህጎች

፲፮. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ


አጭር መግለጫ

የአዲስ አበባ ከተማ የህዝብና የጭነት ትራንስፖርትን በመረጃና በቴክኖሎጂ የተደገፈ፣ ፈጣን፣ ተደራሽ እና አስተማማኝ በማድረግ የከተማውን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ለማፋጠን እና ለህዝብና ለጭነት ትራንስፖርት አገልግሎት የሚዉል መሠረተ ልማት ለማስፋፋትና ለማስተዳደር የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፴፭/፪ሺ፬ን እንደገና ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር ፵፫/፪ሺ፯ አንቀጽ ፵፭ መሠረት የትራንስፖርት ባለስልጣን በመቋቋሙ አደረጃጀቱንና አሠራሩን ለመወሰን የወጣ ህግ ነው፡፡

## የአዲስ አበባ ከተማ የትራንስፖርት ባለስልጣን አደረጃጀትና አሠራርን ለመወሰን የወጣ ደንብ ፸፩/፪ሺ፰

የአዲስ አበባ ከተማ የህዝብና የጭነት ትራንስፖርትን በመረጃና በቴክኖሎጂ የተደገፈ፣ ፈጣን፣ ተደራሽ እና አስተማማኝ በማድረግ የከተማውን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ለማፋጠን፤ ለህዝብና ለጭነት ትራንስፖርት አገልግሎት የሚዉል መሠረተ ልማት ለማስፋፋትና ለማስተዳደር የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፴፭/፪ሺ፬ን እንደገና ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር ፵፫/፪ሺ፯ አንቀጽ ፵፰ መሠረት የትራንስፖርት ባለስልጣን በመቋቋሙ አደረጃጀቱንና አሠራሩን መወሰን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ አንቀፅ ፳፫(፩)(ረ) እና አዋጅ ቁጥር ፴፭/፪ሺ፬ አንቀጽ ፹፬ መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትራንስፖርት ባለስልጣን አደረጃጀትና አሠራርን ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር ፸፩/፪ሺ፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩. "**ከተማ**" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤

፪. "**ከንቲባ**" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርን የሚመራ ዋና አስፈጻሚ ነው፤

፫. "**አስተዳደር**" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፬. "**ቢሮ**" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንገድና ትራንስፖርት ቢሮነው፤

፭. "**ባለሥልጣን**" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ትራንስፖርት ባለሥልጣን ነው፤

፮. "**መንገድ**" ማለት ተሽከርካሪዎችና እግረኞች በተለምዶ የሚጠቀሙበት ማናቸውም አውራጎዳና የከተማ መንገድ ወይም መተላለፊያ ነው፤

፯. "**ትራፊክ**" ማለት በማናቸውም መንገድ አንድ ወይም ብዙ ሆነው የሚተላለፉ እግረኞች ወይም ሰው ተቀምጦባቸው ወይም እየተነዱ ወይም እየተጠበቁ የሚነዱ እንስሶችና ተሽከርካሪዎች ናቸው፤

፰. "**ተሽከርካሪ**" ማለት በመንገድ ላይ የሚሄድ ጋሪ፣ ሰረገላ፣ ብስክሌት፣ ባለሞተር ተሽከርካሪ፣ ግማሽ ተሳቢና ተሳቢ ነው፤

፱. "**ጭነት**" ማለት ማናቸውም ከሰው ውጪ የሆነ በተሽከርካሪ የሚጓጓዝ ግዑዝ ወይም ህይወት ያለው ነገር ማለት ነው፤

፲. "**ታሪፍ**" ማለት ትባለሥልጣኑ የህዝብ ትራንስፖርት ለሚሰጡት አካላት ለሚሰጡት አገልግሎት የሚወስነው የክፍያ ዋጋ መጠን ነው፤

፲፩. "**ተርሚናል**" ማለት ለሕዝብ እና ለንግድ የመንገድ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች አገልግሎት የሚውሉ መናኸሪያዎችና ማቆሚያ ቦታዎች ነው፤

፲፪. "**ዴፖ**" ማለት የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ አውቶቡሶች የሚያርፉበት የሰርቪስ እና የጥገና አገልግሎት የሚያገኙበት ሥፍራ ነው፤

፲፫. "**ሥምሪት**" ማለት የሕዝብ፣ የንግድ፣ የመንገድ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች የቀን እንቅስቃሴ ነው፤

፲፬. "**የሥምሪት ፕሮግራም**" ማለት የሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች የዓመት፣ የወር፣ የሣምንት ወይም የቀን እንቅስቃሴ የሚወስን ድልድል ነው፤

፲፭. "**የስምሪት መስመር**" ማለት በባለሥልጣኑ የሚወሰን የሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች የሥምሪት መነሻና መድረሻ ነው፤

፲፮. "**ተቋም**" ማለት የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት በሕግ የተቋቋመ አካልነው፤

፲፯. "**አዋጅ**" ማለት የአዋጅ ቁጥር ፴፭/፪ሺ፱ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር ፵፫/፪ሺ፯ ማለት ነው፤

፲፰. "**ማኀበር**" ማለት የህዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ስራ ላይ በተሰማሩ ሰዎችና ድርጅቶች የተቋቋመና የተመዘገበ ተቋም ማለት ነው፤

፲፱. "**ሰው**" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ማለት ነው፤

፳. "**መሰረተ ልማት**" ለህዝብና ለጭነት ትራንስፖርት አገልግሎት የሚያግዙ ፌርማታዎች፣ መናኸሪያዎች፣ ዴፖዎች እና ከእነዚህ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ያጠቃልላል፤

፳፩. በዚህ ደንብ ውስጥ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀ አነጋገር ሴትንም ይመለከታል፡፡

**፫. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>**

ይህ ደንብ በከተማው የህዝብና የጭነት ትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት ላይ በተሰማሩ ማኀበራት፣ ተቋማትና ግለሰቦች እና ማናቸውም ለዚህ አገልግሎት በሚውሉ የትራንስፖርት መሠረተ ልማቶች ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

**፬. <u>ዓላማዎች</u>**

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

፩. ፈጣንና ቀልጣፋ የህዝብና የጭነት ትራንስፖርት ተደራሽ መሆኑን ማረጋገጥ፤

፪. የተቀናጀ የህዝብና የጭነት ትራንስፖርት መሠረተ ልማት ማልማትና ማስተዳደር፤

፫. ለተገልጋዮች ፍትሃዊ፣ የተገልጋዩን የመክፈል አቅም ያገናዘበና ጥራት ያለው የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲሰጥ መሥራት፤

፬. በቴክኖሎጂ የተደገፈ የህዝብና የጭነት ትራንስፖርት መረጃ ማዕከል ማደራጀት፡፡

## ክፍል ሁለት

## አደረጃጀት፣ሥልጣንና ተግባር

### ፭. አደረጃጀት

ባለስልጣኑ ዋና ሥራ አስኪያጅና ምክትል ሥራ አስኪያጆች እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ የስራ ክፍሎችና ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

### ፮. የትራንስፖርት ባለስልጣን ስልጣንናተግባር

በአዋጁ ላይ የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩. በከተማው የብዙሃንና የጭነት ትራንስፖርትን በተመለከተ ተገቢውን መረጃ ያደራጃል፣ ያሰራጫል፤

፪. በከተማው የሚንቀሳቀሱ የብዙሃንና የጭነት ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪ አካላት አጠቃላይ የኦፕሬሽን ሥርዓታቸውን በበላይነት ይቆጣጠራል፣ ፈቃድ ይሰጣል እንዲሁም ያግዳል፤

፫. የከተማውን የተማከለ የብዙሃን ትራንስፖርት ሥርዓት እንዲፈጠር ያደርጋል፣የሥምሪት ድልድል የዘጋጃል፣ ታሪፍ አጥንቶ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፣ ሲጸድቅ ለተፈፃሚነቱም ይሠራል፣ ለአፈፃፀም የሚረዱ የቴክኖሎጂ አውታሮችንም ይዘረጋል፤

፬. የከተማውን የትራንስፖርት መሠረተ ልማት ማለትም ለህዝብና ለጭነት ተሽከርካሪዎች አገልግሎት የሚውሉ መናኽሪያዎችን፣ ፌርማታዎችን፣ መጋዘኖችና ዴፖዎችን ይገነባል፣ ያስተዳደራል፤

፭. አጠቃላይ የከተማው የብዙሃንና የጭነት ትራንስፖርትን በተመለከተ መመሪያዎች ያወጣል፣ ሲፈቀድለትም ይተገብራል፤

፮. የከተማውን የብዙሃንና የጭነት ትራንስፖርት አቅርቦትና ፍላጎት ያጠናል፣ አማራጭ መፍትሄዎችን በማቅረብ ለአቅርቦት መጣጣም ፕሮግራሞችን በመቅረጽ ይሠራል፤

፯. ለሕብረተሰቡ ተደራሽ የሆነ የትራንስፖርት መረጃ አገልግሎት ያደራጃል፣ ያሰራጫል፣ የከተማው የትራንስፖርት አገልግሎት በቅንጅት እንዲሰሩ ዕቅድ ያወጣል፤

፰. የከተማውን የብዙሃንና የጭነት ትራንስፖርት መመዘኛ መስፈርቶች፣ ማንዋሎች ደረጃዎች ያወጣል ለተፈፃሚነቱ ይሠራል፤

፱.ለሚሰጠው አገልግሎት ክፍያ ይሰበስባል፤

፲. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በብዙሃንና በጭነት ትራንስፖርት ዘርፍ የሚሰሩ ኦፕሬተሮች፣ ማኀበራት፣ ድርጅቶችና ግለሰቦች እንዲደራጁና እንዲጠናከሩ ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል፣ ለከተማው ትራንስፖርት ቅልጥፍናና ደህንነት መሥራታቸውንም ያረጋግጣል፡፡

፯. **የቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ሥልጣንና ተግባር**

የቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ተጠሪነቱ ለባለስልጣኑ ዋና ስራ አስኪያጅ ሆኖ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡-

፩. የህዝብና የጭነት ትራንስፖርት ሰጪ ማህበራትና ተቋማትን በተሰጣቸው ስምሪትና ፈቃድ መሰረት መስራታቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፤

፪. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በትራንስፖርት ዘርፍ የሚሠሩ ማኅበራት እንዲደራጁና እንዲጠናከሩ ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል፤ ማኅበራቱ ለከተማው ትራንስፖርት ቅልጥፍናና ደህንነት መሥራታቸውን ያረጋግጣል፤

፫. በከተማው አስተዳደር ለተሽከርካሪዎች አገልግሎት የሚውሉ መናኸሪያዎችን፣ ፌርማታዎችን ያስተዳድራል፤

፬. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፩፣ ፪ እና ፫ የተጠቀሱትን ተግባራት ክንውን ውጤት መሰረት የመረጃ ትንተና ያዘጋጃል፤

፭. ሌሎች ከባለስልጣኑ ተለይተው የሚሰጡት ተግባራትን ያከናውናል፡፡

፰. **የዋና ሥራ አስኪያጁ ስልጣንና ተግባር**

ዋና ሥራ አስኪያጁ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩. በአዋጁና በዚህ ደንብ መሠረት ለባለሥልጣኑ የተሰጡትን ስልጣንና ተግባራት ያከናውናል፤ ሀላፊነትና ግዴታዎችን ይወጣል፤

፪. የባለሥልጣኑን ስራዎች ያቅዳል፣ ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤

፫. ሠራተኞችን በመንግስት ሠራተኞች ህግ መሰረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፤

፬. ከሶስተኛ ወገኖች ጋር ለሚደረገው ግንኙነት ባለሥልጣኑን ይወክላል፤

፭. የባለሥልጣኑን የሥራ ዕቅዶችና ፕሮግራሞች እንዲሁም በጀት በማዘጋጀት በቢሮ አስገምግሞ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በስራ ላይ ያውላል፤

፮. ባለሥልጣኑን ውጤታማ ሊያደርጉ በሚያስችሉ ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች ላይ ትኩረት በማድረግ የአሰራር ሥርዓቶችን ይዘረጋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

፯. በቢሮ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

፱. **የምክትል ሥራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባር**

እያንዳንዱ ምክትል ሥራ አስኪያጅ ተጠሪነቱ ለዋና ሥራ አስኪያጁ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩. በባለሥልጣኑ የዕቅድ ዝግጅትና አፈጻጸም ሪፖርት ዝግጅት ዋናውን ሥራ አስኪያጅ በመደገፍ ይሠራል፤

፪. ተለይቶ ሲወከል ዋና ሥራ አስኪያጁ በሌለበት ወይም መሥራት በማይችልበት ጊዜ ዋናውን ሥራ አስኪያጅ ተክቶ ተግባራትን ይፈጽማል፤

፫. በዋና ስራ አስኪያጅ በሚደረግ የሥራ ምደባ መሰረት ምክትል ዋና ስራ አስኪያጆች የተሰጣቸውን ተግባራት ይፈጽማሉ፤

፬. ሌሎች በዋና ሥራ አስኪያጅ የሚሰጡ ተግባራትን ያከናዉናል፡፡

፲. <u>የዋና ሥራ አስኪያጁ እና የምክትል ሥራ አስኪያጆች አሿሿም</u>

የባለሥልጣኑ ዋና ሥራ አስኪያጅ እና ምክትል ሥራ አስኪያጆች በከንቲባው ይሾማሉ፡፡

## <u>ክፍል ሶስት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

፲፩. <u>የመተባበር ግዴታ</u>

ማንኛውም ሰው የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች ስራ ላይ ለማዋል ከባለሥልጣኑ ጋር የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

፲፪. <u>የበጀት ምንጭ</u>

የባለሥልጣኑ በጀት በከተማው አስተዳደር የሚመደብ ይሆናል፡፡

፲፫. <u>የሂሳብ መዛግብት አያያዝ</u>

፩. ባለሥልጣኑ በከተማው አስተዳደር የፋይናንስ አስተዳደር ሕግ መሰረት የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፤

፪. የባለሥልጣኑ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በከተማው አስተዳደር ዋናው ኦዲተር መስሪያ ቤት ይመረመራሉ፡፡

፲፬. <u>መመሪያ የማውጣት ስልጣን</u>

ይህንን ደንብ ስራ ላይ ለማዋል ቢሮው መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፲፭. <u>ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ህጎች</u>

ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

፲፮. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ ከመስከረም ፪ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ**

**ጳጉሜ ፮ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም**

**ድሪባ ኩማ**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ አደረጃጀትና አሰራርን ለመወሰን የወጣ ደንብ ፸፪/፪ሺ፰ አጭር መግለጫ

**ማውጫ**

፩. አጭር ርዕስ

፪. ትርጓሜ

፫. የፆታ አገላለፅ

፬. የተፈፃሚነት ወሰን

፭. ዋና መስሪያ ቤት

፮. ዓላማዎች

፯. የኤጀንሲው አደረጃጀት

፰. የኤጀንሲዉ ሥልጣንና ተግባር

፱.የቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ሥልጣንና ተግባር

፲.የዋና ዳይሬክተሩ ስልጣንና ተግባር

፲፩. የምክትል ዳይሬክተሮች ስልጣንና ተግባራት

፲፪. የዋና ዳይሬክተሩና ምክትል ዳይሬክተሮች አሿሿም

፲፫. የመተባበር ግዴታ

፲፬. በጀት

፲፭. የሂሳብ መዛግብት አያያዝ

፲፮.መመሪያ የማውጣት ስልጣን

፲፯. ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ህጎች

፲፰. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

<u>አጭር መግለጫ</u>

በመረጃ እና በቴክኖሎጂ የተደገፈ የትራፊክ አመራር ስርዓት ለመዘርጋት፣ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ቦታዎችን በመለየት ለማልማት፣ ለማስፋፋትና ለማስተዳደር በማስፈለጉ እና የከተማውን የትራፊክ መረጃ መሰረት ያደረገ የህብረተሰብ ግንዛቤ በመፍጠር የትራፊክ ደህንነትን ለማረጋገጥ የትራፊክ ሕግን በአግባቡ ማስከበር አስፈላጊ በመሆኑ የወጣ ህግ ነው፡፡

<u>**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ አደረጃጀትና አሰራርን ለመወሰን የወጣ ደንብ ፸፪/፪ሺ፰**</u>

የከተማውን ትራፊክ ፍሰት ለማሳለጥና ተደራሽ ለማድረግ፣ የመንገድ ትራፊክ ደህንነቱን ችግር መፍታት በማስፈለጉ፤

በመረጃ እና በቴክኖሎጂ የተደገፈ የትራፊክ አመራር ስርዓት ለመዘርጋት፣ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ቦታዎችን በመለየት ለማልማት፣ ለማስፋፋትና ለማስተዳደር በማስፈለጉ፤

እንዲሁም የከተማውን የትራፊክ መረጃ መሰረት ያደረገ የህብረተሰብ ግንዛቤ በመፍጠር የትራፊክ ደህንነትን ለማረጋገጥ የትራፊክ ሕግን በአግባቡ ማስከበር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ በአዋጅ ቁጥር ፺፫/፪ሺ፯ አንቀጽ ፺፯ ድንጋጌ መሰረት የተቋቋመና ስልጣንና ተግባራት የተደነገገ በመሆኑ፤

በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ አንቀፅ ፳፫(፩) (ረ) እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላትን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር ፴፭/፪ሺ፬ አንቀጽ ፹፬ ድንጋጌ መሰረት የከተማው አስተዳደር ካቢኔ ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

<u>**ክፍል አንድ**</u>

<u>**ጠቅላላ ድንጋጌዎች**</u>

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ ደንብ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ አደረጃጀትና አሰራርን ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር ፸፪/፪ሺ፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. <u>ትርጓሜ</u>**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩. ‹‹**ከተማ**›› ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤

፪.‹‹**አስተዳደር**›› ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፫. ‹‹**ቢሮ**›› ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንገድና ትራንስፖርት ቢሮ ነው፤

፬.‹‹**ኤጀንሲ**›› ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ ነው፤

፭. ‹‹**መንገድ**›› ማለት ለማናቸውም ተላላፊ ክፍት ካልሆነ የግል መንገድ በስተቀር ተሽከርካሪዎች በተለምዶ የሚጠቀሙበት ማናቸውም ጎዳና፣ የከተማ መንገድ፣ አውራ ጎዳና ወይም መተላለፊያ ነው፤

፮. ‹‹**ትራፊክ**›› ማለት በማናቸውም መንገድ ላይ አንድ ወይም ብዙ ሆነው የሚተላለፉ እግረኞች፣ እንስሶችና ተሽከርካሪዎች ናቸው፤

፯.‹‹**ተሽከርካሪ**›› ማለት በመንገድ ላይ የሚሄድ ጋሪ፣ ሰረገላ፣ ብስክሌት፣ ባለሞተር ተሽከርካሪ፣ ግማሽ ተሳቢና፣ ተሳቢ ናቸው፤

፰. ‹‹**የትራፊክ ስርዓት**›› ማለት በአንድ በተወሰነ ቦታ የሚደረግ የትራፊክ እንቅስቃሴና እንቅስ ቃሴው የሚመራበት የሰው ሃይል፣ የመሣሪያዎ ችና የአሠራር አግባብ ቅንጅት ነው፤

፱. ‹‹**አዋጅ**›› ማለት የአዋጅ ቁጥር ፴፭/፪ሺ፬ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር ፵፫/፪ሺ፯ ነው ፤

፲. ‹‹**ሰው**›› ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

**፫. <u>የፆታ አገላለፅ</u>**

በዚህ ደንብ ውስጥ አገባቡ ልዩ ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው አነጋገር ለሴትም ጾታ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**፬. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>**

ይህ ደንብ በከተማው አስተዳደር የትራፊክ እንቅስቃሴዎችና የተሽከርካሪ ማቆሚያ ቦታዎች ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

**፭. <u>ዋና መስሪያ ቤት</u>**

፩. የኤጀንሲው ዋና መስሪያ ቤት በከተማ በማዕከል ይሆናል፤

፪. እንደ አስፈላጊነቱም በከተማው የተለያዩ ቦታዎች ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

**፮. <u>ዓላማዎች</u>**

ኤጀንሲው የሚከተሉት አላማዎች ይኖሩታል፡-

፩. የከተማውን ትራፊክ ፍሰት የተሳለጠና ደህንነቱ የተጠበቀ ማድረግ፤

፪. ማናቸውንም የመንገድ ትራፊክ መረጃዎችን ማደራጀትና ተደራሽ ማድረግ ፤

፫.ድንገተኛ የከተማ ትራፊክ ክስተት ሲያጋጥም አፋጣኝ መፍትሄ መስጠት፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባር</u>

**፯. <u>የኤጀንሲው አደረጃጀት</u>**

፩. ዋና ዳይሬክተር፤

፪. ሁለት ምክትል ዳይሬክተሮች፤ እና

፫. አስፈላጊ የስራ ክፍሎችና ሰራተኞች ይኖሩታል፡፡

**፰. <u>የኤጀንሲዉ ሥልጣንና ተግባር</u>**

ኤጀንሲው በአዋጁ የተሰጡ ግዴታዎችን ተፈጻሚ ለማድረግ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩. በትራፊክ ደንብ ተላላፊዎች ላይ በሕግ መሠረት የሚጣል ቅጣት ራሱ ወይም ውክ ልና በሚሰጠው ተቋም አማካኝነት በከተማው አስተዳደር የፋይናንስ ሕግ መሠረት ይሰበስባል፤

፪. የከተማውን ትራፊክ አመራርና አስተዳደር ሥራ ይፈጽማል፣ በበላይነት ይቆጣጠራል፣ ለአገልግሎቱ ሥልጠት የሚያግዙ ስልቶችን ይቀይሳል፣ ይተገብራል፤

፫. ስለከተማ አስተዳደሩ ትራንስፖርት አገልግ ሎት እንዲሁም የትራፊክ ሥርዓት ለሚመለከ ታቸው አካላት መድረኮችን በማመቻቸት ግንዛቤ ይፈጥራል፤

፬. የትራፊክ ኢንጂነሪንግ ሥራዎች ይሠራል፣ ችግር ያለባቸውን መንገዶች በመለየት የዲዛይን፣ የምልክት አመላካች ሥራዎች እንዲሚሉ ያደርጋል፤

፭. የፖርኪንግ አገልግሎት ፈቃድ ያድሳል፣ ፖርኪንግ መናኸሪያዎችን አገልግሎት ያስፋ ፋል፣ የተሽከርካሪ ፍሰት ይቆጣጠራል፣ከትራንስፖርት ባለስልጣን ጋር በመተባበር የጭነት መንቀሳቀሻ ፈቃድ ቁጥጥር ሥርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊም ያደርጋል፤

፮. የመንገድ ትራፊክ ክስተት መረጃ ያደራጃል ያሰራጫል፣ ለሚመለከታቸው አካላት የሥልጠና ተግባራትን ያከናውናል፤

፯. የትራፊክ ትምህርታዊ ፕሮግራሞችን በማዘጋ ጀት ለህብረተሰቡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ይሰራል፤

፰. የከተማው ትራፊክ ስርዓት ማሻሻል የሚረ ዱት የቴክኖሎጂ አውታሮችን ይዘረጋል፣ ያስተዳድራል፣ ተደራሽነታቸውንም ያረጋግ ጣል፤

፱. ከትራፊክ አመራር እና ደህንነት ጋር የተያያዙ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

**፱.የቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ሥልጣንና ተግባር**

ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ተጠሪነቱ ለኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር ሆኖ የሚከተሉትን ተግባራት ይፈፀ ማል፡-

፩. የትራፊክ ትምህርታዊ ፕሮግራሞችን በማዘ ጋጀት ለህብረተሰቡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ይሰራል፤

፪. የከተማውን የመንገድ ትራፊክ ይቆጣጠራል፣ በትራፊክ ደንብ ተላላፊዎች ላይ በሕግ መሠረት የሚጣል ቅጣት ራሱ ወይም ውክ ልና በሚሰጠው ተቋም አማካኝነት በከተማው አስተዳደር የፋይናንስ ሕግ መሠረት ይሰበስባል፤

፫. ሌሎች ከኤጀንሲው ተለይተው የሚሰጡት ተግባራትን ያከናውናል፡

**፲.የዋና ዳይሬክተሩ ስልጣንና ተግባር**

ዋና ዳይሬክተሩ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩. በአዋጁና በዚህ ደንብ መሠረት ለኤጀንሲው የተሰጡትን ስልጣን፣ ተግባራትና ሀላፊነቶች ያከናውናል፤

፪. የኤጀንሲውን ስራዎች ያቅዳል፣ ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤

፫. ሠራተኞችንና ዝቅተኛ የስራ ሃላፊዎችን በህጉ መሰረት ይቀጥራል፣ ያሰናብታል፤

፬. ከሶስተኛ ወገኖች ጋር ለሚደረገው ግንኙነት ኤጀንሲውን ይወክላል፤

፭. የኤጀንሲውን የሥራ ዕቅዶችና ፕሮግራሞች እንዲሁም በጀት በማዘጋጀት በቢሮው አስገምግሞ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

፮. ኤጀንሲውን ውጤታማ ሊያደርጉ በሚያስችል ስትራተጂያዊ ጉዳዮች ላይ ትኩረት በማድረግ የአሰራር ሥርዓቶችን ይዘረጋል አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

፯. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የስራ ድርሻውን ለምክትል ዳይሬክተሮቹ በውክልና ሊያስተ ላልፍ ይችላል፣

፰. በቢሮው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

## ፲፩. የምክትል ዳይሬክተሮች ስልጣንና ተግባራት

ተጠሪነታቸዉ ለዋና ዳይሬክተሩ ሆኖ ምክትል ዳይሬክተሮች የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖራቸዋል፡-

፩. የኤጀንሲዉን ዕቅድ በማዘጋጀትና ተግባርና ሀላፊነትን ለመወጣት ዋና ዳይሬክተሩን በማገዝ ይሠራሉ፤

፪.የኤጀንሲዉ ዋና ዳይሬክተር በሌለበት በእርሱ ተለይቶ የተወከለዉ ተክቶ ይሠራል፤

፫. የተመደቡበትን የሥራ ክፍልና ዘርፍ ዕቅድ በማዘጋጀት ለኤጀንሲዉ ያቀርባል፣ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋሉ፤

፬. ሌሎች ከዋና ዳይሬክተሩ የሚሰጡ ተግባራ ትን ያከናዉናሉ፡፡

## ፲፪. የዋና ዳይሬክተሩና ምክትል ዳይሬክተሮች አሿሿም

የኤጀንሲዉ ዋና ዳይሬክተርና ምክትል ዳይሬክተሮች በከተማዉ ከንቲባ ይሾማሉ፡፡

## ክፍል ሶስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## ፲፫. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች ስራ ላይ ለማዋል የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

## ፲፬. በጀት

የኤጀንሲው በጀት በከተማው አስተዳደር ይመደባል፡፡

## ፲፭. የሂሳብ መዛግብት አያያዝ

፩. ኤጀንሲው በከተማው አስተዳደር የፋይናንስ አስተዳደር ሕግ መሰረት የተሟላና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፤

፪. የኤጀንሲው የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በከተማው አስተዳደር ዋናው ኦዲተር ይመረመራሉ፡፡

**<u>፲፮.መመሪያ የማውጣት ስልጣን</u>**

ይህንን ደንብ ስራ ላይ ለማዋል ቢሮው መመሪያ የማውጣት ስልጣን ይኖረዋል፡፡

**<u>፲፯. ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ህጎች</u>**

፩. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተሽከርካሪዎች ማቆሚያና ጥበቃ አገልግሎት የኅብረት ሥራ ማኅበር ማደራጃ ደንብ ቁጥር ፲፩/፪ሺ፩ በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

፪. ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማኛውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖ ረውም፡፡

**<u>፲፰. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ ከመስከረም ፫ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ**

**ጳጉሜ ፮ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም**

**ድሪባ ኩማ**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን አደረጃጀትና አሠራርን ለመወሰን የወጣ ደንብ ፸፫/፪ሺ፰ አጭር መግለጫ

<u>ማውጫ</u>

፩. አጭር ርዕስ

፪. ትርጓሜ

፫. የተፈፃሚነት ወሰን

፬. አደረጃጀትና ተጠሪነት

፭. የባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባር

፮. የቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ሥልጣንና ተግባር

፯. የባለሥልጣኑ ዋና ሥራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባራት

፰.የምክትል ዋና ስራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባር

፱. የዋና ሥራ አስኪያጁ እና የምክትል ሥራ አስኪያጆች አሿሿም

፲. የመተባበር ግዴታ

፲፩. የበጀት ምንጭ

፲፪.የሂሳብ መዛግብት አያያዝ

፲፫. መመሪያ የማውጣትሥልጣን

፲፬. ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ህጎች

፲፭. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

አጭር መግለጫ

በከተማችን እየተሰጠ ያለውን የአሽከርካሪ፣ ተሽከርካሪ እና ከእነዚህ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ተቋማ ትን ብቃት ለማረጋገጥና ፈቃድ ለመስጠት፣ በቴክኖ ሎጂ በማደራጀት ግልፅ፣ ጥራት ያለው፣ ቀልጣፋና ተደራሽ አገልግሎት በመስጠት ብቃት ያለው አሽከርካሪና ተሽከርካሪ እንዲኖር ለማድረግ የወጣ ህግ ነው፡፡

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን አደረጃጀትና አሠራርን ለመወሰን የወጣ ደንብ ፸፫/፪ሺ፰

በከተማችን እየተሰጠ ያለውን የአሽከርካሪ፣ ተሽከርካሪ እና ከእነዚህ  ጋር ተያያዥነት ያላቸው ተቋማ ትን ብቃት ለማረጋገጥና ፈቃድ ለመስጠት፣ በቴክኖ ሎጂ በማደራጀት ግልፅ፣ ጥራት ያለው፣ ቀልጣፋና ተደራሽ አገልግሎት በመስጠት ብቃት ያለው አሽከርካሪና ተሽከርካሪ እንዲኖር ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

እንዲሁም ከአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት ለመምራት፣ ለማስተባበር፣ አቅማቸውን ለማሳደግ እና አፈጻጸማቸውን መከታተልና መቆጣጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ እንዲሁም የህብረተሰቡን ደህንነት ለመጠበቅና ተጠቃሚነቱን ለማረጋገጥ፤

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የማዘጋጃ ቤታዊና አስፈጻሚ አካላትን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር ፵፫/፪ሺ፯ አንቀጽ ፵፮ መሰረት የአሽከ ርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን ተቋቁሞ ሥልጣንና ተግባሩ የተደነገገ ሲሆን አደረጃ ጀቱንና አሠራሩን መወሰን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፺፭ አንቀፅ ፳፫(፩)(ረ) መሰረት ይህንን ደንብ አውጥ ቷል፡፡

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን አደረጃጀትና አሠራር ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር ፸፫/፪ሺ፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ  በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩. "**ከተማ**" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤

፪. "**ክንቲባ**" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ነው፤

፫. "**አስተዳደር**" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፬. "**ቢሮ**" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንገድና ትራንስፖርት ቢሮ ነው፤

፭. "**ባለሥልጣን**" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ  የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን ነው፤

፮."**ተሽከርካሪ**" ማለት በመንገድ ላይ የሚሄድ ባለሞተር ተሽከርካሪ፣ ግማሽ ተሳቢና ተሳቢ ነው፤

፯. **"ተቋም"** ማለት የአሽከርካሪና የተሽከርካሪ ጋር ተያይዞ ያሉ አገልግሎቶችን ለመስጠት ህጋዊ ፈቃድ አውጥቶ የሚሰራ የተሽከርካሪ መመርመሪያ፣ጋራዥ፣ ጎሚስታ፣ የመኪና እጥበት፣ የአሽከርካሪ ማሰልጠኛ እና ተያያዥ አገልግሎት የሚሰጥ አካል ነው፤

፰. **"አዋጅ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፴፭/፪ሺ፬ እና ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር ፵፫/፪ሺ፯ ነው፤

፱. **"ምዝገባ የተደረገለት ተሽከርካሪ"** ማለት ተፈላጊ ሰነዶች መሟላታቸው ተረጋግጦ በባለንብረቱ ስም ምዝገባ የተደረገለት ተሽከርካሪ ነው፤

፲. **"መንገድ"** ማለት ለተላላፊ ክፍት ካልሆነ የግል መንገድ በስተቀር ተሽከርካሪዎች በተለምዶ የሚጠቀሙበት ጎዳና፣ የከተማ መንገድ ወይም መተላለፊያ ነዉ፤

፲፩. **"ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት"** ማለት የባለስልጣኑን ህጎች የሚያስፈፅም እና አገልግሎቶችን የሚሰጥ አካል ነው፤

፲፪. **"የተሽከርካሪ ምርመራ"** ማለት አንድ ተሽከርካሪ በመንገድ ላይ የቴክኒክ ብቃትና ምቾት ያለው መሆኑና መንቀሳቀስ የመቻል ብቃቱን ለማረጋገጥ የሚደረግ የቴክኒክ ምርመራ ነው፤

፲፫. **"የመንጃ ፈቃድ"** ማለት ባለሞተር ተሽከርካሪዎ ችን ለመንዳት የሚያስችል ከዚህ ደንብ መውጣት በፊት የተሰጡት እንደተጠበቁ ሆኖ በዚህ ደንብ እና ደንቡን መሰረት በማድረግ በሚወጣ መመ ሪያ መሰረት የሚሰጥ ፍቃድ ነው፤

፲፬. **"ንድፈ ሃሳብ ፈተና"** ማለት የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋጋጫ ለመስጠት መሰረታዊ የሆነ የማሽከርከር እውቀት ለመመዘን የሚሰጥ የጽሁፍ ፈተና ነው፤

፲፭.**"የተግባር ፈተና"** ማለት የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋጋጫ ለመስጠት መሰረታዊ የሆነ የተግባር የማሽከርከር ችሎታ ለመመዘን የሚሰጥ ፈተና ነው፤

፲፮. **"ማሰልጠኛ ተቋም"** ማለት በህግ እውቅና ያለው መንግስታዊ ወይም የግል የአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋም ነው፤

፲፯. **"ማዕከል"** ማለት የአሽከርካሪ የብቃት ማረጋጋጫ አገልግሎት ለመስጠት በህግ የተቋቋመ ነው፤

፲፰.**"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ማለት ነው፤

፲፱. በዚህ ደንብ ውስጥ በልዩ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር በወንድ ጾታ የተገለጸው አገላለጽ ለሴትም ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**፫. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>**

ይህ ደንብ በከተማው የአሽከርካሪና የተሽከርካሪ ብቃት የማረጋገጥና፣ የፈቃድ አገልግሎት መስጠት ላይ በተሰማሩ ተቋማት፣ ግለሰቦች፣ የተሽከርካሪ አካላት ጥገና ሥራ ላይ የተሰማሩ ተቋማት እና ማናቸውም ለዚህ አገልግሎት በሚውሉ መሠረተ ልማቶች ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

## ክፍል ሁለት

## አደረጃጀት፣ሥልጣንና ተግባር

### ፬. አደረጃጀትና ተጠሪነት

ባለስልጣኑ የሚከተለው አደረጃጀት ይኖረዋል፡-

፩. ሥራ አስኪያጅና ሁለት ምክትል ሥራ አስኪ ያጆች፣ በመንግሥት ሠራተኞች ህግ የሚተዳደሩ አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞችና የስራ ክፍሎች ይኖሩታል፡፡

፪. የባለስልጣኑ ዋና መስሪያ ቤት አዲስ አበባ ከተማ በማዕከል ደረጃ ሆኖ፤ እንደአስፈላጊ ነቱም ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት በከተማው ውስጥ ሊኖረው ይችላል፡፡

### ፭. የባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባር

በአዋጁ የተደነገገዉ እንዳለ ሆኖ ባለስልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩. የተሽከርካሪ ዓመታዊ ምርመራ በራሱ ወይም በሕግ አግባብ ውክልና በሠጠው አካል ያካሂዳል፤የብቃት ደረጃ በማያሟሉ ተሽከርካሪ ዎች ላይ ተገቢ እርምጃ ይወስዳል፤

፪. የትራንስፖርት ደንብና ህግ የሚተላለፉ አሽከርካሪዎች ላይ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፤

፫. የባለሞተር ተሽከርካሪዎችን የማሽከርከር ሥልጠና ለሚሰጡ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች የሥራ ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፣ አግባብነት የሌለው ተግባር ሲፈጸም ተገቢውን የዕርምት እርምጃ ይወስዳል፤

፬. በተሽከርካሪ ምርመራ አገልግሎት ላይ ለሚሰማሩ ተቋማት፣ በአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋማት አገልግሎት ላይ ለሚሰማሩ ተቋማት እንዲሁም በጋራዥና በጎሚስታ አገልግሎት ለሚሰማሩ ግለሰቦችም ሆነ ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይሰጣል አስፈላጊውን ቁጥ ጥር ያደርጋል፤

፭. የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ መረጃዎችን በተመራጭ ቴክኖሎጂ በመታገዝ ያደራጃል፣ ያሰራ ጫል፣ እንደ አስፈላጊነቱም ስራ ላይ እንዲ ውሉ ያደርጋል፤

፮. ከአሽከርካሪና ከተሽከርካሪ ጋር ተያይዞ ያሉ አገልግሎቶችን ሊያሻሽሉ የሚችሉ የጥናትና ምርምር ስራዎችን ያከናውናል፤

፯. ሌሎችም ከአሽከርካሪና ከተሽከርካሪ ጉዳዮች ጋር የተያያዙ ተግባራት ያከናውናል፡፡

### ፮. የቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ሥልጣንና ተግባር

በአዋጁ ለባለስልጣኑ የተሰጠው ሥልጣን እንደተ ጠበቀ ሆኖ የቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት የሚከተ ለው ስልጣንና ተግባር ይኖረዋል፡-

፩. የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ብቃት ያረጋግጣል፣ እንዲሁም ተገቢውን ገቢ ይሰበስባል፤

፪. ተሽከርካሪዎችን ይመዘግባል፣ የሥም ዝውውር አገልግሎቶችን ያከናውናል፤ ከዚህ ጋር የተያያዙ የአገልግሎት ክፍያዎችን ይሰበስባል፤

፫. የንድፈ ሀሳብና የተግባር ፈተና ይሰጣል፤

፬. የአሽከርካሪነት ብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፣ ያድሳል ፣ የአገልግሎት ክፍያ ይሰበስባል፤

፫. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፩ እና ፪ የተጠቀ ሱትን ተግባራት ክንውን ውጤት መሰረት የመረጃ ትንተና ያዘጋጃል፣ለአገልግሎቱ ክፍያ ይሰበስባል፤ የተገኘውን ገቢ ኦዲት ያደርጋል፤

፬. ሌሎች ከባለስልጣኑ ተለይተው የሚሰጡ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ፬. የባለሥልጣኑ ዋና ሥራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባራት

፩. የባለስልጣኑን ሥራ በበላይነት ያቅዳል፣ ያደ ራጃል፣ ይመራል፣ያስተዳድራል፣ይቆጣጠራል፣ አፈጻጸሙን ይገመግማል፤

፪. የባለሥልጣኑን የሥራ ዕቅዶችና ፕሮግራሞች እንዲሁም በጀት በማዘጋጀት ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

፫. ባለስልጣኑ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርገው ማናቸውም ስምምነቶች ባለስልጣኑን በመወከል ይፈራረማል፣ ውሎቹና ስምምነቶቹ ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል፤

፬. ባለስልጣኑን ውጤታማ ሊያደርጉ በሚያስችሉ ስትራተጂያዊ ጉዳዮች ላይ ትኩረት በማድረግ የአሰራር ሥርዓቶችን ይዘረጋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

፭. የባለስልጣኑን ፋይናንስ ያንቀሳቅሳል፣ ወጪዎ ችን ይፈቅዳል፣ ያጸድቃል፣ የፋይናንስ እና ንብረት አያያዝና አጠቃቀም በመመሪያው መሠረት መተግበሩን ያረጋግጣል፤

፮. የተለያዩ የለውጥ እርምጃዎች ተግባራዊ መደረጋ ቸውንና ለተቋሙ ያስገኙትን ውጤት ይገምግ ማል፣ሊወሰዱ የሚገባቸው እርምጃዎች ይወስ ዳል ከአቅም በላይ የሆኑትን ጉዳዮች የውሳኔ ሐሳብ ለቢሮው ያቀርባል፣ ሲወሰንም ተግባራዊ ያደረጋል፤

፯. አዳዲስ የዕውቀትና የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲ ኖር ተሞክሮ ከሚወሰድባቸው የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ተቋማት ጋር የቻርተሩን ድንጋጌ በማክበር ተገቢውን ግንኙነት ይመሠርታል፤

፰. የተሻሻሉ አዳዲስ የአሰራር ዘዴዎችን በመቀየስና ሠራተኞችን በማወያየት ተግባራዊ የሚሆኑበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

፱. በሥራው ሂደት ላይ የሚመክርና በሥራ ግምገ ማዎች በዕቅዶችና ውሣኔዎች ላይ የሚወያይ የማኔጅመንት ኮሚቴ ያቋቁማል፣ ስብሰባውን ይመራል፤ ውሳኔዎችን ያስተላልፋል፤

፲. ሠራተኞችና የስራ ሃላፊዎችን በህጉ መሰረት ይቀጥራል፣ ያሰናብታል፤

፲፩. ሌሎች ከቢሮዉ ተለይተው የሚሰጡት ተግባራ ትን ያከናውናል፡፡

## ፰.የምክትል ዋና ስራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባር

እያንዳንዱ ምክትል ሥራ አስኪያጅ ተጠሪነቱ ለዋና ሥራ አስኪያጁ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣ ንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩. በባለሥልጣኑ የዕቅድ ዝግጅትና አፈጻጸም ሪፖርት ዝግጅት ዋናውን ሥራ አስኪያጅ በመደገፍ ይሠራል፤

፪. ተለይቶ ሲወከል ዋና ሥራ አስኪያጁ በሌለበት ወይም መሥራት በማይችልበት ጊዜ ዋናውን ሥራ አስኪያጅ ተክቶ ተግባራትን ይፈጽማል፤

፫. በዋና ስራ አስኪያጅ በሚደረግ የሥራ ምደባ መሰረት ምክትል ዋና ስራ አስኪያጆች የተሰ ጣቸውን ተግባራት ይፈጽማሉ፤

፬. ሌሎች በዋና ሥራ አስኪያጅ የሚሰጡ ተግባ ራትን ያከናዉናል፡፡

**፱. <u>የዋና ሥራ አስኪያጁ እና የምክትል ሥራ አስኪያጆች አሿሿም</u>**

የባለሥልጣኑ ዋና ሥራ አስኪያጅ እና ምክትል ሥራ አስኪያጆች በከንቲባው ይሾማሉ፡፡

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

**፲. <u>የመተባበር ግዴታ</u>**

ማንኛውም ሰው የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች ስራ ላይ ለማዋል የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

**፲፩. <u>የበጀት ምንጭ</u>**

የባለሥልጣኑ በጀት በከተማው አስተዳደር ይመደባል፡፡

**<u>፲፪.የሂሳብ መዛግብት አያያዝ</u>**

፩. ባለሥልጣኑ በከተማው አስተዳደር የፋይናንስ አስተዳደር ሕግ መሰረት የተሟላና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፤

፪. የባለሥልጣኑ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በከተማው አስተዳደር ዋና ኦዲተር እና በውስጥ ኦዲተር ይመረመራሉ፡፡

**፲፫. <u>መመሪያ የማውጣትሥልጣን</u>**

ቢሮው ይህንን ደንብ ሥራ ላይ ለማዋል መመሪያ የማውጣት ሥልጣን አለው፡፡

**፲፬. <u>ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ህጎች</u>**

ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማኛውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

**፲፭. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ ከመስከረም ፫ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ**

**ጳጉሜ ፮ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም**

**ድሪባ ኩማ**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤቶች ዳኞች መከተል ስለሚገባቸው ሥነ-ምግባር ለመወሰን የወጣ ደንብ ፳/፪ሺ፩ አጭር ርዕስ

አጭር መግለጫ

የዳኝነት ነፃነት ሊጠበቅ የሚችለው ዳኞች በዳኝነት ሥራቸውም ሆነ በግል ህይወታቸው አርአያነት ያለው ከፍተኛ ሥነ-ምግባር ሲያሳዩ ብቻ መሆኑን በማመን፤ዳኞች በአኗኗራቸውና በዕለት ተዕለት ተግባራቸው ሊከተሏቸው የሚገባ የዳኝነት ሥራ አፈፃፀምና ሥነ-ምግባር ደንብ እንዲሁም በዳኞች ላይ የሚቀርቡ የዲስፕሊን አቤቱታዎች የሚመሩበትን ሥነ-ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑና የዲስፕሊን ክስ የቀረበበት መሆኑን አውቆ የቀረበበትን ክስ የሚከላከልበትን ሥነ-ስርዓት ለመዘርጋት የወጣ ህግ ነው፡፡

፩.አጭር ርዕስ

፪. ትርጓሜ

፫. የተፈፃሚነት ወሰን

፬. ጥንቁቅ ስለመሆን

፭. አርአያነት

፮. ፍትሐዊነት

፯.የፍርድ ቤት ሠራተኞችን ሥነ-ምግባር መቆጣጠር

፰. ሰአት አክባሪነት

፲. ስለ ንብረት አጠቃቀም

፲፩. ምስጢር ጠባቂነት

፲፪. የዳኛ ክችሎት መነሳት

፲፫. መደለያ አለመቀበል

፲፬. አላስፈላጊ ጥቅም

፲፭. ሥልጣንን ያለአግባብ መጠቀም

፲፮. ተጠያቂነት

፲፯. ህጎችን በትክክል በሥራ ላይ ስለማዋል

፲፰. ያለማዳላት

፲፱. ትጋትና ብቃት

፳.ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት

፳፩. የፍርድ ቤቱን ክብር ስለመጠበቅ

፳፪. ተግባብቶ በቡድን መስራት

፳፫. ተከራካሪ ወገኖችን ስለመስማት

፬.የፍርድ ሂደቱን ስርዓት ስለማስከበር

፳፭. የፍርድ አሰጣጥ

፳፮. የጥፋተኝነትና የቅጣት አወሳሰን

፳፯. በሃሳብ ስለመለየት

፳፰.የችሎት ሠራተኞችን የሥራ አፈፃፀም መቆጣጠር

፳፱. የፍርድ ቤት መዛግብት ከአስፀያፊና አስነዋሪ ቃላትና አስተያየት ነፃ ስለማድረግ

፴. ክስ፣ መልስ እና አቤቱታዎች በአግባቡ መቅረባቸውን መቆጣጠር

፴፩. ስለ ዲስፕሊን ጥፋቶች

፴፪.የዲስፕሊን ክስ ስለማቅረብ

፴፫. የዲስፕሊን ክስ አቀራረብ

፴፬. ስለክስ ማጣራት

፴፭.ከሥራ አግዶ ስለማቆየት

፴፮.የጉባዔው የአሰራር ሥነ-ስርዓት

፴፰.ሚስጥር ስለመጠበቅ

፴፱.ሥራን በገዛ ፈቃድ መልቀቅ

፵.የቅጣት ውሳኔ ከግል ፋይል ጋር ስለማያያዝ

፵፩.የቅጣቱ ውሳኔ እንዲነሳ ስለመጠየቅ

፵፪.ደንቡን ስለማሻሻል

፵፫.ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች

፵፬. ደንቡ ስለሚፀናበት ጊዜ

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤቶች ዳኞች መከተል ስለሚገባቸው ሥነ-ምግባር ለመወሰን የወጣ ደንብ ፳/፪ሺ፩

የተቀላጠፈና ውጤታማ የዳኝነት አገልግሎት የሚሰጡ፣ በህዝብ ዘንድ አመኔታን ያተረፉ የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት አካል መኖር ያለበት መሆኑን በመገንዘብ፣

የዳኝነት ነፃነት ሊጠበቅ የሚችለው ዳኞች በዳኝነት ሥራቸውም ሆነ በግል ህይወታቸው አርአያነት ያለው ከፍተኛ ሥነ-ምግባር ሲያሳዩ ብቻ መሆኑን በማመን፣

ዳኞች በአኗኗራቸውና በዕለት ተዕለት ተግባራቸው ሊከተሏቸው የሚገባ የዳኝነት ሥራ አፈፃፀምና ሥነ-ምግባር ደንብ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በዳኞች ላይ የሚቀርቡ የዲስፕሊን አቤቱታዎች የሚመሩበትን ሥነ-ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑና የዲስፕሊን ክስ የቀረበበት መሆኑን አውቆ የቀረበበትን ክስ የሚከላከልበትን ሥነ-ስርዓት መዘርጋት ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፣

በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፳፫/፩ (ረ) እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤቶች አዋጅን ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር ፴፩/፲፱፻፺፱ዓ.ም አንቀጽ ፴፪(፩) በተሰጠው ስልጣን መሠረት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ ይህን ደንብ አውጥቷል ፡፡

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**፩.አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤቶች የዳኞች ሥነ-ምግባር ደንብ ቁጥር ፳/፪ሺ፩ ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩."**ዳኛ**" ማለት በአዲስ አበባ ከተማ የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤቶች ውስጥ ተሹሞ የዳኝነት ሥራ የሚሰራ ሰው ሲሆን ግራና ቀኝ ዳኞችንም የሚጨምር ነው፣

፪."**ጉባዔ**" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ የማህበራዊ ፍርድ ቤቶች የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ነው፣

፫."**የጉባዔው ሰብሳቢ**" ማለት የማህበራዊ ፍርድ ቤቶች የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ጽህፈት ቤት ኃላፊ ነው፣

፬."**የዲስፕሊን ጥፋት**" ማለት በዚህ ደንብ የተመለከተው ጥፋት ነው፣

፭."**ቢሮ**" ማለት የከተማው አስተዳደር የፍትህና ህግ ጉዳዮች ቢሮ ነው፣

፮."**የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት**" ማለት የከተማው አስተዳደር የዳኝነት አካል የሆነ፣ በእያንዳንዱ ቀበሌ የተቋቋመና የዳኝነት ተግባራትን የሚያከናውን ፍርድ ቤት ነው፣

፯."**ሥነ-ምግባር**" ማለት ዳኞች በስራቸው ላይ እና ከስራቸው ውጪ በግል ህይወታቸው የተጣለባ ቸውን የሙያ ኃላፊነት ከዳር ለማድረስ ሊከተሉት የሚገባ ባህሪና ተግባር ነው፤

፰."**ሰው**" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፱.በዚህ ደንብ ውስጥ በልዩ ሁኔታ ካልተገለፀ በስተቀር በወንድ ፆታ የተገለጹ አገላለጾች ለሴት ጾታም ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

፫. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ ደንብ በአዲስ አበባ ከተማ የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤቶች ዳኞች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

፬. <u>አላማ</u>

ደንቡ የሚከተሉት አላማዎች ይኖሩታል፡-

፩.ዳኞች የዳኝነት ተግባራቸውን ሲያከናውኑ ሊኖራቸው ስለሚገባ ሥነ-ምግባር ለመደንገግ፤

፪.የዲስፕሊን ጥፋት የፈፀመ ዳኛ በፈፀመው ጥፋት ተፀፅቶ እንዲታረምና ወደፊት በብቃት ስራውን ለማከናወን እንዲችል ለማስተማርና የማይታረም ሆኖ ሲገኝ ለማሰናበት፤

፫.በዳኞች ላይ የሚቀርብ የዲሲፕሊን ክስ አቀራረብ፣ አወሳሰንና አፈፃፀም በህግ መሰረት እንዲሆን ለማድረግ፡፡

<u>ክፍል ሁለት</u>

<u>ስለዳኝነት ሥነ-ምግባርና የሥራ አፈፃፀም መርሆዎች</u>

<u>ምዕራፍ አንድ</u>

<u>የዳኝነት ሥነ-ምግባር</u>

፭. <u>ጥንቁቅ ስለመሆን</u>

ዳኛ አስተዋይ፣ ትሁት፣ ታጋሽና በአሠራሩም ጥንቁቅ መሆን አለበት፡፡

፮. <u>አርአያነት</u>

ዳኛ በማህበረሰቡ ውስጥ በሚኖርበት ጊዜ በአስተሳሰቡ፣ በጠባዩ፣ በአድራጎቱና መጥፎ አካባቢዎች ባለመሆን ለህብረተሰቡ አርአያ መሆን አለበት፡፡

፯. <u>ፍትሐዊነት</u>

ዳኛ የዳኝነቱን ተግባር በሚያከናውንበት ጊዜ ከንቱ ክብርና ውዳሴ ሳይሻ፣ በስሜትም ሳይመራ፣ ያለአንዳች ፍርሃትና ስጋት በህግ መስራት አለበት፡፡

፰.<u>የፍርድ ቤት ሠራተኞችን ሥነ-ምግባር መቆጣጠር</u>

ዳኛ

በፍርድ ቤት ሠራተኞችና በራሱ መካከል መናናቅን የሚፈጥሩ ግንኙነቶችን ከመመስረት መታ ቀብ

አለበት፤ሠራተኞቹም የፍርድ ቤቱን ክብር እንዲጠብቁና ለተገልጋዮች ሁሉ ትህትና እንዲያሳዩ መቆጣጠር ይጠበቅበታል፡፡

**፱. ሰአት አክባሪነት**

፩. ዳኛ የመንግስት የሥራ ሰዓትን ለስራው ብቻ ማዋል አለበት፤

፪. በቂ ምክንያት ሳይኖረው ወይም ፈቃድ ሳይቀበል ከሥራ ገበታው መለየት የለበትም፤ የሥራ ሰዓ ትን በማክበር ለሌሎች አርአያ መሆን ይገባዋል፡፡

**፲. ስለ ንብረት አጠቃቀም**

ዳኛ ለፍርድ ቤቱ ሥራ አገልግሎት ተብለው ለሚቀርቡለት መገልገያ ንብረቶች ተገቢውን ጥንቃቄ በማ ድረግ ለፍርድ ቤቱ የሥራ አገልግሎት ብቻ ሊያውል ይገባል፡፡

**፲፩. ምስጢር ጠባቂነት**

፩. ዳኛ ፍርድ ቤቱ ሥራውን እንዴት እያከናወነ እንደሆነ፣ ስለ አሰራራቸው ሥነ ስርዓት በተመለከተ በመገናኛ ብዙሃን አስተያየት መስጠት ይችላል፤

፪. የፍርድ ሥራን ሚስጥራዊ ጠባይ ለመጠበቅ ሲባል ዳኛ በቀረበለት ጉዳይ ላይ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት አብረውት ከሚያስችሉት ዳኞች ጋር ካልሆነ በስተቀር በዝርዝር ጉዳይ ላይ ከማንኛውም ሌላ ሰው ጋር በግል መወያየት ወይም በማናቸውም መገናኛ ብዙሃን መግለጫ ወይም አስተያየት መስጠት የለበትም፤

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ዳኛ አብረውት ከሚያስችሉት ዳኞች ጋር ሲወያይ የተከራካሪ ወገኖችን ማንነት ሳይገልጽ በጭብጡ ላይ ብቻ መሆን ይኖርበታል፡፡

**፲፪. የዳኛ ከችሎት መነሳት**

፩.ዳኛ የቀረበለትን ጉዳይ አላይም ማለት አይችልም፤

፪.ዳኛ አንድን ጉዳይ እንዳያይ በህግ የተከለከለ መሆኑን እንዳወቀ መቃወሚያ እስኪቀርብበት ድረስ ሳይጠብቅ ምክንያቱን በሚገባ ገልጾ ከችሎት መነሳት አለበት፡፡

**፲፫. መደለያ አለመቀበል**

ለዳኝነት በቀረበ፣ በሚቀርብ ወይም በተወሰነ ጉዳይ ምክንያት ዳኛ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ጉቦ፣ መደለያ፣ ስጦታ ወይም ሌላ ጥቅም ከባለጉዳይ ወይም ከሌላ ማንኛውም ሰው ላይ መቀበል የለበትም፡፡

**፲፬. አላስፈላጊ ጥቅም**

ዳኛ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለራስ ለማግኘት ወይም ለሌሎች ለማስገኘት መስራት የለበትም ፡፡

**፲፭. ሥልጣንን ያለአግባብ መጠቀም**

ዳኛ የማይገባውን ጥቅም ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ሥልጣኑንና ክብሩን መሣሪያ ማድረግ የለበትም ፡፡

**፲፮. ተጠያቂነት**

፩.ዳኞች ህግን መሰረት ሳያደርጉ ለሚሰጧቸው ውሳኔዎችና ለሚያከናውኗቸው ሌሎች ተግባራት ህጋዊ ኃላፊነት አለባቸው፤

፪.ዳኛ ለቢሮው፣ ለጉባዔው(ለጉባዔው ሰብሳቢ)፣ አግባብ ላለው የሥራ ኃላፊ ወይም የሥራ ክፍል የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት በማዘጋጀትያቀርባል፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## የሥራ አፈፃፀም ግምገማ መርሆዎች

### ፲፯. ህጎችን በትክክል በሥራ ላይ ስለማዋል

፩. ዳኛ ለሚሰጠው ፍርድ፣ ውሳኔ፣ ትዕዛዝ ወይም ብይን ሁሉ በአገሪቱ የወጡ ህጎችን በትክክል ሥራ ላይ መተግበር አለበት፤

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ዳኛ ወደነገሩ ከመግባቱ በፊት ጉዳዩን ለማየት የዳኝነት ሥልጣን ያለው እና ጉዳዩ የክስ ምክያት ያለው መሆኑን ማረጋገጥ ይገባዋል፡፡

### ፲፰. ያለማዳላት

ዳኛ በዘር፣ በፆታ፣ በብሔር፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ ፖለቲካ አመለካከት፣ በማህበራዊና ሌሎች ምክንያቶች ልዩነት ሳያደርግ በቀረበለት ፍሬ ነገር እና ማስረጃ ላይ ብቻ በመመስረት ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

### ፲፱. ትጋትና ብቃት

፩. ዳኛ ለህግ ስርዓትና የፍትህ አስተዳደር እድገት ጥረት ማድረግ አለበት፤

፪. ዳኛው የዳኝነት ሥራው ላይ ተገቢውን ትጋትና ጥረት እንዲያሳይ፣ በህግ ላይ ያለውን እውቀት ለማዳበርና የሙያ ብቃቱን ለማሳደግ በቢሮው ወይም በጉባዔው በሚሰጠው ስልጠና ላይ መካፈል አለበት፡፡

### ፳.ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት

፩. ዳኛው በአማራጭ የግጭት መፍቻ መንገዶች ሊፈቱ የሚችሉ ጉዳዮችን ሁሉ በተቻለ ፍጥነት እልባት እንዲያገኙ ጥረት ማድረግ አለበት፤

፪. ዳኛ በቂ ምክንያት ከሌለው በስተቀር የቀረበለትን ጉዳይ በተቻለ ፍጥነት መወሰን አለበት፡፡

### ፳፩. የፍርድ ቤቱን ክብር ስለመጠበቅ

ዳኛ ግዴታውን በሚወጣበት ጊዜና በችሎት አመራሩ የፍርድ ቤቱን ክብር መጠበቅ አለበት፡፡

### ፳፪. ተግባብቶ በቡድን መስራት

ዳኛ አብረውት ከሚያስችሉት ዳኞች እና የሥራ ባልደረቦቹ ጋር ተግባብቶ፣ ተባብሮና ተከባብሮ መስራት አለበት፡፡

### ፳፫. ተከራካሪ ወገኖችን ስለመስማት

፩. ዳኛ በችሎት በስርዓት የሚያነጋግሩትን ተከራካሪ ወገኖችን፣ ምስክሮችን ጠበቆችን ወይም የህግ ኤክስፐርቶችን (ነገረ ፈጆችን) ሁሉ አድልኦ በሌለበት ሁኔታ መስማት አለት፤

፪. ዳኛ የባለ ጉዳዮችን መብትና ክብር መጠበቅ ይኖርበታል፡፡

**፳፬.<u>የፍርድ ሂደቱን ስርዓት ስለማስከበር</u>**

፩. ዳኛ የፍርድ ሂደት ስርዓት ባለው መንገድ እንዲሄድ ማድረግ አለበት፤

፪.የፍርድ ሂደቱ በተቀላጠፈ መንገድ እንዳይፈፀም ተከራካሪ ወገኖች ተገቢ ያልሆነ ጠባይ ሲያሳዩ፣ ተገቢ ያልሆነ ድርጊት ሲፈጽሙ፣ ሳይዘጋጁ ሲቀርቡና ያልረባ ምክንያት ሲያቀርቡ ዳኛው በአንቀጽ ፳፫ የተደነገገውን ከግምት ውስጥ በማስገባት አጥፊዎችን በአግባቡ መገሰጽና ማረም አለበት፤ አስፈላጊም ሲሆን ተገቢውን እርምጃ መውሰድ አለበት፡፡

**፳፭. <u>የፍርድ አሰጣጥ</u>**

የዳኛ የእጅ ጽሁፍ የሚነበብ፣ ንፁህ እና መደበኛ ያልሆነ ምህፃረ-ቃላት የሌለበት መሆን አለበት፤ እንዲሁ የሚናገረውም ሆነ በጽሁፍ የሚያስተላልፈው መልዕክት ግልፅና በቀላሉ ለመረዳት የሚቻል መሆን አለበት፡፡

**፳፮. <u>የጥፋተኝነትና የቅጣት አወሳሰን</u>**

ዳኛ በደንብ መተላለፍ ጉዳይ የጥፋተኝነት ውሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ ተከሳሹ በተከሰሰበት አንቀጽ፣ ፈጸመ የተባለውን የደንብ መተላለፍ፣ ድርጊቱን ለመፈጸሙ የቀረበውን ማስረጃና የተከሳሹን መከላከያ በብርቱ ጥንቃቄ መመዘን አለበት፤ በተጨማሪም ስለቅጣት ዓላማዎችና አወሳሰን የተደነገጉትን መርሆዎች በጥንቃቄ በመመዘን መሆን አለበት፡፡

**፳፯. <u>በሃሳብ ስለመለየት</u>**

ዳኛ በሃሳብ ከሌሎች ዳኞች በሚለይበት ጊዜ የተፋጠነ ፍትህ ለመስጠት እንዲያስችል የልዩነት ሃሳቡን ያለማዘግየት ማስቀመጥ አለበት፡፡ በሃሳብ ተለይቶ የሚጽፈውም አስተያየት የሚለይባቸውን ነጥቦች ከማስፈር አልፎ የሥራ ጓደኞቹን፣ የሌሎች ግለሰቦችንም ሆነ የህብረተሰብ ክፍሎችን ስሜትም ሆነ ክብር ያለአግባብ የሚነካ አስተያየት መሰንዘር የለበትም፡፡

**፳፰.<u>የችሎት ሠራተኞችን የሥራ አፈፃፀም መቆጣጠር</u>**

የችሎት ሠራተኞች ሥነ-ስርዓት እንዳያጓድሉ፣ በሥራቸው ላይ ቸልተኝነት እንዳያሳዩ ወይም ሥራቸውን ለግል ፍላጎት መጠቀሚያ እንዳያውሉ ዳኛው መቆጣጠርና ተገቢውን ምክርና ተግሳጽ መስጠት ይገባዋል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ሕጋዊ እርምጃ ሊወስድ ይችላል፡፡

**፳፱. <u>የፍርድ ቤት መዛግብት ከአስፀያፊና አስነዋሪ ቃላትና አስተያየት ነፃ ስለማድረግ</u>**

ዳኛ በማንኛውም ወገን የሚቀርበውን የፍርድ ቤት መዛግብት አካል የሚሆኑ አቤቱታዎች፣ ሌሎች ጽሁፎች ወይም በቃል የሚነገሩ ቃላትና አስተያየቶች ለፍርድ አሰጣጥ አስፈላጊ

ሆነው እስካልተገኙ ድረስ ፀያፍና አስነዋሪ ከሆኑ ቃላት ወይም አስተያየቶች ነፃ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

፴. <u>ክስ፣ መልስ እና አቤቱታዎች በአግባቡ መቅረባቸውን መቆጣጠር</u>

ዳኛ ክስ፣ መልስ እና አቤቱታዎች አግባብ ያለው የሥነ-ሥርዓት ሕግ በሚያዘው መሰረት ተዘጋጅተው የቀረቡ መሆናቸውን ማረጋገጥና መቆጣጠር አለበት፡፡

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>ስለዲስፕሊን ጥፋቶች፣ የዲስፕሊን ክስ አመሠራረትና አወሳሰን ሥነ-ስርዓት</u>

### <u>ምዕራፍ አንድ</u>

### <u>የዲስፕሊን ጥፋቶች</u>

፴፩. <u>ስለ ዲስፕሊን ጥፋቶች</u>

፩.የዲስፕሊን ቅጣት የሚያስከትሉ ጥፋቶች፡-

ሀ) ጉቦ፣ መደለያ፣ ስጦታ ወይም ሌላ ጥቅም መቀበል ወይም እንዲሰጠው መጠየቅ፤

ለ) ያለበቂ ምክንያት ከሥራ መቅረት ወይም የሥራ ሰዓት አለማክበር፤

ሐ) በዳኝነት ሥልጣንን አላግባብ መጠቀም፤

መ)በሥራ ሰዓት የግል ሥራ መሥራት፤

ሠ)በሥራ አፈፃፀም ግድፈት መፈፀም፤

ረ) ያለበቂ ምክንያት ቀጠሮ ማብዛትና ባለጉዳዮችን ማጉላላት፤

ሰ) በቸልተኝነት፣በመለገም ወይም ሆን ብሎ በሥራ ላይ በደል ማድረስ፤

ሸ) ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለራስ ለማግኘት ወይም ለሌለ ሰው ለማስገኘት በማሰብ በአማላጅት መሥራት፤

ቀ)ሰክሮ በስራ ላይ መገኘት ወይም በአደባባይ በመታየት የሙያውን ሥነ-ምግባርና የፍርድ ቤቱን ክብር ማጉደል፤

በ) በሥራ ላይ ለሞራልና ለመልካም ጠባይ ተቃራኒ የሆነ ድርጊት መፈፀም፤

ተ) ሆን ብሎ ወይም በከባድ ቸልተኝነት በመስሪያ ቤቱ ንብረት ላይ ጉዳይ ማድረስ፤

ቸ) ከሥራ ባልደረቦቹ ጋር በመግባባትና ተባብሮ ባለመሥራት በሥራ ላይ እንቅፋት መፍጠር፤

ኀ)በሥራ ላይ ተገቢ ጥረትና ትጋት አለማድረግ፤

ነ)ሌሎች በተመሳሳይ ደረጃ የሚታዩ ቀላል ጥፋቶችን መፈፀም፤

ኘ)ከዳኝት ሥራው በተጨማሪ የጥብቅና ስራ ወይም ከህግ ውጭ ፍቃድ ሳያገኙ የህግ ስራ መስራት፡፡

፪.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ከፊደል "ሀ" እስከ "ቸ"ድረስ የተዘረዘሩት ከባድ የዲስፕሊን ጥፋቶች ሲሆኑ ከፊደል "ኀ" እስከ "ኘ" ድረስ የተዘረዘሩት ደግሞ ቀላል የዲስፕሊን ጥፋቶች ናቸው፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## የዲስፕሊን ክስ አመሠራረትና አወሳሰን

### ፴፪.የዲስፕሊን ክስ ስለማቅረብ

፩.የዳኝነት የሥነ-ምግባር ወይም የሥራ አፈፃፀም ጉድለት በዳኛ ተፈጽሟል የሚል ማንኛውም ሰው አቤቱታ ሊያቀርብ ይችላል፤

፪.ጉባዔው በራሱ በቂ ምክንያት ሲኖረው በማንኛውም ዳኛ ላይ የዲስፕሊን ክስ እንዲጣራ ማዘዝ ይችላል፡፡

### ፴፫. የዲስፕሊን ክስ አቀራረብ

፩.አቤቱታ አቅራቢው ክሱን በጽሁፍ አዘጋጅቶ ማስረጃዎቹን አያይዞ፣ማስረጃዎቹ የሚገኙት በሌላ አካል እጅ ከሆነም ይህንኑ ጠቅሶ ማቅረብ ይኖርበታል፤

፪.ዳኛ የሥራ አፈፃፀም ወይም የሞያ ሥነ-ምግባር ጉድለት ፈጽሟል የሚል አቤቱታ አቅራቢ ለጉባዔው ሰብሳቢ አቤቱታውን ያቀርባል፡፡

### ፴፬. ስለክስ ማጣራት

፩.ጉባኤው የቀረበለትን የሥራ አፈፃፀምና የሞያ ሥነ-ምግባር ጉድለት ክስ በራሱ ለማጣራት ወይም ለአጣሪ ኮሚቴ ሊመራው ይችላል፤

፪.ጉባዔው ክሱ ተገቢ ሆኖ ካላገኘው ለአቤቱታ አቅራቢው በጽሁፍ ይህንኑ ያሳውቃል፤

፫.ጉባዔው የቀረበው ክስ ተገቢሆኖ ሲያገኘው ተከሳሽ መልሱንና ማስረጃዎቹን ለጉባዔው እንዲያቀርብ ያዛል፤

፬.ክስ የቀረበበት ዳኛ ለቀረበበት ክስ መልስና መከላከያ ለማቅረብ እንዲችል የቀረበበትን ክስ በዝርዝር የሚገልጽ የክስ ጽሁፍ፣ ክሱን ለማረጋገጥ የቀረበበትን ማስረጃ፣ መልስ የሚሰጥበትን ቀን፣ ሰዓት እና ቦታ ከሚገልጽ መጥሪያ ጋር እንዲደርሰው ይደረጋል፡፡

### ፴፭.ከሥራ አግዶ ስለማቆየት

፩.ከባድ የዲስፕሊን ጥፋት ፈጽሟል ተብሎ የክስ አቤቱታ የቀረበበት ዳኛ ጉዳዩ ተጣርቶ የመጨረሻ ውሳኔ እስኪሰጠው ድረስ ከሥራ ወይም ከሥራና ከደመወዝ ታግዶ እንዲቆይ ጉባዔው ሊያዝ ይችላል፤

፪.ከሥራና ከደመወዝ ታግዶ የሚቆይበት ጊዜ እጅግ ቢበዛ ከ፪ ወር አይበልጥም፤

፫.ከዚህ በላይ በተገለፀው መልኩ የታገደው ዳኛ ከቀረበበት ክስ ነፃ ከሆነ የተያዘው ደመወዝ ይለቀቅለታል፡፡

**፴፮.**<u>**የጉባዔው የአሰራር ሥነ-ስርዓት**</u>

የጉባኤው የአሰራር ስነ-ስርዓት እንደሚከተለው ይሆናል፡-

፩.በማንኛውም ስብሰባ ከአባሎች ፪/፫ኛው ሲገኙ ምልዓተ-ጉባኤ ይሆናል፤

፪.ማናቸውም ጉዳይ በስብሰባው በተገኙ አባላት በድምፅ ብልጫ ይወሰናል፤

፫.የጉባዔው አባላት ድምጽ እኩል ከሆነ የጉባኤው ሰብሳቢ ያለበት ወገን የጉባዔው ውሳኔ ይሆናል፤

፬.ጉባዔው በድምጽ ብልጫ በሚወስንበት ጊዜ ሁሉ የአነስተኛ ድምጽ አስተያየት ከነምክንያቱ በስብሰባው ቃለ ጉባኤ መመዝገብ አለበት፡፡

**፴፯.**<u>**የዲሲኘሊን ቅጣት**</u>

፩.ጉባዔው የቀረበለትን የዲስፕሊን ክስ ከቀረበው ማስረጃ ጋር መርምሮ የዲስፕሊን ጥፋት መፈፀሙን ሲያረጋግጥ የሚከተሉት ቅጣቶች አንዱን ሊወስን ይችላል፡-

ሀ) የቃል ማስጠንቀቂያ፤

ለ) የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ፤

ሐ) ከሥራ ማሰናበት፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፩ "ሀ" እና "ለ" የተመለከተቱት ለቀላል የዲስፕሊን ጥፋቶች ተግባራዊ ሲሆኑ በተራ ቁጥር "ሐ" የተመለከተው ደግሞ ለከባድ የዲስፕሊን ጥፋት ተግባራዊ ይሆናል፤

፫.ዳኛ ቀላል የዲስፕሊን ጥፋት ፈጽሞ ሲገኝ ክሱን ለጉባዔው ማቅረብ ሳያስፈልግ የጽህፈት ቤቱ የሥራ ኃላፊ በተራ ቁጥር ፩ "ሀ" እና "ለ" የተመለከቱትን የቃልና የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት ይችላል፤ ውጤቱንም ለጉባዔው ሪፖርት ያቀርባል፡፡

**፴፰.**<u>**ሚስጥር ስለመጠበቅ**</u>

፩.ማንኛውም ለጉባዔው የሚቀርብ የዲስፕሊን ጉዳይ በሚስጢር እንዲጠበቅ ይደረጋል፤

፪.የዲስፕሊን ጉዳዮች ምስጥራዊነታቸው ሊቀር የሚችለው ጉባዔው ሲፈቅድ ብቻ ይሆናል፡፡

**፴፱.**<u>**ሥራን በገዛ ፈቃድ መልቀቅ**</u>

፩.ማንኛውም ዳኛ በማንኛውም ጊዜ ስራውን በገዛ ፈቃዱ ለመተው ይችላል፤

፪.ስራን በገዛ ፈቃድ ለመልቀቅ የሚቀርበው ጥያቄ ዳኛው ስራውን ለመልቀቅ ከሚፈልግበት ቀን አንድ ወር አስቀድሞ በጽሁፍ መቅረብ አለበት፤

፫.ከላይ ያለው እንደተጠበቀ ቢሆንም የዲስፕሊን ክስ የቀረበበት ዳኛ በራሱ ፈቃድ ከስራ ቢለቅ ጉዳዩ ውሳኔ ከማግኘቱ በፊት መልቀቂያ አይሰጠውም፤

፬.ዳኛ በማንኛውም ምክንያት አገልግሎቱ ሲያቋርጥ ወይም ሲለቅ የአገልግሎት ስርተፍ ኬት ይሰጠዋል፡፡ የአገልግሎት ሰርተፍኬቱም ላይ የሚከተለው መገለፅ ይኖርበታል፡-

ሀ.የአገልግሎት ዘመን የጀመረበትንና የተቋረጠበትን ቀን፣

ለ.ስራውን የለቀቀበት ምክንያት፣

ሐ.በአገልግሎቱ ዘመን የሥራ አፈፃፀሙ ምን እንደሚመስል በጉልህ የሚገልፁ ማስረጃዎች፣

መ.ዳኛው በአገልግሎት ዘመኑ በየጊዜው የያዘው የስራ መደብና ደረጃው ከነ ደመወዙ፡፡

**፵.የቅጣት ውሳኔ ከግል ፋይል ጋር ስለማያያዝ**

፩.ጉባዔው የቅጣት ውሳኔ የሰጠባቸው የዲስፕሊን ጉዳዮች ከዳኛው የግል ማህደር ጋር እንዲያያዝ ይደረጋል፤

፪.ጉባዔው የሰጠው ውሳኔ ከሥራ መሰናበትን የሚመለከት ከሆነ የተሰጠው ውሳኔ ከዳኛው ማህደር የሚያያዘው ውሳኔው አግባብ ላለው የቀበሌው ምክር ቤት ቀርቦ ሲፀድቅ ነው፤

፫.ተቀባይነት ያጡ ወይም ውሳኔ ያላገኙ የዲስፕሊን ጉዳዮች ከዳኛው የግል ማህደር ጋር አይያያዙም፡፡

**፵፩.የቅጣቱ ውሳኔ እንዲነሳ ስለመጠየቅ**

፩.ከሥራ መሰናበት ቅጣት ካልተወሰነበት በስተቀር ቅጣት የተወሰነበት ዳኛ ውሳኔው እንዲነሳ ለጉባዔው ማመልከት ይችላል፤

፪.የቅጣት ውሳኔው እንዲነሳ ጉባኤው ሲወስን ከተቀጭው ማህደር የተያያዘው የጥፋተኝነት ውሳኔ ከማህደሩ እንዲወጣ ይደረጋል ዳኛወውም እንዳልተቀጣ ይቆጠራል፡

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፵፪.ደንቡን ስለማሻሻል**

ይህ ደንብ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ ሊሻሻል ይችላል፡፡

**፵፫.ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች**

ይህን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ የተደነገጉትን ጉዳዮች በተመለከተ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

**፵፬. ደንቡ ስለሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ ከግንቦት ፳፰ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ**

**ግንቦት ፳፯ ቀን ፪ሺ፩ዓ.ም**

**ኩማ ደመቅሳ**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንገድ አጠባበቅ ደንብ ቁጥር ፪/፲፱፻፺፫ዓ.ም

ማውጫ

፩. አጭር ርዕስ

፪. ትርጓሜ

ክፍል ሁለት

፫. የተከለከሉ ድርጊቶች

፬.ቅጣት

፭. ቅጣቱ የሚጨምራቸው /የማያስቀራቸው ጉዳዮች

፮. አስፈፃሚ አካላት

ክፍል ሦስት

፯. ስለ አቤቱታ አቀራረብ፣

፰. ስልጣን ውክልና እና መመሪያዎችን ስለመቀበል

ክፍል አራት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፱. መመሪያ ማውጣት

፲. ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች

፲፩. ገደቡ የሚጸናበት ጊዜ

አጭር መግለጫ

የከተማው መንገድ ደረጃውና ንጽሕናው ተጠብቆ የመንገድ ተጠቃሚው በአግባቡ እንዲገለገልበት ለማድረግ፣ በመንገድ ላይ የሚፈጸሙ ሕገ ወጥ ተግባራትን በመከላከል መንገዶች ለታለመላቸው ዓላማዎች ለማዋልና ሕገወጥ ድርጊት የሚፈጽሙትን ለማስተማርና ለጥፋቱ ተመጣጣኝ የሆነ ቅጣት ለመጣል የተደነገገ ሕግ ነው፡፡

# <u>የአዲስ አበባ ከተማ የመንገድ አጠባበቅ ደንብ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንገድ አጠባበቅ ደንብ ቁጥር ፪/፲፱፻፺፩ዓ.ም</u>

በአዲስ አበባ ከተማ በአውራ መንገድ፣ በእግረኛ ማቆሚያዎችና በመሳሰሉ ለሕዝብ መገልገያ የተሰሩና የታሰቡ የሕዝብ ምብረቶች ላይ ከጊዜ ወደ ጊዜ ሕገወጥ በሆነ መንገድ የንግድ ሱቆች፣ ኮንቴነሮችና ግንባታዎች በመስራት የኮንስትራክሽን ተረፈ ምርት፣ አፈርና የመሳሰሉትን በመድፋት፣ የንግድ ዕቃ በመደርደርና መሰል ተግባሮችን በመፈጸም መንገዶች ለታለመላቸው ዓላማዎች እንዳይውሉ በመደረጋቸው

እነዚህ ሕገወጥ ተግባሮች የዘወትር ክትትል በማድረግ ማስወገድና የከተማው መንገድ ደረጃውና ንጽሕናው ተጠብቆ የመንገድ ተጠቃሚው በአግባቡ እንዲገለገልበት ማድረግ የከተማው አስተዳደር ፍላጎት በመሆኑ

ህገወጥ ግንባታውን ያደረጉ ሰዎች ግንባታውን ከማፍረስ በተጨማሪ ሌላ ጊዜ ደግመው እንዳያጠፉ፣ ሌሎችም እነሱን አይተው ወደጥፋት እንዳይገቡ በማድረግ ለማስተማርና ለጥፋቱ ተመጣጣኝ የሆነ ቅጣት መጣል ተገቢ በመሆኑ

የአዲስ አበባ ከተማ ጊዜያዊ አስተዳደር በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፷፩/፲፱፻፺፭ዓ.ም አንቀጽ ፲፬ (ረ) እና ፳፯ (፪) በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን ደንብ እንደሚከተለው አውጥቷል፡፡

፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንገድ አጠባበቅ ደንብ ቁጥር ፪/፲፱፻፺፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. <u>ትርጓሜ</u>

፩. በዚህ ደንብ ውስጥ በሌላ ሁኔታ ካልተመለከተ በስተቀር የሚጠቀሱ ቃላትና ሃሳቦች ትርጉማቸው የአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ባለስልጣን ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፯/፲፱፻፺፯ ውስጥ በተመለከተው መሰረት ይሆናል፤

፪. "መንገድ" ማለት በአዲስ አበባ ማስተር ፕላን መሰረት ለመንገድነት የተያዙና የተመደቡትን ክፍት ቦታዎች ይጨምራል፤

፫. "ባለስልጣን"ማለት አዲስ አበባ ከተማ መንገዶ ባለስልጣን ማለት ነው፤

፬."ማስተር ፕላን" ማለት የፀደቀው የአዲስ አበባ ከተማ ፕላን ማለት ነው፤

፭."የመንገድ ደረጃ" ማለት ባለስልጣኑ በስልጣን ክልሉ ውስጥ ያሉትን ነባር መንገዶች እንዲሁም ወደፊት የሚሰሩ አዲስ መንገዶች፣ ዋና መንገድ፣ መስቀለ መንገድ፣

መጋቢ መንገድ፣ የውስጥ ለውስጥ መንገድ፣ የመንደር መንገድ በሚባሉ ደረጃዎች የሚመድባቸውን ማለት ነው፡፡

## ክፍል ሁለት

## ክልከላዎች ቅጣት የማይጨምራቸው/ የማያስቀራቸው ጉዳዮች እና አስፈጻሚ አካላት

፫. የተከለከሉ ድርጊቶች

፩. በመኪና መንገዶች፣ በማስተር ፕላን ለመንገድነት በተያዙ ክፍት ቦታዎች፣ በእግረኛ መንገዶች፣ በአደባባዮች በድሬይኔጅ መስመሮች፣ በቱካዎችና በክዳኖቻቸው፣ በማንሆሎችና በክዳኖቻቸው፣ በእግረኛ መከለከያዎች፣ በትራፊክ መብራቶች፣ በትራፊክ ምልክቶች በመንገድ መብራቶችና ቋሚዎች (ፖሎች)፣ በድልድዮችበአጠቃለይ ባለስልጣኑ በተቋቋመበት በደንብ ቁጥር ፺/፲፱፻፺ መሰረት የሚያስተዳድረቸው ንብረቶች ላይ ማናቸውም ዓይነት ግንባታ ክልከላ፣ ክለላ ማድረግ፣ መንገዶችን መቁረጥ፣ መስበር፣ መቆፈር፣ ለብቻውም ሆነ ከሕጋዊ ይዞታ ጋር በተያያዘ መልኩ መገንባት፣ ማገናኘት፣ ማስፋፋት፣ መቀጠል፣ ውይም ማጠርና መሠል ተግባሮች የተከለከሉ ናቸው

፪. ባለስልጣኑ በደንብ ቁጥር ፺/፲፱፻፺ መሰረት በሚያስተዳድራቸው ንብረቶች ላይ ተገቢውን ፍቃድ ሳያገኙ ማናቸውንም ዓይነት ተግባር መፈጸም አይቻልም

፬.ቅጣት

፩. ማንኛውም ሰው ከላይ በአንቀጽ ፫ የተመለከቱትን ድርጊቶችን ፈጽሞ ሲገኝ ከዚህ ደንብ ጋር ተያይዞ በሚገኘው ሰንጠለዥ ሀ መሰረት ይቀጣል

፪. አጥፊው በሰንጠለዡ ላይ የተመለከተውን ገንዘብ መክፈል ያልቻለ መሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ በእስራት ተለውጦለት ይቀጣል፡፡ቅጣቱ ወደ እስራት የሚለውጠውና የሚፈጽመው በከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔ ይሆናል፡፡

፫. አጥፊው በተሽከርካሪ አማካኝነት ጥፋቱን ፈጽሞ ሲገኝ የቅጣቱን መጠን ለባለስልጣኑ ገቢ እስከሚያደርግ ድረስ ትራፊክ ፖሊስ ሠሌዳውን በመፍታት ይይዛል፡፡ የተቀጣበትን ገንዘብ ገቢ አድርጎ ደረሰኝ ሲያቀርብ ሌዳው በተፈታ ፬፰ ሰዓት ውስጥ አጥፊው ገንዘቡን ገቢ አድርጎ ካልቀረበ የቅጣቱ ገንዘብ እስከሚከፈል ጊዜ ድረስ ተሽከርካሪው ይያዛል፡፡

፬. በሰንጠረዡ"ሀ" ፫.፩ ፫.፺ እና ፫.፲ የተመለከቱትን የጥፋት ዓይነቶች ለሚመለከተው ጥቆማ ያደረገ የቅጣቱ ገንዘብ ገቢ እንደሆነ ሃምሳ በመቶ (፶ በመቶ) የጠቋሚ አበል ይከፈለዋል፡፡

፰. <u>ቅጣቱ የሚጨምራቸው /የማያስቀራቸው ጉዳዮች</u>

በሠንጠረዥ "ሀ" የተመለከተቅጣት፤

ሀ) በወንጀል የሚያስጠይቅ ድርጊት ከሆነ የወንጀሉን ቅጣት በፍጹም አያስቀሩም፤

ለ)ቅጣቱ ሕገወጡን ነገር ለማስወገድና ለመተካት ባለስልጣኑ የሚያወጣውን ወጭዎች አይጨምርም፤

ሐ) የተበላሸ ነገር ካለ አጥፊው በተተመነው ልክ የመክፈል ግዴታውን አያስቀርም፤

መ)ተደጋጋሚ ጥፋተኞች በእስር እንዲቀጡ ባለስልጣኑ ፍርድ ቤት ክስ የማቅረብ መብቱን አያስቀርም፤

ሠ)ባለስልጣኑ በተደጋጋሚ አጥፊዎች ላይ ተጨማሪ እርምጃ በአስተዳደሩ አካላት እንዲወሰዱ የማስደረግ መብቱን አያስቀርም፤

፺. <u>አስፈፃሚ አካላት</u>

፩. በዚህ ደንብ መሰረት በሠንጠረዥ "ሀ" የተመለከቱትንጥፋቶች፤

፪.በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፩ መሠረት እና በዚህ ደንብ አንቀፅ ፺ መሠረት የማስፈፀም ሀላፊነት እና ውክልና የተሠጣቸው አካሎች የተቀበሉትን ሥልጣንና ተግባር በሥራ ላይ ሲያውሉ ስለዚህ ጉዳይ የወጡ ወይም የሚያወጡ ሕጎች ደንቦችና መመሪያዎችን፤ ከባለስልጣኑ የሚሰጡ ጥዕዛዞችን መከተልና መጠበቅ ይኖርባቸዋል፡፡

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>ስለ አቤቱታ አቀራረብ፣ ስለ ሥልጣን ውክልና እናመመሪያዎችን ስለመቀበል</u>

፺. <u>ስለ አቤቱታ አቀራረብ፤</u>

፩. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ እንደተጠበቀ ሆኖ

ሀ) ተቀጪው የማይስማማበትን ምክንያት በማስረጃ አስደግፎ በመግለጽ አቤቱታውን በ ፫ የስራ ቀናት ውስጥ ለአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ባለስልጣን ማቅረብ ይቻላል፡፡ ባለስልጣኑም የቅጣት ትኬቱን ከሰጠው አካል ጋር በመሆን አቤቱታውን በማየት በ፲ ቀናት ጊዜ ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፡፡ አቤቱታ የቀረበበት አካል ጥፋት መፈጸሙ ሲረጋገጥ ተገቢ ሕጋዊ እርምጃ ይወሰድበታል፡፡

ለ) ቅጣቱ ሳይነሳ ከቀረና ተቀጪው በውሣኔው ካልተስማማ ቅጣቱን ለባለስልጣኑ ከፍሎ በዚህአንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሰረት አቤቱታውን ለአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪ ደረጃ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይቻላል፡፡

፪. ተቀጪው በተሰጠው የቅጣት ትኬት የማይስማማ ሲሆን ለባለስልጣኑ ከፍሎ በ፲፰ ቀናት ውስጥ ለአዲስ አበባ

ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፡፡

፳. <u>ስልጣን ውክልና እና መመሪያዎችን ስለመቀበል</u>

፩. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ባለስልጣኑ ይህን ደንብ ለማስፈፀምበአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሥር ላሉ መንግስታዊና ሕዝባዊ አካላት ውክልና መስጠት ይቻላል፡፡

፪. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፩ መሠረት እና በዚህ ደንብ አንቀፅ ፺ መሠረት የማስፈፀም ሀላፊነት እና ውክልና የተሠጣቸው አካሎች የተቀበሉትን ሥልጣንና ተግባር በሥራ ላይ ሲያውሉ ስለዚህ ጉዳይ የወጡ ወይም የሚያወጡ ሕጎች ደንቦችና መመሪያዎችን ፤ ከባለስልጣኑ የሚሰጡ ጥዕዛዞችን መከተልና መጠበቅ ይኖርባቸዋል፡፡

| | | |
|---|---|---|
| 3.1. | ለግንባታም ሆነ ለሌላ ጉዳይ የሚሆኑ ድንጋይ፡አፈር፡ወዘተ መንገድ ላይ ማራገፍ የትራንስፖርት ባለስልጣን የሾፌሩን መንጃ ፈቃድ በማገድ ከሚጥለው ቅጣት በተጨማሪ | 500 |
| 3.2 | ለግንባታም ሆነ ለሌላ ጉዳይ የሚሆኑ ድንጋይ መፍለጥ ወይም መጥረብ | 50 |
| 3.3 | ቆሻሻ መጣል፣ ጭቃ ማቡካት፣ ቋሚም ሆነ ጊዚያዊ ክልከላና መሰናክል ማድረግ | 50 |
| 3.4 | የንግድ ዕቃ ወይም ሌላ ዕቃ ለአጭርም ሆነ ለረጅም ጊዜ ማስቀጥ | 50 |
| 3.5 | ማንኛውም ሰው በሕጋዊ መንገድ ከያዘው ይዞታ ውጭ በመሆኑ መንገድን፣ በማስተር ፕላኑ መሰረት ለመንገድነት የተያዙ ክፍት ቦታዎችን፣ በመንገዶች ግራና ቀኝ ያሉ የእግረኛ መንገድን የሸቀጥ ዕቃዎችን ደርድሮ በማስቀመጥ ወይም ለተጠቀሚ የሚሆን ወንበሮችን መደርደር፣ ዛፍና አትክልት በመትከል መንገደኛንም ሆነ ተሽከርካሪን ማሰናከል መንገድ ላይ ማቆም ክልክል ነው የሚል ወይም መሰል ምልክትም ሆነ ማናቸውንም ግንባታ ማቆም ቤት መስራትና አጥር ማጠር | 50 |
| 3.6 | በመንገድ ላይ ከብት ማሰማራት፣ የከብተ ንግድ ማካሄድ | 50 |
| 3.7 | አውቆም ሄነ በድንገተኛ ሁኔታ በድልድዮች በመንገድ መብራቶችና ቋሚዎች (ፖሎች)፣ በትራፊክ ምልክቶች በትራፊክ መብራቶች በእግረኛ መከላከያዎች፣በማንሆሎች፣ በፉካዎች ወይም በክዳኖቻቸው በአጠቃላይ ባለስልጣኑ በደንብ ቁጥር፺/0፱)( መሰረት በሚያስተዳድራቸው ንብረቶች ላይ ጉዳት አድርሶ ለባለስልጣኑም ለትራፊክ ፖሊስ አለማሳወቅ | 500 |
| 3.8 | መንገዶችን ማሻሻል፣ መቀየር ፣ መቀነስ፣ በበር መዝጋት፣ በኬላ ማጠር፣ መቁረጥ፣ መስበር፣ መቆፈር ወይም በሌላ ሁኔታ ተሽከርካሪም ሆነ እግረኛው እንዳይተላለፍ ማድረግ | 500 |

| | | |
|---|---|---|
| 3.9 | የዋና መንገዶች በማናቸውም ምክያት አለመዘጋት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በነዘን ምክንያት ሳይሆን የእግረኛውንም ሆነ የተሽከርካሪን መንገድ ድንኳን በመጣል (በመትከል) በከፊልም ሆነ በሙሉ መዝጋት | 150 |
| 3.10 | የግንባታ ተረፈ ውጤቶችን፣ አፈር ወዘተ መድፋት | 1000 |
| 3.11 | ሆን ብሎ የመጸዳጃ ቤት ፍሳሽ ከመንገድ ጋር ማገናኘት እና መልቀቅ | 500 |
| 3.12 | ባለስልጣኑ መንገድም ሆነ ሌሎች ስራዎችን ካጠናቀቀ በኃላ የተቀመጡትንምብረቶች ሥራ ላይ የዋሉም ሆነ የተረፉ ግብዓቶችን በመንቀል በመቆፈር በማንሳት ወይም በማናቸውም ሁኔታ መውሰድ ለታለመላቸው ዓላማ እንዳይውል ማድረግ | 500 |
| 3.13 | መንገድ ላይ የተበላሹ ተሽከርካሪ መጠገን ድንጋየ መደርደር ጭኖ የሚሄዱትን በመንገድ ላይ መንጠባጠብ ወይም መጣል | 100 |
| 3.14 | የማይሰራ መኪና፣ ተሳቢ፣ ተጎታች ቡቴ ወዘተ ማቆም በጎታች መኪና ለማንሳት ከሚጠይቀው ወጪ በተጨማሪ | 500 |
| 3.15 | በመንገድ ላየ ተሽከርካ ማሳጠብ | 100 |
| 3.16 | የመንገድ አካፋይ፣ ደሴቶችን (ሜድያን) የሚያፈርሱት ተሽከርካሪ ጉዳት የደረሰበትን ንብረት ግምት እጥፍ ይከፍላል፡፡ | |

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፱. መመሪያ ማውጣት

ይህ ደንብ ለማስፈጸም ባለስልጣኑ መመሪያዎችን ለማውጣት ይችላል፡፡

፲. ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች

ከዚህ ደንብ ጋር የማይጣጣም ሕግ ወይም አሰራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ልይ ተፈጻሚነት አይኖረውም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንገድ ታራፊክ ደኅንነትደንብ ቁጥር ፳/፲፱፻፺ ላይ ሠንጠረዥ “ሀ"

፩. የመጀመሪያ የቅጣት እርከን ተራ ቁጥር ፪፣ ፲፩፣እና ፲፪

፪. ሁለተኛ የቅጣት እርከን ተራ ቁጥር ፲፳

፫. ሦስተኛው የቅጣት እርከን ተራ ቁጥር ፱፣ ፲፫ እና፲፬

፬. አምስተኛው የቅጣት እርከን ተራ ቁጥር ፰፣ ፱ እና ፲ የተመለከቱትን የጥፋት ዓይነቶች በዚህ ደንብ ተተክተዋል፡፡

፲፩. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በአዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል

አዲስ አበባ

ነሐሴ ፳፫ ቀን ፲፱፻፺፳ ዓ.ም

# የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ሕዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ምክር ቤት ለማቋቋም የወጣ ደንብ ቁጥር ፵፩/፪ሺ፲፫

ማውጫ


ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

፩. አጭር ርዕስ

፪. ትርጓሜ

፫. መቋቋም

፬. አላማ

፭. የተፈፃሚነት ወሰን

ክፍል ሁለት

ስለምክር ቤቱ አካላትና አባላት

፮. ስለምክር ቤቱ አካላት

፯. ስለምክር ቤቱ አባላት

፰. ስለምክር ቤቱ ጽህፈት ቤት

ክፍል ሶስት

ስልጣን፣ ተግባርና የስብሰባ ስነ-ስርዐት

አጭር መግለጫ

፱. የምክር ቤቱ ስልጣንና ተግባር

፲. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስልጣንና ተግባር

፲፩. የምክር ቤቱ ሰብሳቢ ስልጣንና ተግባር

፲፪. የምክር ቤቱ ምክትል ሰብሳቢ

፲፫. የምክር ቤቱ ፀሀፊ ስልጣንና ተግባር

፲፬. የምክር ቤቱ አባላት መብት

፲፭. የምክር ቤቱ አባላት ግዴታ

፲፮. የምክር ቤቱ የስብሰባ ስነ-ስርዐት

ክፍል አራት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፲፯. በጀት

፲፰. ስለሂሳብ መዝገብ አያያዝ

፲፱. መመሪያ የማውጣት ስልጣን

፳. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ


ይህ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ሕዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ምክር ቤት መቋቋምን፣ አላማውን እና የተፈፃሚነት ወሰንን ይደነግጋል፡፡ በተጨማሪም ስለአስተባባሪው ምክር ቤት አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባር እንዲሁም አጠቃላይ ሁኔታ በዝርዝር ይደነግጋል፡

<u>በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ሕዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ምክር ቤት ለማቋቋም የወጣ ደንብ ፵፩/፪ሺ፫</u>

በታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብግ ንባታ በከተማዋ ነዋሪዎች የተፈጠረውን መነሳሳት ወደ ላቀ ደረጃ በማሸጋገር የሕዳሴው ጉዞ፣ ግቦችና እሴቶች ላይ ብሔራዊ መግባባትን ማጠናከርበ ማስፈለጉ፤ የከተማዋ ነዋሪዎች የታሪካዊውን የህዳሴ ግድብ ግንባታ ለማሳካት፣ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ የሚያደርጉበትንና በሂደቱም የቁጠባ ባህል እና በራስ የመተማመን መንፈስ የሚያዳብሩበትን ሁኔታ ለመፍጠር የሕዝቡን ንቅናቄ በተደራጀ አኳኋን መምራት በማስፈለጉ፤

የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፰አንቀጽ ፳፫ /፩/ ረ/ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

<u>ክፍል አንድ</u>

<u>ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>

<u>፩. አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ “በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ሕዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ምክር ቤት አደረጃጀትና አሰራር ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፵፩/፪ሺ፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪.<u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩. “ከተማ” ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፡፡

፪. “ምክር ቤት” ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ሕዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ምክር ቤት ነው፡፡

፫. “ኮሚቴ” ማለት አንድን ጉዳይ ለማከናወን እንደ አስፈላጊነቱ በምክር ቤቱ የሚቋቋም አስተባባሪ፣ ቋሚ፣ ንዑስ ወይም ጊዜያዊ ኮሚቴ ነው፡፡

፬. “የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ” ማለት በከተማው ከንቲባ የሚሰየም ሆኖ በመንግስት፣ በምክር ቤቱና በብሔራዊ ምክር ቤቱ የታላቁ የህዳሴ ግድብን በተመለከተ የሚቀመጡ አቅጣጫዎች እና ውሳኔዎች የሚያስፈፅምና የሚከታተል አካል ነው፡፡

፭. “አስተዳደር” ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፡፡

፮. “ብሔራዊ ምክር ቤት” ማለት በሚንስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፵፬/፪ሺ፫መሰረት የተቋቋመው የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ሕዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ብሔራዊ ምክር ቤት ነው፡፡

፲. “ጽሕፈት ቤት” ማለት በዚህ ደንብ መሰረት የተቋቋመ የምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤት ነው፡፡

፲፩.“ሕዝባዊ ተሳትፎ” ማለት በዓባይ ወንዝ ላይ ለሚሰራው ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ድጋፍ እና የገንዘብ መዋጮ ለመሰብሰብ፣ ግንባታ ውን በስፋት ለማሳወቅ ወይም ለማበረታታት ታስበው በማናቸውም የሕብረተሰብ አደረጃጀቶች፣ በሙያ ማህበሮች ወይም ቡድኖች የሚዘጋጁ ሕዝባዊ ስብሰባዎች፣ ሰልፎች፣ የህዝብ ትርኢቶች፣ የንግድና የመሳሰ ሉትን እንቅስቃሴዎች ያካትታል፡፡

፫. መቋቋም

፩. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ የሕዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ምክር ቤት በዚህ ደንብ መሰረት ተቋቁሟል፡፡

፪. ምክር ቤቱ የራሱ ጽሕፈት ቤት ይኖረዋል፡፡

፫. ምክር ቤቱ ተጠሪነቱ ለአዲስ አባባ ከተማ ከንቲባ ይሆናል፡፡

፬. ዓላማ

፩. በታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ዙሪያ በከተማዋ ነዋሪዎች የተፈጠረውን መነሳሳት ወደ ላቀ ደረጃ በማሸጋገር በህዳሴው ጉዞ ግቦችና እሴቶች ላይ ብሔራዊ መግባባትን ለማጠናከር፤

፪. የህዝቡ ንቅናቄ በተደራጀ አኳኋን እየተመራ የታሪ ካዊው የህዳሴ ግድብ ግንባታ እውን እንዲሆን ህዝቦች የዜግነት ድርሻቸውን እንዲወጡ ለማድረግ በሂደቱ የከተማዋ ነዋሪዎች የቁጠባ ባህል እና በራስ የመተማመን መንፈስ በቀጣይነት የሚያዳብ ሩበትን ሁኔታለመፍጠር፤

፫. በታላቁ የሕዳሴ ግድብ ግንባታ የተፈጠረውን የህዝቡን በጎ ስሜትና አቅም በላቀ ደረጃ ተጠቅሞ በከተማችን ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ለውጥን ይበልጥ ለማረጋገጥ ተጨማሪ አቅም እንዲሆን ማስቻል፤

፬. የከተማችን ነዋሪዎች በተለያዩ ሕዝባዊ ተሳትፎዎች የሚሳተፉበትን ሁኔታ በማመቻቸት ለግድቡ ግንባታ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ማስቻል፤

፭. በከተማችን ነዋሪዎች የአባይ ወንዝ ፍትሐዊ ተጠቃሚነት አስተሳሰብ እንዲዳብርና ልማታችንን ለማደናቀፍየ ሚንቀሳቀሱ ኃይሎችን በንቃት ለመመከት፡፡

፭. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ ደንብ የታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታን ለመደገፍ በከተማው በሚከናወን ማንኛውም ሕዝባዊ ተሳትፎ እንቅስቃሴ ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ሰለ ምክር ቤቱ አካላትና አባላት

፮. ስለ ምክር ቤቱ አካላት

ምክር ቤቱ የሚከተሉት አካላትይኖሩታል:-

፩. የምክር ቤቱ ጉባኤ፤

፪. ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ፤

፫. እንደአስፈላጊነቱ የሚቋቋሙ ኮሚቴዎች፤ እና

፬. የምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤት፡፡

፮. <u>ስለ ምክር ቤቱ አባላት</u>

የምክር ቤቱ አባላት ቁጥር ፩፻፶ ሆኖ የሚከተሉትን አባላት ያካተተ ይሆናል:-

፩. የከተማው ምክትል ከንቲባ--------------------ሰብሳቢ፤

፪. የከንቲባው የህዝብ ግንኙነት አማካሪ------------------------------------------------ ምክትል ሰብሳቢ፤

፫. የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ (ያለድምፅ)----------------ፀሐፊ፤

፬. የከተማው ዋና ሥራ አስኪያጅ--------------------አባል፤

፭. የከተማው ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ-----------------አባል፤

፮. የከተማ አስተዳደር ቢሮዎች፣ ኤጀንሲዎች፣ ኮሚሽ ኖች፣ የባለስልጣን መስሪያ ቤቶች፣ የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት የከተማው የልማት ድርጅቶችና ሌሎች በተመሳሳይ ደረጃ የሚገኙ-------------አባል፤

፯. የዓሥሩ ክፍለ ከተማ ዋና ስራ አስፈፃሚዎች -------------አባል፤

፰. የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተወካይ ------------------------------------አባል፤

፱. የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተወካይ----------------አባል፤

፲. ከየኃይማኖት ተቋማቱ ተወካይ ----------------------አባል፤

፲፩. የአዲስ አበባ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ተወካይ ------------------------------------አባል፤

፲፪. የጥቃቅንና አነስተኛ አንቀሳቃሾች ተወካይ-------አባል፤

፲፫. መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተወካይ----------አባል፤

፲፬. የቲያትር ባለሙያዎች ማህበር ተወካይ-----------አባል፤

፲፭. የፊልም ባለሙያዎች ማህበር ተወካይ-------------አባል፤

፲፮. የሙዚቀኞች ማህበር ተወካይ------------------------አባል፤

፲፯. የወጣቶች ፌዴሬሽን ተወካይ -------------------አባል፤

፲፰. የሴቶች ፌዴሬሽን ተወካይ--------------------------አባል፤

፲፱.የነዋሪዎች ፎረም ተወካይ ---------------------------አባል፤

፳. የወጣቶች ፎረም ተወካይ------------------------------አባል፤

፳፩. የሴቶች ፎረም ተወካይ-------------------------------አባል፤
፳፪. የወጣቶች ማህበራት ተወካይ-----------------------አባል፤
፳፫. የሴቶች ማህበራት ተወካይ---------------------------አባል፤
፳፬. የመምህራን ማህበር ተወካይ-------------------------አባል፤

፳፫.የሙያ ማህበራት (የህግ፣ የጤና፣ የምህንድስና፣ የኢኮኖሚክስ እናየሌሎች ማህበራት)ተወካይ---- አባል፤
፳፬. የሰራተኛ ማህበራት ተወካይ -----------------------አባል፤
፳፮. የአሰሪዎች ማህበር ተወካይ--------------------------አባል፤
፳፰. የአካል ጉዳተኞች ማህበር ተወካይ-----------------አባል፤
፳፱. የዕድሮች ህብረት ተወካይ --------------------------አባል፤
፴. የታዋቂ ሰዎች ተወካይ----------------------------------አባል፤
፴፩. የምሁራን ተወካይ -------------------------------------አባል፤
፴፪. የኢትዮጵያ አርበኞቸ ማህበር ተወካይ------------አባል፤
፴፫. የሥራ አሥፈጻሚ ኮሚቴ በዚህ አንቀጽ ከተመለከተው በተጨማሪ የምክር ቤቱ አባል እንዲሆኑ ሊፈቅድይችላል፡፡

፰. ስለ ምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤት

የምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤት:-

፩. ራሱን የቻለ የህግ ሰውነትይኖረዋል፤
፪. በከተማው ከንቲባ የሚሾም አንድ የጽሕፈት ቤት ኃላፊና ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ኮንትራክት ሰራተኞች ይኖሩታል፤
፫. የምክር ቤቱን የዕለት ተዕለት የስራ እንቅስቃሴ ይፈጽማል፣ይከታተላል፤
፬. የምክር ቤቱን ውሳኔዎች ያስፈጽማል፤ ለሚመለከታቸው አካላትያስተላልፋል፤
፭. በሰብሳቢው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራትያከናውናል፡፡

## ክፍል ሦስት

## ስልጣን፣ ተግባርና የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት

፱. የምክር ቤቱ ስልጣንና ተግባር

ምክር ቤቱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራትይኖሩታል፡-

፩. በዚህ ደንብ የተመለከቱትን ዓላማዎች ለማስፈፀም በሰ ብሳቢው የሚቀርቡለትን የአጭርና የረዥም ጊዜ እቅዶች፣ መርሃ ግብሮች እና ፕሮጀክቶችን ያጸድቃል፤
፪. ከሚመለከታቸው ሌሎች የመንግስት አካላት ጋር በመ መካከር እና በመቀናጀት መላው የከተማ ነዋሪ ለግድቡ ግንባታ አስተዋጽኦ የሚያደርግበትን ስልት ይቀይሳል፤
፫. የህዝቡ ስሜት ግለቱን ጠብቆ እንዲሄድ የሚያስችሉ የንቅናቄ ሥራዎችን ውጤታማ በሆነ አግባብ እንዲፈፀም ማስቻል፣ በተለይም የህዝቡን ንቅናቄ ለማጠናከር የሚያስችሉ መድረኮች በከተማ፣ በክፍለ ከተማ፣ በወረዳ፣ በመንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች እና በግል ተቋማት ጭምር መድረኮች እንዲፈጠሩ ያመቻቻል፤
፬. ከግድቡ ግንባታ ህዝባዊ ተሳትፎ ልምድ እንዲሁም የሕዝቡን መልካም ስሜት በመጠቀም የከተማዋ ነዋሪ በተጀመሩት የልማትና የመልካም አስተዳደር ስራዎች እንዲሁም በሁሉም የሃገር ግንባታ መስኮች ተሳትፎውን እንዲያጎለብትና እንዲያጠናክር ያበረታታል፣ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
፭.የከተማችን ነዋሪ በየአደረጃጀቱና በየተቋሙ የቁጠባ ባህል እንዲያዳብር ድጋፍና ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፤
፮.በከተማችን ከቦንድ ሽያጭ በተጨማሪ የሕዝባዊ ተሳትፎ እንቅስቃሴ በመጠቀም ተጨማሪ ገቢ እንዲሰበሰብ ያደርጋል፤
፯. በከተማዋ ለታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ስለተሰበሰበው የገቢ መጠን ከፌደራል መንግስትና ከብሔራዊ ምክር ቤቱ ጋር በመመካከር ለከተማዋ ነዋሪዎች እንዲገለጽ ያደርጋል፤
፰.የከተማችን የታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ የገቢ አሰባሰብ ሥርአት ከብሔራዊ ምክር ቤቱ የገቢ አሰባሰብ ሥርዓት ጋር የተጣጣመ መሆኑን ያረጋግጣል፤
፱. የከተማዋ ነዋሪዎች ብሔራዊ መግባባትን እንዲፈጥሩና በፀረ ልማት ኃይሎች የግድቡን ግንባታ ለማደናቀፍ የሚከናወኑ ማናቸውንም እንቅስቃሴዎች የሚያመክን የህዝብ ግንኙነት ሥራዎች እንዲከናወኑ ይደርጋል፤

፲. ዓላማውን ለማስፈጸም አስፈላጊ የሆኑ ቋሚ፣ ጊዚያዊ፣ ወይም ንኡሳን ኮሚቴዎችን ያደራጃል፣ ሪፖርታቸውን ያዳምጣል፤

፲፩.እንደአስፈላጊነቱ ተመሳሳይ የምክር ቤት አደረጃጀት በክፍለ ከተማና በወረዳ ደረጃ እንዲቋቋም ያደርጋል፤ ስልጣንና ተግባራቸውንም ይወስናል፤

፲፪.የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት የሚወስን መመሪያ ያወጣል፤

፲፫.ከብሄራዊ ምክር ቤቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

፲. <u>የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስልጣንና ተግባር</u>

የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በከተማው ከንቲባ የሚሰየም ሰብሳቢና ፀሐፊ ጨምሮ ከ ፯ የማያንሱ ዓባላት ይኖሩታል፤ ተጠሪነቱ ለምክር ቤቱ ሆኖ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩. የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ከተማ አቀፍ ሥራዎችን የአጭርና የረጅም ጊዜ ዕቅድ ይገመግማል፤ የአፈጻጸም አቅጣጫዎች ያስቀምጣል፤ ለእቅዱ ተፈጻሚነት ትኩረት ሰጥቶ ያስተባብራል፤

፪. እቅዱን ለማስፈጸም አስፈላጊ የሆኑኮሚቴዎችን በመ ንግስትና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች፣ በግል ተቋማት፣ እና የተለያዩ አደረጃጀቶችን ያቋቁማል፤ ኃላፊነ ታቸውን በትክክል መወጣታቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

፫. እቅዱን ለማስፈጸም በየደረጃው የተቋቋሙ ኮሚቴዎችን የግንኙነት ጊዜ አስቀምጦ የሥራ እንቅስቃሴያቸውን ወቅታዊ ሪፖርትያዳምጣል፤ እንዲሁም እንደ ኮሚቴ ያከናወናቸውን ተግባራት በጋራ ይገመግማል፤ ወርሃዊ ሪፖርት ለከተማው ከንቲባና ለምክር ቤቱ ሰብሳቢ ያቀርባል፤

፬. ለታላቁ የህዳሴ ግድብ ገቢ ማስገኛ የተጣለውን ግብ ተግባራዊ ለማድረግ የቦንድ ሽያጭና የህዝባዊ ተሳትፎ እነቅስቃሴን ያስተባብራል፤ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤

፭. ከተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት አስፈላጊ የሆኑ ሰራተኞችን በትውስት የሚመጡበትን ሁኔታያመቻቻል፡፡

፲፩.<u>የምክር ቤቱ ሰብሳቢ ስልጣንና ተግባር</u>

፩.በዚህ ደንብ አንቀጽ ፱ መሰረት ለምክር ቤቱ የተሰጡትሥልጣንና ተግባራት በአግባቡ መፈጸ ማቸውን ያረጋግጣል፣ በበላይነት ይቆጣጠራል፡፡

፪.የምክር ቤቱን ስብሰባዎች ይመራል፡፡

፫.የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ በመሆን ይሰራል፡፡

፬.የምክር ቤቱን አስቸኳይ ስብሰባዎች ይጠራል፡፡

፭.በዚህ ደንብ አንቀጽ ፱ንኡስ አንቀጽ ፲መሰረት ለሚቋቋሙ ኮሚቴዎች ሰብሳቢ ይሰይማል፡፡

፮.ምክር ቤቱን በመወከል ግንኙነት ያደርጋል፡፡

፯.ለምክር ቤቱ ተጠሪ የሆኑ አካላት ኃላፊዎችን ይሰይማል፡፡

፰.የምክር ቤቱን ውሳኔ አፈጻጸም ይከታተላል፡፡

፱. የምክር ቤቱን የአጭርና የረዥም ጊዜ ዕቅድና በጀት ለምክር ቤቱ በማቅረብ ያስፀድቃል፡፡

፲. በየሩብ ዓመቱ እና በየስድስት ወሩ የምክር ቤቱን የዕቅድ ክንውን አፈጻጸም ለምክር ቤቱ ያቀርባል፡፡

፲፩. በምክር ቤቱና በብሔራዊ ምክር ቤቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

፲፪. <u>የምክር ቤቱ ምክትል ሰብሳቢ</u>

፩. ሰብሳቢው በሌለበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ሰብሳቢውን ተክቶ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፩ለሰብሳቢው የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት ያከናውናል፡፡

፪. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ፀሐፊ በመሆን ይሰራል፡፡

፫. በሰብሳቢው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናወናል፡፡

፲፫.<u>የምክር ቤቱ ፀሐፊ ስልጣንና ተግባር</u>

፩. ጽሕፈት ቤቱን ያደራጃል፤ ለጽሕፈት ቤቱ አስፈላጊ የሆኑ ሰራተኞችን ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፡፡

፪. የምክር ቤቱን የአጭርና የረዥም ጊዜ ዕቅድ እንዲሁም በጀት ያዘጋጃል፤ ሲጸድቅና ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡
፫. ለምክር ቤቱ የሚቀርቡትን አጀንዳዎች ከሰብሳቢው ጋር በመመካከር ያዘጋጃል፡፡
፬. የምክር ቤቱን ቃለ ጉባኤዎች ይመዘግባል፣ ይይዛል፡፡
፭. ምክር ቤቱን የሚመለከቱ ሰነዶች መያዛቸውን ያረጋግጣል፡፡
፮. ያለ ድምጽ በሥራ አስፈፃሚ ኰሚቴ ስብሰባ ይሳተፋል፡፡
፯. በሰብሳቢው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

፲፬. የምክር ቤቱ አባላት መብት

ማንኛውም የምክር ቤቱ አባል:-

፩. በምክር ቤቱ ስብሰባ የመሳተፍና ሃሳቡን በነጻነት የመግለጽ፤
፪. በምክር ቤቱ በሚደራጁ ቋሚ፣ ጊዜያዊ ወይም ንዑሳን ኮሚቴዎች በአባልነት የመሳተፍ፤
፫. በምክር ቤቱ የሚተላለፉ ውሳኔዎችን የማወቅ መብት ይኖረዋል፡፡

፲፭. የምክር ቤቱ አባላት ግዴታ

ማንኛውም የምክር ቤቱ አባል፡-

፩. በምክር ቤት መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባ በሰዓቱ የመገኘት፤
፪. በምክር ቤቱ በሚደራጁ ቋሚ ጊዜያዊ ወይም ንዑሳን ኮሚቴዎች በአባልነት የመስራት፤
፫. በምክር ቤቱ በሚደራጁ ቋሚ፣ ጊዜያዊ ወይም ንዑሳን ኮሚቴዎች አገልግሎት በነፃ የመስጠት፤
፬. ምክር ቤቱ በሚስጥር እንዲጠበቁ ያስተላለፋቸውን ውሳኔዎች ሚስጥር የመጠበቅ ግዴታ አለበት፡፡

፲፮. የምክር ቤቱ የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት

፩. ምክር ቤቱ በየሦስት ወሩ መደበኛ ስብሰባ ይኖረዋል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሰብሳቢው አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡
፪. ማናቸውም የምክር ቤቱ ስብሰባ ከምክር ቤቱ አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፡፡
፫. የምክር ቤቱ ውሳኔ የሚያልፈው በስብሰባው ከተገኙ የምክር ቤቱ አባላት ከግማሽ በላይ ሲደ ገፍ ይሆናል፡፡

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፲፯. በጀት

፩. በከተማ አስተዳደሩ የሚመደብ በጀት፤
፪. ከዕርዳታ እና ስጦታ፤ እንዲሁም
፫. ከልዩ ልዩ የገቢ ምንጮች የሚሸፈን ይሆናል፡፡

፲፰. ሰለ ሂሳብ መዝገብ አያያዝ

፩.ጽሕፈት ቤቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፡፡
፪. የጽሕፈት ቤቱ ሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በአስተዳዳሩ ዋና ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች ይመረመራሉ፡፡

፲፱.መመሪያ የማውጣት ስልጣን

የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ይህን ደንብ ለማስፈጸም የሚረዱ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

፳. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ ደንብ ከግንቦት ፳፭ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ<br>
ግንቦት ፳፭ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም<br>
ኩማ ደመቅሳ<br>
የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ

## በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኪነ ጥበብ የፈጠራ ሥራዎች፣ ባለሙያዎች ማበረታቻና የአገልግሎት ክፍያ አፈፃፀምን ለመደንገግ የወጣ ደንብ ፵/፪ሺ፰ አጭር መግለጫ

ማውጫ

1. ክፍል አንድ ጠቅላላ
2. ክፍል ሁለት ስለ ክፍያ ተመንና አፈፃፀም
3. ክፍል ሦስት ስለተከለከሉ ድርጊቶችና ቅጣት
4. ክፍል አራት ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

አጭር መግለጫ

የፈጠራ ሰዎች ኪነ-ጥበብን ለልማት ለማዋል ህብረተሰቡን እያዝናኑ በማስተማር ለሚፈጠረው መልካም አስተዳደር ለሚያበረክቱት የፈጠራ አስተዋጽኦና ለሚሰጡት ድጋፍ በየደረጃው የሚያበረታታና ቴአትር ቤቶችን በገበያ ተወዳዳሪ የሚያደርግ የተሻሻለ የክፍያ አፈፃፀም የሚደነግግ ህግ ነው፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኪነ ጥበብ የፈጠራ ሥራዎች፣ ባለሙያዎች ማበረታቻና የአገልግሎት ክፍያ አፈፃፀምን ለመደንገግ የወጣ ደንብ ፶፫/፪ሺ፭**

በከተማዋ ፈጣን ልማትና ዕድገትን ለማምጣት፣ ኪነ-ጥበብን ለልማት ተግባር ለማዋልና ህብረተሰቡን እያዝናኑ ለማስተማር ልዩ ልዩ የኪነ-ጥበብ ውጤቶች የሆኑ የፈጠራ ሥራዎችን ከፈጠራ ባለሙያዎች አወዳድሮ በግዥ ለማግኘትና በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችል ወጥ የሆነ የክፍያ ደንብ ባለመኖሩ አዲስ አሰራር ማዘጋጀት በማስፈለጉ፣

የፈጠራ ሰዎች ኪነ-ጥበብን ለልማት ለማዋል ህብረተሰቡን እያዝናኑ በማስተማር ለሚፈጠረው መልካም አስተዳደር ለሚያበረክቱት የፈጠራ አስተዋጽኦና ለሚሰጡት ድጋፍ በየደረጃው የሚያበረታታና ቴአትር ቤቶችን በገበያ ተወዳዳሪ የሚያደርግ የተሻሻለ የክፍያ አፈፃፀም ደንብ በማስፈለጉ

መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ መሥሪያ ቤቶችና ተቋማት ከቴአትር ቤቶች ለሚፈልጓቸው ልዩ ልዩ የኪነ-ጥበብ ውጤቶችና የአዳራሽ ኪራይ አገልግሎት፣ ከቴአትር ቤቶች መድረክ ውጭ ለሚሰጡ የኪነ-ጥበብ ውጤቶች አገልግሎት ለተሳታፊ የኪነ-ጥበብና የቴክኒክ ባለሙያዎች የጽዳት መጠበቂያና የላብ ማካካሻ ክፍያ ተመኖችን ከወቅቱ የገበያ ሁኔታ ጋር አገናዝቦ መወሰን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የኪነ-ጥበብ ዝንባሌ ያላቸውን ህፃናትና ወጣቶችን በማሰልጠን ትምህርታቸውን በማያስተጓጉል ሁኔታ በህፃናትና ወጣቶች ቴአትር በሚቀርቡ ትርኢቶች ላይ ለማሳተፍና ቴአትር ቤቱ የኪነ-ጥበብ ባለሙያዎች መፍለቂያና መኮትኮቻ እንዲሆን ለማስቻል በዚህ መድረክ ለሚሳተፉ ህፃናትና ወጣቶች የማካካሻና ማበረታቻ የክፍያ ሥርዓት መወሰን በማስፈለጉ

በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩አንቀጽ ፲፱፻፺፭ ንዑስ አንቀጽ (፩)ረ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ «በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኪነ-ጥበብ ፈጠራ ሥራዎች፣ የባለሙያዎች ማበረታቻና የአገልግሎት ክፍያዎች አፈጻጸም ደንብ ቁጥር ፶፫/፪ሺህ፭» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪ ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፣

፩ «ከተማ» ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፣

፪. «አስተዳደር» ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፣

፫. «ቢሮ» ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ነው፣

፬. «አዋጅ»ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፴፭/፪ሺ፬ ነው፣

፭. «ቴአትር ቤቶች» ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ሥር የሚተዳደሩ ቴአትር ቤቶች ነው፣

፮ «ልዩ ልዩ የኪነ-ጥበብ የፈጠራ ጽሁፍና ዝግጅቶች » ማለት የመድረክ፣ የቴሌቪዥንና የሬዲዮ ድራማዎች፣ የፊልም ፅሑፎች፣ የዘፈን ግጥሞች፣ የዘፈን ዜማዎች ሙዚቃዊ ድራማዎች የዳይሬክቲንግ ወይም የዝግጅት ፈጠራዎች የሙዚቃ ቅንብር፣ የውዝዋዜ ቅንብሮች የመሳሰሉት ነው፣

፯ «የፈጠራ መብት» ማለት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፮ የተጠቀሱትን የፈጠራ ሥራዎች ፈጥረው የሚያቀርቡ ባለሙያዎች የሚያገኙት የክፍያ መብት ነው፣

፰ «የኪነጥበብ ባለሙያዎች» ማለት በልዩ ልዩ የኪነጥበብ ውጤቶች ውስጥ የሚሣተፉ ተዋንያን፣ ድምፃዊያን፣ የሙዚቃ መሣሪያ ተጫዋቶች፣ የውዝዋዜ ባለሙያዎች፣ የውዝዋዜ አሰልጣኞች፣ ረዳት አዘጋጆች፣ የዝግጅት አስተባባሪዎች ቴክኒካል ዳይሬክተሮች፣ ስቴጅ ማኔጀሮች፣ ፕሮዳክሽን ማኔጀሮች፣ ኤዲተሮች፣ ካሜራ ማኖች የመሣሰሉት ባለሙያዎች ነው፣ ተያያዥነት ያላቸውን የሙያ ዘርፎች የሚያካትት ነው፣

፲ «የክፍያ ተመን» ማለት በዚህ ደንብ አባሪ የሆኑ የልዩ ልዩ ክፍያዎችን ተመን የሚያሳየው በአባሪ ሠንጠረዥ ውስጥ የተመለከቱት ክፍያዎች ናቸው፣

፲፩«የቴክኒክ ባለሙያዎች» ማለት ልዩ ልዩ የኪነጥበብ ውጤቶች በተሟላ ሁኔታ አዘጋጅቶ ለማቅረብ በመድረክ ዲዛይንና ፕሮዳክሽን፣ በመብራት ዲዛይንና ፕሮዳክሽን በድምፅ ዲዛይንና ፕሮዳክሽን፣ በውበት ወይም በገፅ ቅብ ዲዛይንና ፕሮዳክሽን፣ በአልባሳትና በቁሣቁስ ዲዛይንና ፕሮዳክሽን ሥራዎች ለትርኢቱ ቴክኒካል ድጋፍ የሚሰጡ ባለሙያዎች ነው፣

፲፪ «የማበረታቻ ክፍያ»ማለት የኪነጥበብ እና ለቴክኒክ ባለሙያዎች ለሚያደርጉት ሙያዊ አስተዋፅኦ በየትርኢቱ የሚከፈል የማነቃቂያ ክፍያ ነው፣

፲፫«በቴአትር ቤቶች የሚሰጡ ልዩ ልዩ አገልግሎቶች» ማለት ለተለያዩ ጉዳዮች አዳራሾችን ማከራየት ፣ የባህልና የዘመናዊ ሙዚቃና ውዝዋዜ ዝግጅቶችን' የመድረክ ቴአትሮች"' ለተለያዩ ድርጅቶች በቁርጥ ክፍያ የሚሰጡ አገልግሎቶች ነው፣

፲፬«የፅዳት መጠበቂያና የላብ ማካካሻ ክፍያ» ማለት የመድረክ ቴአትሮች ወይም የባህልና የዘመናዊ ሙዚቃና ውዝዋዜ ዝግጅቶችን ከቴአትር ቤቶች መድረክ ውጪ ወይም ከአዲስ አበባ ከተማ ውጪ በቁርጥ ክፍያ ለሌሎች ድርጅቶች አገልግሎቶችን በሚሰጥበት ጊዜ በትርኢቱ ለሚሳተፉት የኪነጥበብ ባለሙያዎችና የቴክኒክ ድጋፍ ሰጪዎች የፀጉር መሰሪያ፣ የፅዳት መጠበቂያ እና ለላብ ማካካሻ የሚከ ል ክፍያ ነው፣

፫ <u>የደንቡ ተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ ደንብ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ሥር በሚተዳደሩት ቴአትር ቤቶች፣ ከራሳቸውና ከውጭ ተሠርተው ለህዝብ የሚቀርቡትን የልዩ ልዩ የኪነ-ጥበብ የፈጠራ ውጤቶችን ባለመብቶች፣የኪነጥበብ የቴክኒክ ባለሙያዎች እና በዚህ ደንብ ውስጥ የተገለፁትን አገልግሎት ለማግኘት በሚፈልጉት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

፬ የፆታ አገላለፅ

በዚህ ደንብ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ እስካልሆነ ድረስ በወንድ ፆታ የተገለፀ ቃል ለሴት ፆታም ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

፭መሠረታዊ መርሆዎች

፩. የከተማዋን ፈጣን ልማትና ዕድገትለማምጣትና ለማፋጠን፣

፪. ኪነ-ጥበብን ለልማት ተግባር ለማዋልና ህብረተሰብን እያዝናኑ ለማስተማር፣

፫. ልዩ ልዩ የኪነ-ጥበብ ውጤቶች የሆኑ የፈጠራ ስራዎች ከፈጠራ ባለሙያ አወዳድሮ በግዥ በማግኘት በስራ ላይ ለማዋል፣

፬. ወጥ የሆነ የባለሙያዎች ማበረታቻና የአገልግሎት ክፍያ ደንብ ለማውጣትና የከተማ አስተዳደሩን ገቢ አቅም ለማሳደግ፡፡

፮. ዓላማ

፩. ኪነጥበባዊ የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁ፣ ኪነጥበብ ለልማት በሚል ፍልስፍና የተመሩ፣ የከተማዋን አስተዳደር ቁልፍ የትኩረት አቅጣጫዎች በዋናነት መሠረት ያደረጉ፣ ህብረተሰቡን አያዝናኑ የሚያስተምሩ ልዩ ልዩ የኪነጥበብ ውጤቶችን፣ በተለያዩ የማስተላለፊያ መንገዶች ለህብረተሰቡ በማቅረብ ግንዛቤ በሚያስጨብጡ ሥራዎች ህዝባዊ ንቅናቄ በመፍጠር በኪነጥበብ ውጤቶቹ የረካ፣ አስተሳሰቡ የተለወጠና ለልማት የተነሣሣ ህብረተሰብ ለመፍጠር፣

፪. ባህል የሚያንፀባርቁ ባህላዊና ዘመናዊ ሙዚቃዎችንናውዝዋዜዎችን በእኩልነትና በስፋት አዘጋጅቶ በማቅረብ በማንነታቸው እንዲኮሩና በመፈቃቀድ ላይ የመሰረቱትን አንድነት እንዲያጠናክሩ ለማገዝ፣

፫. የባህል ወረርሺኞችን በመከላከል በጐ ባህላችንን ለማዳበር በልዩ ልዩ መድረኮችና የኪነጥበብ ውጤቶች በህብረተሰቡ ዘንድ ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ ለመስራት፣

፬. የተለያዩ የኪነጥበብ ውጤቶች የፈጠራ ባለቤቶችን የኪነጥበብና የቴክኒክ ባለሙያዎችን እንዲሁም ድጋፍ ሰጪዎችን ለተዋጡ ፈጠራዎችና ሥራዎች የሚያነሣሣናየሚያበረታታ መንፈስ ለመፍጠር፣

፭. በግሉ ዘርፍ በከተማዋ እየተስፋፉ የመጣውን አበረታች የሀገርኛ ፊልሞች የማምረት እንቅስቃሴ መስመር እንዳይስት፣ እንደመንግስት ተቋም ኃላፊነቱን ለመውሰድና የወደፊቱን

የፊልም እንዱስትሪ እድገት ሀገራዊ ፋይዳ ያለው አቅጣጫ የማስያዝ የአርአያነት ሚና ለመጫወት፣

፯. ቴአትር ቤቶች ቀድሞ በተወሰነ መልኩ በመድረክ ብቻ ተወስነው ሲሰጡ የነበረውን አገልግሎት በማስፋት በፊልም፤ በቴሌቪዥንና በሬዲዮ ድራማዎችም አገልግሎቶቻቸውን በማስፋት በገበያ ተወዳዳሪና የልማቱ አጋዥ ኃይል ለማድረግ፣

፰. ለተለያዩ የኪነጥበብ ውጤቶች የፈጠራ ባለቤቶች ውስን የነበረውን አሠራር በሌሎችም አማራጮች በማስፋት የፈጠራ ስራዎች እጥረትን መቅረፍ፣

፱. በከተማዋ ውስጥ የሚገኙ የሀገሪቱን ብሔር ብሔረሰቦችባህል የሚያንፀባርቁ ባህላዊና ዘመናዊ ሙዚቃዎችንና ውዝዋዜዎችን በእኩልነትና በስፋት አዘጋጅቶ በማቅረብ በማንነታቸው እንዲኮሩና በመፈቃቀድ ላይ የመሰረቱትን አንድነት እንዲያጠናክሩ ለማገዝ፣

፲. የባህል ወረርሺኞችን በመከላከል በጎ ባህላችንን ለማዳበር በልዩ ልዩ መድረኮችና የኪነጥበብ ውጤቶች በህብረተሰቡ ዘንድ ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ ለመስራት፣

፩. የተለያዩ የኪነጥበብ ውጤቶች የፈጠራ ባለቤቶችን የኪነጥበብና የቴክኒክ ባለሙያዎችን እንዲሁም ድጋፍ ጪዎችን ለተዋጡ ፈጠራዎችና ሥራዎች የሚያነሣሣና የሚያበረታታ መንፈስ ለመፍጠር፣

፮ በግሉ ዘርፍ በከተማዋ እየተስፋፋ የመጣውን አበረታች የሀገርኛ ፊልሞች የማምረት እንቅስቃሴ መስመር እንዳይስት፣ እንደ መንግስት ተቋም ኃላፊነቱን ለመውሰድና የወደፊቱን የፊልም እንዱስትሪ እድገት ሀገራዊ ፋይዳ ያለው አቅጣጫ የማስያዝ የአርአያነት ሚና ለመጫወት፣

፯ ቴአትር ቤቶች ቀድሞ በተወሰነ መልኩ በመድረክ ብቻ ተወስነው ሲሰጡ የነበረውን አገልግሎት በማስፋት በፊልም፤ በቴሌቪዥንና በሬዲዮ ድራማዎችም አገልግሎቶቻቸውን በማስፋት በገበያ ተወዳዳሪና የልማቱ አጋዥ ኃይል ለማድረግ፣

፰ ለተለያዩ የኪነጥበብ ውጤቶች የፈጠራ ባለቤቶች ውስንየነበረውን አሠራር በሌሎችም አማራጮች በማስፋት የፈጠራ ስራዎች እጥረትን መቅረፍ፣

## ክፍል ሁለት

### ፫ ስለ ክፍያ ተመንና አፈፃፀም

የኪነ-ጥበብ የፈጠራ ስራዎች፣ የኪነ-ጥበብ የቴክኒክ ባለሙያዎች ማበረታቻና ስለሚሰጡ አገልግሎቶች የክፍያ አፈፃፀምና ተመን ከዚህ ደንብ ጋር አባሪ በሆነው ሠንጠረዥ መሠረት ይሆናል፡፡

### ፬ ከዚህ የሚከተሉት የፈጠራ መብቶችና አገልግሎቶች የማበረታቻ ክፍያ የሚፈፀምባቸው ይሆናሉ

፩ የመድረክ፣ የቴሌቭዥን ወይም የሬዲዮ ድራማ የፊልም፤ ሙዚቃዊ ድራማ፤ የስፖት፣ ደራሲ

፪ ዳይሬክተር

፫ ተዋንያኖች

፬ የግጥም ደራሲዎች

፭ የዜማ ደራሲዎች

፮ የሙዚቃ አቀነባባሪዎች

፯ የሙዚቃ ማሣሪያ ተጫዋቾች

፰ ድምፃዊያን

፱ የውዝዋዜ አቀናባሪዎች

፲ ተወዛዋገሮች

፲፩ የዝግጅት አስተባባሪዎች

፲፪ የቴክኒክ ባለሙያዎች

፲፫ የሙዚቃና ውዝዋዜ ዝግጅት የማቅረብ አገልግሎቶች

፲፬ የቴአትር ኘሮዳክሽን የማቅረብ አገልግሎቶች

፲፭ የኪነ ጥበብ ውጤቶችን አዘጋጅቶ የማቅረብ አገልግሎቶች

፲፮ ስቴጅ ማናጀር

፲፯ የተጋባዥ የኪነጥበብ ባለሙያዎች የመድረክ ክፍያ

፲፰ ለተሣታፊ ባለሙያዎች የሚሰጥ የፅዳት መጠበቂያና የላብ ማካካሻ

፲፱ ፕሮዳክሽን ማናጀር

፳ ዲዛይነሮች

፳፩ ኤዲተሮች

፲ ክፍያዎችን የመፈፀም ስልጣን ፤

፩ ቴአትር ቤቶች አዘጋጅተው ለሚያቀርቧቸው ልዩ ልዩ የኪነጥበብ ውጤቶችና ባለሙያዎች አስፈላጊው የሆኑትን እና ከዚህ ደንብ ጋር አባሪ ለሆኑ የክፍያ ተመን መሠረት ክፍያዎችን የመፈፀም ስልጣን አላቸው፡፡

፪ ቢሮው ወይም በስሩ የሚተዳደሩት ቴአትር ቤቶች ከራሳቸውና ከውጭ ተሰርተው ለህዝብ የሚያቀርቡትን ልዩ ልዩ የኪነጥበብ ውጤቶችና ለሚያሣትፉቸው ባለሙያዎች በክፍያ ተመን ሠንጠረዥ ውስጥ የተገለፁትን አስፈላጊ ክፍያዎች የመፈፀም ስልጣን አላቸው፡፡

፫. ቴአትር ቤቶች አዘጋጅተው የሚያቀርቧቸውን ልዩ ልዩ የኪነጥበብ ውጤቶችና የኪነጥበብ ባለሙያዎችን ለማግኘት በሚያወጡት መስፈርት መሠረት የሚፈለገው ኪነጥበባዊ የጥራት ደረጃቸው ብቁ ሆኖ መገኘቱ ሲረጋገጥ በዚህ ደንብ አባሪ ሆኖ በተያያዘው የክፍያ ሠንጠረዥ ተመን መሠረት ክፍያ የመፈፀም ስልጣን አላቸው፡፡

፲፩ ስለ ክፍያዎች

ልዩ ልዩ የኪነጥበብ ውጤቶችን ፈጥረው ለሚያቀርቡ የፈጠራ ባለመብቶች፣ በልዩ ልዩ የኪነጥበብ ሙያዎች ለሚሣተፉ የኪነጥበብና የቴክኒክ ባለሙያዎች የፈጠራ ሥራ፣የባለሙያ የማበረታቻ ክፍያ በቴአትር ቤቶች ለሚሰጡ አገልግሎቶች የሚከፈለው የአገልግሎት ክፍያ መጠን ከዚህ ደንብ ጋር አባሪ ሆኖ በተያያዘው ሠንጠረዥ መሠረት ይሆናል፡፡

## ክፍል ሦስት
## ስለተከለከሉ ድርጊቶችና ቅጣት

**፲፪የተከለከሉ ድርጊቶች**

ክፍያ እንዲፈፀምላቸውና እንዲጠየቅባቸው ከተፈቀዱትና ዝርዝራቸው በዚህ ደንብና ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ውስጥ ከሚገለፁት ክፍያ ወይም ተመን ውጭ ክፍያ መፈፀምና መጠየቅ የተከለከለ ነው፡፡

**፲፫ ስለ ቅጣት**

ከዚህ ደንብ ድንጋጌዎች ውጪ ክፍያ የሚፈፅም ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ጥቅም ለማስገኘት የተሳሳተ/የሀሰት/ ማስረጃ በማቅረብ ክፍያ የሚጠይቅ ማንኛውም ፣ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ ሌሎች አግባብ ባላቸው ህጎች የተደነገገው ቅጣት እንደተጠበቀ ሆኖ የፍርድ ቤት ወይም የሌላ መሥሪያ ቤት ውሣኔን ሳይጠብቅ በመንግስት ሠራተኛ የዲሲፕሊን አፈፃፀም ደንብ መሠረት ዘስፈላጊው እርምጃዎችን ሁሉ ይወስዳል፡፡

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፲፬ ደንቡን ስለማሻሻል**

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህንን ደንብ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

**፲፭ ተጠያቂ ስለመሆን**

በዚህ ደንብ የተጣለበትን ግዴታ ያልተወጣና የተሰጠውንም መብት በአግባቡ ያላከበረ አግባብ ባለው ህግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

**፲፮ የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም መንግሥታዊ የሆነ ወይም መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ወይም ግለሰብ ህግና ደንብን እንዲያስከብር ሥልጣን የተሰጠውን የከተማው አስተዳደር አካል ይህን ደንብ ለማስፈፀም በሚደረግ ማንኛውም እንቅስቃሴ የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

**፲፯ መመሪያ የማውጣት ስልጣን**

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ይህንን ደንብ ለማስፈፀም የሚረዳ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፲፰ ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች**

ይህንን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

**፲፱ ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በአዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ
ጥር ፲፭ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም
ኩማ ደመቅሣ
የአ.አ.ከተማ ከንቲባ

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የደንብ ጥሰትን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና የደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽህፈት ቤት አደረጃጀትና አሠራር ለመወሰን የወጣ ደንብ አጭር መግለጫ ፶፬/ ፪ሺ፫

ማውጫ

1. ክፍል አንድ ጠቅላላ ድንጋጌዎች
2. ክፍል ሁለት የጽህፈት ቤቱ አደረጃጀት፣ ተጠሪነት፣ሥልጣንና ተግባር
3. ክፍል ሦስትስለ ቁጥጥር ኦፊሰሮች
4. ክፍል አራት ስለተከለከሉ ድርጊቶች
5. ክፍል አምስት ስለሕገወጥ ንብረት አወራረስ፣ አሻሻጥና አወጋገድ
6. ክፍል ስድስት ስለቅጣትና አቤቱታ አቀራረብ
7. ክፍል ሰባት ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

አጭር መግለጫ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የደንብ መተላለፍና ሌሎች ሕገወጥ ተግባራት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተበራከቱ  የመጡትን የደንብ ጥሰት ተግባራትን ለመቆጣጠር እና ለመቅጣት የወጣ ደንብ ነው፡፡

# <u>የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የደንብ ጥሰትን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና የደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽህፈት ቤት አደረጃጀትና አሠራር ለመወሰን የወጣ ደንብ ፶፬/ ፪ሺ፭</u>

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የደንብ መተላለፍና ሌሎች ሕገወጥ ተግባራት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተበራከቱ በመምጣታቸው፤

በከተማው ውስጥ የደንብ መተላለፍና ተያያዥ ሕገወጥ ተግባራትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር እንዲሁም አግባብነት ያለውን እርምጃ ለመውሰድ የደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽህፈት ቤት በአዋጅ ቁጥር ፴፯/፪ሺ፭ የተቋቋመ በመሆኑ

የደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽህፈት ቤት አደረጃጀት እና አሠራርን በዝርዝር የህግ ማዕቀፍ መደንገግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፳፫/፩ (ረ) እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚና ማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፴፭/፪ሺ፬  በአንቀጽ ፹፬ በተሰጠው ስልጣን መሠረት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

## <u>ክፍል አንድ</u>

## <u>ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>

፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የደንብ ማስከበር አገልግሎት ደንብ ቁጥር ፶፬/ ፪ሺ፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩. "ከተማ"  ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤

፪. "አስተዳደር" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፫. "ከንቲባ" ማለት የከተማውን አስተዳደር የሚመራ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ነው፤

፬. "አዋጅ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላትን እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፴፭/፪ሺ፬ን እንደገና ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር ፴፯/፪ሺ፭ ነው፤

፭. "የቁጥጥር ኦፊሰር" ማለት በዚህ ደንብ የተመለከተውን የደንብ መጣስ ተግባር ለመከላከልና ለመቆጣጠር የተቀጠረ ወይም የተመደበ የደንብ መተላለፍ ክትትልና ቁጥጥር  አፊሰር ነው፤

፮. "ሕገወጥ የመሬት ወረራ" ማለት አግባብ ካለው የከተማው አስተዳደር አካል ፈቃድ ሳይገኝ መሬትን መያዝ ነው፤

፯. “ሕገወጥ የመሬት ይዞታ ማስፋፋት” ማለት አግባብ ካለው የከተማው አስተዳደር አካል በሕጋዊ መንገድ ከተሰጠው ቦታ በተጨማሪነት አስፋፍቶ መያዝ ነው፤

፰. “ሕገወጥ ግንባታ” ማለት በሕገወጥ የመሬት ወረራ ወይም በሕገወጥ የመሬት ይዞታ ማስፋፋት በተያዘ ቦታ ወይም በሕጋዊ ይዞታ ላይ ያለግንባታ ፈቃድ የተገነባ ማንኛውም ግንባታ ነው፤

፱. “ሕገወጥ የመንገድ ላይ ንግድ” ማለት በከተማ አስተዳደሩ በተወሰኑ ቀናት በመንገድ ላይ ለመነገድ ከተፈቀደባቸው መንገዶች ወይም ከንግድ መደብሮች በስተቀር በሌላ ማንኛውም መንገድ ወይም ቦታ የሚካሄድ ንግድ ነው፤

፲. “መንገድ” ማለት በከተማ አስተዳደሩ የሚገኙ ዋና መንገዶች፣ መለስተኛ መንገዶች፣ መጋቢ መንገዶች፣ የውስጥ ለውስጥ መንገዶች፣ የመንደር መንገዶች፣ አደባባይ እና የአደባባይ ዙሪያዎች፣ የመንገድ አካፋይ ደሴቶች፣ በመንገድ ግራና ቀኝ ያሉ የእግረኛና የቢስክሌት ማስተላለፊያዎች፣ ድልድይ እና የጎርፍ ማስወገጃ መስመሮችን እና በከተማው መሪ ኘላን መሠረት ለመንገድነት የተያዘን ቦታ ይጨምራል፤

፲፩. “ደረቅ ቆሻሻ” ማለት ከመኖሪያ ቤት፣ ከንግድ፣ ከኢንዱስትሪ፣ ከተቋማት፣ ከጋራዥ፣ ከመንገድ ፅዳት፣ ከግንባታ፣ ከግብርና፣ ከመሬት ቁፋሮና በጠቅላላው ከሕብረተሰቡ ሥራዎችና በእንስሳት ምክንያት የሚፈጠር፣ ጠጣርና ከፊል ጠጣር ቆሻሻ ነው፤

፲፪. “ፈሳሽ ቆሻሻ” ማለት ከመኖሪያ ቤትም ሆነ ከማንኛውም ድርጅት የሚወጣ የልብስ፣ የምግብና መጠጥ ዕቃዎች እጣቢ፣ አተላ፣ አምቡላ፣ የመፀዳጃ ቤት ፈሳሽ፣ የእንስሳት ማደሪያ ፍሳሽ፣ መርዛማ ንጥረ ነገር ያዘለ ወይም ያላዘለ ፍሳሽ ነው፤

፲፫. “ጽህፈት ቤት” ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽህ ፈት ቤት ነው፤

፲፬. “የሥራ ሂደት” ማለት የጽህፈት ቤቱን ተግባር እንደየአግባቡ ለመፈፀም ከከተማ እስከ ወረዳ ድረስ የተደራጀ የሥራ ክፍል ነው፤

፲፭. “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

፫. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ ደንብ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሚፈጸም የደንብ መተላለፍ እና ተያያዥ ሕገ ወጥ ድርጊቶች ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

፬. <u>የፆታ አገላለጽ</u>

በዚህ ደንብ ውስጥ በልዩ ሁኔታ ካልተገለፀ በስተቀር በወንድ ፆታ የተገለጹ አገላለጾች ለሴት ጾታም ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

## ክፍል ሁለት

## የጽህፈት ቤቱ አደረጃጀት፣ ተጠሪነት፣ሥልጣንና ተግባር

፭. አደረጃጀት

ጽህፈት ቤቱ የሚከተለው አደረጃጀት ይኖረዋል፡-

፩. ዋናና ምክትል ሥራ አስኪያጅ፣

፪. አስፈላጊ የሥራ ክፍሎች፣

፫. አስፈላጊ ሠራተኞች ፣

፬. በክፍለ ከተማና ወረዳ በጽህፈት ቤት ደረጃ ተደራጅቶ የተለያዩ የስራ ክፍሎች እና አስፈላጊ ሰራተኞች ይኖሩታል፡፡

፮. ተጠሪነት

፩. ጽህፈት ቤቱ ተጠሪነቱ ለከተማው ከንቲባ ነው፤

፪. በክፍለ ከተማ ደረጃ የተደራጀው ጽህፈት ቤት ተጠሪነቱ ለክፍለ ከተማው ዋና ስራ አስፈጻሚ እና ለከተማው የደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽህፈት ቤት ይሆናል፤

፫. በወረዳ ደረጃ የተደራጀው ጽህፈት ቤት ተጠሪነቱ ለወረዳው ዋና ስራ አስፈፃሚ እና ለክፍለ ከተማው የደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽህፈት ቤት ይሆናል፡፡

፯. የጽህፈት ቤቱ ሥልጣንና ተግባር

ጽህፈት ቤቱ በአዋጅ ቁጥር ፴፯/፪ሺ፭ የተሠጠው አጠቃላይ ሥልጣንና ተግባር እንዲሁም በሌሎች ህጐች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክፍለ ከተማና የወረዳ ጽህፈት ቤቶችን በማስተባበር የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩. በከተማው አስተዳደር ክልል የሚፈፀም የጽዳት መጓደል፣ ሕገወጥ የመንገድ ላይ ንግድ ፣ ሕገወጥ ግንባታ፣ ሕገወጥ የመሬት ወረራ፣ ሕገወጥ የመሬት ይዞታን ማስፋፋት፣ በሕገወጥ መንገድ የውጭ ማስታወቂያ መለጠፍ፣ መትከል፣ ማንጠልጠልን ይከላከላል፤ ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፤

፪. በክፍት እና ዝግ የመናፈሻ ቦታዎች፣ የመንገድ አካፋዬች፣ ዳርቻዎችና አደባባዬች የሚከናወኑ ሕገወጥ ተግባራትን ይከላከላል፣ ይቆጣጠራል እርምጃ ይወስዳል፤

፫. ሕገወጥ ዕርድን ይከላከላል፣ ይቆጣጠራል፣ እርምጃ ይወስዳል፣ ያስወስዳል፤

፬. ባልተፈቀደ ቦታ የእንስሳት ዝውውር እና ግብይትን ይቆጣጠራል፣ እርምጃ ይወስዳል፤

፭. ሕገወጥ የፈሳሽ እና የመፀዳጃ ቤት ፍሳሽን ከጎርፍ ማስወገጃ መስመር ጋር ማገናኘትና መልቀቅ፣ የማንሆሎችን ክዳን መክፈት፣ ፉካዎችን እና የጎርፍ ማስወገጃ መስመርን መድፈን ወይም ጉዳት ማድረስን ይከላከላል፣ ይቆጣጠራል እርምጃ ይወስዳል፤

፮. ያለ ፈቃድ አሸዋ፣ አፈር፣ ማንኛውንም ተረፈ ምርቶችን በመንገድ ላይ መድፋት ማንጠባጠብ፣ ድንጋይ ወይም እንጨት መፍለጥን፣ እጣና በማውረድ መከመርን ጭቃ ማቡካትን ይከላከላል፣ ይቆጣጠራል፣ እርምጃ ይወስዳል፤

፯. በመንገድ ላይ የተበላሸን ተሽከርካሪ ማቆም፣ ተሽከርካሪ በመንገድ ላይ መጠገን ወይም ማስጠገን፣ ማጠብ ወይም ማሳጠብን ይከላከላል፣ ይቆጣጠራል፣ እርምጃ ይወስዳል፤

፰. መንገዶችን ማሻሻል፣ መቀየር፣ መቀየስ፣ በበር መዝጋት፣ በኬላ ማጠር መቁረጥን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ እርምጃ ይወስዳል፤

፱. በመንገድ ላይ የንግድ ዕቃዎችን ለረዥም ጊዜ ማስቀመጥ፣ ዛፍ ወይም አትክልት መትከል፣ ያለፈቃድ ድንኳን መጣል፣ የብየዳም ሆነ ሌላ ማንኛውንም የትራፊክ እንቅስቃሴንና ዕይታን የሚከላከሉ ተግባራትን ይቆጣጠራል፣ ይከላከላል፣ እርምጃ ይወስዳል፤

፲ ባድልድዮች፣ በመንገድ መብራቶች፣ በትራፊክ መብራቶች፣ በእግረኛ መከላከያዎች ምልክትን ማጣመም ወይም ማበላሸትን ይከላከላል፣ ይቆጣጠራል፣ እርምጃ ይወስዳል፤

፲፩. በመንገድ መብራት ምሰሶ፣ በድልድይ፣ በመንገድ ምልክት እና በእግረኛ የመንገድ መከላከያ አጥር ላይ ባነር፣ ማስታወቂያ ወይም የማስታወቂያ ሰሌዳ መለጠፍ ወይም መትከልን ይከላከላል፣ ይቆጣጠራል፣ እርምጃ ይወስዳል፤

፲፪. የትራፊክ እንቅስቃሴ እና ደህንነትን የሚያውኩ በመንገድ ወይም በትራፊክ መብራት ላይ የሚከናወን ልመናን፣ ንግድን ወይም ሌላ ማንኛውም የትራፊክ እንቅስቃሴን የሚያውክ ወይም ለአደጋ የሚያጋልጥ ተግባርን ከትራፊክ ፖሊስ ጽህፈት ቤት ጋር በቅንጅት ይከላከላል፣ ይቆጣጠራል፣እርምጃ ይወስዳል፤

፲፫. በማናቸውም የመንግስት ሀብትና ንብረት ላይ ስርቆት እንዳይፈፀም ይከላከላል፤ ስርቆት ተፈጽሞ ሲገኝ ህጋዊ እርምጃ እንዲወ ሰድ አግባብ ላለው አካል ያሳውቃል፤

፲፬. ጫት ማስቃምን ወይም ሺሻ ማስጨስን ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ይከላከላል፣ ይቆጣጠራል፣ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

፲፭. በትምህርት ተቋማት ዙሪያ ዕፅ መጠቀሚያ ቤት፣ ፊልም ወይም ቪዲዮ ቤት፣ ጭፈራ ቤት፣ መጠጥ ቤት፣ ቁማር ቤት መክፈትን ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ይከላከላል፣ ይቆጣጠራል፣ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

፲፮. በከተማው አስተዳደር ከደንብ ማስከበር ጋር በተያያዘ የወጡ ደንቦችን፣ ስለሚደረጉ ቁጥጥ ሮች እና ስለሚወሰዱ ዕርምጃዎች በተለያዩ ዘዴዎች ለህብረተሰቡ ግንዛቤ ያስጨብጣል፤

፲፯. ከጽህፈት ቤቱ ተልዕኮ አንፃር በደንብ መጣስ ተግባሮች ላይ ቅድመ ጥናት ያደርጋል፣ በጥናቱ የተገኙ ውጤቶችን መሠረት በማድ ረግ ይፈፅማል፤

፲፰. በገንዘብ የሚያስቀጡ የደንብ መጣስ ተግባራትን የቅጣት ገቢ በከተማው አስተዳደር የፋይናንስ ሕግ መሠረት እንዲሰበሰብ ያደርጋል፤

፲፱. ከደንብ ጥሰትና ማስከበር ጋር በተያያዘ ከከተማው አስተዳደርና ሌሎች መስሪያ ቤቶች ጋር በቅንጅትና በትስስር ይሰራል፣

፳. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የቁጥጥር ኦፊሰርን ከአንድ ክፍለ ከተማ ወይም ወረዳ ወደ ሌላ ክፍለ ከተማ ወይም ወረዳ በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት በመመደብ ሊያሰራ ይችላል፣

፳፩. የቁጥጥር ኦፊሰሮች የስነ-ምግባር መመሪያ ያዘጋጃል፣ ተግባራዊ ያደርጋ፡፡

፰. <u>የጽህፈት ቤቱ ሥራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባር</u>

የጽህፈት ቤቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ፡-

፩. ጽህፈት ቤቱን በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፣

፪. የጽህፈት ቤቱን ሥልጣንና ተግባር በስራ ላይ ያውላል፣

፫. የጽህፈት ቤቱን ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፣

፬. ለጽህፈት ቤቱ በተመደበ በጀትና የሥራ ዕቅድ መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፣ በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል፣

፭. ከሶስተኛ ወገን ጋር ለሚኖረው ግንኙነት ጽህፈት ቤቱን ይወክላል፣

፮. የጽህፈት ቤቱን ሰራተኞች አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ይቀጥራል፣ ያሰናብታል፣

፯. ስለ ጽህፈት ቤቱ የሥራ አፈፃፀም ወቅታዊ ሪፖርት ለከንቲባው ያቀርባል፣

፰. በከንቲባው ተለይተው የሚሰጡ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

፱. <u>የጽህፈት ቤቱ ምክትል ሥራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባር</u>

፩. ዋና ሥራ አስኪያጅ በሌለበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፣

፪. በዋና ሥራ አስኪያጁ ወይም በከንቲባው ተለይተው የሚሰጠውን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>ስለ ቁጥጥር ኦፊሰሮች</u>

፲. <u>የቁጥጥር ኦፊሰሮች ምልመላና ሥልጠና</u>

፩. የቁጥጥር ኦፊሰሮች ሥነ ምግባራቸውና የአካል ብቃታቸው እንዲሁም ሌሎች አግባብነት ያላቸው መስፈርቶችን በማሟላት በወረዳው ነዋሪ ተወካዮች ሲመሰከር ይመለመላሉ፣

፪. የቁጥጥር ኦፊሰሮችን ምልመላ ለማስፈፀም በየወረዳው አግባብነት ካላቸው አካላት የተውጣጣ ኮሚቴ ይቋቋማል፣

፫. በኮሚቴው የተመለመሉ ዕጩዎች ወደ ሥል ጠና ከመግባታቸው በፊት ኅብረተሰቡ አስተያየት እንዲሰጥ ለህዝቡ ግልጽ በሆነ ቦታ ዝርዝራቸው ይለጥፋል፣

፬. የተመለመሉ የቁጥጥር ኦፊሰሮች አግባብነት ያለውን ሥልጠና መውሰድና ብቁ መሆናቸው ሲረጋገጥ ብቻ ለሥራው ይቀጠራሉ፣

፫. የቁጥጥር ኦፊሰሮች ደመወዝና ሌሎች ጥቅማጥቅሞች በከተማው አስተዳደር ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ በሚወሰነው መሠረት ይሆናል፤

፬. የተመለመለ ዕጩ የቁጥጥር ኦፊሰር በሥልጠና ሂደት ብቁ ያለመሆኑ ከተረጋገጠ የመቀጠር መብት አይኖረውም፤

፭. ማንኛውም በቁጥጥር ኦፊሰርነት የተቀጠረ ሰው የ፫ አመት የአገልግሎት ግዴታ አለበት፤

፮. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፭) የተቀመጠውን የአገልግሎት ጊዜ ሳያጠናቅቅ ከስራው የሚለቅ የቁጥጥር ኦፊሰር ጽህፈት ቤቱ ለስልጠና ለእርሱ ያወጣውን ማናቸውም ወጪ መክፈል ይኖርበታል፡፡

፲፩. <u>የቁጥጥር ኦፊሰሮች ተግባርና ግዴታ</u>

ማንኛውም የቁጥጥር ኦፊሰር፡-

፩. በዚህ ደንብና በሌሎች የደንብ መተላለፍን በሚመለከት በስራ ላይ ባሉ ደንቦች መሠረት የመከላከል፣ የመቆጣጠርና እርምጃ የመውሰድ ተግባር ያከናውናል፤

፪. ስራውን በሚያከናውንበት ጊዜ የሥራ መለያ ልብስ መልበስና ማንነቱን የሚገልጽ የደረት ባጅ በማንጠልጠል በግልጽ እንዲታይ ማድረግ አለበት፤

፫. በተመደበበት የስራ ክልል በማንኛውም ጊዜ የመከላከልና የመቆጣጠር ተግባራትን ያከናወናል፤

፬. ሕገወጥ ግንባታ መፈፀሙን ሲመለከት ወይም ጥቆማ ሲደርሰው ወደ ማንኛውም ግቢ በመግባት በዚህ ደንብ መሠረት ሕገወጥ ግንባታውን የመከላከል፣ የመቆጣጠርና ተገቢውን እርምጃ የመውሰድ ግዴታ አለበት፤ ሆኖም ከህግ አግባብ ውጪ በሰው መብትና ንብረት ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት ተጠያቂ ይሆናል፤

፭. በዚህ ደንብ መሠረት የደንብ ጥሰት ለፈፀመ ማንኛውም ሰው ተገቢውን የቅጣት ማስታወቂያ ፎርም በመሙላት ይሰጣል፤ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤

፮. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፭ መሠረት መቀጮውን ገቢ ያላደረገ ደንብ ተላላፊ በደንቡ መሠረት ገቢ ያላደረገውን መቀጮ ተፈጻሚ እንዲሆን ለወረዳው የሥራ ሂደት ያሳውቃል፤

፯. ማንኛውም ሰው የፈፀመው የደንብ ጥሰት በዚህ ደንብ ከተመለከተው በተጨማሪ በወንጀል ሕግ የሚያስቀጣ ከሆነ ተቆጣጣሪ ኦፊሰሩ ከተገቢው ማስረጃ ጋር ጉዳዩን ለሚመለተው አካል ማቅረብ አለበት፤

፰.በከተማው አስተዳዳር የመንግስት ሰራተኛ አስተዳደር ሕግ የተመለከተው የስነምግባር መርህ እንደተጠበቀ ሆኖ በጽህፈት ቤቱ የሚወጣውን የሥነ-ምግባር መመሪያ በመከተል ስራውን ሊፈጽም ይገባል፤

፱. በወረዳው የደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽህፈት ቤት የሚሰጡትን የሥራ ግዴታዎች በአግባቡ የመወጣት ኃላፊነት አለበት፡፡

## ክፍል አራት

## ስለተከለከሉ ድርጊቶችክፍል አንድ

፲፪. ስለ ሕገወጥ የመሬት ወረራ እና ሕገወጥ ግንባታ ስለመከልከሉ

በሌሎች ህጐች መሠረት የሚከተሉት የተከለከሉ ናቸው፡-

፩. የከተማ ቦታን በሊዝ ስለመያዝ በወጣው አዋጅና ደንብ በመተላለፍ ህገ ወጥ የመሬት ወረራና ማስፋፋት እና ሕገወጥ ግንባታ ማካሄድ፤

፪. ስለ ቆሻሻ አያያዝ፣ አሰባሰብና አወጋገድ የወጣውን ደንብ በመተላለፍ ደረቅ ወይም ፈሳሽ ቆሻሻ በከተማው ክልል ባልተፈቀደ ቦታ መጣል ወይም መልቀቅ፤

፫. ስለ መንገድ አጠባበቅ በወጣው ደንብ መሠረት የመንገድን ደህንነት የሚጐዱ ተግባራትን መፈፀም ፤

፬. ስለ ውጭ ማስታወቂያ የወጣውን ደንብ በመተላለፍ የከተማውን ጽዳትና ውበት የሚያበላሽ ማስታወቂያ መለጠፍ፣ መትከል፣ መገንባት፣ ማንጠልጠል፣ ማሠራጨት፡፡

፲፫. ጫት ማስቃም ፣ ሺሻ ማስጨስ እና የጎዳና ንግድ ስለመከልከሉ

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የተከለከሉ ድርጊቶች ናቸው፡-

፩. ጫት ማስቃም ወይም ሺሻ ማስጨስ፤

፪. በማንኛውም ትምህርት ተቋም ዙሪያ፡-

ሀ. ፊልም ወይም ቪዲዮ ማሳየት፤

ለ. የቀንም ሆነ የሌሊት የጭፈራ ቤት ንግድ ሥራ ማከናወን፤

ሐ. ማንኛውንም ዓይነት የአልኮል መጠጥ መሸጥ፤

መ. ቁማር መጫወት ወይም ማጫወት፤

፫. በሚመለከተው የከተማ አስተዳደር አካል ካልተፈቀደ በስተቀር የጎዳና ንግድ ማከናወን፡፡

## ክፍል አምስት

## ስለሕገወጥ ንብረት አወራረስ፣ አሻሻጥና አወጋገድ

፲፬. ንብረት ስለመውረስ

፩. ይህን ደንብ በመተላለፍ በመንገድ ላይ ሕገወጥ ንግድ ሲካሄድበት የተገኘ ሸቀጥ ወይም ንብረት ይወረሳል፤

፪. በመንገድ ላይ ለንግድ ወይም ለሌላ ማንኛውም ተግባር የተቀመጠ ዕቃ በተሰጠው ማስጠንቀቂያ መሠረት ካልተነሳ ይወረሳል፤

፫. ይህን ደንብ በመተላለፍ የተከናወነ ሕገወጥ ግንባታ በሚኖርበት ወቅት ግንባታውን ያከናወነው ሰው በ፫ ቀናት ጊዜ ውስጥ ግንባታውን እንዲያፈርስ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ እንዲደርሰው ይደረጋል፤

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ መሠረት ሕገወጥ ግንባታውን እንዲያፈርስ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት በተጠቀሰው ጊዜ ግንባታውን ለማፍረስ ፈቃደኛ ያልሆነ እንደሆነ ግንባታውን በማፍረስ ንብረቱ ይወረሳል፤

፭. ሕገወጥ ግንባታውን ለማፍረስ የወጣውን ወጪ ህገ ወጥ ገንቢው መተካት አለበት፡፡

፲፭. ስለተወረሰ ንብረት አያያዝ

፩. ተቆጣጣሪ ኦፊሰሮች ይህ ደንብ በመጣሱ የተወረሰን ንብረት በየወረዳው ለሚገኘው የደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽህፈት ቤት ያስረክባሉ፤

፪. የተወረሰውን ንብረት ወደ ወረዳው የደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽህፈት ቤት ለማድረስ የወጣውን ወጪ ንብረቱ የተወረሰበት ሰው የመሸፈን ግዴታ አለበት፤

፫. የወረዳው የደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽህፈት ቤት የተወረሰን ንብረት በአግባቡ በመጠበቅ ይይዛል፤ መያዙን ያረጋግጣል፤

፬. የወረዳው የደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽህፈት ቤት የተወረሰ ንብረትን እንደ ንብረቱ ልዩ ባህሪ እንዲቀመጥ ያደርጋል፡፡

፲፮. ስለተወረሰ ንብረት አሻሻጥ እና አወጋገድ

፩. በዚህ ደንብ መሠረት የተወረሰ ንብረት በግልጽ ጨረታ ይሸጣል፤

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት በጨረታ ሊሸጥ የማይችል ማንኛውም የተወረሰ ንብረት በከተማ አስተዳደሩ የግዥና ንብረት አስተዳደር ሕግ መሠረት በመሰረዝ ይወገዳል፤

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት ከጨረታ ሽያጭ የሚገኘው ገቢ በከተማው አስተዳደር ፋይናንስ አስተዳደር ሕግ መሠረት ለወረዳው ፋይናንስ ጽህፈት ቤት ገቢ መደረግ አለበት፤

፬. በዚህ አንቀጽ ስለተወረሰ ንብረት አሻሻጥ እና አወጋገድ ዝርዝር አፈፃፀምን በተመለከተ ይህን ደንብ ለማስፈፀም በሚወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

## ክፍል ስድስት

## ስለቅጣትና አቤቱታ አቀራረብ

፲፯. ስለቅጣትና እርምጃ

፩. በወንጀል ሕግ እና በሌላ ሕግ የተመለከተው ኃላፊነትና ቅጣት እንደተጠበቀ ሆኖ ይህንን ደንብ የጣሰ ማንኛውንም ሰው፡-

ሀ. እንደ ጥፋቱ ሁኔታ ድርጊቱን የማስቆም፣ የማዘጋት፣ የማሸግ፣ የማስነሳት እርምጃ የቁጥጥር ኦፊሰሮች ይወስዱበታል፤ እንዲሁም

ለ. ከዚህ ደንብ ጋር አባሪ በተደረገው ሰንጠረዥ መሠረት አስተዳደራዊ ቅጣት ይቀጣል፤

፪. በዚህ ደንብ መሠረት ቅጣት የተጣለበት ማንኛውም ደንብ የተላለፈ ሰው በተቆጣጣሪ ኦፊሰር የተሰጠውን የቅጣት ማስታወቂያ በመያዝ ወዲያውኑ ጥፋቱ በተፈፀመበት ወረዳ በሚገኘው የሥራ ሂደት መቀጮ ገቢ ማድረግ አለበት፤

፫. በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሠረት የቅጣት ማስታወቂያ ፎርም ለመቀበል ፍቃደኛ ካልሆነ ተቆጣጣሪ ኦፊሰሩ ከአካባቢው ፖሊስ ጋር በመተባበር የቅጣት ማስታወቂያውን እንዲቀበል ያስገድዳል፤

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሠረት መቀጮውን ገቢ ያላደረገ ሰው የተጣለበትን የቅጣት መቀጮ መጠን እጥፍ እንዲከፍል ይደረጋል፤

፭. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፬ መሠረት መቀጮውን ገቢ ለማድረግ ያልቻለ ወይም ፈቃደኛ ያልሆነ ሰው በማህበራዊ ፍርድ ቤት እስከ ሶስት ወር በሚደርስ የማረፊያ ቤት እስራት ሊቀጣ ይችላል፡፡

፲፰. <u>ስለተደጋጋሚ ጥፋትና ቅጣት</u>

በዚህ ደንብ በአንቀጽ ፲፯ የተደነገገው ቢኖርም በተደጋጋሚ የደንብ መተላለፍ የፈፀመ ማንኛውም ሰው የሚቀጣው ቅጣት እጥፍ ይሆናል፡፡

፲፱.<u>ቅጣትን ስለማስፈፀም</u>

፩. በክፍለ ከተማ ፍትህ ጽህፈት ቤት ስር የሚመለከተው የስራ ሂደት በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፯ ንዑስ አንቀጽ ፪ በተመለከተው መሠረት መቀጮውን ገቢ ያላደረገን ሰው ጥፋቱ በተፈፀመበት ወረዳ በሚገኘው ማህበራዊ ፍርድ ቤት ክስ በማቅረብ ቅጣቱን ያስፈጽማል፤

፪. ማህበራዊ ፍርድ ቤት በዚህ ደንብ የተመለከተውን የደንብ መተላለፍ መቀጮ በቀረበለት መሠረት ያስፈጽማል፡፡

፳.<u>ስለአቤቱታ አቀራረብ</u>

፩ ይህንን ደንብ በመተላለፍ ቅጣት የተጣለበት ማንኛውም ሰው የቅጣቱ ማስታወቂያ ከተሰጠው ቀን አንስቶ በ፫ የስራ ቀናት ጥፋቱ በተፈፀመበት ወረዳ ለሚገኘው የደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽህፈት ቤት ሊያቀርብ ይችላል፤

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት አቤቱታ ማቅረብ የሚቻለው ተቀጭው መቀጮ የከፈለበትን ደረሰኝ አያይዞ ሲያቀርብ ነው፤

፫. የወረዳው ደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽህፈት ቤት የቀረበውን አቤቱታ ከዚህ ደንብና ሌሎች አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር አገናዝቦ በመመርመር በቀረበው አቤቱታ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፤

፬. አቤቱታው ተመርምሮ የተከፈለው ቅጣት አላግባብ መሆኑ ሲረጋገጥ በከተማው አስተዳደር ፋይናንስ ሥርዓት መሠረት ቅጣት የተከፈለው ገንዘብ ተመላሽ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሰባት</u>
## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

፳፩. <u>የመተባበር ግዴታ</u>

ማንኛውም ሰው ይህን ደንብ የማክበርና የማስከበር ግዴታ አለበት፡፡

፳፪. <u>መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

ጽህፈት ቤቱ ይህን ደንብ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉትን መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል፡፡

፳፫.<u>ስለተሻሩና ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች</u>

፩. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንገድ አጠበባበቅ ደንብ ቁጥር ፪/፲፱፻፺፰ አባሪ በሆነው ሠንጠረዥ "ሀ" በትራፊክ ፖሊስ እንዲፈፀሙ ከተመለከቱት ጥፋቶች በስተቀር ሌሎች በደንቡ የተዘረዘሩት የጥፋት አይነቶች በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

፪. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቆሻሻ አያያዝ አሰባሰብና አወጋገድ ደንብ ቁጥር ፲፫/፲፱፻፺፯ አባሪ የሆነው የቅጣት ጠንጠረዥ ተሽሮ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ተተክቷል፡፡

፫. ይህን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ የተደነገጉትን ጉዳዮች በተመለከተ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

፴፬. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ ከሐምሌ ፩ ቀን ፪ሺ፰ ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ጥቅምት ፴፪ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም

ኩማ ደመቅሳ

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ

<u>የቅጣት ሰንጠረዥ ፩</u>

| ተ.ቁ | የጥፋት አይነቶች | የቅጣት መጠን |
|---|---|---|
| ፩ | አግባብ ካለው የመንግስት አካል ፈቃድ ሳያገኝ የመንግስትን መሬት በማናቸውም መንገድ መያዝ | ብር ፰ሺ |
| ፪ | በህጋዊ መንገድ ከተያዘው የቦታ ስፋት መጠን በላይ የመንግሰት መሬት አስፋፍቶ መያዝ | ብር ፫ሺ |
| ፫ | አግባብ ካለው አካል ፈቃድ ሳያገኝ የመንግስትን መሬት በመያዝ ወይም ህጋዊ ይዞታን በማስፋፋት ህገወጥ ግንባታ መገንባት | ብር ፺ሺ፰መቶ |
| ፬ | በሕጋዊ የመሬት ይዞታ ላይ አግባብ ካለው አካል የግንባታ ፈቃድ ሳያገኝ ማንኛውም ግንባታ ማካሄድ | ብር ፪ሺ |

የቅጣት ሰንጠረዥ ፪

| ተ.ቁ | የጥፋት ዓይነቶች | የቅጣት መጠን |
|---|---|---|
| ፩ | ቆሻሻ በአግባቡ አለመያዝ ወይም ማዝረክረክ<br>• ከመኖሪያ ቤት ከሆነ<br>• ከድርጅት ከሆነ | ብር ፮ መቶ<br>ብር ፪ መቶ |
| ፪ | የመኖሪያ ቤትን ወይም የድር ጅትን ፊት ለፊት ያለውን የአካባቢ ንጽህና በአግባቡ አለመጠበቅ<br>• ከመኖሪያ ቤት ከሆነ<br>• ከድርጅት ከሆነ | ብር ፶<br>ብር ፮ |
| ፫ | ደረቅ ቆሻሻ ባልተፈቀደ ቦታ መጣል<br>• ከመኖሪያ ቤት<br>• ከኢንዱስትሪ<br>• ከጤና ተቋም<br>• ከሌሎች ድርጅቶች | ብር ፮ መቶ<br>ብር ፯ሺ<br>ብር ፭ሺ<br>ብር ፩ሺ |
| ፬ | ጥቃቅን ቆሻሻዎችን ተገቢ ባልሆኑ ቦታዎች መወርወር | ብር ፮መቶ |
| ፭ | ባልተፈቀደ ቦታ ላይ አሮጌ መኪና፣ ቆርቆሮ፣ አሸዋ፣ አፈር፣ ወዘተ መቆለልና ማስቀመጥ | ብር ፭መቶ |
| ፮ | ከገንዳ ውጭ ቆሻሻ መድፋት | ብር ፲ |
| ፯ | የጥቃቅን ቆሻሻ መያዣዎችን አለአግባብ መጠቀም ወይም ማበላሸት | ብር ፫መቶ |
| ፰ | ቆሻሻን እያዝረከረኩና ሳይሸፈኑ ማሽከርከር | ብር ፶ |
| ፱ | ከተሽከርካሪዎች ላይ በመሆን ቆሻሻዎችን የሚወረውር አሽከርካሪ ወይም ተሳፋሪ | ብር ፮ |

| | | |
|---|---|---|
| ፲ | በእንስሳት እርባታና የማቆያ ቦታዎች ቆሻሻዎችን በአግባቡ አለመያዝና አለማስወገድ | ብር ፭ መቶ |
| ፲፩ | የቀንድና የጋማ ከብት እንደዚሁም ውሾችን ወይም ለማዳ እንስሳትን ይዞ በመዞር ባልተፈቀደ ቦታ እንስሳቱን ማፀዳዳት | ብር ፪ መቶ |
| ፲፪ | ያልተሸፈነ ጭነት በጋማ ከብት በማጓጓዝ ከተማ ማቆሸሽ | ብር ፫ መቶ |

| | | |
|---|---|---|
| ፲፫ | የሞቱ እንስሳት ባልተፈቀደ ቦታ ሲጥል የተገኘና የተረጋገጠበት<br>• የቀንድ ከብት<br>• ሌሎች እንስሳት | <br>ብር ፫መቶ<br>ብር ፪መቶ |
| ፲፬ | ህገ ወጥ እርድ<br>• አራጅ<br>• ተጠቃሚ ግለሰብ<br>• ተጠቃሚ ድርጅት | <br>ብር ፭ ሺ<br>ብር፩ ሺ፭መቶ<br>ብር፯ ሺ፭መቶ |
| ፲፭ | የቀንድ ከብትና የመሳሰሉትን ባልተፈቀዱ ቦታዎች ላይ በማቆየት ከተማ ማቆሸሽ | ብር ፪መቶ |
| ፲፮ | ከግንባታ ወይም ከፍርስራሽ የሚመነጭ ቆሻሻ ወይም አፈር ባልተፈቀደ ቦታ መጣል | ብር ፭መቶ |
| ፲፯ | ልዩ ቆሻሻዎችን በአግባቡ አለመያዝ ወይም አለመጣል | ብር ፭መቶ |
| ፲፰ | አደገኛ ቆሻሻዎችን በአግባቡ አለመያዝና አለማስወገድ<br>• የኢንዱስትሪ ከሆነ<br>• የጤና ተቋም ከሆነ | <br>ብር ፲ ሺ<br>ብር ፯ ሺ |
| ፲፱ | ባልተፈቀደ ቦታና ሁኔታ ቆሻሻ፣ ሬንጅ፣ ፕላስቲክ ወይም የመሳሰ ሉትን ማቃጠል<br>• ግለሰብ<br>• ድርጅት | ብር ፪ መቶ<br>ብር ፭ መቶ |
| ፳ | የገበያ ቦታ አቆሸሸ መነሣት | ብር ፫ መቶ |

| | | |
|---|---|---|
| ፳፩ | በአገልግሎት ተቋማትና የማምረቻ ድርጅቶች ተገቢ የሆነ የጥቃቅን ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ዕቃ<br>• አለማስቀመጥ<br>• በአግባቡ አለማስወገድ | <br><br>ብር ፪ መቶ<br>ብር ፩ መቶ |
| ፳፪ | በመንገድ ወይም ከመፀዳጃ ቤት ውጭ ሽንት መሽናት ወይም መጸዳዳት | ብር ፶ |

| ተቁ | የጥፋት አይነቶች | የቅጣት መጠን |
|---|---|---|
| ፩ | <u>የቅጣት ሰንጠረዥ ፫</u> | ብር ፩ ሺ |
| ፪ | ለግንባታም ሆነ ለሌላ ጉዳይ የሚሆኑ ድንጋይ በመንገድ ላይ መፍለጥ ወይም መጥረብ | ብር፭ መቶ |
| ፫ | በመንገድ ላይ ጭቃ ማቡካትም ሆነ ማንኛውም መሰናክል ማድረግ | ብር፭ መቶ |
| ፬ | የንግድ ዕቃ ወይም ሌላ ዕቃ ለአጭርም ሆነ ለረጅም ጊዜ ማስቀመጥ | ብር ፫ መቶ |
| ፭ | ማንኛውም ሰው በሕጋዊ መንገድ ከያዘው ይዞታ ውጭ በመሆን መንገድን፣ በማስተር ፕላኑ መሠረት ለመንገድነት የተያዙ ክፍት ቦታዎችን፣በመንገዶች ግራና ቀኝ ያሉ የእግረኛ መንገድን የሸቀጥ እቃዎችን ደርድሮ በማስቀመጥ | ብር ፫ሺ |

| | | |
|---|---|---|
| | ወይም ለጠጠ ቃሚ የሚሆን ወንበሮችን መደር ደር፣ ዛፍና አትክልት በመትከል መንገደ ኛንም ሆነ ተሽከርካሪን ማሰናከል፣ መንገድ ላይ “ማቆም ክልክል ነው” የሚል ወይም መሰል ምልክቶችም ሆነ ማናቸውንም ንባታ ማቆም፣ ቤት መሥራትና አጥር ማጠር፣ | |
| ፮ | በመንገድ ላይ ከብት ማሰማራ የከብት ንግድ ማካሄድ | ብር ፰ |
| ፯ | አውቆም ሆነ በድንገተኛ ሁኔታ በድል ድዮች፣ በመንገድ መብራቶችና ቋሚ ዎች (ፖሎች)፣ በትራፊክ ምልክ ቶች፣ በትራፊክ መብራቶች በእግረኛ መከላ ከያዎች፣ በማንሆሎች፣ በፍካዎች ወይም በክዳኖቻቸው ላይ ጉዳት ማድረስ | ብር፯ መቶ |

| | | |
|---|---|---|
| ፰ | መንገዶችን ማሻሻል፣ መቀየር ፣ መቀየስ፣ በበር መዝጋት፣ በኬላ ማጠር፣ መቁረጥ፣ መስበር፣ መቆፈር ወይም በሌላ ሁኔታ ተሽከርካሪም ሆነ እግረኛ እንዳይተላለፍ ማድረግ | ብር ፩ ሺ |
| ፱ | የዋና መንገዶች በማናቸውም ምክንያቶች አለመዘጋት እንደተጠበቀ ሆኖ በኀዘን ምክንያት ሳይሆን የእግረኛንም ሆነ የተሽከርካሪን መንገድ ድንኳን በመጣል(በመትከል) በከፊልም ሆነ በሙሉ መዝጋት | ብር፩ መቶ ፶ |
| ፲ | በመንገድ ላይ የግንባታ ተረፈ ውጤቶችን መድፋት | ብር ፩ ሺ |
| ፲፩ | ሆን ብሎ የመፀዳጃ ቤት ፍሳሽ ከመንገድ ጋር ማገናኘት እና መልቀቅ | ብር ፩ ሺ |
| ፲፪ | መንገድ ላይ የተበላሸ ተሽከርካሪ መጠገን; ድንጋይ መደርደር፣ የተጫነን ማንኛውም ነገር ማንጠባጠብ ወይም መጣል | ብር ፩ ሺ |
| ፲፫ | በመንገድ ላይ ተሽከርካሪ ማሳጠብ | ብር ፪ |

| | | |
|---|---|---|
| | | መቶ |
| ፲፩ | በተወሰኑ ቀናት የንግድ ስራን ለመነገድ ተለይተው ከተፈቀዱበት መንገዶች በስተቀር የንግድ ሥራን በመንገድ ላይ ማካሄድ | ብር ፭ መቶ |
| ፲፭ | በመንገዶች፣ በድልድዬች በትራፊክ መብራቶች፣ ምልክቶች፣በፖሎች ወይም በእግረኛ መከላከያ ያለፈቃድ ማስታወቂያ ወይም ባነር መለጠፍ ወይም ማንጠልጠል | ብር ፭ መቶ |

<u>የቅጣት ሰንጠረዥ ፬</u>

| ተ.ቁ | የጥፋት አይነቶች | የቅጣት መጠን |
|---|---|---|
| ፩ | ጫት ማስቃም | ብር ፩ ሺ.፭ መቶ |
| ፪ | ሺሻ ማስጨስ | ብር ፩ ሺ. |
| ፫ | በትምህርት ተቋማት ዙሪያ፡-<br>• ፊልም ወይም ቪዲዮ ማሳየት<br>• የቀንም ሆነ የሌሊት የጭፈራ የንግድ ሥራ ማከናወን<br>• ማንኛውንም ዓይነት የአልኮልን መጠጥ መሸጥ<br>• ቁማር መጫወት ወይም ማጫወት | ብር ፩ ሺ.<br>ብር ፪ ሺ.<br>ብር ፫ ሺ.<br>ብር ፩ ሺ. |

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ፶፮/፪ሺ፲ ዓ.ም አጭር መግለጫ

ማውጫ

1. ክፍል አንድ ጠቅላላ
2. ክፍል ሁለት የመንግስት መሥሪያ ቤት አደረጃጀት
3. ክፍል ሦስት የሰው ሀብት ዕቅድ፣ ስምሪት እና የሥራ አፈጻጸም ምዘና ንኡስ ክፍል አንድ ምልመላና መረጣ
4. ክፍል አራት የሥራ ሰዓትና ፍቃድ
5. ክፍል አምስት ተጨማሪ የድጋፍ እርምጃ የሚስፈልጋቸው የኅብረተሰብ ክፍልች የሥራ ሁኔታ
6. ክፍል ስድስት በሥራ ላይ ስለሚደርስ ጉዳት
7. ክፍል ሰባት የመንግሥት ሠራተኞች የመረጃ አያያዝ
8. ክፍል ስምንት መብቶችና ግዴታዎች
9. ክፍል ዘጠኝየዲስፕሊን እርምጃዎች እና የቅሬታ አፈታት
10. ክፍል አስር የመንግሥት ሠራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤት ክፍል
11. አስራ አንድ የሥራ ውል ማቋረጥና ማራዘም ክፍል
12. አሥራ ሁለት ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

አጭር መግለጫ

በመንግስት መስሪያ ቤት ውስጥ ያለ ሰራተኞችን ወጥነት ባለው መልኩ ለመምራትና እውቀታቸውንና ችልታቸውን በተገቢው ሁኔታ ለመጠቀም የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት ለመዘርጋት ለማስቻል የወጣ ህግ ነው።

# <u>የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ፶፯/፪ሺ፲ ዓ.ም</u>

በመንግስት መስሪያ ቤት ውስጥ የሚካሄደውን የምልመላና መረጣ ሥርዓትን በመሰረታዊነት በመለወጥና በከተማ ደረጃ የሙያና የሥራ ብቃት ማረጋገጫ ሥርዓት በመዘርጋት፣ እንዲሁም የመንግስት ሠራተኛው በዚህ ሥርዓት ውስጥ እንዲያልፍ በማደረግ ብዝሀነትን ያረጋገጠና በከተማ ውስጥ እየተመዘገበ ያለውን እደገት ለማስቀጠል የሚያስችል ፐብሉክ ሰርቪስ ለመገንባትና የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፐሮግራም በሰው ሃብት ሥራ አመራር ረገደ ያመጣቸውን ውጤቶች ለማጎልበትና ለማስቀጠል የሚያስችል ሕግ ማውጣት በማስፈለጉ፤

በመንግስት መስሪያ ቤት ውስጥ ያለ ሰራተኞችን ወጥነት ባለው መልኩ ለመምራትና እውቀታቸውንና ችልታቸውን በተገቢው ሁኔታ ለመጠቀም የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

የመንግስት መስሪያ ቤቶች ያሉትን ሠራተኞች በማቆየትና አዳዲስ ሰራተኞችን በመሳብ ተወዳዳሪ ለመሆን እንዱችለ የተሻሻለ የሥራ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ያስተዳድራል ሆኖ በመገኙቱ፤ እንዲሰጠው

በተሸሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፩ሺ፱፻፺፭ (እንደተሸሻለ) አንቀጽ ፲፩(፩) እና (፪) (ሐ) መሰረት የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡

## <u>ክፍል አንድ</u>

## <u>ጠቅላላ</u>

### <u>፩. አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር ፶፯/፪ሺ፲ ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ፡፡

### <u>፪. ትርጓሜ</u>

የቃለ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

፩. "ከተማ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤

፪. "ካቢኔ" ማለት አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ ነው፤ ይሆናል

፫. "አስተዳደር" ማለት የአዲስ ከበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፬. "የመንግሥት ሠራተኛ" ማለት በአስተዳደሩ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ውስጥ በቋሚነት ተቀጥሮ የሚሰራ ሰው ነው፤ ሆኖም የሚከተለትን አይጨምርም፤

ሀ) የቢሮ ሃላፊዎችን፣ ምክትል የቢሮ ሃላፊዎችን፣ እንዲሁም በተመሣሣይ ደረጃና ከዚያ በላይ የሆኑ ባለስልጣኖችን

ለ) የከተማ፣ የክፍለ ከተማና የወረዳ ምክር ቤት አባላትን፤

ሐ) የአዲስ አበባ ከተማ ፍርዴ ቤት ዳኞችንና ዓቃቢያን ሕግን፤

መ) የአስተዳደሩ ፖሊስ አባላትን እንዲሁም በፖሊስ ደንብ የሚተዳደሩ ሌሎች ሠራተኞችን፤

ሠ) አግባብ ባለው ሌላ ሕግ በዚህ አዋጅ እንዲይሸፈኑ የተደረጉ ሠራተኞችን፤

ረ) በከተማ፣ በክፍለ ከተማና በወረዳ የሚገኙ ሌሎች ተሿሚዎች፤

፭. "ጊዜያዊ ሠራተኛ" ማለት በመንግሥት መሥሪያ ቤት ውስጥ የዘላቂነት ባሕርይ በላለው ወይም ሁኔታዎች ሲያስገድድ በቋሚ የሥራ መደብ ላይ በጊዚያዊነት ተቀጥሮ የሚሠራ ሰው ነው፤ ሆኖም የሚከተለትን አይጨምርም፤

ሀ) በቀን ሂሳብ እየተከፈሊቸው የሚሠሩ የቀን ሠራተኞችን፤

ለ) በመንግሥት መሥሪያ ቤት ውስጥ ለሙያ መልመጃ ወይም ለተግባር ሥልጠና የተመደቡ ሰዎችን፤

ሐ) ከመንግሥት መሥሪያ ቤት ጋር በሚገቡት ውል መሠረት ዋጋ እየተከፈሊቸው በራሳቸው የንግድ ሥራ ወይም የሙያ ሓላፊነት የሚሠሩ ሰዎችን፤

መ) ባሊቸው ልዩ እውቀትና ችልታ ምክንያት ከመንግሥት መሥሪያ ቤት ጋር በሚገቡት ውል መሠረት ዋጋ እየተከፈሊቸው በትርፍ ጊዜያቸው የሚሠሩ ባለሙያዎችን፤

፮. "የመንግሥት መሥሪያ ቤት" ማለት ራሱን ችል በአዋጅ ወይም በደንብ የተቋቋመና ከመንግሥት በሚመደብለት በጀት የሚተዳደር የከተማው አስተዳደር መሥሪያ ቤት ነው፤

፯. "ቢሮ"ወይም "የቢሮ ሓላፊ"ማለት እንደ ቅደም ተከተለ የአስተዳደሩ የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ ወይም ሓላፊ ነው፤

፰. "የበላይ ሓላፊ" ማለት የመንግሥት መሥሪያ ቤትን በበላይነት የሚመራ ወይም ምክትልቹ ናቸው፤

፱. "የሥራ መደብ" ማለት በአንድ የመንግስት ሠራተኛ ሙለ የሥራ ጊዜ እንዲከናወኑ ሥልጣን ባለው አካል የተሰጡ ተግባርና ኃላፊነቶች ናቸው፤

፲. "የደረጃ ዕድገት" ማለት የመንግሥት ሠራተኛን ከያዘው የሥራ ደረጃ ከፍ ወዳለ የሥራ ደረጃ ማሳደግ ነው፤

፲፩. "የብቃት ማረጋገጫ ስርዓት" ማለት አንድ የመንግስት ሠራተኛ ወይም አዲስ ተቀጣሪ ሰው ሰለተመደበበት ወይም ስለሚቀጠርበት የስራ መደብ ብቁ ስለመሆኑ የሚረጋገጥበትስርዓት ነው፡፡

፲፪. "ደመወዝ" ማለት በአንድ የሥራ ደረጃ ለተመደቡ ሥራዎች የተወሰነ መነሻ ክፍያ ወይም የእርከን ክፍያ ነው፤

፲፫. "የሥራ ሁኔታ" ማለት በመንግሥት መሥሪያ ቤት እና በመንግሥት ሠራተኞች መካከል ያለ ጠቅላላ የሥራ ግንኙነት ሲሆን ይህም የሥራ ሰዓትን፣ ደመወዝን፣ ልዩ ልዩ ፈቃድችን፣

የሥራ አካባቢ ጤንነትና ደህንነትን፣ የሠራተኞች የሥራ ስንብት ሁኔታና ክፍያ፣ የዲስፕሊን አፈጻጸምና የቅሬታ አቀራረብ ሥነ-ሥርዓቶችን እና የመሳሰለትን ያጠቃልል፤

፲፬. “ድልድል” ማለት አንድን የመንግሥት ሠራተኛ በተመሳሳይ ደረጃና ደመወዝ ወይም ከፍ ባለ ደረጃና ደመወዝ ወይም በሠራተኛው ስምምነት ዝቅ ባለ ደረጃ መድቦ ማሠራት ነው፤

፲፭. "የዲስፕሊን እርምጃ" ማለት ማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ ይህንን አዋጅ ወይም አዋጁን ለማስፈፀም የሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎችን ወይም የሥነ-ምግባር ደንብ በመተሊለፍ ለሚያደርሰው ጥፋት የሚወሰንበት ቅጣት ነው፤

፲፮.“ጾታዊ ትንኮሳ” ማለት በሥራ ቦታ የሚፈጸም ሆኖ ከሌላው ወገን ፈቃድ ውጪ የሚቀርብ የወሲብ ሀሳብ ወይም ጥያቄ ወይም ሌላ ወሲባዊ ተፈጥሮ ያለው የቃል ወይም የአካል ንኪኪ ተግባር ሲሆን የሚከተለትን ያካትታል፤

ሀ) ከሌላው ወገን ፈቃድ ውጪ የመሳም፣ የሰውነት አካልን የመዲሰስ፣ የመጎንተል ወይም የመሳሰለውን የሰውነት ንክኪ የመፈጸም ድርጊት፤

ለ) ወሲብ አዘል በሆነ ሁኔታ ተጠቂውን መከታተል ወይም እንቅስቃሴውን መገደብ፤

ሐ) ለቅጥር፣ ለደረጃ እድገት፣ ለዝውውር፣ ለድልድል፣ ለሥልጠና፣ ለትምህርት፣ ለጥቅማ ጥቅሞች ወይም ማንኛውንም የሰው ሀብት ሥራ አመራር ተግባር ለመፈጸም ወይም ለመፍቀድ ወሲብን እንደ ቅድመ ሁኔታ ማስቀመጥ፡፡

**<u>፫. የጾታ አገላለፅ</u>**

በዚህ አዋጅ ውስጥ በወንድ ጾታ የተደነገገው የሴትንም ጾታ ያካትታል፡፡

**<u>፬. የተፈጻሚነት ወሰን</u>**

ይህ አዋጅ “የመንግሥት መሥሪያ ቤት” እና “የመንግሥት ሠራተኛ” በሚል ትርጉም በሚሸፈኑ መስሪያ ቤቶችና ሠራተኞች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

ክፍል ሁለት የመንግስት መሥሪያ ቤት አደረጃጀት፣ የሥራ ምዘና፣ የደመወዝ ስኬል እና አበል

**<u>፭. የመንግስት መሥሪያ ቤት አደረጃጀት</u>**

፩. ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት የተቋቋመበትን ዓላማ ስኬታማ ለማድረግ የሚያስፈልገውን አደረጃጀትና የሰው ኃይል ፍላጎት አጥንቶ ለቢሮው አቅርቦ ያስወስናል፡፡

፪. ቢሮው የአስፈጻሚ መስሪያ ቤቶችን አደረጃጀት አግባብነትና ውጤታማነት እያጠና ማሻሻያ ሲያስፈልግ ለካቢኔ ለውሳኔ ያቀርባል፡፡

**<u>፮. የሥራ ምዘና</u>**

፩. ቢሮው ተስማሚ የሥራ ምዘና ዘዴ በመምረጥ በማንኛውም መሥሪያ ቤት ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

፪. ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ደረጃቸው ያልተወሰነሊቸው አዲስ የሥራ መደቦችን የሥራ ዝርዝር አዘጋጅቶ ለቢሮው በማቅረብ ደረጃቸውን ያስወስናል፡፡

፫. የሥራ ምዘናና ደረጃ አወሳሰን አግባብ ባለው የፌዳራል መንግስት ሕግ መሠረት የሚወሰን ይሆናል፡፡

**፯. የደመወዝ ስኬል**

፩. የመንግሥት ሠራተኞች የደመወዝ ስኬል የመንግስትን የፋይናንስ አቅም፣ የህዝቡን አጠቃላይ የኑሮ ሁኔታ፣ የዋጋ ደረጃዎች እና አግባብነት ያላቸውን ሌሎች ሁኔታዎች ባገናዘበ መንገድ በየጊዜው እየተጠና የሚወሰን ይሆናል፡፡

፪. ቢሮው ያስተዳድራል ሆኖ ባገኘው ጊዜ ከሚመለከታቸው የመንግስት መስሪያ ቤቶች ጋር በመተባበር የደመወዝ ስኬል በማጥናትና በማዘጋጀት ለካቢኔ ለውሳኔ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም አፈጻጸሙን ይቆጣጠራል፡፡

**፫. የደመወዝ ስኬል**

ለእያንዳንዱ ደረጃ መነሻና መድረሻ ደመወዝ፣ እንዲሁም በየጊዜው የሚደረገውን የደመወዝ ጭማሪ የሚያመለክቱ እርከኖች ይኖሩታል፡፡

**፰. እኩል ዋጋ ያላቸው ሥራዎች እኩል ደመወዝ ስለመክፈል**

እኩል ዋጋ ያላቸው ሥራዎች ሁለ እኩል መነሻ ደመወዝ ይኖራቸዋል፡፡

**፱. የደመወዝ ክፍያ**

፩. ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት በየወሩ መጨረሻ ለሠራተኞቹ ወይም ለሕጋዊ ወኪሎቻቸው የደመወዝ ክፍያ ይፈጽማል፡፡

፪. የማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ ደመወዝ፣

ሀ) ሠራተኛው ስምምነቱን በጽሑፍ ሲገልጽ፣

ለ) በፍርድ ቤት ትዕዛዝ፣ ሐ) በሕግ በተደነገገው መሠረት፣ ካልሆነ በስተቀር ሊያዝ ወይም ሊቆረጥ አይችልም፡፡ ፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ (ለ) ወይም (ሐ) መሠረት ከሠራተኛ ደመወዝ በየወሩ የሚቆረጠው ከደመወዙ አንድ ሦስተኛ አይበልጥም፡፡

**፲. አበል**

፩. ማንኛውም አበል የሚከፈለው የመንግሥትን ሥራ ለማከናወን ያስተዳድራል ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው፡፡

፪. ቢሮው የአበል ዓይነቶችን እና ክፍያዎችን እያጠና ለካቢኔ ለውሳኔ ያቀርባል፣ ሲፈቀደም አፈጻጸማቸውን ይቆጣጠራል፡፡

## ክፍል ሦስት

## የሰው ሀብት ዕቅድ፣ ስምሪት እና የሥራ አፈጻጸም ምዘና ንኡስ ክፍል አንድ ምልመላና መረጣ

**፲፩. የሰው ሀብት ዕቅድ**

፩. የሰው ሀብት ዕቅድ አላማ ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት በስትራቴጂያዊ ዕቅድ ላይ የተቀመጡትን አላማዎች ለማሳካት የሰው ሀብት ፍላጎት ለመተንበይ፣ የሚያስፈልገውን የሰው ሀብት በዓይነትና በብዛት ለማሟሊት፣ ለማልማት፣ በአግባቡ ለመጠቀም የሚያግዙ እርምጃዎችን ለመውሰድና ውጤቱንም በየጊዜው እየገመገመ ማሻሻያ ለማድረግ ነው፡፡

፪. ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ስትራቴጂያዊ ዕቅደን መሠረት በማድረግ የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ የሰው ሀብት ዕቅደን አጥንቶ ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡

፫.ክፍት የሥራ መደቦችን በሠራተኛ ማስያዝ የሚቻለው የሰው ሀብት ዕቅድን መሠረት በማድረግ በደረጃ ዕድገት ወይም በቅጥር ወይም በዝውውር ወይም በድልድል ይሆናል፡፡

፬.ቢሮው የሰው ሀብት ዕቅድን በተመለከተ ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፡፡

**፲፪. ወደ መንግስት መስሪያ ቤት የመግቢያና የብቃት ማረጋገጫ ሥርዓት**

፩. በክፍት የሥራ መደቦች ላይ አመልካቾች ተወዳድረው የሚቀጠሩበትና የሚያድጉበት የመግቢያና የብቃት ማረጋገጫ ሥርዓት በፌደራል መንግስት በሚዘጋጁ መመዘኛዎችና መለኪያዎች መሰረት ይሆናል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፩) የተመለከተውን የመግቢያና የብቃት ማረጋገጫ ሥርዓትን የሚያስፈጽም ተቋም ሊቋቋም ይችላል ፡፡

**፲፫. ምልመላና መረጣ**

፩. የመንግሥት የሠራተኛ ቅጥር የሚፈጸመው በሀገር አቀፍ ደረጃ በሚወጣው መመዘኛ በሚሰጠው የፈተና ውጤት ወይም በሌላ ማናቸውም ዓይነት ተጨባጭ የሙያና ሥራ ብቃት ማረጋገጫ ላይ ብቻ ተመስርቶ ይሆናል፡፡

፪. በብሔረሰብ፣ በፆታ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ አመለካከት፣ በአካል ጉዳት፣ በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ወይም በሌላም ሁኔታ በሥራ ፈላጊዎችም ሆነ በመንግሥት ሠራተኞች መካከል ልዩነት ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡

፫. በዚህ አዋጅ ከአንቀጽ ፵፰ እስከ ፶፩ የተጠቀሱት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በክፍት የሥራ መደብ ላይ ሠራተኛ የሚመደበው ለሥራ መደቡ የሚጠየቀውን ተፈሊጊ ችሎታ የሚያሟሊና ከሌሎች ተወዳዳሪዎች ጋር ተወዳድሮ ይወክላልጫ ያለው ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡

**፲፬. የመንግሥት ሠራተኛ ሆኖ ለመቀጠር የማያስችለ ሁኔታዎች**

፩. የሚከተሉት የመንግሥት ሠራተኛ ሆነው ሉቀጠሩ አይችለም፤

ሀ) ዕድሜው ከ፲፰ ዓመት በታች የሆነ ሰው፤

ለ) ቅጣቱ ከተፈጸመ፣ በይርጋ ከታገደ ወይም በይቅርታ ከተሠረዘ በኋላ አምስት ዓመት ያለፈው ካልሆነ በስተቀር የሙስና፣ የእምነት ማጉደል፣ የስርቆት፣ የማጭበርበር ወይም የአስገድዶ መድፈር ወንጀል ፈጽሞ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት የተፈረደበት ማንኛውም ሰው፤

ሐ) የብቃት ማረጋገጫ ማስረጃ የላለው ሰው፤

መ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፯ መሠረት ቃለ- መሀላ ለመፈጸም ፈቃደኛ ያልሆነ ሰው፡፡ ፪. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)(ለ) እንደተጠበቀ ሆኖ ከማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፹፰ መሠረት በዲስፕሊን ጉድለት ምክንያት ከሥራ የተሰናበተ

ሰው ከሥራ ከተሰናበተበት ጊዜ ጀምሮ አምስት ዓመት ከመሙሊቱ በፊት በመንግሥት ሠራተኛነት ሉቀጠር አይችልም፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)(ሐ) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም አመልካች በመንግሥት ሥራ ተቀጥሮ ለማገልገል ብቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ከኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ምርመራ በስተቀር የጤንነት ማረጋገጫ የሕክምና ምርመራ እና በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፩)(ለ) ከተጠቀሱት ወንጀልች ነጻ መሆኑን የሚያረጋግጥ ከፖሉስ የተሰጠ ማስረጃ የማቅረብ ግድታ አለበት፡፡

፬. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)(ሀ) ቢኖርም ዕድሜያቸው ከ፲፬ ዓመት በላይ የሆናቸውና አሥራ ስምንት ዓመት ያልሞሊቸው ወጣቶች ስለሚቀጠሩበትና ስለሥራ ሁኔታቸው ቢሮው መመሪያ ያወጣል፡፡

፲፫. የውጭ አገር ዜጎች ቅጥር

የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የውጭ ዜጎችን በትውልድ አገራቸው በተለያዩ መብቶች ተጠቃሚ ለማድረግ በወጣው አዋጅ ቁጥር ፪፻፸/፲፱፺፬ አንቀጽ ፭(፪) እና የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፩(፪) እንደተጠበቁ ሆነው ዜግነቱ ኢትዮጵያዊ ያልሆነ ሰው በመንግሥት ሠራተኛነት ሉቀጠር አይችልም፡፡

፲፬. ማስታወቂያ ስለማውጣትና ስለቅጥር አፈጻጸም

፩. ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ክፍት ሥራ ቦታ ሲኖረው ማስታወቂያ በማውጣት አመልካቾች እንዲመዘገቡ መጋበዝ አለበት፡፡

፪. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት በገበያ ላይ እጥረት ባለባቸው ሙያዎች ከከፍተኛ ትምህርት ተቋሞች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ምሩቃንን በመጋበዝ በማወዳደር ቅጥር መፈጸም ይችላል ፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፪) መሰረት የሚቀጠሩ ምሩቃን በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፬ ንዑስ አንቀጽ (፩)(ሐ) የተመለከተውን የብቃት ማረጋገጫ ማቅረብ አለባቸው፡፡

፬. የመንግስት ሰራተኞች ቅጥር አፈጻጸም ዝርዝር ሁኔታ ቢሮው መመሪያ ያወጣል፡፡

፲፮. ቃለ-መሐላ

የተመረጠው አመልካች ሥራ ከመጀመሩ በፊት የሚከተለውን ቃለ-መሐላ ይፈጽማል፤

"እኔ --------------------- በመንግሥት ሠራተኛነቴ ከሁለም በላይ አድርጌ በእውነት፣ በታማኝነትና ሥነ-ምግባር ሕዝብን ለማገልገልና የመንግሥትን ፖሉሲዎች ለመፈጸም፣ በማንኛውም ጊዜ ሕገ- መንግሥቱንና የአገሪቱን ሕጎች ለማክበር እና በሥራዬ ምክንያት ያወቅሁትንና በሕግ ወይም በሚመለከተው አካል ውሳኔ በምስጢርነት የተመደቡትን ለሌላ ለማንኛውም ወገን ሊለመግለጽ ቃል እገባለሁ፡፡"

**፲፰. የመቀጠሪያ ደመወዝ አወሳሰን**

ማንኛውም አዲስ ተቀጣሪ የመንግሥት ሠራተኛ በመንግሥት ሠራተኞች የደመወዝ ስኬል መሠረት ለተቀጠረበት የሥራ መደብ የተወሰነው ደረጃ መነሻ ደመወዝ ይከፈለዋል፡፡

**፲፱. የሙከራ ጊዜ**

፩. የሙከራ ጊዜ ዓላማ አዲስ የተቀጠረ የመንግሥት ሠራተኛ ስለ ሥራ አፈጻጸሙ ክትትል እየተደረገ ብቃቱን ለማረጋገጥ ይሆናል፡፡

፪. የተመረጠው አመልካች የሥራ መደቡን መጠሪያ፣ የተመደበበትን ደረጃ፣ ደመወዙንና ሥራውን የሚጀምርበትን ቀን የሚገልጽ በአሰሪው መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ወይም ሠራተኛን ለመቅጠር ውክልና በተሰጠው የሥራ ሓላፊ የተፈረመ የሙከራ ቅጥር ደብዳቤ በሥራ መደቡ ከሚያከናውነው የሥራ ዝርዝር መግለጫ ጋር ይሰጠዋል፡፡

፫. የሠራተኛው የሙከራ ጊዜ በተቀጠረበት የሥራ መደብ ላይ ለስድስት ወር ሆኖ የሥራ አፈጻጸም ምዘና ውጤቱ ከመካከለኛ በታች ሆኖ ከተገኘ የሙከራ ጊዜው ለተጨማሪ ሦስት ወር ሊራዘም ይችላል ፡፡

፬. በተራዘመው የሙከራ ጊዜ ውስጥ ሠራተኛው መካከለኛ ወይም ከዚያ በላይ የተጠቃለለ የሥራ አፈጻጸም ምዘና ውጤት ካላገኘ ከሥራ ይሰናበታል፡፡

፭. የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፱ (፫) እና (፬) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በሙከራ ላይ ያለ የመንግሥት ሠራተኛ በሥራ ምክንያት በሚመጣ በሽታ ወይም በሥራ ላይ በሚደርስ አደጋ ምክንያት ከሥራ የቀረ እንደሆነ ያልጨረሰውን የሙከራ ጊዜ ከሕመሙ ወይም ከጉዳቱ ከተነሳበት ጊዜ አንስቶ እንዲጨርስ ይደረጋል፡፡

፮. በሙከራ ላይ የሚገኝ የመንግሥት ሠራተኛ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ከአንድ ወር በታች በሥራው ላይ ካልተገኘ በሥራው ላይ የተገኘበት ጊዜ ብቻ ታስቦ የሥራ አፈጻጸም ይሞላለታል፡፡

፯. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) ድንጋጌ ቢኖርም በወሊድ ምክንያት ከአንድ ወር በላይ በሥራዋ ላይ ያልተገኘች የሙከራ ሠራተኛ የወሊድ ፈቃድ እንደተጠናቀቀ የሙከራ ጊዜ እንድትጨርስ ይደረጋል፣ ሆኖም በሙከራ ሥራዋ ላይ ያልተገኘችበት ጊዜ ከአንድ ወር በታች ከሆነ የሥራ አፈጻጸም ምዘና ውጤቷ በሥራ ላይ በቆየችበት ጊዜ ታስቦ ይሞላላታል፡፡

፰. በዚህ አዋጅ በሌላ አኳኋን ካልተደነገገ በስተቀር በሙከራ ላይ ያለ የመንግሥት ሠራተኛ የሙከራ ጊዜውን የጨረሰ የመንግሥት ሠራተኛ ያለው መብትና ግድታ ይኖረዋል፡፡

፱. በሙከራ ላይ ያለን የመንግስት ሠራተኛ የሥራ አፈጻጸም ወቅቱን ጠብቆ ያልሞላ የሥራ ሓላፊ በዲሲፕሊን ተጠያቂ ይሆናል፡፡

__፳. ቋሚ የመንግሥት ሠራተኛ ስለመሆን__

፩. በሙከራ ጊዜው መካከለኛ ወይም ከዚያ በላይ የሥራ አፈጻጸም ምዘና ውጤት ያስመዘገበ የመንግሥት ሠራተኛ በቋሚነት መቀጠሩን የሚያረጋግጥ ደብዳቤ ይሰጠዋል፡፡

፪. በሙከራ ላይ የሚገኝ የመንግሥት ሠራተኛ የሥራ አፈጻጸም ምዘና ውጤት ጊዜውን ጠብቆ ያልተሞላለት እንደሆነ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፱(፫) እና (፬) የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የሥራ አፈጻጸም ምዘና እንዲሞላ ተደርጎ ለሙከራ ከተቀጠረበት ቀን ጀምሮ ቋሚ የመንግስት ሠራተኛ ይሆናል፡፡

__፳፩. ጊዜያዊ ሠራተኛ ስለመቅጠር__

፩. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ጊዚያዊ ሠራተኛ ሊቀጥር የሚችለው የዘላቂነት ባሕርይ በሌለው ሥራ መደብ ላይ ነው፤ ሆኖም ሁኔታዎች ሲያስገድዱ በቋሚ የሥራ መደብ ላይ ጊዚያዊ ሠራተኛ መቅጠር ይችላል ፡፡

፪. አንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ከፍተኛ ባለሙያ ለሚጠይቅ ማናቸውም ክፍት የሥራ መደብ በደረጃ ዕድገት፣ በዝውውር ወይም በቅጥር ኢትዮጵያዊ ባለሙያ ለማግኘት የማይቻል መሆኑን በማረጋገጥ የውጭ አገር ዜጋ በጊዜያዊነት ሊቀጥር ይችላል፡፡

፫. ኢትዮጵያውያን የሆኑ ጊዚያዊ ሠራተኞች አቀጣጠር፣ የሚኖራቸው መብቶችና ግዴታዎች እንዲሁም ስለሚጠበቁሊቸው የሥራ ሁኔታዎች ዝርዝር ሁኔታ የከተማው ካቢኔ በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

፬. የውጭ አገር ዜጋ ጊዚያዊ ሠራተኞች አቀጣጠር፣ የሚኖራቸው መብቶችና ግዴታዎች እንዲሁም ስለሚጠበቁሊቸው የሥራ ሁኔታዎች ዝርዝር ሁኔታ አግባብ ባለው በፌዳራል መንግስት ሕግ መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

__፳፪. ሥራዎችን በውል ለሦስተኛ ወገኖች አሸጋግሮ ስለማሠራት__

፩. ያስተዳድራል ሆኖ ሲገኝ ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ቢሮውን በማስፈቀድ የሕዝብን ጥቅም በማይጎዳ መልኩ የተወሰኑ የሥራ መደቦችን ወይም ሥራዎችን ለግል ድርጅቶች ወይም ለሌሎች ተቋማት በውል በማሸጋገር እንዲሠሩ ማድረግ ይችላል ፡፡

፪. ለግል ድርጅቶችና ለሌሎች ተቋማት በውል ሊሸጋገሩ ስለሚችለ ሥራዎች ቢሮው ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ ያወጣል፡፡

__፳፫.የመንግስት ሰራተኛን በጋራ ስለመቅጠር__

፩. የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የአንድ የመንግሥት ሠራተኛ ልዩ እውቀትና ሙያዊ አቅም ለሥራቸው እጅግ ያስተዳድራል ሆኖ ሲያገኙት በጋራ ሊቀጥሩት ይችሊለ፡፡

፪. የቅጥሩ ሁኔታ፣ ቅጥሩ የሚቆይበት ጊዜ፣ ደመወዝ አከፋፈልና ሌሎች የስራ ሁኔታዎች ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናለ፡፡ ንኡስ ክፍል ሁለት የደረጃ ዕድገት

፫. የደረጃ ዕድገት አላማ የደረጃ ዕድገት አሰጣጥ አላማ ሥራው ብቃት ባለው ሠራተኛ እንዲከናወን ለማስቻል፣ የመሥሪያ ቤቱን የሥራ ውጤት ለማሻሻል እና ሠራተኛውን ለማበረታታት ነው፡፡

**፳፰. የደረጃ ዕድገት አሰጣጥ**

፩. ማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ ለደረጃ እድገት ለመወዳደር የዚህን አዋጅ አንቀጽ ፲፪(፩) መሠረት የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡

፪. የሙከራ ጊዜውን ያጠናቀቀ የመንግሥት ሠራተኛ በደረጃ ዕድገት ዝርዝር አፈጻጸም መመሪያ ውስጥ ለውድድር የማያበቁት ሁኔታዎች ከላለ በስተቀር በመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ውስጥ ለወጣ ክፍት የሥራ መደብ በደረጃ እድገት በማመልከት ለመወዳደር ይችላል ፡፡

፫. የደረጃ ዕድገት ስለሚሰጥበት ሌሎች ዝርዝር ሁኔታዎች ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

**ንኡስ ክፍል ሦስት**

**ዝውውርና ድልድል**

**፳፱. የውስጥ ዝውውር**

፩. አንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ለሥራው ያስተዳድራል ሆኖ ሲያገኘው ግልጽ የሆነ አሠራርን በመከተል አንድ የመንግሥት ሠራተኛን በዚያው መስሪያ ቤት ውስጥ እኩል በሆነ የሥራ ደረጃና ደመወዝ ወደ ሌላ የሥራ መደብ ወይም ከአንድ የሥራ ቦታ ወደ ሌላ ሥራ ቦታ በማዛወር ሊያሠራ ይችላል ፡፡

፪.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም በመሥሪያ ቤቱ ላይ አደጋ እንዲይደርስ ለመከላከል ወይም አደጋው ያደረሰውን ጉዳት ለማስተካከል ሲባል አንድን የመንግሥት ሠራተኛ ደመወዙ ሳይቀነስ፣ ደረጃው ወይም የሥራው ዓይነት ሳይጠበቅ ከአንድ ዓመት ሊልበለጠ ጊዜ በጊዜያዊነት አዛውሮ ማሠራት ይችላል ፡፡

፫. የመንግሥት ሠራተኛ በጤና መታወክ ምክንያት በያዘው የሥራ መደብ ወይም ባለበት የሥራ ቦታ ላይ ሊሠራ አለመቻለ በሐኪም ማስረጃ ሲረጋገጥ፣

ሀ) በተመሳሳይ ደረጃ ሊመደብበት የሚችል ክፍት የሥራ መደብ ካለ በያዘው ደረጃ፣ ወይም

ለ) በተመሳሳይ ደረጃ ሊመደብ የሚችልበት ክፍት የሥራ መደብ ከላለና ሠራተኛው ዝቅ ባለ ደረጃ ላይ ለመሥራት ፈቃደኛ ከሆነ ደረጃው ተቀንሶ፣ወደ ሚስማማው የሥራ መደብ ወይም የሥራ ቦታ ይዛወራል፡፡

፬. የአንድ የመንግሥት ሠራተኛ የሥራ መደብ የተሰረዘ እንደሆነ በመሥሪያ ቤቱ ውስጥ ተመሳሳይ ደረጃ ወዲለው የሥራ መደብ ይዛወራል፡፡

**፷፯. በተጠባባቂነት ማሠራት**

፩. ሁኔታዎች ሲያስገድዱ አንድን የመንግሥት ሠራተኛ ከአንድ ዓመት ሊልበለጠ ጊዜ ከፍ ያለ ደረጃ ባለው የሥራ መደብ ላይ በተጠባባቂነት እንዲሠራ ማድረግ ይቻላል፡፡

፪. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም ከአንድ ዓመት በላይ ለሚፈጅ ትምህርት ወይም ስልጠና የሄደን የመንግሥት ሠራተኛ ለመተካት ትምህርቱ ወይም ሥልጠናው ለሚፈጀው ጊዜ ድረስ የሥራ መደቡን ግልጽ በሆነ መስፈርት በውድድር በተጠባባቂ ሠራተኛ ማሠራት ይቻላል፡፡

፫. ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ በተጠባባቂነት እንዲሠራ ሲደረግ የተጠባባቂነት አበል ይከፈለዋል፡፡

፬. ቢሮው የመንግሥት ሠራተኛ በተጠባባቂነት ስለሚመደብበት ሁኔታና ስለሚከፈለው የተጠባባቂነት አበል መጠን ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፡፡

**፷፰. ከሌላ መሥሪያ ቤት የሚደረግ ዝውውር**

፩. አንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ለሥራው ያስተዳድራል ሆኖ ሲያገኘውና ሊኪና ተቀባይ መሥሪያ ቤቶች እንዲሁም ሠራተኛው ሲስማሙ አንድን የመንግሥት ሠራተኛ እኩል በሆነ ደረጃና ደመወዝ ቢሮውን በማሳወቅ አዛውሮ ማሠራት ይችላል፡፡

፪. የሚመለከተው መንግሥት ሠራተኛ፣ የክልለ የመንግሥት መሥሪያ ቤት እና የፌዳራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሲሰማሙ እንዲሁም በክልለ ዝውውርን ለማጽደቅ ስልጣን የተሰጠው አካል ሲያጸድቀው አንድን የመንግሥት ሠራተኛ ከክልል ወይም ከፌደራል መንግስት መስሪያ ቤትወደ አስተዳደሩ የመንግሥት መሥሪያ ቤት እኩል በሆነ ደረጃና ደመወዝ አዘዋውሮ ማሠራት ይቻላል፡፡

፫. በተመሳሳይ ደረጃ ለመቀጠር አመልክቶ በውድድሩ የተመረጠ የመንግስት ሠራተኛ በዝውውር ሥርዓት እንዲመደብ ይደረጋል፡፡

፬. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚዛወር ሠራተኛ የአስተዳደሩ የመንግሥት ሠራተኞች ሕግ በሚያዘው መሠረት በያዘው የሥራ ደረጃና በአገልግሎት ዘመኑ ምክንያት ያገኝ የነበረው ደመወዝና መብቶቹ አይቀነሱበትም፡፡

፭. የትዳር አጋሮችን ለማገናኘት ሲባል አንድን የመንግስት ሠራተኛ በተመሳሳይ ደረጃና ደመወዝ፣ ተመሳሳይ ደረጃና ደመወዝ ካልተገኘ በሠራተኛው ስምምነት ዝቅ ባለ ደረጃ አዛውሮ ማሰራት ይቻላል፡፡

**፷፱. የትውስት ዝውውር**

፩. ያስተዳድራል ሆኖ ሲገኝ ላኪው የመንግሥት መሥሪያ ቤትና ሠራተኛው ሲስማሙ አንድን የመንግሥት ሠራተኛ በሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም የክልል ወይም የፌዳራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም የመንግሥት የልማት ድርጅት ወይም መንግሥታዊ

ወዲልሆኑ ድርጅቶች ከአንድ ዓመት ለማይበልጥ ጊዜ በትውስት ተዛውሮ እንዲሠራ ማድረግ ይቻላል፡፡

፪. ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ያስተዳድራል ሆኖ ሲያገኘው ከመንግሥት ልማት ድርጅት ወይም ከክልል መንግሥት ወይም ከፌዳራል መሥሪያ ቤት ወይም መንግሥታዊ ካልሆነ ድርጅት አንድን ሠራተኛ ከአንድ ዓመት ለማይበልጥ ጊዜ በትውስት አዛውሮ ማሠራት ይችላል ፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም አስተዳደሩ በሀገር ወይም በሕዝብ ላይ የሚደርስ ድንገተኛ አደጋን ለመከለከል ወይም አደጋው ያደረሰውን ጉ ዳት ለማስተካከል ሲባል አንድን የመንግሥት ሠራተኛ በያዘው ደመወዝ ከአንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወደ ሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም በክልለ መንግሥት ጥያቄ መሠረት ወደ ክልል መንግሥት መሥሪያ ቤት ከአንድ ዓመት ለማይበልጥ ጊዜ በትውስት አዛውሮ ማሠራት ይችላል ፡፡

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በትውስት የተዛወረ ሠራተኛ፣

ሀ) ደመወዝና ማንኛውም ጥቅሙ በዝውውሩ ምክንያት ሳይጓደል በትውሰት አዛውሮ በሚያሰራው መስሪያ ቤት ይፈጸምለታል፤

ለ) የሥራ አፈጻጸም ምዘና ውጤቱ በትውሰት አዛውሮ በሚያሰራው መስሪያ ቤት ተሞልቶ ለቀጣሪው መሥሪያ ቤት ይተሊለፋል፤

ሐ) የዲስፐሊን ጥፋት የፈጸመ እንደሆነ በትውስት ተቀባዩ መስሪያ ቤት ለቀጣሪ መሥሪያ ቤቱ ከዝርዝር ማስረጃ ጋር ያሳውቃል፣ ቀጣሪ መሥሪያ ቤቱም ጉዳዩን አጣርቶ እንደ ያስተዳድራልነቱ ተገቢውን እርምጃ ይወስዲል፡፡

**__፴. ድልድል__**

፩. የመንግሥት መሥሪያ ቤት አዲስ አደረጃጀት አጥንቶ ተግባራዊ ሲያደርግ ሠራተኞቹን በማወዳደር ደልድል ማሠራት አለበት፡፡

፪. በማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት የሚገኝ ክፍት የሥራ መደብ ከሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት በሚደለደል የመንግሥት ሠራተኛ እንዲያዝ የሚደረገው መሥሪያ ቤቱ የተዘጋ ወይም ትርፍ የሰው ኃይል ሲኖረው ወይም የሥራ መደቡ የተሰረዘ ከሆነና ድልድለን ቢሮው ሲወስን ነው፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚደለደል ሠራተኛ ቀደም ሲል ይዞት በነበረው ደረጃና በአገልግሎት ዘመኑ ምክንያት ያገኝ የነበረው ደመወዝና ጥቅሞቹ አይቀነሱበትም፡፡

## __ንኡስ ክፍል አራት__

## __የሥራ አፈጻጸም__

**__፴፩. የሥራ አፈጻጸም ምዘና__**

፩. የሥራ አፈጻጸም ምዘና ዓላማ በሥራ እቅድ ላይ የተመሠረተ ሆኖ፡-

ሀ) ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ ሥራውን በሚጠበቀው መጠን፣ ጥራት፣ ጊዜ እና ወጪ በተሟላ ሁኔታ እንዲያከናውን ለማድረግ፤

ለ) ተከታታይ የሥራ አፈጻጸም ምዘና በማካሄድ የመንግስት ሠራተኛውን ጠንካራና ደካማ ጎኖች በመለየት ቀጣዩ የሥራ አፈጻጸሙ እንዲሻሻል በማድረግ ውጤታማ እንዲሆን ለማብቃት፤

ሐ) የመንግሥት ሠራተኛውን የሥልጠናና የመሻሻል ፍላጎት በትክክል ለይቶ ለማወቅ፤

መ) በውጤት ላይ የተመሠረተ ማትጊያ ለመስጠት፤

ሠ) የመንግስት መሥሪያ ቤቱ በተጨባጭ መረጃ ላይ ተመሥርቶ አስተዳደራዊ ውሳኔዎችን እንዲሰጥ ለማስቻል፤ ነው፡፡

፪. በመንግስት መስሪያ ቤት የሚከናወን የሥራ አፈጻጸም ምዘና ሥርዓት፡-

ሀ) ግልጽና በተጨባጭ መረጃ ላይ የተመሠረተ የውጤት ምዘና ለማከናወን የሚያስችል፤

ለ) የተከናወነው ሥራ ከተመደበው በጀት፣ ጊዜ፣ መጠንና ጥራት ጋር በማነጻጸር ትክክለኛውን ውጤት ለመመዘን የሚያስችል፤

ሐ) የቡድን አሠራርንና የጋራ ተነሳሽነትን የሚያጎለበት፤

መ) በመንግሥት ሠራተኞች ወይም ቡድኖች መካከል ጤናማ የውድድር መንፈስን በመፍጠር ተቋማዊ ውጤትን ለማሻሻል የሚያግዝ፤

ሠ) በአፈጻጸም ተከታታይነትና ተመጋጋቢነት ባሊቸው ሥራዎች መካከል አንደ በሌላኛው ውጤት ላይ የሚያሳድረውን ተፅዕኖ ለመገምገም የሚያስችል፣ መሆን አለበት፡፡

**<u>፴፪. የመወዝ ጭማሪና ማበረታቻ አወሳሰን</u>**

፩. የመንግሥት ሠራተኛ የደመወዝ እርከን ጭማሪ የሚያገኘው በሥራ አፈጻጸም ምዘና ውጤት ላይ በመመስረት በየሁለት ዓመቱ ይሆናል፡፡

፪. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የሥራ አፈጻጸም ውጤትን መሰረት በማድረግ ለመንግስት ሠራተኛ ማበረታቻ ይሰጣል፡፡

፫. ቢሮው የሥራ አፈጻጸም ምዘና ስለሚከናወንበት ሥርዓት፣ የእርከን ጭማሪ እና ማበረታቻ ስለሚሰጥበት ሁኔታ ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ ያወጣል፡፡

## <u>ክፍል አራት የሥራ ሰዓትና ፍቃድ</u>

## <u>ንኡስ ክፍል አንድ የሥራ ሰዓት</u>

**<u>፴፫. መደበኛ የሥራ ሰዓት</u>**

የመንግሥት ሠራተኞች መደበኛ የሥራ ሰዓት እንደየሥራው ሁኔታ የሚወሰን ሆኖ በሳምንት ከ፴፱ ሰዓት መብለጥ የለበትም፡፡

**<u>፴፬. የሥራ መግቢያና መውጫ ሰዓት</u>**

የመንግሥት ሠራተኞች የሥራ መግቢያና መውጫ ሰዓት አግባብ ባለው የፌዳራል መንግስት ሕግ መሰረት ተፈጻሚ ይደረጋል ፡፡

**<u>፴፭. የትርፍ ሰዓት ሥራ</u>**

፩. የትርፍ ሰዓት ሥራ ለሠራ ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ በሠራተኛው ምርጫ መሠረት የማካካሻ ዕረፍት ወይም የትርፍ ሰዓት ክፍያ ይሰጠዋል፡፡

፪. የትርፍ ሰዓት ሥራ ስለሚፈቀደባቸው ሁኔታዎች፣ ስለክፍያው መጠንና የማካካሻ ዕረፍት ስለሚሰጥበት ሁኔታ ቢሮው ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፡፡

**ፀ፮. የሕዝብ በዓላት እና የሳምንት የዕረፍት ቀናት**

፩. ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ በሕዝብ በዓል፣ በሳምንት የዕረፍት ቀናት ወይም በመንግሥት ውሳኔ መሥሪያ ቤቶች ዝግ ሆነው በሚውለበት ቀን ባለመሥራቱ መደበኛ የደመወዝ ክፍያ አይቀነስበትም፡፡

፪. የሥራው ሁኔታ አስገድድ በሕዝብ በዓል ወይም በመንግሥት ውሳኔ መሥሪያ ቤቶች ዝግ ሆነው በሚውለበት ቀን እንዲሠራ የታዘዘ የመንግሥት ሠራተኛ ምርጫውን መሠረት በማድረግ የትርፍ ሰዓት ክፍያ ወይም የማካካሻ ዕረፍት ይሰጠዋል፡፡ዝግ ሆነው በሚውለበት ቀን እንዲሠራ የታዘዘ የመንግሥት ሠራተኛ ምርጫውን መሠረት በማድረግ የትርፍ ሰዓት ክፍያ ወይም የማካካሻ ዕረፍት ይሰጠዋል፡፡

፪. ከአንድ ዓመት በላይ ያገለገለ ሠራተኛ ለእያንዳንዱ ተጨማሪ ዓመት አንድ የሥራ ቀን እየታከለበት የዓመት ዕረፍት ፈቃድ ያገኛል፣ ሆኖም የሚሰጠው የአንድ የዓመት ዕረፍት ፈቃድ ከ፴ የሥራ ቀናቶች መብለጥ የለበትም፡፡

፫. በሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት፣ በፌዳራል ወይም በክልል መንግሥት መሥሪያ ቤት ቀደም ሲል የተሰጠ አገልግሎት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) አፈጻጸም የሚታሰብ ይሆናል፡፡

**ፀ፱. የዓመት ዕረፍት ፈቃድ አሰጣጥ**

፩. የዓመት ዕረፍት ፈቃድ የመሥሪያ ቤቱን ዕቅድ መሠረት በማድረግና በተቻለ መጠን የሠራተኛውን ፍላጎት በማመዛዘን በሚዘጋጀውና ሠራተኛውም እንዲያውቀው በሚደረግ ፕሮግራም መሠረት በበጀት ዓመቱ ውስጥ ይሰጣል፡፡

፪. ሠራተኛው የዓመት ዕረፍት ፈቃደን በሚወስድበት ጊዜ በዕረፍት ላይ የሚቆይበትን የወር ደመወዙን በቅድሚያ ሉወስድ ይችላል ፡፡

፫. የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፀ፯ (፪) እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ የመንግሥት ሠራተኛ አስራ አንድ ወሩን ካጠናቀቀ በኋላ ባገለገለበት በጀት ዓመት ለሰጠው አገልግሎት የዓመት ዕረፍት ፈቃደ በአገልግሉቱ መጠን ተሰልቶ እንዲሰጠው ይደረጋል፡፡

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የበጀት ዓመቱ ከመጠናቀቁ በፊት የዕረፍት ፈቃድ ወስድ አገልግሉቱን በራሱ ፈቃድ ያቋረጠ የመንግስት ሰራተኛ አገልግሎትያልሰጠበት ጊዜ ታስቦ በፈቃድ ላይ እያለ የተከፈለውን ደመወዝ እንዲመልስ ይደረጋል፡፡

**፹. የዓመት ዕረፍት ፈቃድ ማስተሊለፍ**

፩. የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፀ፱ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም የሥራው ሁኔታ በማስገደደ ምክንያት መሥሪያ ቤቱ ለሠራተኛው የዓመት ዕረፍት ፈቃደን በበጀት ዓመቱ ውስጥ ሊሰጠው ያልቻለ እንደሆነ የመሥሪያ ቤቱ የበላይ ሓላፊ ከሁለት የበጀት ዓመት ሊልበለጠ ጊዜ ሉያስተሊልፈው

ይችላል ፣ ሆኖም ያልተጠቀመበት የዓመት ዕረፍት ፈቃድ በሦስተኛው በጀት ዓመት ለሠራተኛው መሰጠት አለበት፡፡

፪. የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፯ (፫) ድንጋጌ ቢኖርም ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የዓመት ዕረፍት ፈቃደ ለሚተላለፍበትና ፈቃደ በገንዘብ ተለውጦ እንዲሰጠው ለሚጠይቅ ሠራተኛ በጀት በቅድሚያ በማስያዝ ከተላለፈው የዓመት ዕረፍት ፈቃድ ውስጥ የመጀመሪያውን የአንድ ዓመት ዕረፍት ፈቃድ ብቻ በገንዘብ ተለውጦ እንዲሰጠው ማድረግ አለበት፡፡

፫. የአንድ መንግሥት ሠራተኛ የዓመት ዕረፍት ፈቃድ በገንዘብ ሲለወጥ የሠራተኛው የአንድ ቀን ደመወዝ የሚታሰበው ያልተጣራ የወር ደመወዙን በ፴ ቀናት በማካፈል ነው፡፡

**<u>፵፩. ያልተወሰደ የዓመት ዕረፍት ፈቃድ</u>**

፩. የመንግሥት ሠራተኛው አገልግሎት በመቋረጡ ያልተወሰደ የዓመት ዕረፍት ፈቃድ የሥራ ቀናቶች ብቻ ታስበው በገንዘብ ተለውጦ ይሰጠዋል፡፡

፪. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፰ መሠረት ለተዛወረ ወይም በአንቀጽ ፴(፪) መሠረት ለተደለደለ የመንግሥት ሠራተኛ ተፈፃሚ አይሆንም፤ ሆኖም ሠራተኛው በነበረበት የመንግሥት መሥሪያ ቤት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵(፩) መሠረት የተላለፈለት የዓመት ወደ ተዛወረበት ወይም ወደ ተደለደለበት የመንግሥት መሥሪያ ቤት ይተላለፍለታል፡፡

**<u>፵፪. የወሊድ ፈቃድ</u>**

፩. ነፍሰጡር የሆነች የመንግሥት ሠራተኛ፣

ሀ) ከእርግዝናዋ ጋር የተያያዘ ምርመራ ለማድረግ ሐኪም በሚያዘው መሠረት ደመወዝ የሚከፈልበት ፈቃድ ይሰጣታል፤

ለ) ከመውለድ በፊት ዕረፍት እንድታደርግ ሐኪም ካዘዘ ደመወዝ የሚከፈልበት ዕረፍት ይሰጣታል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ፈቃድ እንደ ህመም ፈቃድ አይቆጠርም፡፡

፫. ነፍሰጡር የሆነች የመንግሥት ሠራተኛ መውለጃዋ ሲደርስ እወልዳለሁ ብላ ከገመተችበት ቀን በፊት ፴ ተከታታይ ቀናት የቅድመ ወሊድ ፈቃድ፣ እንዲሁም ስትወልድ ከወለደችበት ቀን ጀምሮ ፺ ተከታታይ ቀናት፣ በአጠቃላይ ፻፳ ተከታታይ ቀናት ደመወዝ የሚከፈልበት የወሊድ ፈቃድ ይሰጣታል፡፡

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት ሠራተኛዋ የተሰጣት የቅድመ ወሊድ ፈቃድ ከማለቁ በፊት ከወለደች ያልተጠቀመችበትን ቀሪ የቅድመ ወሊድ ፈቃድ ከወለደች በኋላ እንድትጠቀምበት ይደረጋል፡፡

፫. ሠራተኛዋ የወሰደችው የቅድመ ወሊድ ፈቃድ ሲያልቅ ያልወለደች እንደሆነ እስከምትወልድበት ቀን ድረስ ባለት የሥራ ቀናት የምትቆይበት ዕረፍት በበጀት ዓመቱ ካሊት የዓመት ዕረፍት ፈቃድ ወይም በበጀት ዓመቱ የዓመት ፈቃድ የሌላት እንደሆነ ከሚቀጥለው የበጀት ዓመት የዕረፍት ፈቃዶ ይተካል፡፡

፬. ሠራተኛዋ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተወሰነውን የወሊድ ፈቃድ ከጨረሰች በኋላ ብትታመምና ተጨማሪ ፈቃድ የሚያስፈልጋት መሆኑ በሀኪም ከተረጋገጠ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፫(፩) በተደነገገው መሠረት የሕመም ፈቃድ መውሰድ ትችላለች፡፡

፭. ማንኛውም ስድስት ወር የሞሊት ነፍሰጡር የሆነች የመንግስት ሠራተኛ የቅድመ ወሊድ ፈቃድ ከመውሰዶ በፊት ጽንሱ የተቋረጠባት ከሆነ ይህንኑ የሚያረጋግጥ የህክምና ማስረጃ ስታቀርብ የ፷ ቀን የድህረ ወሊድ ፈቃድ ይሰጣታል፡፡

፮. የቅድመ ወሊድ ፈቃድ ከወሰደች በኋላ የጽንስ መቋረጥ ካጋጠማት የወሰደችው የቅድመ ወሊድ ፈቃዶ ተቋርጦ በዚህ  አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፫) የተመለከተው የ፺ ቀን የድህረ ወሊድ ፈቃድ ይሰጣታል፡፡

፱. ከሦስት እስከ ስድስት ወር ባለው የእርግዝና ጊዜ ውስጥ የፅንስ መቋረጥ ያጋጠማት የመንግሥት ሠራተኛ ደመወዝ የሚከፈልበት ፴ ተከታታይ ቀን ፈቃድ ይሰጣታል፡፡ ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ የትዳር ጓደኛው ስትወልድ ደመወዝ የሚከፈልበት ፲ የሥራ ቀን ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡

__፵፫. የሕመም ፈቃድ__

፩. ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ በሕመም ምክንያት ሥራ መሥራት ያልቻለ እንደሆነ ደመወዝ የሚከፈልበት የሕመም ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሙከራ ጊዜውን ሊጠናቀቀ የመንግሥት ሠራተኛ የሚሰጥ የሕመም ፈቃድ በተከታታይ ወይም በተለያየ ጊዜ ቢወስድም ሕመሙ ከደረሰበት የመጀመሪያ ቀን አንስቶ ባለው አስራ ሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ከስምንት ወር ወይም በአራት ዓመት ውስጥ ከአሥራ ሁለት ወር አይበልጥም፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የሚሰጥ የሕመም ፈቃድ ለመጀመሪያዎቹ ስድስት ወራት ከሙሉ ደመወዝ ጋር እና ለሚቀጥለት ሁለት ወራት ከግማሽ ደመወዝ ጋር ይሆናል፡፡

፬. የሙከራ ጊዜውን ያሊጠናቀቀ የመንግሥት ሠራተኛ ከታመመ የህክምና ማስረጃ የሚቀርብበት የአንድ ወር የሕመም ፈቃድ ከደመወዝ ጋር ይሰጠዋል፡፡

__፭. ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ ሲታመም፣__

ሀ) ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ካሊጋጠመው በስተቀር በተቻለ ፍጥነት መታመሙን ለመሥሪያ ቤቱ ማሳወቅ አለበት፣

ለ) በተከታታይ ከሦስት ቀናት ወይም በአንድ የበጀት ዓመት ውስጥ ከስድስት ቀናት በላይ በሕመሙ ምክንያት ከሥራ የቀረ እንደሆነ ለመታመሙ የሕክምና ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡

፯. የሙከራ ጊዜውን ያጠናቀቀ የመንግስት ሠራተኛ በዓመት ፈቃድ ላይ እያለ መታመሙን የሚያረጋግጥ የህክምና ማስረጃ ካቀረበ የዓመት ፈቃደ ተቋርጦ የሕመም ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡

፰. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፯) መሠረት የተቋረጠው የዓመት ፈቃድ የሕመም ፈቃደ እንደተጠናቀቀ እንዲቀጥል ይደረጋል፡፡

**፴፬. የህክምና ማስረጃ**

፩. "የሕክምና ማስረጃ" ማለት በሀገር ውስጥ አግባብ ባለው ባለሥልጣን ፈቃድ ከተሰጠው የግልም ሆነ የመንግሥት የሕክምና ተቋም የሚሰጥ ወይም ከሀገር ውጭ የተገኘና ስለትክክለኛነቱ አግባብ ባለው ባለሥልጣን የተረጋገጠ የምስክር ወረቀት ነው፡፡

፪. የምስክር ወረቀቱ ስለመንግሥት ሠራተኛ የጤና ሁኔታና ስለሚሰጠው የሕመም ፈቃድ መግለጽ አለበት፡፡

**፴፭. ለግል ጉዳ የሚሰጥ ፈቃድ**

ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ ለሐዘን፣ ለጋብቻ እና ለፈተና በአንድ የበጀት ዓመት ውስጥ ሰባት የሥራ ቀናት ፈቃድ ከደመወዝ ጋር ይሰጠዋል፡፡

**፴፮. ከደመወዝ ጋር የሚሰጥ ልዩ ፈቃድ**

ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ፣

፩. ከፍርድ ቤት ወይም ከሌሎች ሥልጣን ከተሰጣቸው አካላት መጥሪያ ሲደርሰው የተጠራበት ጉዳይ ለሚጠይቀው ጊዜ፣

፪. ከሕዝባዊ ምርጫ ጋር በተያያዘ ጉዳይ ሲሆን ምርጫው ለሚወስድበት ጊዜ፣ ከደመወዝ ጋር ልዩ ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡

**፴፯. ያለደመወዝ የሚሰጥ ልዩ ፈቃድ**

፩. የመንግሥት ሠራተኛ በበቂ ምክንያት ደመወዝ የማይከፈልበት ልዩ ፈቃድ እንዲሰጠው ሲጠይቅና የመሥሪያ ቤቱን ጥቅም የማይጎዳ ሲሆን የመሥሪያ ቤቱ የበላይ ሓላፊ ከአንድ ዓመት ለማይበልጥ ጊዜ ሊፈቅድለት ይችላል ፡፡

፪. የመንግሥት ሠራተኛ በሕዝብ ምርጫ ተወዳዳሪ ሆኖ ሲቀርብ የምርጫ ቅስቀሳ በሚካሄዴበት ወቅት እና ምርጫው በሚከናወንበት ጊዜ ያለ ደመወዝ ፈቃድ እንዲሰጠው ይደረጋል፡፡

፫. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ቢኖርም የመንግሥት ሠራተኛው ያለደመወዝ ልዩ ፈቃድ እንዲሰጠው የጠየቀው የመንግሥት መሥሪያ ቤትን በሚመለከት የፕሮጀክት ሥራ ላይ በመመደቡ ወይም በትዳር ጓደኛው ለዱፕልማቲክ ሚሲዮን ሥራ በውጭ ሀገር መመደብ

ምክንያት ከሆነ ልዩ ፈቃድ የፕሮጀክት ወይም የዱፕልማቲክ ሚሲዮን ሥራው እስከሚጠናቀቅ ሊለው ጊዜ ሊሰጠው ይችላል ፡፡

## ክፍል አምስት

## ተጨማሪ የድጋፍ እርምጃ የሚስፈልጋቸው የኅብረተሰብ ክፍልች የሥራ ሁኔታ

### ፺፰. ለሴት ሠራተኞች የሚጠበቁ የሥራ ሁኔታዎች

፩. ማንኛውም የመንግስት መሥሪያ ቤት ሴት የመንግሥት ሠራተኞችን ለማብቃትና በውሳኔ ሰጪ የሥራ ቦታዎች ላይ እንዲመደቡ ለማድረግ የሚያስችለ የተጨማሪ ድጋፍ እርምጃዎችን መውሰድ አለበት፡፡

፪. ሴቶች በቅጥር፣ በደረጃ እድገት፣ በዝውውር፣ በድልድል፣ በትምህርትና ሥልጠና አፈጻጸም የተጨማሪ ድጋፍ እርምጃ ተጠቃሚ መሆን አለባቸው፡፡

፫. ነፍሰ ጡር የሆነችን የመንግሥት ሠራተኛ በቅጥር ወይም በደረጃ ዕድገት ከተመደበችበት የሥራ መደብ ወደ ሌላ የሥራ መደብ መድቦ ማሰራት የተከለከለ ነው፤ ሆኖም ለራሷ ጤንነት ወይም ለፅንሱ አደገኛ መሆኑ በሕክምና ማስረጃ ሲረጋገጥ ተስማሚ ወደ ሆነ የሥራ መደብ ወይም የሥራ ቦታ ተመድባ እንድትሰራ መደረግ አለበት፡፡

፬. ማንኛውም የመንግስት መስሪያ ቤት ሴት የመንግስት ሠራተኛ ነፍሰጡር በሆነችበት ጊዜና ከወለደችበት ቀን ጀምሮ በአራት ወር ጊዜ ውስጥ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፹፯ መሠረት በሚያደርገው የሠራተኛ ቅነሳ ከሥራ ሊያሰናብታት አይችልም፡፡

፭. ማንኛዋም ሴት የመንግሥት ሠራተኛ አንድ ዓመት ያልሞሊውን ሕጻን ልጇን ለማሳከም በህክምና ማስረጃ ለተረጋገጠ ጊዜ ደመወዝ የሚከፈልበት ፈቃድ ይሰጣታል፤ በተለያየ ምክንያት እናት ባትኖር ይህ ፈቃድ የመንግስት ሠራተኛ ለሆነ የልጁ አባት ወይም አሳዲጊ ይሰጣል፡፡ ፮. ማንኛውም የመንግስት መስሪያ ቤት ሴት የመንግስት ሠራተኞች ህጻናት ልጆቻቸውን የሚያጠቡበትና ህጻናቱን የሚንከባከቡበት የህጻናት ማቆያ ማቋቋም አለበት፤ ዝርዝር አፈጻጸሙ የሚመለከተው የመንግስት መስሪያ ቤት በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

### ፺፱. ለአካል ጉዳተኞች የሚጠበቁ የሥራ ሁኔታዎች

፩. አካል ጉዳተኞች በቅጥር፣ በደረጃ ዕድገት፣ በዝውውር፣ በድልድል፣ በትምህርትና ሥልጠና አፈጻጸም የተጨማሪ ድጋፍ እርምጃ ተጠቃሚ መሆን አለባቸው፡፡

፪. ማንኛውም የመንግስት መስሪያ ቤት የሥራ አካባቢው ለአካል ጉዳተኛ ሠራተኞቹ ምቹ መሆኑን ማረጋገጥ፣ ለሥራ የሚያስፈልጉ መሣሪያዎችንና ቁሳቁሶችን ማሟሊትና ስለአጠቃቀማቸው ያስተዳድራል ሥልጠና እንዲያገኙ ማድረግ አለበት፡፡

፫. ማንኛውም የመንግስት መስሪያ ቤት ለሚያስፈልገው የአካል ጉዳተኛ የሆነ የመንግስት ሠራተኛ ተገቢውን ድጋፍ ሊሰጥ የሚችል ረዳት እንዲመደብለት የማድረግ ሓላፊነት አለበት፡፡

፬. በሌሎች ሕጎች ለአካል ጉዳተኞች የተሰጡ መብቶች ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም ተግባራዊ ይሆናል፡፡

፺. አነስተኛ ብሔራዊ ተዋጽኦ ስላላቸው ብሔር፣ ብሔረሰብና ህዝቦች የሚጠበቁ የሥራ ሁኔታዎች

፩. በመንግስት መስሪያ ቤት ውስጥ የሚፈጸም የሠራተኛ ስምሪት የብሔር፣ ብሔረሰብና ህዝቦች ሚዛናዊ ተዋጽኦ ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት፡፡

፪. በመንግስት መስሪያ ቤቱ ውስጥ አነስተኛ ብሔራዊ ተዋፅኦ ያላቸው የብሔር፣ ብሔረሰብና ህዝቦች በቅጥር፣ በደረጃ ዕድገት፣ በዝውውር፣ በድልድል፣ በትምህርትና ሥልጠና አፈጻጸም የተጨማሪ ድጋፍ እርምጃ ተጠቃሚ መሆን አለባቸው፡፡

**፺፩. መመሪያ ስለማውጣት**

በዚህ ክፍል ለተመለከቱት የተጨማሪ የድጋፍ እርምጃዎች አፈጻጸም ቢሮው ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፡፡ ክፍል ስድስት የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት

**፺፪. አላማና ተፈጻሚነት**

፩. የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት አላማ፣

ሀ) የመንግሥት ሠራተኞችን ደህንነትና ጤንነት በመጠበቅ የሥራ ብቃትን ማጎልበት፣

ለ) የሥራ ቦታን ለመንግሥት ሠራተኞች ደህንነትና ጤንነት በሚስማማ መልኩ ማዘጋጀት፣ ማሻሻልና መጠበቅ፣ እና

ሐ) የመንግሥት መሥሪያ ቤት በጎ በሆነ ማህበራዊ ሕይወት ላይ ተመሥርቶ አመርቂ የሥራ ውጤት እንዲያስመዘግብ ማብቃት ይሆናል፡፡

፪. የዚህ ክፍል ድንጋጌዎች ለጊዜያዊ ሠራተኞችም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ስድስት

## በሥራ ላይ ስለሚደርስ ጉዳት

**፺፫. በሥራ ላይ ስለሚደርስ ጉዳት**

፩. “በሥራ ላይ የሚደርስ ጉዳት” ማለት በሥራ ላይ የሚደርስ አደጋ ወይም በሥራ ምክንያት የሚመጣ በሽታ ነው፡፡

፪. “በሥራ ላይ የሚደርስ አደጋ” ማለት የመንግስት ሠራተኛው መደበኛ ሥራውን በማከናወን ላይ እንዳለ ወይም ከሥራው ጋር በተያያዘ ምክንያት በአካለ ወይም በአካለ የተፈጥሮ ተግባር ላይ በድንገት የሚደርስ ጉዳት ሲሆን የሚከተለትን ይጨምራል፤

ሀ) የመንግሥት ሠራተኛው ከመደበኛ ሥራው፣የሥራ ቦታው ወይም የሥራ ሰዓቱ ውጭ ሥልጣኑ በሚፈቅድለት ሰው የተሰጠውን ትዕዛዝ በመፈጸም ላይ እያለ የደረሰን ጉዳት፤

ለ) ሥልጣኑ በሚፈቅድለት ሰው የተሰጠው ትዕዛዝ ባይኖርም የመንግሥት ሠራተኛው በመሥሪያ ቤቱ ውስጥ የደረሰን ድንገተኛ አደጋ ወይም ጥፋት ለመከላከል በሥራ ሰዓት ወይም ከሥራ ሰዓት ውጭ በሚፈጽመው ተግባር ምክንያት የደረሰን ጉዳት፤

ሐ) የመንግሥት ሠራተኛው ወደ ሥራ ቦታው ወይም ከሥራ ቦታው መሥሪያ ቤቱ ለሠራተኞች አገልግሎት እንዲሰጥ በመደበው የመጓጓዣ አገልግሎት ወይም መሥሪያ ቤቱ ለዚህ ተግባር በተከራየውና በግልጽ በመደበው የመጓጓዣ አገልግሎት በመጓዝ ላይ በነበረበት ጊዜ የደረሰን ጉዳት፤

መ) የመንግሥት ሠራተኛው ከሥራው ጋር በተያያዘ ተግባሩ ምክንያት ከሥራው በፊት ወይም በኋላ ወይም ሥራው ለጊዜው ተቋርጦ በነበረበት ጊዜ በሥራው ቦታ ወይም በመሥሪያ ቤቱ ግቢ ውስጥ በመገኘት የደረሰበትን ማንኛውንም ጉዳት፤

ሠ) የመንግሥት ሠራተኛው ሥራውን በማከናወን ላይ ባለበት ጊዜ በመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ወይም በሦስተኛ ወገን ድርጊት ምክንያት የደረሰበትን ጉዳት፡፡

፫. "በሥራ ምክንያት የሚመጣ በሽታ" ማለት የመንግሥት ሠራተኛው ከሚሠራው የሥራ ዓይነት ወይም ሥራውን ከሚያከናውንበት አካባቢ የተነሳ በሽታን ለሚያስከትሉ ሁኔታዎች ተጋልጦ በመቆየቱ ምክንያት የደረሰ የጤና መታወክ ሲሆን፣ ሥራውን በሚያከናውንበት ቦታ የሚዛመቱና የሚይዙ ነዋሪ ወይም ተሊሊፊ በሽታዎችን አይጨምርም፡፡

፬. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፫) የተመለከተው ቢኖርም በመደበኛ ሥራው ምክንያት ተሊሊፊ ወይም ነዋሪ በሽታዎችን በማጥፋት ላይ የተሰማራ የመንግስት ሠራተኛ በዚሁ በሽታ ከተያዘ በሥራ ምክንያት የመጣ በሽታ እንደያዘው ይቆጠራል፡፡

፭. በሥራ ላይ በሚደርስ ጉዳት ምክንያት የሚከሰት የአካል ጉዳት መጠን አግባብ ባለው የመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ይወሰናል፡፡

፮. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ቢኖርም ሠራተኛው ሆነ ይወክላል በተለይም በመሥሪያ ቤቱ አስቀድሞ በግልጽ የተሰጡትን የደህንነት መጠበቂያ መመሪያዎች በመጣስ ወይም በመጠጥ ወይም በአደንዛዥ ዕፅ ሰክሮ በሥራ ላይ በመገኘቱ የደረሰበት ጉዳት በሥራ ምክንያት እንደደረሰ ጉዳት አይቆጠርም፡፡ የአደጋ መከሊከያ እርምጃዎች ፩. ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት፣

ሀ) የሥራ ቦታው በሠራተኞች ደህንነትና ጤንነት ላይ አደጋ የማያስከትል መሆኑን ማረጋገጥ፣

ለ) የአደጋ መከሊከያ መሣሪያዎችንና ቁሳቁሶችን ለሠራተኞች የማቅረብና ስለአጠቃቀማቸው መመሪያ የመስጠት፣ ሓላፊነት አለበት፡፡

፪. ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ፣

ሀ) ደህንነትና ጤንነትን ለመጠበቅ የወጡ መመሪያዎችን የማክበር፣

ለ) የተሰጡትን የአደጋ መከሊከያ መሣሪያዎችንና ቁሳቁሳችን በአግባቡ የመጠቀም፣ እና

ሐ) አደጋ ሉያስከትለ የሚችለ ሁኔታዎች መኖራቸውን ሲገምት ለሚመለከተው የመሥሪያ ቤቱ ሓላፊ ወዱያውኑ የማሳወቅ፣ ግዴታ አለበት፡፡

፫. ቢሮው የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት የመጠበቂያና የመከሊከያ ዘዴዎችን ያጠናል፤ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ሥራ ላይ እንዱያውለት ሥልጠና ስለሚሰጥበት ሁኔታ ያመቻቻል፡፡

፬. ቢሮው በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ውስጥ የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት ተግባራዊ መሆኑን ይቆጣጠራል፤ የአደጋ መከሊከያ እርምጃዎችን በተመለከተ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

## ፺፫. የአካል ጉዳት

፩. “የአካል ጉዳት” ማለት የመሥራት ችልታ መቀነስን ወይም ማጣትን በሚያስከትል ሁኔታ በሥራ ላይ የሚደርስ ጉዳት ነው፡፡

፪. በሥራ ላይ የደረሰ የአካል ጉዳት ጊዜያዊ የአካል ጉዳት፣ ዘላቂ ከፊል የአካል ጉዳት፣ ዘላቂ ሙለ የአካል ጉዳት ወይም ሞትን የሚያስከትል ውጤት ይኖረዋል፡፡

## ፺፬. ጊዜያዊ የአካል ጉዳት

“ጊዜያዊ የአካል ጉዳት” ማለት ለተወሰነ ጊዜ በሙለ ወይም በከፊል የመሥራት ችልታን ማጣት ነው፡፡

## ፺፭. ዘላቂ ከፊል የአካል ጉዳት

“ዘላቂ ከፊል የአካል ጉዳት” ማለት የመሥራት ችልታ የሚቀንስ የማይድን በሥራ ላይ የሚደርስ ጉዳት ነው፡፡

## ፺፮. ዘላቂ ሙለ የአካል ጉዳት

“ዘላቂ ሙለ የአካል ጉዳት” ማለት ጉዳት የደረሰበትን የመንግሥት ሠራተኛ ማናቸውንም ደመወዝ የሚያስገኝ ሥራ ለመሥራት የሚከለክለው የማይድን በሥራ ላይ የሚደርስ ጉዳት ነው፡፡

## ፺፱. ከሥራ በመጣ ጉዳት ምክንያት የሚሰጥ ህክምና እና ፈቃድ

፩. በሥራው ምክንያት ጉዳት ለደረሰበት የመንግሥት ሠራተኛ በሀገር ውስጥ ለሚሰጡ ለሚከተለት የሕክምና አገልግልቶች የሚያስፈልገው ወጪ በመሥሪያ ቤቱ ይሸፈናል፤

ሀ) የጠቅላላና የልዩ ሕክምና እንዱሁም የቀድ ሕክምና ወጪዎች፤

ለ) የሆስፒታልና የመድኃኒት ወጪዎች፤

ሐ) የማንኛውም ያስተዳድራል ሰው ሰራሽ ምትክ ወይም ተጨማሪ አካልችና የአጥንት ጥገና ወጪዎች፡፡

፪. ጉዳት ለደረሰበት የመንግሥት ሠራተኛ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚሰጠው የህክምና አገልግሎት በግል የህክምና ተቋም እንዲሰጠው የሚደረገው አገልግልቱ በመንግሥት የሕክምና ተቋማት ሊሰጠው የማይችል ሲሆን ብቻ ነው፡፡

፫. በሥራ ምክንያት ጉዳት የደረሰበት ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ የጉዳቱ መጠን ታይቶ በህክምና ማስረጃ በሚገለጸው መሰረት ከጉዳቱ ድኖ ወደ ሥራው እስከሚመለስ ወይም በጉዳቱ ምክንያት ለዘለቄታ መሥራት የማይችል መሆኑ በሕክምና ማስረጃ እስከሚረጋገጥ ድረስ የሕመም ፈቃድ ከሙሉ ደመወዝ ጋር ይሰጠዋል፡፡ የመንግሥት ሠራተኛው ለዘለቄታው መሥራት ያለመቻለ በሕክምና ማስረጃ ከተረጋገጠ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፰ የተደነገጉት ጥቅሞች ይጠበቁለታል፡፡

፬. ሠራተኛው ሕክምናውን በአግባቡ ባለመከታተለ ወይም በሐኪም የተሰጠውን ትዕዛዝ ባለማክበሩ ሕክምናውን ያጓተተ እንደሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) መሠረት የሚሰጠው ሕክምና እና ፈቃድ ይቋረጥበታል፡፡

፭. ቢሮው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ስለተመለከተው የህክምና ወጪ አከፋፈል የአፈጻጸም መመሪያ ያወጣል፡፡

## ፰. የጉዳት ጡረታ አበል እና የጉዳት ዳረጎት

፩. ከሥራ በመጣ የአካል ጉዳት ምክንያት ዘላቂ ሙሉ ወይም ከፊል የመሥራት ችልታውን ያጣ ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ በመንግሥት ሠራተኞች የጡረታ ሕግ የተሰጡት መብቶችና ጥቅሞች ይጠበቁለታል፡፡

፪. ከባድ የአካል ወይም ከባድ የመልክ መበለሸትን ያስከተለ ጉዳት የመሥራት ችልታ ማጣትን ባያስከትልም ለጉዳት ካሣ አከፋፈልና ለሌሎች ጥቅማጥቅሞች አሰጣጥ ሲባል እንደ ዘላቂ ከፊል የአካል ጉዳት ይቆጠራል፡፡

፫. በመንግሥት ሠራተኞች የጡረታ ሕግ የተደነገገው የአካል ጉዳት መጠን አወሳሰን ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) አፈጻጸም ተግባራዊ ይሆናል፡፡

፬. የመንግሥት ሠራተኛ በደረሰበት ጉዳት ምክንያት የሞተ እንደሆነ፣ በመንግሥት ሠራተኞች የጡረታ ሕግ መሠረት የጡረታ አበል ለተተኪዎቹ ይከፈሊል፡፡

## ፰፩. ከግብር ነፃ ስለመሆን

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፰ መሠረት የሚደረግ ክፍያ ከግብር ነፃ ይሆናል፤ እንዲሁም በእዳ ምክንያት ሊያዝ ወይም ማቻቻያ ሊደረግ ወይም ባለመብቱ ሊያስተሊልፈው አይችልም፡፡

**፷፪. ከሦስተኛ ወገን ስለሚጠየቅ የካሣ ክፍያ**

፩. በሠራተኛው ላይ የደረሰው ጉዳት በሦስተኛ ወገን ጥፋት ምክንያት የደረሰ እንደሆነ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ በጉዳቱ ምክንያት ለሠራተኛው ባወጣው ወጪ መጠን ጉዳቱን ካደረሰው ወገን ካሣ የመጠየቅ መብት ይኖረዋል፡፡

፪. ሠራተኛው ጉዳቱን ካደረሰበት ወገን ካሣ የተቀበለ እንደሆነ መሥሪያ ቤቱ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፱(፩) እና (፫) መሠረት ያወጣውን ወጪ ከሠራተኛው ደመወዝ ላይ ይቀንሳል፤ ሠራተኛው የተቀበለው የካሣ መጠን መሥሪያ ቤቱ ካወጣው ወጪ ያነሰ ከሆነ ልዩነቱን መሥሪያ ቤቱ ከሦስተኛው ወገን መጠየቅ ይችላል ፡፡

**ክፍል ሰባት**

**የመንግሥት ሠራተኞች የመረጃ አያያዝ**

**፷፫. የግል ማኅደር**

፩. ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት እና ቢሮው ስለእያንዳንዱ የመንግሥት ሠራተኛ ወይም ጊዜያዊ ሠራተኛ አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች በዘመናዊ ሁኔታ አደራጅተው ይይዛሉ፡፡

፪. ቢሮው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚልኩለት የሰው ሀብት መረጃዎች ይህን አዋጅና አዋጁን ለማስፈጸም የወጡ መመሪያዎችን የተከተለ መሆናቸውን በማረጋገጥ ይመዘግባል፡፡

፫. ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ በግል ማህደሩ ውስጥ የሚገኙትን ማስረጃዎች የመመልከት ወይም ቅጂውን የመውሰድ መብት አለው፡፡

፬. ከሚመለከታቸው የአስተዳደር ሠራተኞች በስተቀር፣ ያለሠራተኛው ስምምነት፣ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ወይም በሕግ በተደነገገው መሠረት ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም ሰው የመንግሥት ሠራተኛውን የግል ማህደር ማየት አይችልም፡፡

፭. የመንግሥት ሠራተኛው እንዲያውቀው ያልተደረገ ወይም ያልተገለጸለትን የጽሁፍ ማስረጃ በግል ማህደሩ ውስጥ ማስቀመጥ ክልክል ነው፡፡

**፷፬. የመንግሥት ሠራተኞችን መረጃ የማደራጀት ሓላፊነት**

፩. ቢሮው፣

ሀ) በከተማ አቀፍ ደረጃ የሰው ሀብት ሥራ አመራር መረጃ ሥርዓት በወጥነት እንዲተገበር የማድረግ፣

ለ) በአስተዳደሩ ውስጥ የሚገኙ የመንግሥት ሠራተኞችን መረጃ ቋት የማደራጀት፣

ሐ) የመንግሥት ሠራተኞችን የሚመለከቱ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን የመሰብሰብ፣ የማጠናቀር እና የማሰራጨት ሓላፊነት አለበት፡፡

፪. ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት በቢሮው ለሚደራጀው የሰው ሀብት መረጃ ቋት መረጃዎችን ወቅቱን ጠብቆ የመሊክ ግዴታ አለበት፡፡

፫. ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት የእያንዳንዱን ሠራተኛ መረጃ ለቢሮው መሊክ አለበት፡፡

## ክፍል ስምንት

## መብቶችና ግዴታዎች

### ፷፭. የመንግስት መሥሪያ ቤቶች ሓላፊነት

በዚህ አዋጅ በሌሎች ድንጋጌዎች የተመለከቱት ኃላፊነቶች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት የሚከተለት ኃላፊነቶች ይኖሩታል፤

፩. የመንግስት ሠራተኞች በመንግስት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ሕጎች ላይ በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው የማድረግ፤

፪. የመሥሪያ ቤቱ የሥራ አካባቢ ከማንኛውም ዓይነት ኃይማኖታዊ ተግባራት ነጻ መሆኑን የማረጋገጥ፤

፫. ለእያንዳንዱ የመንግሥት ሠራተኛ የሥራ ዝርዝር መግለጫ የመስጠትና በሥራ ዕቅድ ላይ ተመሥርቶ የሠራተኛውን የሥራ አፈጻጸም ውጤት የመለካት፤

፬. ለመንግሥት ሠራተኞች ለሥራ የሚያስፈልጓቸውን መሣያዎች የማቅረብና አጠቃቀማቸውን የማሳወቅ፤

፭. የሥራ አካባቢውን ለመንግሥት ሠራተኞች ጤንነትና ደህንነት አመቺ የማድረግ፡፡

### ፷፮. የመንግሥት ሠራተኞች ግዴታዎች

ማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ የሚከተለት ግዴታዎች ይኖሩበታል፤

፩. ለሕዝብና ለሕገ መንግሥቱ ታማኝ መሆንና የሕግ የበላይነትን የማክበር፤

፪. መንግሥት የሚያወጣቸውን ሕጎችና ፖሊሲዎችን በብቃት የመፈጸም፤

፫. በማናቸውም ሁኔታ ሕዝብንና ሀገርን ያለአድልዎ የማገልገል፤

፬. መሊ ዕውቀቱንና ችሎታውን ለሕዝብ አገልግሎት የማዋል፤

፭. በሥራ ዝርዝሩ የተመለከቱትንና በቅርብ ሓላፊው የሚሰጠውን ሕጋዊ ትዕዛዝ የመፈጸም፤

፮. በማናቸውም ሁኔታ በሥራ ቦታ ላይ የግል እምነቱን ወይም ኃይማኖቱን የሚያንጸባርቅ ተግባር አለመፈጸም፤ ፮. ምስጢር ተብለው የተለዩና በሥራው አጋጣሚ ያወቃቸውን የመሥሪያ ቤቱን ምስጢሮች የመጠበቅ፤

፰. በተገልጋዮች መካከል በፆታ፣ በቋንቋ፣ በዘር፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ አመለካከት፣ በአካል ጉዳት ወይም በሌሎች ልዩነት በሚፈጥሩ ሁኔታዎች መድል ያለመፈጸም፤

፱. ለመስሪያ ቤቱ የሚሰጠውን አገልግሎት የሚያጓድል ወይም በማናቸውም አኳኋን ከተመደበበት ሥራ ጋር የሚቃረን ወይም ከመንግስት ሠራተኝነቱ ጋር የማይጣጣም ማናቸውንም ሌላ ሥራ ያለመስራት፤

፲. ሥራውን ለፖለቲካ ጥቅሙ ያለማዋልና በዚህም ምክንያት አድል ያለመፈጸም፤

፲፩. በመንግስት ሠራተኝነቱ ለሰጠው ወይም እንዲሰጥ ለሚጠበቀው አገልግሎት ማንኛውንም ዓይነት ስጦታ ወይም ዋጋ ያላቸው ነገሮች ያለመጠየቅ ወይም ያለመቀበል፤

፲፪. ለሥራ ማከናወኛ የተሰጡትን መሣሪያዎችና መገልገያዎች በአግባቡ የመጠቀምና የመጠበቅ፤ ፲፫. ከኤች አይ ቪ/ኤድስ በስተቀር ከሥራው ጋራ በተያያዘ በበቂ ምክንያት የህክምና ምርመራ እንዲያደርግ በመንግስት መሥሪያ ቤቱ ሲጠየቅ ለምርመራ የመቅረብ፤

፲፬. ስለሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት ጥበቃ የወጡ መመሪያዎችን የማክበር፡፡

፷፯. በእዳ የመጠየቅ ሓላፊነት

ማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ ለሥራው ማከናወኛ በተሰጡት መሣሪያዎችና መገልገያዎች ላይ በሚደርስ ጉዳት ወይም ጥፋት በዕዳ ተጠያቂ የሚሆነው ጉዳቱ ወይም ጥፋቱ በሠራተኛው ቸልተኝነት ወይም ሆነ ተወካይ በተፈፀመ ድርጊት ምክንያት የደረሰ እንደሆነ ነው፡፡

## ክፍል ዘጠኝ

## የዲስፕሊን እርምጃዎች እና የቅሬታ አፈታት

## ንኡስ ክፍል አንድ የዲስፕሊን እርምጃዎች

### ፷፰. የዲስፕሊን ቅጣት ዓላማ

የዲስፕሊን ቅጣት ዓላማ የመንግሥት ሠራተኛው በፈጸመው የዲስፕሊን ጉድለት ተፀፅቶ በአመለካከቱና በሥነምግባሩ እንዲታረምና ብቁ ሠራተኛ እንዲሆን ለማስቻል ወይም የማይታረም ሆኖ ሲገኝ ለማሰናበት ነው፡፡

### ፷፱. የዲስፕሊን ቅጣት ዓይነቶችና አመዳደብ

፩. የዲስፕሊን ጉድለት የፈጸመ የመንግሥት ሠራተኛ እንደጥፋቱ ክብደት ከሚከተለት ቅጣቶች አንደ ሊወሰንበት ይችላል ፤

ሀ) የቃል ማስጠንቀቂያ፤

ለ) የጽሐፍ ማስጠንቀቂያ፤

ሐ) እስከ አሥራ አምስት ቀን ደመወዝ የሚደርስ መቀጮ፤

መ) እስከ ሦስት ወር ደመወዝ የሚደርስ መቀጮ፤

ሠ) እስከ ሁለት ዓመት ለሚደርስ ጊዜ በሥራ ደረጃ እና ደመወዝ ዝቅ ማድረግ፤

ረ) ከሥራ ማሰናበት፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)(ሀ) እስከ (ሐ) የተዘረዘሩት ቅጣቶች ቀላል ቅጣቶች ተብለው ይመደባሉ፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)(መ) እስከ (ረ) የተዘረዘሩት ቅጣቶች ከባድ የዲስፕሊን ቅጣቶች ተብለው ይመደባል፡፡

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)(ሠ) መሠረት ከሥራ ደረጃና ደመወዝ ዝቅ በማድረግ የተቀጣ የመንግሥት ሠራተኛ የቅጣት ጊዜውን ሲያጠናቅቅ፣

ሀ) ከመቀጣቱ በፊት ይዞት ከነበረው የሥራ መደብ ጋር ተመሳሳይ ክፍት የሥራ መደብ ካለ ያለምንም ተጨማሪ የደረጃ ዕድገት ሥነ-ሥርዓት፣

ለ) ከመቀጣቱ በፊት ይዞት ከነበረው የሥራ መደብ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ክፍት የሥራ መደብ ካልተገኘ ክፍት የሥራ መደቡ በተገኘ ጊዜ ያለምንም ተጨማሪ የደረጃ ዕድገት ሥነ-ሥርዓት፣ በሥራ መደቡ ላይ እንዲመደብ ይደረጋል፡፡ ፭. አንድ የመንግሥት ሠራተኛ በዲስፕሊን ከተቀጣ በኋላ ቅጣቱ በሪከርድነት ሊቆይና ሊጠቀስበት የሚችለው፣

ሀ) ቀላል የዲስፕሊን ቅጣት ከሆነ ቅጣቱ ከተወሰነበት ቀን ጀምሮ ለሁለት ዓመት፤

ለ) ከባድ የዲስፕሊን ቅጣት ከሆነ ቅጣቱ ከተወሰነበት ቀን ጀምሮ ለአምስት ዓመት፤ ይሆናል፡፡

<u>፸. ከባድ የዲስፕሊን ቅጣት የሚያስከትሉ ጥፋቶች</u>

የሚከተሉት ጥፋቶች ከባድ የዲስፕሊን ቅጣት የሚያስከትሉ ጥፋቶች ናቸው፤

፩. ሕጋዊ ትእዛዝን ባለማክበር፣ በቸልተኝነት፣ በመለገም፣ ወይም ሆነ ይወክላል የአሠራር ሥነ-ሥርዓት ወይም የመንግስትንፖሊሲባለመከተልበሥራሊ ይ በደል ማድረስ፤

፪. ጉዳዮችን ሆን ይወክላል ማዘግየት ወይም ባለጉዳዮችን ማጉሊሊት፤

፫. ሥራ እንዲይሠራ ሆን ይወክላል ማወክ ወይም ከሚያውኩት ጋር መተባበር፤

፬. በቀላል የዲስፕሊን ቅጣት እርምጃዎች ባለመታረም ያለበቂ ምክንያት በተደጋጋሚ ከሥራ መቅረት ወይም የሥራ ሰዓት አለማክበር፤

፭. በሥራ ቦታ በጠብ አጫሪነት መደባደብ፤

፮. በልማዳዊ ስካር ወይም በአደንዛዥ ዕፅ ሱስ በመመረዝ ሥራን መበደል፤

፯. ጉቦ መቀበል ወይም እንዲሰጠው መጠየቅ፤

፰. በሥራ ቦታ ለሕዝብ ሞራል ተቃራኒ የሆነ ድርጊት መፈጸም፤

፱. የላብነት ወይም የእምነት ማጉደል ድርጊት መፈጸም፤

፲. የማታለል ወይም የማጭበርበር ድርጊት መፈጸም፤

፲፩. በመሥሪያ ቤቱ ንብረት ላይ ሆን ይወክላል ወይም በቸልተኝነት ጉዳት ማድረስ፤

፲፪. በሥልጣን አለአግባብ መጠቀም፤

፲፫. በሥራ ቦታ ላይ ያታዊ ትንኮሳ ወይም ጥቃት መፈፀም፤

፲፬. በዚህ አንቀጽ ከተዘረዘሩት ጋር ተመሳሳይ ክብደት ያለው ሌላ የዲስፕሊን ጉድለት መፈጸም፡፡

**<u>፸፩. የዲስፕሊን እርምጃ አወሳሰድ</u>**

፩. ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት መደበኛ የዲስፕሊን ምርመራ የሚያካሂድና የውሳኔ ሀሳብ ለመሥሪያ ቤቱ የበላይ ሓላፊ የሚያቀርብ የዲስፕሊን ኮሚቴ ማቋቋም አለበት፡፡

፪. የዲስፕሊን ቅጣት የማንኛውንም ፍርድ ቤት ውሳኔ ሳይጠብቅ ወይም ሳይከተል ሊወሰን ይችላል ፡፡

**<u>፸፪. ሠራተኛን ከሥራና ከደመወዝ አግድ ስለማቆየት</u>**

፩. ማንኛውንም የመንግሥት ሠራተኛ ከሥራና ከደመወዝ አግድ ማቆየት የሚቻለው፣

ሀ) ከተጠረጠረበት ጉዳይ ጋር አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎች በማበሊሸት፣ በመደበቅ ወይም በማጥፋት ምርመራውን ያሰናክሊል፤

ለ) በመንግሥት ንብረት ላይ ተጨማሪ ጉዳት ያደርሳል፤

ሐ) ከተከሰሰበት ጥፋት ክብደት አንጻር የሌሎችን ሠራተኞች ሞራል የሚነካ ወይም የተገልጋዩ ሕዝብ በመሥሪያ ቤቱ ላይ ሉኖረው የሚገባውን እምነት ያዛባል፤ወይም

መ) ተፈጸመ የሚባለው ጥፋት ከሥራ ያስወጣል፤ተይወክላል ሲገመት ነው፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት አንድ ሠራተኛ ከሥራና ከደመወዝ ታግድ ሊቆይ የሚችለው ከሁለት ወር ለማይበልጥ ጊዜ ይሆናል፡፡ ፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ

(፪) መሠረት ከሥራና ከደመወዝ ታግድ እንዲቆይ የሚደረግ የመንግሥት ሠራተኛ ከመደበኛ ሥራው ታግድ የሚቆይበት ጊዜና ከሥራ የታገደበት ምክንያት በመሥሪያ ቤቱ የበላይ ሓላፊ ወይም በተወካዩ በጽሐፍ እንዱገለጽለትና ቢሮው በግልባጭ እንዱያውቀው ይደረጋል፡፡

፬. የመንግሥት ሠራተኛው በተከሰሰበት የዲስፕሊን ጥፋት ምክንያት ከሥራ እንዱሰናበት ካልተወሰነበት በስተቀር በእግደ ወቅት ሳይከፈለው የቀረው ደመወዝ ያለወለድ ይከፈለዋል፡፡

፭. የመንግሥት ሠራተኛው ከሥራ በመታገዱ ምክንያት ከዕግድ ጋር ያልተያያዙ ሌሎች መብቶቹንና ግዴታዎቹን ተፈጻሚነት አያስቀርም፡፡

፮. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ ቢኖርም ከሥራና ደመወዝ ታግድ የቆየ ሠራተኛ ከሥራ እንዱሰናበት ወይም በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት ደመወዙ እንዱከፈለውና ወደ ሥራው እንዱመለስ ሳይደረግ የዕግድ ጊዜ ካበቃ፣

ሀ) የመዘግየቱ ምክንያት የዲስፕሊን ክሱን የማጣራቱ ሂደት ውስብስብነት ከሆነ የመንግሥት ሠራተኛው ግማሽ ደመወዙ እየተከፈለው፣ ወይም

ለ) ለመዘግየቱ ምክንያት የሆነው የመንግሥት ሠራተኛው ራሱ ከሆነ ያለደመወዝ ክፍያ፣ እግደ እስከ አንድ  ወር ድረስ እንዲራዘም የመሥሪያ ቤቱ የበላይ ሓላፊ ሊወስን ይችላል ፡፡

፯. ከሥራና ደመወዝ ታግድ የቆየ የመንግሥት ሠራተኛ ከሥራ እንዲሰናበት ወይም በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት ደመወዙ እንዲከፈለውና ወደ ሥራው እንዲመለስ ሳይደረግ መደበኛውም ሆነ የተራዘመው የዕግድ ጊዜ ከተጠናቀቀ የሥራና የደመወዝ እግደ ተነስቶ የዲስፐሊን ክሱ መታየት ይቀጥሊል፤ ሆኖም ለመዘግየቱ ምክንያት የሆኑ የኮሚቴ አባሊትና የሥራ ሓላፊዎች በዲስፐሊን ጥፋት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

**<u>፸፫. የይርጋ ጊዜ</u>**

፩. ቀላል የዲስፐሊን ቅጣት የሚያስከትል ጥፋት የፈፀመ የመንግሥት ሠራተኛ የፈጸመው ጥፋት ከታወቀበት ቀን ጀምሮ እስከ ስድስት ወር እርምጃ ካልተወሰደበት በዲስፐሊን ተጠያቂ አይሆንም፤ ሆኖም በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ እርምጃ ያልወሰደው የሥራ ሓላፊ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

፪. በወንጀል ጭምር የሚያስጠይቅ ከባድ የዲስፐሊን ቅጣት የሚያስከትል ጥፋት የፈጸመ የመንግሥት ሠራተኛ የወንጀለን ክስ ለማቅረብ በወንጀል ሕጉ በተቀመጠው የይርጋ ጊዜ ውስጥ በዲስፐሊን ካልተከሰሰ በጥፋቱ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

፫. በወንጀል የማያስጠይቅ ከባድ የዲስፐሊን ቅጣት የሚያስከትል ጥፋት የፈጸመ የመንግሥት ሠራተኛ የደንብ መተሊለፍ ክስን ለማቅረብ በወንጀል ሕጉ  በተደነገገው የይርጋ ጊዜ ውስጥ በዲስፐሊን ካልተከሰሰ በጥፋቱ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

፬. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፪) እና (፫) የተደነገጉት የዲስፐሊን ክስ ማቅረቢያ የይርጋ ጊዜያት ቢኖሩም የዲስፐሊን ክስ ለማቅረብ ሓላፊነት ያለበት የሚመለከተው የሥራ ሓላፊ ጥፋት መፈጸሙን ካወቀበት ቀን ጀምሮ በስድስት ወር ውስጥ ክሱን ካሊቀረበ በዲስፐሊን ጥፋት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

፭. ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ ከገንዘብ ጋር የተያያዙ መብቶቹን ለሚመለከተው አካል በስድስት ወር ውስጥ ካሊቀረበ በይርጋ ይታገዳል፡፡

## <u>ንኡስ ክፍል ሁለት</u>

## <u>የቅሬታ አቀራረብና አፈታት</u>

**<u>፸፬. ቅሬታ</u>**

ለዚህ ንኡስ ክፍል አፈጻጸም “ቅሬታ” ማለት የመንግስት ሠራተኛ ከቅርብ ሓላፊው ወይም ከሚመለከተው የሥራ ሓላፊ ጋር በሚደረግ ውይይት ሉፈታ ያልቻለና በመደበኛ የማጣራት ሂደት ምሊሽ ሉያገኝ የሚገባው አቤቱታ ነው፡፡

**፸፩. የቅሬታ አቀራረብና አፈታት አላማ**

የመንግሥት ሠራተኞች ቅሬታ አቀራረብና አፈታት የሚከተለት አላማዎች ይኖሩታል፤

፩. ለቅሬታዎች አፋጣኝ መፍትሔ የመስጠት፤

፪. ለቅሬታዎች መንስዔ ሊሆኑ የሚችለ ስህተቶችንና ድክመቶችን የማረም፤ እና

፫. ሁለንም የመንግሥት ሠራተኞች በእኩልነት ለማስተናገድ የሚያስችል እና ፍትሐዊ የሆነ አሠራር በማስፈን የሰመረ የሥራ ግንኙነት የማዳበር፡፡

**፸፪. የቅሬታ አጣሪ ኮሚቴ ማቋቋም**

ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት የመንግሥት ሠራተኞች የሚያቀርቡትን ቅሬታ እየተቀበለ በማጣራት የውሳኔ ሀሳብ ለመሥሪያ ቤቱ የበላይ ሓላፊ የሚያቀርብ የቅሬታ አጣሪ ኮሚቴ ማቋቋም አለበት፡፡

**፸፫. የቅሬታ አጣሪ ኮሚቴው ተግባር**

የቅሬታ አጣሪ ኮሚቴ ከሚከተለት ጋር በተያያዘ የመንግሥት ሠራተኛው የሚያቀርባቸውን ቅሬታዎች እያጣራ የውሣኔ ሀሣብ የማቅረብ ሓላፊነት አለበት፤

፩. ከሕጎችና መመሪያዎች አተረጓጎም ወይም አፈጻጸም፤

፪. ከመብቶችና ጥቅሞች አጠባበቅ፤

፫. ከሥራ አካባቢ ጤንነትና ደህንነት ሁኔታዎች፤

፬. ከሥራ ምደባና ደረጃ አሰጣጥ፤

፭. ከሥራ አፈጻጸም ምዘና፤

፮. በሥራ ሓላፊ ከሚፈጸሙ ተገቢ ያልሆኑ ተፅዕኖዎች፤

፯. በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፱ ንዑስ አንቀጽ (፩)(ሀ) እና (ለ) በተመለከቱ መሠረት ከሚወሰደ የዲስፕሊን እርምጃዎች፤

፰. የሥራ ሁኔታዎችን ከሚመለከቱ ሌሎች ጉዳዮች፡፡

**፸፰. አስተዳደራዊ ውሳኔ**

፩. "አስተዳደራዊ ውሳኔ" ማለት የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ሓላፊ በዚህ ክፍል የተደነገጉትን ጉዳዮች በሚመለከት በቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ወይም በዲስፕሊን ኮሚቴ ተጣርተው በቀረቡ ጉዳዮች ወይም በቀጥታ በሕግ በተሰጡት ሌሎች ጉዳዮች ላይ በጽሁፍ የሚሰጠው ውሳኔ ነው፡፡

፪. የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም የመንግስት መስሪያ ቤቱ የበላይ ሓላፊ ሥነ-ሥርዓቱን ሳይጠብቅም ሆነ በቃል የሚሰጠው ውሳኔ ለሰራተኛው ፍትህ የማግኘት መብት ለማረጋገጥ ሲባል ሰራተኛው በቃለ መሃላ ካረጋገጠ እንደ አስተዳደር ውሳኔ ይቆጠራል፡፡

## ክፍል አስር

## የመንግሥት ሠራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤት

**፹፱. መቋቋም**

፩. የመንግሥት ሠራተኞች በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፺፩ መሰረት የሚያቀርቡትን የስራ ክርክር አይቶ የሚወስን አስተዳደር ፍርድ ቤት (ከዚህ በኋላ“ የአስተዳደር ፍርድ ቤት” እየተባለ የሚጠራ ) በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

፪. የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ የሚቀርቡለትን ይግባኞች መርምረው ውሳኔ የሚሰጡ ችሎቶች ይኖሩታል፡፡

፫. እያንዳንዱ ችሎት በቢሮው የሚሰየሙ አንድ ሰብሳቢና ሁለት አባላት ያሉት ዳኞች ይኖሩታል፡፡

፬. የአስተዳደር ፍርድ ቤት ዳኞች ሥራቸውን ስለሚሠሩበት ሁኔታ፣ መጠበቅ ስለሚገባቸው ሥነ-ምግባር፣ እና ሌሎች ሁኔታዎች በቢሮው በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፡፡ ፺. የአስተዳደር ፍርድ ቤት ሥልጣንና አሠራር

፩. የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ፣

ሀ) የሚቀርቡለትን ጉዳዮች በዳኝነት የማየትና ትዕዛዝና ውሳኔ የመስጠት፣

ለ) የመንግሥት ሠራተኛ ውሳኔ ተሰጥቷል ይወክላል በቃለ መሃሊ አስደግፎ የሚያቀርበውን ይግባኝ ተቀይወክላል የማየት፣ የዳኝነት ስልጣን ይኖረዋል፡፡

፪. አስተዳደር ፍርድ ቤቱ የሚሰጣቸው ትዕዛዞችና ውሳኔዎች እንደ ማናቸውም የፍትሐብሔር ፍርድ ቤት ትዕዛዞችና ውሳኔዎች ይቆጠራሉ፡፡

**፺፩. በአስተዳደር ፍርድ ቤት ስለሚታዩ ጉዳዮች**

የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ የሚከተሉትን ጉዳዮች አይቶ የመወሰን ሥልጣን ይኖረዋል፤

፩. ከሚከተሉት ጋር በተያያዘ በመንግሥት ሠራተኞች የሚቀርቡለትን ይግባኞች፤

ሀ) ከሕግ ውጪ ከሥራ መታገድ ወይም አገልግሎት መቋረጥ፤

ለ) ከከባድ የዲስፕሊን ቅጣት ውሳኔ፤

ሐ) ከሕግ ውጪ የደመወዝ ወይም ሌሎች ክፍያዎች መያዝ ወይም መቆረጥ፤

መ) በሥራ ምክንያት ከደረሰ ጉዳት የመነጨ መብት መጓደል፤

ሠ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፹፯(፯) ከተመለከተው በስተቀር በቅሬታ አጣሪ ኮሚቴ ታይተው ውሳኔ ከተሰጠባቸው ጉዳዮች፤

ረ) የሥራ መልቀቂያና የአገልግሎት ማስረጃ ለማግኘት ከቀረበ ጥያቄ፤

፪. ጊዜያዊ ሠራተኞችና በማቋቋሚያ ሕጋቸው የመንግስት ሠራተኞች ሕግ መሠረታዊ አላማዎችን በመከተል በራሳቸው የውስጥ መመሪያ ሠራተኞቻቸውን እንዲያስተዳድሩ የተፈቀደሊቸው መሥሪያ ቤቶች ውስጥ ተቀጥረው የሚሰሩ ሠራተኞች የሚያቀርቧቸውን ይግባኞች፡፡

፫. የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ይግባኝ የተባለበትን አስተዳደራዊ ውሳኔ ከመረመረ በኋላ ውሳኔውን ለማጽናት፣ ለመሻር ወይም ለማሻሻል ይችላል ፡፡

፬. የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ውሳኔ በሰጠ በአምስት የስራ ቀናት ውስጥ የውሳኔን ግልባጭ ለይግባኝ ባዩ ወይም ለመስሪያ ቤቱ ተወካይ እንዲደርሰው ማድረግ አለበት፡፡

፭. የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ በፍሬ ነገር ክርክር የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፤ ሆኖም የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ውሳኔ የሕግ ስህተት አለበት ይወክላል የሚከራከር ወገን የፍርድ ቤቱ ውሳኔ በደረሰው በ፷ ቀን ውስጥ ይግባኙን ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡

## ፹፪. የውሳኔ አፈጻጸም

፩. ማንኛውም የመንግስት መስሪያ ቤት የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ የሰጠውን ውሳኔ በደረሰው በአስር የስራ ቀናት ውስጥ መፈጸም አለበት፡፡

፪. በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፹፩(፫) እና (፬) መሠረት ፍርድ ቤቱ የሰጠው ውሳኔ እስከ ፴ ቀን ድረስ አልተፈጸመልኝም በማለት የውሳኔው ተጠቃሚ ሲያመለክት የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ውሳኔውን እንዲያስፈጽምለት ለአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ይመራለታል፡፡

፫. የአስተዳደር ፍርድ ቤቱን ውሳኔ ያሊስፈጸመው የመስሪያ ቤቱ የበላይ ሓላፊ በመስሪያ ቤቱና በሠራተኛው ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## ክፍል አስራ አንድ

## የሥራ ውል ማቋረጥና ማራዘም

## ፹፫. በራስ ፈቃድ የሥራ ውል ስለማቋረጥ

፩. ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ በማንኛውም ጊዜ የአንድ ወር ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ሥራውን በፈቃደ ሊለቅ ይችላል ፤ ሆኖም መስሪያ ቤቱ ሠራተኛውን በቀሊለ ሉተካው የሚችል ከሆነ የአንድ ወሩን ጊዜ ሳይጠብቅ ስንብቱን ሉፈቅድለት ይችላል ፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተውን የአንድ ወር የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ሳይሰጥ አገልግልቱን ያቋረጠ የመንግሥት ሠራተኛ ግዴታው ባለመወጣቱ ለሚደርሰው ጉዳት እንደተገቢነቱ በፍትሐ ብሔር እና በወንጀል ሕግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

፫. የመንግሥት ሠራተኛው ለሥራው እጅግ ያስተዳድራልና በቀሊለ ለመተካት የማይቻል ሆኖ ሲገኝ ወደ ፊት ከሚቀጠርበት መስሪያ ቤት ጋር በመስማማት የመልቀቂያውን ጥያቄ ሠራተኛው ካመለከተበት ቀን ጀምሮ ከሦስት ወር ለማይበልጥ ጊዜ ሉራዘም ይችላል ፡፡

**፹፬. በሕመም ምክንያት አገልግሎት ስለማቋረጥ**

፩. ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፫(፪) ወይም (፬) በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ወደ ሥራ ለመመለስ ካልቻለ በሕመም ምክንያት አገልግሎቱ ይቋረጣል፡፡

፪. የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፱(፫) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በሥራው ምክንያት ጉዳት የደረሰበት የመንግሥት ሠራተኛ ለዘለቄታው መሥራት አለመቻለ በሕክምና ማስረጃ ሲረጋገጥ አገልግሎቱ ይቋረጣል፡፡

፫. በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፮ ንዑስ አንቀጽ (፫) (ለ) መሠረት በሚፈጸመው ዝውውር ተስማምቶ ለመስራት ፈቃደኛ ያልሆነ የመንግሥት ሠራተኛ አገልግሎቱ ይቋረጣል፡፡

**፹፭. በችሎታ ማነስ ምክንያት ከሥራ ማሰናበት**

፩. የሙከራው ጊዜውን ያጠናቀቀ የመንግስት ሠራተኛ በሥራ አፈጻጸም ውጤቱ የችሎታ ማነስ ከታየበት ተገቢው የአቅም ማጎልበት ሥልጠናዎች ተሰጥተውት ካልተሻሻለ አገልግሎቱ ይቋረጣል፡፡

፪. የመንግሥት ሠራተኛ ያለውን ዕውቀትና ችሎታ እየተጠቀመ በተመደበበት ሥራ ላይ የሥራ አፈጻጸም ውጤቱ በተከታታይ ለሶስት ጊዜ ከሚጠበቀው ውጤት በታች ከሆነ በችሎታ ማነስ አገልግሎቱ ይቋረጣል፡፡

፫. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ ቢኖርም ለተከታታይ አምስት ዓመታት ከፍተኛ የሥራ አፈጻጸም ምዘና ውጤት ሲያገኝ የነበረ የመንግሥት ሠራተኛ የሥራ አፈጻጸም ምዘና ውጤቱ በተከታታይ ለአራት ጊዜ ከሚጠበቀው ውጤት በታች ካልሆነ በስተቀር ከሥራ አይሰናበትም፡፡

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) መሠረት የመንግሥት ሠራተኛውን ከሥራ ማሰናበት የሚቻለው እንደአስፈላጊነቱ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፩ ላይ የተቀመጠውን የሥራ አፈጻጸም ምዘና አላማ በመከተል ይሆናል፡፡

**፹፮. ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ከሥራ ማሰናበት**

፩. የሙከራ ጊዜውን ያጠናቀቀ የመንግሥት ሠራተኛ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት በሥራ ገበታው ላይ ካልተገኘ ምክንያቱን በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለመሥሪያ ቤቱ ማሳወቅ አለበት፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ሪፖርት የተደረገለት የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ሓላፊ ወይም ተወካዩ ሠራተኛው ከሥራ ገበታው ላይ የተለየበት ምክንያት ከአቅም በላይ መሆኑን ካረጋገጠ የመንግሥት ሠራተኛው ይዞት የነበረውን የሥራ መደብ ለስድስት ወር ክፍት አድርጎ መጠበቅ አለበት፡፡ ሆኖም የመንግሥት ሠራተኛው በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ወደ ሥራው ካልተመለሰ ከሥራ ማሰናበት ይቻላል፡፡

፫. የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ ቢኖርም የመንግስት ሰራተኛው ከስድስት ወር በላይ በሥራ ላይ ያልተገኘው በእስር ምክንያት ከሆነና ከተጠረጠረበት የወንጀል ድርጊት በነፃ ስለመለቀቁ ማስረጃ ካቀረበ የመንግስት መስሪያ ቤቱ ባለው ክፍት የሥራ መደብ ቀደም ሲል ይከፈለው የነበረውን ደመወዝ እያገኘ ወደ ሥራ እንዲመለስ ማድረግ አለበት፡፡

፬. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የሙከራ ጊዜውን ያጠናቀቀ የመንግሥት ሠራተኛ ባልታወቀ ምክንያት ለተከታታይ አሥር ቀናት ከመደበኛ የሥራ ቦታው ላይ ከተለየ በየአስር ቀናት ልዩነት በተከታታይ ለሁለት ጊዜ በማስታወቂያ ተጠርቶ ለመንግስት መሥሪያ ቤቱ ሪፖርት ካሊደረገ ከሥራ ይሰናበታል፡፡

፭. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት በማስታወቂያ ጥሪ የተደረገለት የመንግሥት ሠራተኛ ከሥራ ከተለየበት ቀን ጀምሮ አንድ ወር ከመሙሊቱ በፊት ወደ ሥራው ለመመለስ ለመንግስት መሥሪያ ቤቱ ሪፖርት ካደረገ የመሥሪያ ቤቱ የበላይ ሓላፊ ሠራተኛው ከሥራ የቀረበትን ምክንያት በመመርመር የሚወስደው አስተዳደራዊ እርምጃ እንደተጠበቀ ሆኖ ወደ ሥራው እንዲመለስ ይደረጋል፡፡

፮. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) ቢኖርም ከስራ የተሰናበተ ሰራተኛ ከሥራ ከቀረበት ቀን ጀምሮ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ከሥራ የቀረበት ምክንያት ከአቅም በላይ ለመሆኑ ለመሥሪያ ቤቱ ሪፖርት ካደረገና በቂ ማስረጃ ካቀረበ በመሥሪያ ቤቱ ውስጥ ተመሳሳይ የሆነ ክፍት የሥራ መደብ ከተገኘ የመሥሪያ ቤቱ የበላይ ሓላፊ ወይም ተወካዩ ሲፈቅድ ወደ ሥራ ሊመለስ ይችላል ፡

፯. የሙከራ ጊዜውን ያሊጠናቀቀ የመንግሥት ሠራተኛ ባልታወቀ ምክንያት ለአንድ ወር ጊዜ በሥራ ገበታው ላይ ካልተገኘ ያለተጨማሪ ሥነ-ሥርዓት አገልግሎቱ ይቋረጣል፡፡

<u>፯. የሠራተኛ ቅነሳ</u>

፩. ማንኛውንም የመንግሥት ሠራተኛ፣

ሀ) የሥራ መደቡ ሲሰረዝ፣

ለ) መሥሪያ ቤቱ ሲዘጋ፣

ሐ) ትርፍ የሰው ኃይል ሲኖር፣

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴(፩) መሠረት ለመደልደል ካልተቻለ ወይም የመንግሥት ሠራተኛው ዝቅ ባለ የሥራ ደረጃ ላይ ለመሥራት ፈቃደኛ ካልሆነ ከሥራ ይሰናበታል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) (ሐ) መሠረት ቅነሳ የሚደረገው የመንግሥት ሠራተኛው በመሥሪያ ቤት ውስጥ በተመሳሳይ የሥራ መደብ ላይ ካለ ሌሎች የመንግሥት ሠራተኞች ጋር ሲወዳደር በሥራ ውጤቱና ባለው ችልታ ዝቅተኛ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

**፹፰. በዲስፕሊን ምክንያት ከሥራ ማሰናበት**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፱ ንዑስ አንቀጽ (፩) (ሠ) መሠረት በዲስፕሊን ቅጣት የተወሰነበትና በአስተዳደራዊ ይግባኝ ውሳኔው ያልተሻረለት የመንግሥት ሠራተኛ አገልግሎቱ ይቋረጣል፡፡

**፹፱. በዕድሜ ምክንያት አገልግሎት ስለማቋረጥ**

፩. ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፺፫ መሠረት አገልግሎቱ ካልተራዘመ በስተቀር በሕግ ከተወሰነው የመጦሪያ ዕድሜ ከደረሰበት የመጨረሻ ወር የመጨረሻ ቀን ጀምሮ አገልግሎቱ እንዲቋረጥ ይደረጋል፡፡ ፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በጡረታ ለሚሰናበት የመንግሥት ሠራተኛ ጡረታ ከመውጣቱ ከሶስት ወር በፊት በጽሑፍ እንዲያውቀው ይደረጋል፡፡

**፺. በሞት ምክንያት አገልግሎት ስለማቋረጥ**

፩. ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ ከሞተበት ቀን ጀምሮ አገልግሎቱ ይቋረጣል፡፡

፪. አገልግሎቱ በሞት ምክንያት የተቋረጠ የመንግሥት ሠራተኛ የሞተበት ወር ሙሉ ደመወዙ እንዲሁም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፩(፩) መሠረት ሊልተወሰደ የዓመት ዕረፍት ፈቃድ የሚፈጸም ክፍያ ለትዳር ጓደኛው፣ የትዳር ጓደኛ ከላለውለሕጋዊ ወራሾች ይከፈሊል፡፡

፫. አግባብ ባለው የጡረታ ሕግ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ በሞት ምክንያት አገልግሎቱ ሲቋረጥ ለሚሠራበት መሥሪያ ቤት በጽሑፍ ሊሳወቃቸው የትዳር ጓደኛ ወይም በስሩ ይተዳደሩ ለነበሩ ቤተሰቦች የሦስት ወር ደመወዝ በአንድ ጊዜ ይከፈሊል፤ ሆኖም የትዳር ጓደኛውን ወይም በሥሩ የሚተዳደሩ ቤተሰቦቹን ሳያስመዘግብ የሞተ እንደሆነ ሥልጣን ካለው አካል ወይም ፍርድ ቤት በሚሰጥ ማስረጃ መሠረት ክፍያው ይፈጸማል፡፡

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት የሚሰጠው ክፍያ ከግብርና ከጡረታ መዋጮ ነጻ ይሆናል፤ እንዲሁም በእዳ ወይም በማቻቻያነት ሊያዝ አይችልም፡፡

**፺፩. የአገልግሎት ምስክር ወረቀት አሠጣጥ**

፩. ለማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ የሚሰጥ የሥራ ልምድ የምስክር ወረቀት ሠራተኛው ሲያከናውን የነበረውን የሥራ ዓይነት፣ የአገልግሎት ዘመኑና ሲከፈለው የነበረውን ደመወዝ የሚገልጽ መሆን አለበት፡፡

፪. የሥልጠና ውል ግዴታ ወይም በመንግሥት መሥሪያ ቤቱ የሚፈለግበት ማናቸውም እዳ ያለበት የመንግስት ሠራተኛ በማንኛውም ምክንያት አገልግሎቱን ሲያቋርጥ የውል ግዴታው ስለመፈጸሙ ወይም ከእዳ ነጻ መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ ከማግኘቱ በፊት የሥራ ልምድ የምስክር ወረቀት አይሰጠውም፡፡

፫. የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፪) በሥራ ላይ እያለ የሥራ ልምድ የምስክር ወረቀት ለሚጠይቅ የመንግስት ሠራተኛ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

**፺፪. አገልግሎት ሲቋረጥ የሚፈጸም ክፍያ**

፩. የሙከራ ጊዜውን ያጠናቀቀ የመንግሥት ሠራተኛ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፹፯ መሠረት በቅነሳ ምክንያት ከሥራ ከተሰናበተና የሥራ ውል በተቋረጠበት ዕለት የጡረታ አበል የማይከፈለው ከሆነ፣

ሀ) ለመጀመሪያ አንድ ዓመት የሦስት ወር ደመወዝ፣

ለ) በተጨማሪ ለአገለገለበት ለእያንዳንዱ ዓመት የወር ደመወዙ አንድ ሦስተኛ እየታከለ፣ ይከፈለዋል፤ ሆኖም የሚሰጠው ክፍያ ከሠራተኛው የአሥራ ሁለት ወር ደመወዙ መብለጥ የለበትም፡፡

፪. የሙከራ ጊዜውን ለጨረሰና ከአንድ ዓመት በታች ሊገለገል የመንግስት ሠራተኛ የሚፈጸመው ክፍያ ከአገልግሎቱ ጋር ተመጣጣኝ ይሆናል፡፡

**፺፫. አገልግሎትን ማራዘም**

፩. የመንግሥት ሠራተኛ የመጦሪያ ዕድሜው ከደረሰ በኋላ በአንድ ጊዜ እስከ አምስት ዓመት በጠቅሊሊው ከአሥር ዓመት ለማይበልጥ ጊዜ አገልግሎቱን ማራዘም ይቻላል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የአንድን የመንግሥት ሠራተኛ አገልግሎት ማራዘም የሚቻለው፣

ሀ) የሠራተኛው ትምህርት፣ ልዩ ዕውቀትና ችልታ ለመሥሪያ ቤቱ ሥራ ጠቃሚ ሆኖ ሲገኝ፤

ለ) በደረጃ ዕድገት፣ በዝውውር ወይም በቅጥር ተተኪ ሠራተኛ ለማግኘት አለመቻለ ሲረጋገጥ፤

ሐ) ሠራተኛው ለሥራው ብቁ መሆኑ በሕክምና ማስረጃ ሲረጋገጥ፤

መ) ሠራተኛው አገልግሎቱን ለመቀጠል ሲስማማ፤ እና

ሠ) የአገልግሎቱ መራዘም ጥያቄው የመጦሪያ ዕድሜው ከመድረሱ ከሦስት ወር በፊት ለቢሮው ቀርቦ ሲፈቀድ፤ነው፡፡

## ክፍል አሥራ ሁለት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፺፬. የቅጥር፣ የደረጃ ዕድገት፣ የደመወዝ ጭማሪና ሌላ ጥቅም ስለመሰረዝ**

፩. የሐሰት የትምህርት ወይም የሥራ ልምድ ማስረጃ በማቅረብ ወይም ሥልጣን በላለው ሰው ወይም ይህን አዋጅ ወይም አዋጁን ለማስፈጸም የወጣውን ደንብና መመሪያ ወይም ሌላ ማናቸውንም ሕግ በመተሊለፍ የተፈፀመ ቅጥር፣ የደረጃ ዕድገት፣ የደመወዝ ጭማሪ ወይም ሌላ ጥቅም በዲስፕሊንና በወንጀል የሚያስከትለው ተጠያቂነት እንደተጠበቀ ሆኖ በመሥሪያ ቤቱ የበላይ ሓላፊ ወይም በቢሮው በማናቸውም ጊዜ ይሰረዛል፡፡

፪. የቅጥር፣ የደረጃ ዕድገት፣ የደመወዝ ጭማሪ ወይም ሌላ ጥቅም የተሰረዘበት የመንግሥት ሠራተኛ በዲስፕሊንና በወንጀል መጠየቁ እንደተጠበቀ ሆኖ የመሰረዙ እርምጃ እስከተወሰደበት ጊዜ ድረስ የተከፈለውን ደመወዝና ሌሎች ጥቅሞች እንዲመልስ አይጠይቅም፡፡

፫. ከሕግ ውጭ ቅጥር፣ የደረጃ ዕድገት፣ የደመወዝ ጭማሪ ወይም ሌላ ጥቅም እንዲሰጥ ሆን ይወክላል ወይም በከባድ ቸልተኝነት የፈቀደ የሥራ ሓላፊ ወይም የኮሚቴ አባል አግባብ ባለው የዲስፕሊን፣ የወንጀል ሕግ እና የፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት የተጠቀሰው ጥፋት መፈጸሙን የመሥሪያ ቤቱ የበላይ ሓላፊ ወይም ቢሮው ከደረሰበት ጥፋቱን ለማረም የሚያስችል እርምጃ መውሰድ እና ሓላፊውን ወይም የኮሚቴ አባለን በወንጀልና በፍትሐብሔር ሕግ ተጠያቂ ለማድረግ ሥልጣን ሊለው የመንግሥት አካል የተፈጸመውን ድርጊት በማስረጃ አስደግፎ ማቅረብ አለበት፡፡

**፺፩. የሥልጣን ውክልና ስለመስጠት**

ቢሮው የፐብሊክ ሰርቪሱን የሰው ሀብት ሥራ አመራር ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ ያስተዳድራል ሆኖ ሲያገኘው በዚህ አዋጅ የተሰጠውን ሥልጣንና ሓላፊነት ለመሥሪያ ቤቶች በውክልና ማስተሊለፍ ይችላል፡፡

**፺፪. የአዋጁን አፈጻጸም መቆጣጠር**

፩. ቢሮው ይህን አዋጅና በአዋጁ መሠረት የሚወጡትን ደንቦችና መመሪያዎች በትክክል በሥራ ላይ መዋሊቸውን የመቆጣጠር ሥልጣንና ሓላፊነት ይኖረዋል፡፡

፪. ቢሮው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተሰጠውን ሥልጣንና ሓላፊነት ተግባራዊ ለማድረግ በማናቸውም ጊዜ፣

ሀ) በመንግስት መሥሪያ ቤቶች በመገኘት ወይም እንዲሊኩለት በማዘዝ ማህደሮችንና ሌሎች መረጃዎችን መመርመር፤ እና

ለ) ጉዳዩ የሚመለከተውን የሥራ ሓላፊ ወይም ሌሎች የመንግስት ሠራተኞች በቃል ወይም በጽሁፍ እንዲያስረደ መጠየቅ፤ይችላል ፡፡

፫. ቢሮው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት በሚያደርገው ምርመራ ወይም በሌላ በማናቸውም መንገድ ሕግ መጣሱን ወይም አድል መፈጸሙን ከደረሰበት፣

ሀ) ትክክል ያልሆነ አሠራር እንዲስተካከል የማዘዝ፤

ለ) ጉዳዩ ውሳኔ እስኪያገኝ ድረስ አፈጻጸሙን የማገድ፤

ሐ) ለድርጊቱ ተጠያቂ በሆነው የሥራ ሓላፊ ወይም የመንግሥት ሠራተኛ ላይ ተገቢው አስተዳደራዊ እርምጃ እንዲወሰድበት የማድረግ፤ እና

መ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፺፬ (፬) መሠረት የመፈጸም፤ ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

## ፺፯. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

፩. ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ካቢኔው ሊያወጣ ይችላል ፡፡

፪. ቢሮው ይህን አዋጁ ለማስፈጸም ያስተዳድራል የሆኑ ሌሎች የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል ፡፡

## ፺፰. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

፩. ቢሮው ለክፍት የሥራ መደቦች አመልካቾች በፈተና ተወዳድረው የሚመረጡበትን የመግቢያና የብቃት ማረጋገጫ ሥርዓት መዘርጋት የሚያስችለ መመዘኛዎችና መለኪያዎች በከተማ ደረጃ እስኪዘረጋ ድረስ የመንግሥት ሠራተኞች ቅጥርን፣ የደረጃ እድገትን፣ ዝውውርና ድልድልን በተመለከተ በዚህ አዋጅ በተደነገጉት ሌሎች መስፈርቶች ብቻ አፈጻጸማቸው ይቀጥሊል፡፡

፪. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግስት ሠራተኞች የዲስፕሊን አፈጻጸምና የቅሬታ አቀራረብ ሥነሥርዓት ደንብ ቁጥር ፳፯/፪ሺ፪ እና በሥራ ላይ ያለ መመሪያዎች የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች እስካልተቃረኑ እና በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፺፯ መሠረት በሚወጡ ደንቦች እና መመሪያዎች እስከሚተኩ ድረስ ተፈጻሚነታቸው ይቀጥሊል፡፡

## ፺፱. የተሻሩ እና ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች

፩. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር ፯/፪ሺ፪ በዚህ አዋጅ ተሸሯል፡፡

፪. ይህን አዋጅ የሚቃረን ማናቸውም የአስተዳደሩ አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ፣ የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ ውስጥ የተደነገጉትን ጉዳዮች በሚመለከት ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

፻. አዋጁ የሚጸናበት ቀን

ይህ አዋጅ፡- ፩. በአንቀጽ ፵፪ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተመለከተውን የወሊድ ፍቃድ በሚመለከት ረገድ ከታህሳስ ፮ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም ጀምሮ፤

፪. ሌሎች ድንጋጌዎችን በሚመለከት ረገድ ከሚያዝያ ፲፯ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም ጀምሮ፤ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ

ድረባ ኩማ

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ

## ከኃላፊነት የሚነሱ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የበላይ ኃላፊዎች፣ ከፍተኛ ኃላፊዎች፣ ሌሎች ኃላፊዎች፣ በቋሚነት የሚሠሩ እና ልሎች የምክር ቤት አባላትና ዳኞች የሚያገኙአቸውን መብቶችና ጥቅሞች ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ለመተካት የወጣ አዋጅ ፷፩ /፪ሺ፲ አጭር መግለጫ


<u>ማውጫ</u>

፭. የመቋቋሚያ አበል

፮. የሥራ ስንብት ክፍያ

፯. የመኖሪያ ቤት  እና የመኖሪያ ቤት አበል

፰. የተሽከርካሪ አገልግሎት እና አበል

፱. የሕክምና አገልግሎት

፲. የግል ደህንነት ጥበቃ አገልግሎት

፲፩. የአገልግሎት የምስክር ወረቀት

፲፪.  የባለመብቱ ከዚህ ዓለም በሞት መለየት

፲፫. የመቋቋሚያ አበል

፲፬. የሥራ ስንብት ክፍያ

፲፭. የመኖሪያ ቤት እና የመኖሪያ ቤት አበል

፲፮. የተሽከርካሪ አገልግሎት እና አበል

፲፯. የሕክምና አገልግሎት

፲፰. የግል ደኅንነት ጥበቃ አገልግሎት

፲፱.የሥራ ምደባ

፳. የአገልግሎት የምስክር ወረቀት

፳፩. የባለ መብቱ ከዚህ ዓለም በሞት መለየት

፳፪. የመቋቋሚያ አበል

፳፫.ስለ ሥራ ስንብት ክፍያ

፳፬. የመኖሪያ ቤት አበል

፳፭. የተሽከርካሪ አበል

፳፮. የሕክምና አገልግሎት

፳፯. የአገልግሎት የምስክር ወረቀት

፳፰.  የባለመብቱ ከዚህ ዓለም በሞት መለየት

፳፱. የመቋቋሚያ አበል

፴. የሥራ ስንብት ክፍያ

፴፩. የመኖሪያ ቤት አበል

፪. የተሽከርካሪ አበል

፴፫. የአገልግሎት የምስክር ወረቀት

፴፬.. የባለመብቱ ከዚህ ዓለም በሞት መለየት

፴፭. የመኖሪያ ቤት አበልና የተሽከርካሪ አበል ግምት

፴፮.የአገልግሎት ዘመን አቆጣጠርና የመብቶች ግንኙነት

፴፯. መብቶችና ጥቅሞችን ስለሚያሳጡ ሁኔታዎች

፴፰.መብቶችና ጥቅሞችን የሚያቋርጡ ሁኔታዎች

፴፱. ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም ኃላፊነት    የተሰጣቸው አካላት

፵. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

፵፩. የተሻሩና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች

፵፪.  አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

<u>አጭር መግለጫ</u>

የከተማ ኣስተዳደሩ ከኃላፊነት የሚነሱ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የበላይ ኃላፊዎች፣ ከፍተኛ ኃላፊዎች፣ ሌሎች ኃላፊዎች፣ በቋሚነት የሚሠሩ እና ልሎች የምክር ቤት አባላትና ዳኞች የሚያገኝአቸውን መብቶችና ጥቅሞች ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ለመተካት የወጣ አዋጅ ነው።

## ከኃላፊነት የሚነሱ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የበላይ ኃላፊዎች፣ ከፍተኛ ኃላፊዎች፣ ሌሎች ኃላፊዎች፣ በቋሚነት የሚሠሩ እና ልሎች የምክር ቤት አባላትና ዳኞች የሚያገኛቸውን መብቶችና ጥቅሞች ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ለመተካት የወጣ አዋጅ ፷፩ /፪ሺ፲

የአዲስ አበባ ከተማ የበላይ ኃላፊዎች፣ ከፍተኛ ኃላፊዎች፣ በቋሚነት የሚሠሩ እና የማይሰሩ የምክር ቤት አባላትና ዳኞች  ሕዝባዊ አደራ በመሸከም ለከተማይቱ ሕዝብ ጥቅም የሚሰሩ እና የማይሰሩ በመሆናቸው ከኃላፊነት ሲነሱ ከጉስቁልና የራቀ ኑሮ እንዲኖሩ ማድረግና ለጥቃት ተጋላጭ እንዳይሆኑ ጥበቃና ከለላ መስጠት አስፈላጊ በመሆኑ፣

የአዲስ አበባ ከተማ የበላይ ኃላፊዎች፣ ከፍተኛ ኃላፊዎች፣ ዳኞች፣ በቋሚነት የሚሠሩ የምክር ቤት አባላት በኃላፊነት በነበሩበት ወቅት ያካበቱትን ዕውቀትና ልምድ ለመጠቀም አመቺ ሁኔታ መፍጠር ስለሚያስፈልግ፣

በሥራ ላይ ያሉ የአዲስ አበባ ከተማ የበላይ ኃላፊዎች፣ ከፍተኛ ኃላፊዎች፣ በቋሚነት የሚሠሩ የምክር ቤት አባላትና ዳኞች ለወደፊት ኑሯቸው ሳያስቡና ሳይሰጉ ለከተማው ልማትና ዕድገት በቅንነት፣ በታማኝነትና በትጋት እንዲሰሩ ማበረታታት አስፈላጊ በመሆኑ፤

ከእነዚህ ሁኔታዎች በመነሣት ከኃላፊነት የሚነሱ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሪዎች፤ ከፍተኛ ኃላፊዎች፣ በቋሚነት የሚሰሩ የምክር ቤትአባላትና ዳኞች የሚያገኟቸን መብቶችና ጥቅሞች ለመወሰን የወጣውን አዋጅ አዋጅ ቁጥር ፴፮/፪ሺ፬ መተካት በማስፈለጉ፤

በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱ (እንደተሻሻለ) አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (?)፣ አንቀጽ ፲፩ ንዑስ አንቀጽ (፪) /ሐ/ የተደነገገውን ተግባራዊ ለማድረግ የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

**፩. ‹‹አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ <<ከኃላፊነት የሚነሱ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የበላይ ኃላፊ፣ ከፍተኛ ኃላፊ፣ ሌላ ኃላፊ፣ በቋሚነት የሚሠሩ እና ልሎች የምክር ቤት አባላትና ዳኞች የሚያገኟቸውን መብቶችና ጥቅሞች ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ፷፩/፪ሺ፲>> ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ

፩. “ከተማ” ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፣

፪. “የከተማ አስተዳደር” ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፣

፫. “የከተማ የበላይ ሀላፊ” ማለት የከተማ ከንቲባ፣ ምክትል ከንቲባ ወይም በምክትል ከንቲባ ደረጃ የተሾመ ኃላፊ ወይም አማካሪ ነዉ፣

፬. "የከተማ ከፍተኛ ሀላፊ" ማለት የቢሮ ሀላፊ፣ የፕላን ኮሚሽን ኃላፊ፣ የዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ኃላፊ፣ የገቢዎች ባለሥልጣን ኃላፊ፣ የከተማ ሥራ አስኪያጅ፣ የክፍለ ከተማ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይም በእነዚህ ደረጃዎች የተሾመ ሀላፊ ወይም አማካሪ ነዉ፣

፭. "የከተማ ሌላ ኃላፊ" ማለት የቢሮ ምክትል ኃላፊ፣ የከተማ ምክትል ሥራ አስኪያጅ፣ የፕላን ኮሚሽን ምክትል ኃላፊ፣ የዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ምክትል ኃላፊ፣ የገቢዎች ባለሥልጣን ምክትል ኃላፊ፣ የክፍለ ከተማ ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይም በእነዚህ ደረጃዎች የተሾመ ኃላፊ ወይም አማካሪ ነው፡፡

፮."ዳኛ" ማለት የከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ወይም ምክትል ፕሬዚዳንት፣ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት፣ የከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ዳኛ፣ የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ ፕሬዚዳንት ወይም የከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ ፕሬዚዳንት ነዉ፣

፯. "በቋሚነት የሚሠራ የምክር ቤት አባል" ማለት የከተማ ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ፣ የከተማ ምክር ቤት ምክትል አፈ-ጉባዔ፣ የከተማ ምክር ቤት ጸሐፊ፣ የከተማ ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ወይም የክፍለ ከተማ ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ ነዉ፣

፰. "ባለመብት"ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የሚሰጡ መብቶችና ጥቅሞችን ለማግኘት ብቁ የሆነ ሰው ነው፣

ሀ. «ቤተሰብ»ማለት የአንድን ባለመብት የትዳር ጓደኛና 18 አመት ያልሞላቸውን ልጆች ያጠቃልላል፣

ለ. «ተተኪ» የሚለው ቃል አግባብ ባለው የጡረታ ሕግ የተሰጠውን ትርጓሜ ይይዛል፣

ሐ. «ከኃላፊነት የሚነሳ» ማለት በጥፋት ካልሆነ በስተቀር በልሎች ማናቸውም ምክንያቶች የሚነሳ ባለመብት ነው፡፡

**<u>፫. የፆታ አገላለጽ</u>**

በዚህ አዋጅ ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

**<u>፬. የተፈፃሚነት ወሰን</u>**

ይህ አዋጅ ከኃላፊነት በሚነሱ የከተማ አስተዳደር የበላይ ኃላፊዎች፣ የከተማ ከፍተኛ ኃላፊዎች፣ ልሎች ኃላፊዎች፣ በቋሚነት የሚሠሩና ልሎች የምክር ቤት አባሎች እና ዳኞች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## ከኃላፊነት የሚነሱ የከተማ የበላይ ኃላፊዎች፣ የከተማ ከፍተኛ ኃላፊዎች እና ልሎች ኃላፊዎች መብቶችና ጥቅሞች

### ፩. የመቋቋሚያ አበል

፩. የከተማ የበላይ ኃላፊ፣ የከተማ ከፍተኛ ኃላፊ፣ ሌላ ኃላፊ፡-

ሀ/ ቢያንስ አንድ የምርጫ ዘመን አገልግሎ ከኃላፊነት ከተነሳ ወይም፣

ለ/ ከአንድ የምርጫ ዘመን ግማሽ ያላነሰ አገልግሎ በሕመም፣ በአካል ጉዳት ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ሌላ ምክንያት ከኃላፊነት ከተነሳ የመቋቋሚያ አበል ይከፈለዋል፡፡

፪. በዚህ አንቀፅ ንዑሥ አንቀፅ (፩) መሠረት የሚከፈለው የመቋቋሚያ አበል ለመጀመሪያው የአንድ ዓመት አገልግሎት የስድስት ወር ደመወዝ ሆኖ ከአንድ ዓመት በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የአንድ ወር ደመወዝ እየታከለ ይታሰባል፡፡ሆኖም ጠቅላላ የመቋቋሚያ አበል ክፍያው ከሃያ አራት (፳፬) ወራት ደመወዝ መብለጥ የለበትም፡፡

### ፪. የሥራ ስንብት ክፍያ

፩. የከተማ የበላይ ኃላፊ፣ የከተማ ከፍተኛ ኃላፊ፣ ወይም ሌላ ኃላፊ የሥራ ስንብት ክፍያ ይከፈለዋል፡፡ ሆኖም ባለመብቱ የተጠቀሰውን ክፍያ የሚያገኘው ወደ መንግስት ሥራ የማይመለስ ከሆነ ነው፡፡

፪. በዚህ አንቀፅ ንዑሥ አንቀፅ (፩) መሠረት የሚከፈለው የሥራ ስንብት ክፍያ ለመጀመሪያው የአንድ ዓመት አገልግሎት የሥድስት (፮) ወራት ደመወዝ ሆኖ ከአንድ ዓመት በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የመጨረሻው ወር ደመወዝ አንድ ሁለተኛእየታከለ ይሰላል፣ ሆኖም የሚከፈለው ጠቅላላ የሥራ ስንብት ክፍያ ከአስራ ስምንት ወራት ደመወዝ መብለጥ የለበትም፡፡

### ፫. የመኖሪያ ቤት  እና የመኖሪያ ቤት አበል

፩. የከተማ የበላይ ኃላፊ፣ የከተማ ከፍተኛ ኃላፊ ወይም ሌላ ኃላፊ፡-

ሀ. ቢያንስ ሁለት የምርጫ ዘመን አገልግሎ ከኃላፊነት ከተነሣ፣ ወይም ለ. አንድ የምርጫ ዘመን እና ከግማሽ ያላነሰ አገልግሎ በሕመም፣ በአካል ጉዳት ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ሌላ ምክንያት ከኃላፊነት ከተነሣ፣ በራሱ ወይም በባለቤቱ ስም የግል መኖሪያ ቤት የልለው ከሆነ ለራሱና ለቤተሰቡ መኖሪያነት የሚያገለግል ራሱ ኪራይ እየከፈለ የሚገለገልበት የመኖሪያ ቤት እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡ የመኖሪያ ቤቱ ደረጃም፡-

ሐ. የከተማ የበላይ ኃላፊ ሲሆን ሦስት መኝታ  ክፍሎች ያሉት፣

መ. የከተማ ከፍተኛ ኃላፊ ወይም ሌላ ኃላፊ  ሲሆን ሁለት መኝታ ክፍሎች ያሉት፣

፪. የከተማ የበላይ ኃላፊ፣ የከተማ ከፍተኛ ኃላፊ ወይም ሌላ ኃላፊ፡-

ሀ. ቢያንስ አንድ የምርጫ ዘመን አገልግሎ ከኃላፊነት ከተነሳ፣ ወይም

ለ. ከአንድ የምርጫ ዘመን ግማሽ ያላነሰ አገልግሎ በህመም ፣ በአካል ጉዳት ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ሌላ ምክንያት ከኃላፊነት ከተነሳ፣ የመኖሪያ ቤት አበል ይከፈለዋል፤ የሚከፈለው የመኖሪያ ቤት አበል በአንድ ግዜ የሚከፈል ሆኖ፡-

ሐ. ባለመብቱ የከተማ የበላይ ኃላፊ ከሆነ መነሻው የዘጠኝ (፱) ወራት ሙሉ ክፍያ ሆኖ ከአንድ የምርጫ ዘመን በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የአንድ ወር ክፍያ አንድ ሁለተኛ እየታከለ ይሰላል፡፡

መ. ባለመብቱ የከተማ ከፍተኛ ኃላፊ ከሆነ መነሻው የስድስት (፮) ወራት ሙሉ ክፍያ ሆኖ ከአንድ የምርጫ ዘመን በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የአንድ ወር ክፍያ አንድ ሁለተኛ እየታከለ ይሰላል፡፡

ሠ. ባለመብቱ ሌላ ኃላፊ ከሆነ መነሻው የአራት (፬) ወራት ሙሉ ክፍያ ሆኖ ከአንድ የምርጫ ዘመን በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የአንድ ወር ክፍያ አንድ ሁለተኛ እየታከለ ይሰላል፡፡

፫. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የሚከፈለው ክፍያ ከሃያ አራት (፳፬) ወራት የመኖሪያ ቤት አበል መብለጥ የለበትም፡፡

**<u>፰. የተሽከርካሪ አገልግሎት እና አበል</u>**

፩. የከተማ የበላይ ኃላፊ፣ የከተማ ከፍተኛ ኃላፊ ወይም ሌላ ኃላፊ፡-

ሀ. ቢያንስ አንድ የምርጫ ዘመን አገልግሎ ከኃላፊነት ከተነሳ፣ ወይም

ለ. ከአንድ የምርጫ ዘመን ግማሽ ያላነሰ አገልግሎ በሕመም፣ በአካል ጉዳት፣ ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ሌላ ምክንያት ከኃላፊነት ከተነሳ፤ የተሽከርካሪ አበል ይከፈለዋል፡፡ የሚከፈለው የተሽከርካሪ አበል በአንድ ግዜ የሚከፈል ሆኖ፡-

ሐ. የከተማ የበላይ ኃላፊ ሲሆን መነሻው የዘጠኝ (፱) ወራት ሙሉ ክፍያ ሆኖ ከአንድ የምርጫ ዘመን በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የአንድ ወር ክፍያ አንድ ሁለተኛ እየታከለ ይሰላል፤

መ. የከተማ ከፍተኛ ኃላፊ ሲሆን መነሻው የስድስት (፮) ወራት ሙሉ ክፍያ ሆኖ ከአንድ የምርጫ ዘመን በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ አመት አገልግሎት የአንድ ወር ክፍያ አንድ ሁለተኛ እየታከለ ይሰላል፤

ሠ. ሌላ ኃላፊ ሲሆን መነሻው የአራት (፬) ወራት ሙሉ ክፍያ ሆኖ ከአንድ የምርጫ ዘመን በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የአንድ ወር ክፍያ አንድ ሁለተኛ እየታከለ ይሰላል፡፡

፪. የከተማ የበላይ ኃላፊ፡- ሀ) ቢያንስ ሁለት የምርጫ ዘመን አገልግሎ ከኃላፊነት ከተነሳ፣ ወይም

ለ) አንድ የምርጫ ዘመን ከግማሽ ያላነሰ አገልግሎ በሕመም፣ በአካል ጉዳት፣ ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ሌላ ምክንያት ከኃላፊነት ከተነሳ፣ አንድ የቤት አውቶሞቢል በመንግስት ይመድብለታል፡፡ በዚህ መሰረት ለሚመደበው የቤት አውቶ ሞቢል የሹፌር ደመወዝ፣ የነዳጅ፣ የጥገና እንዲሁም ሌላ ወጪ በመንግስት ይሸፈናል፡፡

፫. የከተማ ከፍተኛ ኃላፊ ወይም ሌላ ኃላፊ፡-

ሀ. ቢያንስ ሁለት የምርጫ ዘመን አገልግሎ ከኃላፊነት ከተነሣ፣ ወይም

ለ. አንድ የምርጫ ዘመን ከግማሽ ያላነሰ አገልግሎ በሕመም፣ በአካል ጉዳት፣ ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ሌላ ምክንያት ከኃላፊነት ከተነሣ፣ የተሸከርካሪ አበል ይከፈለዋል፡፡ የሚከፈለው የተሸከርካሪ አበል በአንድ ጊዜ ሆኖ፡-

ሐ. ለከተማ ከፍተኛ ኃላፊ ሲሆን መነሻው የዘጠኝ /፱/ ወራት ሙሉ ክፍያ ሆኖ ከአንድ የምርጫ ዘመን በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የአንድ ወር ክፍያ አንድ ሁለተኛ እየታከለ ይሰላል፡፡

መ. ሌላ ኃላፊ ሲሆን መነሻው የስድስት (፮) ወራት ሙሉ ክፍያ ሆኖ ከአንድ የምርጫ ዘመን በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የአንድ ወር ክፍያ አንድ ሁለተኛ እየታከለ ይሰላል፡፡

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ ወይም (፫) መሠረት የሚከፈለው ክፍያ ከሀያ አራት (፳፬) ወራት የተሸከርካሪ አበል ክፍያ መብለጥ የለበትም፡፡

**<u>፱. የሕክምና አገልግሎት</u>**

፩. ከኃላፊነት የሚነሣ የከተማ የበላይ ኃላፊ፡-

ሀ/ ለራሱና ለቤተሰቡ በአገር ውስጥ በመንግስት የጤና ተቋም በነፃ ወይም እንደ ሁኔታው በግል የጤና ተቋም በመንግስት ወጭ የሕክምና አገልግሎት ያገኛል፤

፪.ከኃላፊነት ለሚነሣ የከተማ የበላይ ኃላፊ የሚሰጠው የአገልግሎት የምስክር ወረቀት በከተማ ምክር ቤት አፈ ጉባኤ፣ ለከተማ ከፍተኛ ኃላፊ ወይም ሌላ ኃላፊ የሚሰጥ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት በከንቲባ ይፈረማል፡፡

፫. የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ማንኛውም ከኃላፊነት የተነሳ ኃላፊ፡-

ሀ/ በመንግስት ሆስፒታሎች ለሚሰጠው የህክምና አገልግሎት ቅድሚያ ያገኛል፣ ለ/ በሕዝባዊ ስብሰባዎች የክብር ቦታ ይሰጠዋል፡፡

የባለመብቱ ከዚህ ዓለም በሞት መለየት

፩. የከተማ የበላይ ኃላፊ፣ የከተማ ከፍተኛ ኃላፊ ወይም ሌላ ኃላፊ በሥራ ላይ እያለ ከዚህ አለም በሞት የተለየ እንደሆነ፣

ሀ. ከሞቱ ጋር በተያያዘ ምክንያት ለሚከተሉት ወጭዎች መሸፈኛ ይሆን ዘንድ የሦስት ወር ደመወዝ ለቤተሰቡ ይከፈላል፣

ለ. ከኃላፊነት ቢነሳ ኖሮ ሊከፈለው ወይም ሊሠጠው ይገባ የነበረው የመቋቋሚያ አበል፣ የሥራ ስንብት ክፍያ፣ የኪራይ መኖሪያ ቤት፣ የተሽከርካሪ አበል ወይም የተሽከርካሪ አገልግሎት ለቤተሰቡ ይከፈላል ወይም ይሰጣል፡፡

ለ/ የሕክምና ቦርድ በሚሰጠው ማስረጃ ውጭ አገር በመንግስት ወጭ መታከም ይችላል፤

ሐ/ ከኃላፊነት የሚነሳ የከተማ የበላይ ኃላፊ ለራሱና ለባለቤቱ በአገር ውስጥ የጤና ተቋም ተኝቶ ለመታከም የሕክምና አገልግሎት የሚሰጠው በአንደኛ ደረጃ ማዕረግ ይሆናል፤

፲. ከኃላፊነት የሚነሣ የከተማ ከፍተኛ ኃላፊ እና ሌላ ኃላፊ ለራሱና ለቤተሰቡ በመንግስት የጤና ተቋም በነፃ የሕክምና አገልግሎት ያገኛል፡፡

## ፲. የግል ደህንነት ጥበቃ አገልግሎት

፩. ከኃላፊነት የሚነሳ የከተማ የበላይ ኃላፊ በኃላፊነት ላይ በነበረበት ወቅት የግል ደህንነት ጥበቃ ይደረግለት የነበረ ከሆነ ከኃላፊነት ሲነሳም ለእሱና ለቤተሰቡ ጥበቃ ይደረግለታል፣

፪. የጥበቃ ኃይሉ ዓይነትና መጠን ጥበቃውን በሚያካሂደው አካል ይወሰናል፡፡

## ፲፩. የአገልግሎት የምስክር ወረቀት

፩. ከኃላፊነት የሚነሳ የከተማ የበላይ ኃላፊ፣ የከተማ ከፍተኛ ኃላፊ ወይም የከተማ ሌላ ኃላፊ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡

፪. ከኃላፊነት ለሚነሣ የከተማ የበላይ ኃላፊ የሚሰጠው የአገልግሎት የምስክር ወረቀት በከተማ ምክር ቤት አፈ ጉባኤ፣ ለከተማ ከፍተኛ ኃላፊ ወይም ሌላ ኃላፊ የሚሰጥ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት በከንቲባ ይፈረማል፡፡

፫. የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ማንኛውም ከኃላፊነት የተነሳ ኃላፊ፡-

ሀ/ በመንግስት ሆስፒታሎች ለሚሰጠው የህክምና አገልግሎት ቅድሚያ ያገኛል፣

ለ/ በሕዝባዊ ስብሰባዎች የክብር ቦታ ይሰጠዋል፡፡

## ፲፪. የባለመብቱ ከዚህ ዓለም በሞት መለየት

፩. የከተማ የበላይ ኃላፊ፣ የከተማ ከፍተኛ ኃላፊ ወይም ሌላ ኃላፊ በሥራ ላይ እያለ ከዚህ አለም በሞት የተለየ እንደሆነ፣

ሀ. ከሞቱ ጋር በተያያዘ ምክንያት ለሚከተሉት ወጭዎች መሸፈኛ ይሆን ዘንድ የሦስት ወር ደመወዝ ለቤተሰቡ ይከፈላል፣

ለ. ከኃላፊነት ቢነሳ ኖሮ ሊከፈለው ወይም ሊሠጠው ይገባ የነበረው የመቋቋሚያ አበል፣ የሥራ ስንብት ክፍያ፣ የኪራይ መኖሪያ ቤት፣ የተሽከርካሪ አበል ወይም የተሽከርካሪ አገልግሎት ለቤተሰቡ ይከፈላል ወይም ይሰጣል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ማንኛውም ባለመብት ከኃላፊነት ተነስቶ ጥቅሞቹን ከማግኘቱ በፊት ከዚህ ዓለም በሞት ቢለይ ሊከፈለው ወይም ሊሰጠው ይገባ የነበረው የመቋቋሚያ አበል፣ የሥራ ስንብት ክፍያ፣ የመኖሪያ ቤት አበል፣ ወይም የኪራይ መኖሪያ

ቤት፣ የተሽከርካሪ አበል ወይም የተሽከርካሪ አገልግሎት ለቤተሰቡ ይከፈላል ወይም ይሰጣል፡፡

፫. የከተማ የበላይ ኃላፊ በሥራ ላይ እያለ ወይም ከኃላፊነት ተነስቶ ከዚህ ዓለም በሞት የተለየ እንደሆነ፣ ሀ. ዜና ዕረፍቱና አጭር የሕይወት ታሪኩ በከተማው መንግስት የብዙሀን መገናኛ ዘድዎች አማካኝነት ይነገራል፣

ለ. ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣን የከተማውን አስተዳደር በመወከል በቀብሩ ስነ-ሥርአት ላይ ተገኝቶ የአበባ ጉንጉን ያስቀምጣል፣

ሐ. የቀብሩ ስነ-ሥርአት ወጪ በከተማው አስተዳደር ይሸፈናል፣

፬. የከተማ የበላይ ኃላፊ፣ የከተማ ከፍተኛ ኃላፊ ወይም ሌላ ኃላፊ ከዚህ ዓለም በሞት መለየት በዚህ አዋጅ መሠረት ቤተሰቡ በአገር ውስጥ ሊያገኝ የሚገባውን የህክምና አገልግሎት እንዲቋረጥ አያደርግም፡

## ክፍል ሶሥት

## ከኋላፊነት የሚነሱ የምክር ቤት አባላት መብቶችና ጥቅሞች

### ፲፫. የመቋቋሚያ አበል

፩ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ የተደነገገው የመቋቋሚያ አበል ከኃላፊነት ለተነሳ በቋሚነት ለሚሠራ የምክር ቤት አባል ተፈፃሚነት ይኖረዋል፣

፪. በቋሚነት የሚሠራ የምክር ቤት አባልን ሳይጨምር የከተማ ምክር ቤት አባል አንድ የምርጫ ዘመን አጠናቆ ከኋላፊነት ሲነሳ የተጣራ ብር አስራ አምስት ሺህ (15 ሺህ ብር) በጻረጎት መልክ ይከፈለዋል፡፡ በተከታታይ ከአንድ የምርጫ ዘመን በላይ ያገለገለ ከሆነ ለእያንዳንዱ ተጨማሪ አንድ የምርጫ ዘመን የተጣራ ብር አሥራ አምስት ሺህ (15 ሺህ ብር) አንድ አራተኛ እየታከለ ይከፈለዋል፡፡ የከተማ ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴ አባል በዚህ ላይ ሶስት ሺህ (3,000.00) ተጨምሮ የተጣራ አስራ ስምንት ሺህ ብር (18,000.00) ይከፈለዋል፡፡

፫. ማንኛውም የምክር ቤት አባል የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተጠቃሚ የሚሆነው ቢያንስ ከ3/4 (25%) በላይ በምክር ቤት ስብሰባዎችና በሚሰጡት ተግባራት ላይ የተሳተፈ፣ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ሳይሳተፍ ከቀረ በምክር ቤቱ የአሰራርና ሥነ ምግባር ደንብ መሰረት ያሳወቀ ከሆነ ነው፡፡

### ፲፬. የሥራ ስንብት ክፍያ

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፯ የተደነገገው የስራ ስንብት ክፍያ በቋሚነት ለሚሠራ የምክር ቤት አባልም ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**፲፭. የመኖሪያ ቤት እና የመኖሪያ ቤት አበል**

፩. በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፯ ንዑስ አንቀፅ (፩) /ሀ/ /ለ/ /ሐ/ የተደነገገው የኪራይ መኖሪያ ቤት ለከተማ ምክር ቤት አፈ-ጉባኤም ተፈፃሚ ይሆናል፤

፪ በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፯ ንዑስ አንቀፅ (፩) (ሀ)/ ለ/ /መ/ የተደነገገው የኪራይ መኖሪያ ቤት ለከተማ ምክር ቤት ምክትል አፈ-ጉባኤ፣ ለከተማ ምክር ቤት ፀሐፊ፣ ለከተማ ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ፣ ለክፍለ ከተማ ምክር ቤት አፈ-ጉባኤም ተፈፃሚ ይሆናል፤

፫. በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፯ ንዑስ አንቀፅ (፪) (ሀ) /ለ/ /ሐ/ የተደነገገው የመኖሪያ ቤት አበል ለከተማ ምክር ቤት አፈ-ጉባኤም ተፈፃሚ ይሆናል፤

፬. በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፯ ንዑስ አንቀፅ (፪) (ሀ) /ለ/ /መ/ የተደነገገው የመኖሪያ ቤት አበል ለከተማ ምክር ቤት ምክትል አፈ-ጉባኤ፣ ጸሀፊ፣ ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ፣ ለክፍለ ከተማ ምክር ቤት አፈ- ጉባኤም ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**፲፮. የተሽከርካሪ አገልግሎት እና አበል**

፩. በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፰ ንዑሥ አንቀፅ (፪) የተደነገገው የተሽከርካሪ አገልግሎት ለከተማ ምክር ቤት አፈ-ጉባኤም፣ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

፪. በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፰ ንዑስ አንቀፅ (፩) (ሀ) /ለ/ /ሐ/ እና ንኡስ አንቀጽ (፬) የተደነገገው የተሽከርካሪ አበል ለከተማ ምክር ቤት አፈ-ጉባኤም ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

፫. በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፰ ንዑስ አንቀፅ (፩) (ሀ) /ለ/ /መ/፣ ንዑስ አንቀጽ /፫/ (ሀ) /ለ/ /ሐ/ እና ንኡስ አንቀጽ (፬) የተደነገገው የተሽከርካሪ አበል ለከተማ ምክር ቤት ምክትል አፈ-ጉባዔም ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

፬. በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፰ ንዑስ አንቀፅ (፩) (ሀ) /ለ/ /ሠ/፣ ንዑስ አንቀጽ /፫/ (ሀ) /ለ/ /መ/ እና ንኡስ አንቀጽ (፬) የተደነገገው የተሽከርካሪ አበል ለከተማ ምክር ቤት ፀሐፊ፣ ለከተማ ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ፣ ለክፍለ ከተማ ምክር ቤት አፈ-ጉባኤም ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**፲፯. የሕክምና አገልግሎት**

፩. በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፱ ንዑስ አንቀጽ (፩) ሥር የተደነገገው የሕክምና አገልግሎት ከሀላፊነት ለሚነሳ የከተማ ምክር ቤት አፈጉባኤም ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

፪. በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፱ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው የሕክምና አገልግሎት ከሀላፊነት ለሚነሳ የከተማ ምክር ቤት ምክትል አፈጉባኤ፣ ፀሐፊ፣ ለከተማ ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ፣ ለክፍለ ከተማ ምክር ቤት አፈጉባኤም ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ፲፰. የግል ደኅንነት ጥበቃ አገልግሎት

፩. የከተማው ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ ወይም ምክትል አፈ-ጉባኤ በኃላፊነት ላይ በነበረበት ወቅት የግል ደህንነት ጥበቃ ይደረግለት የነበረ ከሆነ ከኃላፊነት ሲነሳም ለራሱና ለቤተሰቡ ጥበቃ ይደረግላቸዋል፡፡

፪. የጥበቃ ኃይሉ ዓይነትና መጠን ጥበቃውን በሚያካሂደው አካል ይወስናል፡፡

## ፲፱.የሥራ ምደባ

፩. ከመመረጡ በፊት የመንግስት መስሪያ ቤት ወይም የመንግስት የልማት ድርጅት ሠራተኛ የነበረ በቋሚነት የሚሠራ የምክር ቤት አባል ከኃላፊነት ሲነሳ ወደ ቀድሞ ሥራው ለመመለስ ከጠየቀና አስተዳደሩ ከተስማማ ወደ ስራው እንዲመለስ ወይም የቀድሞ የሥራ ቦታው ክፍት ካልሆነ በተመሳሳይ የሥራ ቦታ ላይ እንዲመደብ ይደረጋል፡፡

፪. ከኃላፊነት የተነሳው በቋሚነት የሚሠራ የምክር ቤት አባል ቀድሞ በነበረበት የመንግስት መስሪያ ቤት ወይም የመንግስት የልማት ድርጅት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ሊመደብ ካልቻለ በሌላ የመንግስት መስሪያ ቤት ወይም የመንግስት የልማት ድርጅት በሚገኝ ተመሳሳይ ክፍት የሥራ ቦታ ላይ ሊመደብ ይችላል፡፡

፫. ከኃላፊነት የሚነሳው በቋሚነት የሚሠራ የምክር ቤት አባል በምክር ቤቱ ውስጥ ያገለገለበት ዘመን በተመደበበት የመንግስት መሥሪያ ቤት ወይም የልማት ድርጅት ውስጥ እንደተሰጠ አገልግሎት ይቆጠርለታል፡፡

፬. የዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (፩) እስከ (፫) ድንጋጌዎች በሹመት የሚያዙ ቦታዎችን በሚመለከት ተፈፃሚ አይሆኑም፡፡

## ፳. የአገልግሎት የምስክር ወረቀት

፩. ከኃላፊነት የተነሳ በቋሚነት የሚሠራ የምክር ቤት አባል እና ሌላ የከተማ ምክር ቤት አባል የአገልግሎት የምስክር ወረቀት ይሠጠዋል፡፡

፪. ከኃላፊነት ለሚነሳ አፈ-ጉባኤ፣ ምክትል አፈጉባኤ፣ የሚሰጥ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት በከተማ ከንቲባ፣ ከኃላፊነት ለሚነሳ በቋሚነት ለሚሰራ ሌላ የምክር ቤት አባል ወይም ለልሎች የምክር ቤት አባላት የሚሰጥ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት በአፈ-ጉባኤ ይፈረማል፡፡

፫. በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፩ ንዑስ አንቀጽ (፫) የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ከኃላፊነት የተነሳ ኃላፊ ስለሚያገኛቸው ጥቅሞች የተደነገጉት ከኃላፊነት ለሚነሳ በቋሚነት የሚሰራ የምክር ቤት አባልም ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**፳፩. የባለ መብቱ ከዚህ ዓለም በሞት መለየት**

፩. ማንኛውም በቋሚነት የሚሠራ የምክር ቤት አባል በሥራ ላይ እያለ ከዚህ ዓለም በሞት ቢለይ፡-

ሀ. ከሞቱ ጋር በተያያዘ ምክንያት ለሚከተሉ ወጭዎች መሸፈኛ የሦስት ወር ደመወዝ ለቤተሰቡ ይከፈላል፣

ለ. ከኃላፊነት ቢነሳ ኖሮ ሊከፈለው ወይም ሊሰጠው ይገባ የነበረው የመቋቋሚያ አበል፣ የሥራ ስንብት ክፍያ፣ የመኖሪያ ቤት አበል፣ የኪራይ መኖሪያ ቤት፣ የተሽከርካሪ አበል ወይም የተሽከርካሪ አገልግሎት ለቤተሰቡ ይከፈላል ወይም ይሰጣል፡፡

፪. ማንኛውም ባለመብት ከኃላፊነት ተነስቶ ጥቅሞቹን ከማግኘቱ በፊት ከዚህ ዓለም በሞት ቢለይ ሊከፈለው ወይም ሊሰጠው ይገባ የነበረው የመቋቋሚያ አበል፣ የሥራ ሥንብት ክፍያ፣ የኪራይ መኖሪያ ቤት፣ የመኖሪያ ቤት አበል፣ የተሽከርካሪ አበል ወይም የተሽከርካሪ አገልግሎት ለቤተሰቡ ይከፈላል ወይም ይሰጣል፡፡

፫. የከተማ ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ ወይም ምክትል አፈ-ጉባዔ ከዚህ ዓለም በሞት መለየት በዚህ አዋጅ መሠረት ቤተሰቡ በአገር ውስጥ ሊያገኝ የሚገባውን ሕክምና እንዲቋረጥ አያደርግም፡፡

፬. የከተማው ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ ወይም ምክትል አፈ-ጉባኤ በሥራ ላይ እያለ ወይም ከኃላፊነት ተነስቶ ከዚህ አለም በሞት ቢለይ፣

ሀ/ ዜና ዕረፍቱና አጭር የህይወት ታሪኩ በከተማው አስተዳደር የመገናኛ ብዙሀን ዘድዎች አማካኝነት ይነገራል፣ ለ/ የከተማው አስተዳደር ከፍተኛ ባለስልጣን በቀብሩ ሥነ-ሥርዓት ላይ ተገኝቶ የአበባ ጉንጉን ያስቀምጣል፣

ሐ/ የቀብሩ ሥነ-ሥርዓት ወጪ በከተማው አስተዳደር ይሸፈናል፡፡

፭. በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፩ ንዑስ አንቀጽ (፫) የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ከኃላፊነት የተነሳ ኃላፊ ስለሚያገኛቸው ጥቅሞች የተደነገጉት ከኃላፊነት ለሚነሳ በቋሚነት የሚሰራ የምክር ቤት አባልም ተፈፃሚ ይሆናል፡፡ ክፍል አራት ከኃላፊነት ስለሚነሱ የሕግ ተርጓሚ አካላት መብቶችና ጥቅሞች ዘርፍ አንድ ከኃላፊነት የሚነሳ የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት ወይም ምክትል ፕሬዚዳንት መብቶችና ጥቅሞች

**፳፪. የመቋቋሚያ አበል**

፩. የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ወይም ምክትል ፕሬዚዳንት፡-

ሀ/ ቢያንስ አምስት ዓመት አገልግሎ ከኃላፊነት ከተነሳ ወይም፣

ለ. ከሁለት ዓመት ተከሉ ያላነሰ ጊዜ አገልግሎ በህመም፣ በአካል ጉዳት ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ሌላ ምክንያት ከኃላፊነት ከተነሳ የመቋቋሚያ አበል ይከፈለዋል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚከፈለው የመቋቋሚያ አበል ለመጀመሪያው የአንድ አመት አገልግሎት የስድስት ወር (፮) ደመወዝ ሆኖ ከአንድ ዓመት በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የአንድ ወር ደመወዝ እየታከለ

ይታሰባል፡፡ ሆኖም ጠቅላላው የመቋቋሚያ አበል ክፍያ ከሀያ አራት ወር ደመወዝ መብለጥ የለበትም፡፡

**፷፫.ስለ ሥራ ስንብት ክፍያ**

በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፯ ከኃላፊነ ለሚነሱ ኃላፊዎች የስራ ስንብት ክፍያ የተደነገገው ከኃላፊነት ለተነሱ የከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ወይም ምክትል ፕሬዝዳንት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡ ሆኖም ባለመብቱ የተጠቀሰውን ክፍያ የሚያገኘው ወደ መንግስት ስራ የማይመለስ ሲሆን ብቻ ነው፡፡

**፷፬. የመኖሪያ ቤት አበል**

፩. ከኃላፊነት የሚነሳ የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ኘሬዚዳንት ወይም ምክትል ኘሬዚዳንት፡-

ሀ. ቢያንስ አምስት አመት አገልግሎ ከኃላፊነት ከተነሳ ወይም

ለ. ከሁለት ዓመት ተኩል ያላነሰ አገልግሎ በህመም፣ በአካል ጉዳት ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ሌላ ምክንያት ከኃላፊነት ከተነሳ፣ የመኖሪያ ቤት አበል ይከፈለዋል፤

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚከፈለው የመኖሪያ ቤት አበል በአንድ ጊዜ የሚከፈል ሆኖ መነሻው የስድስት ወራትሙሉ ክፍያ ሆኖ ከአምስት አመት በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የአንድ ወር ክፍያ አንድ ሁለተኛ እየታከለ ይሰላል፡፡

**፷፭. የተሽከርካሪ አበል**

፩. የከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ኘሬዚዳንት ወይም ምክትል ኘሬዚዳንት፡-

ሀ/ ቢያንስ አምስት ዓመት አገልግሎ ከኃላፊነት ከተነሳ፣ ወይም

ለ/ ከሁለት ዓመት ተኩል ያላነሰ ጊዜ አገልግሎ በሕመም፣ በአካል ጉዳት ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ሌላ ምክንያት ከኃላፊነት ከተነሳ የተሽከርካሪ አበል ይከፈለዋል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚከፈለው የተሽከርካሪ አበል በአንድ ጊዜ የሚከፈል ሆኖ መነሻው የስድስት ወራት ሙሉ ክፍያ ሆኖ ከአምስት አመት በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ አመት አገልግሎት የአንድ ወር ክፍያ አንድ ሁለተኛ እየታከለ ይሰላል፡፡ ሆኖም የሚሰጠው ጠቅላላ ክፍያ ከአስራ ስምንት ወር የተሽከርካሪ አበል መብለጥ የለበትም፡፡

**፷፮. የሕክምና አገልግሎት**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፱ ንኡስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው የህክምና አገልግሎት ከኃላፊነት የሚነሳ የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ኘሬዚዳንት ወይም ምክትል ኘሬዚዳንትም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**፳፯. የአገልግሎት የምስክር ወረቀት**

፩. ከኃላፊነት የሚነሳ የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ወይም ምክትል ፕሬዚዳንት የአገልግሎት ምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡-

፪. ከኃላፊነት ለሚነሳ የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ወይም ምክትል ፕሬዚዳንት የሚሰጠው የአገልግሎት የምስክር ወረቀት በከተማው አፈ-ጉባኤ የሚፈረም ይሆናል፡፡

፫. የአገልግሎት ምስክር ወረቀት የተሰጠው ከኃላፊነት የሚነሳ የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ወይም ምክትል ፕሬዚዳንት፡-

ሀ/ በከተማው አስተዳደር የመንግስት ጤና ድርጅቶች ለሚሰጠው የሕክምና አገልግሎት ቅድሚያ ያገኛል፣

ለ/ በሕዝባዊ ስብሰባዎች የክብር ቦታ ይሰጠዋል፣

**፳፰. የባለመብቱ ከዚህ ዓለም በሞት መለየት**

፩. የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ወይም ምክትል ፕሬዚዳንት በስራ ላይ እያለ ከዚህ ዓለም በሞት የተለየ እንደሆነ፡-

ሀ/ ከሞቱ ጋር በተያያዘ ምክንያት ለሚከተሉ ወጭዎች መሸፈኛ የሦስት ወር ሙሉ ደመወዝ ለቤተሰቡ ይከፈላል፤

ለ/ ከኃላፊነቱ ቢነሳ ኖሮ ሊከፈለው ይገባ የነበረው የመቋቋሚያ አበል፣ የሥራ ስንብት ክፍያ፣ የመኖሪያ ቤት አበል፣የተሽከርካሪ አበል ለቤተሰቡ ይከፈላል፡፡

፪. የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ወይም ምክትል ፕሬዚዳንት ከኃላፊነቱ ከተነሳ በኋላ ጥቅሞቹን ከማግኘቱ በፊት ከዚህ አለም በሞት ቢለይ ሊከፈለው ይገባ የነበረው የመቋቋሚያ አበል፣ የሥራ ስንብት ክፍያ፣ የመኖሪያ ቤት አበል የተሽከርካሪ አበል ለቤተሰቡ ይከፈላል፡፡

፫. የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ወይም ምክትል ፕሬዚዳንት ከዚህ አለም በሞት መለየት በዚህ አዋጅ መሠረት የተጠበቀለትን ቤተሰቡ በአገር ውስጥ የሕክምና አገልግሎት የማግኘት መብት እንዲቋረጥ አያደርግም፡፡

## ዘርፍ ሁለት

## ከኃላፊነት የሚነሳ የከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ፕሬዚዳንት፣ የከተማ ቦታ ማስለቀቅና ካሣ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ፕሬዚዳንት ወይም የከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ዳኛ መብቶችና ጥቅሞች

**፳፱. የመቋቋሚያ አበል**

፩. ከኃላፊነት የሚነሳ የከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት፣ የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ፕሬዚዳንት፣ የከተማ ቦታ ማስለቀቅና ካሣ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ፕሬዚደንት ወይም የከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ዳኛ፡-

ሀ. ቢያንስ አምስት ዓመት አገልግሎ ከኃላፊነት ከተነሳ፣ ወይም ለ. ከሁለት ዓመት ተኩል ያላነሰ ጊዜ አገልግሎ በህመም፣ በአካል ጉዳት ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ሌላ ምክንያት ከኃላፊነት ከተነሳ የመቋቋሚያ አበል ይከፈለዋል፤

## ፴. የሥራ ስንብት ክፍያ

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፺ ከኃላፊነት ስለተነሱ ኃላፊዎች የተደነገገው ከኃላፊነት ለሚነሳ የከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት፣ የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ፕሬዚዳንት፣ የከተማ ቦታ ማስለቀቅና ካሣ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ኘሬዚዳንት ወይም የከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ዳኛም ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ፴፩. የመኖሪያ ቤት አበል

፩. ከኃላፊነት የሚነሳ የከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት፣ የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ፕሬዚዳንት፣ የከተማ ቦታ ማስለቀቅና ካሣ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ኘሬዚደንት ወይም የከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ዳኛ፡-

ሀ/ ቢያንስ አምስት ዓመት አገልግሎ ከኃላፊነት ከተነሳ፣ ወይም

ለ/ ከሁለት ዓመት ተኩል ያላነሰ ጊዜ አገልግሎ በህመም፣ በአካል ጉዳት ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ሌላ ምክንያት ከኃላፊነት ከተነሳ፣ የመኖሪያ ቤት አበል ይከፈለዋል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚከፈለው የመኖሪያ ቤት አበል በአንድ ጊዜ የሚከፈል ሆኖ መነሻው የሶስት ወራት ሙሉ ክፍያ ሲሆን ከአምስት ዓመት በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ አመት አገልግሎት የአንድ ወር ክፍያ አንድ ሁለተኛ እየታከለ ይሰላል፡፡ ሆኖም የሚሰጠው ጠቅላላ ክፍያ ከአሥራ ስምንት ወራት የመኖሪያ ቤት አበል መብለጥ የለበትም፡፡

## ፪. የተሽከርካሪ አበል

፩. ከኃላፊነት የሚነሳ የከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት፣ የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ፕሬዚዳንት፣ የከተማ ቦታ ማስለቀቅና ካሣ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ኘሬዚደንት ወይም የከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ዳኛ፡-

ሀ/ ቢያንስ አምስት ዓመት አገልግሎ ከኃላፊነት ከተነሳ፣ ወይም

ለ/ ከሁለት ዓመት ተኩል ላላነሰ ጊዜ አገልግሎ በህመም፣ በአካል ጉዳት ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ሌላ ምክንያት ከኃላፊነት ከተነሳ የተሽከርካሪ አበል ይከፈለዋል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚከፈለው የተሽከርካሪ አበል በአንድ ጊዜ የሚከፈል ሆኖ መነሻው የሶስት ወራት ሙሉ አበል ሆኖ ከአምስት ዓመት በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የአንድ ወር ክፍያ አንድ ሁለተኛ እየታከለ ይሰላል፡፡ ሆኖም የሚሰጠው ጠቅላላ ክፍያ ከአስራ ስምንት (፲፰) ወር የተሽከርካሪ አበል መብለጥ የለበትም፡፡

## ፴፫. የአገልግሎት የምስክር ወረቀት

፩. ከኃላፊነት የሚነሳ የከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት፣ የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ፕሬዚዳንት፣ የከተማ ቦታ ማስለቀቅና ካሣ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ

ኘሬዚደንት ወይም የከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ዳኛ የአገልግሎት ምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡-

፪. ከኃላፊነት የሚነሳ የከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት፣ የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ፕሬዚዳንት፣ የከተማ ቦታ ማስለቀቅና ካሣ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ኘሬዚደንት ወይም የከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ዳኛ የሚሰጠው የአገልግሎት ምስክር ወረቀት በአስተዳደሩ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ኘሬዚደንት የሚፈረም ይሆናል፡፡

**፴፬.. የባለመብቱ ከዚህ ዓለም በሞት መለየት**

፩. ከኃላፊነት የሚነሳ የከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት፣ የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ፕሬዚዳንት፣ የከተማ ቦታ ማስለቀቅና ካሣ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ኘሬዚዳንት ወይም የከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ዳኛ በስራ ላይ እያለ ከዚህ ዓለም በሞት የተለየ እንደሆነ፡-

ሀ/ ከሞቱ ጋር በተያያዘ ምክንያት ለሚከተሉት ወጭዎች መሸፈኛ የሦስት ወር ሙሉ ደመወዝ ለቤተሰቡ ይከፈላል፣

ለ/ ከኃላፊነት ቢነሳ ኖሮ ሊከፈለው ይገባ የነበረው የመቋቋሚያ አበል፣ የሥራ ስንብት ክፍያና፣ የመኖሪያ ቤት አበል፣ የተሽከርካሪ አበል ለቤተሰቡ ይከፈላል፡፡

፪. ከኃላፊነት የሚነሳ የከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት፣ የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ፕሬዚዳንት፣ የከተማ ቦታ ማስለቀቅና ካሣ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ኘሬዚዳንት ወይም የከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ዳኛ ከኃላፊነቱ ከተነሳ በኋላ ጥቅሞቹን ከማግኘቱ በፊት ከዚህ ዓለም በሞት ቢለይ ከኃላፊነት ቢነሳ ኖሮ በዚህ አዋጅ መሰረት ሊከፈለው ይገባ የነበረው የመቋቋሚያ አበል፣ የሥራ ስንብት ክፍያ፣ የመኖሪያ ቤት አበል፣ የተሽከርካሪ አበል ለቤተሰቡ ይከፈላል፡፡

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፴፭. የመኖሪያ ቤት አበልና የተሽከርካሪ አበል ግምት**

፩. የሚከፈለው የመኖሪያ ቤት አበል ተመን የወቅቱን የመኖሪያ ቤት ኪራይ ዋጋ መጠን ግምት ውስጥ በማስገባት የከተማ አስተዳደር ካቢኔ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፤

፪. የሚከፈል የተሽከርካሪ አበል ተመን የወቅቱን የነዳጅ፣ የቅባት፣ የዘይት፣ የጥገናና ተሽከርካሪ ለማንቀሳቀስ፣ የሚያስፈልጉ ልሎች ወጪዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት የአዲስ አበባ የከተማ አስተዳደር ካቢኔ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

**፴፮.የአገልግሎት ዘመን አቆጣጠርና የመብቶች ግንኙነት**

፩. የከተማ የበላይ ኃላፊ፣ የከተማ ከፍተኛ ኃላፊ ወይም ሌላ ኃላፊ ከመሾሙ በፊት በምክር ቤት አባልነቱ ምክንያት በከፍተኛ ኃላፊነት /በተሿሚነት/ የሰጠው አገልግሎት ቢኖር በዚህ አዋጅ መሠረት ለሚያዝ አገልግሎት ይታሰብለታል፣

፪. ከኃላፊነት የሚነሳ የከተማዉ ምክር ቤት አፈጉባኤ፣ ምክትል አፈጉባኤ፣ ፀሐፊ፣ የቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ወይም የክፍለ ከተማ አፈ-ጉባኤ እንዲሁም በተመሳሳይ ደረጃ ላይ ያለ ተሿሚ ለተጠቀሰው ኃላፊነት ከመመረጡ በፊት በከፍተኛ የመንግስት ኃላፊነት የሰጠው አገልግሎት ቢኖር በዚህ አዋጅ መሠረት ለሚያዘው አገልግሎት ይታሰብለታል፡፡

፫. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) እና (፪) መሠረት ከኃላፊነት የሚነሳ ሀላፊ ለተጠቀሰው ኃላፊነት ከመሾሙ ወይም ከመመረጡ በፊት በፌድራሉ መንግስት ከፍተኛ የሥራ ኃላፊነት፣ በፌድሬሽን ምክር ቤት ወይም በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባልነት የሰጠው አገልግሎት በዚህ አዋጅ መሠረት ለሚያዘው አገልግሎት ይታሰብለታል፡፡

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩፣ ፪ እና ፫ ድንጋጌዎች ሥር የተጠቀሰው የቀድሞ አገልግሎት በዚህ አዋጅ ወይም አግባብ ባላቸው ልሎች ሕጐች መሠረት ለባለመብቱ አስቀድሞ መብቶችና ጥቅሞች አስገኝቶለት ከሆነ በዚህ አዋጅ መሠረት እንደ አዲስ በሚያዝለት አገልግሎት ውስጥ የሚታሰብ አይሆንም፡፡

፭. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩፣ ፪ እና ፫ ድንጋጌዎች ሥር የተጠቀሰው የቀድሞ አገልግሎት የተሻለ መብትና ጥቅም የሚያስገኝ ከሆነ ባለመብቱ ይህንኑ የተሻለውን መብትና ጥቅም እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡

፮. በአንድ ጊዜ የምክር ቤት አባልና ከፍተኛ የመንግስት ሥራ ኃላፊ የነበረ ባለመብት በምክር ቤት አባልነቱና በከፍተኛ የመንግስት ኃላፊነቱ የሚያገኛቸው መብቶችና ጥቅሞች መካከል የሚበልጠውን ያገኛል፡፡

፯. ከኃላፊነት የሚነሳ ባለመብት በተለያዩ የኃላፊነት ደረጃዎች ላይ ተመድቦ አገልግሎት ይሰጥ ከነበረ በማናቸውም ጊዜ ተመድቦበት ለነበረው ከፍተኛ የኃላፊነት ደረጃ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚሰጠው መብትና ጥቅም ይጠበቁለታል፡፡

**፴፯. መብቶችና ጥቅሞችን ስለሚያሳጡ ሁኔታዎች**

፩. የከተማ የበላይ ኃላፊ፣ የከተማ ከፍተኛ ኃላፊ ወይም ሌላ ኃላፊ በሚከተሉት ምክንያቶች ከኃላፊነቱ ሲነሳ በዚህ አዋጅ መሠረት ተፈቅደው የሚሰጡትን መብቶችና ጥቅሞች አያገኝም፡-

ሀ/የመንግስት ፖሊሲዎችን ባለመፈፀሙ ወይም ባለማስፈፀም፣

ለ/ በስልጣኑ ያለአግባብ በመገልገሉ፣

ሐ/ የሙስና ተግባር በመፈፀሙ፣

መ/ ሚስጥራዊ መረጃዎችን ላልተፈቀደለት ወገን በመግለጹ ወይም አሳልፎ በመስጠቱ ወይም

ሠ/ በወንጀል ወይም በዲሲፕሊን ኃላፊነት የሚያስጠይቅ ማናቸውንም ሌላ ድርጊት በመፈፀሙ፡፡

፪. የከተማው ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ፣ ምክትል አፈ-ጉባኤ፣ ፀሐፊ፤ የቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ፣ ሌላ የከተማ ምክር ቤቱ አባል፣ እንዲሁም የክፍለ ከተማ ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ በሚከተሉት ምክንያቶች ከኃላፊነት ወይም ከምክር ቤት አባልነት የተወገደ እንደሆነ በዚህ አዋጅ መሠረት ተፈቅደው የሚሠጡትን መብቶችና ጥቅሞች አያገኝም፡-

ሀ/ የመራጮችን አመኔታ በማጣቱ ወይም

ለ/ በስነ-ምግባር ረገድ ይወክላልሹ ሆኖ በመገኘቱ፡፡

፫. ባለመብቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ድንጌዎች ሥር በተጠቀሰው መሰረት ተገቢውን ሥርዓት ሳይከተል ኃላፊነቱን በገዛ ፈቃድ የለቀቀ ወይም የተወ ከሆነ በዚህ አዋጅ መሠረት የተፈቀዱለትን መብቶችና ጥቅሞች አያገኝም፡፡

<u>፴፰.መብቶችና ጥቅሞችን የሚያቋርጡ ሁኔታዎች</u>

፩. በዚህ አዋጅ መሠረት የተገኙ መብቶችና ጥቅሞች የመኖሪያ ቤት ኪራይን ሳይጨምር በሚከተሉት ምክንያቶች ሊቋረጡ ይችላሉ፡-

ሀ/ ባለመብቱ ሕገ መንግስታዊ ሥርዓቱን ለማፍረስ ከሞከረ፣

ለ/ የሐገርን ሉዓላዊነት አደጋ ላይ በሚጥል ተግባር ላይ ተሰማርቶ ወይም ተሣትፎ ከተገኘ፣

ሐ/ የሀገር ክህደት ወንጀል ከፈፀመ፣

መ/ በኃላፊነት ላይ በነበረበት ወቅት ያገኛቸውን የከተማ አስተዳደሩንም ሆነ ሀገራዊ ጉዳዮች በሚመለከቱ ሚስጥራዊ መረጃዎችን ካልጠበቀ ወይም፣

ሠ/ ሕገ መንግስቱንና በሕገ መንግስቱ መሠረት የተቋቋሙትን ተቋሚት ካላከበረ፣

ረ/ ከኃላፊነት የተነሳ ዳኛ በጥብቅና ሥራ ላይ የተሠማራ ከሆነ፡፡

ሰ/ ከኃላፊነት የተነሳ የከተማው አስተዳደር ከፍተኛ ሀላፊ ሥልጣኑን ከለቀቀበት ጊዜጀምሮ ሁለት ዓመት ሣይሞላው ቀድሞ ሲመራው ከነበረው የመንግስት መስሪያ ቤት ጋር ቀጥታ ግንኙነት ባለው የግል ድርጅት ወይም መንግስታዊ ባልሆነ ዓለም አቀፍ ድርጅት ወይም መንግስታዊ ባልሆነ ድርጅት ውስጥ ተቀጥሮ ከተገኘ፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከፊደል ተራ (ሀ-ሠ) መሠረት መብቶችና ጥቅሞች የሚቋረጡት ባለመብቱ ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት የጥፋተኘነት ውሳኔ ከተሰጠበት በኋላ እንደአግባብነቱ በከተማው ወይም በክፍለ ከተማ ምክር ቤት ቀርቦ ሲፀድቅ ይሆናል፣

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ፊደል ተራ (ረ) እና (ሰ) መሠረት ጥቅሞች የሚቋረጡት ባለመብቱ ጥፋተኛ መሆኑ ስልጣን ባለው አካል ከተጣራ በኋላ በከተማው ምክር ቤት ቀርቦ ውሳኔ ሲያገኝ ይሆናል፡፡

፬. በዚህ አዋጅ መሠረት በተሰጠው መብት ወይም ጥቅም ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ለመገልገል የማይፈልግ ባለመብት ይህንኑ ለሚመለከተዉ አካል በጽሁፍ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

**፲፱. ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም ኃላፊነት የተሰጣቸው አካላት**

፩. ከኃላፊነት ለሚነሱ የከተማው አስተዳደር የሥራ ኃላፊዎች የከንቲባ ጽህፈት ቤት፣

፪. ከኃላፊነት ለሚነሱ የከተማ ሕግ አውጭ ኃላፊዎችና ተመራጮች የከተማ ምክር ቤት ጽህፈት ቤት፣

፫. ከኃላፊነት ለሚነሱ የሕግ ተርጓሚ ኃላፊዎችና ተሿሚዎች በከተማዉ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት፣

፬. እያንዳንዳቸው የሚቀርቡት የተጠቃሚነት ጥያቄና የሚያገኙት ጥቅማጥቅም በከተማው አስተዳደር በፐብሊክ ሰርቪሱና የሰው ኃብት ልማት ቢሮ እና በፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ አማካኝነት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**፳. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

የከተማው አስተዳደር ካቢኔ ይህንን አዋጅ በተሟላ ሁኔታ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉትን ደንቦችና መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፳፩. የተሻሩና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች**

፩. ከኃላፊነት የሚነሱ የአዲስ አበባ ከተማ መሪዎች፣ ከፍተኛ ኃላፊዎች፣ በቋሚነት የሚሠሩ የምክር ቤት አባላትና ዳኞች የሚያገ?ቸውን መብቶችና ጥቅሞች ለመወሠን የወጣ አዋጅ ቁጥር ፴፮/፲፱፻፺፬ በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

፪. ይህንን አዋጅ የሚቃረኑ ማናቸውም የከተማው አስተዳደር ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ እና የተለመደ አሠራር በዚህ አዋጅ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

**፳፪. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሐምሌ ፳ ቀን ፲፱፻፺፲ ዓ.ም
ድረባ ኩማ
የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መደበኛ ያልሆነ የንግድ ሥራ ለመምራትና ሥርዓት ለማስያዝ የወጣ ደንብ፻፷/፪ሺ፱

ማውጫ


፩. አጭር ርዕስ
፪. ትርጓሜ
፫. አላማ
፬.የተፈፃሚነት ወሰን
፭. መዝገብ ስለማቋቋም
፮. ስለመመዝገብ
፯.የምዝገባ መስፈርት
፰. ስለምዝገባ ማመልከቻና ውሳኔ አሰጣጥ
፱ የምዝገባ መረጃዎችን ስለማስተላለፍ
፲.እውቅና ስለመስጠት
፲፩.ስለምዝገባ ለውጥ ወይም ማሻሻያ
፲፪.ምትክ ደረት ላይ የሚንጠለጠል የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያ ስለመስጠት
፲፫.ከመዝገብ ስለመሰረዝ እና አስተዳደራዊ እርምጃ ስለመውሰድ
፲፬.የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያ አሠጣጥ
፲፭.በተመዘጋቢ የሚሠራ መደበኛ ያልሆነ የንግድ ሥራ ዝርዝር
፲፮.ደረት ላይ ስለሚንጠለጠል የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ እና እድሳት
፲፯.የተመዘገበና ተንጠልጣይ የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያ የተሰጠው ሰው መብትና ግዴታ
፲፰.ድጋፍና ቁጥጥር ስለማድረግ
፲፱.የክፍያ መጠን
፳.ከቢሮው ጋር በመተባበር ይህን ደንብ የሚያስፈጽመው አስፈፃሚ አካላት ዝርዝር፣ ተግባር እና ኃላፊነት
፫.የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ቢሮ፡-
፫. የትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ፡-
፬. ፭.የአዲስ አበባ መንገዶች ባለሥልጣን፡-

፮.የደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽሕፈት ቤት፡-
፯.አዲስ አበባ ከተማ ፖሊስ ኮሚሽን፡-
፰.የጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ፡-
፱.የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ፡-
፲.የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ፡-
፲፩.የምግብ፣ የመድሃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን፡-
፲፪.የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ባለሥልጣን፡-
፳፩.አስተዳደራዊ እርምጃ
፳፪.በአስተዳደራዊ እርምጃዎች ላይ ቅሬታ ስለማቅረብ


<u>አጭር መግለጫ</u>

በዚህ አይነት የንግድ ሥራ ውስጥ የተሠማሩ ዜጎች ለራሳቸው የሥራ ዕድል ፈጥረው በመገኘታቸው እና የንግዱ አካሄድ የህጋዊ ነጋዴዎችን ገበያ በማይሻማ መልኩ ሥርአት በማስያዝ በቀጣይ ወደ መደበኛ የንግድ ሥርዓት የሚሸጋገሩበት መንገድ ማመቻቸት ለማስቻል የወጣ ህግ ነው፡፡

## <u>የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መደበኛ ያልሆነ የንግድ ሥራ ለመምራትና ሥርዓት ለማስያዝ የወጣ ደንብ ፰/፪ሺ፱</u>

በከተማችን በመካሄድ ላይ ያለው መደበኛ ያልሆነ የንግድ እንቅስቃሴ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተስፋፋ በመምጣቱ በዘርፉ በርካታ ሰዎች በተለይም ወጣቶችና ሴቶች ሲሳተፉበት በመታየቱ፤

በዚህ አይነት የንግድ ሥራ ውስጥ የተሠማሩ ዜጎች ለራሳቸው የሥራ ዕድል ፈጥረው በመገኘታቸው እና የንግዱ አካሄድ የህጋዊ ነጋዴዎችን ገበያ በማይሻማ መልኩ ሥርአት በማስያዝ በቀጣይ ወደ መደበኛ የንግድ ሥርዓት የሚሸጋገሩበት መንገድ ማመቻቸት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ዘርፉ በግብይት ሥርአቱ ውስጥ ሕጋዊ እውቅና ተሰጥቶት በሥርዓት መምራት በማስፈለጉ፤ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፷፫ንዑስ አንቀፅ (፩) (ረ)እና በአዲስአበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚና ማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፴፭/፪ሺ፬ (እንደተሻሻለ) አንቀፅ ፹፬መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

### <u>ክፍል አንድ</u>

### <u>ጠቅላላ ድንጋጌ</u>

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ ደንብ ‹‹የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መደበኛ ያልሆነ ንግድ ሥራ ለመምራትና ሥርዓት ለማስያዝ የወጣ ደንብ ቁጥር ፹፰/፪ሺ፱ዓ.ም››ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. <u>ትርጓሜ</u>**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡

፩ ‹‹**አስተዳደር**››ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፪ ‹‹**የንግድ ሕግ**›› ማለት በ፲፱፻፶፪ ዓመተ ምህረት የወጣው የንግድ ሕግ ነው፤

፫ ‹‹**አዋጅ**›› ማለት የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር ፱፻፹/፪ሺ፰ ነው፤

፬ ‹‹**ቢሮ**›› ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የንግድ ቢሮ ነው፤

፭ ‹‹**የክፍለ ከተማ ጽሕፈት ቤት**››ማለት በአስተዳደሩ አደረጃጀት መሠረት በሁለተኛ የእርከን ደረጃ የሚገኝ የንግድ ጽህፈት ቤት ነው፤

፮. ‹‹**የወረዳ ጽሕፈት ቤት**››ማለት በአስተዳደሩ አደረጃጀት መሠረት በሶስተኛ የእርከን ደረጃ የሚገኝ የንግድ ጽህፈት ቤት ነው፤

፯. ‹‹**መደበኛ ያልሆነ ነጋዴ**›› ማለት በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ መሠረት ያልተመዘገበና የንግድ ፈቃድ የሌለው መደበኛ ያልሆነ ንግድ ሥራ ላይ የተሠማራ ወይም ለመሠማራት

የሚፈልግ እስከ ብር ፲ሺ. /አሥር ሺ. ብር/ ካፒታል ያለው ይህን ደንብና አግባብነት ያላቸውን ህጎች አክብሮ ለመሥራት ፈቃደኛ የሆነ ሰው ነው፤

፰. ‹‹**መደበኛ ያልሆነ የንግድ ሥራ**›› ማለት በመደበኛው የንግድ ህግ ወይም አዋጅ የማይመራ ቀላል የንግድ ሥራ ሲሆን ግለሰቡ በአዋጁ መሠረት ሳይመዘገብና የንግድ ሥራ ፈቃድ ሳያወጣ ወይም ቋሚ የንግድ ቤት ወይም ቦታ ሣይኖረው በዚህ ደንብ መሠረት በጎዳና፣ በአደባባይ በከፊል በየመንገዱ ዳርቻ በሚገኝ ትንንሽ ተለጣፊ እና ተንጠልጣይ የዕቃ መደርደርያ ይዞ እስከ ብር ፲ሺ. /አሥር ሺህ ብር/የሚገመት በአነስተኛ ካፒታል የሚሠራ የንግድ ሥራ አይነት ነው፡፡ ሆኖም በግብርና፣ በእደ-ጥበብ የተሠማሩ ሰዎች ምርታቸውን ቢሸጡ ይህ ትርጉም አይመለከታቸውም፤

፱. ‹‹**መዝገብ**›› ማለት መደበኛ ያልሆነ የንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩ ሰዎች የሚመዘገቡበት በቢሮው የሚዘጋጅ ዋና ወይም ባህረ መዝገብ ነው፤

፲. ‹‹**ቋሚ የንግድ ቦታ**›› ማለት ተለይቶ ለንግድ የተመደበ ወይም የተዘጋጀ ለንግድ ሥራ ቀን፣ ሰዓት እና የሥራ ዘርፍ (መስክ) ፕሮግራም የወጣለትና በዚሁ መሠረት ሳይቋረጥ ቦታው ለልማት እስኪፈለግ ድረስ መደበኛ ያልሆነ ንግድ ሥራ የሚካሄድበት ቦታ ነው፤

፲፩. ‹‹**ጊዜያዊ የመነገጃ ቦታ**›› ማለት ለንግድ ሥራ ቀንና ሰዓት ፕሮግራም ያልተያዘለት የንግድ ዘርፍ ወጥቶለት ለዚሁ ተብሎ በሚዘጋጁ ጎዳናዎች አደባባዮች በጊዜያዊነት መደበኛ ያልሆነ ንግድ የሚካሄድበት ቦታ ነው፤

፲፪.‹‹**መደበኛ ያልሆነ ጽዳት**›› ማለት የጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ በመደበኛነት በዕቅድ ከሚያፀዳቸው የተለያዩ ቦታዎች፣ ጎዳናዎች፣ መንገዶች፣ ደሴቶች በተለየ ሁኔታ መደበኛ ያልሆነ ንግድ የሚካሄድባቸውን ሥፍራዎች በሙሉ ሥራውን ተከትሎ ግብይቱ በተወሠነለት ዕለትና ሠዓት ከተከናወነ በኋላ በልዩ ሁኔታ የሚካሄድ የጽዳት ሥራ ነው፤

፲፫.‹‹**በማዕከል የሚካሄድ ድጋፍ እና ቁጥጥር**›› ማለት መደበኛ ያልሆኑ የንግድ ሥራ እንዲካሄድ በተፈቀደበት ቦታ፣ ጎዳና፣ መንገድ፣ ደሴት ውስጥ የሚደረግ ድጋፍ እና ቁጥጥር ነው፤

፲፬. ‹‹**ከማዕከል ውጪ የሚካሄድ ድጋፍና ቁጥጥር**››ማለት መደበኛ ያልሆነ የንግድ ሥራ እንዲካሄድ ከተፈቀደበት ቦታ፣ ጎዳና፣ መንገድ፣ ደሴት ውጪ ባልተፈቀደ ቦታ የሚካሄድ ድጋፍ እና ቁጥጥር ነው፤

፲፭.‹‹**የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያ**›› ማለት በደረት ላይ የሚንጠለጠል ሆኖ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፰ በተተረጎመው መሠረት መደበኛ ያልሆነ የንግድ ሥራ ለሚሠራ መደበኛ ያልሆነ ነጋዴ በበጀት አመቱ የተሰጠ ወይም የታደሰ ወይም በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፯ መሠረት ያለቅጣት የሚታደስበት ጊዜ ያላላፈበት የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያ ወይም መለያ ነው፤

፲፮.‹‹**አስተዳደራዊ እርምጃ**››ማለት ይህን ደንብና አግባብነት ያላቸው መመሪያዎች ተላልፎ በሚገኝ መደበኛ ያልሆነ ነጋዴ ላይ እንደአስፈላጊነቱ በቢሮው ወይም በክፍለ ከተማው ጽሕፈት ቤት ወይም በወረዳው ጽሕፈት ቤትአማካይነት ከቃል ማስጠንቀቂያ ጀምሮ የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያ እስከ መሠረዝ የሚወሰድ እርምጃ ነው፡፡

**<u>፫. አላማ</u>**

**የዚህ ደንብ ዓላማ፡-**

፩. መደበኛላልሆነየንግድሥራ እውቅና በመስጠት የሥራው ዘርፍ የሚመራበትን ስርዓት በማዘጋጀት ለኢኮኖሚውና ለማኅበራዊ እንቅስቃሴ አጋዥ እንዲሆን ማስቻል፤

፪. በዘርፉየሚታዩት ችግሮች ለማስወገድና ድጋፍ በማድረግ በቀጣይ ወደ መደበኛ ንግድ ስርዓት እንዲገባ ማስቻል ነው፡፡

**<u>፬.የተፈፃሚነት ወሰን</u>**

ይህ ደንብ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክልል ውስጥ መደበኛ ባልሆነ የንግድ ሥራላይ በተሠማራ ማንኛውም ሰው ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>ስለ ምዝገባ</u>

**<u>፭. መዝገብ ስለማቋቋም</u>**

፩. በቢሮው የሚተዳደር ከተማ አቀፍ ተፈፃሚነት ያለው መደበኛ ባልሆነ ንግድ ሥራ ላይ የተሠማራ ማንኛውም ሰው የሚመዘገብበት መዝገብ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪. ቢሮው በዚህ ደንብ መሠረት በአስተዳደሩ ውስጥ የሚገኝ መደበኛ ባልሆነ ንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ማናቸውንም ሰው ይመዘግባል፡፡

**<u>፮. ስለመመዝገብ</u>**

፩. ማንኛውም ሰው በመዝገብ ሳይመዘገብ በአስተዳደሩ ክልል ውስጥ በየትኛውም ቦታ መደበኛ ባልሆነ ንግድ ሥራ ላይ መሰማራት አይችልም፡፡

፪. ማንኛውም ሰው በመዝገብ የሚመዘገበው በሚሠራበት አካባቢ በሚገኝ የወረዳ ጽሕፈት ቤት ነው፡፡

፫. ማንኛውምሰው በመዝገብ የሚመዘገበው አንድ ጊዜ ብቻ ነው፡፡

**<u>፯.የምዝገባ መስፈርት</u>**

መደበኛ ባልሆነ የንግድ ሥራ ላይ ለመሰማራት የሚፈልግ አመልካች የሚከተሉትን ሰነዶች ከማመልከቻው ቅጽ ጋር በማያያዝ በሚሠራበት አካባቢ በሚገኝ የወረዳ ጽሕፈት ቤት ማቅረብ አለበት፡፡

፩. አመልካቹ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ የተነሳው ፪ (ሁለት) ጉርድ ፎቶ ግራፍ፤

፪. አመልካቹ በአስተዳደሩ ውስጥ ከሚኖርበት ወረዳ የታደሰ የነዋሪነት መታወቂያ ወረቀት፤

፫. ከግብር ሰብሳቢው መስሪያ ቤት የተሰጠ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፤ እና

፬. አመልካቹ በአሁኑ ወቅት በመደበኛ ንግድ ሥራ ላይ ወይም ሌላ ማንኛውም ሥራ ላይ ያልተሠማራ ሥራ አጥ መሆኑን በአስተዳደሩ ውስጥ ከሚኖርበት ወረዳ አስተዳደር ጽሕፈት ቤት የጽሁፍ ማስረጃ፡፡

፭. አመልካቹ ይህን ደንብ እና ደንቡን ተከትሎ የሚወጣውን መመሪያ አክብሮ ለመሥራት ፈቃደኛ መሆኑን በሚያቀርበው ማመልከቻ ላይ ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

**፰. <u>ስለምዝገባ ማመልከቻና ውሳኔ አሰጣጥ</u>**

፩. ማንኛውም መደበኛ ባልሆነ ንግድ ሥራ ላይ ለመሰማራት የሚፈልግ ሰው ሥራ ከመጀመሩ በፊት ቢሮው ያዘጋጀውን የማመልከቻ ቅጽ በመሙላት በዚህ ደንብ አንቀጽ ፯ ላይ የተጠቀሱትን ማስረጃዎች በማያያዝ ለወረዳው ጽሕፈት ቤት ማቅረብ አለበት፡፡

፪. ማናቸውምለምዝገባየቀረበማመልከቻተቀባይነትያለውሆኖከተገኘ የወረዳው ጽሕፈት ቤት በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፱(፩) መሠረት የተወሰነውን ክፍያ በማስከፈል መዝግቦ መደበኛ ያልሆነ ነጋዴ ደረት ላይ የሚንጠለጠል የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያ ይሰጠዋል፡፡

፫. ቢሮው ለምዝገባ አገልግሎት የሚውሉ ወጥ ቅፆችን ያዘጋጃል፤በክፍለ ከተማ ጽሕፈት ቤት አማካይነት ለወረዳ ጽሕፈት ቤት እንዲዳረስ ያደርጋል፡፡

፬. ማንኛውምበመደበኛየንግድሥራላይየተሰማራ ሰው ወይም በአዋጁ መሠረት በንግድ መዝገብ የተመዘገበ ነጋዴ በዚህ መዝገብ መመዝገብ የተከለከለ ነው፡፡

**፱. <u>የምዝገባ መረጃዎችን ስለማስተላለፍ</u>**

፩. በዚህ ደንብ መሠረት ምዝገባ ያደረገ የወረዳ ጽሕፈት ቤት ለዚህ ጉዳይ በሚዘጋጅ ቅጽ አማካይነት የምዘገባ መረጃዎችን በየዕለቱ ለክፍለ ከተማ ጽህፈት ቤት ያስተላልፋል፣ የክፍለ ከተማ ጽሕፈት ቤት በሁለተኛው ቀን ለቢሮው ያስተላልፋል፡፡

፪. ቢሮውበዚህአንቀጽንዑስአንቀጽ፩ መሠረት የተላለፈለትን የምዝገባ መረጃዎች በዚህ ደንብ አንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሠረት መዝግቦ ይይዛል፡፡ እንደ አስፈላጊነቱ በሚዘጋጅ ሶፍትዌር ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ላይ ይመዘግባል፡፡

**፲.<u>እውቅና ስለመስጠት</u>**

በዚህ ደንብ መሠረት ተመዝግቦ ደረት ላይ የሚንጠለጠል የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያ የተሰጠው ማንኛውም ሰው ሕጋዊ ሆኖ አንስተኛ የንግድ ሥራ የሚሠራ መሆኑ በዚህ ደንብ መሰረት እውቅና ተሰጥቶታል፡፡

**፲፩.ስለምዝገባ ለውጥ ወይም ማሻሻያ**

፩. ማንኛውም ሰው የንግድ ሥራውን ለማካሄድ ከተመዘገበበት እና ከተመደበበት የሥራ ቦታ አካባቢ ወደ ሌላ የሥራ ቦታ አካባቢ ለመለወጥ ከፈለገ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፯ ንዑስ አንቀፅ (፪) እና ፰ ንዑስ አንቀፅ (፪) መሠረት በቅድሚያ ያደረገውን ምዝገባ ማሰረዝና ከወረዳው ጽሕፈት ቤት የተሰጠውን ደረት ላይ የሚንጠለጠል የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያ ለወረዳው ጽሕፈት ቤት መመለስ፣ በቀጣይ መሸኛ ወረቀት በመውሰድ ወደ መረጠው አካባቢ የሚገኝ የወረዳ ጽሕፈት ቤት በመሄድ መሸኛውን በማቅረብ ሌላ ደረት ላይ የሚንጠለጠል የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያ በመውሰድ መነገድ ይችላል፡፡

፪. ማንኛውምሰው ተመዝግቦ የሚሰራውን የንግድ መስክ አይነት መለወጥ ወይም ማሻሻል ከፈለገ የተመዘገበበት ወረዳ ጽሕፈት ቤት በመቅረብ በቢሮው የተዘጋጀውን ቅጽ በመሙላት የሚሠራውን የንግድ መስክ አይነት መለወጥ ወይም ማሻሻል ይችላል፡፡

፫. የምዝገባ ለውጥ ወይም ማሻሻያ ስለመቅረቡ እና ተቀባይነት ስለማግኘቱ የወረዳው ጽሕፈት ቤት ማረጋገጫ መስጠትና እና ተቀባይነት ያገኘበትን ቀን፣ ስለምዝገባው ለውጥ ወይም ማሻሻያ በዝርዝር በመግለጽ ለአመልካቹ እና ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡ ይህ የጽሑፍ ማረጋገጫ ካልተሰጠ በስተቀር የቀረበው የምዝገባ ለውጥ ወይም ማሻሻያ እንደተለወጠ ወይም እንደተሻሻለ አይቆጠርም፡፡

**፲፪.ምትክ ደረት ላይ የሚንጠለጠል የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያ ስለመስጠት**

፩.መደበኛ ያልሆነ ንግድ ሥራ ምዝገባ ያደረገ ማንኛውም ሰው የተሰጠው የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያ የጠፋበት ወይም የተበላሸበት ከሆነ ቀደም ሲልለሰጠው የወረዳ ጽሕፈት ቤት በጽሑፍ በማመልከት ምትክ የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያ ማግኘት ይችላል፡፡

፪.የሽግግርጊዜፈቃድ ወይም መታወቂያ የተበላሸበት ማንኛውም ሰው ምትክ እንዲሰጠው ሲጠይቅ የተበላሸውን ይመልሳል፡፡

፫.ወረዳው ማመልከቻ ሲቀርብለት ለጠፋው ወይም ለተበላሸው የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያ በዚህ ደንብ በደንብ የተመለከተውን ክፍያ በማስከፈል ምትክ ፈቃድ ወይም መታወቂያ ይሰጣል፡፡

**፲፫. ከመዝገብ ስለመሰረዝ እና አስተዳደራዊ እርምጃ ስለመውሰድ**

መደበኛ ባልሆነ ንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሰው በሚከተሉት ምክንያቶች ከመዝገብ ይሰረዛል፤

፩.የንግድ ሥራውን ከተወ፤

፪.ከሞተ፤

፫.ሐሰተኛ መረጃ ወይም ሰነድ አቅርቦ መመዝገቡ ከተረጋገጠ፤

፬.ከተፈቀደለትና በመታወቂያው ላይ ከተገለጸው ቦታ ወይም ቀን ወይም ሰዓት ወይም መደበኛ ያልሆነ ንግድ ሥራ ውጪ ወይም ባልተፈቀደ ሥራ ላይ ተሠማርቶ ከተገኘ፣

፭.ቢሮው ወይም የወረዳጽሕፈት ቤቱየሚጠይቃቸውን መረጃዎች በትክክል እና በወቅቱ ያላቀረበ እንደሆነ፣

፮.የሸማቹን የጤናና የጽዳት አጠባባቅ፣ የአካባቢ እንክብካቤ፣ የንግድ ዕቃውን ጥራት ወይም አይነት ደረጃ ካጓደለ ወይም ሌላ ሕገ ወጥ ተግባር ከፈጸመ ወይም በኮንትሮባንድ የገቡ ዕቃዎች ወይም የራሱ ያልሆነውን በአዋጁ መሠረት በመደበኛ ንግድ ሥራ ላይ የተሠማራ ነጋዴ ዕቃ ይዞ ከተገኘ፣

፯.ደረት ላይ የሚንጠለጠል የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሠረት ካልታደሰ፣

፰.ሸማቹን በማታለል ወይም በማሳሳት ተግባር ላይ ከተገኘ ወይም በማንኛውም ሌላ ሁኔታ ይህን ደንብ የጣሰ እንደሆነ፣ቢሮው አጥፊውን ከመዝገብ ይሰርዛል፡፡ አጥፊውም ቢሮው የሰጠውን ደረት ላይ የሚንጠለጠል የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያ ተመላሽ ያደርጋል፡፡

## ክፍል ሦስት

## የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያ አሠጣጥ

### ፲፬.የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያ አሠጣጥ

፩.በዚህ ደንብ መሠረት መደበኛ ያልሆነ ንግድ ሥራ ላይ የተሰማራን ሰው የመመዝገብና ደረት ላይ የሚንጠለጠል የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያ የመስጠት ሥልጣን የቢሮው ነው፣

፪.ቢሮው በሚሰጠው ውክልና መሠረት የወረዳ ጽሕፈት ቤት በዚህ ደንብ መሠረት መደበኛ ያልሆነ ንግድ ሥራ ላይ የተሠማራን ሰው ይመዘግባል፣ ደረት ላይ የሚንጠለጠል የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ቁጥጥርና ድጋፍ ያደርጋል፣ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፣ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም የሰጠውን የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያ ያግዳል፣ ይሠርዛል፡፡

### ፲፭.በተመዝጋቢ የሚሠራ መደበኛ ያልሆነ የንግድ ሥራ ዝርዝር

መደበኛ ባልሆነ ንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ሰው የሚሠራው መደበኛ ያልሆነ የንግድ የሥራ አይነት፣ የሥራ መስክ ወይም የሥራ ዘርፍ ዝርዝር በሕግ የተፈቀደ መሆን ይገበዋል፡፡ በተጨማሪም ይህ አይነቱ የንግድ ሥራ የሙያ ብቃት መረጋገጫና መስፈርት የማያስፈልገው የንግድ ሥራ አይነት መሆን አለበት፣ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የሚያስፈልገው መደበኛ ያልሆነ የንግድ ሥራ ከሆነ ግን ማረጋገጫውን ማቅረብ አለበት፡፡

## ፲፮. ደረት ላይ ስለሚንጠለጠል የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ እና እድሳት

፩.በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲ንዑስ አንቀፅ (፪) መሠረት የተሰጠ የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፫በተዘረዘሩት ምክንያቶች ካልተሠረዘ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሠረት እስከታደሰ ድረስ የፀና ይሆናል፡፡

፪.መደበኛ ባልሆነ ንግድ ሥራ ላይ ለተሰማራ ማንኛውም ሰው የተሰጠውን ደረት ላይ ተንጠልጣይ የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያ የበጀት አመት ካበቃ በኋላ ባለው ፮ ወራት ጊዜ ውስጥ ማለትም ከሐምሌ ፩ ቀን ጀምሮ እስከ ታህሣሥ ፴ ቀን ድረስ ከግብር አስከፋይ መስሪያ ቤት ክሊራንስ በማቅረብ እና በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፱ንዑስ አንቀፅ (፪) መሠረት ተገቢው ክፍያ ተከፍሎ በየአመቱ በመዝጋቢው አካል መታደስ አለበት፡፡

፫.በዚህአንቀጽንዑስአንቀጽ (፩) በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ደረት ላይ ተንጠልጣይ የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያውን ሳያድስ የቀረ ሰው በሚቀጥሉት ስድስት ወራት ውስጥ ማለትም ከጥር ፩ ቀን እስከ ሰኔ ፴ ድረስ ባሉት ወራት የመደበኛ የሽግግር ፈቃድ ወይም መታወቂያ ማሳደሻ ክፍያ እጥፍ ብር ፻ /አንድ መቶ ብር/ በመክፈል ፈቃዱን ማደስ ይችላል፡፡

፬.በዚህአንቀጽ መሠረት የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያውን ያላሳደሰ ሰው ከመዝገብ ይሰረዛል፡፡ ተመዝጋቢው የተሰጠውን ደረት ላይ የሚንጠለጠል የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይምመታወቂያ መመለስ አለበት፡፡ ካይመልስ ቢቀር በእጁ እንዳለ እንደተሠረዘ ይቆጠራል፡፡

## ፲፯.የተመዘገበና ተንጠልጣይ የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያ የተሰጠው ሰው መብትና ግዴታ

ማንኛውም በዚህ ደንብ መሰረት የተመዘገበና ተንጠልጣይ የሽግግር ጊዜ ፈቃድወይም መታወቂያ የተሰጠው ሰው፡-

**፩.መብቶች**

ሀ. በመዝገብ ያስመዘገበውን እና የተፈቀደለትን መደበኛ ያልሆነ የንግድ ሥራ ማካሄድ፤ የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያ መውሰድ፤

ለ. የተሰጠው የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ቢጠፋ ወይም ቢበላሽ ምትክ መውሰድ፤

ሐ. የሚነግደውን መደበኛ ያልሆነ የንግድ ሥራ ዘርፍ እና የሚነግድበት ቦታ ወይም አካባቢ ለወረዳው ጽሕፈት ቤት አሳውቆ የመለወጥ፣ የማሻሻል፤

**፪. ግዴታዎች እና ክልከላዎች**

ሀ. በዚህ ደንብ መሠረት በውክልና መመዝገብም ሆነ ምዝገባውን ማደስ የተከለከለ ነው፤

ለ. ወረዳው በተፈቀደለትና በመደበው ቦታ፣ ዕለት፣ሰዓት፣እና የሥራ ዘርፍ ላይ ብቻ መሥራት አለበት፤

ሐ. መደበኛ ላልሆነንግድ ሥራ የሚይዛቸው ዕቃዎችንጥራት፣ መጠን፣ ይዘት መለወጥ ወይም ማጓደል፣ ሸማቹን እና ተጠቃሚውን ማጉላላት የለበትም፤

መ. መደበኛ ላልሆነ ንግድ ሥራ የሚይዛቸውን የኢንዱስትሪ ምርቶች፣ የገዛበትን ህጋዊ ደረሠኝ ማቅረብ አለበት፤

ሠ. ለሸማቹና ለተጠቃሚው ተገቢውን ክብር መስጠት አለበት፤
የተሳሳቱ ወይም ተመሳስለው የተሰሩ ምርቶችን መሸጥ የለበትም፤

ሰ. የብቃት ማረጋገጫ ወይም መስፈርት የሚያስፈልጋቸውን ምርቶች መያዝ የለበትም፤

ሸ. ከመዝጋቢው አካል የተሰጠውን ተንጠልጣይ መለያ ወይም መታወቂያ በሥራ ላይ በሚሆንበት ጊዜ አንገቱ ላይ በማጥለቅ በግልጽ እንዲታይ ማድረግ፤

ቀ. የተሰጠውን ተንጠልጣይ የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያ እንዳይበላሽ በጥንቃቄ መያዝ፤ለሌላ ሰው አሳልፎ መስጠት የለበትም፤

በ. በመዝጋቢው አካል መረጃ ሲጠየቅ መረጃውን ወዲያው መስጠት አለበት፤

ተ. መደበኛ ያልሆነንግድ ሥራውን ሲጨርስ አካባቢውን በአግባቡ ማጽዳት አለበት፤

ቸ. የአካባቢውን ንጽህና፣ ፀጥታና ደህንነት መጠበቅ አለበት፤

ኀ. ባልተፈቀደ ቦታ መነገድና የትራፊክ እንቅስቃሴ ማወክ የለበትም፤

ነ. በዚህ ደንብ መሠረት የተመዘገበ ሰው በአዋጁ መሠረት መመዝገብና የንግድ ፈቃድ ማውጣት የለበትም፡፡

__፲፰.ድጋፍና ቁጥጥር ስለማድረግ__

፩.የወረዳው ቁጥጥር ባለሙያዎች የተመዘገበና ደረት ላይ የሚንጠለጠል የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያ የተሰጠው ሰው ግዴታዎቹን በትክክል መወጣቱንና በዚህ ደንብ መሠረት ሥራው መካሄዱን ለማረጋገጥ ድጋፍና ቁጥጥር ያደርጋሉ፡፡

፪.ቢሮውወይም ጽሕፈት ቤት ለቁጥጥር ሥራ የሚያሠማራው የቁጥጥር ሠራተኛ የተሰጠውን የመስሪያ ቤት መታወቂያ መደበኛ ያልሆነ ንግድ ሥራ ላይ ለተሰማራው ሠው በቅድሚ ማሳየት ይኖርበታል፡፡

## __ክፍል አራት__
## __የክፍያ መጠንና የባለ ድርሻ አካላት ሚና__

__፲፱.የክፍያ መጠን__

፩.ማንኛውም መደበኛ ያልሆነ ንግድ ሥራ መዝገብ ላይ ለመመዝገብ እና ደረት ላይ የሚንጠለጠል የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያ የሚወስድ ሰው ለምዝገባና ለመታወቂያ አገልግሎት ብር ፸ /ሰባ ብር/ ይከፍላል፡፡

፪.ማንኛውም መደበኛ ያልሆነ ንግድ ሥራ መዝገብ ላይ የተመዘገበና ደረት ላይ የሚንጠለጠል የሽግግር ጊዜ ወይም መታወቂያ የወሰደ ሰው ተንጠልጣይ የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያውን ለማሳደስ ብር ፶ /ሃምሳ ብር/ ይከፍላል፡፡

__፳.ከቢሮው ጋር በመተባበር ይህን ደንብ የሚያስፈጽመው አስፈፃሚ አካላት ዝርዝር፣ ተግባር እና ኃላፊነት__

፩.ከዚህ በታች የተጠቀሱት የከተማው አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት በቢሮው አስተባባሪነት በጋራ እና በቅንጅት ይሠራሉ፣

ሀ.የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ቢሮ፤

ለ. የትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ፤

ሐ.የአዲስ አበባ መንገዶች ባለሥልጣን፤

መ.የደንብ ማስከር አገልግሎት ጽህፈት ቤት፤

ሠ.የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን፤
ረ.የጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ፤
ሰ.የኮሙኒዩኬሽን ጉዳዮች ቢሮ፤
ሸ. የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ፤
ቀ. የምግብ፣ የመድሀኒትናየጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን፤
በ. የአዲስ አበባ ከተማ ገቢዎች ባለሥልጣን፡፡

፪.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተመለከቱት የከተማው አስፈፃሚ አካላት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚና ማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፴፭/፪ሺ፬(እንደተሻሻለ) የተሰጣቸው ስልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ ደንብ ውስጥ እንደ የድርሻቸው የሚከተሉትንተግባራት ይፈፅማሉ፡፡

**<u>፫.የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ቢሮ፡-</u>**

የመነገጃ ቦታ ዝግጅት በተመለከተ የከተማው ፕላን በሚፈቅደው የመሬት አጠቃቀምና አግባብ ያላቸው ሕጎችን መሠረት በማድረግ በዚህ ደንብ መሠረት መደበኛ ወዳልሆነንግድ ለሚገቡ ሰዎች ቋሚና ጊዚያዊ የመነገጃ ቦታዎች በማጥናት ይለያል፣ የመነገጃ ቦታ ያዘጋጃል፣ ይመድባል፣ ከቢሮው ጋር በመሆን መደበኛ ባልሆነ ንግድ ሥራ ላይለሚሠማሩ ሰዎች የሥራ ቦታ ይፈቅዳል፡፡

**<u>፬. የትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ፡-</u>**

ከከተማው የትራንስፖርትእና የትራፊክ እንቅስቃሴ ጋር አጣጥሞ መደበኛ ያልሆኑ ንግድ ሥራዎች የሚካሄዱባቸውን አካባቢዎች የመለየት ሥራ ይሠራል፤ አጠቃቀሙን ከቢሮው ጋር በጋራ ይሠራል፡፡

**<u>፭.የአዲስ አበባ መንገዶች ባለሥልጣን፡-</u>**

በከተማው ውስጥ የሚገኙ መንገዶችን ደረጃ በማውጣት በአካባቢው የሚገኙ የመንግስት፣ የሕዝብ፣ የአለም አቀፍ ተቋማት እና ልዩ የሥራ ባህሪ ያላቸው ሥፍራዎችን በመለየት መደበኛ ላልሆነ ንግድ ሥራ የተከለከለ፣ በከፊል የተፈቀደ እና የተፈቀደ በማለት ይለያል፡፡ የለያቸውን ጎዳናዎች፣ መንገዶች፣ ደሴቶች ለቢሮው፣ ለፖሊስ ኮሚሽን፣ ለደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽሕፈት ቤት፣ ለጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ በጽሑፍ ያሳውቃል፡፡

**<u>፮.የደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽሕፈት ቤት፡-</u>**

ሀ. ከማዕከል ውጪ የሚካሄድ የንግድ ቁጥጥር ያካሂዳል፤
ለ. በዚህ ደንብ መሠረት የፀና የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያ ያልያዘ ሰው በማንኛውም ባልተፈቀደ ቦታ የንግድ ሥራ እንዳያከናውን ይከላከላል፡፡

**<u>፯.አዲስ አበባ ከተማ ፖሊስ ኮሚሽን፡-</u>**

በሌላሕግ የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተለውን ተግባር ያከናውናል፡-
ሀ. በዚህ ደንብ መሠረት የሚነግድ ሰው በደረት ላይ የሚንጠለጠል የሽግግር ጊዜ ፈቃድ ወይም መታወቂያ ያለው መሆኑን ያረጋግጣል፤
ለ. ከተፈቀደለት አካባቢ ወይም ንግድ ሥራ ወይም ከተፈቀደለት ቀንና ሰዓት ውጪ የንግድ ሥራ ያለመስራቱንና የትራፊክ እንቅስቃሴ ያለማወኩን ይቆጣጠራል፤
ሐ.መደበኛ ያልሆነ የንግድ እንቅስቃሴ የሚካሄድበትን አካባቢ ሰላምና ፀጥታ መጠበቁን ይቆጣጠራል፡፡

**፰.የጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ፡-**

ኤጀንሲው ልዩ የጽዳት ፕሮግራም በማውጣት በዚህ ደንብ መሠረት መደበኛ ያልሆነ ንግድ የሚካሄድባቸውን መንገዶችና አካባቢዎች መደበኛ የጽዳት ሥራ ጊዜውን ሳይጠብቅ ጽዳት ያካሂዳል፡፡

**፱.የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ፡-**

ቢሮው በዚህ ደንብ መሠረት ስለመደበኛ ያልሆነ የንግድ ሥራ ሕጋዊነትና አሠራር ለህብረተሰቡ ግንዛቤ መፍጠር የሚያስችሉ ሥራዎች ይሠራል፡፡

**፲.የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ፡-**

ቢሮው በዚህ ደንብ መሠረት መደበኛ ያልሆነ የንግድ ሥራ ላይ ለተሰማሩ የህብረተሰብ ክፍሎች፡-

ሀ. የተለያዩ ሥልጠናዎችን በመስጠት እና የገንዘብ ቁጠባ ባህላቸውን አዳብረው  ወደ መደበኛው የንግድ ሥራ እንዲሸጋገሩ ያደርጋል፤

ለ. የፋይናንስና ብድር አገልግሎት የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል

**፲፩.የምግብ፣ የመድሃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን፡-**

ባለሥልጣኑ በዚህ ደንብ መሠረት የሚከናወኑ መደበኛ ያልሆኑ የንግድ ሥራዎችን አስመልክቶ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ከምግብ እና ከጤና እንክብካቤ ጋር በተያያዘ አስፈላጊውን ቁጥጥር ያደርጋል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል፡፡

**፲፪.የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ባለሥልጣን፡-**

ባለሥልጣኑ በዚህ ደንብ መሰረት፡-

ሀ. መደበኛ ባልሆነ የንግድ ሥራ ላይ የተሠማሩ ሠዎች መክፈል ያለባቸውን ግብር ይወስናል፤ ይሠበስባል፤ የግብር ግዴታቸውን ለተወጡት ክሊራንስ ይሰጣል፤

ለ.መደበኛ ባልሆነ የንግድ ሥራ ላይየተሰማሩ ሰዎች የኮንትሮባንድ ዕቃዎችን እንዳይነግዱ ይከላከላል፤ ይቆጣጠራል፤ ህጋዊ እርምጃም ይወስዳል፡፡

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፳፩.አስተዳደራዊ እርምጃ**

፩.ይህን ደንብ ጥሶ የሚገኝ ማንኛውም መደበኛ ያልሆነ ንግድ ሥራ መዝገብ ላይ ተመዝግቦ የሚገኝ ሰው እንደጉዳዩ አግባብ በቢሮው የሚወሰድበት አስተዳደራዊ እርምጃ እንደተጠበቀ ሆኖ አግባብ ባለው የወንጀል ሕግ ድንጋጌ መሠረት ይቀጣል፡፡

፪.በዚህ ደንብ አንቀጽ፮ ንዑስ አንቀጽ ፩ እና አንቀጽ ፲፯ ንዑስ አንቀጽ ፪ እና ፫ ላይ የተጠቀሰውን ተላልፎ በየትኛውም አካባቢ ወይም ሥፍራ መደበኛ ባልሆነ ንግድ ሥራ ላይ ተሰማርቶ የሚገኝ ሰው አግባብ ባለው የወንጀል ሕግ ይቀጣል፤ ይዞት የሚገኘው ንብረት ወይም ዕቃ ተሽጦ ለመንግስት ገቢ ይሆናል፡፡

**፳፪.  በአስተዳደራዊ እርምጃዎች ላይ ቅሬታ ስለማቅረብ**

በዚህ ደንብ መሠረት በክፍለ ከተማው ወይም በወረዳው ጽሕፈት ቤት አስተዳደራዊ እርምጃ ወይም ቅጣት የተወሰደበት ማንኛውም ሰው እርምጃው ወይም ቅጣቱ ከተፈጸመበት ቀን ጀምሮ ባሉት ፲፭የሥራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን በአስተዳደራዊ እርከን ደረጃ ተዋረዱንበመጠበቅ ለወረዳው ጽሕፈት ቤት፣ ለክፍለ ከተማው ጽሕፈት ቤት ወይም ለቢሮው አቤቱታ በጽሑፍ

ሊያቀርብ ይችላል፡፡ አቤቱታ የቀረበለት አካል በ፲(አስር) የሥራ ቀናት ውስጥ ለቀረበለት አቤቱታ መልስ በጽሑፍ ለአቤቱታ አቅራቢው ማሣወቅ አለበት፡፡

**፳፫.ደንቡንስለማሻሻል**

ካቢኔው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህን ደንብ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

**፳፬.ተጠያቂ ስለመሆን**

በዚህ ደንብ የተጣለበትን ኃላፊነትና ግዴታ ያልተወጣ ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

**፳፭.የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰው ይህን ደንብ ለማስፈጸም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

**፳፮.መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

ቢሮውይህን ደንብ ለማስፈጸም የሚረዳ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፳፯.ተፈፃሚነት ስለሚኖራቸው ህጐች**

ይህን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም የከተማው አስተዳደር ደንብ ወይም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

**፳፰.ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ ከነሐሴ ፬ ቀን ፪ሺ፱ዓመተ ምህረት ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ነሐሴ ፬ ቀን ፪ሺ፱ ዓመተ ምህረት**

**ድሪባ ኩማ**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኮንስትራክሽን ባለሙያዎች የስነምግባር ደንብ አጭር መግለጫ
## ፻፪/፪ሺ፲

**ማውጫ**

1. **ክፍል አንድ ጠቅላላ**
2. **ክፍል ሁለት ድንጋጌዎች**
3. ክፍል ሶስት እርምጃ አወሳሰድ

**አጭር መግለጫ**

**በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ የኮንስትራክሽን ዘርፍ የተሰማሩ አካላትን የሙያ ስነ ምግባር የሚወስን እና የሚታዩ የስነምግባር ብልሹነቶች ለማረም የተዘጋጀ ደንብ፡፡**

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኮንስትራክሽን ባለሙያዎች የስነምግባር ደንብ ፻፪/፪ሺ፲

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚና ማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፴፭/፪ሺ፬ ዓ.ም (እንደተሻሻለ) አንቀፅ ፹፬ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ

፩. አጭር ርእስ

ይህ ደንብ ‹‹የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኮንስትራክሽን ባለሙያዎች የስነምግባር ደንብ ቁጥር ፻፪/፪ሺ፲ ዓ.ም›› ተብሎ ሊጠቀስ ይቻላል፡፡

፪. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩. ‹‹ከተማ›› ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፪.‹‹ባለሙያ›› ማለት በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ተሳታፊ የሆነ ባለሙያ ማለትም መሀንዲስ፣ የኪነ ህንጻ ባለሙያ፣ ቀያሽ፣ የንድፍ ስራ ባለሙያ…ወዘተ ነው፤

፫. ‹‹የዲዛይን ባለሙያ›› ማለት በአማካሪዎች እና ባለሙያዎች መመሪያ ቁጥር ፳፪ በተጠቀሰው መሰረት ስራውን የሚያከናውን የኪነ ህንጻ ባለሙያ፣ የስትራክቸራል መሀንዲስ፣ የሳኒተሪ መሃንዲስ፣ የኤሌክትሪካልና ኔትወርክ መሃንዲስ፣ ሜካኒካል መሃንዲስ፣ ወይም ባለሙያ መሀንዲስ ነው፤

፬.‹‹ቀጥተኛ ቁጥጥር›› ማለት በተመዘገበና ፈቃድ ባለው መሀንዲስ ቁጥጥር ስር የሚዘጋጅ ስራ ወይም አንድ ብቃቱ የተረጋገጠ መሀንዲስ ወይንም ጥልቅ የሆነ እውቀት ባለው መሃንዲስ ክትትል የተሰራ ስራ ነው፤

፭. ‹‹ተለማማጅ መሀንዲስ›› ማለት ብቃት ላለው ምህንድስና ፍቃድ የታጨ እና በተለማማጅ መሀንዲስነት የሚሰራ ሰው ነው፤

፮. ‹‹የሙያ ፈቃድ›› ማለት በኢፌድሪ ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የሚሰጥ ህጋዊ ሰነድ ነው፡፡

፯. ‹‹ሙያዊ የምህንድስና ስራ ላይ የሚከሰት ቸልተኝነት›› ማለት ከሙያው በሚጠበቀው ሙያዊ ግዴታ፣ ክህሎት እና ውሳኔ እንዲሁም ትኩረት መሰረት ባደረገ መልኩ በሙያው መስራት አለመቻል ነው፤

፰. ‹‹ብቁ መሀንዲስ›› ማለት በሀገሪቱ ህግጋት መሰረት የምህንድስና ሙያን እንዲሰራ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ነው፤

፱. ‹‹ብቃት ያለው የምህንድስና ስራ›› ማለት በምህንድስና ስራ ሙያ ትምህርት ስልጠና እና ልምድ አማካይነት የዳበረን የሙያ እውቀት፣ ክህሎት፣ ችሎታ እና የሙያ ግምት አወሳሰድ መሰረት አድርጎ ሳይንስን በኢንጂነሪንግ ስርአቶች እና መዋቅሮች ላይ መጠቀም ነው፤

፲. ‹‹የባለሙያ ምህንድስና ስራ›› ማለት የማቴሪያሎችን ዲዛይን እና መረጣን በተመለከተ ሀሳብ የማመንጨት ፣ የመፈተሽ ፤ የመገምገም፣ የማቀድ ፣ የማማከር ሲሆን ይህም እንደዚህ ዓይነት የማማከር፣ ሀሳብ የማመንጨት፣ የማጣራት፣ የመመዘን፣ የማቀድ፣ ዲዛይን የማድረግ፣ መረጣ የማካሄድ፣ የማስተዳደር ወይም የአካል ቅኝት የማከናወን የምህንድስና ህግጋት እውቀትን፣

ቀመሮችን፣ ማቴሪያሎችን፣ ልምድን እና የግንባታ ዘዴዎችን በሚጠይቁ ስራዎች ላይ የግንባታ ውሎችን ማስተዳደር፣ የሳይት ላይ ቁጥጥር ስራ ማከናወን ወዘተ ነው፤

፲፩. ‹‹ጉባኤ›› ማለት በዚህ ደንብ መሰረት የተቋቋመ የስነ ምግባር ኮሚቴ ነው፤

፲፪. ‹‹አጣሪ ኮሚቴ›› ማለት በዚህ ደንብ መሠረት የተቋቋመ የስነምግባር ጉባኤ ነው፤

፲፫. ‹‹የይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ›› ማለት በዚህ ደንብ መሰረት የተቋቋመ የይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ ነው፤

፲፬. ‹‹እገዳ›› ማለት በተወሰነ ጊዜ ከከተማው የባለሙያዎች ምዝገባ ዝርዝር መዝገብ ለተወሰነ ጊዜ መታገድ ነው፤

፲፭. ‹‹ቢሮ›› ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኮንስትራክሽን ቢሮ ነው፤

፲፮. ‹‹አጭር ምዝገባ›› የፌደራልን የሙያ ፈቃድ በመያዝ በቢሮዉ የሚካሄድ ምዝገባ ነዉ፤

፲፯. በዚህ ደንብ ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

፫. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ ደንብ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ በኮንስትራክሽን ዘርፍ በተሰማሩ ባለሙያዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

፭. አላማ

፩.ማህበረሰቡን የማገልገል ራእይ እንዲይዙ ማድረግ፤

፪. እንዲሁም ከሙያ ተግባር የሚጠበቁ መሰረታዊ መርሆዎችን ማስቀመጥ፤

፫.ሙያዊ ስነምግባርንና ሙያዊ ያልሆነ ተግባርን ለመለየትና በህግ ጉዳዩን ለመመርመር የሚያስችል አሰራር ሂደትን ማስጠበቅ፤

፬. የህብረተሰቡን ደህንነት መጠበቅና እና ከፍተኛ ስታንዳርድ ያለው ሙያዊ ጽናት እና ተግባርን ማበረታታት፡

## ክፍል ሁለት
## ድንጋጌዎች

፮. መሰረታዊ መርሆች

፩. ዕውቀታቸውንና ክህሎታቸውን ለሰብአዊ ፍጡርና ለአካባቢያቸው ደህንነት ሲል የበለጠ መሥራት፤

፪. ከውስጥ በሆነ ሀቀኝነት አድሎዖ ሳያደርግ ሕዝብን፤ ተቋሙንና ደንበኛን ማገልገል፤

፫. ባለሙያ ለሚሠራው ወይም ለሚያደርጋት ሥራ ኃላፊነት መውሰድ፤

፬. የሙያ ብቃትና ክብር ለማሳደግ መነሳሳት/መጣር፤

፭. ሕብረተሰቡን በሙያውና በቴክኒክ ዲሲፒሊን እንዲኖረው ማገዝ ይጠበቅበታል፡፡

፯. መሰረታዊ ህጎች

፩. የህዝብ ደህንነትእናጤና

ማንኛውም ባለሙያ፡-

ሀ) የአጠቃላይ ህዝቡ ህይወት፣ ጤና እና ደህንነት በባለሙያው የግል ሙያዊ አስተያየት እና ውሳኔ የተመሰረቱ መሆናቸዉን እውቅና ሊሰጥ ይገባል፤

ለ) ተቀባይነት ባላቸው የምህንድስና ስታንዳርዶች መሰረት በተዘጋጁና ለህዝብ ጤና እና ደህንነት ተስማሚ መሆናቸው በተረጋገጠላቸውና በራሳቸው የተመረመሩ የዲዛይን ሰነዶች ብቻ ማጽደቅ አለበት፤

ሐ) ቀድሞ የገመተው ሙያዊ ግምት እውን ሳይሆን ሲቀር እና የህዝቡ ጤና እና ደህንነት ለአደጋ ሲጋለጥ ሁኔታዎቹ ሊያስከትሉት የሚችሉትን ውጤቶች በተመለከተ ለደንበኞች እና አሰሪዎች ማሳወቅ አለበት፤

መ) በዚህ ደንብ የሰፈሩ ማናቸውም ድንጋጌዎች ሲጣሱ ለሚመለከተው ባለስልጣን በጽሁፍ ማሳወቅ እና ተጨማሪ መረጃ ወይም እገዛ ለመስጠት መተባበር አለበት፤

ሠ) በሲቪክ ጉዳዮች ላይ ገንቢ አገልግሎት ለመስጠት እንዲሁም የማህበረሰቡን ደህንነት እና ጤና ደረጃ ከፍ ለማድረግ እና አስተማማኝ በሆነ የልማት ስራ አማካኝነት አካባቢን ለመጠበቅ የሚያስችሉ አጋጣሚዎች መፈለግና መተግበር ይኖርበታል፤

ረ) የህዝቡን አጠቃላይ የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል አስተማማኝ የልማት መርህን በመከተል አካባቢን ለማሻሻል መትጋት ይጠበቅበታል፡፡

፪. <u>ስለሙያብቃትናኃላፊነት</u>

ማንኛውም ባለሙያ፡-

ሀ) አንድን የምህንድስናን ስራ የሚያከናውነው በሚመለከተው የምህንድስና ዘርፍ በትምህርት ወይም በቴክኒክ ልምድ ብቁ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው፤

ለ) በትምህርትም ሆነ በልምድ አማካኝነት ብቁ ያልሆኑባቸውን ጉዳዮች በያዙ የምህንድስና ፕላን ወይም ሰነድ ወይም በኃላፊነታቸው ስር ባልተመረመሩ እና ባልተዘጋጁ ሰነዶች ላይ ፊርማም ሆነ ማህተም ማስፈር የለበትም፤

ሐ) ሕብረተሰቡ ስለ ምህንድስና እና አስተማማኝ ልማት ዕውቀት እንዲኖረው የሚተጋ ከመሆኑም በተጨማሪ ስለ ምህንድስና የተሳሳቱ ፣ ፍትሃዊ ያልሆኑ እና የተጋነኑ መረጃዎችን በማስራጨት ተግባር ላይ መሳተፍ የለበትም፡

መ) ከሙያው ጋር የተገናኙ ሪፖርቶች፣ መግለጫዎች እና ምስክርነቶች በእውነታው ላይ የተመሰረቱ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

ሠ) በበቂ ዕውቀት ላይ የተመሰረተ እና በሙያው ብቃት ያለው የቴክኒክ ዕውቀት ሲኖረው እና የቴክኒክ ጉዳይ ምስክርነት ሲጠየቅ ብቻ የምህንድስና አስተያየት መስጠት ይኖርበታል፤

ረ) መረጃው በማን በኩል እንደተሰራ በግልጽ እስካልተገለጸ ድረስ ለሌሎች አካላት ጥቅም ወይም ለክፍያ ብሎ ማናቸውንም መግለጫዎች፣ ሂሶች ወይም ምህንድስናን የተመለከቱ ክርክሮችን ማቅረብ አይኖርበትም፤

ሰ) ስራውን በተገቢው እና በትክክለኛ መንገድ ማብራራት እንዲሁም የሙያውን ክብር፣ ዋጋ እና ተቀባይነት በሚያሳጣ መልኩ የግል ጥቅም ለማግኘት ተብሎ ከሚፈጸም ተግባር መቆጠብ ይኖርበታል፡፡

፫. <u>ለእያንዳንዱ አሰሪም ሆነ ደንበኛ ሙያዊ ባህሪን በተላበሰ መልኩ ተግባርን መፈጸም</u>

ማንኛውም ባለሙያ፡-

ሀ) ማናቸውንም የሚያውቀውን እና ከአሰሪው ወይም ከደንበኛው ጋር የጥቅም ግጭት ሊፈጥሩ የሚችሉ ሁኔታዎችን ማለትም አገልግሎቱን በሚሰጥበት ወቅት የአገልግሎቱ ጥራት ወይም የግል ውሳኔው ላይ ተፅእኖ የሚያሳድሩ ሁኔታዎች ሲከሰቱ ለአሰሪው ወይም ለደንበኛው ወዲያውኑ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

ለ) በአንድ ፕሮጀክት ላይ ለሚሰጠው አገልግሎት ክፍያን በተመለከተ ያሉ ሁኔታዎች በሙሉ ለሚመለከታቸው አካላት ተገልጸው ስምምነት ላይ እስካልተደረሰ ድረስ በፕሮጀክቱ ወይም

ከዚያው ፕሮጀክት ጋር ለተያያዙ አገልግሎቶች ከአንድ ወገን ብቻ ክፍያን መቀበል ይኖርበታል፤

ሐ) ከአሰሪዎች ወይም ከደንበኛው ጋር ከሚሰሩ ተቋራጮች፣ ወኪሎቻቸው ወይም ሌሎች ወገኖች ማናቸውንም ተጨማሪ ክፍያም ሆነ ሌላ ጥቅም መቀበል ወይም መጠየቅ የለበትም፤

መ) የመንግስት መስሪያ ቤት አማካሪ፣ አባል ወይም ሰራተኛ ከሆነ በሚመለከተው አካል እስካልተፈቀደለት ድረስ ባለሙያው በግልም ሆነ በመንግስት የምህንድስና ስራዎች ላይ በሚሰጡ በግል ድርጅት አገልግሎቶች ላይ ምንም አይነት ተሳትፎ ማድረግ አይኖርበትም፤

ሠ) ባለሙያው ባከናውነው ጥናት መሰረት የታቀደው ፕሮጀክት ስኬታማ እንደማይሆን ካረጋገጠ ይህንኑ ለአሰሪው ወይም ለደንበኞቹ ማሳወቅ ይኖርበታል፤

ረ) በተሰጠው ኃላፊነት ምክንያት የሚያገኘውን ምስጢራዊ መረጃ መጠቀም በደንበኞች፣ በአሰሪዎች ወይም በህብረተሰቡ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያመጣ ከሆነ መረጃዎቹን ለግል ጥቅሙ ማዋል የለበትም፤

ሰ) ማንኛዉም ተቀጣሪ ከመደበኛ ስራው ውጭ ዋናው ቀጣሪ ሳይፈቅድ ሌላ የባለሙያ ሥራ ቅጥር መቀበል አይችልም።

፬. ሙያዊ መልካም ስም እና ፍትሃዊ የሆነ ውድድር

ማንኛውም ባለሙያ፡-

ሀ) አንድ ስራን ለማግኘት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ማናቸውንም ጥቅሞች መደለያዎች ወይም ህገወጥ ክፍያዎችን አይሰጥም፣ አያግባባም ወይም አይቀበልም፤

ለ) የሙያ አገልግሎት ውል ላይ ተግባራዊ በሆነ ብቃት እንዲሁም ለተፈለገው የባለሙያ አገልግሎት አስፈላጊው የትምህርት ደረጃ መሰረት በማድረግ ፍትሃዊ የሆነ ድርድር ማድረግ ይኖርበታል፤

ሐ) በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በቢሮው ፤ አሰራርውና አግባብ ባለው ህግ መሰረት ባለሙያው የሚሰጠውን ሙያዊና ትክክለኛ ውሳኔዎችን የማይሸረሽር ሲሆን ብቻ ባለሙያው ለሰጠው አገልግሎት ክፍያ መጠየቅ ወይም መቀበል ይችላል፤

መ) የትምህርት ማስረጃውንም ሆነ የስራ ልምዱን አሳስቶ ማቅረብ የለበትም፤

ሠ) ዕውቅና ለሚያስፈልጋቸው ሙያዊ ሥራዎች ተገቢውን ዕውቅና መስጠት ይኖርበታል፤ እንዲሁም ለሌሎች ስራዎች ባለቤትነት መብት ዕውቅና መስጠት ይኖርበታል፤ አስፈላጊ ሆኖም ሲገኝ የዲዛይን ሥራዎች፣ የፈጠራ ሥራዎች፣ በጽሁፍ የተዘጋጁ ሰነዶች፣ ወይም ሌሎች ስራዎችን የሰሩና ውጤቶችን ያመጡ ባለሙዎችን ስም መግለጽ ይኖርበታል፤

ረ) የባለሙያ አገልግሎቶችን ማስተዋወቅ ሲፈልግ ምንም አይነት አሳሳች ቋንቋም ሆነ በማንኛውም መልኩ የሙያውን ክብር ዝቅ የሚያደርግ ይዘት በሌለው መልኩ ማድረግ ይኖርበታል፣

ሸ) የማንኛውንም ባለሙያ ሙያዊ ሥራዎችን ፣ ተግባራትን ወይም ቅጥርን በተንኮልም ይሁን በሀሰት፣ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንቀፍ አይኖርበትም፤

ቀ) ያለአሰሪው ፍቃድ የአሰሪውን መገልገያም ሆነ መሳሪያ፣ የላብራቶሪም ሆነ የቢሮ ዕቃዎችን ለግል ሥራው ማዋል የለበትም፡፡

፭. ታማኝነትና የሙያ ክብርን ማጎልበት

ማንኛውም ባለሙያ፡-

ሀ) ሆን ብሎ በሙያ ማጭበርበር፣ እምነት ማጉደል ወይም ከሙያ ስነ ምግባር ውጭ በሆነ ተግባር ላይ መሰማራት የለበትም፤

ለ) በግዢዎች እና ትግበራ ላይ ግልጽነት እንዲሰፍን ይጥራል፡፡

ሐ) በገንዘብ አወጣጥና ቁጥጥር ላይ በከፍተኛ ሁኔታ ታማኝ በመሆን የሃብት አጠቃቀሞችን በላቀ ደረጃ ለመጠቀም እንዲያስችል በግልጽ፣ በቅንነት፣ ከአድልዎ በጸዳ መልኩ እና ለህዝቡ፣ ለአሰሪው፣ ለስራ ባልደረቦቹ እና ደንበኞቹ ታማኝ በመሆን ማገልገል ይኖርበታል፤

መ) በተሰማራባቸው ማናቸውም የኮንስትራክሽን ሥራዎች ላይ ለሚታዩ የጉቦ፣ የማጭበርበር እና የሙስና ተግባራት ላይ በጽናት መታገል ይኖርበታል፤

፯. የሙያ አቅምን በግልም ሆነ የሌሎችን የቅርብ ክትትልና ድጋፍ በማግኘት ስለማሳደግ እና የሰራተኞቹን አቅም ስለማጎልበት

ማንኛውም ባለሙያ፡-

ሀ) በሙያው በመስራት፣ ቀጣይነት ባለው የትምህርት ሂደት በማሳተፍ፣ የቴክኒክ ፅሁፎችን በማንበብ፣ እንዲሁም በባለሙያዎች ስብሰባ እና ሴሚናሮች ላይ በመሳተፍ በሙያው ባለበት ንዑስ ዘርፍ ያለውን ዕውቀት ወቅታዊነት መጠበቅ ይኖርበታል፤

ለ) በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክልል ዉስጥ መስራት የሚፈልግ ማንኛዉም ግለሰብ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኮንስትራክሽን ቢሮ መመዝገብ ይኖርበታል፤

ሐ) በስሩ ያሉ ሰራተኞች በተለያዩ የሙያ ማህበራት ስብሰባ ላይ እንዲሳተፉና ጽሁፎችን እንዲያቀርቡ ማበረታታት ይኖርበታል፤

መ) በስሩ ያሉ ሰራተኞች፣ ተለማማጅ መሀንዲሶች እና የሙያ ስልጣኞችን አቅም መገንባት ይኖርበታል፤

ሠ) በስራ ቅጥር ስምምነቱ መሰረትም የሙያ ደረጃ፣ የደሞወዝ ወሰን እና ልዩ ልዩ ጥቅማ ጥቅሞች እንዲከበሩ በማድረግ በአሰሪው እና ሰራተኞች የጋራ ጥቅም መርህ ላይ በመመስረት መልካም ግንኙነት እንዲኖር ጥረት ማድረግ አለበት፡፡

## ክፍል ሶስት

## እርምጃ አወሳሰድ

### ፰. ሥነስርዓት የማስከበር እና የእርምጃ አወሳሰድ ሂደት

ቢሮው ይህንን ደንብ የማስተዋወቅ፣ የመከታተል እና የማስፈጸም ኃላፊነት የሚኖረው ጉባኤ ያቋቁማል፤ የጉባኤዉ ተግባርና ሃላፊነት የሚከተሉት ናቸዉ

ሀ) የስነ ምግባር ጥሰት አቤቱታዎች ሲቀርቡ ጉዳዩን የሚያጣራ ኮሚቴ ማቋቋም፤

ለ) አንድን የቀረበ የሙያ ስነምግባር ጥሰት ክስ ለማጣራት አጣሪ ኮሚቴ ማቋቋም አስፈላጊ መሆን አለመሆኑን መወሰን፤

ሐ) የሥነ ምግባር ጥሰት ክስን ተቀብሎ ለጉባኤው መምራት፤ የሥነ ምግባር ጥሰት ባይቀርብም በዚህ ደንብ መሰረት የስነ ምግባር ጥሰት መፈጸሙ የታየን ባለሙያ ጉዳይ በኮሚቴዉ ተጣርቶ እንዲቀርብለት መምራት፤

መ) የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች ማስተዋወቅ፤

ሠ) የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች አፈጻጸም መከታተል፤

፱)አባላቱምእንደሙያግዴታቸውሁሉይህንንሚስጥራዊመረጃመጠበቅይኖርባቸዋል፤

፲) የጉባኤው፣የአጣሪ ኮሚቴዉ ወይም የይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ ውሳኔ ከተላለፈ በኋላ የተወሰነበት ባለሙያ ከአስተዳደሩ የባለሙያዎች ምዝገባ የሚታገድ ወይም የሚሰረዝ ሲሆን ይህም ውሳኔ በቢሮው የህትመት ውጤቶች ወይም መደበኛ መጽሄት ላይ ሊታተም ይችላል፤

፲፩) እንደዚህ አይነት እግድ ከባለሙያው ስምና አድራሻ ጋር በባለሙያዎች ማህበር መጽሄት ላይ እንዲሁም በአስተዳደሩ መጽሄት እና የህትመት ውጤቶች ላይ ሊታተም ይችላል፡

፲. የአጣሪ ኮሚቴዉ ተግባርና ኃላፊነት

፩) ጉባኤዉ የመራለትን የስነምግባር ጥሰት ጉዳይ ያጣራል፤ የውሳኔ ሃሳብ ለጉባኤዉ ያቀርባል፤

፪) ኮሚቴዉ በጉባኤዉ ሊቀመንበር የተሰየሙ ሶስት የቦርድ አባላት ይኖሩታል፤

፫) ኮሚቴዉ በጉባኤው የሚሰየም ሰብሳቢ ይኖረዋል፤

፬) ኮሚቴዉ ተፈጸመ የተባለውን የስነምግባር ጥሰት ክስ በዚህ ደንብ ድንጋጌዎች እና ጥፋቱ በተፈጸመበት ጊዜ በስራ ላይ በነበረው የባለሙያዎች ማህበርና ሌሎች የተቋማት የስነምግባር ስታንዳርድ መሰረት ይመረምራል፤

፭) የኮሚቴዉ ሊቀመንበር ተጨማሪ አባላት እንዲመደቡለት የጉባኤዉን ሊቀመንበር ሊጠይቅ ይችላል፤

፮) የጉባኤው ሊቀመንበርም አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው አግባብ ካለው አካል አንድ ተጨማሪ ባለሙያ ሊመድብ ይችላል።

፲፩. የኮሚቴዉ ሰብሳቢና ፀሐፊ ኃላፊነትና ተግባር

፩.የኮሚቴዉ ሰብሳቢ ሃላፊነትና ተግባር

ሀ) ኮሚቴዉን በበላይነት ይመራል፤

ለ) እርሱ በማይኖርበት ጊዜ ከአባላቱ ውስጥ ስብሰባውን የሚመራ ይወክላል፤

ሐ) ኮሚቴዉ የሚመራበትን የሥራ መመሪያ ከኮሚቴዉ አባላት ጋር ያዘጋጃል፤

መ) የሥነ ምግባር ጥሰት ክሶችን ይቀበላል፣

ሠ) ኮሚቴዉ የሚሰጠውን ውሣኔ ለከሳሽ፣ ለተከሳሽ፣ ለሙያ ማህበሩ ለኮንስትራክሽን ሚኒስቴር እና ለቢሮው በጽሁፍ ወይም በኤሌክትሮኒክስ መገናኛ ዘዴ እንዲደርሳቸው ያደርጋል፣

ረ) በዳኝነት አካል ሲጠየቅ የውሳኔውን ቅጂ ይሰጣል፣

፪የኮሚቴዉ ፀሐፊ ኃላፊነትና ተግባር

ሀ) የስብሰባ አጀንዳና ቃለጉባዔ እየያዘና በአግባቡ እያዘጋጀ እንዲፈርሙበት እየያዘና በአግባቡ እያዘጋጀ አባላቱ ያደርጋል፣

ለ) አስፈላጊ መረጃዎች እና ሰነዶች በስብሰባ ወቅት ተሟልተዉ እንዲገኙ በስብሰባ ወቅት ተሟልተው ያደርጋል፣

ሐ) ኮሚቴዉ የተሟሉ ሰነዶች እና መዛግብቶች እንዲኖሩት ያደርጋል፣

መ) ከኮሚቴዉ ሰብሳቢ በሚሠጠው መመሪያ መሰረት አጀንዳ ያዘጋጃል

ሠ) የቦርዱ አባልና ፀሐፊ ሆኖ ይሰራል፣

ረ) የሥነ ምግባር ጥሰት ክስየቀረበባቸውንሰነዶችእና ለምርመራ የተሰበሰቡ መረጃዎችን መዝግቦ ይይዛል፣

ሸ) ውሳኔ የተሰጠባቸውንና ሌሎች ሠነዶችን መዝግቦ በጥንቃቄ ይይዛል፣

፲፪. የባለሙያ ስነምግባር ጥሰት ማጣራት እና ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት

፩) አንድ ተፈጸመ የተባለ የሙያ ስነምግባር ጥሰት ክስ በማንኛውም ሰው አማካይነት ለቦርዱ ጸሐፊ ሊቀርብ ይችላል፡፡

፪) ሁሉም ክሶች በጽሁፍ ሆነው በክስ አቅራቢው ተፈርመው መቅረብ አለባቸው፡፡ የሚቀርበው ክስ የክሱን መንስኤ በአግባቡ መግለጽ አለበት፡፡

፫) ጉባኤዉ በራሱ አነሳሽነት የስነምግባር ጥሰት ክስ ሊያቀርብ ይችላል፡፡ በዚህ መሠረት የሚቀርብ ክስ በፅሁፍ ተዘጋጅቶ በቦርዱ ሊቀመንበር መፈረም ያለበት ሲሆን ለክሱ መንስኤ የሆኑትን ሁኔታዎች በዝርዝር መግለፅ ይኖርበታል፡፡

፬) በጉባኤዉ የሚቀርብ ክስ ልክ በሌላ አካል እንደቀረበ ክስ የሚያዝ ይሆናል፡፡

፭) ጉባኤዉ ተፈጸመ የተባለውን የሙያ ስነምግባር ጥሰት ከተመለከተ በኋላ የሚመለከተው ባለሙያ በጉባኤዉ እምነት መጣራት የሚያስፈልገው ሆኖ ከተገኘ ጉባኤዉ ኮሚቴ በመሰየም ጉዳዩን እንዲያጣራ እና የውሳኔ ሀሳብ እንዲያቀርብ ያደርጋል፡፡

፮) ጉባኤዉ እንደዚህ አይነት ኮሚቴ ለማቋቋም የሚያሳልፈው ውሳኔ በአብላጫ ድምጽ የሚተላለፍ ሆኖ እኩል ድምጽ በሚሰጥበት ወቅት የቦርዱ ሊቀመንበር ያለበት ድምጽ የጉባኤዉ ውሳኔ ይሆናል፡፡

፯) ኮሚቴዉ በተቋቋመ በ፭ የስራ ቀናት ውስጥ የስነ ምግባር ጥሰት ፈፀመ የተባለው ባለሙያ ለቀረበበት ክስ የመከላከያ መልሱን እንዲያቀርብ መጥሪያ ከክሱ ጋር ይልክለታል፡፡

፰) ክስ የቀረበበት ባለሙያ መጥሪያው በደረሰው በ፲ የስራ ቀናት ውስጥ የመከላከያ መልሱን በፅሁፍ ለኮሚቴዉ ያቀርባል፡፡

፱) ከተከሳሽ መከላከያ መልስ ሲደርሰው ጉባኤው ይህንን መከላከያ መልስ ለከሳሹ ቅጂውን ይልክለታል፡፡

፲) ከሳሹም የተከሳሹን መከላከያ መልስ በተቀበለ በ፲ የስራ ቀናት ውስጥ የመልስ መልሱን በፅሁፍ ለጉባኤው ያቀርባል፡፡

፲፩) ከሳሹ የመከላከያ መልሱን መጥሪያው በደረሰው በ፲ የስራ ቀናት ውስጥ ያለበቂ ምክንያት ካላቀረበ ጉባኤው የቀረበውን ክስ ተከሳሹ በሌለበት መመርመር ይጀምራል፡፡

፲፫. <u>ኮሚቴዉ ከጉባኤው የተመራለትን ጉዳይ በተመለከተ፡-</u>

ሀ) ማንኛውንም ሰው መረጃ ሊጠይቅ ይችላል፤

ለ) ማንኛውንም ሰው በአካል ቀርበው ማስረጃ እንዲሰጥ ሊጠይቅ ይችላል፤

ሐ) አስፈላጊ ናቸው ብሎ የሚያስባቸውን ማስረጃዎች ወይም ሰነዶች ከማንኛውም ሰው ሊጠይቅ ይችላል፤

መ) በክስ አቅራቢው ወይም በተከሳሹ መረጃ ወይም ሰነዶች የሚቀርብበትን ጊዜ ገደብ ይወስናል፤

ሠ) በቃል ክርክር ሁለቱም ወገኖች በፅሁፍ ካቀረቧቸው ክርክሮች እንዳይወጡ ያደርጋል፡፡

፲፬. <u>ኮሚቴዉ በቀረበው ክስ ላይ ፍትሃዊ እና ከአድልዎ ነጻ የሆነ የውሳኔ ሐሳብ ለጉባኤው ያቀርባል፤ እንዲሁም፡-</u>

ሀ) ከሳሽና ተከሳሽ በጉባኤው ፊት ጉዳያቸውን እንዲያሰሙ እድል ይሰጣል፡፡

ለ) ከሳሽና ተከሳሽ በቃል ክርክር ወቅት እንዲገኙ እና መስቀለኛ ጥያቄ እንዲያቀርቡ እድል ይሰጣል፡፡

ሐ) ለከሳሽና ለተከሳሽ ውሳኔውን ባሳለፈ በ፮ የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔውን በፅሁፍ ያሳውቃል፡፡

መ) ሁለቱም ወገኖች የይግባኝ መብታቸውን እንዲያውቁት እንዲሁም የይግባኝ አቀራረቡ በዚህ ደንብ መሰረት እንዴት መሆን እንዳለበት እንዲያውቁት ያደረጋል፡፡

፲፬ የኮሚቴዉ ውሳኔ በአብላጫ ድምጽ የሚወሰን ይሆናል፡፡ ኮሚቴዉ ክስ በቀረበለት በ፴ የስራ ቀናት ውስጥ የውሳኔ ሃሳብ ለጉባኤዉ ማቅረብ አለበት፡፡

፲፭ <u>ስለ ጉባኤዉና ይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ ውሳኔዎች</u>

፩) ጉባኤዉ ተከሳሹ ጥፋተኛ መሆኑ የውሳኔ ሀሳብ ሲቀርብለት፣

ሀ) የቀረበው የሙያ ስነምግባር ጥሰት ማእቀብ ሊያስጥል በሚችልበት ደረጃ ከፍተኛ ነው ለማለት በቂ ክስተት እንደሌለ ሊወስን ይችላል፡፡

ለ) ተከሳሽ የሥነ ምግባር ጥሰት እንደፈጸመ በማሳወቅ ተከሳሹ ለጉባኤዉ በጽሁፍ ይህንን ጥፋት በድጋሚ እንደማይፈጽም እንዲያሳውቅ ሊወስን ይችላል፡፡

ሐ) ተከሳሽ ከቢሮው የባለሙያ ምዝገባ ለተወሰነ ጊዜ እንዲታገድ እና ባለሙያው ለቦርዱ በጽሁፍ ይህንን ጥፋት በድጋሚ እንደማይፈጽም ማረጋገጫ እንዲሰጥ ሊወስን ይችላል፡፡

መ) የተከሳሽ የሙያ ደረጃ ለተወሰነ ጊዜ ዝቅ እንዲል ሊወስን ይችላል፡፡

ረ) ተከሳሽ ከከተማዉ ባለሙያዎች መዝገብ ውስጥ እንዲሰረዝ ሊወስን ይችላል፡፡

፩) ጉባኤዉ ለተከሳሽ ፣ ለከሳሽ፣ ለቢሮ፣ የክሱን ሁኔታ፣ ውሳኔውን ያሳለፈበት ምክንያት እንዲሁም ያቀረበውን የእገዳ ውሳኔ ውሳኔውን በወሰነ በ፯ የስራ ቀናት ውስጥ ማሳወቅ ይኖርበታል፤

፫) ጉባኤዉ ተከሳሹ ከቢሮው የባለሙያዎች መዝገብ እንዲታገድ ወይም እንዲሰረዝ ከወሰናና የይግባኝ ጊዜው ካለፈ ውሳኔው የፀና ይሆናል፤

፬) ቢሮው የጉባኤዉን ውሳኔ አሳመኝ ሆኖ ካላገኘው ለይግባኝ ሰሚ ቦርድ ጉዳዩን በማቅረብ ጉዳዩ በዝርዝር እንዲጣራ በጽሁፍ ማዘዝ ይችላል፤

፭) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፬) መሰረት የሚፈጸም ማናቸውም ለይግባኝ ሰሚ ቦርዱ የተመሩ ጉዳዮች እንደይግባኝ ይመረመራሉ፤

፮) የይግባኝ ሰሚ ቦርድ ውሳኔ ለተከሳሽ፣ ለከሳሽ፣ ለቦርድ፣ ለጉባኤ፣ ውሳኔው ከተላለፈበት ቀን ጀምሮ በ፯ የሥራ ቀናት ውስጥ በፅሁፍ የሚሰጥ ይሆናል፤

፯) ቦርዱ እና/ ወይም ይግባኝ ሰሚ ቦርዱ ተከሳሹ ከምዝገባ ዝርዝሩ እንዲሰረዝ ከወሰነ ውሳኔው ተፈጻሚ የሚሆነው ከተወሰነበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፤

፰) ተከሳሹ በዚህ አንቀፅ መሠረት የጽሁፍ ማረጋገጫ እንዲያቀርብ ከተጠየቀ በ፲ የሥራ ቀናት ወይም ቢሮው በሚሰጠው ተጨማሪ ጊዜ ውስጥ ማረጋገጫውን ማቅረብ አለበት፤

፱)ተከሳሽ ጥፋቱን ላለመድገም በዚህ ደንብ መሰረት ማረጋገጫ ካልሰጠ ወይም ለመስጠት ፍቃደኛ ካልሆነ ቦርዱ በራሱ ውሳኔ፡-

ሀ) ባለሙያውን ከሚመለከተው የከተማው አስተዳደር የባለሙያዎች መዝገብ ማረጋገጫው እስኪቀርብለት ድረስ ሊያግድ ይችላል፤ ወይም

ለ) ባለሙያውን ከከተማው አስተዳደር የባለሙያዎች መዝገብ ሊሰርዝ ይችላል፡፡

<u>፲፮. ይግባኝ</u>

ቢሮው ፫ አባላት ያሉት የይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ ያቋቁማል፡፡ ሰብሳቢና ፀሀፊውንም ይሰይማል፡፡

፩) የይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ ሊቀመንበር ወይም ሰብሳቢው ከቢሮው የሚመደብ ሆኖ ከባለሙያ ማህበር ፕሬዚዳንት ወይም አመራር የይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ አባል ይሆናል፤ ፫ኛው አባል ከከተማው ፍትህ ቢሮ የሚወከል የህግ ባለሙያ ይሆናል፡፡

፫) ማንኛውም ሰው በተመሳሳይ ጊዜ የጉባኤና እና የይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ አባል መሆን አይችልም፡፡ የይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ አባል የጉባኤ አባል ሊሆን አይችልም፡፡

፬)በጉባኤዉ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ሰው ውሳኔው በደረሰው በአሥር የሥራ ቀናት ውስጥ ይግባኝ ለይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ ማቅረብ ይችላል፡፡

፭) የይግባኙ ቅጂ ለመረጃ እንዲሆን ለጉባኤዉ፣ ለቢሮ ሀላፊ፣ ለኮሚቴዉ የሚሰጥ ሲሆን ሌላው ተከራካሪ ወገን ለይግባኙ መልስ የመስጠት መብት አለው፡፡

<u>፲፮. የይግባኝ ሰሚ ቦርድ ሰብሳቢና ፀሐፊ ሥልጣንና ተግባራት፤</u>

<u>፩. የይግባኝ ሰሚ ቦርድ ሰብሳቢ ሥልጣንና ተግባር፤</u>

ሀ) የይግባኝ ሰሚ ኮሚቴን በበላይነት ይመራል፤

ለ) እርሱ በማይኖርበት ጊዜ ከአባላቱ ውስጥ ስብሰባውን የሚመራ በቢሮው እንዲወከል ያደርጋል፤

ሐ) የይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ የሚመራበትን የሥራ መመሪያ ከኮሚቴ አባላት ጋር ያዘጋጃል፤

መ) ይግባኞችን ይቀበላል

ረ) የይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ የሚሰጠውን ውሣኔ ለተከራካሪ ወገኖች፣ ለቢሮው በጽሁፍ ወይም በኤሌክትሮኒክስመገናኛዘዴእንዲደርሳቸውያደርጋል፣

ሰ) በዳኝነት አካል ሲጠየቅ የውሳኔውን ቅጂ ይሰጣል፣

፪. የይግባኝ ሰሚ የኮሚቴ ፀሐፊ ሥልጣንናተግባር

ሀ) የስብሰባ አጀንዳና ቃለ ጉባዔ እየያዘና በአግባቡ እያዘጋጀ አባላቱ እንዲፈርሙበት ያደጋል፤

ለ) አስፈላጊ መረጃዎች እና ሰነዶ በስብሰባ ወቅት ተሟልተው እንዲገኙ ያደርጋል፣

ሐ) የይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ የተሟሉ ሰነዶች እና መዛግብቶች እንዲኖሩት ያደርጋል፣

መ) ከይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ በሚሠጠው መመሪያ መሠረት አጀንዳ ያዘጋጃል፣

ሠ) የይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ አባልና ፀሐፊ ሆኖ ይሰራል፣

ረ) ይግባኝ የተጠየቀባቸውን ሰነዶች እና ለምርመራ የተሰበሰቡ መረጃዎችን በአግባቡ መዝግቦ ይይዛል፣

ሰ) ውሳኔ የተሰጠባቸውንና ሌሎች ሠነዶችን በአግባቡ መዝግቦ ይይዛል፡፡

፲፰. የይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባር

፩. ይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ፡-

ሀ) የኮሚቴዉን ውሳኔ በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ሊያጸና ይችላል፡፡

ለ) የኮሚቴዉን ውሳኔ ውድቅ ሊያደርግ ይችላል፡፡

ሐ) የኮሚቴዉን ውሳኔ ከተፈፀመው የሥነ ምግባር ጥሰት ጋር ተመጣጣኝ ሆኖ ካላገኘው ውሳኔው እንዲለወጥ እና ተመጣጣኝ የሆነ ቅጣት እንዲሰጥ ለቦርዱ ሊመልስ ይችላል፡፡

፪. ይግባኙን በሚሰማበት ወቅት ተግባሩን ለመወጣት የይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ በዚህ ደንብ አንቀፅ ፲፰ ስር የተጠቀሱት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡፡

፫. የይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ ውሳኔዎች በአብላጫ ድምጽ ይወሰናሉ፡፡

፬. የይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ ይግባኝ በቀረበለት በ፴ የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

፭. የይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ በይግባኙ ላይ የሚያስተላልፈውን ውሳኔ በጽሁፍ ለሁለቱም ወገኖች፣ ለቦርዱ፣ እና ለቢሮው ውሳኔውን በሰጠ በ፯ የሥራ ቀናት ውስጥ በፅሑፍ ያሳውቃል፡፡

፲፱. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

ቢሮው ይህንን ደንብ በሚገባ ለማስፈፀም አስፈላጊ የሆነውን መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፳. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ ደንብ ከሰኔ ፳፪ ቀን ፪ሺ፲ ጀምሮየፀናይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሰኔ ፳፪ ቀን ፪ሺ፲ ዓመተ ምህረት

ድሪባ ኩማ

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን እንደገና ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር አጭር መግለጫ ፻፳/፪ሺ፲፩

<u>ማውጫ</u>

1. ክፍል አንድ ጠቅላላ ድንጋጌዎች
2. ክፍል ሁለት ስለመቋቋም፣ አደረጃጀት፣ አሰራር፣ ሥልጣንና ተግባር
3. ክፍል ሶስት ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

አጭር መግለጫ

በታክስ አስተዳደር ስርዓት በግብር አስገቢው በሚሰጠው የግብርና ታክስ ውሳኔዎች ላይ የግብር ከፋዩ የሚያቀርበውን አቤቱታ ቀልጣፋ፣ ውጤታማ፣ ፍትሐዊና የሕግ የበላይነትን የሚያረጋግጡ ውሳኔዎችን የሚሰጥና የዘርፉን የመልካም አስተዳደር ችግሮችን መፍታት የሚችል የዳኝነት አካል አደረጃጀትና አሰራር ማሻሻል በማስፈለጉየወጣ ህግ ነው፡፡

# የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን እንደገና ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፻፳/፪ሺ፲፩

በታክስ አስተዳደር ስርዓት በግብር አስገቢው በሚሰጠው የግብርና ታክስ ውሳኔዎች ላይ የግብር ከፋዩ የሚያቀርበውን አቤቱታ ቀልጣፋ፣ ውጤታማ፣ ፍትሐዊና የሕግ የበላይነትን የሚያረጋግጡ ውሳኔዎችን የሚሰጥና የዘርፉን የመልካም አስተዳደር ችግሮችን መፍታት የሚችል የዳኝነት አካል አደረጃጀትና አሰራር ማሻሻል በማስፈለጉ፤

በፌደራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፱፻፹፫/፪ሺህ፰ የታክስ ይግባኝ ጉባኤ አደረጃጀትና አሰራር ጋር የሚጣጣም ተቋም፣ አደረጃጀትና አሰራር መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ፤

የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚ አካላትን እንደገና ለማደራጀት፣ ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን በወጣዉአዋጅቁጥር ፷፬/፪ሺ፲፩ አንቀፅ ፺፰መሠረትይህንደንብአውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን እንደገና ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፻፳/፪ሺ፲፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ዉስጥ፡-

፩. "ከተማ አስተዳደር" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፪. "ከተማ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤

፫. "ምክር ቤት" ማለት የከተማው ምክር ቤት ነው፤

፬. "ከንቲባ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ነው፤

፭. "ባለስልጣን" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የገቢዎች ባለስልጣን ነው፤

፮. "ፕሬዚዳንት" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ፕሬዚዳንት ነው፤

፯. "ዳኛ" ማለት በከንቲባው የሚሾም የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ዳኛ ነው፤

፰. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም የህግ ሰውነት የተሰጠው ማንኛውም አካል ነው፤

፱. "የታክስ አስተዳደር አዋጅ" እና "የታክስ አስተዳደር ደንብ" ማለት እንደ ቅደም ተከተላቸው የፌደራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፱፻፹፫/፪ሺህ፰ እና የሚኒስትሮች ምክር ቤት የፌደራል የታክስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር ፬፻፯/፪ሺህ፱ ናቸው፤

፲. በዚህ ደንብ ጥቅም ላይ የዋሉ ቃላትና ሐረጎች እንደአግባብነታቸው በታክስ አስተዳደር አዋጅ እና በፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር ፱፻፸፱/፪ሺህ፰ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡

፫. የፆታ አገላለጽ

በዚህ ደንብ ዉስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

## ክፍል ሁለት
## ስለመቋቋም፣ አደረጃጀት፣ አሰራር፣ ሥልጣንና ተግባር

፬. መቋቋም

፩. የከተማ አስተዳደሩ የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን (ከዚህ በኃላ "ኮሚሽን" እየተባለ የሚጠራ) የህግ ሰውነት ያለዉ የመዳኘት ሥልጣን የተሰጠዉ አካል ሆኖ በዚህ ደንብ እንደገና ተቋቁሟል፡፡

፪. የኮሚሽኑ ተጠሪነት ለከተማው አስተዳደር ዓቃቤ ሕግ ቢሮ ይሆናል፡፡

፩.አደረጃጀት እና አሰራር

፩. ኮሚሽኑ፡-

ሀ) በከንቲባው የሚሾሙ አንድ ፕሬዚዳንት፣ ምክትል ፕሬዚዳንትና ዳኞች፤

ለ) አስፈላጊ ችሎቶች፣ ሬጅስትራር፣ ሰራተኞችና የስራ ክፍሎች ይኖሩታል፡፡

፪. ኮሚሽኑ የሚከተለውን አሰራር ይከተላል፡-

ሀ) ዳኛ (የሙሉ ጊዜ ወይም የከፊል ጊዜ ዳኛ ሆኖ ሊሾም ይችላል)፤

ለ) እያንዳንዱ ችሎት ሰብሳቢውን ጨምሮ አምስት ዳኞች ይኖሩታል፡፡ ሆኖም ከአባላቱ ሶስቱ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፤

ሐ) ኮሚሽኑ ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ የፍትሐብሄር ሥነ-ሥርዓት ህግ ቁጥር ፶፰፣፶፱፣፷፪፣፷፫፣ እና ፺፪ ድንጋጌዎችን ይከተላል፤

መ) እያንዳንዱ ችሎት ውሳኔ ሲያስተላልፍ ሙሉ ድምፅ ካልተገኘ የአብላጫው ድምፅ ውሳኔ የችሎቱ ውሳኔ ይሆናል፤ ሆኖም ችሎቱ የሚሠጠው ድምፅ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ የችሎቱ ሰብሳቢ ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል፤

ሠ) ማንኛውም ዳኛ በሚያየው ማንኛውም ጉዳይ በአባልነቱ ከሚያከናውነው ተግባር ጋር ሊጋጭ የሚችል ቁሳዊ፣ የገንዘብ ወይም ሌላ ጥቅም ሲኖር ይህንኑ ጥቅም ለፕሬዚዳንቱ መግለፅ ያለበት ሲሆን ፕሬዚዳንቱም ይህንኑ ጥቅም በመመዝገብ ዳኛው በይግባኝ ሰሚነት እንዳይሳተፍ ያደርጋል፤

ረ) ማንኛዉም ዳኛ በዚህ ደንብ መሰረት ግዴታዉን በአግባቡ ለመወጣት በፈፀመዉ ድርጊት ወይም አለማድረግ ምክንያት ምንም ዓይነት ክስ ሊቀርብበት አይችልም፤

ሰ) የኮሚሽኑን አሰራር በተመለከተ የከተማው ዐቃቤ ሕግ ቢሮ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፮. የኮሚሽኑ ስልጣንና ተግባር

የታክስ አስተዳደር አዋጅ ክፍል አስራ ሶስት እና የታክስ አስተዳደር ደንብ ክፍል ሰባት አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፤ ኮሚሽኑ፡-

፩. ይግባኝ የቀረበበትን ጉዳይ መርምሮ ውሳኔውን ያሻሽላል፤ ያፀናል፤ ወይም ይሽራል፤ እንዲሁም አስፈላጊ የሆነውን ተጨማሪ ትዕዛዝ ይሰጣል፤ የሰጠውን ውሳኔና ትዕዛዝ ያስፈፅማል፤

፪. ባለሥልጣኑ የሰጠውን የታክስ ውሳኔ በመቃወም የሚቀርብለትን ይግባኝ በመስማት በፍሬ ነገር ላይ የመጨረሻ ዉሳኔ ይሰጣል፤

፫. አግባብ ባለው ህግ መሰረት ያልቀረበው ይግባኝ ተቀባይነት ያለማግኘቱን በአንድ ወር ውስጥ ለይግባኝ ባይ በጽሑፍ ያሳውቃል፤

፬.በሕግ ይግባኝ በተፈቀደባቸው የማዘጋጃ ቤት ታክስና ቀረጥ ላይ የሚቀርብለትን ይግባኝ መርምሮ ይወስናል፤

፭. በዳኞች የተፈረመ ውሳኔ ለተከራከሪ ወገኖች ይሰጣል፤

፮. በቀረበለት ጉዳይ ላይ መርምሮ ውሳኔ ለመስጠት አግባብነት ያለው ማናቸውም መፅሐፍ፣ መዝገብ ሌላ ፅሁፍም ሆነ ማንኛውም ዓይነት ሌላ ማስረጃ (የኤሌክትሮኒክስ መረጃን ጨምሮ) እንዲቀርብለት ትዕዛዝ ይሰጣል፤

፯. በቀረበው ይግባኝ ተገቢ ውሳኔ ለመስጠት አስፈላጊ የሆነ ሰው ቀርቦ አስፈላጊውን መረጃ እንዲሰጥ ትዕዛዝ ይሰጣል፤

፰. ከቀረበው ጉዳይ ጋር በሚዛመድ ጭብጥ ላይ ተገቢውን ውሳኔ ለመስጠት የሚያስፈልገውን ማናቸውም ትዕዛዝ ለአንድ ወይም ለሁሉም ተከራካሪ ወገኖች ወይም ለማንኛውም ሰው ይሰጣል፣

፱. በታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀፅ ፻፳፱ የተደነገገው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የችሎት ክርክር በሚካሄድበት ወይም ጉዳዩ በሚሰማበት ወቅት የችሎት መድፈር ድርጊት በፈፀመው ተከራካሪ ወገን ወይም በሌላ ሰው ላይ እስከ ብር ፪ሺ፣፭፻ (ሁለት ሺህ አምስት መቶ ብር) የሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ዉሳኔ ይሰጣል፣

፲. በቂ ባልሆነ ምክንያት የችሎቱን ትዕዛዝ ያልፈጸመ ተከራካሪ ወገን ለሌላ ተከራካሪ ወገን ተመጣጣኝ ኪሳራ እንዲከፍል ይወስናል፣

፲፩. አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የሰጠውን ውሳኔና ትዕዛዝ የፖሊስ ሀይል በማዘዝ ያስፈፅማል፡፡

፯. የፕሬዚዳንቱ ስልጣንና ተግባር

ፕሬዚዳንቱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡-

፩. በዚህ ደንብ መሰረት ተጠንቶ በሚመለከተዉ አካል በሚፀድቀው መዋቅር መሰረት የኮሚሽኑን ጽህፈት ቤት ያደራጃል፣

፪. የችሎት ሰብሳቢ ዳኞችንና የችሎት ዳኞችን ይደለድላል፣

፫. ከኮሚሽኑ ችሎቶች የአንዱ ችሎት ሰብሳቢ በመሆን ያገለግላል፣

፬. በሚመለከተው አካል በሚፀድቀው መዋቅራዊ አደረጃጀት መሰረት ለጽህፈት ቤቱ ስራ አስፈላጊ የሆኑ ሰራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፣

፭. የኮሚሽኑን አመታዊ በጀትና የስራ ፕሮግራም በማዘጋጀት ለሚመለከተዉ አካል ያቀርባል፣ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፣

፮. ፕሬዚዳንቱ ለእያንዳንዱ የበጀት ዓመት ኮሚሽኑን የሚመለከት የዕቅድና በጀት አፈጻጸም ሪፖርት በማዘጋጀት ለሚመለከተዉ አካል ያቀርባል፣

፯. እንደአስፈላጊነቱና እንደአግባብነቱ ለምክትል ፕሬዚዳንት፣ ለፕሬዚዳንት ጽህፈት ቤት ረዳት ወይም ከችሎት ሰብሳቢ ዳኞች ለአንዱ ስራዎችን በውክልና መስጠት ይችላል፣

፰. ከሶስተኛ ወገን ጋር በሚደረግ የስራ ግንኙነት ኮሚሽኑን በመወከል ይሳተፋል፣ ተገቢውን ይፈፅማል፡፡

፰. የምክትል ፕሬዚዳንት ስልጣንና ተግባር

፩. ፕሬዚዳንቱ በሌለበት ወይም ስራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶት ይሰራል፣

፪. ከችሎቶቹ የአንዱ ሰብሳቢ ዳኛ በመሆን ያገለግላል፣

፫. በፕሬዚዳንቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

፱. የፕሬዚዳንት፣ ምክትል ፕሬዚዳንትና ዳኞች አሿሿም

፩. ፕሬዚዳንቱና ምክትል ፕሬዚዳንቱ በከንቲባው ይሾማሉ፡፡ ሆኖም ፕሬዚዳንቱ በገዛ ፍቃዱ የስራ ኃላፊነቱን ከለቀቀ፣ ከስራው የታገደ ወይም የተነሳ እንደሆነ ሌላ ፕሬዚዳንት እስኪሾም ድረስ ምክትል ፕሬዚዳንቱ ወይም ከችሎት ሰብሳቢ ዳኞች አንዱ የፕሬዚዳንቱን ስልጣንና ተግባሮች ደርቦ በዉክልና እንዲሰራ ከንቲባው ሊመድብ ይችላል፡፡

፪. ዳኛ ሆኖ የሚሾም ሰው ሊያሟላ የሚገባው መስፈርት፣ የስራ ዘመን እና የዳኝነት አገልግሎት የሚቋረጥበት ሁኔታ በተመለከተ በታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀፅ ፹፯ ንዑስ አንቀፅ ፪፣ ፫፣ ፬ (ሀ እና ለ) እና ፭ የተደነገጉት ድንጋጌዎች በኮሚሽኑ ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

፫. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፪) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በሙሉ ጊዜም ሆነ በከፊል ጊዜ የሚሰሩ ዳኞች በከንቲባው ይሾማሉ፡፡

፬. ዳኛ ሲሰየም የሚከፈለዉ አበል እና ሌሎች ክፍያዎች በከተማው አስተዳደር የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ ተጠንቶ አግባብ ባለው አካል ይወሰናል፣

፭. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፪) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በእያንዳንዱ ችሎት ከሚሰየሙት የከፊል ጊዜ ዳኞች ውስጥ እንደ አስፈላጊነቱ አንዱ ከአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ተወካይ የሚሾምበትን ሁኔታ ከግምት ውስጥ ያስገባ ሊሆን ይችላል፡፡

፲. ይግባኝ ስለማቅረብ

፩. ይግባኝ ሊቀርብበት በሚችል ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ታክስ ከፋይ በታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ ፶፮ እና ፹፰ በተደነገገው መሰረት አስፈላጊውን በማሟላት የይግባኝ ማስታወቂያ ለኮሚሽኑ ሊያቀርብ ይችላል፣

፪. በሕግ ይግባኝ በተፈቀደባቸው የማዘጋጃ ቤት ታክስና ቀረጥ ላይ ለኮሚሽኑ የሚቀርብ ይግባኝታክሱንና ቀረጡን በወሰነው ሕግ በተደነገገው መሠረት ይሆናል፡፡

፲፩. ለኮሚሽኑ ሰነዶችን ስለማቅረብ

፩. ባለሥልጣኑ የይግባኝ ማስታወቂያው በደረሰው በ፴ ቀናት ውስጥ ወይም ኮሚሽኑ በፈቀደው ተጨማሪ ጊዜ ውስጥ፡-

ሀ) የይግባኝ ማመልከቻ የቀረበበትን ይግባኝ የሚባልበት ውሳኔ ግልባጭ፣

ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ (ሀ) በተጠቀሰው ይግባኝ የሚባልበት ውሳኔ ላይ ያልተጠቀሰ ለውሳኔው ምክንያት የሆነ መግለጫ፣

ሐ) ውሳኔውን በይግባኝ ለማየት ለኮሚሽኑ አስፈላጊ የሆነ ማንኛውም ሌላ ሰነድ ለኮሚሽኑ ማቅረብ አለበት፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ (ለ) መሰረት የቀረበው የውሳኔ ምክንያቶች መግለጫ አጥጋቢ ሆኖ ካላገኘው በፅሁፍ ማስታወቂያ ባለሥልጣኑ በማስታወቂያው በተመለከተው ጊዜ ውስጥ የውሳኔውን ምክንያቶች የሚያብራራ ተጨማሪ መግለጫ እንዲያቀርብ ኮሚሽኑ ሊያዝ ይችላል፣

፫. ኮሚሽኑ ለይግባኝ አወሳሰን ሌሎች ሰነዶችን ማየት ጠቃሚ ነው ብሎ ሲያምን ባለሥልጣኑ በጽሁፍ ማስታወቂያ በማስታወቂያው በተገለፀው ጊዜ ውስጥ እነዚህን ሰነዶች እንዲያቀርብ ሊያዝ ይችላል፣

፬. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ መሰረት ለኮሚሽኑ ያቀረበው ማንኛውም መግለጫ እና ሰነድ ቅጅ ለይግባኝ ባይ መስጠት አለበት፡፡

፲፪. የችሎት የስራ ቀናት

፩. በሙሉ ጊዜ የሚመደቡ ዳኞች የስራ ቀናት የሚሆነው የመንግስት መደበኛ የስራ ሰዓትና ቀናት ይሆናል፣

፪. የከፊል ጊዜ ዳኞች የችሎት የሥራ ቀን በሳምንት ሁለት የሥራ ቀናት ይሆናል፣ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በፕሬዚዳንቱ አሳሳቢነት በሌሎች ቀናትም ችሎት ሊኖር ይችላል፡፡

፲፫. የሌሎች ህጎች ተፈጻሚነት

በሌሎች ህጎች ስለግብርና ታክስ ወይም ቀረጥ ስለይግባኝ አቀራረብ የተደነገጉ አግባብ ያላቸው ድንጋጌዎች ተፈፃሚነታቸው የተጠበቀ ነው፡፡

## ክፍል ሶስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፲፬. በጀት

ኮሚሽኑ በከተማ አስተዳደሩ በሚመደብ በጀት ይተዳደራል፡፡

፲፭. የሂሳብ መዛግብት አያያዝ

፩. ኮሚሽኑ የተሟላና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፣

   ፪. የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶችበከተማው ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ይመረመራል፤
   ፫. የኮሚሽኑየሂሳብ መዛግብት፣ የገንዘብ እና  የንብረት ሰነዶች አያያዝና አጠባበቅ የከተማው የፋይናንስ አስተዳደር ሕጎችን የተከተለ ይሆናል፡፡

፲፮. <u>የመተባበር ግዴታ</u>

ማንኛውም ሰው ለዚህ ደንብ ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

፲፯. <u>የመብትና ግዴታ መተላለፍ</u>

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን መብትና ግዴታ በዚህ ደንብ ለኮሚሽኑ ተላልፏል፡፡

፲፰.<u>የተሻሩና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ህጎች</u>

   ፩. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የግብር  ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፳/፲፱፻፺፩ በዚህ ደንብ ተሽሯል፤
   ፪. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጊዚያዊ አስተዳደር በ፲፱፻፺፮ ዓ.ም ባወጣው የአገልግሎት ክፍያዎች ተመን ውስጥ የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ ተመን በዚህ ደንብ ተሽሯል፤
   ፪. ይህንን ደንብ የሚቃረኑ ማናቸውም የከተማው አስተዳደር  ደንብ፣ መመሪያ እና ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

፲፱. <u>መመሪያ የማዉጣት ሥልጣን</u>

ኮሚሽኑ ለዚህ ደንብ አፈጻጸም አስፈላጊ የሆነዉን መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፳. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ ከጥር ፫ ፪ሺህ፲፩ ዓ-ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ጥር ፫ ቀን ፪ሺህ፲፩ ዓ.ም

ታከለ ኡማ በንቲ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንገዶች ባለስልጣን፣ የውኃና ፍሳሽ ባለስልጣን እና የቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን የስራ አመራር ቦርድ ማቋቋሚያ ደንብ ፻፺/፪ሺ፲፩

ማውጫ

1. ክፍል አንድ ጠቅላላ
2. ክፍል ሁለት ስለ ቦርድ መቋቋም፣ ተግባርና ኃላፊነት
3. ክፍል ሶስት ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

አጭር መግለጫ

ለከተማው ነዋሪ እና ለከተማው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማትና እድገት ወሳኝ የሆኑትን የመንገድ፣ የውኃና ፍሳሽ እና በከተማው አስተዳደር የሚካሄዱ የመኖሪያ ቤት ልማት ስራዎችን የሚመራ ቦርድ በማቋቋም ማዕከላዊ በሆነ እና ወጥ የቁጥጥር ስርዓት ባለበት መልኩ ለመምራት እንዲያስችል የወጣ ህግ ነው፡፡

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንገዶች ባለስልጣን፣ የውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን እና የቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን የስራ አመራር ቦርድ ማቋቋሚያ ደንብ ፻፯/፪ሺ፲፩

ለከተማው ነዋሪ እና ለከተማው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማትና እድገት ወሳኝ የሆኑትን የመንገድ፣ የውሃና ፍሳሽ እና በከተማው አስተዳደር የሚካሄዱ የመኖሪያ ቤት ልማት ስራዎችን የሚመራ ቦርድ ማቋቋም አስፈላጊ መሆኑን በማመን፤

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን እንደገና ለማደራጀት፣ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፷፬/፪ሺ፻፲፩ አንቀጽ ፺፬ ንዑስ አንቀጽ /፪/ መሠረት የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

**፩.አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንገዶች ባለስልጣን፣ የውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን እና የቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን የስራ አመራር ቦርድ ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፻፯/፪ሺ፲፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪.ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩. "ከተማ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤
፪. "ከንቲባ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ነው፤
፫. "ከተማ አስተዳደር" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤
፬. "መስሪያ ቤቶች" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንገዶች ባለስልጣን፣ የውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን እና የቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን ናቸው፤
፭. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

**፫. የፆታ አገላለፅ**

በዚህ ደንብ ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

**፬. የተፈፃሚነት ወሰን**

ይህ ደንብ በመስሪያ ቤቶቹ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

### ክፍል ሁለት

### ስለ ቦርድ መቋቋም፣ ተግባርና ኃላፊነት

**፭.የቦርድ መቋቋም**

የመንገዶች ባለስልጣን፣ የውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን እና የቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን የስራ አመራር ቦርድ /ከዚህ በኃላ "ቦርድ" እየተባለ የሚጠራ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

**፮.የቦርዱ አባላት አሰያየም**

፩. ሰብሳቢውን ጨምሮ የቦርዱ አባላት ቁጥር ቢያንስ ሰባት ቢበዛ አስራ አንድ ይሆናል፡፡ ሆኖም የቦርዱ ሰብሳቢ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው የአባላቱን ቁጥር ሊጨምር ይችላል፡፡

፪. የቦርዱ ሰብሳቢ ከንቲባው ወይም እሱ የሚመድበው ሰው ይሆናል፡፡
፫. የቦርዱ ምክትል ሰብሳቢና ሌሎች አባላት በከንቲባው ይሾማሉ፡፡ የቦርዱ አባላት በሙያና በስራ ቅንጅት አግባብነት ካላቸው ተቋሞች ወይም ከልዩ ልዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የተውጣጡ ይሆናሉ፡፡
፬. የቦርዱ አባላት /ሰብሳቢውን ሳይጨምር/ የስራ ጊዜ ሶስት አመት ይሆናል፡፡ አስፈላጊ ሲሆን የቦርድ አባል የስራ ጊዜው ሲያልቅ እንደገና ሊሰየም ይችላል፡፡
፭. ማንኛውም የቦርድ አባል በማንኛውም ምክንያት የቦርድ አባልነቱን የተወ እንደሆነ ሌላ ተተኪ አባል በከንቲባው ይሰየማል፡፡
፮. የዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ /፬/ ድንጋጌ ቢኖርም ለስራው ተገቢ ላለመሆኑ በቂ ምክንያት ካገኘ ከንቲባው የቦርድ አባልን በማንኛውም ጊዜ ሊያነሳው ይችላል፡፡
፯. የቦርዱን ቃለ-ጉባኤ በአግባቡ ለመያዝ፣ የቦርዱን ውሳኔዎችና ሰነዶች በሚገባ አደራጅቶ ለመያዝ ብቃትና ችሎታ ያለው ሰው በከንቲባ ጽህፈት ቤት ወይም ከመስሪያ ቤቶቹ መካከል በአንዱ መስሪያ ቤት በመንግስት ሰራተኝነት ይቀጠራል፡፡
፰. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ /፯/ መሰረት እስኪፈፀም ድረስ የከንቲባ ጽህፈት ቤት ወይም ከመስሪያ ቤቶች መካከል አንዱ መስሪያ ቤት የተጠቀሱትን ተግባራት የሚያከናውን ፀሀፊ ይመድባል፡፡

፯.<u>የቦርዱ ተግባርና ኃላፊነት</u>

፩. የመስሪያ ቤቶቹን ስትራቴጂክ እቅዶች፣ መርሀ-ግብሮች፣ አመታዊ እቅዶችና በጀት ገምግሞ ለሚመለከተው አካል እንዲተላለፍ ይወስናል፡፡ ሲፀድቁም ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፡፡
፪. የመስሪያ ቤቶቹን ወቅታዊ የስራ እቅድ ክንውንና የሂሳብ ሪፖርቶችን እንዲሁም የኦዲት ሪፖርቶች መርምሮ ተገቢውን አመራር ይሰጣል፡፡
፫. የመስሪያ ቤቶቹን ፕሮጀክቶች አፈፃፀም ይከታተላል፤ ይገመግማል፤ አስፈላጊ የሆነውን አመራር ወይም ውሳኔ ይሰጣል፡፡
፬. ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ከተፈቀዱ መደበኛ የግዥ ዘዴዎች ውጭ ግዥ ለመፈፀም መስሪያ ቤቶቹ የሚያቀርቡትን ጥያቄ መርምሮ ተቀባይነት ያለው ሆኖ ካገኘው ለተገቢው ውሳኔ ለከተማው አስተዳደር የፋይናንስ ቢሮ እንዲተላለፍ ይወስናል፡፡
፭. የመስሪያ ቤቶቹን ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃብት ፍላጎት መርምሮ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ኃብት ልማት ቢሮ እንዲቀርብ ይወስናል፡፡
፮. መስሪያ ቤቶቹ ለቦርዱ ውሳኔ በሚያቀርቧቸው ሌሎች ስትራቴጂክ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
፯. መስሪያ ቤቶቹ የተቋቋሙባቸውን አላማዎች ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ የአመራር ተግባራትን ያከናውናል፡፡

፰.<u>የቦርዱ ሰብሳቢ ተግባርና ኃላፊነት</u>

የቦርዱ ሰብሳቢ፡-

፩. ቦርዱን በሰብሳቢነት ይመራል፤ የስብሰባ ጥሪ እንዲተላለፍ ያደርጋል፤ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረግ ግንኙነት ቦርዱን ይወክላል፡፡
፪. የቦርዱ ስብሰባ ወቅቱን ጠብቆ እንዲካሄድ ያደርጋል፤ አስቸኳይ ስብሰባ መጥራት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ጥሪው ለቦርድ አባላቱ እንዲተላለፍ ያደርጋል፡፡
፫. የቦርዱ ውሳኔዎች ተግባራዊ መሆናቸውን ያረጋግጣል፡፡
፬. የቦርዱ ውሳኔዎችና ሰነዶች በቦርዱ ፀሀፊ አማካኝነት በሚገባ ተደራጅተው መያዛቸውን ይከታተላል፡፡

፱.የቦርዱ ስብሰባ ሥነ-ሥርዐት

፩. የቦርዱ ስብሰባ ምልዐተ-ጉባኤ የሚኖረው ከአባሎቹ ከግማሽ በላይ በስብሰባው ሲገኙ ነው፡፡

፪. ቦርዱ በየወሩ ይሰበሰባል፤ ሆኖም እንደ አስፈላጊነቱ ሰብሳቢው በማናቸውም ጊዜ ቦርዱን ሊሰበስብ ይችላል፡፡

፫. የቦርዱ ውሳኔ በሙሉ ድምጽ ወይም በአብላጫ ድምጽ ይተላለፋል፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል በተከፈለ ጊዜ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡

፬. የቦርዱ ፀሀፊ በየስብሰባው በተገኙ አባላት የሚፈረም ቃለ-ጉባኤ ይይዛል፡፡

፭. ቦርዱ የሚመክርባቸውን ጉዳዮች፡-

ሀ/ የመንገዶች ባለስልጣን፤

ለ/ የውኃና ፍሳሽ ባለስልጣን፤

ሐ/ የቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን፤ኃላፊዎች የሚያቀርቡ ይሆናል፡፡

፮. ከስብሰባው ሶስት ቀናት በፊት የቦርዱ ስብሰባ አጀንዳ ለአባላት መድረስ አለበት፡፡

፯. በአጀንዳው ከተያዘ ሌላ አጀንዳ በስብሰባ ላይ ማስያዝ አይፈቀድም፡፡

፰. የአጀንዳዎቹ ቅደም ተከተል በቦርዱ ሰብሳቢ ይወሰናል፡፡

፱. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዐት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፲. የቦርድ አባላት ተጠያቂነት

፩. ማንኛውም የቦርድ አባል በዚህ ደንብና በቦርዱ የውስጥ መመሪያ መሰረት የተጣለበትን ተግባርና ኃላፊነት የመፈፀምና የማክበር ግዴታ አለበት፡፡

፪. የቦርድ አባላቱ ኃላፊነትና ተግባራቸውን በአግባቡ ባለመፈፃማቸው ምክንያት በመስሪያ ቤቶቹ ስራዎች ላይ ጉዳት ቢደርስ አግባብነት ባለው ህግ ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡

## ክፍል ሶስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፲፩. ስለቢሮና ሌሎች ድጋፎች

ለቦርዱ ስራ የሚያስፈልጉ የቢሮና የጽህፈት አገልግሎቶችን የሚያቀርበው የከንቲባ ጽህፈት ቤት ወይም ከመስሪያ ቤቶቹ መካከል አንዱ መስሪያ ቤት ይሆናል፡፡

፲፪. ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ህጎች

ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረኑ የከተማው ካቢኔ ደንቦች፣ መመሪያዎች እና ልማዳዊ አሰራሮች በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

፲፫. ስለ ደንቡ መሻሻል

የከተማው ካቢኔ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህንን ደንብ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

፲፬. መመሪያ ስለማውጣት

ቦርዱ ይህን ደንብ በሚገባ ለማስፈፀም አስፈላጊ የሆነውን መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፲፭. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ ከመጋቢት ፱ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓመተ ምህረት ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ መጋቢት ፱ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም.

ታከለ ኡማ በንቲ

የአዲስ አበባ ከተማ ምክትል ከንቲባ